መግቢያ/ትምህርት 1
ትምህርት 2 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 1-2
ትምህርት 3 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 3፡1-4፡37
ትምህርት 4 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 5፡1-6፡7
ትምህርት 5 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 6፡8-7፡60
ትምህርት 6 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 8
ትምህርት 7 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 9
ትምህርት 8 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 10፡1-11፡18
ትምህርት 9 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 11፡19-12፡25
ትምህርት 10 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 13
ትምህርት 11 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 14፡1-15፡35
ትምህርት 12 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 16
ትምህርት 13 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 17፡1-18፡17
ትምህርት 14 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 18፡18-20፡12
ትምህርት 15 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 20፡13-21፡26
ትምህርት 16 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 22፡1-23፡11
ትምህርት 17 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 23፡23-25፡12
ትምህርት 18 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 25፡13-27፡26
ትምህርት 19 - የሐዋርያት ሥራ፥ ምዕራፍ 27፡27-28፡31
ትምህርት 20 - የሐዋርያት ሥራ ክለሳ

# የሐዋርያት ሥራ

## መግቢያ

### የመጀመሪያ ቀን፡

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ የተልእኮ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የምናጠናው አዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኘውን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገት በኋላ ቤተክርስቲያን እንዴት እንዳደገች የሚገልጹ ታሪኮችን ያካተተ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ታዝዘው ወንጌሉን ለማሰራጨት ሐዋርያት የሠሩትንም ሥራ ያካተተ ነው ሊባል ይችላል። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ክርስቲያኖች በዓለም ሁሉ ስደት በበዛ እንኳ እንዴት አድርገው ስለ ክርስቶስ መመስከር እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው።

ይህን መጽሐፍ በምታጠናበት ወቅት የጥናት መመሪያ ውስጥ የተጻፉትን ነገሮች ቀስ ብለህ በማስተዋል አንብባቸው። ለጥያቄዎችም፣ በጥንቃቄ በማሰብ መልስ ስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በግላችን እንዴት ማጥናት እንደምንችል ማወቁ አስፈላጊ ነው። ይህን የምናደርገውም ጥያቄ መጠየቅ ስንለምድና የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን ትምህርት ስናጤንና ስንመራበት ነው። ስለዚህም ወደ ማብራሪያው ከመግባትህ በፊት፣ ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠትህንና የተወሰነ ክፍል ጊዜ ወስደህ ማንበቡን አትዘንጋ። ማብራሪያው ውስጥ ያልተጠቀሱ አንዳንድ ነገሮችን ልታይ ትችላለህ። ማብራሪያው አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ቃል የሰጠው ትርጓሜ መሆኑንም አስተውል። ስለመልሶቹ በማሰብ የምንማረውን ትምህርት በሕይወትህ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሞክር፤ ይህ ብቻ አይደለም፣ ቃሉን መታዘዝና መጠበቅም አለብህ። ሮሜ 15፡4 እንደሚለው «በመጽናናትና መጽሐፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአል»።

ይህ መጽሐፍ እንደመማሪያ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን እንደ ማብራሪያም ሆኖ ነው የተዘጋጀው። የሐዋርያት ሥራን ስታጠና ወይም ስታስተምር ይህን መጽሐፍ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

የጥያቄዎቹን መልሶች፣ በደብተር ላይ ጻፋቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ከሌለህም፣ በጥናትህ ጊዜ ስለሚረዳህ ለማግኘት ሞክር። ከዚህ ጥናት ጋር ሌላ የሐዋርያት ሥራ ማብራሪያ ብታጠና ይጠቅማል። አዲስ የተተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ ካለህም፣ ከሱ ላይ አንብብ።

ትምህርቶቹ ለተማሪው እንዲያመቹ ተብለው በአምስት ቀን የተከፋፈሉ ናቸው። የአንዱን ቀን ክፍል፣ አንዴ ተቀምጠህ ለመጨረስ ሞክር። አንዳንዶቹ ትምህርቶች ከሌሎቹ ይልቅ ትንሽ ረዘም ስለሚሉ ከምንታጠው ስብሰባ በፊት ሁሉንም

መጨረስህን እርግጠኛ መሆን አለብህ። በትምህርቶቹ ጣልቃ ብዙ ከሌላ ሥፍራ የምትመለከታቸው ጥቅሶች አሉ። «ተመልከት» ተብሉ የተጻፈባቸውን ጥቅሶች ተመልከታቸው። «ተመልከት» የሚል የሌለባቸውን ግን በኋላ ጊዜ ካለህ ተመልከታቸው ወይም በሌላ ጊዜ ልትመለከታቸው ትችላለህ።

# ትምህርት 1

## የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ መግቢያ

የኢየሱስ ሥራ በሁለት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል:-
1) በምድር ላይ የነበረው ጊዜና 2) በመንግሥተ ሰማይ ሆኖ ስለሚያከናውነው ሥራ ነው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በመንግሥተ ሰማያት ላይ ያለውን የኢየሱስን ሥራ መጀመሪያ ያካተተ ነው። ወደ መንግሥተ ሰማያት ከማረጉ በፊት ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የመጨረሻውን ትዕዛዙን ይሰጣቸዋል። ይህም፤ በምድር ላይ የጀመረውን ሥራ እንዲሠሩት አደራ ይላቸዋል። በዓለም ሁሉ ሄዳችሁ የእኔን ወንጌል ስበኩ ብሎ ያዛቸዋል (ማቴ. 28፡19-20 ተመልከት)።

በሐዋርያት ሥራ፤ አስደናቂ የሆነውን የቤተክርስቲያን አጀማመር እንመለከታለን። ቤተክርስቲያን እንዴት እንደጸናችና አድጋ ወደ ዓለም ሁሉ እንደተዳረሰች እናያለን። ከእነዚህ ክንዋኔዎች ዛሬ ለቤተክርስቲያን የሚሆኑ ብዙ ትምህርቶች ይገኙባቸዋል።

ጥያቄ 1:- የሐዋርያት ሥራ 1፡1 አንብብ። የሐዋርያት ሥራ የተጻፈው ለማነው? ይህንን ከሉቃስ 1፡1-4 ጋር አነፃፅረው።

ጥያቄ 2:- የሐዋርያት ሥራ ምዕራፎች 1-8፡3 ድረስ አንብብና የመጽሐፉን ዋና ዋና ሐሳቦች በአጭሩ ግለጽ በዚህ ሳምንት መጽሐፉን ሙሉ በሙሉ በማንበብ ንድፈ ሐሳቦቹን እንዘረዝራለን።

## የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ

የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ፤ የተመረጡ የቤተክርስቲያን ታሪኮችን በጣም በጥንቃቄ ይመዘግባል። ጸሐፊው ለአሕዛብ፤ ክርስትና እንዴት እንደተጀመረና እንዴት እንደተስፋፋ ለማሳየት ይፈልጋል። ለአይሁዳውያን ደግሞ፤ የቤተክርስቲያን መመሥረትና ለአሕዛብ የመመሥከሩ ጉዳይ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍጻሜ እንደሆነ ያሳያል። (ሐዋ. 2፡16-21 እና 3፡24-26 ተመልከት)።

የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ስም በዚህ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ አልተጠቀሰም። ሆኖም «ኢየሱስ ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለጀመረው ሁሉ

መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ» ብሎ ጸሐፊው መግለጹ፤ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የሌላ መጽሐፍ ቀጥያ መሆኑን ያሳያል። ለቴዎፍሎስ የተጻፈው ሌላኛው መጽሐፍ የሉቃስ ወንጌል በመሆኑ፤ ይኸው ጽሐፊ ነው የሐዋርያት ሥራን የጻፈው የሚል ግምትም ያሳድራል። የቤተክርስቲያን ታሪክና የሁለቱም መጽሐፍት ጸሐፊ ሉቃስ እንደሆነ ይጠቅሳል። ሉቃስ የወንጌሉን የመስፋፋት ታሪክ ከጴጥሮስና ከጳውሎስ ሰምቶ የጻፈ ብቻ ሳይሆን፤ እሱም እራሱ በታሪኩ ውስጥ የተካፈለ ነበር። በሐዋርያት ሥራ አንዳንድ ክፍሎች ላይ «እኛ» «ሁላችንም» የሚሉ ቃላቶችን ይጠቀማል፤ ይህም ከጳውሎስ ጋር አብሮ ተጓዥ እንደሆነ ያሳየናል። የሐዋርያት ሥራ 16፡10-17 ተመልከት። (ሐዋ. 20፡5፤ 21፡18፤ 27፡1 እና 28፡16)

ጥያቄ 3፡- ቆላስያስ 4፡14 አንብብ።

ሀ) ሉቃስ ምን ዓይነት ሰው ነበር?

ለ) ይሠራ የነበረው ሥራ ምንድነው?

ጳውሎስ ለቆላስያስ ቤተክርስቲያን መልእክቱን የጻፈው በሮሜ እሥር ቤት ውስጥ ሆኖ ነበር። በሮምም ሉቃስ የጳውሎስ ወዳጅና ሐኪም በመሆን አገልግሏል። ምናልባትም ሉቃስ «የሐዋርያት ሥራ»ን የጻፈው በሮም ከጳውሎስ ጋር በነበረበት ወቅት ሊሆን ይችላል።

## ሁ ለ ተ ኛ ቀ ን፡-

ጥያቄ 4፡- የሐዋርያት ሥራ 8፡4-15፡34 አንብብ። በትንተናው ዕለት ከጀመርከው ዝርዝር በመቀጠል በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ሐሳቦችንም በዝርዝር ጻፍ።

# የ ሐ ዋ ር ያት ሥ ራ የ ተ ጻ ፈ በ ት ዘ መ ን

የሐዋርያት ሥራ የተጻፈበትን ትክክለኛ ጊዜ አናውቅም። የተጻፈበት ጊዜ በመጽሐፉም አልተጠቀሰም። ነገር ግን በመጽሐፉ ውስጥ ከተጠቀሱት የታሪክ ክንዋኔዎች በመነሣት አማካይ የሆነ ጊዜ ልንሰጥ እንችላለን።

ጥያቄ 5፡- የሐዋርያት ሥራ 12፡21-23፤ 11፡28 እና 18፡12 አንብብ። በእነዚህ ጥቅሶች የተገለጹትን ታሪካዊ ክንዋኔዎች በዝርዝር ጻፍ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቅሶ የምናየው በሐዋርያት 16፡10-17 ላይ ጳውሎስ ሁለተኛውን የተልእኮ ጉዞውን በጀመረበት ጊዜ ነው። ሉቃስ በሁለተኛ የጳውሎስ ጉዞ ላይ አብሮት ለጥቂት ጊዜ ያህል ተጉዟል፤ ወደ ሮምም ሲሄድ አብሮት ነበር (59-60 ዓ.ም) (ሐዋ. 20፡13)። በሐዋርያት ሥራ ላይ የተፈጸሙት ክንዋኔዎች የተጠናቀቁት ወደ 60 ዓ.ም አካባቢ ነው። እነዚህን ጊዜያት የወሰነው በሐዋርያት ሥራ በተጠቀሱት ታሪካዊ ክስተቶችና በሌሎች ባልተጠቀሱ ዋና ዋና ክንዋኔዎች ላይ በመመርኮዝ ነው። ለመጥቀስ ያህል፤

በ64 ዓ.ም የሮም ከተማ መቃጠል በዚህ መጽሐፍ ባለመጠቀሱ፤ ምናልባትም ከዚህ ጊዜ በፊት የተጻፈ ሊሆን ይችላል።

ትክክለኛ ጊዜውን ለንጠቅስባቸው የምንችልባቸው በሐዋርያት ሥራ ላይ የተጠቀሱት ታሪካዊ ክንዋኔዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. የሄሮድ አግሪጳ ሞት 44 ዓ.ም ሐዋ. 12፡20-23

ለ. በቀላውዴዎስ ቄሣር ዘመን የነበረው ረሃብ 44-48 ዓ.ም ሐዋ. 11፡28

ሐ. አይሁዳውያን ከሮም የተባረሩበት ጊዜ 49 ዓ.ም ሐዋ. 18፡2

መ. ጋልዩስ ገዥ የነበረበት ጊዜ 52-53 ዓ.ም ሐዋ. 18፡2

ሠ. ፊልክስ ገዥ የነበረበት ጊዜ 52-56 ዓ.ም ሐዋ. 23፡26-24፡27

ረ. የጶርቅዮስ ፊስጦስ ገዥ የነበረበት ጊዜ 57-60 ዓ.ም ሐዋ. ሥራ 24፡27።

እነዚህ ቀናቶች የተገኙት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ባሉ የታሪክ ጽሑፎች ውስጥ ሲሆን፤ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጻፈበትን ዘመን ከ60-63 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ያደርጉታል።

# የ ሐ ዋ ር ያ ት ሥ ራ የ ተ ጻ ፈ በ ት ም ክ ን ያ ት

ጥያቄ 6፡- የሐዋርያት ሥራ 1፡1-4 አንብብና፤ ሉቃስ ለቴዎፍሎስ ሁለተኛ መጽሐፍ የጻፈበትን ምክንያት ግለጽ።

ጥያቄ 7፡- በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዋነኛ የሆነው ለምን ይመስልሃል?

ጥያቄ 8፡- ስለ ሐዋርያት ሥራ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ የተጻፈውን አንብብ። የሐዋርያት ሥራ ስለተጻፈበት ምክንያት የሚገልጸውን ክፍል አጠር ባለ መልክ ጻፈው።

ሉቃስ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደተጀመረና ወደ ዓለም እንደተሰራጨ በጥንቃቄ በትክክልና በዝርዝር መጻፍ የክርስትና ታሪክ አጀማመርን የሚገልጽ ጽሑፍ ለመጻፍ እንደፈለገ ይጠቁመናል። ሉቃስ የኢየሱስን ታሪክና የጥንት ቤተክርስቲያን ታሪክ አንድ ላይ ያጣምራቸዋል። የመጀመሪያው መጽሐፍ «ኢየሱስ በመጀመሪያ ያደረገውንና ያስተማረውን ነገር በሙሉ» ያካተተ ሲሆን፤ ይህም ስለ ኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት የሚያትት ነው። ይህ ሁለተኛው መጽሐፍ ደግሞ፤ ከመንግሥተ ሰማይ በተከታዮች ውስጥ ሆኖ የሚሠራውን ሥራና የሚሰጠውን ትምህርት በተመለከተ የተጻፈ ነው። የጀመረው ሥራ በደቀመዛሙርቱ በኩል እንዲቀጥል ያደረገው፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት ነው። የሐዋርያት ሥራ የተጻፈባቸው ዋነኛዎቹ ምክንያቶች፡-

ሐ. ስለ ክርስትና አጀማመር፤ ስለ ቤተክርስቲያን ምሥረታና ስለ ወንጌል መስፋፋት ታሪካዊ የሆነ ማስረጃ ለማቅረብ ሲሆን፤

ለ. ኢየሱስ መሢሕ እንደሆነ ለአይሁዳውያን በመግለጽ ክርስቲያናዊ የሆነ መከላከያ ለማቅረብ ነው (ሐዋ. 4፡8-12 ተመልከት)። አሕዛብም አሁን የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንዲሆኑ መከላከያ ያቀርባል። (ሐዋ. 25፡8-11 ተመልከት)።

ሐ. አሁን እየተተከሉ ለሚመጡት ቤተክርስቲያኖች የጥንቷን ቤተክርስቲያን ልማዶች፤ ትምህርቶችና መንፈሳዊ ምሳሌዎች በመጥቀስ መመሪያ እንዲሆን ለማድረግ፤

መ. የከረሩ ስደቶችንም እንኳ ክርስትና በድል እንደተወጣቸው ለማሳየት፤

ሠ. ከክህዲዎች አስተሳሰብ፤ ከሮማው መንግሥትና በዚያን ዘመን ሄሌናዊ ከነበረው ከግሪክ ኅብረተሰብ ጋር እንዴት ኖሩ እንደነበርም የሐዋርያት ሥራ ያሳያል።

## ሦ ስ ተ ኛ ቀ ን፡-

ጥያቄ 9፡- የሐዋርያት ሥራ 15፡36-21፤ 16 አንብብ። በዚህ ክፍል የሚገኙትን ዋና ዋና ነጥቦችን በመዘርዘር የዚህን መጽሐፍ ንድፈ ሐሳብ መጻፍህን ቀጥል።

# የ ሐዋርያት ሥራ ዋነኛ ትምህርቶች

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በብሉይና በአዲስ መካከል ያለ መሸጋገሪያ መጽሐፍ ነው። ብሉይ ኪዳን ትኩረት ይሰጥ የነበረው የእግዚአብሔር ሕዝቡ ስለነበሩት አይሁዳውያንን እነርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ የእግዚአብሔር ፕሮግራም አይሁዳውያንና አሕዛብን ያካተተ ነው። አንድ አዲስ መንግሥት ሲቋቋም ሕግጋቶቹ እንደሚቀየሩ ሁሉ፤ የሐዋርያት ሥራም መጽሐፍ ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን የተደረገውን ለውጥ ያንፀባርቃል። ስለዚህም መንፈስ ቅዱስን፤ የቤተክርስቲያን ሥርዓትን፤ ጥምቀትን፤ ወዘተ... በተመለከተ በሐዋርያት ሥራ በመጀመሪያ የተጻፉት ነገሮች በስተመጨረሻ አካባቢ ተለውጠዋል። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉትን ትምህርቶች ሁልጊዜም ቢሆን ማነፃፀር ያለብን፤ መልእክቶቹ ውስጥ ካሉት ትምህርቶች ጋር መሆን አለበት። ብዙዎቹም መልእክቶች የተጻፉት የሐዋርያት ሥራ በተጻፈበት ዘመን፤ ወደ መጨረሻው አካባቢ በመሆኑ ስለቤተክርስቲያን የተሰጠውን ትምህርት የበለጠ እንድንረዳ ያደርጉናል። ጳውሎስ ለየቤተክርስቲያኖቹ መልእክቶቹን የጻፈው በሚንዝበት፥ በእሥር ቤት በነበረበትና ወደ ዕድሜው መጨረሻ በደረሰበት ወቅት ነበር።

ብዙ ሰዎች ሲያስተምሩ በሐዋርያት ሥራ ላይ ብቻ ስለሚያተኩሩ ትምህርታቸው ሁሉንም ነገር ያካተተ አማካይ ትምህርት እንዲሆን አያደርጉትም። በሐዋርያት ሥራ 17፡11 ላይ ስለ ቤሪያውያን «ልበ ሰፊዎች ነበሩና ነገሩ እንደዚህ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃደኝነት ተቀበሉ» ተብሉ

ተጽፎላቸዋል። ጥያቄ 10፡- ወደ ሐሰተኛ ትምህርት እንዳንወድቅ ይህ ልንከተለው የሚገባን ምሳሌ መሆን ያለበት ለምንድነው?

በሐዋርያት ሥራ ጥናታችን ላይ፤ አራት ዋና ዋና ትምህርቶችን እናገኛለን።

ጥያቄ 11፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። የሐዋርያት ሥራ 1፡14፤ 24፤ 2፡42፤ 4፡31። ጸሎትን በተመለከተ ከጥንቷ ቤተክርስቲያን ልንማረው የምንችለውን ነገር በዝርዝር ጻፍ።

1. ጸሎት ፡- የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጸሎት በቤተክርስቲያን ውስጥ ቁልፍ የሆነ ቦታ ተሰጥቶት እንደነበረ ያሳየናል። ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ካረገ በኋላ፤ ደቀመዛሙርቱ ከኢየሱስ እናት እና ከወንድሞቹ ጋር በጸሎት ይተጉ ነበር (ሐዋ. 1፡14)። ኢየሱስን አሳልፎ በሰጠው በይሁዳ ምትክ ሌላ ሰው ለመምረጥ፤ ምሪትን ለማግኘት ይጸልዩ ነበር። (ሐዋ. 1፡24)። የጥንት ክርስቲያኖች እራሳቸውንና ሕይወታቸውን ለሐዋርያቱ ትምህርት ኅብረትና ጸሎት አሳልፈው ሰጥተው ነበር (ሐዋ. 2፡42)። ከጸለዩ በኋላ፤ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ በድፍረትም የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩ (ሐዋ. 4፡31)።

ማሳሰቢያ ፡- ሌሎች ብዙ የጸሎት ጊዜዎችን ታገኛለህ። የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ በምናጠናበት ወቅት፤ በደብተርህ ላይ በጸሎቱ አማካይነት የተፈጸሙትን ነገሮች እንደማስታወሻ አድርገህ ጻፋቸው

ጥያቄ 12፡- ጸሎት ለአንተና ለቤተክርስቲያንህ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? እግዚአብሔር በጸሎትህ ተጠቅሞ የሠራቸውን ታላላቅ ሥራዎች ለምሳሌ ያህል ጥቀስ።

ጥያቄ13፡- የሐዋርያት ሥራ 1፡8 አንብብ። የቤተክርስቲያንን ሥራ በተመለከተ ኢየሱስ የሰጠው ቃል ምንድነው?

2. ምሥክርነት፡- ኢየሱስ ለቤተክርስቲያን የሰጠው የመጨረሻው ትዕዛዝ ምሥክሮቼ ሁኑ የሚል ነው። የጥንት ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች ለመሆን ምንም አይፈሩም ነበር። የጴጥሮስንና የዮሐንስን ድፍረት በአይሁድ ችሎት ፊት ሲያዩ፤ አለቆቹና ሽማግሌዎቹ ተደንቀዋል። ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት እሥር ቤት ከገቡ በኋላ እንኳ «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ አለብን» ይሉ ነበር (ሐዋ. 5፡29)። እስጢፋኖስ የሞተው ምሥክር ለመሆን በነበረው ድፍረት ምክንያት ነበር (ሐዋ. 7፡55-59)። ጳውሎስ በድፍረት በየቤተ መቅደሱና በየእሥር ቤቱ በገዢው ፊት ይመሠክር ነበር። የሐዋርያት ሥራን ጥናታችንን ስንቀጥል ስለዚህ ነገር በሰፊው እናጠናለን።

ጥያቄ14፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ፡- የሐዋርያት ሥራ 4፡18-21፤ 5፡17-18፤ 7፡59-60፤ 12፡1-4። ስለ እምነታቸው ስደት የተቀበሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር ጻፍ።

3. ስደት፡- በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያለማቋረጥ ስለ ክርስቲያኖች ስደት እናነባለን። ጴጥሮስንና ዮሐንስን አስፈራርተዋቸው ነበር (ሐዋ. 4፡18-21)። ደቀመዛሙርቱ በየእሥር ቤቱ ታሥረው ነበር (ሐዋ. 5፡17-18)። እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሞቷል (ሐዋ. 7፡59-60)። ጴጥሮስም እሥር ቤት ገብቷል፤ ያዕቆብ ደግሞ ተሰይፏል። (ሐዋ. 12፡1-4)። በጥንቷ ቤተክርስቲያን ላይ የስደት መዓት መውረዱን የሚያመለክቱ ሌሎች አያሌ አጋጣሚዎች አሉ። ስለ ክርስቶስ ለመሰቃየት ከነበራቸው ፍላጎት ውስጥ ብዙ የምንማረው ነገር አለ።

ጥያቄ 15፡- በኢየሱስ ክርስቶስ ባለህ እምነት ምክንያት ስደትን ተቀብለሃል? እንዴት እንደነበረና በዚያውስ ውስጥ እንዴት ጸንተህ እንደቆምክ ግለጽ።

4. መንፈስ ቅዱስ ፡- የመንፈስ ቅዱስ መምጣትና በክርስቲያኖች ውስጥ መኖር ሕይወት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገለጸው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ገሃድ የወጣውም በጴንጤ ቆስጤ ቀን ነበር(ሐዋ. 2፡1-4)። በዚያን ቀን 3000 ሰዎች ሲያምኑም ታይቷል። (ሐዋ. 2፡41)። ሐዋርያት ወንጌልን እንዲሰብኩ አርኪ የሆነ ድፍረትና ጥበብ በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥቷቸው ነበር። ኢየሱስን ለመቀበል ዝግጁ ወደ ሆኑት ሰዎች እራሱ መንፈስ ቅዱስ ፊሊጶስን፤ ጴጥሮስን፤ ጳውሎስንና ሌሎችን ይመራ ነበር። በእሥር ቤት ውስጥ ይገረፉ የነበሩት ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ማጽናናት ይቀበሉ ነበር።

ጥያቄ 16፡- መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ውስጥ የሚሠራው እንዴት ነው?

## አራተኛ ቀን፡-

# የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ግንኙነት

ጥያቄ17፡- የሐዋርያት ሥራ 21፡17-28፡31 ድረስ ያለውን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ዋና ዋና ሐሳብ በዝርዝር መጻፉን ቀጥል።

ወንጌሉ የተጻፈው የኢየሱስን ምድራዊ ሕይወትና ሞት እንዲጽፉ በተመሩ አራት የተለያዩ ሰዎች ነበር። ወንጌሉ የተጻፈው፥ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት አካባቢ ለነበሩት አራት የተለያዩ ቡድኖች ነበር። ማቴዎስ የጻፈው ለአይሁዳውያን ነው፤ ከማርቆስ ለሮማውያን፤ ሉቃስ ለተቀናት ለማያምኑ አሕዛብ ሲሆን፤ ዮሐንስ ደግሞ ለክርስቲያኖች ነው።

በሐዋርያት ሥራ፤ ደቀመዛሙርቱ ደኅንነት ያለው በክርስቶስ ነው የሚለውን የምሥራቹን ዜና ለዓለም ሁሉ እንዲያስሙ ኢየሱስ የሰጣቸውን ትዕዛዝ ተቀብለው ሲፈጽሙ እናያለን። ይህ ጊዜ፤ እግዚአብሔር ለሰዎች ባለው ዓላማ ውስጥ አዲስ የሽግግር ወቅት ነበር። እግዚአብሔር ካሁን ወዲህ የእርሱ ምስክሮች እንዲሆኑ

ይታ ማንባቸው የነበረው በአይሁዳውያን ላይ ብቻ አልነበረም። የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ለሁሉ ቱም ለአሕዛብና ለአይሁዳውያን ነው የሰጠው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች እኛ ብቻ ነን ብለው ለሚያስቡ አይሁዳውያን ይህ እንግዳ የሆነ አስተሳሰብ ነበር። አሕዛብ ከእኛ ጋር እኩል ናቸው ብሎ መቀበሉ ይከብድባቸው ነበር። የሐዋርያት ሥራ ከአይሁድ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሁሉም ዜጎች የቤተክርስቲያን ዕድገት የተደረገውን ሽግግር ያካተተ መጽሐፍ ነው። በአንዳንድ አይሁዳውያንና አሕዛብ መካከል ከእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ አሕዛብ ሊኖራቸው የሚገባውን ቦታ በተመለከተ ብዙ ግጭቶች ተፈጥረው ነበር።

ይህ የሽግግር ጊዜና ከዚያም በኋላ፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉት መልእክቶች ተጻፉ። ለመጥቀስ ያህል፤ ጳውሎስ የኤፌሶንና የቆላስያስ መልእክቶቹን የጻፈው በሮም እሥር ቤት ውስጥ ሳለ ነበር ምናልባትም ደግሞ 1ቆሮንቶስን የጻፈው በሁለተኛው የተልእኮ ጉዞው ላይ ለሁለት ዓመት ቤኤፌሶን በተቀመጠበት ወቅት ነው (ሐዋ. 19፡10 ተመልከት)። እነዚህ መልእክቶች የተጻፉት፤ በሐዋርያት ሥራ ላይ የተገለጹት ክንዋኔዎች በሚፈጸሙበት ወቅት በመሆኑ፤ የጥንታዊቱን ቤተክርስቲያን ዓላማዎች ጠንቅቆ ለመረዳት አብረው ከሐዋርያት ሥራ ጋር መጠናት አለባቸው።

ጥያቄ 18፡- የቤተክርስቲያናቸው ትምህርት በሐዋርያት ሥራ ላይ ብቻ እንዲመሠረት የሚያደርጉ ሰዎችን ታውቃለህን? ካወቅህ ዓይነታቸውን ዘርዝር፤ ስለትምህርታቸውም በመግለጽ ለምን ሚዛናዊ እንዳልሆነ ግለጽ?

# የሐዋርያት ሥራ ንድፈ ሐሳብ

የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ንድፈ ሐሳብ በብዙ ዓይነት መንገድ ልንገልጸው እንችላለን፤ ሆኖም ይህ አጭር ክፍፍል የመጽሐፉን አምስት ዋና ክፍሎችን ይሰጣል።

1. የቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም መመሥረት፤ ሐዋ. 1፡1-8፡3

2. ወንጌሉ አይሁዳውያንን ብቻ ሳይሆን አሕዛብንም ያጠቃለለበት የሽግግር ጊዜ፤ ሐዋ. 8፡4-11፡18።

3. በሮማው ዘመን መንግሥት የነበረው የአሕዛብ ቤተክርስቲያን፤ ሐዋ. 11፡19-15፡35።

4. የሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎት፤ ሐዋ. 15፡36-21፡16።

5. የጳውሎስ መታሠር፤ ሐዋ. 21፡17-28፡31።

# የዚህ ጥናት ዓላማ

1. የዚህ ጥናት ዓላማ ከጴንጤቆስጤ ቀን አንስቶ ቤተክርስቲያን ወደ አሕዛብ ዘንድ ገብታ እስከደገበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ መከታተል ነው። ኢየሱስ በሐዋርያት ሥራ 1፡3

ላይ የሰጠውን ተልእኮ ለማሟላት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሐዋርያቱና በተከታዮቹ አማኞች ሕይወት ውስጥ እንዴት ይሠራ እንደነበር እናያለን።

2. ከኢየሩሳሌም አንሥቶ እስከ ይሁዳ ድረስ፤ እስከ ሰማርያንና እስከ አሕዛብ ዓለም ድረስ ቤተክርስቲያንን እንዴት እንደተስፋፋች በዓለም ካርታ ላይ ምልክት ማድረግ መቻል አለብህ።

3. በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን ችግሮች ከዛሬይቱ የቤተክርስቲያን ችግሮች ጋር ማዛመድ መቻል አለብህ።

4. መንፈስ ቅዱስ የቀድሞዎቹን አማኞች እንዴት ይመራ እንደነበር፤ ድፍረትን ይሰጥ እንደነበር፤ በጉዞአቸው እንዴት ይረዳቸው እንደነበር፤ በችግሮቻቸው ወቅት እንዴት ያድናቸውም እንደነበር ማየት አለብህ ይህንንም ዛሬ በሕይወትህ ከሚያጋጥሙህ ነገሮች ጋር አዛምዳቸው።

የሐዋርያት ሥራን በምታጠናበት ወቅት እነዚህን ዓላማዎች በአእምሮህ ውስጥ አድርጋቸው። ብዙ ጊዜም፤ መለስ እያልክ ተመልከታቸው።

## አምስተኛ ቀን። ክለሳ

ትምህርቶቹን ከልስና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

1. ሉቃስ ለምንድነው የጥንትዋን ቤተክርስቲያን ታሪክ ለመጻፍ ብቁ ሊሆን የቻለው?

2. በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በጣም ዋነኛ መጽሐፍ የሆነው ለምንድነው?

3. የሐዋርያት ሥራ አራት ዋና ዋና ትምህርቶች ምንና ምን ናቸው?

4. አምስቱ የሐዋርያት ሥራ የተጻፈባቸው ምክንያቶች ምንና ምን ናቸው?

ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጁ ለመሆን ቀደም ብለህ የመወያያዎቹን ጥያቄዎች ተመልከት።

## ሳምንታዊው ስብሰባ።

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ፡- መሪው ከ 5 እስከ 10 ደቂቃ የሚፈጅ በዚህ ሳምንት የትምህርት ክፍል ላይ ያተኮረ ቃሉን ከተማሪዎቹ ጋር የሚካፈልበትን ጊዜ ማዘጋጀት አለበት።

2. ጸሎት፡- ለ10 ደቂቃ ያህል፤ ስለ እያንዳንዳችሁና ስለ ቤተክርስቲያን ችግር ጸልዩ።

3. ክለሳ፡- ለ 15 ደቂቃ ያህል፤ የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ። መምህሩ ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን አጠናቀው መሥራታቸውንና መረዳታቸውን ለማወቅ ሲል የተማሪዎችን መልስ ማየት አለበት። እያንዳንዱ ተማሪ የተማራቸውን አንዳንድ ነገሮችን በዝርዝር ጻፍ። መሪው በዚህ ጊዜ ውስጥ አጠር ያለች ፈተና ሊትሰጥ ትችላለህ።

4. ውይይት:- በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። እያንዳንዱ ሰው ሐሳቡን ማካፈሉን እርግጠኛ ሁን። እነዚህን ጥያቄዎች ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ ማዘጋጀትህን አረጋግጥ።

ሀ. በአካባቢህ የተለየ እምነት ያላቸው ሰዎች አሉ? ስለሚያስተምሩት ነገር ተወያዩና ስህተቶቻቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጠቁም። ሌሎቹ በሐሰተኛ ትምህርት እንዳይታለሉና ጸንተው እንዲቆሙ ለመርዳት እንድትችል አስቀድመህ ማወቅ ይገባል። የቤተክርስቲያን አባላት ከሐሰተኛ ትምህርቶች እንዲጠበቁ፤ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው የሚችለው እንዴት ነው?

ለ. በሐዋርያት ሥራ የሚገኙትን አራቱን ዋና ዋና ትምህርቶች በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ዛሬ የምትጠብቋቸው እንዴት ነው? ካልሆነስ ለምንድነው የማይጠብቋቸው? በእነዚህ አራት ነገሮች በኩል፤ ቤተክርስቲያንህ ልታድግበት የምትችልባቸውን አንዳንድ መንገዶች በዝርዝር ጻፍ።

ሐ. ላንተና ለቤተክርስቲያንህ ለምን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ማጥናት እንደሚያስፈልግ በዝርዝር ግለጽ። ከዚህ ጥናት ምን እማራለሁ ብለህ ነው ተስፋ የምታደርገው?

5. ጸሎት:- የተማርከውን ነገር እግዚአብሔር በተግባር እንድታውለው ይረዳህ ዘንድ በመጠየቅ ስብሰባውን በጸሎት ደምድመው።

# ትምህርት 2

የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 እና 2

## የመጀመሪያ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 1:1-26

በዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን የምንኖር ሰዎች ከምናገኛቸው ልዩ የሆኑ በረከቶች አንዱ የመንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ መሥራት ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር መንፈሱን ለተወሰኑ ሰዎች ይሰጥ የነበረው የተወሰነ ዓላማ ወይም ነገር እንዲያሟሉለት ነው። አንዳንድ ጊዜ ዓላማው ከተፈጸመ በኋላ ወይም በዚያ ሰውዩ ሕይወት ኃጢአት ከሰለጠነ፤ መንፈስ ቅዱስ ሕይወቱን ትቶ ይወጣ ነበር። (ለምሳሌ ንጉሥ ሳኦል መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 11:6፤ 16:14)። በአዲስ ኪዳን ግን፤ መንፈስ ቅዱስ በሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ይወርዳል፤ ሰውዩው ኃጢአት ቢሠራም ትቶት አይሄድም። በሐዋርያት ሥራ ጥናታችን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የነበረውን የሥራ ድርሻ እንዴት በአዲስ ኪዳን ዘመን እንደተለወጠ እናያለን። ይህም፤ በዘመናችን ያለውን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በደንብ እንድንገነዘብ ያደርገናል።

ኢየሱስ ወደ አባቱ ከመሄዱ በፊት፤ የጀመረውን ሥራ ደቀመዛሙርቱ እንዲሠሩለት ሲል ያስተምራቸውና ያሰለጥናቸው ነበር። ደቀመዛሙርቱ የተሰጣቸውን

ሥራ በተገቢው መንገድ እንዲፈጽሙ፣ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ ብሎ ቃል ገብቶላቸው ነበር(ዮሐንስ 16፡7-14)። ከትንሣኤው በኋላ፣ ለ40 ቀን ያህል፣ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ለመንፈስ ቅዱስ መምጣት ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ፣ ያስተምራቸው ነበር። የሐዋርያት ሥራ ኢየሱስ በመንግሥተ ሰማያት ላይ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሥራውን መሥራት የጀመረበት መሆኑን የሚዘግብ መጽሐፍ ነው። ከሐዋርያቱ ሥራ ጊዜ አንሥቶ እግዚአብሔር፣ በኢየሱስ ለሚያምኑ ሰዎች በሙሉ መንፈስ ቅዱስን እንደ ስጦታ መስጠት ጀምሯል።

ጥያቄ 1፡- የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 እና 2 አንብብ። ሀ. ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ይጠባበቁ በነበረበት ወቅት፣ ምን እያደረጉ ነበር? ለ. መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ ምን ነገር ሆ ነ?

ኢየሱስ ከእነርሱ ተለይቶ እንደሚሄድ ከመሞቱ በፊት ለደቀመዛሙርቱ በግልፅ ነግሮአቸዋል (ዮሐ. 14፡1-4 ተመልከት)። ይህም ቢሆን፣ ከሙታን ስለመነሣቱ ማስረጃ እንደሚፈልጉ ያውቅ ስለነበር ለአርባ ቀን ያህል ለደቀመዛሙርቱ ተገልጦላቸው ነበር። የትንሣኤው ምስክርነት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ያውቅ ነበር። እንደ ሌሎች ሃይማኖቶች ሳይሆን፣ ክርስትና የተመሠረተው፣ መሪ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መነሳት ላይ ነው። ኢየሱስም የሚመጣውን መንግሥቱን በተመለከተ ትምህርት ሰጥቷል። ኢየሱስ በቅርብ ጊዜ እንደሚለያቸው ያስጠነቅቃቸው ነበር። ለደቀመዛሙርቱ ግን መሄዱን በዚያን ጊዜ ሙሉ በሙሉ አልተረዱም ነበር፣ ከአረገ በኋላ ግን የተናገረውን ያስታውሱት ነበር። የሱ መንግሥት እንደምትመጣ የሰጠው የተስፋ ቃል ደቀመዛሙርቱን እሱ ሲለያቸው ዝግጁ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

ሐዋርያት ሥራ 1፡1-26 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 2፡- ሀ. 1. የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ማነው? 2. የሐዋርያትን ሥራ የጻፈው ለማነው? (ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ተመልከት)። ለ. ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለምን ያህል ጊዜ ነበር በምድር ላይ የቆየው? ሐ. መንፈስ ቅዱስ እስኪላክላቸው ድረስ ደቀመዛሙርቱ ምን እንዲያደርጉ ኢየሱስ አዘዛቸው? መ. የአስቆሮቱ ይሁዳ ምን ሆነ? ሠ. በይሁዳ ምትክ ሌላ ሰው መምረጥ ያስፈልገናል ብሎ ጴጥሮስ የተናገረው ለምንድነው?

የክርስትና እውነተኛነት የተመሠረተው፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ላይ ነው። ከሙታን የመነሣቱ እውነታ ከሞተ በኋላ ባዩት ሰዎች ተረጋግጧል። ኢየሱስ በአንድ ጊዜ 500 ለሚያክሉ ሰዎች ተገልጧል። በአርባ ቀን ጊዜ ውስጥ፣ ብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር። አሥሩ የኢየሱስ መገለጦች፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተመዝግበዋል (ማቴ. 28፡9፣ 16-27፣ ማርቆ. 16፡9፣ ሉቃስ 24፡15-31፣ ዮሐ. 20፡19-24፣ 26-28፣ 21፡1-1-24፣ ሐዋ. 1፡2-9፣ 9፡1-5፣ 1ቆሮ. 15፡5-8)። ለትንሣኤው ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ያስፈልጋል?

3፡- ትንሣኤው በክርስትና እምነት ውስጥ ዋነኛው ነገር የሆነው ለምንድነው?

የክርስትና እምነት ዋነኛው መሠረት፤ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው። ጳውሎስም በ 1ቆሮ. 15:7፤ ላይ «ክርስቶስ ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናትና እስካሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ ብሎ ይናገራል። ይህ የሆነበት ምክንያት ያለ ትንሣኤው ኢየሱስ የመጨረሻው መስዋዕት ስለመሆኑ የምናገኘው ማስረጃ ባለመኖሩ ይህንን የኃጢአት መስዋዕት እግዚአብሔር ይቀበለው አይቀበለው ማወቅ ስለማንችል ነው። ልክ እንደ ሌሎቹ ሃይማኖቶች እኛም እንከተል የነበረው የሞት መሪ ይሆን ነበር። መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ለሚያምኑት የኢየሱስ ትንሣኤ እውነተኛ እንደሆነ በልባቸው ያረጋግጥላቸዋል።

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው የመጨረሻ ትዕዛዝ «በኢየሩሳሌምም፥ በይሁዳም ሁሉ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» የሚል ነው (ሐዋ. 1:8) (ማቴ. 28:18-20 ተመልከት)። የሐዋርያት ሥራ 1:8 ለዚህ መጽሐፍ ቁልፍ የሆነች ለዋናው ሐሳብ መሠረት የሆነች ቁጥር ናት። በሐዋርያት ሥራ ላይ ያለው ታሪክ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ወደ ይሁዳ፥ ወደ ሰማሪያ ብሎም ወደ ተቀረው የሮማው መንግሥት ግዛት እንዴት እንደተስፋፋ የሚያሳይ ነው።

ጥያቄ 4:- የሐዋርያት ሥራ 1:8 በቃልህ አጥና።

በሐዋርያት ሥራ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ በሙሉ የእኔ ምሥክሮች ይሆናሉ ብሎ አስቦ ነበር። የቤተክርስቲያንም ዋነኛ ሐላፊነት ይህ ነው። ምንም እንኳን ቤተክርስቲያን በሌሎች በጎ አድራጊ ተግባሮች (ለምሳሌ ልማት የጤና ፕሮግራም እናትና አባት የሌላቸውን ማሳደግ) ብትካፈልም፤ ዋነኛው ዓላማዋ ለሌሎች የምሥራቹ ዜና ማስተላለፍ መሆን አለበት። እነዚህ በተጨማሪ የምናከናውናቸው ሌሎች ሥራዎች ዋና ተግባራችን ከሆነው የኢየሱስን ስም እስከ አዓለም ዳርቻ ከማዳረስ እንዳያፈናቅሉን መጠንቀቅ ይኖርብናል።

ጥያቄ 5:- ሀ. ቤተክርስቲያንህ የሐዋርያት ሥራ 1:8 የምትፈጽመው እንዴት ነው?
ለ. አንዳንድ ቡድኖች ይህንን ዓይነቱን ሥራ ከመሥራት ተፈናቅለው ሌላ ሥራ ወደ መሥራት እንዴት እንደተሸጋገሩ ግለጽ።

በሐዋርያት 1:8 ላይ ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱ የምሥክርነት ሥራ የሚጀምረው እዚያው ከትውልድ አገራቸው ከኢየሩሳሌም እንደሆነ ተናግሯል። ይህም በሐዋርያት ሥራ 1-7 ባሉት ምዕራፎች ውስጥ መፈጸሙን እናያለን። ቤተክርስቲያኒቱም የነበረችው በሕዝቡ መኖሪያ በሆነችው በኢየሩሳሌም ከተማ እንደሆነ ለመገንዘብ እንችላለን።

ከዚሁም በኋላ ቤተክርስቲያኒቱ የአይሁዳውያን አገር ወደ ሆነችውና የደቀመዛሙርቱ የዜግነት ማዕከል ወደ ሆነችው ይሁዳ ድረስ መዘርጋት ነበረባት። ይህም በሐዋ. 8-11 ባሉት ምዕራፎች ውስጥ ተፈጽሞ እናየዋለን።

ሦስተኛ ደግሞ፤ ደቀመዛሙርቱ አንድ ዓይነት ባህል ወደ ነበራቸው ነገር ግን ከእነርሱ የተለዩ ብሔረሰቦች ወደሆኑ መሄድ ነበረባቸው። በፓለስቲና ይኖሩ ወደ ነበሩት የብሔርና የሃይማኖት ልዩነት ወደ ነበራቸው ወደ ሰማርያውያን መሄድ

ነበረባቸው። ይህ ሥራ በሐዋ. 8 ላይ ተጠቅሷል። ይህ አግራ የሆኑ ሰዎች ከአርሞች አብሮ እንደሚሠሩ ዓይነት ነው፤ በኢትዮጵያዊነታቸው አንድ ቢሆኑም፤ በብሔረሰብ ደረጃ የተለያዩ ናቸው።

በመጨረሻም፤ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ምንም ዓይነት ግንኙነት ከሌላቸው ከዓለም ሕዝቦች ጋር ተገናኝተው ስለ እነርሱ ማሰብ እንዳለባቸው ይናገራል። ይህ መፈጸም የተጀመረው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ላይ ሲሆን፤ በተለይ ግን በደንብ የሚታየው በሐዋርያት ሥራ 13-28 ባሉት ምዕራፎች ውስጥ ነው።

ይህ የምሥክርነት ሐላፊነት ላለባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጥሩ የሆነ ንድፈ ሐሳብ ነው። ማንኛይቱም ቤተ ክርስቲያን ምሥክርነቷን ወደ ራሷ ወደሆነችው ኢየሩሳሌም ማለት ወደ ቀበሌዋ ማዳረስ ይኖርባታል። በዚሁ ብቻ መወሰንም የለባትም፤ በሀገሯ ወዳሉት ሕዝቦች ሁሉ እንዲዳረስም ማድረግ አለባት። ይህም የቤተክርስቲያኒቱ ይሁዳና ሰማርያ መሆኑ ነው። እኛ ሁላችንም ብንሆን ወንጌሉን ወደ መላው ዓለም የማዳረሱ ፍላጎትና ሐላፊነት እንዲሰማን ያስፈልጋል።

ጥያቄ 6:- ሀ. ለአንተ ቤተክርስቲያን ኢየሩሳሌም፤ ይሁዳ ሰማሪያና የምድር ዳርቻ የሚሆኑት ሥፍራዎች ምንድናቸው? ለ. ወደ እነዚህ የተለያዩ ሥፍራዎች ቤተክርስቲያንህ የምትደርሰው ወይም ለመድረስ የምታቅደው እንዴት ነው?

በአገራችንና በዓለም ዙሪያ ለሌሎች በመመሥከሩ ሥራ ውስጥ የምንሳተፍ ከሆነ የሐዋርያት ሥራን ታሪክ እየቀጠልን ነው ማለት ነው፤ ምክንያቱም ወንጌል ገና በዓለም ዙሪያ ሁሉ መዳረስ አለበት። የኢየሱስ ተከታይ የነበሩት ምሥክሮች ሥራቸውን የጀመሩት ከኢየሩሳሌም ነው። እንዴትስ አድርገው ከኢየሩሳሌም በመነሳት በዚያን ጊዜ ይታወቅ ወደ ነበረው ዓለም እንደተስፋፉም እናጠናለን።

ጥያቄ 7:- አንተና ቤተክርስቲያንህ ይህን የምሥክርነት ሥራ እንዴት በመቀጠል ላይ እንዳላችሁ ግለጽ።

ደቀመዛሙርቱ ከዚህ በፊት ለእስራኤል መንግሥት ትመልሳለህን ብለው በጠየቁት ጊዜ ኢየሱስ «አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም» ብሎ ነው የመለሰላቸው (ሐዋ. 1:7)።

ጥያቄ 8:- ለምንድነው አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ የሚመጣበትን ጊዜ ለመወሰን የሚጥሩት?

የጥንቷ ቤተክርስቲያን ምዕመናኖች ኢየሱስ ወደ ምድር ቶሎ ተመልሶ መንግሥቱን ይመሠርታል ብለው ይጠብቁ ነበር። እስከ አሁን እስከ 2000 ዓመት ድረስ ደግሞ ምፅዓቱን ያዘገየዋል ብለው አልገመቱም ነበር። ሁላችንም ኢየሱስ በእኛ የሕይወት ዘመን ሊመለስ ይችላል ብለን በመጠባበቅ መኖር አለብን። ይህም ቢሆን መቼ እንደሚመጣ ግን አናውቅም። ባናውቅም፤ ስለእኛ ተመልሶ እስከሚመጣ ድረስ ለእርሱ ታማኞች ሆነን እንኑር። ክርስቶስ የሚመጣበትን ጊዜ መወሰኑ፤ በእኛ በኩል

ስሕተት ብቻ ሳይሆን፤ ያ የተወሰነው ጊዜ ሲደርስና ገና ኢየሱስ ሳይመጣ ሲቀር፤ የክርስቶስ ስም በማያምኑ ሰዎች እጅጉን እንዲዋረድ እናደርጋለን።

ደቀመዛሙርት የእርሱ ምሥክሮች እንዲሆኑ ካዘዛቸው በኋላ፤ «ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል እንዲጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ እንዳጠመቀ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ» ብሎ አላቸው (የሐዋርያት ሥራ 1:4-5)።

መጥምቁ ዮሐንስ፤ የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር መንግሥት ዝግጁ እንዲሆኑ፤ ለንስሐ ይጠራቸዋል። አይሁዶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጠንቅቀው ያውቃሉ፤ ጥምቀትም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመተላለፋቸው ንስሐ እንዲገቡ የሚገልጹበት ሥርዓት ነው (ማቴ. 3:6 እና ማርቆ. 1:5 ተመልከት)።

**ጥያቄ 9:- ሀ. ስለ ውሃ ጥምቀት፤ ቤተክርስቲያንህ የምትሰጠው ትምህርት ምንድነው? ወይም የውሃ ጥምቀት የሚሰጥበት ምክንያት ምንድነው ትላለች? ለ. ጥምቀትን በተመለከተ ሰዎች የሚያምኗቸው አንዳንድ የተሳሳቱ ትምህርቶች ምንና ምን ናቸው?**

ከመጀመሪያው ጊዜ አንስቶ የውሃ ጥምቀት በክርስቲያኖች ዘንድ የተለመደ ነው። ጥምቀት፤ ያ የሚጠመቀው ሰውዬ የኢየሱስ ተከታይ እንደሆነ የሚያስመሠክርበት ሥርዓት ነው። ከጥምቀት ጋር ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ መቀበልና ስለ ኃጢአት ንስሐ መግባት የሚሉት ተግባሮች አለባቸው። ጳውሎስ ጥምቀትን ከክርስቶስ ጋር አብሮ እንደመቀበር እንደሆነ ወይም የቀድሞውን አኗኗር እንደመተው አድርጎ ያቀርበዋል (ሮሜ 6:3-4)። ሆኖም፤ የቀድሞውን አኗኗር መተው ማለት ቀን በቀን ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ማድረግ ለመንፈስ ቅዱስና ለእግዚአብሔር ቃል በየቀኑ መታዘዝ ማለት ነው። የጥምቀት ሥርዓት በራሱ ምንም ኃይል የለውም፤ ነገር ግን ሰውዬው በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ሕይወት እንዳገኘ የሚያስመሠክርበት ሥርዓት ነው።

**ጥያቄ 10:- ሀ. በኢየሱስ ላይ ያለህን እምነት መጠመቅ አለባችሁ የሚለውን ትዕዛዙን በመጠበቅ አስመስክረሃልን? ካላስመሰከርክስ ለምን? ለ. በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ተጠምቀዋልን? ካልተጠመቁስ ለምን?**

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የአብ ስጦታ ነው፤ ይህንንም የምናገኘው ኢየሱስ ከኃጢአት ያድነናል ብለን በእምነት ስንቀበለው ነው። ኢየሱስ የሰው ልጆችን በሙሉ ከኃጢአት ታድጓቸዋል፤ ለተቀበሉት ሰዎች ደግሞ አዲስ ሕይወት ይሰጣቸዋል። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ አዲሱን ሕይወታችንን በደንብ እንድንኖር ኃይልን ይሰጠናል።

ኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከሰጣቸው በኋላ፤ ደቀመዛሙርቱ ወደ መንግሥተ ሰማያት በክብር በደመና ተሸፍኖ ሲሄድ ተመልክተውታል። አንጋጠው እየተመለከቱት ሳለ ሁለት መላእክቶች መጥተው፤ ይህ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ

ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት ልክ እንደዚሁ ዳግመኛ ወደ ምድር ይመለሳል የሚል የተስፋ ቃል ይሰጧቸውና ያጽናኗቸዋል። ይህም፤ ሲመጣ አመጣጡ የሚታይና ምናልባትም በክብር በደመና በደብረዘይት ተራራ የሚገለጥ ዓይነት ሳይሆን አይቀርም ማለት ነው (ማቴ. 24፡30 ተመልከት)።

ጥያቄ 11፡- የኢየሱስን ደግሞ ምፅዓት፤ በተስፋ እየተጠባበክ ነው? ይህ በሕይወትህ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ነው የሚያኖረው?

ኢየሱስ እንዳዘዛቸው ደቀመዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው መንፈስ ቅዱስን ሲጠባበቁ ነበር። ከኢየሱስ እናት ከማሪያም፤ ከወንድሞቹና ከሌሎቹ ሴቶች ጋር ተገናኝተው በብርቱ ያለማቋረጥ ይጸልዩ ነበር። የኢየሱስ ወንድሞች በእርሱ እንደሚያምኑ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዚህ ሥፍራ ነው። ከትንሣኤው በፊት፤ በኢየሱስ ላይ ጥርጣሬ አድሮባቸው ነበር (ዮሐንስ 7፡3-5 ተመልከት)። ወደ በኋላ አካባቢ፤ አንደኛው በኢየሩሳሌም የሚገኘው ቤተክርስቲያን መሪ እንደሆነ እናያለን።

እማኞቹ መንፈስ ቅዱስን እየተጠባበቁ ሳለ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ያጠኑ ነበር። በዚያም፤ ዳዊት ጠላት በሆነው ምትክ ሌላ እንዲመረጥ የተነበየውን ትንቢት አገኙ (መዝ. (109)፡8)። ደቀመዛሙርቱ ይህ ትንቢት ስለ ይሁዳ በሌላ አሥራ ሁለተኛ ደቀመዛሙርት ስለመተካት የተነገረ ነው ብለው ተመለከቱት። ኢየሱስን ከካደ በኋላም፤ ይሁዳ ሠላሳውን ብር ለካህናቱ አለቃ መልሶ ሰጥቶ እራሱን ሰቀለ (ማቴ. 27፡3-10 ተመልከት)። በኋላ ላይም፤ ምናልባት ማንም ሬሳውን ስላልቀበረው በስብሶ ወደ መሬት ብመውደቁ ተሰንጥቆ ይሆናል። ለካህናቱም የሰጠው ገንዘብ፤ ለመቃብር ቦታ መግዣ ነው የዋለው።

በይሁዳ ቦታ ሰው ለመተካት፤ ሐዋርያቱ፥ ሐዋርያ ለመሆን ማሟላት የሚገባው ሁለት ነገሮችን ካሟላ በኋላ ከባርናባስና ከማትያስ መካከል አንዱን መርጠዋል። እነዚህ መሟላት የነበረባቸው ነገሮች፡- 1. ይህ ሰዎ ኢየሱስ በዮሐንስ ከተጠመቀበት ጊዜ ነሥቶ እስከ ዓረገበት ጊዜ ድረስ በእርሱ መሆን አለበት፤ 2. ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ የሚመሠክርም መሆን አለበት።

ሐዋርያቱ ከጸለዩ በኋላ ዕጣ ጣሉ፤ ዕጣው ለማቴዎስ በመውጣቱ በይሁዳ ፋንታ እሱ ተተካ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ሲባል በእስራኤላውያን ዘንድ የተለመደው ዕጣ መጣል ነበር። ሆኖም፤ መንፈስ ቅዱስ ከመጣ ይህን ዓይነቱን ሥርዓት ይጠቀሙበት አይጠቀሙበት የሚገልጽ ምንም ማስረጃ የለም። በምትኩ ግን ዛሬ ላሉ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚገለጽላቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለሆነም በእግዚአብሔር ፊት አንዳንድ ሙከራዎችን ወይም ዕጣን በመጣል ፈቃዱ መሆኑና አለመሆኑን ለመለየት ጥረት ማድረግ የለብንም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ቃሉን ማጥናት አለብን፤ እግዚአብሔር የገለጠልንን በታማኝነት እየጠበቅን መኖር አለብን።

ጥያቄ 12፡- ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በሕይወታቸው ያለውን ፈቃድ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው የሚወስኑት?

ደቀመዛሙርቱ ሌላ ሐዋሪያ በመምረጣቸው ስሕተተኞች ናቸው የሚል ማስረጃ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አናገኝም። አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ ገና ስላልተሰጣቸው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ነበሩ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ አሥራ ሁለተኛው ደቀመዝሙር ጳውሎስ መሆን ነበረበት ይላሉ። ሆኖም ይህ ነገር በአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ውስጥ በግልጽ የተቀመጠ ነገር አይደለም።

ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ የተናገራቸው የመጨረሻዎቹ ቃላቶች ያተኮሩት በመንፈስ ቅዱስ ላይና በተከታዮች ምሥክር የመሆን አስፈላጊነት ላይ ነበር። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን እሱ ሊሰጣቸው ያለውን ኃይል እንዲጠባበቁ ነገሯቸዋል፤ ይህን ያለው አንድ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ምሥክር ሆኖ ለእርሱ ክብር መኖር የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት ብቻ እንደሆነ ስለሚያውቅ ነው። መንፈስ ቅዱስ በመጠባበቅ ላይ ሳሉ፤ ደቀመዛሙርቱ ጊዜያቸውን ያሳልፉ የነበረው በመጸለይ ነበር። እራሳቸውንም ለወደፊቱ አገልግሎታቸው ዝግጁ ለማድረግ፤ በይሁዳ ምትክ የሚተካውን ሰው ሾመዋል።

የእግዚአብሔር ልጆች ልክ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመኑ፤ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ። የመንፈስ ቅዱስ ዓላማ ለአማኞች ኃይል መስጠት ነው። ይህንንም በማድረግ የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖራቸውና በድፍረት ስለክርስቶስ እንዲመሰክሩ ያደርጋቸዋል።

ጥያቄ 13:- የመንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወትህ መምጣት፤ የለወጠህ እንዴት ነው?

## ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 2:1-13

ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ባረገበት ጊዜ፤ ደቀመዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ይጠባበቁ ነበር። በሚጠባበቁበት ወቅት የእግዚአብሔር ቃል ያጠኑና ይጸልዩ ነበር። ይህ ተስፋ የተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ «... እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ» የሚለውን የኢየሱስን ትዕዛዝ እንዲፈጽሙ፤ ዝግጁ ያደርጋቸዋል (ሐዋ. 1:8)።

ኢየሱስ ካረገ ከአሥር ቀን በኋላ፤ ደቀመዛሙርቱ ለጸሎት ተሰብስበው በነበሩበት ወቅት፤ እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይልካል። ይህ እግዚአብሔር ሕዝቦቹን የሚያስተዳድርበት አዲስ ዘመን የተከፈተበት ወቅት ነው። ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ሞቶ ከሙታን በተነሣ ጊዜ፤ ቀጥታ ፊት ለፊት ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበትን አዲስ መንገድ ነው የከፈተልን። ኢየሱስ ባረገበት ጊዜ ደግሞ፤ ቃል የገባበትን ስጦታ ልኳል። ስለዚህም አንዳንዱ አማኝ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ሲሆን፤ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይቀበላል።

የሐዋርያት ሥራ 2:1-13 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ። ጥያቄ 14 ሀ. 1. አብ ይልክላችኋል ብሎ ኢየሱስ ተስፋ የሰጠው ስጦታ ምንድነው? 2. ስጦታው እንደተላከ የሚያረጋግጡልን ምልክቶች ምንና ምንድናቸው? 3. ስጦታው የተሰጠው

ለነማነው? ለ. 1. ለምን ነበር በኢየሩሳሌም ብዙ ሰዎች የነበሩት? 2. ከየት የት አገር ነው የመጡት?

መንፈስ ቅዱስ የመጣው፣ «በጴንጤቆስጤ ዓመት በዓል ወይም በበዓለ ሃምሳ» ላይ ነበር። ጴንጤቆስጤ ማለት ሃምሳ ነው። «የሳምንታት ክብረ በዓል» የሚልም ስያሜ ይሰጠው ነበር፣ ምክንያቱም ይህ ቀን የሚውለው ፋሲካ በዋለ ከሰባት ሳምንታት ወይም ከ ሃምሳ ቀን በኋላ በመሆኑ ነው። ይህ ጊዜ ደግሞ የገብስ የመከር ጊዜ የሚጠናቀቅበት በመሆኑ «የመከሩ ክብረ በዓል» የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል (ኦሪት ዘሌዋውያን 23፡15-16)። ይህ በዓለ ሃምሳ፣ ከዋነኞቹ የአይሁዳውያን መንፈሳዊ ክብረ በዓሎች ውስጥ አንደኛው ነው፣ በዚህም ጊዜ ወንድ የተባለ ማንኛውም አይሁዳዊ ቤተመቅደስ ድረስ መጥቶ እግዚአብሔርን ማምለክ ነበረበት። በአለም የተበታተኑት አይሁዳውያን ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው እግዚአብሔርን የሚያመልኩበትም አሥራታቸውን የሚከፍሉበት ጊዜ በመሆኑም፣ ዋነኛው መንፈሳዊ ክብረ በዓል ነው። ደግሞም ብዙ አይሁዳውያን ከተለያዩ አገሮች፣ እግዚአብሔር መንፈሱን በላከበት ወቅት በኢየሩሳሌም ተከማችተው የነበሩት ለዚህ ነው።

በኢየሩሳሌም ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች አይሁዳውያንና የቀድሞውን የአይሁዳውያንን ሃይማኖት ይከተሉ የነበሩ በአኅራባች አገሮች ይገኙ የነበሩ አሕዛብ ናቸው። ከሰሜን አፍሪካ፣ ከዓረብያ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከእስያና እንደ ሮም ሩቅ ከሆነም ሀገር አይሁዳውያን መጥተው ነበር። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሱን በዚህን ጊዜ የላከው አውቆ ነው፣ ምክንያቱም ከእነዚህ መካከል በኢየሱስ የሚያምኑት ሰዎች ክብረ በዓሉን አክብረው ወደ ሚኖሩበት አገር ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን ወንጌሉንም እያስፋፉት ይሄዱ ነበርና ነው።

ጥያቄ 15፡- ከዚህ መጽሐፍ ጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከትና እነዚህ አይሁዳውያን ከየት የት እንደመጡ ተመልከት።

ኢየሱስ እንዳዘዛቸው በበዓለ ሃምሳ ዕለት የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች በአንድ ቦታ ተቀምጠው የእግዚአብሔር አብን ስጦታ ይጠባበቁ ነበር። ኢየሱስ «ኃይልን ትቀበላላችሁ» የሚል የተስፋ ቃል ሰጥቷቸው ነበር። ደቀመዛሙርቱ በራሳቸው ምንም ኃይል የላቸውም ሆኖም ወንጌሉን በዓለም ሁሉ የማሰራጨቱ ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ነበር። እየጸለዩ በመጠባበቅ ላይ ሳሉ፣ የኢየሱስን የመጨረሻውን ትዕዛዝ እንዴት አድርገን ነው የምንጠብቀው ብለው ሳይጠይቁ አልቀሩም። ይህ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀመዛሙርት አድርጉ» የሚለው ትዕዛዝ የተሰጠው ለደቀመዛሙርቱ ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬ ኢየሱስን ለምንከተል ሰዎችም ጭምር ነው።

ጥያቄ 16፡- ሀ. ኢየሱስ ተስፋ የሰጠው ኃይል በአንተ ውስጥ አለ? ለ. የዚህ ኃይል መኖር በሕይወት ውስጥ የሚታየው ወይም የሚገለጸው እንዴት ነው?

ጥያቄ 17፡- «እስከ ምድር ዳርቻ ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ» የሚለውን የኢየሱስን ትዕዛዝ ለመፈጸም በሕይወትህ ምን ምን ነገሮች ነው የምታደርገው?

ደቀመዛሙርቱ በጸሎት ይጠባበቁ በነበረበት ወቅት፤ በድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ዓይነት ድምፅ ከሰማይ መጣ። ይህ ድምፅ፤ ተሰብስበው የነበሩበት ቤት ሞላው። እንደ እሣት የተከፋፈሉ ልሣኖች በእያንዳንዱ አማኝ ላይ ተቀመጡባቸው፤ ከዚያም ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ። ከዚያም ወዲያውኑ ደቀመዛሙርቱ፤ የሚሆነውን ነገር ለማየት ተሰብስበው በነበሩበት ሰዎች ቋንቋ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመሩ። ሰዎቹ የገሊላ ሰዎች በእነርሱ ቋንቋ በመነጋገራቸው በጣም ተደነቁ። አንዳንዶች ደቀመዛሙርቱ ሰክረዋል ብለው ያሾፉባቸው ነበር፤ ሌሎች ግን «ይህ ምን ይሆን? ብለው ጠየቁ።

ጥያቄ 18፡- እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲልክ፤ ይህን ዓይነት ምልክት ያሳየው ለምንድነው?

ጥያቄ 19፡- ዛሬስ እኛ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበልን እርግጠኞች የምንሆነው እንዴት ነው?

አስታውስ፤ ይህ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የብሉይና የአዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ጊዜ ነው፤ እግዚአብሔር በአዲስ መንገድ ከሰዎች ጋር በመንፈስ ቅዱስ መገናኘት የጀመረበት ጊዜ ነው። ስለዚህም፤ ይህን የሽግግር ጊዜ ገሃድ ለማውጣት ተስፋ ለሚያደርጉት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንደመጣ ለማሳየትና ይህ ለውጥ እንደተካሄደ የብሉይ ኪዳንን የመሥዋዕትና የክብረ በዓል የአምልኮ ሥርዓት ብቻ የሚያውቁት እንዲረዱት ሲል፤ እነዚህን ምልክቶች (የእሳት ልሣኖች) እንደ ማስረጃ ተጠቅመባቸው።

ዛሬ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እንደላከ ለማረጋገጥ፣ እግዚአብሔር የልሣንን ስጦታ መጠቀም የለበትም። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን፤ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በነፃ እንደሚሰጥ ተጽፏል። መንፈስ ቅዱስም ከእኛ መንፈስ ጋር በመሆን የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ይመሰክርልናል (ሮሜ 8፡16 እና 1ኛ ዮሐ. 3፡24 ተመልከት)። መንፈስ ቅዱስ በእኛ ሕይወት ስለመኖሩ ትልቅ ማስረጃ ሊሆነን የሚችለው፤ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች እግዚአብሔር በሕይወታችን በሚሠራው ሥራ በእኛ ውስጥ ተገልጠው ሕይወታችንን መለወጡ ሲታይ ነው (ገላ 5፡22-23 ተመልከት)።

አማኞች በሌሎች ሰዎች የቋንቋ ልሣኖች የተናገሩበት ወቅት ይህ ብቻ ነው። ከሌሎች ስፍራዎች ግን ሰዎች በሚታወቅ የሰዎች ቋንቋ ይሁን በማይታወቅ ቋንቋ ልሣኖች ይናገሩ እንደነበሩ የሚታወቅ ነገር የለም (ሐዋ. 8፡14-17፤ 10፡44-46፤ 19፡1-7)። ይህም ቢሆን፤ በሁሉም አማኝ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መኖር የሚታወቀው በልሳን በመናገራቸው ብቻ እንዳልሆነ፤ ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንረዳለን። በተጨማሪም ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12፤ ይህ በልሣን የመናገር ስጦታ ለአንዳንድ ሰዎች ብቻ የሚሰጥና፤ ከስጦታዎች ሁሉ የበታች እንደሆነ በግልጽ ያስቀምጠዋል።

ጥያቄ 20፡- አንዳንድ ክርስቲያኖች ከሚያስተምሩት ትምህርት ይህ ለየት የሚለው እንዴት ነው?

ለሁላችን አደገኛ ሆኖ የሚገኘው ነገር ልባችን ቀና ባለመሆኑ ምክንያት አምልኮአችን ባዶና ሥርዓት ብቻ ሆኖ ሲቀር ነው። ይህም በተለይ በልሣን የመናገር ችሎታ ወይም ስጦታ አለን ብለው ለሚኩራሩት ሰዎች በበለጠ አደጋ ላይ የሚጥላቸው ይሆናል። አምልኮአችን «በመንፈስና በእውነት» ሳይታገዝ ዝም ብሎ ልማድ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን (ዮሐ 4፡24 አንብብ)። በነቢዩ አሞፅ ዘመን አይሁዳውያን በራሳቸው ኃይል ሙሉ በሙሉ ደስተኞች ሆነው ስለነበር፤ በሕይወታቸው ውስጥ ብዙ ኃጢአትን ይለማመዱ ነበር። እግዚአብሔርም በነቢዩ በኩል «ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ ተፀይፌዋለሁ፤ የተቀደሰም ጉባዔአችሁ ደስ አያሰኘኝም» ብሎ ተናግሯል (አሞፅ 5፡21-27)። አይሁዳውያን መሥዋዕታቸውን በማቅረብ ለእግዚአብሔር ክብር ይሰጣሉ ተብለው የሚገምቱትን በዓላትን ያከብሩ ነበር፤ ነገር ግን ልባቸው ትክክል አልነበረም። ጽድቅን ከመለማመድ ፈንታ እነርሱ ጣዖቶችን ነበር የሚያመልኩት።

እኛም ብንሆን ቤተክርስቲያን በመሄድ መዘምራን ሆነን በማገልገል፤ አሥራታችንን በወቅቱ በመክፈል፤ ቃሉን በማስተማር ወይም በመመስከር እና በልሣን በመናገር ወይም ተአምራትን በመሥራት ላይ እያለን እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ላናመልከው እንችላለን። በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት ካለ ወይም ደግሞ የምናገለግለው ከተሳሳተ አስተሳሰብ ተነሣሥተን ከሆነ እግዚአብሔር ቅር ይሰኛል፤ አምልኳችንም አገልግሎታችንም ባዶ ይሆናል።

ጥያቄ 21፡- አምልኮህ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይመስልሃል ወይስ ዝም ብለህ በዘልማድ የአምልኮ ሥርዓቶችን በመከታተል ላይ ነህ? ለመልስህ ምክንያቶችን ሥጥ።

ለጥንት ክርስቲያኖች ቃል ተገብቶላቸው የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለኢየሱስ እንዲኖሩና ምስክሮችም እንዲሆኑ ኃይልን ሰጥቷቸዋል። የእግዚአብሔርን ቃል የማንታዘዝና በመንፈስ ቅዱስ የማንመራ ከሆነ፤ ክርስቶስን ልናገለግል ወይም ለእርሱ ልንኖር አንችልም። መታዘዝ የእግዚአብሔር ኃይል እንዲወርድ ያደርገዋል። በሌላው ወገን ደግሞ ኃጢአትና አለመታዘዝ መንፈስ ቅዱስ በራሳችን ሕይወት በእኛ ውስጥ አልፎ በሌሎች ሕይወት ውስጥ እንዳይሠራ እንቅፋት ይሆናሉ በዚህም ምክንያት የፈለገነውን ያህል ለእርሱ ክብር ለመሥራት ብንሞክር፤ ኃይሉ በእኛ ውስጥ አይገለጥም።

ጥያቄ 22፡- በሕይወትህ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የሚቀናቀን ነገር አለን? ካለ ለትንሽ ጊዜ ቆም በልና ኃጢአትህን ተናዘዝ።

በሕይወታቸው ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በመኖሩ፤ የጥንቶቹ ሐዋርያት ዓለምን ለመቀየር ችለዋል። ዛሬ ግን ብዙ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እምብዛም አይታይም። ምናልባትም ለዚህ ይሆናል በዓለም ላይ ጉልህ የሆነው ተጽዕኖ የማናሳየው። የመንፈስ

ቅዱስ ኃይል በልሣን በመናገር ብቻ ሳይሆን፤ በአነጋገራችንና በአኗኗራችንም ጥምር ጽኑ ምሥክሮች እንደሚያደርገን አድርገን ብንመለከተው፤ ዓለምን መቀየር በቻልን ነበር። ሆኖም ይህ ኃይል በሕይወታችን ውስጥ እንዲታይ እራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት አለብን። ይህን እያደረግን ነው?

## ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 2፡14-41

አይሁዳውያን ከብዙ የተለያዩ አህጉሮች ለበዓለ ሃምሳ በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ሳሉ መንፈስ ቅዱስ የቤተክርስቲያንን መመሥረት ለማብሠር በታላቅ ኃይል ወረደ። ይህ በተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ሁከትን ፈጠረ፤ አንዳንዶቹ በሁኔታው ተደንቀው ነበር ሌሎች ደግሞ ሰዎቹ ሰክረው ነው ብለው ነገሩን ችላ ብለውት ነበር።

ብዙ ጊዜ የደቀመዛሙርቱ መሪ የነበረው ጴጥሮስ፤ ብድግ አለና የበዓለ ሃምሳውን ስብከቱን መስበክ ጀመረ። በስብከታቸው ደቀመዛሙርቱ ብዙ ጊዜ ስለ አለፈው የእስራኤላውያን ወይም የአይሁዶች ታሪክ ይጠቅሱ ነበር። ያለፈውን ታሪክ የሚናገሩበት ምክንያት ነበራቸው። ይህን ክፍል እያነበብክ ሳለ፤ እስቲ ለምን ጴጥሮስ ታሪኩን እንደተናገረ ለማወቅ ሞክር።

የሐዋርያት ሥራ 2፡14፡41 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ። ጥያቄ 23 ሀ. ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር ያደረገው ማነው? ለ. የጴጥሮስን መልእክት በአንድ ሐሳብ የሚያጠቃልል ቁጥር ጥቀስ። ሐ. ጴጥሮስ መልእክቱን የሚያቀርበው ለማነው? መ. ጴጥሮስ የትኞቹን የብሉይ ኪዳን ነቢያት ነው የሚጠቅሰው ሠ. ጴጥሮስ የብሉይ ኪዳኑን ክፍል የጠቀሰው ምንን ለማስረዳትና ለመግለጽ ፈልጎ ነው? ረ. «ምን ማድረግ አለብን?» ብለው ሲጠይቁት፤ ጴጥሮስ የሰጣቸው መልስ ምንድነው?

ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ሆኖ በዙሪያቸው ለተሰበሰቡት ሰዎች፤ ይህ የሚያዩት እሣትና የሚሰሙት ንግግር (ልሣን) የብሉይ ኪዳን ትንቢት እንደሆነ ይነግራቸዋል። የብሉይ ኪዳን ነብያት የጻፏቸው ትንቢቶች ለአይሁዳውያን የሚያውቋቸው በመሆናቸው፤ እግዚአብሔር ምን እንደሚሠራ ለማስረዳት ይጠቀምባቸዋል።

ጴጥሮስ ንግግር ያደረገው ከሌላ አገር ለመጡና በዛው በኢየሩሳሌም ውስጥ ይኖሩ ለነበሩ አይሁዳውያን ነው። ንግግሩንም የሚጀምረው፤ ከነቢዩ ኢዩኤል ትንቢት ላይ በመጥቀስ ነው። ሐዋርያቱ የመንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ መውረድ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚሠራበትን አዲስ የሆነ ዘመን እንደ ጀመረ የሚያሳይ መሆኑን ተረድተውት ነበር። የብሉይ ኪዳን ዘመን አሁን እንደተፈጸመ አውቀዋል፤ ይኖሩ የነበረውም «በመጨረሻዎቹ ቀኖች ውስጥ ነው። በመጨረሻዎቹ ቀኖች እንደሚኖሩ የሚያሳየው ትልቁ ማስረጃ «ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ» የሚለው የተስፋ ቃል መፈጸሙ ነው። መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ለሚያምኑ ሰዎች በሙሉ ነው፤ ለአይሁድ ለአሕዛብም። ኢዩኤል በተጨማሪም «ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን

ያልማሉ፤ ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች አገልጋዮቼ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ» ብሎ ተናግሯል (ኢዩኤል 2፡28-32)። ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ጊዜ እግዚአብሔር፤ መንፈሱን ለነቢዛዝት ብቻ መስጠቱ በመተው፤ አሁን መንፈስ ቅዱሱን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ይሰጣል። እግዚአብሔር መንፈሱን ሲሰጥ የዕድሜ፤ የፆታና፤ የዜግነት፤ ልዩነት ፍጹም አያደርግም።

ጥያቄ 24፡- ይህ የተለየ ፆታና ጎሳ ባላቸው ሰዎች ላይ ሊኖር ስለሚገባው አመለካከት የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?

ከመንፈስ ቅዱስ መምጣት ጋር፤ በኢየሱስ ለማያምኑ ሁሉ ሁለተኛ ታላቅ በረከት ይፋ ሆኖላቸዋል። ወንድ ይሁን ሴት፤ ባሪያ ይሁን ጌታ፤ ሁሉም ከእግዚአብሔር መነጋገር ይችሉ ነበር፤ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር። እግዚአብሔር የሰጣቸውን መልእክት ከሌሎች ለመስማት ሲሉ ወደ ሰው መሄድ አልነበረባቸውም። የወንጌሉ መልእክት የአይሁዳውያን መንፈሳዊ መሪዎች በሆኑ በካህናትና በሽማግሌዎች ዘንድ ብቻ የተያዘ አይሆንም። በበዓለ ሃምሳና ከዚያን በኋላ፤ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በድንቅና በተአምራት ታጅቦ ሰዎችን ትንቢት እንዲናገሩ አድርጓቸዋል። እነዚህ በጥንቲቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ ለየት ያሉ ባሕሪያት የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ያመለክታሉ። ሆኖም አንዳንዶቹ የኢዩኤል ትንቢቶች ገና አልተፈጸሙም ነበር (ሐዋ. 2፡19-12፤ ከሉቃስ 21፡11፤ 25 ጋር ተመልከት)።

ጥያቄ 25፡- ሙሉ በሙሉ በበዓለ ሃምሳ ዕለት ያልተፈጸመው የኢዩኤል ትንቢት የትኛው ነው?

ጴጥሮስ፤ አዲስ ዘመን መምጣቱን ከተናገረ በኋላ፤ የወንጌሉ ዋነኛ መሠረት ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ለአይሁዳውያን ይገልጽላቸዋል። ይህ መልእክቱ በጥንት ዘመን በተለይም ለአይሁዳውያን የቀረቡትን ዓይነት መልእክቶችን ያመለክታል።

1. ኢየሱስ በሕዝቡ ፊት ያደረገውን አገልግሎት ለአንድ አፍታ መለስ ብሎ ይጠቅሰዋል፡- ይህም መሲሕ መሆኑን የሚያረጋግጡልንን ምልክቶችና ተአምራቶችን ነው።
2. ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ ይናገራል፤ ለዚህም ደቀመዛሙርቱ የዓይን ምስክሮች ናቸው፤ በተጨማሪም ይህ እራሱ መሢሕ እንደሆነ ማረጋገጫ ነው።
3. ከብሉይ ኪዳን ትንቢቶች በመነሣት፤ ኢየሱስ መሢሕ እንደሆነ ያረጋግጣል።
4. በመጨረሻም፤ ሰዎቹ ንስሐ ገብተው፤ ኢየሱስን አምነው እንዲቀበሉት ይገፋፉቸዋል።

ጥያቄ 26፡- ከእነዚህ አራት ነገሮች ውስጥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መቅረብ አለበት ብለህ የምትገምተው የተኛው ነው? ከእነዚህ ውስጥ ላልዳኑት ሰዎች እስኪድኑ ድረስ ብዙም አያስፈልጋቸውም ብለህ የትምገምታቸው የተኛዎቹን ነው? ለምን?

አይሁዳውያን ይህ ከሮማውያን ቅኝነት ያድነናል ብለው የሚገምቱትን መሢሕ መሞት ሊቀበሉትና ሊገነዘቡት አልቻሉም። ስለዚህም ጴጥሮስ፤ የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች በመጥቀስ፤ ስለመሢሑ ሞት የተተነበዩትን ትንቢቶች ያሳያቸዋል። ዳዊት በመዝሙረ ዳዊት (16)፡10 ላይ፤ ስለመሢሑ ሲናገር፤ ነፍሱን በሲዖል እንደማያስቀራትና በሥጋው በመቃብር ውስጥ ቀርቶ እንደማይበሰብስ ገልጿል። ዳዊት በዚህ ሥፍራ የሚናገረው ስለ ራሱ አልነበረም። ጴጥሮስ፤ ዳዊት «ቅዱስህንም» ብሎ የሚጠራው የናዝሬቱን ኢየሱስን እንደሆነና፤ እሱንም እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሳው ነው የሚናገረው። ኢየሱስም በበዓለ ሃምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስን ወደ ላከው ወደ አብ ነው ያረገው።

ጴጥሮስም በመቀጠል፤ «እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም (መሢሕ) እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይወቅ» ብሎ ይናገራል። የእስራኤልን ሕዝብ ይመራል ተብሎ ከጥንት ጀምሮ የሚጠበቀው፤ እግዚአብሔር የሚመርጠው መሢሕ እሱ ነበር። በዚያን ጊዜም ስለሆነው ነገር ጴጥሮስ የሰጠውን ማብራሪያ ብዙ ሰዎች በመቀበላቸው «ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?» ብለው ይጠይቃሉ፤ ጴጥሮስም፤ «ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና» አላቸው፤ (ሐዋ. 2፡37-39)።

**ጥያቄ 27፡-** ይህን ጥሪ ተቀብለህ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀብለሃልን? ጥሪው የተሠጠው፤ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ለመሆን ለሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ ነው።

**ጥያቄ 28፡-** ለሌሎች ስትመሠክር ያንተ ምሥክርነት ከጴጥሮስ መልእክት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? የሚለያየውስ እንዴት ነው? ለምንድነው የተለየ የሆነው?

**ጥያቄ 29፡-** የሐዋርያት ሥራ 2፡38 ከማቴዎስ 28፡19 ጋር አነፃፅር።
ሀ. እነዚህ ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ናቸው?
ለ. ጴጥሮስ «በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ» ያለውና ኢየሱስ ደግሞ «በአብ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቁ» ያለው ለምንድነው?

ብዙ ሰዎች በሐዋርያት ሥራ ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ እያለ፤ ለምንድነው በማቴዎስ 28፡19 ላይ ደግሞ በአብ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቁ የሚል ትዕዛዝ ኖረ ብለው ይጠይቃሉ (ሐዋ. 2፡38፤ 8፡16፤ 10፡48፤ 19፡5 ተመልከቱ)። እነዚህ ጥቅሶች እንደ ማረጋገጫ በመጠቀም፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከአሁን ወዲህ አብ ወይም መንፈስ ቅዱስ የሉም ያለው ኢየሱስ ብቻውን ነው ብለው ይናገራሉ። ከአዲስ ኪዳን ትምህርቶች እግዚአብሔር አንድ ቢሆንም፤ አብ፤ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በውስጡ እንዳሉ በግልጽ እናያለን። አብ ወልድን እንደላከው፤ አብና ወልድ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን እንደላኩ እናነባለን። ምንም እንኳ ስለ ሥላሴዎች

በቂ የሆነ ማብራሪያ ባንሰጥም፣ እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆናቸውና የሦስቱም በአንድ ጊዜ ውስጥ መኖራቸው አሌ የማይባል ግልጽ የሆነ ነገር ነው (ዮሐ 3፡16፣ 14፡16፣ 15፣26፣ 2ቆሮ. 13፡14)።

በሐዋርያት ሥራ ታሪክ ውስጥ ደቀመዛሙርቱ በኢየሱስ ስም ያጠምቁ የነበረው፣ በጊዜው የአይሁድን ሃይማኖት ይከተሉ ለነበሩት አይሁዳውያን ወይም አሕዛብ ብቻ ይሰብኩ ስለነበር ነው። በፊቱንም ቢሆን እነርሱ በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያምኑ ነበር። በእነርሱ ዋነኛውና ትልቁ ነገር በመስቀል ላይ የሞተው የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር እንደነበረና ስለ ኃጢአታቸው የሞተ እንደሆነ ማመናቸው ነበር። በኢየሱስ ማመናቸውን የገለጹት፣ በስሙ በመጠመቅ ነው። ኢየሱስ ግን «አሕዛብን ሁሉ እያስተማራችሁ ደቀመዛሙርቴ አድርጉ» ብሏል፣ አሕዛብ ደግሞ እንደ አይሁዳውያን ስለ እግዚአብሔር የጠለቀ እውቀት አይኖራቸውም፣ ስለዚህም ስለ እግዚአብሔር አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ትምህርት መማር አለባቸው። እነርሱ እምነታቸውን መግለጽ ያለባቸው ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ ነው።

ጥያቄ 30፡- በሐዋርያት ቤተክርስቲያን አባል ለሆኑ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ ሦስትም እንደሆነ የምትገልጽላቸው እንዴት ነው?

የተለያዩ ትምህርቶችን ሙሉ በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማስተያየት መመርመር እንዳለብን መዘንጋት የለብንም። ብዙ ጊዜ የሐሰት ትምህርቶች የሚጀምሩት አንድ መምህር ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዲትን ጥቅስ ወስዶ ከሷ ጋር የሚስማሙ አንድ ወይም ሁለት ጥቅሶችን ጨምሮ ትምህርቱን በዛ ላይ ሲመሠርት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን የጥቂት ጥቅሶችን ብቻ መጠራቀሚያ አለመሆኑን አስተውል! እምነታችን መመሥረት ያለበት በጥቂት ጥቅሶች ላይ ብቻ ነይሆን መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ በመመልከት በሱ ላይ ነው መመሥረት ያለብን።

የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስ ከእግዚአብሔር መላኩን ሁሉም ቢሆን እንደካዱ ነው። ጴጥሮስ ደግሞ በመልእክቱ ኢየሱስ የሠራው ነገር በሙሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ አበክሮ ይገልጽ ነበር። እግዚአብሔር ወደ ሞት መራው፣ ከሞት አስነሣው ከፍ ከፍ አደረገው። ይህ ደግሞ፣ ብዙዎችን ኢየሱስ እውነተኛው መሢሕ እንደሆነ አሳመናቸው።

በበዓለ ሃምሳ፣ ኢየሱስ ካረገ ከአሥር ቀን በኋላ፣ የወንጌሉ ምሥክሮች ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በጴጥሮስ ውስጥ አድሮ ብዙዎች ኢየሱስን እንደ መሢሕና እንደ አዳኛቸው እንዲቀበሉት ገፋፍቷቸዋል። በዚያን ዕለት፣ ሦስት ሺህ ሰዎች በአማኞች ማኅበር ውስጥ ተጨምረዋል።

በወንጌል ምሥክርነታችን ውስጥ ዋነኛ የሆነ ነገር ምንድነው? ለሰዎች አትስከሩ ሲጋራ አታጭሱ ወይም ዝሙት አትፈጽሙ ብሎ መንገሩ ነውን? ብዙ ወንጌላውያን

ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከማስረዳት ሰዎች ከዳኑ በኋላ ማድረግ የሚገባቸውን ነገር በማስረዳቱ ላይ ብዙ ጊዜ ጊዜያቸውን ይጨርሳሉ። አንድን ሰው ሊያድነው የሚችለው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለው እምነቱ ብቻ ነው። ሰዎች የተደነገጉ ሕግጋቶችን ለመጠበቅ ሲሉ አኗኗራቸውና አካሄዳቸውን ሊለውጡ ይችላሉ፤ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ እምነታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ካላደረጉ ይጠፋሉ። በምሥክርነታችን ውስጥ ትዕዛዘንና በኢየሱስ ላይ ያለን እምነት እንዳናቀላቅል መጠንቀቅ ይኖርብናል። ምንም እንኳ ሕግጋቱ ጥሩዎች ቢሆንም፤ እነሱን መጠበቁ አያድነንም።

ጥያቄ 31፡- ሀ. አንዳንድ ሰዎች ሲመሰክሩ እንዴት አድርገው በኢየሱስ ከማመኑ በላይ ይልቅ ሕግጋቱን በመጠበቁ ላይ እንዲያተኩሩ ምሣሌ በመሥጠት አስረዳ። ለ. አንተ እንዴት አድርገህ ለሰዎች እንደምትመሠክርና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደምትነግር ምሣሌ ስጥ።

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 2፡42-47

በበዓለ ሃምሳ ዕለት፤ የቃል ኪዳን ተስፋ የተጣለበትና የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነው መንፈስ ቅዱስ፤ በአማኞች ላይ ወረደና በምሥክርነታቸው ኃይልን አጎናፀፋቸው። ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ቃልና የመንፈስ ቅዱስ ኃይልም ብዙዎችን ወደ ጌታ ሳበ። መንፈስ ቅዱስ በተጨማሪም፤ አዳዲሶቹን አማኞች በመንፈስ እንዲያድጉ አድርጓቸዋል።

ዛሬ በትምህርታችን ውስጥ፤ መንፈስ ቅዱስ በቀድሞዎቹ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እንዴት ይሠራ እንደነበር እንመለከታለን።

የሐዋርያት ሥራ 2፡42-47 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 32፡- ሀ. ከበዓለ ሃምሳ በኋላ አማኞቹ የነበራቸው ሕብረት ምን ዓይነት እንደነበር ግለጽ። ለ. በሐዋ. 2፡42-47 ላይ፤ በአማኞቹ ሕይወት ውስጥ ይታዩ የነበሩትን ተግባሮች በዝርዝር ጻፍ። ሐ. እነዚህ ምግባሮች በቤተክርስቲያንህ ውስጥ እንዴት እንደሚታዩ ግለጽ።

ሰዎችን ወደ ክርስቶስ አምጥቶ በፈለጉት መንገድ እንዲሄዱ ማድረጉ ብቻ በቂ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እርሱን ለማወቅ የሚመጡ ሁሉ በእምነታቸውና በዕውቀታቸው እንዲያድጉ ይፈልጋል። በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት መጨረሻ ላይ ያሉ ጥቅሶች አዳዲሶች ክርስቲያኖች በእምነታቸው እንዲያድጉ ደቀመዛሙርቱ ምን ያደርጉ እንደነበር ይገልጻሉ።

ጥያቄ 33፡- ቤተክርስቲያንህ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች የምታደርጋቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? ምን ዓይነት ትምህርት ነው የሚሰጣቸው? የምትከታተሏቸውስ እንዴት ነው? ይህ ሊሻሻል የሚችለውስ እንዴት ነው?

# የሐዋርያቱ ተግባራት ያተኩሩ የነበረው በአራት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ነበር፡-

አንደኛ፡- በሐዋርያቱ ይሰጥ የነበረው ትምህርት ነበር። እነርሱ ከኢየሱስ ጋር ይኖሩ ስለነበር ከእርሱም ዘንድ በመማራቸው፤ ለማስተማር ብቁ ነበሩ። አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ ሲመጣ፤ ብዙ ጊዜ ስለ እውነት ያለው እውቀት በጣም ትንሽ ነው። ስለዚህም፤ በመጀመሪያ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ማድረግ ያለብን ነገር መሠረታዊ የሆኑትን እውነታዎች ከእግዚአብሔር ቃል ላይ በመውሰድ ማስተማር ነው። ስለ ጸሎት፤ ስለ ምሥክርነት፤ የእግዚአብሔርን ቃል ስለማጥናትና እግዚአብሔርን ስለማምለክ መማር አለባቸው። በተጨማሪም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙትንና የማያሰኙትንም ነገሮች መማር አለባቸው።

ሁለተኛ፡- ኅብረት ነበራቸው። የጥንት ክርስቲያኖች በአዲሱ እምነታቸውና በጌታ እውቀት እንዲያድጉ እርስ በርሳቸው መተጋገዝ እንዳለባቸው ተገንዝበው ነበር። የወንጌልን እውነታዎች ለማስረዳት መተጋገዝ አለባቸው። በስደትና የገንዘብ ችግር ባጋጠማቸውም ወቅት እርስ በርሳቸው መተጋገዝ አለባቸው። እነርሱም ንብረታቸውን መከፋፈልና በእምነታቸውም በኅብረት የመቆሙን ነገር ተስማምተውበታል።

ሦስተኛ ፡-እንጀራውን አብሮ የመቁረሱ ጉዳይም ነበር፤ ይህም ማለት የጌታን እራት በአንድ ላይ ይካፈሉ ነበር ማለት ነው።

የጥንት ክርስቲያኖች ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሐዋርያት ለመማር ጽኑ የሆነ ፍላጎት ስለነበራቸው፤ ወደየቤታቸው አይመለሱም ነበር። እንደምታስታውሱት፤ ብዙዎቹ አዳዲስ ክርስቲያኖች ከኢየሩሳሌም ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቀት ካለው ቦታ ነበር የመጡት። ወደ ቤታቸውም ከመምለሳቸው በፊት በእምነታቸው እንዲጸኑ ተገቢ የሆነውን ትምህርት በሙሉ በተቻለ መጠን መማር አለባቸው። ብዙዎቹ ደቀመዛሙርቶች የመጡት ከገሊላ ስለሆነ በኢየሩሳሌም ቤት አልነበራቸውም። ስለዚህም በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩት ክርስቲያኖች፤ ቤታቸውን ለእነዚህ አዳዲስ ክርስቲያኖች በመክፈት መጠለያና ምግብ ይሰጧቸው ነበር። አብረው ተቀምጠው በሚበሉበት ወቅት፤ ቃሉን የሚካፈሉበትና የኢየሱስ ሞት መታሰቢያ የሆነውን የጌታ እራት የሚያስቡበትም ጊዜ ነበራቸው።

በመጨረሻም፤ አብረው ይጸልዩ ነበር። ጸሎት፤ ከእግዚአብሔር የምንገናኝበት መንገድ ነው። እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ለመሥራትና ሕይወታችንንም ለመለወጥ የሚጠቀምበት መንገድ ነው። የጥንት ክርስቲያኖች ለአንድ የክርስቶስን ሕይወትና ለቤተክርስቲያን ዕድገት ጸሎት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ተገንዝበው ነበር።

የጥንት ክርስቲያኖች ገና አይሁዳውያን ስለ ነበሩ፤ እግዚአብሔርን በቤተመቅደስ ውስጥ ማምለኩን አላቋረጡም ነበር። በዚያም ሥፍራ፤ የእምነታቸውን እውነተኝነት ለሁሉም ሰዎች አሳይተዋል። የነበራቸው ደስታና ፍቅር ለሌሎች እንደ ምሥክር ሆኖ

በመታየቱ፤ ብዙዎቹን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ማመኑ ስቧቸዋል። ዛሬም፤ የማያምኑት ሰዎች ወደ ክርስቶስ ለማምጣት፤ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ባሕሪዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ መታየት አለባቸው።

በዮሐንስ 17፡22-23 ላይ ኢየሱስ እሱና አብ አንድ እንደሆኑ አማኞችም እንደዚሁ አንድ እንዲሆኑ ይጸልይላቸዋል። በአንድነታችንም ዓለም እሱ ማን እንደሆነ እንድታውቅና ሰዎች በእርሱ እንዲያምኑም ጸልዮዋል።

ጥያቄ 34፡- በቤተክርስቲያንህ ውስጥ የአማኞች አንድነት ስለ ክርስቶስ ለዓለም ምሥክር የሚሆን ዓይነት ነው?

አዳዲስ ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ወደ መጀመሪያው አካባቢ ጌታን ሲቀበሉ፤ በጌታ ሙላት ውስጥ ነው የሚኖሩት። በዚህም ጊዜ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት አዳዲሶቹ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያጠኑ፤ እንዲጸልዩ እንዲመሰክሩና ስለ ጌታ ኢየሱስ ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስተማር አለብን። ከሌሎቹ ክርስቲያኖች ብዙ ጥበቃና ፍቅር ያስፈልጋቸዋል። ከዚያም ከትንሽ ጊዜ በኋላ ፍቅራቸው እየቀዘቀዘ ይመጣል፤ እንደ በፊቱም ቶሎ ቶሎ አያድጉም።

ጥያቄ 35፡- ቤተክርስቲያንህ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች የምታደርገውን እንክብካቤ የበለጠ ልታጠናክርባቸው የምትችልባቸውን መንገዶች ጥቀስ።

# አምስተኛ ቀን፡-    የክለሳ ጥያቄዎች

1. በብሉይ ኪዳን ውስጥ፤ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምን ነበር?

2. ከበዓለ ሃምሳ ወዲህ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ከበፊቱ ለየት የሚለው እንዴት ነው?

3. ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ፤ ምን ዓይነት ማስረጃ ነው ያለው?

4. አሁን ባለው የክርስትና ጥምቀትና በመጥምቁ ዮሐንስ ጊዜ በነበረው ጥምቀት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

5. አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ የሚጠቀመው መቼ ነው?

6. ክርስትና በተጀመረበት አካባቢ ለምንድነው ድንቅና ተአምራት ብዙ ጊዜ ይታይ የነበረው?

7. እውነተኛ አምልኮ ምንድነው?

8. ለአይሁዳውያን የቀረበው የወንጌል መልእክት ላይ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ለእስራኤላውያን ታሪክ ከሚጠቀሰው ክፍልና ከትንቢቶቹ ቀንጨብ ተደርጎ የተጠቀሰው ለምንድነው?

9. ሦስቱ ዋና ዋና የጥንቷ ቤተክርስቲያን ባሕሪያት ምን ምን ነበሩ?

10. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እንዳይሠራ እንቅፋት የሚያጋጥመው መቼ ነው?

ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከትና፣ ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. የመወያያ ጥያቄዎች፡-

ሀ) 1. የሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ በመመርኮዝ፣ ለቤተክርስቲያንህ ኢየሩሳሌም፣ ይሁዳ፣ ሰማርያና ዓለም የሆኑ ቦታዎችን ግለጽ። 2. ቤተክርስቲያንህ ያላዳረሰችውን ቦታዎች በዝርዝር ግለጽ። 3. ቤተክርስቲያንህ ለሰዎች ወንጌልን የማዳረሱን ተግባር፣ አሁን ከምታደርገው በላይ እንዴት አድርጋ ነው ልታቀላጥፈውና ልታሻሽለው የምትችለው?

ለ) 1. አንድን ክርስቲያን በምሥክርነቱ ድፍረትና ኃይል እንዲኖረው የሚያደርገው ምንጩ ምንድነው? 2. ይህንን ኃይል ልናሰናክለው የምንችለው እንዴት ነው? 3. በቤተክርስቲያን የዚህ ኃይል መኖር የሚታየው እንዴት ነው?

ሐ) 1. በቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ምስረታ አካባቢ ድንቅና ተአምራት ያስፈለጉት ለምንድነው? 2. እነዚህን ነገሮች እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ቤተክርስቲያናት የተጠቀመባቸው እንዴት ነው?

መ) 1. ዛሬ በቤተክርስቲያኖቻችን ውስጥ ያለው አንድነት፣ ፍቅርና ኅብረት ልክ እንደ መጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን ኃይል ያለው ምሥክርነት የሌለው ለምንድነው? 2. እንደ ጥንቲቷ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ኃይል ከእኛ ጋር እንዲሆን ማድረግ የሚገባን ነገር ምንድነው?

ሠ) 1. ጴጥሮስ ወንጌልን ለሰዎች ለማስተላለፍ ያቀረበውን መልእክት፣ ዛሬ ብዙ ሰዎች ከሚያስተላልፉት ጋር አነፃፅረው። እንዴት ነው የሚመሳሰሉት? እንዴትስ ነው የሚለያዩት? 2. የጴጥሮስን መልእክት በመከተል፣ ምሥክርነታችንን የበለጠ ለማሻሻል የምንችለው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 3

የሐዋርያት ሥራ 3፡1-4፡37

## የመጀመሪያ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 3፡1-10

የሐዋርያት ሥራ ታሪክ፤ ክርስትና እንዴት ከጥቂት ሰዎች ከ500 ከማይበልጡ ደቀመዛሙርት ተነሥቶ፤ በዓለም ዙሪያ በሺሕ የሚቆጠሩ አማኞች እስኪኖሩት ድረስ እንዴት እንዳደገ የሚያትት ነው። ባለፈው ሳምንት መንፈስ ቅዱስ በጥቂት አማኞች ላይ ወረደ የእግዚአብሔር ሥራ የሆነውን፤ ዓለምን በወንጌል የማዳረሱን ተግባር ለመፈጸም እንዲችሉ እንዴት ዝግጁ እንዳደረጋቸው አንብበናል። ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ ጋር አብሮ የመጣው በልሣን የመናገር ስጦታ ብዙ አይሁዳውያንን ወንጌልን እንዲሰሙ ገፋፍቷቸዋል። በጴጥሮስም የመጀመሪያ መልእክት አማካኝነት እንደምናነበው 3.000 ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አምነዋል።

ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ መሢሕ ነው የሚለውን መልእክት እየሰበኩ ሳለ፤ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በየቀኑ እያደገች ነበር። ሕዝቡም የአማኞች አንድነት፤ ፍቅርና ኅብረት ባየ ጊዜ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ማመኑ ተስቧል። እነዚህ ሦስት ነገሮች፡- ፍቅር፤ አንድነትና ኅብረት ዛሬም ቢሆን የማያምኑ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት በየቤተክርስቲያኖቻችን መኖር የሚገባቸው ነገሮች ናቸው። የማያምኑ ሰዎች በቤተክርስቲያንህ ውስጥ እነዚህን ሦስት ነገሮች እያዩ ነው?

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የቀረበው መልእክት የሰው ፈጠራ እንዳልሆነ ነገር ግን ከእግዚአብሔር እንደሆነ አይሁዳውያን ሊገነዘቡ የቻሉት እንዴት ነው? በክርስትና ታሪክ ውስጥ ወንጌላውያን የሚሰብኩት ስብከት እውነተኛ መሆኑን ለማሳየት እግዚአብሔር ሁሌም ቢሆን በዚህ ጊዜ ተአምራትን ያሳይ ነበር። በዚህም መሠረት መንፈስ ቅዱስ ከወረደ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደቀመዛሙርቱ በእግዚአብሔር ኃይል ታግዘው ተአምራትን ለመሥራት ብቁ ሆኑ በዚህም ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ የቀረበው መልእክት እውነተኛ እንደሆነ ተረድተዋል።

ጥያቄ 1፡- ሀ) እግዚአብሔር በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ይመጡ የነበሩት የማያምኑ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰበከው እውነተኛ እንደሆነ ለማሳየት ተአምራትን የተጠቀመው እንዴት ነው? ለ) ውጤቱስ ምን ነበር?

በዛሬ ቀን ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማይ ካረገና መንፈስ ቅዱስ በደቀመዛሙርቱ ላይ ከወረደ በኋላ በእነርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለተፈጸመው ተአምራት እናጠናለን።

ጥያቄ 2:- የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 3ና 4 አንብብ። ጴጥሮስ የፈጸመው የመጀመሪያ ተአምር ውጤት ምን ነበር?

ጥያቄ 3:- የሐዋርያት ሥራ 3:1-10 እንደገና አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ። ሀ) የመጀመሪያው ተአምራት የተፈፀመው የት ነው? ለ) ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተመቅደሱ ይሄዱ የነበረው ለምንድነው? ሐ) ጴጥሮስና ዮሐንስ ለሰውዬው ፈውስን ለማስገኘት ሲሉ የተጠቀሙበት ስም ምንድነው? መ) አንካሳው ሰውዬ ከተፈወሰ በኋላ ሕዝቡ ለዚህ የሰጠው ምላሽ ምን ዓይነት ነበር?

በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ በደቀመዛሙርቱ ላይ ከወረደ ከጥቂት ቀናት በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለመጸለይ ወደ ቤተመቅደስ ይሄዳሉ። አይሁዳውያን በቀን ውስጥ ሦስት ጊዜ የመጸለይ ልማድ ነበራቸው። ከቻሉ ወደ ቤተመቀስ ሄደው ይጸልዩ ነበር፤ የመጀመሪያው የጸሎት ጊዜያቸው ከጠየቁ ወደ 3 ሰአት አካባቢ ነበር፤ ሁለተኛው የጸሎት ጊዜያቸው ደግሞ ከቀኑ 9 ሰዓት አካባቢ ሲሆን፤ የመጨረሻው የጸሎት ጊዜ ደግሞ ጀንበር ስትጠልቅ አካባቢ ነው።

በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙዎቹ አማኞች አይሁዳውያን ስለነበሩ ክርስትና የቀድሞው የአይሁድ ሃይማኖት ክፍል እንደሆነ ተደርጎ ነበር የሚቆጠረው። እስከ 64 ዓ.ም ድረስ እንደ ተለየ ሃይማኖት ተደርጎ አይቆጠርም ነበር። ስለዚህም የጥንቶቹ የአይሁድ ክርስቲያኖች በየምኩራቡ ወይም በየቤተመቅደሱ ከሌሎች አይሁዳውያን ጋር አብረው ያመልኩና ይጸልዩ ነበር። ከብዙ ዓመታት በኋላ ክርስቲያኖች ለብቻቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ ማምለክ ጀመሩ። ለክርስቲያን ዋናው ነገር የማምለኪያው ቦታ ሳይሆን ለአምልኮ ያለው አመለካከት ነው፤ ኢየሱስ እንዳለው «በእውነትና በመንፈስ ማምለክ» አለብን (ዮሐ. 4:24)።

ጥያቄ 4:- ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች ለማምለክ የምንችለው በቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ ነው ብለው የሚያስቡት ለምንድነው? ለ) ይህ ትክክል ነው? ሐ) የቤተክርስቲያን ሕንፃ ጥቅም ምንድነው?

ጴጥሮስና ዮሐንስ መልካም በሚሉት በአንደኛው የቤተ መቅደስ ደጃፍ ወደ ቤተመቅደሱ ሲገቡ፤ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ አንካሳ የነበረ ሰውዬ ምጽዋትን ለመናቸው። አይሁዳውያን ለደሆች ገንዘብ በመስጠት ከእግዚአብሔር የተለየ ምስጋና እንቀበላለን ብለው ይገምቱ ነበር። በዚህም ምክንያት ብዙ አይሁዳውያን ወደ ቤተመቅደሱ ሲገቡ ለደሆች ይመፀውቱ ነበር። ስለዚህም ይህ ቦታ ለድሆችና ለለማኞች ጥሩ የዕርዳታ ማገኛ ሥፍራ ሆነላቸው።

ጥያቄ 5:- ይህ አንዳንድ በኢትዮጵያ ከሚገኙ ልማዶች ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ሰውዬው ዮሐንስና ጴጥሮስ እንዲመፀውቱት ሲለምናቸው ጴጥሮስ አንካሳውን ሰውዬ «ብርና ወርቅ የለኝም ይህን ያለኝን እሰጥሃለሁ» ብሎ ይናገረዋል። ሰውዬው ተስፋ ያደርግ የነበረው ፍራንክ ይሰጡኛል ብሎ ነበር፤ ነገር ግን ጴጥሮስ «ወደ እኛ

ተመልከት» ብሎ ሲናገረው አንካሳው ሰውዬ በእምነት ተመለከተ (ሐዋ. 3፡16 ተመልከት)። ምን ያህል እንደነበረው አናውቅም ነገር ግን እግዚአብሔር አንካሳነቱን ለማዳን የሚያስችለውን ያህል እምነት ነበረው። ጴጥሮስም «በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ» ብሎ እጁን ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም እግሩና ቁርጭምጭሚቱ ጸና ወደ ላይ ዘሎም ቆመና መመላለስ ጀመረ፤ እግዚአብሔርንም ማመስገን ጀመረ። በዙሪያው የነበሩትና በውጭ ይለምን የነበረው አንካሳ መሆኑን ያስተዋሉት ሰዎች በጣም ተገረሙ።

ጥያቄ 6፡- የሐዋርያት ሥራ 1፡8 አንብብ። በኢየሱስ ተስፋ የተሰጡትና በጴጥሮስና በዮሐንስ ሕይወት ውስጥ የታዩት ሁለት ምልክቶች ምንድናቸው?

ኢየሱስ ወደ መንግሥቱ ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ ሁለት ቃል የገባላቸው ነገሮች ነበሩ። አንደኛ፤ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ኃይል እንደሚያገኙ ቃል ገብቶላቸው ነበር። ይህ ኃይል በአንካሳው ሰውዬ መፈወስ ተገልጿል። ኢየሱስ ግን ምሥክሮችም እንደሚሆኑ ቃል ገብቶላቸው ነበር። በነገው ዕለት ጴጥሮስ ይህን በተአምራት አማካኝነት የተገኘውን አጋጣሚ ተጠቅሞ እንዴት ለብዙ ሰዎች ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሠከረ እናያለን።

ከዚህ ታሪክ ተአምራትን በተመለከተ ሁለት ልንማራቸው የሚገቡን ዋና ዋና ነገሮች አሉ። አንደኛ ተአምራቱ የተፈጸመው ችግረኛውን አንካሳ ሰውዬ ለመርዳት ብቻ አይደለም። በተጨማሪም ለጴጥሮስና ለዮሐንስ ክብርና ሞገስንም ለማስገኘት አይደለም። በምትኩ ግን ሁልጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ተአምራትን ሲሠራ፤ የወንጌሉ መልእክት እውነተኛ እንደሆነ ነው የሚያሳየው። እግዚአብሔር በቤተመቅደሱ ይገኙ የነበሩት አይሁዳውያን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነገረውን መልእክት ለማዳመጥ ዝግጁ እንዲሆኑ በዚህ ተአምራት ተጠቀመ። ተአምራቱ ደግሞ ዮሐንስ ጴጥሮስ የእግዚአብሔር መልእክተኞች እንደነበሩና የኢየሱስ ክርስቶስን አገልግሎት የሚቀጥሉ እንደሆኑ የሚያስመሰክርም ነው። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲገለጽ ሰዎች ወንጌልን ወደ መስማቱ ይሳባሉ።

ሁለተኛ ተአምራት የሚፈጽሙት በአንድ በሆነ ሰው ኃይል ሳይሆን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል እንደሆነ እናያለን። የመፈወሱ ሥልጣን የሚገኘው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ስም» ሳይሆን በእግዚአብሔር ልጅ በሆነው ከሙታን በተነሣውና አዳኝ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አይሁዳውያን «ስም» የሚለውን ቃል የተጠቀሙት ስለ እግዚአብሔር ባሕሪና ሥልጣን ለመናገር ነው። ስለዚህም ጴጥሮስ «በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም» ሲል ፈዋሹ ኃይል ያለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ በእርሱ ኃይል እንዳልሆነ ነው የሚገልጸው። እሱ ይህ የመፈወስ ሥልጣን የተሰጠኝ ከኢየሱስ ነው፤ ሰውዬው ሊድን የቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል አማካኝነት ነው፤ ነው የሚለው። ተአምራቶች በሚፈጸሙበት ወቅት ወይም ሰዎችን የሚባርኩ ነገሮችን ስንፈጽም፤ ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት አለብን እንጂ እራሳችን እንደፈጸምነው አድርገን መመካት የለብንም። አንዳንድ ጊዜ፤ እግዚአብሔር

ተአምራትን እንዲፈጽሙ የሚጠቀምባቸው ሰዎች ኃይሉ የራሳቸው የሆነ ይመስላቸውና ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ይነፍጉታል።

ጥያቄ 7፡- ሀ) ሰዎች ተአምራትን ሲፈጽሙ አይተህ ታውቃለህ? ምን ዓይነት ተአምራት እንደነበር ግለጽ። ለ) ክብር የሆነው ለኢየሱስ ነው ወይስ ተአምራቱን ለፈጸመው ሰውዬ ሰፋ አድርገህ አብራራው።

ጴጥሮስ «የናዝሬቱን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም» የተጠቀመው ለምንድነው? ይህ ለኢየሱስ የተሰጠው ስያሜ በወንጌሎቹና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ብቻ ነው እንጂ በመልእክቶቹ ውስጥ አይገኝም። በዚህን ጊዜ «ኢየሱስ» የሚለው ስም የታወቀ ነበር። ጴጥሮስም የትኛው ኢየሱስ እንደሆነ ይህን የመፈወስ ሥልጣን የሰጠው ሁሉም ሰው እንዲያውቅ ይፈልግ ነበር። ይህም ከናዝሬት የመጣው ኢየሱስ ነው እንጂ ከሌላ ከይሁዳ ክፍል የመጣ አይደለም። ይህ ኢየሱስ ደግሞ አይሁዳውያን ያድነናል ብለው የሚጠብቁት መሢሕ ክርስቶስ ነው።

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ብዙ ተአምራትን ይጠቀምባቸው የነበሩ ጊዜያትና ጥቂት ተአምራትን ይጠቀምባቸው የነበሩ ጊዜያት ነበሩ። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ብዙ ተአምራትን የሚፈጽሙ ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ አካባቢ ሲሰበክ ነው። ነገር ግን እንደ ወንጌሉ በደንብ ከተመሠረተ በኋላ የተአምራቱ ቁጥር ከበፊቱ ያንሣል። ይህም የሚሆነው የወንጌሉ ኃይል እንደ አስቀድሞ በመገለጹ ነው። እግዚአብሔርን ተአምራትን የሚፈጽመው ኃይሉን ለማሳየት ብቻ አይደለም። አስተውል፤ ተአምራት በተለይ የሚፈጽሙት ለማያምኑ ሰዎች የወንጌሉን እውነተኛነት ለማሳየት ነው።

ዛሬ ተአምራትን በተመለከተ ሊኖረን የሚገባን አመለካከት ላይ ብርቱ ጥንቃቄ መውሰድ ይኖርብናል። አስተውል ሰይጣንም እራሱ ተአምራትን መፈጸም ይችላል። ባለፉት ዘመናት ውስጥ በእርሱ እስር ውስጥ ለማቆየት በጠንቋዮች አማካኝነት ተአምራትን ፈጽሟል። እግዚአብሔር ይሁን ሰይጣን ተአምራቱን የሚሠራው ልናውቅ የምንችለው እንዴት ነው? ሁለት ዋና ዋና መፈተኛዎች አሉ። አንደኛ ተአምራት ሲፈጸምም እራስህን በዚህ ተአምራት ውስጥ ክብር የተሰጠው ለማነው? ብለህ ጠይቅ። ተአምራቱን ለፈጸመው ሰውዬ ነው ወይስ ለእግዚአብሔር ነው ክብሩ የሚደርሰው? እግዚአብሔር በአገልጋዩ ውስጥ ሆኖ ተአምራትን ሲፈጽም ሁሌም ክብር የሚሆነው ለእርሱ ነው። በዛሬውም ታሪክ እንደምታየው ታምራቱ በተፈጸመበት ወቅት የተፈወሰው ሰውዬና ሰዉ በሙሉ ምስጋና ያቀረበው ለእግዚአብሔር ነው እንጂ ለጴጥሮስና ለዮሐንስ አልነበረም።

ሁለተኛ የዚህ ተአምራት ውጤቱ ምንድነው? ብለን ልንጠይቅ ይገባል። ወንጌሉን የሚያስተላልፍ ነው ወይስ ለሰውዬው ክብርን የሚያስገኝ ነው? እግዚአብሔር በተአምራት ውስጥ ያለው ዓላማ ወንጌል ማዳረስ ነው እንጂ አንድ ግለሰብን ማሞካሸት አይደለም።

ጥያቄ 8:- ሀ) ተአምራት ለእግዚአብሔር ክብር ሳይገኝ ወይም ወንጌሉ ሳይስፋፋ ስለቀረበት ስለአንድ የምታውቀው አጋጣሚ ግለጽ። ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብርን ያጎናጸፈ አንድ ሌላ ተአምራት ግለጽ።

አስታውል፤ ትልቁ ተአምራት የአንድ ሰው ሥጋዊ ፈውስ ሳይሆን የኃጢአተኛውን ሕይወት እግዚአብሔር ቀይሮ የእግዚአብሔር ልጅ የሚያደርገው ተአምር ነው። ተአምራትን ፍለጋ እዚህም እዚያም አትወሰድ። በምትኩ ግን እግዚአብሔር በአንተ ተጠቅሞ ከተአምራት ሁሉ የበላይ የሆነውን አንድን ሰው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የማምጣቱን ተግባር እንድትፈጽም ፅኑ የሆነ ፍላጎት ይኑርህ።

# ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 3:11-26

በጥንቷ ቤተክርስቲያን ድንቅና ተአምራት ይፈጽሙ የነበረው የተመልካቾቹን ሐሳብ ለማሰባሰብ፤ ከሙታን የተነሣውን የኢየሱስ ክርስቶስን ኀይልና የሐዋርያቱን ምስክርነት እውነተኛነት ለማሳየት ነው። ጴጥሮስና ዮሐንስ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ አንካሳ የነበረውን ሰው ሲፈውሱ ከቤተመቅደሱ ይገኙ የነበሩት ብዙ ሰዎች ተገረሙ፤ የጴጥሮስንም መልእክት ለመስማት ዝግጁ ሆኑ።

ጥያቄ 9:- አንካሳው ሰውዬ እንዲፈወስና የእግዚአብሔር ኃይል እንዲለቀቅ ያደረገው ነገር ምንድነው? (3:16)

የክርስቶስን ኃይል እውነትኛነት ለሌሎች ልናሳምን የምንችለው የተለወጡን ሕይወቶች እንደ ማስረጃ በማቅረብ ነው። ስለ እምነታችን አንዱና እውነተኛው ማስተማመኛ የኛ የግል ምሥክርነት ነው። ሰዎች የተለወጠን ሕይወት አይተው ሊክዱ አይችሉም።

የሐዋርያት ሥራ 3:11-26 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 10:- ሀ) ጴጥሮስ መልእክቱን ያቀረበው ለእነማን ነው? ለ) በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ለኢየሱስ የተሰጡትን የተለያዩ ስሞች በዝርዝር ጻፋቸው። ሐ) ይህ በጴጥሮስ የቀረበው መልእክት በበዓለ ሃምሳ ዕለት በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ ከቀረበው ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 እና የሐዋርያት ሥራ 17:26 አነፃፅር።

አንካሳው ሰውዬ ከተፈወሰ በኋላ የምሥራቹ በቤተመቅደሱ ተሰብስበው በነበሩት አይሁዳውያን መካከል ወዲያውኑ ተሰማ። በቤተመቅደሱ ደጃፍ ሆኖ ይለምን የነበረው ሰውዬ ጤናማ ሆኖ እግዚአብሔርን በቤተመቅደስ እያመሰገነ ሲያዩት በጣም ተደነቁ። ጴጥሮስም «... በዚህ ስለምን ትደነቃላችሁ በገዛ ኃይላችን ... እንዲመላለስ እንዳደረግነው?» ብሎ ይናገራቸዋል። ጴጥሮስ የተፈጸመው ተአምራት በእርሱ ኃይል እንዳልሆነ የተናገረው ወዲያውኑ በቅጽበት ነበር። እሱም ሁላችሁም እንዳያችሁት ለሰውዬው ፍጹም መፈወስን የሰጠው የኢየሱስ ስም፤ በእርሱም ላይ የነበረው እምነት ነው አላቸው፤ (ሐዋ. 3:12ና 16)። ጴጥሮስ ፈዋሽ የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል እንዲለቀቅ ያደረገው ነገር የአንካሳው ሰውዬ እምነት እንደሆነ ተረድቷል።

ጴጥሮስ የዘመን የተአምራት ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መሰከረ። አንካሳው ሰውዬ የተፈወሰው በኢየሱስ ስምና ኃይል እንደመሆኑ መጠን ለሰዎቹ ሁሉ ይህ ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ መሢህ እንደሆነ ማስረጃ ሆኖላቸዋል። እሱ ለመቀበል አሻፈረኝ ያሉትን አንዳንድ አይሁዳውያን እንኳ አሳምኗል። ያለ ምንም ጥርጥር ይህ ተአምር ሲፈጽም ያዩ ብዙዎች ሰዎች ከጥቂት ጊዜ በፊት ኢየሱስ ክርስቶስን ሲሰቀል አይተዋል።

የጴጥሮስ መልእክት የሚያተኩረው ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚሰጠው መግለጫ ላይ ነው።

ጥያቄ 11፡- ከእኛ ስብከቶችና ምሥክርነት ጋር ይህ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ብዙዎቹ አይሁዳውያን ከጥቂት ወራት በፊት ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ያለጥርጥር ምሥክሮች በመሆናቸው ጴጥሮስ መልእክቱን የሚጀምረው ከዚሁ ከኢየሱስ ስቅለት ነው። በአንክሮ ይጠባበቁት የነበረውን መሢሕ በማዋረዳቸውና በማጥላላታቸው ይከሳቸዋል። በአይሁዳውያን መካከል ለመሢሑ ይሰጥ የነበረውን «ቅዱሱንና ጻድቁን» የሚለውን የተለመደ ስያሜ ነው ለመሢሑ የሰጠው። ይህም የሆነው የሚመጣው መሢሕ ቅዱስና ከኃጢአት የተለየ መሆኑን አይሁዳውያን ያውቁ ስለነበር ነው። በተጨማሪም የእርሱ መንግሥት እንደ ምድራዊ ነገሥታት ዓይነት ሳይሆን የጻድቅ መንግሥት ነበር የሚሆነው። ጴጥሮስ ኢየሱስ እንዲሞትና ነፍሰ ገዳዩ በምትኩ እንዲሰጣቸው የጠየቁበትን ጊዜ እንዲያስታውሱ በማድረግ በደላቸውን ይገልጽላቸዋል። በተጨማሪም ጴጥሮስ «የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ምሥክሮች ነን» ይላቸዋል (ቁ. 15)።

በመልእክቱ ውስጥ ጴጥሮስ አራት ልዩ የሆኑ ስሞችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰጥቷል።

1 - የእግዚአብሔር አገልጋይ፡- የእግዚአብሔር አገልጋይ የተባለው መሢሑ ሲሆን አሳቡም የመጣው ከኢሳይያስ ነው፤ (ኢሳ 52፡13-53፡12ን ተመልከት)። እግዚአብሔር እዚህ ላይ ለሕዝቡ ኃጢአት ሲል ስለሚሞተና ታዛዥ ስለሆነው አገልጋይ ይተነብያል።

2- ቅዱሱ፡- እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያለውን ምኞት ቅዱስ ሆኖ በመኖር ሙሉ በሙሉ ያሟላው ኢየሱስ ነው። እንደሌሎች ሰዎች ኃጢአት አልሠራም ነበር።

3- ጻድቁ፡- ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር ያልምንም ኃጢአት እንኳን በስምምነት የኖረው ኢየሱስ ብቻ ነው።

4 - የሕይወት ራስ፡- ጴጥሮስ ኢየሱስ የሕይወት ምንጭ እንደሆነ ተገንዝቦ ነበር። ኢየሱስ ለሚያምኑበት ሰዎች ዘላለማዊ ሕይወት መስጠቱ ብቻ ሳይሆን የሕይወትንም ፈጣሪና ጠባቂዋም እሱ ራሱ ነው።

ለማያምኑ ሰዎች በምንሰጠው ምሥክርነት ውስጥ ማካተት ያለብን ነገር ምንድነው? ለአይሁዳውያን የቀረበው የጴጥሮስ መልእክት ለኛም ጥሩ ምሳሌ ሊሆነልን ይችላል።

1. ወንጌል ምንጊዜም ቢሆን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። አይሁዳውያንም ስለ እግዚአብሔር አብ በቂ የሆነ ግንዛቤ ስለነበራቸው ጴጥሮስ የኢየሱስ ሞት እንዲሁ እንደ አጋጣሚ የሆነ ነገር ሳይሆን በእግዚአብሔር ፍቃድ ለዓላማው የሆነ እንደ ነበር ያሳያቸዋል። ጴጥሮስም በመቀጠል ምንም እንኳ ካለማወቅ የተነሣ አይሁዳውያን ስሕተት ቢሠሩም እግዚአብሔር በነቢያት በኩል ተናግሮት የነበረውን ትንቢት በክርስቶስ መከራ መቀበል አማካኝነት ፈጽሞታል። እንግዲህ በምሥክርነታችን ውስጥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ ልንጠቅሳቸው የሚገቡን ሁለት ዋና ዋና እውነታዎች አሉ።

ሀ - የማያምኑ ሰዎች ኢየሱስ ስለ ኃጢአታቸው እንደሞተላቸው የኃጢአታቸውን ዋጋ እንደከፈለላቸውና በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖራቸው እንደሚችል ማወቅ አለባቸው።

ለ - ከዚህ ጋር ታክሎም፤ ኢየሱስ ከሙታን የመነሣቱን እውነታና የምናመልከው አዳኛችን የሞተ እንዳልሆነ መጥቀስ ይኖርበታል። ጴጥሮስም «የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሣው» ብሎ ተናግሯል።

2. ሌሎቹንም የኃጢአት ይቅርታን እንዲያገኙ እምነታቸውን በኢየሱስ ላይ ማድረግ እንዳለባቸው ማስገንዘብ አለብን። ኃጢአታቸውም ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ መግባትና መመለስ አለባቸው።

እነዚህ አይሁዳውያን የኢየሱስን ከሙታን መነሣት ያዩትን ሰዎች ምሥክርነት ሊክዱ አይችሉም። የምሥክርነታቸውም እውነተኛነት በኢየሱስ ስም በዳነው በአንካሳው ሰውዬ መፈወስ ጭብጥ ሆኗል። የጴጥሮስ መልእክት ልክ እንደ በዓለ ሃምሳው ቀን፤ አይሁዳውያን ይጠባበቁት የነበረው ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ እንደነበረ ነው። ኢየሱስን በመግደላቸው አይሁዳውያን የአባቶቻቸውን የአብርሃምን የይስሐቅና የያዕቆብን አምላክ ክደዋል። ጲላጦስ ኢየሱስን ለሞት የሚያደርሰው ምንም ወንጀል አላገኘበትም፤ አይሁዳውያን ደግሞ ነፃ እንዲለቀው አለፈቀዱለትም። ሆኖም ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ዓላማና ዕቅድ ጋር የሚስማማ ነበር። ምክንያቱም ለሰው ሁሉ ደኅንነት ሊኖር የቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በኩል ነው።

አይሁዳውያን በብሉይ ኪዳን ቃል የተገባለትን መሲሕ ይጠባበቁ ስለነበር፤ ጴጥሮስ ይህ መሲሕ ኢየሱስ ነው ብሎ ይነግራቸዋል። አንድ ቀን እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን በብሉይ ኪዳን የሰጣቸውን የተስፋ ቃል በሙሉ የሚያሟላላቸው ኢየሱስ ነው። ሆኖም፤ እነዛ የተስፋ ቃሎች ይፈጸሙ ዘንድ፤ በመጀመሪያ እነርሱ እምነታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማድረግ አለባቸው። በዚህም ምክንያት ኃጢአታቸው ይደመሰስ ዘንድ ጴጥሮስ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው ንስሐ እንዲገቡ ያሳስባቸዋል። እሱ ያገኘውን ዓይነት ስጦታ ሕዝቡ እንዲያገኝ ይጓጉ ነበር።

ጴጥሮስ ሙሴ «ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል» ብሎ የተናገረውን ቃል ያስታውሳቸዋል (ቁ. 22)። ከሳሙኤል ጊዜ በኋላ የነበሩት ነቢያትም ስለሚመጣው መሢሕ እንደተነበዩና አይሁዳውያን ደግሞ የእነዚህ ነብያቶች ልጆችና በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተገባላቸው አባቶች ልጆች እንደሆኑ አሳወቃቸው። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ያስነሣው እነርሱን ሊባርካቸውና ከጠማማ መንገዳቸው ሊመልሳቸው ብሎ እንደሆነም በደንብ አስረድቷቸዋል።

የክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት በነቢያት ተስፋ የተሰጠ ነገር ነው። የእርሱ ዳግመኛ ምፅአት ልጆቹ ለሆኑ ሁሉ በረከትን የሚያስገኝላቸው ነው እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ወራሾች ለሆኑት ለአይሁዳውያንና ክርስቶስን ተቀብለው የደኅንነቱ ተካፋዮች ለሚሆኑ አሕዛብ በረከተን ያመጣላቸዋል።

3. የወንጌሉ መልእክት ለማያምኑ ሰዎች ጥብቅ የሆነ ማስጠንቀቂያ ያዘለም ነው። ጴጥሮስም «ያንንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች» ብሎ አስጠንቅቋቸዋል። ለሚያምኑ ሰዎች ወንጌሉ የዘላለም ሕይወት ይኖራቸዋል የሚል የተስፋ ቃል አለው፤ ለማያምኑት ደግሞ በገሃነም እሳት የዘላለም ጥፋት እንደሚያገኛቸው ይናገራል።

ጥያቄ 12፡- ሕይወትህን መርምር። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ ተቀብለሃልን? ካልተቀበልክ፤ የእግዚአብሔርን ፍርድ ከመቀበልህ በፊት ይህን ውሳኔ አድርግ።

ጥያቄ 13፡- ለማያምን ሰው በምትሰጠው ምሥክርነት ውስጥ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ነገሮች እንዴት እንደምታካትታቸው አብራራ።

የአንካሳው ሰውዬ መዳን፤ የወንጌልን የደኅንነት መልእክት በሥዕላዊ መግለጫ የሚያሳይ ነው። ለሰው የሚያስፈልገውን ነገር ያሳያል፤ እራሱን ሊረዳ አይችልም። የሚያስፈልገውን ነገር እያሰበ፤ ዕርዳታ አገኛለሁ ብሎ በመገመት ወደ ጴጥሮስ ይመለከታል። ሊያድነውም የቻለው እምነቱ ነው። እምነት፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ሕይወት የመስጠት ሥልጣንና ኃይል እንዳለው መቀበል ማለት ነው። እምነት የእግዚአብሔር ኃይል በሕይወታችን ውስጥ ገቢራዊ እንዲሆን ያደርጋል። ለቃሉ ታዛዦች መሆናችን ደግሞ በክርስቲያኖች ሕይወት ያለማቋረጥ የእግዚአብሔር ኃይል እንዲፈስ ያደርጋል።

እምነት ልንፈጥረው የምንችለው ነገር አይደለም። እምነት በመስቀሉ ላይ ለተገለጸው የኢየሱስ ፍቅር የምንሰጠው ምላሽ ነው። ምህረትን እንዳናገኝ እርግጠኞች ስንሆን ለፍቅሩ ምላሽ እንድንሰጥ ብቁ ያደርገናል (ሐዋ. 3፡16)። እምነታችን የሚገለጸው እርሱን በምንቀበልበት ወቅት ነው። የእምነትን ስጦታ የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ችግር ሲያጋጥመን የሚያስፈልገንን እምነት መስጠቱን አያቋርጥም። እምነት ለእግዚአብሔር ምንም ነገር እንደማይሳነው አውቆ በእርሱ መታመን ነው።

መንፈሳዊ፥ ሥጋዊና ስሜታዊ የፈውስ ኃይልን የሚሰጥ ከሙታን የተነሣው ጌታ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንድንጸልይ ድፍረቱን የሚሰጠን የእምነት ስጦታ ነው። የምናቀርበው የጸሎት ጥያቄ ለእርሱ ክብር የማያስገኝ ከሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጸልይም፤ በዚህም ምክንያት የእርሱ ኃይል አይገለጥም።

ጥያቄ 14:- ዮሐንስ 14:12-14 እና 15:5-8 አንብብ። ሀ) በእርሱ ስም ከጸለይን ኢየሱስ የገባልን ቃል ምንድነው? ለ) በቁጥር 7 ላይ እንደተጠቀሰው የምንጠይቀውን ሁሉ እንድናገኝ ማድረግ ያለብን ምንድነው? ሐ) የኢየሱስን ስም ኃይል በቅጡ ተገንዝበኸዋልን?

በስሙ ማንኛውንም ዓይነት ነገር ከጠየቅን ኢየሱስ እንደሚፈጽምልን ቃል ገብቶልናል፤ ይህ ሲባል ግን አንድ መጥፎ ነገር እንዲሰጠን ወይም በራስ ወዳድነት አንድን ነገር እንድናገኝ በስሙ ብንለምን ይሰጠናል ማለት አይደለም። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት መጸለይ ማለት ነው። ምን ጊዜም ቢሆን ለእግዚአብሔር ክብር የሚሰጥ ማንኛውንም ዓይነት ብንጠይቅ እንደምናገኘው እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ኢየሱስ እንደሚናገረው እርሱን የሚያስከብረውን ነገር ልናውቅ የምንችለው በእርሱ ውስጥ ስንኖር ነው። አንድ አማኝ ከክርስቶስ ጋር ኅብረትና አንድነት ከሌለው ምንም ዓይነት ፍሬ ሊያፈራ አይችልም። አንድ ከግንዱ ላይ የተቆረጠ ቅርንጫፍ የሞተ እንደሚሆን ሁሉ፤ እኛም በኢየሱስ ውስጥ መኖርን ካቋረጥን የማንጠቅምና ፍሬ የማናፈራ እንሆናለን።

ጥያቄ 15:- እግዚአብሔር መልስ የሰጠባቸውን የተለያዩ የጸሎት ጥያቄዎችህን በዝርዝር ጻፋቸው። ለጸሎትህ መልስ ስለሰጠህ እግዚአብሔርን አመስግነው።

# ሦስተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 4:1-22

በትናንትናው ጥናታችን አንካሳ የሆነ ሰውዬ መልካም በሚሉት የቤተመቅደሱ ደጃፍ አካባቢ እንደተፈወሰ አይተናል (ሐዋ. 3:2)። ይህ ደጃፍ የትልቁና በሰው በጣም ይጨናነቅ የነበረው የቤተመቅደስ መግቢያ ነበር። ደጃፉ የነበረው:- ለመሥዋዕት የሚሆኑ እንስሳት የሚሸጡበትና የገንዘብ መንዛሪዎች ጠረጴዛ ይገኝበት በነበረው በአሕዛብ አደባባይ ላይ ነበር። ሕዝቡ የተፈወሰውን ሰው ለማየት ግር ብሎ ሲሰበሰብ የቤተመቅደሱ ዘበኞችና ሰዱቃውያን ደግሞ ሁኔታውን ለማጣራት መጥተው ነበር።

ዛሬ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ከመታዘዝና ለሰው ከመታዘዝ መካከል ምርጫ ማድረግ እንዳለባቸው እናያለን። እምነታችንም የሚፈተነው በእንደዚህ ዓይነት ምርጫዎች ውስጥ ስናልፍ ነው። ይህ ውሳኔ በስተመጀመሪያ እንደ ቀላል ነገር ሊቆጠር ይችላል፤ ሆኖም ብዙ ጊዜ በእምነታችን ተጠራጣሪዎች እንድንሆንና ለክርስቶስ ያለንን ምሥክርነታችንን የሚያጠፋ ነገር ነው። አንድ አማኝ ስለ ክርስቶስ ሲል ፀንቶ ቢቆም ሊወገዝና ስደት ሊደርስበት ይችላል፤ ነገር ግን ምሥክርነቱ ብርቱ ነው የሚሆነው

በተጨማሪም በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር የሚቆምበትን ኃይል የልብ ሰላምና የሕይወት ትርጉምን ይሰጠዋል።

የሐዋርያት ሥራ 4፡ 1-22 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 16፡- ሀ) ሰዱቃውያን እነማን ናቸው? ስለእነዚህ ሰዎች ያለውን ማብራሪያና ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ አንብብ። ለ) ሰዱቃውያን የጴጥሮስን መልእክት የተቃወሙት ለምንድነው? ሐ) ጴጥሮስና ዮሐንስ ምን ተደረጉ? መ) ሕዝቡ ለጴጥሮስ መልእክት የሰጠው ምላሽ ምን ዓይነት ነው?

ካህናቱና የቤተመቅደሱ ዘበኞች የተከሰተውን ነገር ለመመርመር ሲመጡ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ይይዟቸዋል። በዚህም ቀን ጴጥሮስና ዮሐንስ ምሽቱን ያሳለፉት በእሥር ቤት ውስጥ ሲሆን በማግሥቱ ግን የአይሁድ ሽማግሌዎች የሕግ ምሁራን፣ የሊቀ ካህናቱ ወገኖች ያጠቃለለው በአይሁድ ችሎት ፊት ቀረቡ። በአዲስ ኪዳን ዘመን ይህ ችሎት ወይም የፍርድ ሸንጎ ሊቀካህናቱን፣ ጻፊዎችን ወይም የሕግ ሰዎችን፣ ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያንን አጠቃልሎ የያዘ ነበር።

በአዲስ ኪዳን ዘመን የነበሩት ሽማግሌዎች ወይም አለቆች የቆዩና ያረጁትን የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍትን በአዲስ መጽሐፍ ላይ በማጠቃለል የሚገለብጡ ካህናት ነበሩ። ይህም ሥራ በጣም አስፈላጊ ነበር፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ሊባዛ የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ በመሆኑ ነው። እነዚህ ሰዎች ብዙ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት የሕጉን መጽሐፍ በመገልበጥ ስለሆነ ለሕጉ ትክክለኛ ትርጉም የሚሰጡ ሊቃውንት ናቸው ተብሎ ነበር የተቆጠሩት። በዚህም ምክንያት በሕጉ ትርጉም ላይ ውሳኔ እንዲሰጡበት በማለት እየተጠሩ በየችሎቱ ቀርበው እንደ ፈራጆች ዳኝነትን ይሰጡ ነበር። ኢየሱስም የእነመሀ ሰዎች ውሳኔ ብዙ ጊዜ ይቃረን ነበር።

በሸንጎው የነበሩት ሌሎቹ ሰዎች ደግሞ ሰዱቃውያንና ፈሪሣውያን ናቸው (ማቴ. 26፡3፤ 57 እና 59)። ሰዱቃውያን በአይሁዳውያን መካከል የሚገኙ የሃይማኖትና የፖለቲካ ሰዎች ናቸው። በሕዝቡ ዘንድ ብዙም የታወቁ አለነበሩም፤ ሆኖም ከሃብታም ካህናትና ከመሬት ከበርቴዎች የተቀናጀ ቡድን አባላት ነበሩ። ኢየሱስ ይኖርበት በነበር ዘመን ሊቀ ካህናቱና ቤተሰቡ የዚህ የሰዱቃውያን ቡድን አባላት ናቸው። ካህን የመሆንን ሥልጣን የሰጣቸው የሮማው መንግሥት ነው። የአምስቱን የሙሴ የሕግ መጽሐፍትን በደንብ ይከተሉ ነበር፤ ሆኖም የሙታን ትንሣኤ የለም የሞቱ ሰዎች አይፈረድባቸውም መላእክትም ወይም ክፉ መናፍስት የሉም ብለው ያምኑ ነበር። ከዚህ የሽማግሌዎችና የአለቆች ስብስብ ውስጥ ብዙዎቹ ሰዱቃውያን ነበሩ። በሙታን ትንሣኤ ያምኑ ስላልነበር ጴጥሮስ ስለኢየሱስ ትንሣኤ ሲናገር በጣም ተናደዱ።

ፈሪሣውያን ደግሞ በአይሁዳውያን መካከል የሚገኙ የሃይማኖት ሰዎች ናቸው። በዚህ የሽማግሌዎችና የአለቆች ስብስብ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ፖለቲካዊ የበላይነት በአይሁድ ሕዝብ እንዲኖራቸው ሲሉ ሁሌ ከሰዱቃውያን ጋር ይጣሉ ነበር። ምንም እንኳ ፈሪሣውያን ከሰዱቃውያን በብዛት ያነሱ ቢሆንም በተራ ሕዝብ በጣም የተደገፉ

ነበሩ። የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት ቀለል ባለ መንገድ በማቅረብና የራሳቸውንም አዳዲስ ሕግጋት በማከል ሕዝቡ ሕግጋቱን እንዲጠብቅ ያደርጉት ነበር።

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሦስት ቡድኖች የእስራኤልን ሕዝብ ፖለቲካዊና መንፈሳዊ መሪነትን ያዋቀሩ ናቸው። ልክ እንደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እኩሌ በብሉይ ኪዳን ሕግጋት ሥር ነው የሚኖረው እኩሌ ደግሞ ሕግጋቱን ተላልፏል በማለት ፍርድም ያስተላልፋሉ። ከጥቂት ቀናት በፊትም በኢየሱስ ላይ የሞት ፍርድ የበየነበት ይህ የሽማግሌዎቹ ችሎት ነበር። አሁንም እነዚህ ሰዎች ጴጥሮስና ዮሐንስን ሰውዬውን እንዴት እንደፈወሱት ይጠይቋቸዋል።

ጥያቄ 17፡- እነዚህ ሽማግሌዎች በጴጥሮስና በዮሐንስ ሕይወት ውስጥ ካዩት ነገር በጣም ያስገረማቸው ምንድነው?

ጥያቄ 18፡- ጴጥሮስ የፈፀመውን ተአምር ሽማግሌዎች ሊክዱ የማይችሉት ለምንድነው?

ጥያቄ 19፡- መልካም ነገር በመሥራትህ ተጠይቀህ ወይም ፍርድ ተቀብለህ ታውቃለህ? ሰፋ አድርገህ ግለጸው።

ጴጥሮስም ሽማግሌዎቹ ለጠየቁት ጥያቄ በድፍረት «እናንተ በሰቀላችሁት እግዚአብሔር ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደህና ሆኖ በፊታችሁ እንደቆመ ለሁላችሁ ለእስራኤልም ሕዝብ የታወቀ ይሁን። እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው» ብሎ ይመልስላቸዋል (መዝ. (118)፡22)። ጴጥሮስ ከጥቂት ቀናት በፊት ኢየሱስ ያደረገውን ንግግር ሽማግሌዎቹ እንዲያስታውሱት ያደርጋቸዋል። እነዚህ የአይሁድ መሪዎች ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር ጴጥሮስ ይጠባበቁት ስለነበረው መሲሕ መናገሩን ወዲያውኑ ነው የተረዱት። ጴጥሮስ በግልጽ ለመሲሑ ሞት ተጠያቂ ያደረገው እነርሱን ነው። ሆኖም መሲሕና የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሆነውን ከሙታን የመነሣቱንም እውነታ ገልጾላቸዋል።

በመቀጠልም ጴጥሮስ ለወንጌሉ መልእክት መሠረት የሆነ ንግግር ያደርጋል። «መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (ሐዋ. 4፡12)።

ጥያቄ 20፡- ቁጥር 12 በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አራት ውስጥ ቁልፍ የሆነች ቁጥር ናት። ጥናትህን ከመቀጠልህ በፊት ይህችን ጥቅስ በቃልህ አጥናት።

እነዚህ አይሁዳውያን ብሉይ ኪዳንን ከተከተልን እንድናለን ብለው ያስቡ ነበር። ጴጥሮስ ግን ኢየሱስ ከመጣ በኋላ በእግዚአብሔር አብ ብቻ ማመኑ በቂ እንዳልሆነ ያሳያቸዋል። ኢየሱስ ስለ ኃጢአታቸው እንደሞተና ከሙታን እንደተነሣ ማመንም አለባቸው። በእግዚአብሔር እናምናለን የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ ነገር ግን በሌላ ነቢይ ስም ወይም አስታራቂ በኩል ወይም ደግሞ ጥሩ ሥራ በመሥራት በራሳቸው መንገድ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመድረስ ይጥራሉ! መጽሐፍ ቅዱስ ግን ወደ እግዚአብሔር

የሚወስድ አንድ ብቸኛ መንገድ እንዳለ ነው የሚናገረው፡- ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው።

ጥያቄ 21፡- በሌላ አምላክ ለሚያምኑ ወይም በመንፈሳዊ መሪዎች ላይ ለሚታመኑና በኢየሱስ ክርስቶስ ለማያምኑ ሰዎች ይህ ምን ማለት ነው?

ጥያቄ 22፡- 1ኛ ጢሞ. 2፡5 አንብብ። በእግዚአብሔርና በሰው ብቸኛ መካከለኛ የሆነው ማነው?

ኢየሱስ «እኔ መንገድም እውነትም ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ብሏል (ዮሐንስ 14፡6)። ብዙ ሰዎች ብቁዎች ነን ብለው በማሰብ ወይም ደግሞ የመሐመድን ወይም የሌላን ሰው ትምህርት በመከተል መንግሥተ ሰማያት እንገባለን ብለው ተስፋ ያደርጋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ የሚያድን ስም ወይም ሰው እንደሌለ ይናገራል። በዓለማችን ዛሬ ይህንን ነገር ያልተረዱ ብዙ ሰዎች አሉ።

ጥያቄ 23፡- ሀ) ይህንን መልእክት ለማስተላለፍ ስትል ቤተክርስቲያንህ ምን እየሠራች ነው? ለ) ይህንን እውነታ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል ብለህ የምትገምታቸው ሰዎች በአካባቢህ አሉ? እነማን ናቸው?

ሽማግሌዎች የአንካሳውን ሰውዬ መዳን ችላ ሊሉት አይችሉም። ሰውዬው ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር ቆሞ በመፈወሱ ምክንያት ለእግዚአብሔር ምሥጋና ያቀርባል። ሽማግሌዎች ይህ ስለ ኢየሱስ የሚሰጠው ትምህርትና ተአምራቶቹ በሕዝቡ ላይ ያላቸውን ሥልጣንና ኃይል የሚቀናቀን በመሆኑ ፈርተው ነበር። በሌላው ፊት ደግሞ ኢየሩሳሌም በሙሉ ስለዚህ ተአምራት ሰምቶ እግዚአብሔርን እያመሰገነ በመሆኑ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሊቀጡ አልቻሉም። አንዱና ብቸኛው አማራጫቸው ጴጥሮስና ዮሐንስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዳያስተምሩ ወይም እንዳይናገሩ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ነው።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ሊወስኑበት የሚገባቸው አማራጭ ሁኔታ ፊታቸው ተደቅኗል። የሽማግሌዎችን ትዕዛዝ ነው መቀበል ያለባቸው ወይስ የኢየሱስን ትዕዛዝ? ኢየሱስ «ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ ብሎ ነበር (ሐዋ. 1፡8) በተጨማሪም «ሂዱ ... ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሩ» ብሏል (ማቴ. 28፡19-20)። «እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደሆነ እናንተ ፍረዱ፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም» (ሐዋ. 4፡19-20)። ጴጥሮስና ዮሐንስ ለእግዚአብሔር እንታዘዛለን ብለው ወሰኑ። በሥልጣን ያሉ ሰዎች ትዕዛዝ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚቃወሙና የሚፃረሩ ከሆነ ክርስቶስን ሁልጊዜም ቢሆን ቅድሚያ የነገሥታት ንጉሥ ለሆነው ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ቅድሚያ መስጠት አለበት። ሆኖም በሥልጣን ያሉትን ሰዎች ትዕዛዝ ሳይጠብቅ ሲቀር በፖለቲካ ሥልጣን ያሉት እንደሚቀጡት መገንዘብ አለበት። አማኞች ይህንን ቅጣት በትዕግሥት መቀበል አለባቸው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ልጆቹ ስለእርሱ ሲመሰክሩ ከከፉ

ይጠብቃቸው (ዳን. 3፡16-18)። በሌላ ጊዜ ደግሞ፤ ለእሥር ወይም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 7 ላይ እንዳለው እንደ እስጢፋኖስ ለሞት ይዳረጋሉ።

ሽማግሌዎች ጴጥሮስና ዮሐንስ እነርሱን ለመቃወም የነበራቸውን ድፍረት ሲያዩ በጣም ተገርመው ነበር። እነርሱም ከሰቀሉትና ጴጥሮስ ከሙታን ተነሥቷል ከሚለው ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ ተገንዝበዋል።

ጥያቄ 24፡- ስለ እግዚአብሔር መናገርና መመሥከር ሲገባህ ሰዎችን መፍራትህ አንዳንዴ ዝም ብለህ እንድታልፍ የሚያደርግህ በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ጥያቄ 25፡- ሰዎች አንተ የኢየሱስ ተከታይ እንደሆንክ የሚገነዘቡት በምን ዓይነት መንገድ ነው?

በአካባቢህ ላሉት ሰዎች ሕይወትህ ኢየሱስን የሚያሳየው እንዴት ነው?

እስካሁን ድረስ የሃይማኖት መሪዎች በጴጥሮስና በዮሐንስ ላይ ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር የለም። ኢየሱስ በሰዎች ዘንድ ብዙ ተቀባይነት በማግኘቱ ፈርተው ነበር፤ በዚህም ምክንያት ኢየሱስን ለሞት ዳረጉት። አሁን ደግሞ በደቀመዛሙርቱ በኩል የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ እየተሠራ ነው፤ ይህም እርሱ ኃይላቸውን የሚቀናቀን ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በመጨረሻም ጴጥሮስና ዮሐንስ በኢየሱስ ስም ካሁን ወዲህ እንዳይሰብኩ በማዘዝ ይለቋቸዋል።

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 4፡23-37

ጴጥሮስና ዮሐንስ ወንጌልን ከሰበኩ በኋላ አንካሳውን ሰውዬ ይፈውሱታል። በቀረቡት መልእክትና በነበራቸው መልካም ምግባር ምክንያት እሥር ቤት ገብተው ነበር። በተላቀቁም ጊዜ፤ በክርስቲያኖች ላይ ብዙ ጭቆና እንደሚፈጸም በመረዳታቸው ቶሎ ብለው ወደ ሌሎቹ ወደተቀሩት ክርስቲያኖች ይመለሳሉ። በዚህ ሳምንት በስደቱ ላይ የነበራቸውን አመለካከት እናያለን።

ዛሬ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ዓለም አቀፍ የሆነ ተቃውሞ አለ። ቅዋሚው የሰው ንጽሕናን በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል የሚያቀርበው መመዘኛ ላይ ነው። ከጥንት ክርስቲያኖች ምሳሌነት ብዙ ልንማር እንችላለን። ለዚህ ዓመፀኛ ዓለም ተገቢውን ምላሽ ይሰጡት የነበረው ክርስቲያን በሚጠቀምበት በታላቁ መሣሪያ ማለት በጸሎት ነው።

ሁለቱ ደቀመዛሙርት ከዓመፀኞቹ ሽማግሌዎች ዘንድ በመነሣት ወደ ክርስቲያኖቹ ይመለሳሉ፤ ምናልባትም እነዚህ ይጸልዩላቸው ይሆን ነበር። የሆነባቸውን ነገር በሙሉ በዝርዝር ከገለጹ በኋላ የካህናት ሽሞቹና ሽማግሌዎቹ የሰጧቸውን ማስጠንቀቂያዎች ነገሯቸዋል። ሌሎች ይህን ሲሰሙ በጸሎት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ወደ እግዚአብሔር አሰሙ።

የሐዋርያት ሥራ 4፡23-27 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 26:- ሀ) ጸሎታቸውን ያቀረቡት ለማነው? ለ) ይህ ጸሎት ስለ ክርስቲያኖቹ እምነት የሚያሳየን ነገር ምንድነው? ሐ) በጸለዩበት ወቅት እግዚአብሔርን የጠየቁት ነገር ምንድነው? መ) በጸለዩ ጊዜ እግዚአብሔር መልስ የሰጠው እንዴት ነው? ሠ) ጉልህ ለሆነው ለእግዚአብሔር መልስ አማኞቹ ምን ዓይነት ምላሽ ነው የሰጡት? ረ) አማኞቹ ንብረቶቻቸውን በአንድነት ይጠቀሙባቸው የነበረው ለምንድነው? ሰ) በርናባስ ማነው? የስሙስ ትርጓሜ ምንድነው? ሸ) በርናባስ መሬቱን የሸጠው ለምንድነው?

ክርስቲያኖቹ የጴጥሮስንና የዮሐንስን ገለጻ ከሰሙ በኋላ መጸለይ ጀመሩ። እ'ዚአብሔርን «ሁሉን የፈጠርህ» ብለው ይጠሩታል። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንደሚቆጣጠር ምድራዊ ነገሥታትና ውሳኔዎቻቸውን እንኳ ሁሉ እንደሚቆጣጠር ያዩ'ናሉ። አንተ ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም በእነርሱም የሚኖሩትንም ሁሉ የፈ ጠርክ» በማለት ፈጣሪነቱን ይመሠክራሉ።

ጥያቄ 27:- በምትጸልይበት ወቅት የምትጸልየው በእግዚአብሔር ሁሉን ፈጣሪነት ላይና ሁሉን ገዢነት ላይ በሙሉ ልብ ተማመንህ ነው? ይህ በጸሎት ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ነው የሚያኖረው?

ክርስቲያኖች በሙሉ ልብ ተማምነው ነበር የሚጸልዩት ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል የሚናገራቸው ነገሮች በአካባቢያቸው ሲፈጸሙ ያዩ ነበርና ነው። ከመዝሙረ ዳዊት 2:1-2 ላይ ይጠቅሳሉ። አይሁዳውያኑ የብሉይ ኪዳን ጠበብት፣ ይህ የመዝሙር ክፍል ስለ መሢሑ ነው የሚጠቅሰው ብለው ያምኑ ነበር። ክርስቲያኖቹ በዳዊት መጻፉንና አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ ይታወቅ የነበረውን ነገር ያምኑ ነበር፣ ሲፈጸምም አይተዋል። ሄሮድስ፤ ጲላጦስ፤ የአይሁድ ሕዝብና የሮም ወታደሮች በኢየሱስ ላይ የዶለቱት ሸረብ እንዲፈፀም እግዚአብሔር እንደፈቀደና በሱ ውጥን ሥር እንደሆነ አሁን ተረድተዋል። የኢየሱስ ሞት ድል እንጂ ሽንፈት አልነበረም።

ጥያቄ 28:- እግዚአብሔር በሰዎች የከፋት ሥራ ተጠቅሞ ዓላማውን ሲፈጽም አይተህ ታውቃለህ? ሰፋ አድርገህ ግለጸው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት አምስት ወጣቶች የወንጌሉን መልእክት ይዘው አደገኛው የሕንድ ጎሳ ይገኝበት ወደነበረው ወደ ደቡብ አሜሪካ ጫካ ያመራሉ። አምስቱም ሰዎች በእነዚህ የአሜሪካ ሕንዶች ይገደላሉ። በእነዚህ ሰዎች ሞት ምክንያት ግን የአንዱ ሰውዬ ሚስትና የሌላኛው እህት ወንጌሉን ለሰዎቹ ማካፈል ቻሉ። ይህ የሚያሳዝን ዜና በዓለም ሁሉ በተሠራጨበት ወቅት ብዙ ወጣቶች በሞቱት አምስት ሰዎች ምትክ እንሄዳለን ብለው ምኞታቸውን ለእግዚአብሔር ገለጡ። በዚህም ምክንያት ብዙ ሚሲዮናውያን ወንጌሉን ወዳልሰሙ ሰዎች ይዘው ሄዱ። እግዚአብሔር የእነዚህ አምስት ሰዎች ሞት ወንጌሉን ለማሰራጨት ተጠቀመበት።

ጥያቄ 29:- እግዚአብሔር ሞትን፤ ህመምን፤ ወይም አደጋን ተጠቅሞ ይቃወመው የነበረውን ሰው ሲናገር አይተህ ታውቃለህ? ሰፋ አድርገህ ግለጸው።

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኖቹን በመፈጸሙ ካመሰገኑትና የሁሉም ፈጣሪ መሆኑን ገልጸው እምነታቸውን ካሳዩ በኋላ የጥንቶቹ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን የጠየቁትን ነገር አተኩረህ እይ። በአደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ያውቁታል፤ እግዚአብሔርም ይህ እንዲመለከትላቸው ይጠይቁታል። ማስፈራራት እንዲቆም ወይም በስደቱ ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስባቸው አልጠየቁትም። ክርስቲያኖች ቃሉን የሚናገሩበትን ድፍረት እግዚአብሔር እንዲሰጣቸውና ድንቅና ተአምራት መፈጸሙን እንዲቀጥል ነው የጠየቁት። ኃይል የፈለጉት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥራ ሳይፈጽሙ እንዳይቀሩ ሲሉ ነው። በአገልጋዩ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በኩል ክብሩ ለእግዚአብሔር እንዲደርስ ይሻሉ።

ጥያቄ 30:- በስደትና በችግር ውስጥ ተዋክበን ሳለ እንዴት ነው መጸለይ ያለብን?
ጥያቄ 31:- ክርስቲያኖች ከጸለዩ በኋላ እግዚአብሔር መልስ የሰጣቸው እንዴት ነው?

ምናልባት በዚያን ቀን ለክርስቲያኖቹ የሰጣቸውን ዓይነት ግልጽና ቅፅበታዊ የጸሎት መልስ እግዚአብሔር እንዲሰጠን እንፈልግ ይሆናል። ምንም እንኳ እንደዚያ ቀን ቤቱን ባያናውጠው፤ በቃሉ ውስጥ ተስፋውን ሰጥቶናል። በሐዋርያት ሥራ 4:24-30 ላይ ደቀመዛሙርቱ በሙሉ ልብ ተማምነው ነበር፤ ይህም የሆነው በክርስቶስ ውስጥ ስለነበሩና ትዕዛዙን ይጠብቁ ስለነበር ነው። ይህም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲለምኑ አድርጓቸውል።

ጥያቄ 32:- 1ኛ ዮሐንስ 5:14፤ 3:21-22 እና ዮሐንስ 15:7 አንብብ። በምንጸልይበት ወቅት እነዚህ ጥቅሶች ምን መተማመኛ ይሰጡናል?

ጥያቄ 33:- ስትጸልይ በጸሎትህ ትተማመናለህ? የማትተማመን ከሆነ፤ በእነዚህ ጥቅሶች ላይ በመመርኮዝ ምክንያቱን መርምር። ትንቢተ ኢሳይያስ 59:2 እና ያዕቆብ 1:5-8፤ 4:2-3 ተመልከት። በምንጸልይበት ወቅት የምንፈልጋቸውን መልሶች የማናገኘው ለምንድነው?

የኢየሩሳሌም የነበሩት ክርስቲያኖች በራስ መተማመን የታየው ይጸልዩበት የነበሩበት ቤት ልክ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደያዘው በተናወጠበት ወቅት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በድፍረት የተናገሩት በመንፈስ ቅዱስ በመሞላታቸው ነው። የጥንቶቹ ክርስቲያኖች ይመራቸውና ያረጋግጥላቸው ዘንድ እኛ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናገኘውን ዓይነት የተጻፈ ቃል ኪዳንና ምስክርነት አልነበራቸውም። በምንጸልይበት ወቅት፤ እግዚአብሔር የሚሠጠን የትኛው ዓይነት መልስ ለእኛ ጥሩ እንደሆነ ማመን አለብን።

ስደቱ ክርስቲያኖቹን በአንድነት በጸሎት እንዲሰበሰቡ አድርጓቸዋል። አብረው በሚጸልዩበት ወቅት ስለ እያንዳንዳቸው የማሰብና የአንድነት መንፈስ ነበራቸው። ዓላማቸው አንድ ነበር፤ ስለ እያንዳንዱም ችግር ግድ ይላቸዋል። በራስ ወዳድነት የራሳቸውን ንብረት ተንገብግበው ከመያዝ ይልቅ ያላቸውን ንብረት በሙሉ ይከፋፈሉ ነበር። ሰይጣን በአንድነት ውስጥ ኃይል እንዳለ ስለሚያውቅ ሊያፈራርሰው

ይሞክራል። በሚቀጥለው ሳምንት መልካም ምግባር እንኳ አነሣሡ ከተሳሳተ አስተሳሰብ ከሆነ፣ ጠቃሚ እንደማይሆን እንመለከታለን።

ጥያቄ 34፡- ሀ) በቤተክርስቲያንህ የሚገኙ ክርስቲያኖች «አንድ ልብና አንዲት ነፍስ» አላቸው? ለ) ይህ የሚገለጸው እንዴት ነው? ካልሆነስ ለምንድነው? ሐ) ይህ ነገር ተፈጻሚ እንዲሆን ባለፉት ጊዜያት ስደት የተጫወተው ሚና ምን ያህል ነው? መ) አንድነትን ሰፋ ባለ ለማጠናከር ሲባል፣ ምን ማድረግ ይገባናል?

በአማኞቹ መካከል የነበረውን አንድነትና ፍቅር ድሃ ለሆኑት እንዲያስቡ አድርጓቸዋል። ብዙ የነበራቸው ከሌላቸው ጋር ይካፈሉ ነበር። ቤትና መሬት የነበራቸው ንብረታቸውን ሸጠው ገንዘቡን ለሐዋርያቱ ይሰጡ ነበር፣ እነሱም ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ያከፋፍሉ ነበር። ሃብታሞቹ ሰዎች ይሰጡ የነበረው ተገደው ሳይሆን ከፍቅር የተነሣ ድሃ ለሆኑት በማሰባቸው በመጨነቃቸው ነው።

ጥያቄ 35፡- አንድን ክርስቲያን ለድሃ ለመስጠት የሚያነሣሣው ስሜት ምን መሆን ነው ያለበት?

ከአማኞቹ መካከል፣ ትውልዱ ከቆጵሮስ የሆነ ዮሴፍ የሚባል ሌዋዊ ነበር። ሐዋርያቱ «በርናባስ» ብለው ነበር የሚጠሩት፥ ትርጓሜውም የመጽናናት ልጅ ነው። ወደ በኋላ ስለ በርናባስና ስለ የማጽናናት አገልግሎት ብዙ እንማራለን (ሐዋ. 11፡22-24)። በርናባስ መሬቱን ሸጠ፣ ገንዘቡን ደቀመዛሙርት እግር ሥር ያስቀምጣል። የሰጠውም ከፍቅር የተነሣ፣ ሌሎችን ለመርዳት ሲል ነው። በክርስቲያኖቹ መካከል መሬትን ሽጥ ወይም ንብረትህን ሽጥ የሚል ሕግ አልነበረም። ይኖሩ ይበሉና ይጸልዩ የነበረው በአንድ ላይ ነበር፣ ይህም አብረው እንዲጠነከሩ ረድቷቸዋል። ይህ በአካባቢያቸው ይኖሩ ለነበሩት ሰዎች ትልቅ ምሥክርነት ነበር።

ጥያቄ 36፡- የእግዚአብሔር ቃል ስለመስጠት ምን ይላል? 2ኛ ቆሮ. 9፡6-18፣ ማቴ. 6፡1-4፣ ዘኍ. 16፡17፣ 1ኛ ቆሮ. 16፡2 አንብብ። ይህንን ነገር በሕይወትህ ውስጥ እየተለማመድክ ነው? እስቲ እራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ። 1) እንዴት ነው መስጠት ያለብኝ? 2) ምን ያህል ነው መስጠት ያለብኝ? 3) መቼ ነው መስጠት ያለብኝ 4) ለምንድነው የምሰጠው? 5) ለመስጠት የሚያነሣሣኝ ስሜት ዋነኛ ነገር የሚሆነው ለምንድነው?

የጥንቶቹ ክርስቲያኖችና በርናባስ ትክክለኛውን ሐሳብ ይዘው ነበር የሚሰጡት። ለተቸገሩ በማሰብ ከፍቅር ተነሣሥተው ነበር የሚሰጡት። በገላትያ 6፡2 ላይ ጳውሎስ «ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም፣ እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ይፈጽም» ብሎ የጻፈውን ምክር ይከተሉ ነበር።

ጥያቄ 37፡- በቤተ ክርስቲያንህ የሚደረገው አሰጣጥ ድሆችን ሊረዳ የሚችለው እንዴት ነው?

## አምስተኛ ቀን፡-

ትምህርቱን ከልስና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ለክርስትና እውነተኛነት ማስረጃ ሊሆነው የሚችለው አንጹና ግልጽ የሆነው ነገር ምንድነው?
2. በጥንቷ ቤተክርስቲያን ወቅት የድንቆቹና የተአምራቱ ዓላማ ምን ነበር?
3. ጴጥሮስ በድፍረት ስለ ወንጌል እንዲመሠክር ያደረገው ነገር ምንድነው?
4. ሽማግሌዎቹ እነማን ነበሩ?
5. ሰዱቃውያን ያምኑበት የነበረው ነገር ምንድነው?
6. የወንጌሉ መልእክት ማካተት የሚገባውን ነገር በተመለከተ አጠር ያለ ማብራሪያ ስጥ።
7. በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 4 ውስጥ የሚገኘውን ቁልፍ የሆነውን ጥቅስ ጻፍ።
8. በምንጸልይበት ወቅት መተማመኛ የሚሰጠን ነገር ምንድነው?
9. እምነታችንን የሚያጠነክር ዛሬ እኛ ክርስቲያኖች ያለን የጥንቶቹ ክርስቲያኖች ግን የሌላቸው ነገር ምንድነው?
10. ከበርናባስ ምግባር ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው?

ለሳምንታዊው ስብሰባ ለመዘጋጀት የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. ክለሳ
4. ውይይት

ሀ/ 1. አንድ ሰው ክርስትና እውነት ከእግዚአብሔር እንደሆነ ማስረጃ ከፈለገ ከሁሉም በላይ የሆነ ማረጋገጫ ምንድነው? 2. ይህ ማስረጃ በቤተክርስቲያንህ ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው?

ለ/ መቼ ነው ባለሥልጣኖችን ተቃውመን እግዚአብሔርን መከተል ያለብን? ይህ በሕይወትህ እንዴት እንደተፈጸመ ምሣሌዎች በመስጠት አሳይ።

ሐ/ 1. አንድ ክርስቲያን ድሃን በተመለከተ ምን ሐላፊነት አለው? 2. ይህ ሐላፊነት እንዴት እንደተከናወነ ከራስህና ከቤተክርስቲያንህ አገልግሎት መሠረት በማድረግ አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

መ/ ለጸሎታችን መልስ እንዳናገኝ የሚያደርጉን ነገሮች ላይ ተወያይ።

ለቤተክርስቲያንህ አባላት ይህ ልታስተምራቸው የምትችለው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 4

የሐዋርያት ሥራ 5፡1-6፡7

## የመጀመሪያ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 5፡፡1-11

ባለፈው ሳምንት ስለ አንካሳው ሰውዬ መፈወስና ደቀመዛሙርቱ ስለ ኢየሱስ በመመስከራቸው ለመጀመሪያ ግዜ ስለመታሠራቸው አጥንተናል። እንዳየነው ምንም እንኳ የአይሁድ መሪዎች ስለ ኢየሱስ አታስተምሩም ቢሏቸውም እነሱ «እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደሆነ ፍረዱ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም» ብለው ይመልሱላቸዋል። ምሥክሮቼ ሁኑ የሚለው የኢየሱስ ትዕዛዝ፤ ስለ ኢየሱስ አታስተምሩ ከሚለው የአይሁድ አለቆች ትዕዛዝ ይልቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ከእሥር ቤት ከተለቀቁ በኋላ እግዚአብሔር እንደገና መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር እንደሆነ ገልጾላቸዋል። መንፈስ ቅዱስ ከጥንቶቹ ክርስቲያኖች ጋር እንደሆነ የታየበት አንድ ሁኔታ እነዚህ ክርስቲያኖች በነበራቸው በቀረበ ኅብረት ውስጥ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቁ በኋላ ሁሉም የአንድ አካል አባል ሆኑ ይህም የክርስቶስ አካል ነው (1ኛ ቆሮ. 12፡13)። ይህ ኅብረት ንብረታቸውን ለማካፈል ፈቃደኞች አድርጓቸዋል። አንድ ሰው ተቸግሮ ሲያዩ ንብረት የነበራቸው ወይም መሬታ ያላቸው ይሸጡና ለተቸገረው እንዲያከፋፍሉ ገንዘቡን አምጥተው ለሐዋርያቱ ይሰጣሉ። ዛሬ ግን ሰይጣን በኃጢአትና በግብዝነት በመጠቀም ይህን ኅብረት እንዴት ለማፍረስ እንደሞከረ እናያለን።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ኃጢአት ካለ ቤተክርስቲያን ማድረግ ያለባት ነገር ምንድነው? በዛሬው ትምህርት፤ እግዚአብሔር ኃጢአትን ምን ያህል እንደሚጠላ ለማሳየት ሐናንያና ሰጲራ ላይ የማያዳግም እርምጃ ይወስድባቸዋል። በቤተክርስቲያን ውስጥ፤ ከምንገኝበት እውነተኛ የመንፈሳዊ ደረጃ ይበልጥ በደህና ሁኔታ እንገኛለን ብለን ለማሳየት እንገፋፋ ይሆናል። ይህ ግብዝነት ነው እግዚአብሔርም ከእርሱ ዘንድ ኃጢአትን መሸፈን እንደማይችሉ አሳያቸው።

ጥያቄ 1፡- ሀ) በሕይወትህ ውስጥ ግብዝነት አለብህ? እንዴት ነው የሚታየው? ለ) አስመሳይ ሆነህ ትገኛለህን? ኃጢአትህን ለመሸፈን ትሞክራለህ? መልሱ አዎን ከሆነ አሁኑኑ ከእግዚአብሔር ይቅርታ ለምን።

ጥያቄ 2:- የሐዋርያት ሥራ 5:1-6:7 አንብብ። ሀ) ስደቱ በጨመረ ቁጥር ደቀመዛሙርቱ የሚሰጡት ምላሽ ምን ዓይነት ነበር? ለ) ብዙ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች በመምጣታቸው ምክንያት ደቀመዛሙርቱ ያደረጉት ነገር ምንድነው?

የሐዋርያት ሥራ 5:1-11 እንደገና አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ። ጥያቄ 3 ሀ) የሐናንያም ስጦታ ውስጥ ስሕተት የነበረው ምንድነው? ለ) ደቀመዛሙርቱን ለማታለል የፈለገበት ምክንያት ምንድነው? ሐ) ጴጥሮስ የሐናንያንና የሰጲራን ዕቅድ ያወቀው እንዴት ነው? መ) እግዚአብሔር በቅጽበት ይህን ዓይነት ቁርጥ ያለ እርምጃ የወሰደው ለምን ይመስልሃል?

በመካከላቸው በነበረው ፍቅር ምክንያት በኢየሩሳሌም ይገኙ የነበሩት ክርስቲያኖች እንዴት አድርገው ንብረታቸውን ይከፋፈሉ እንደነበረ ባለፈው ሳምንት አይተናል። አንዱ የጥንቶቹን ክርስቲያኖች ንብረታቸውን እንዲሸጡ ያነሳሳቸው ምክንያት ኢየሱስ ዳግመኛ ቶሎ ብሎ ይመጣል ብለው በማሰባቸውና ምድራዊ ነገሮች አያስፈልጉንም ብለው በመገመታቸው ነው። እግዚአብሔር ይህንን እንዲያደርጉ አላዘዛቸውም፥ እንዲያውም አንዳንድ ጠበብት እነዚህ የጥንት ክርስቲያኖች ንብረታቸውን ቤታቸውን ወዘተ... መሸጣቸው ወደ በኋላ አካባቢ የኢየሩሳሌምን ቤተክርስቲያን ድሃ እንድትሆን ያደረገው አንዱ ምክንያት ነበር ብለው ይገምታሉ። በሐዋርያት ሥራ 11:27-30 እና 2ቆሮ. 14 አሕዛብ ክርስቲያኖች አይሁዳውያን ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን በገንዘብ ሁለት ጊዜ መርዳት እንደነበረባቸው እናያለን። እግዚአብሔር ሁሌም ቢሆን ክርስቲያን ወገኖቻችንና የተቸገሩ ሰዎችን እንድንረዳ ይፈልጋል። ሆኖም ይህን በምናደርግበት ወቅት ሌሎችን ለዛች ለተወሰነች ጊዜ ብቻ ሳይሆን እስከ ዘለቄታው ድረስ እንድንረዳቸው ጥበብ ያስፈልገናል።

ባለፈው ሳምንት በርናባስ ብለው የሚጠሩት ዮሴፍ ለደቀመዛሙርቱ ስላደረገው ቸርነት ስጦታ አንብበናል። ያለጥርጥር ይህ ስጦታ የተለየ ደስታን በአማኞቹ መካከል ፈጥሯል፤ በርናባስም በታላቅ ክብር ያዩት ነበር። ሐናንያና ሚስቱ ሰጲራ ሌሎች በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኙ የነበሩ አማኞች መሬታቸውን ለመሸጥ ይወስናሉ። ለዚህ ያነሣሣቸው ሐሳብ ግን የተለየ ነበር። በርናባስ በበጎ አስተሳሰብ በመነሣሣት አማኞችን ለመርዳት ሲል ነው የሰጠው፤ ሐናንያና ሰጲራ ግን መሬታቸውን የሸጡት በአማኞቹ ዘንድ መንፈሳዊያን ሆነው ለመታየት ስለፈለጉ ነው። ያለጥርጥር በርናባስ ያገኘውን ዓይነት ሙገሳ ለማግኘት ይሹ ነበር። ካገኙት ገንዘብም ከፊሉን ለቤተክርስቲያን ለመስጠት ይስማማሉ። ይህ እንደዚህ ሆኖ ሳለ ለሰዎቹ ከሽያጩ ያገኙትን ገንዘብ በሙሉ እንደሰጡ አድርገው ነበር የሚናገሩት። በሌሎች ዓይን መልካም ሆነው በመታየት ሙገሳን ለማግኘት ነበር የሚፈልጉት። ሆኖም፥ ይናገሩና ይኖሩ የነበረው የውሸት ኑሮ ነው። ይህ ደግሞ ግብዝነት ነው፤ ግብዝነት ደግሞ ኃጢአት ነው። ይህ ኃጢአት በቤተክርስቲያን ላይ የተሠራ ብቻ ሳይሆን በራሱ በእግዚአብሔር ላይ የተሠራ ኃጢአት ነው።

ምናልባትም ሐናንያና ሰጲራ ያደረጉትን ለጴጥሮስ የነገረው መንፈስ ቅዱስ ይሆናል። ሐናንያ ወደ ጴጥሮስ መጥቶ የሸያጩን ገንዘብ ሊሰጠው ሲል ጴጥሮስ «ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ?» ብሎ ይጠይቀዋል (ቁ. 3)። መሬቱ የሐናንያ ንብረት ነበር፥ ከሸጠው በኋላ ገንዘቡ ያራሱ ነው። መሬቱን እንዲሸጥ ወይም ገንዘቡን እንዲሰጥ ያስገደደው ማንም ሰው የለም። ሃብታሞቹ ክርስቲያኖች መሬታቸውን እንዲሸጡ የሚያስገድድ ምንም ዓይነት ሕግ በቤተክርስቲያን ውስጥ አለነበረም። ሐናንያ ግን ገንዘቡን ካመጣ በኋላ ከመሬቱ ሽያጭ ያገኘው ይህ ብቻ እንደሆነ ለማስመሰል ሞከረ።

ጥያቄ 4:- ዛሬ ክርስቲያኖች ይህን የመሰለ ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጽሙት እንዴት ነው?

ይህ በቤተክርስቲያን ውስጥ የተፈጸመው የመጀመሪያ ኃጢአት የግብዝነትና የማታለል ኃጢአት ነበር። ቤተክርስቲያን ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ሙሉ በሙሉ በእውነተኛነት ታማኞች ልንሆንበት የሚገባ ቦታ ነው። በሐናንያና በሰጲራ ላይ የወረደው የእግዚአብሔር ፍርድ ቅጽበታዊና የማያዳግም ነበር። ጴጥሮስ ኃጢአቱን ጠቆመ፤ ፍርዱን ግን የሰጠው እግዚአብሔር ነው። ጴጥሮስ ሐናንያ ገንዘቡን በማስቀረቱ አልወቀሰውም። ነገር ግን እውነት ያልሆነን ነገር እንደ እውነት አድርጎ ለማቅረብ በመሞከሩ የዋሸው መንፈስ ቅዱስን ነው።

ጴጥሮስ ከፈረደበት በኋላ ሐናንያ ሞተ፤ አንስተውም ቀበሩት። ከሦስት ሰዓት በኋላ፥ ባሏ ምን እንደሆነ ያላወቀችው ሰጲራ፤ ከመሬቱ ሽያጭ ስላገኙት ገንዘብ ብትጠየቅ እሷም እራሷ ትዋሻለች፤ በዚህም ምክንያት ትሞታለች።

ለምንድነው ይህ በጣም ከባድ የሆነ ኃጢአት የሆነው? ለእኛ የበለጠ መንፈሳዊ ሆነን ለመታየት ብንዋሽ ይህን ያህል ከባድ አይሆንብንም። ለእግዚአብሔር የሠራነውን ሥራ በተመለከተ፥ ወደ ክርስቶስ ያመጣናቸውን ሰዎች በተመለከተ ... ወዘተ. እንዋሻለን እውነቱን ወደማይመስል ደረጃ ላይ እናደርሰዋለን። ይህ ያልሆኑትን ያህል መንፈሳዊ ሆኖ የመገኘት በሽታ በቤተክርስቲያን ውስጥ የተለመደ በሽታ ነው። ጴጥሮስ ይህ ሐናንያና ሰጲራ በቤተክርስቲያን ላይ የፈጸሙት የግብዝነት ኃጢአት ቀጥታ የተፈጸመው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ላይ እንደሆነ ይጠቁማል። ለሌሎች ሰዎች ውሸት ስንናገር የምንዋሸው ሰዎቹን ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርንም ጭምር ነው።

ጥያቄ 5 :-እኛ ትንሽ ናቸው ብለን የምንገምታቸው በእግዚአብሔር ዓይን ሲታዩ ግን ስሕተት የሆኑ አንዳንድ ኃጢአቶችን ዘርዝረህ ጻፍ።

አንዳንዴ እግዚአብሔር ለምን እንዲህ ዓይነት የጠበቀ ፍርድ በሐናንያና በሰጲራ ላይ ወሰደ ብለን ልንገረም እንችላለን። «በቤተክርስቲያኑ ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሐት ሆነ» (ቁ. 11)። በዚህ ሥፍራ ፍርሐት ሲል ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት ማለት ነው፤ ይህም የሱን ፈራጅነትና ኃያልነት መገንዘብ ነው። እንዲሁ ያለው አስተሳሰብ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰ ሕይወት እንድንኖር ይገፋፋናል።

**ጥያቄ 6:- እግዚአብሔር ትፈራዋለህ፤ ታከብረዋለህ? ይህ በሕይወትህ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ምንድነው/**

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብዝነት ወይም አታላይነት ባለበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊሠራ አይችልም። በቤተክርስቲያን ውስጥ በአባላቱ መካከልና በእግዚአብሔር ፊት ግልጽነት ታማኝነት መኖር አለበት። ብዙ ቤተክርስቲያናች ዛሬ የምስክርነት ደብዛቸው ጠፍቷል፤ ምክንያቱም ኃጢአታቸውን እየሸፈኑ መንፈሳዊ ለመሆን የሚሹ ብዙ ሰዎች ውስጥ ውስጡን በመስግስጋቸው ነው። ይህ በተራ አባላትም ላይ ቢታይ አያስደንቅም፤ ሆኖም ብዙ ጊዜ የቤተክርስቲያን መሪዎች የሚኖሩት በግብዝነት በመሆኑ ያስገርማል።

ሐናንያና ሰጲራ ለምን ማታለል እንደፈለጉ አናውቅም። ምናልባት ግን በራናባስ ሲሰጥ የነበረውን ክብርና ደስታ በማየታቸው፤ እነርሱም ይህን ዓይነት ክብር ለማግኘት ሲሉ ይሆናል።

**ጥያቄ 7:- በቤተክርስቲያን ውስጥ ገንዘብ ከመስጠትህና ከማገልገልህ በስተኋላ ለዚህ ያነሣሣህ ወይም የገፋፋህ ነገር ምንድነው?**

ዛሬ፤ ገንዘብ ለራሳቸው እየያዙ ከልብ ለጋስ የሆኑ መስለው ለመገኘት የሚጥሩ ሰዎች አሉ። በቅርብ ቀን በአንድ አገር አንድ በቴሌቪዥን ይሰብክ የነበረ ወንጌላዊ ለአገልግሎት ማገዣ እንዲሆን ለእግዚአብሔር ሥራ እንዲውል ሰዎች ይሰጡት በነበረው ገንዘብ ተጠቅሞ ለራሱ የተንጣለለ ቤት ሠራ፤ ልብስ ገዛበት ለሌላም ለግሉ ለሆነ ነገር አዋለው። ዛሬ፤ ገንዘቡን በሕገ ወጥ ስለተጠቀመበት እሥር ቤት ገብቷል።

ሌላ ወንጌላዊ ደግሞ እርሱ ራሱ ብርኩሰት ሕይወት እየኖረ ኃጢአትን በመቃወም ይናገር ነበር፤ ተገቢውም የሥነ-ሥርዓት ቅጣት ተቀበለ፤ ሆኖም ካሁን ወዲህ የሱ መልእክት በብዙ ሰዎች የሚታመን አይሆንም። እነዚህ ሁለት ሰዎች በወንጌሉ ምሥክርነት ላይና በቤተክርስቲያን ስም ላይ ብዙ ጉዳት አድርሰዋል።

**ጥያቄ 8:- እግዚአብሔር ዛሬ ልክ ሐናንያና ሰጲራ ላይ በብርቱ እንደፈረደባቸው በእኛ ላይ ቢፈርድ በቤተክርስቲያንህ ምን ይሆን ነበር ብለህ ታስባለህ?**

በሐናንያና በሰጲራ ላይ የወረደው የእግዚአብሔር ፍርድ ለጥንቷ ቤተክርስቲያን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነበር። እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላና ኃጢአተኛውንም እንደሚቀጣ የሚያሳይ ነው። አንድ አማኝ ኃጢአት ለመሥራት ካሰበ፤ ሰይጣን ደግሞ በተግባር እንዲፈጽመው ይገፋፋዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ባለጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራል ይላል (1ጴጥ. 5:8)። በጥንቷ ቤተክርስቲያን የተፈጸሙት ብዙዎች ነገሮች እንደምሳሌም እንደመመሪያ እንዲሆኑ ተብሉ የተፈጸሙ ናቸው። እግዚአብሔር ኃጢአት ላይ ሁሌ እንዲህ ዓይነት ቅጽበታዊ የሆነ የማያዳግም ፍርድ አይሰጥም። አንዳንድ ጊዜ ግን ሞትን እንደ መቀጣጫ ሊጠቀምበት ይችላል (1ቆሮ. 11:27-32)። ምንም እንኳ ሁሌም ኃጢአት ላይ ቅጽበታዊ የሆነ ፍርድ ባይሰጥም፥ ኃጢአትን መፍረዱ አይቀርም። ልባችንና የምንነሣሣበት ሐሳባችን አብጠርጥሮ ያውቀዋል።

ጥያቄ 9:- የእራሳችንን ሕይወት ከግብዝነትና ከተሳሳተ አስተሳሰብ ልንጠብቅ የምንችለው እንዴት ነው?

ከክፉ መናፍስት ጋር ጦርነቱ የሚካሄደው በአእምሯችን ውስጥ ነው። አንድ ነገር ለማግኘት ፅኑ የሆነ ፍላጎት ቢያድርብን ወይም በአንድ ሰው ላይ ብንቀና፤ ይህን ዓይነት አስተሳሰብ ኃጢአት ወደ መሥራቱ ይመራል። ሐናንያና ሰጲራ ለጋስና መንፈሳዊ ሆኖ ለመቅረብ ከነበራቸው ምኞት የተነሳ ብዙ ገንዘብ ለቤተክርስቲያን ለመስጠት ፈለጉ፤ ነገር ግን ከገንዘቡ ከፊሉን ለራሳቸው ማስቀረትም ፈለጉ። ይህ ኃጢአታቸውም ለሞት ዳረጋቸው።

ጥያቄ 10:- 2ቆሮ. 10:3-6፤ ኤፌሶን 6:10-18 እና ፊልጵሲዩስ 4:8-9 አንብብ። ኃጢአትን ልንዋጋ የምንችልባቸውን የተለያዩ መንገዶችን በዝርዝር ጻፍ።

በዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ ተፈጸመ ተብሎ በተመዘገበው የቤተክርስቲያ ኃጢአት ላይ እግዚአብሔር የማያወላዳ እርምጃ የወሰደው የጥንቷ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን የቅድስና ደረጃ ጠንቅቃ እንድታውቅ ነው። ዛሬ ይህ ደረጃ በግብፅ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተመዝግቧል። እግዚአብሔር ለሰዎች ንስሐ የሚገቡበት ጊዜ በመስጠቱ በፀጋና በምሕረት የተሞላ ነው (2ጴጥ. 3:9)።

# ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 5:12-20

ይህ እግዚአብሔር በሐናንያና በሰጲራ ላይ የወሰደው ቅጽበታዊ የፍርድ ውሣኔ በክርስቲያኖቹና በማያምኑ ዝንድ ፍርሐት ፈጠረ። ክርስቲያኖቹ እግዚአብሔር ዓይኑን ለኃጢአት ዞር እንደማያደርግ ተገነዘቡ፤ ይህም ፍርሐት ቤተክርስቲያኗን ወደ ቅድስና መራት፤ በዚህም ምክንያት ብዙ የማያምኑ ሰዎች ወደ ክርስትና ተማርከዋል።

ጥያቄ 11:- አንድ ሰው ክርስቲያን ነኝ እያለ የሚሠራው ሥራ ግን የማስመሰል ዓይነት ቢሆን ስለሰውዬው ለይተን የምናውቀው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ምንም እንኳ ኢየሩሳሌም በሚገኙት ክርስቲያኖች ላይ ትልቅ የሆነ ፍርድ ቢወርድባቸው የእግዚአብሔር ጥበቃ ግቢቶ ኃጢአት ላይ እርምጃ መውሰድ የቤተክርስቲያኒቱን ንፅሕና ጠብቋል። መለኮታዊ የሆነ ኃይል ጣልቃ መግባቱ በጉልህ የሚታይ ነገር ነው። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ አብረው ተሰብስበው የነበሩት ክርስቲያኖች «ቤተክርስቲያን የሚል ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጣቸው በሐዋርያት ሥራ 5:11 ላይ ነው።

የእግዚአብሔር ኃይል በሙላት ሲገለጥ የሰይጣንም ተቃውሞ በዚያው መጠን ይጨምራል።

ጥያቄ 12:- እግዚአብሔር በሚሠራበት ወቅት፤ በቤተክርስቲያን ላይ ተቃውሞ ጨምሮ አይተህ ታውቃለህ? ይህ እንዴት እንደሆነ አብራራ።

የሐዋርያት ሥራ 5:12-20 አንብብና እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 13፡- ሀ) አማኞች የተሰበሰቡት የት ነው ለ) ሕዝቡ በአማኖቹ የነበረው ግምት እንዴት ነው? ሐ) ሰዎቹ ከክርስቲያኖቹ ጋር ለመቀላቀል የፈሩት ለምንድነው? መ) በነበሩት ክርስቲያኖች ቁጥር የተጨመሩት እነማን ናቸው? ሠ) ብዙዎች ጴጥሮስን ይፈልጉ የነበረው ለምንድነው? ረ) ሰዱቃውያኑና ሊቀካህናቱ የተናደዱት ለምንድነው? ሐ) ደቀመዛሙርቱን ከእሥር ቤት ያወጣቸው ማነው?

ክርስቲያኖቹ ቤተመቅደስ እየገቡ መጸለዩን አላቋረጡም፤ በቤተመቅደሱ በስተምሥራቅ በኩል ይገኝ ወደ ነበረው የሰሎሞን ደጅ መመላለሻ አካባቢ ይሰበሰቡ ነበር። ብዙ የማያምኑ ሰዎች ሲጸልዩ ከአማኞቹ ጋር ለመቀላቀል ቢፈሩም እንኳ በጣም ያከብሯቸው ነበር። እምነታቸው ሙሉ በሙሉ እውነተኛ ያልሆኑ ሰዎች ምን ይሆኑ እንደነበር ስለተረዱ፥ ሰው ሁሉ መፍራትን ተምሮ ነበር። ይህም ቢሆን፥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብዙ ሰዎች በጌታ ያምኑ ነበር፤ ቁጥራቸውም ይጨምር ነበር።

ሐዋርያቱ ድንቅና ተአምራት መፈጸሙን ቀጠሉበት። የታመሙትን በድንቅ ይፈውሱ ነበር፤ እርኩሳን መናፍስትንም ያስወጡ ነበር። እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ በጴጥሮስ ውስጥ ይሠራ ነበር፤ እምነት የነበራቸውም ገና ጥላው ሲነካቸው ይፈወሱ ነበር። አንዳንዶች እንደሚያስቡት በጴጥሮስ ጥላ ውስጥ ወይም በመሃረብ ወይም በሌሎች በተባረኩ እቃዎች ውስጥ ምንም ኃይል አልነበረም። ኃይሉ ያለው ከሙታን በተነሣው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ነው። ይህ ኃይል በሕይወታችን የሚሰራጨው በእርሱ ስናምን ነው።

ቤተክርስቲያኒቱ በእምነቷ እየጠነከረች በሄደች ቁጥር የመንፈስ ቅዱስ መኖር በገሃድ ይታይ ጀመረ፤ ድንቅና ተአምራት ግን እየቀነሱ መጡ። ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ይፈውሳል፤ ግን ሁልጊዜ ለየት ባሉ ድንቅ አኳኋኖች አይደለም። በመድኃኒትና በሰለጠኑ ዶክተሮችም ሊጠቀም ይችላል። አሁን የጥንቷ ቤተክርስቲያን ታሪክ የተመዘገበበት የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት አለን፤ ይህም ስለ መንፈስ ቅዱስ መኖር ተገቢውን ማስረጃ የሚሰጠንና የሚያስተምረን ነው። ዛሬም እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ባሉ ሕዝቦቹ ሥራውን እየሠራ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከኃጢአት የምትድን ማንኛዋም ነፍስ ተአምራት ተፈጽሞባታል።

ሐዋርያቱ ይሰብኩ ያስተምሩና ተአምራትን ይሠሩ ስለነበር ብዙ ሰዎች አምነዋል። ይህም፤ ካህናቱና ሰዱቃውያኑ እንዲናደዱና እንዲቀኑ አድርጓቸዋል።

ጥያቄ 14፡- ሀ) የሃይማኖት መሪዎች የቀኑት ለምን ይመስልሃል? ለ) የሃይማኖት መሪዎች ሲቀኑ አይተህ ታውቃለህ? ምን አደረጉ?

ለሁለተኛ ጊዜ ካህናቱና ሰዱቃውያኑ ሐዋርያቱን ይዘው ወኅኒ ቤት ከተቷቸው። ባሁኑ ጊዜ ጴጥሮስና ዮሐንስ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም ደቀመዛሙርት ጭምር ነበሩ፤ ወደ ወኅኒ መውረድ የነበረባቸው፤ ይህም የሆነው ስለኢየሱስ በመመስከራቸው ነው። በዚያን ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ የወኅኒውን በሮች ይከፍትላቸውና

ያስወጣቸዋል። ደቀመዛሙርቱንም «ሂዱና ቆማችሁ የዚህን የሕይወት ቃል ሁሉ ለሕዝቡ በመቅደስ ንገሩ» አላቸው (ሐዋ. 5፡20)።

ጥያቄ 15፡- «የዚህን የሕይወት ቃል ሙሉ መልእክት ትርጉም ምንድነው? በወንጌሉ መልእክት ውስጥ ይካተታሉ የምትላቸውን ነገሮች እስቲ በዝርዝር ጻፍ።

በክርስቶስ ውስጥ ያለው የዚህ የእግዚአብሔር አዲስ የሕይወት ሙሉ ቃል ከሥጋ ደዌ ከመፈወስ በላይ ነው። አዲስ ሕይወት የሚጀምረው ኃጢአተኞች መሆናችንን አውቀን ከዚህ የሚያድነን ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ስንገነዘብ ነው። በእምነት እንቀበለዋለን፤ ከዚያም ከኃጢአታችን እንርቃለን። ሆኖም፥ ይህ ገና የአዲሱ ሕይወት መጀመሪያ ነው። በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በእውቀታችን ማደግ አለብን። ለመንፈስ ቅዱስና ለቃሉ መታዘዝ ስንጀምር በክርስቶስ ያገኘነው አዲስ ሕይወት የሠላምና የደስታ ይሆንልናል። በክርስቶስ ያለው ሕይወታችንም ኑሮአችን ዓላማ ያለው ያደርገዋል።

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ስደት ቤተክርስቲያንን በማጥራት ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ስደት ሕይወታቸውን ሙሉ ለሙሉ ለጌታ ያልሰጡትን አበጥሮ ያወጣቸዋል። ሁሌም ቢሆን ያዋጣናል ብለው በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች አሉ። ስደት ሲመጣ ግን፥ ቶሎ ብለው ፊታቸውን ዞር ያደርጋሉ። በነገው ዕለት፤ የጥንቶቹ ክርስቲያኖች ለስደት የሰጡትን ምላሽ እናያለን።

ጥያቄ 16፡- በስደት ምክንያት ቤተክርስቲያን ሲጠራ አይተህ ታውቃለህ? ካላየህ፤ ጠና ያሉ የቤተክርስቲያንህን ሰዎች ስደትን እንዳዩ ጠይቅና በቤተክርስቲያንስ ላይ ምን ያህል ለውጥ እንዳመጣ ጠይቅ።

ኢየሱስ «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ ዐለምን አሸንፌአለሁ» ብሎ በመናገር ደቀመዛሙርቱን ያጽናናቸዋል። እግዚአብሔር ችግርና ስደትን በመጠቀም፤ ሰላሙንና ፀጋውን እየሰጠን እምነታችን እንዲጠነክር ያደርጋል (2ቆሮ. 1፡3-4፤ ሮሜ 5፡3፤ 8፡35)።

# ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 5፡21-42

ሐዋርያቱ ለሁለተኛ ጊዜ በካህናቱና በሰዱቃውያን ይያዛሉ። በመጀመሪያው ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ነው የተለቀቁት። በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩ ነበር የተነገራቸው። እነሱ ግን ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ነው የምንታዘዘው አሉ። ማስተማራቸውንና መፈወሳቸውን በመቀጠላቸውም የአማኞቹ ቁጥር እየጨመረ መጣ። ካህናቱና ሰዱቃውያኑ ብዙዎች ወደ ክርስቶስ ሲሄዱ አዩ፤ በዚህም የሥልጣናቸው ጉዳይ አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን ተገነዘቡ። ንዴታቸውና ቅናታቸው እንደገና ደቀመዛሙርቱን እንዲይዙና ወኅኒ እንዲከቷቸው አደረጋቸው። ለሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔርን ከመታዘዝና ለሰው ሥልጣን ከመገዛት መካከል ደቀመዛሙርቱ መምረጥ ነበረባቸው።

ለቤተክርስቲያን ትልቁና አስጊው ነገር ስደት አይደለም። አስጊው ሁኔታ ቤተክርስቲያን በአንድ ሀገር ተቀባይነትንና ሞገስን ስታገኝ ነው፤ ምክንያቱም በዚሁ ጊዜ እየደከመች ትመጣለችና ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሰዎች ክርስቲያን የሚሆኑት እራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ሳይሰጡ ነው። ወዲያውኑም ቤተክርስቲያን ከዓለም ተለይታ ከመኖር ፈንታ፤ ዓለምን እየመሰለች ትመጣለች። ቤተክርስቲያን በስደትም ይሁን በሰላም ጊዜ ወለም ዘለም የማይሉ ክርስቲያኖች ያስፈልጓታል። ለዚህ ዓለም አሠራርና በዙሪያቸው ላለው ተፅዕኖ ራሳቸውን አሳልፈው ከመስጠት ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ዝግጁ መሆን አለባቸው።

የሐዋርያት ሥራ 5፡21-42 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ። ጥያቄ 17 ሀ) ሸንጎውንና የእስራኤልን ሕዝብ ሽማግሌዎች የጠሩት እነማን ናቸው? ለምንድነው በአንድነት የተጠሩት? ለ) ሎሌዎቹ ወደ ወኅኒ ሲሄዱ ምን አገኙ? ሐ) መልአኩ ከወኅኒ ቤቱ ካወጣቸው በኋላ፤ ደቀመዛሙርቱ የሄዱት የት ነው? መ) ሎሌዎቹ ደቀመዛሙርቱን ከቤተመቅደስ ለማምጣት ኃይል ያልተጠቀሙት ለምንድነው? ሠ) በደቀመዛሙርቱ ላይ የቀረበው ክስ ምን ነበር?

መልአኩ ደቀመዛሙርቱን ከወኅኒ ካወጣቸው በኋላ፤ «ሂዱና ቆማችሁ የዚህን የሕይወት ቃል ሁሉ ለአሕዛብ በመቅደስ ንገሩ» ያለውን ትዕዛዝ አክብረዋል። ምንም እንኳ እንደገና እንደሚያሳስራቸው ቢያውቁም እምነታቸውን ለመደበቅ አልሞከሩም። በነጋታውም ሕዝቡን ማስተማር ጀመሩ። ሊቀካህኑ ደግሞ ሸንጎውንና የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሲልኩ የወኅኒው በር ተዘግቶ ደቀመዛሙርት ከውስጡ ወጥተው ያገኛሉ። ከዚያም አንድ ሰው ደቀመዛሙርቱ በቤተመቅደስ ሕዝቡን ያስተምራሉ ብሎ ተናገረ።

ከዚህ ቀደም ብሎ ጴጥሮስና ዮሐንስ ምንም እንዳያስተምሩ ቢታዘዙም ማስተማራቸውን እንደሚቀጥሉበት ለባለሥልጣኖቹ በግልጽ ተናግረዋል (ሐዋ. 4፡18-20)። በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳያስተምሩ ከተናገሯቸው በኋላ፤ ሳይቀበሉት መቅረታቸው ካህናቱንና ሰዱቃውያኑን አናዷቸዋል። ሐዋርያቱ ለኢየሱስ ሞት ተጠያቂ ያደረጉት ሸንጎውን ነው ብለውም ተናደውባቸዋል። ሆኖም ኢየሱስ በተፈረደበት ወቅት ሕዝቡ «ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን» ብሏል (ማቴ. 27፡25)። ይህ ደግሞ እነርሱ በማያውቁት መንገድ እውነት ሆኖባቸዋል። ስለዚህም ወንጀለኞቹ በሸንጎው የነበሩት ካህናት ብቻ ሳይሆኑ ሕዝቡም ጭምር ነው።

የቤተመቅደሱ የዘበኞቹ አዛዥ ከሎሌዎቹ ጋር ሆኖ ደቀመዛሙርቱን ወደ ሸንጎው አመጣቸው። ሎሌዎችን ኃይል እንዳይጠቀሙ ያደረጋቸው፤ የተናደዱትን ካህናት እንዳይገድሏቸው ያደረገው ነገር ሕዝቡን መፍራታቸው ነው።

ሊቀካህኑ በኢየሱስ ስም ማስተማራቸውን በመቀጠላቸው ገሥፃቸው ጥያቄም ጠየቃቸው። ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀመዛሙርትም «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» ብለው መለሱለት። ከዚያም ለራሳቸው መከላከያ ከማቅረብ ፈንታ ለተሰበሰበው ሸንጎ የወንጌሉን የምሥራች አሰሙ።

በዚህን ጊዜ ብዙዎቹ በሸንጎ የተሰበሰቡት ሰዎች በጣም ተናደዱ፤ ሊገድሏቸውም ተነሡ። ነገር ግን ገማልያል የሚባል ፈሪሣዊ በሕዝቡ ዘንድ የተከበረ መምህር፤ የእነጳውሎስ አስተማሪም የነበረ ደቀመዛሙርቱን እንዲያስወጧቸው አዘዘ። በመቀጠልም ሸንጎው እነዚህን ሰዎች በነፃ እንዲለቃቸው ሐሳብ አቀረበ። ገማልያል፤ ዓመፅ ስላስነሡ ሁለት ሰዎች ይጠቅሳል፤ እነዚህ ሰዎች ከሞተ በኋላ ተከታዮቻቸውም ተበታተኑ። ለሸንጎው ምክሩንም ሲሰጥ፤ «ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተዉአቸው ይህ ሐሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደሆነ ይጠፋልና። ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ... በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ» ይላቸዋል (ቁጥ. 35-39)። የገማልያልም ምክር ሐሳባቸውን አስለወጣቸው፤ ሸንጎውም እንዲገረፉ አደረገና በድጋሚ በኢየሱስ ስም እንዳይሰብኩ ካዘዘ በኋላ በነፃ ይፈታቸዋል።

ጥያቄ 18 ፡-ሀ) እውነተኛ ክርስቲያኖች በስደት ውስጥ ሲያልፉ የሚያስገኘው ውጤት ምንድነው? ለ) አንተ ወይም የምታውቀው ሰው ስለእምነታችሁ ተሰዳችሁ ታውቃላችሁ? ስለደረሰባችሁ ነገር ሰፋ አድርገህ ግለጽ።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚረዳውና ነፃ የሚያወጣው በማይጠበቁ ነገሮች በመጠቀም ነው። ሐዋርያቱን ለመርዳት ሲል በገማልያል ተጠቀመ። ሆኖም ልጆቹን ሁልጊዜ ከችግር ነፃ አያወጣቸውም። ብዙ ክርስቲያኖች በፍርድ ቤት ፊት ቆመዋል፤ ብዙዎችም ሞተዋል። ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀመዛሙርት በእስራኤል ሸንጎ ፊት ከቀረቡ እነሆ አሁን 2000 ዓመታት ሊሆነው ነው። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ግን እስካሁን ፀንታ ቆማለች፤ የኢየሱስ ክርስቶስም ወንጌል አሁንም እየተሰበከ ነው። ገማልያል እንደተናገረው «ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ታጠፉዋቸው ዘንድ አይቻላችሁም»

ምናልባት ገማልያል ፖለቲካዊ ንቅናቄ እንዳያስነሣ ብሎ ይሆናል። ወይም ደግሞ ጴጥሮስ «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባናል» በማለቱ፤ ለሐዋርያቱ ይገባኛ ብሎ መከላከያ ማቅረብ ፈልጎ ይሆናል። ወይም ደግሞ በድብቅ አማኝ ሊሆንም ይችላል (ዮሐንስ 12፡42)። እኛ እናውቅም እንጂ እግዚአብሔር ገማልያልን ሸንጎው ሐሳቡን እንዲቀይር ተጠቅሞበታል።

ይህንን ስንል ሐዋርያቱ ወይም ደቀመዛሙርቱ ያለምንም ሰቆቃና ችግር በነፃ ተለቀቁ ማለታችን አይደለም። ምንም ነገር ባያደርጉም፤ ተገርፈው የሃይማኖት መሪዎቹ ንዴት ሊበርድ የሚችልበት ዋነኛው መንገድ ይህ ነበር። እንደገናም፤ ደቀመዛሙርቱ ወይም ሐዋርያቱ በኢየሱስ እንዳይሰብኩ ትዕዛዝ ይሰጣቸዋል።

ደቀመዛሙርቱ ቀን በቀን ወደ ቤተመቅደስ እየሄዱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሢሕ የመሆኑን የምሥራች ዜና ይሰብኩ ነበር። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ታዛዥ መሆናቸውን ቀጠሉበት።

ደቀመዛሙርቱ ስለኢየሱስ መከራ በመቀበል ላይ የነበራቸው አመለካከት በጣም ለየት ያለ ነበር። የአይሁድ መሪዎች በፈጸሙባቸው ሕገወጥ ሥራ እንዲቀጡ እግዚአብሔርን ከመጠየቅ ይልቅ አመሰገኑ። ስለ ኢየሱስ ስም ሲባል መከራ መቀበሉ መታደል እንደሆነ ተገንዝበውታል። ጳውሎስ ስደት መቀበልን «የመከራው ተካፋይ

ለመሆን ነው» (ፊል. 3፡10) ብሎ ይጠራዋል። ስለ ኢየሱስ ስም መሰቃየት አሳፋሪ ነገር አድርጎ ከመቁጠሩ ይልቅ ስቃዩ ራሱ ለእግዚአብሔር ክብር ያለንን ታማኝነትና ለክብሩም ሲባል በመከራና ስቃይ የምናልፍ መሆናችንን የብቃት ማረጋገጫችንና ማስተማመኛ ምልክታችን መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።

ጥያቄ 19፡- ሀ) ዛሬ ክርስቲያኖች የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ ዓይነት ስደቶችና መከራ እስቲ በዝርዝር ጻፋቸው። ለ) ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ለስደት የሚሰጡት ምላሽ ምን ዓይነት ነው? ሐ) እነዚህ መከራዎች የሚያዋርዱ ሳይሆኑ ክብር የሚሰጡ የሚሆኑበት ምክንያት እንዴት ነው?

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 6፡1-7

ምንም እንኳ ሁለት ጊዜ በሃይማኖት መሪዎቹ በኢየሱስ ስም እንዳይሰብኩ ቢታዘዙም ማስተማራቸውንና ተአምራት መሥራታቸውን ቀጥለውበታል። ብዙ ሰዎችም አምነውበታል። በቤተክርስቲያን የሚሰበሰቡት ሰዎች ቁጥር ሲጨምር ችግሮችም አብረው ተጨምረዋል። ሐናንያና ሰጲራ ስለ ግብዝነታቸውና ስለ አታላይነታቸው በተፈረደባቸው ጊዜ የነበረውን አንድ የቤተክርስቲያን ችግር አይተናል። አሁን ደግሞ በአማኞች መካከል ሌላ ችግር ይነሣል።

የሐዋርያት ሥራ 6፡1-7 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 20፡- ሀ) በቤተክርስቲያን ውስጥ የተነሣው ችግር ምን ነበር? ለ) በችግሩ ውስጥ የተካፈሉት ሁለት ቡድኖች እነማን ናቸው? ሐ) አሥራ ሁለት ደቀመዛሙርት ለችግሩ መፍትሔ ያገኙለት እንዴት ነው? መ) ሰባት ሰዎች የመረጠው ማነው? ሠ) እነዚህ ሰዎች ማሟላት ያለባቸውን ነገር ሰፋ አድርገህ ግለጽ። ረ) የተመረጡት ሰዎች ምን ማድረግ ነበረባቸው? ሰ) ሐዋርያቱ የራሳቸው ሐላፊነት ምንድነው ብለው ነበር የሚያስቡት?

በቤተክርስቲያንም ውስጥ አንድ እንኳ በጎሳዎች መካከል፣ በባህል ልዩነትና እርስ በርስ ካለመተማመን የተነሣ የሚመጡ ግጭቶች አሉ። የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ባደገች ጊዜ በአማኞቹ መካከል ብዙ የግሪክ አይሁዳውያን (ሄለናውያን) ነበሩ። የግሪክን ቋንቋና ባህል የተማሩ እነዚህ ግሪክ አይሁዳውያን በሌሎች አገሮች ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው። እነርሱ በይሁዳ አድገው የዕብራይስጥና የአረማይክን ቋንቋ የሚናገሩትን አይሁድ ያህል ክብርና ተደማጭነት አልነበራቸውም። በሌላም በኩል ሄብራይክ-አይሁዳውያን (ዕብራዊ-አይሁዳውያን) በመባልም ይታወቁ ነበር። ታዲያ ክርስቲያን የሆኑት ዕብራውያን አይሁድም ከሌሎች ሥፍራ ከመጡት ይበልጥ የራሳቸውን ሕዝብ በማገልገልና አድሎ በማድረግ በደል ፈጽመዋል። የግሪክ-አይሁዶችና በሄብራይክ-አይሁዶች ላይ ቅሬታ ነበራቸው። የሄብራይክ አይሁዶች ትውልዳቸው በኢየሩሳሌም ሲሆን ይናገሩ የነበረው የዕብራይስጥ ወይም አረማዊ ቋንቋ ነበር፤ እነዚህም ሰዎች የብሉይ ኪዳን ሕግጋት በድንብና በትክክል እንጠብቃለን ብለው ያምኑ ነበር።

ጥያቄ 21፡- በጎሳዎች መካከል፣ በቤተሰብ መካከል ወይም በደሃና በሃብታም መካከል፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያጋጠሙህ አለመግባባትና ግጭቶች አሉን? ይህስ ቤተክርስቲያንህን ምን ያህል ጎድቷታል።

ሰይጣን የቤተክርስቲያንን አንድነት ለማውደም ማንኛውንም ዓይነት መንገድ ይጠቀማል። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን አንድነት ከሚያጠፉት አንዱ መንገድ፥ በአንድ ክፍል ውስጥ ያለውን ሕዝብ በሌላው ክፍል ውስጥ ካለው ሕዝብ ይበልጥ እንክብካቤ ተደርጎ ለሌላው ግን እምብዛም ትኩረት ሳይሰጥ ሲቀር ነው። ይህ እንዳይሆን አጥብቀን መጠንቀቅ አለብን።

የእግዚአብሔር ቃል በመሰበኩ ምክንያት፣ ቤተክርስቲያን በሕዝብ ብዛት እያደገች መጥታለች። ይህ በጣም የሚያስደስት ነው፤ ሆኖም፥ ይህም ብዙ ችግሮች በቤተክርስቲያን ውስጥ አስከትሏል። ችግር የተነሣው የዕቃ ሥርጭትንና ገንዘብን በተመለከተ ነበር። ባሎቻቸው የሞቱባቸው የሄሌናዊው አይሁዶች መበለቶች በየዕለቱ የሚሰጣቸው የምግብ ስርጭት በአግባቡ እንዳልነበረ አቤቱታ አቅርበዋል። ብዙ ጊዜ፥ ቤተክርስቲያን ውስጥ ችግሮች የሚነሡት ገንዘብን ወይም ዕቃዎችን በተመለከተ ነው። በጥንቃቄ ወጪና ገቢን መመዝገብና የሚሠራጩትንም ነገሮች በአግባቡ ማሰራጨት በጣም አስፈላጊ ነው።

በቤተክርስቲያን ዕድገት ምክንያት የመሪነቱን ሐላፊነት ሌሎችም መጋራታቸው ሆኗል። ደቀመዛሙርቱ፤ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸውም አዩ።

ጥያቄ 22፡-እንዲህ ዓይነት ችግር በቤተክርስቲያንህ ቢያጋጥምህ ምን ዓይነት እርምጃ ነበር የምትወስደው?

የጥንቷ ቤተክርስቲያን የሚረዳቸው የሌላቸውን መበለቶች ጉዳይ ትኩረት ሰጥታ እነርሱን የመርዳቱን ሐላፊነት ወስዳለች። ሆኖም፤ ደቀመዛሙርቱ ለቤተክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ችግሮች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ተቀዳሚ ተግባራቸው ቃሉ ማስተማሩና መጸለዩ እንደሆነ ያምናሉ። ዕቃዎችን ለተቸገሩ ሰዎች የማከፋፈል አገልግሎት በቤተክርስቲያን ውስጥ መኖር አለበት፤ ሆኖም ከመንፈሳዊው አገልግሎት በላይ መሆን የለበትም። ሐዋርያት በቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ምሥረታ ላይ የሁለቱንም አገልግሎቶች አስፈላጊነት ተገንዝበዋል።

ለችግሩ የሰጡት መፍትሔ፤ ብልህ አማራጭ ነበር። ሐዋርያቱ ደቀመዛሙርቶቻቸውን ሁሉ ሰበሰቡ። ሐዋርያቱ የተጠሩት ቃሉን ለማስተማርና ለመጸለይ እንደሆነና ይህንንም እንደሚያምኑበት ይገልጻሉ። ስለዚህም፤ ክርስቲያኖቹ ከመሐከላቸው መንፈሳዊ የሆኑና (በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ) የምግብ ስርጭቱን ለመቆጣጠር ብቁ የሆኑትን ሰዎች እንዲመዘግቡ ይጠይቋቸዋል። ምንም እንኳ እነዚህ ሰዎች የተመረጡት ለምግብ ስርጭት ብቻ ቢሆንም፤ ሐዋርያቱ ተገቢ የሆነ መንፈሳዊ ብቃት ሊኖራቸው እንደሚገባም ተገንዝበዋል። በቤተክርስቲያን ሐላፊነት ለሚወስዱ ሰዎች እነዚህ ሁለት መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው። እግዚአብሔር ለተለያዩ ሰዎች

የተለያዩ ስጦታዎችንና ችሎታዎችን ሰጥቷቸዋል፤ ከዚህም ሁሉ በላይ ግን መንፈሳዊ ሰዎች መሆን አለባቸው።

ጥያቄ 23፡- ሐላፊነት እንዲይዙ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚመረጡ ሰዎች ትልቁና ዋነኛው መመዘኛ መንፈሳዊነታቸው የሆነው ለምንድነው?

ደቀመዛሙርቱ፤ በቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት ውስጥ ዕርዳታ የሚሰጡ ሰባት ሰዎችን መረጡ። የግሪክ ስሞቻቸው የመረጧቸው በሙሉ ሄሌናዊ አይሁዶች እንደሆኑ ያመለክታል። ምናልባትም የግሪክ አይሁዶች ብቻ የተመረጡት ይህ በጥቂት ሰዎች የቀረበው የአድሎ አቤቱታ ቆሞ አንድነታቸው እንደቀድሞው የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ይሆናል። ሄብራይክ አይሁዳውያን ብቻ ቢመረጡ ኖሮ ተቃውሞው ይቀጥል ነበር። ስለ ፊሊጶስና ስለ እስጢፋኖስ ወደ በኋላ ብዙ እንማራለን። ኒቆላዎስ ደግሞ ምናልባት፤ በዮሐንስ ራዕይ 2፡6 ላይ ኒቆላውያን የሚባለው የሐሰት ትምህርት መሪ ሊሆን ይችላል።

ጥያቄ 24፡- ሀ) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው «ዲያቆን» የሚለው ትርጓሜ፤ ብዙ በኢትዮጵያ በሚገኙ ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ካለው «ዲያቆን» ከሚለው ትርጓሜ የሚለያየው እንዴት ነው? ለ) ለምንድነው ይህ የሆነው?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተለመደው ዲያቆን የሚሆኑት «ወጣቶች» አልነበሩም። በምትኩ ግን፥ በሽማግሌዎች (ሐዋርያቱ) ሥልጣን ሥር ሆነው የቀን ተቀን ጉዳዮችን ለምሳሌ ችግሮችን የመርዳቱን ጉዳይ የሚመሩ መሪዎች ናቸው።

የክርስቶስ አካል በተገቢው መንገድ ይገነባ ዘንድ እና በቤተክርስቲያን ውስጥ ተገቢው አንድነት ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር የተለያዩ ስጦታዎችን ይሰጣል (ኤፌ 4፡11-13)። የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት፤ ሞትና ትንሣኤ የዓይን ምሥክሮች የነበሩት ሐዋርያት፤ የቤተ ክርስቲያኑ መሠረት ሆነው ወንጌሉን እንዲያስተምሩና እንዲጸልዩ ሐላፊነት ተሰጥቷቸዋል። አንዳንድ ስጦታዎች ከሌላው የሚበልጡ ይመስላሉ፤ ነገር ግን የእኛን ታማኝነት እግዚአብሔር የሚያየው በዛችው በሰጠን ስጦታ አጠቃቀማችን ነው። እያንዳንዱ የክርስቶስ አካል አባል የሆነ ሁሉ፤ በታማኝነት በተሰጠው ስጦታ የታቀደውን ዓላማ ሲፈጽምበት፤ ያኔ ቤተ ክርስቲያን ትጠናከራለች።

ጥያቄ 25፡- አንድ ክርስቲያን በተሳሳተ አስተሳሰብ ተነሣሥቶ ቢያገለግል የሚከተለው ነገር ምንድነው? ለምሳሌ ለገንዘብ ወይም ለራሱ ክብር ብሎ ቢያገለግል?

በሐዋርያት ሥራ 1፤8 ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ፤ ለክርስቲያኖች በሙሉ ነው። ሁሉም ክርስቲያኖች የትም ይሁኑ፤ የክርስቶስ ምሥክሮች እንዲሆኑ ነው የተጠሩት። ሆኖም ለእያንዳንዱ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን የሚጠቀምባቸውን ልዩ ስጦታዎችን እግዚአብሔር ሰጥቷል። ችሎታዎቻችንን፤ ስጦታዎቻችንና የተከፈቱልንን አጋጣሚዎች በተጠቀምንበት አኳኋን ይፈረድብናል። የቤተ ክርስቲያን ሥራ ለሰባኪዎች፥ ለወንጌላውያንና ለአስተማሪዎች ብቻ የሚተዉ አይደለም። እያንዳንዳችን ሐላፊነቱን ልንሸከም ይገባናል። አንዳንዶች ወደ ሌላ ሥፍራ ይሄዳሉ፥

ሌሎች ደግሞ እነርሱን ይረዳሉ። አንዳንዶች ደግሞ ይሰብካሉ ወይም ያስተምራሉ! ወይም ዕቃዎችን በማስተካከል ያገለግላሉ ... ወዘተ። ሁሉም መጸለይ ይችላሉ!! ሁላችንም በአንድነት ለዓለም ምሥክሮች ነን።

ጥያቄ 26፡- አንተ በደንብ የማያውቁህ ሰዎችን መንፈሳዊ ስጦታዬ ምን ይመስላችኋል? ብለህ ጠይቅ። ስጦታህን እንዴት አድርገህ እየተጠቀምክበት ነው?

# አምስተኛ ቀን

ትምህርቱን ከልስና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የጥንት አማኞችን ኅብረት አብራራ።
2. ሀ) የሐናንያና የሰጲራ ኃጢአት ምን ነበር?
   ለ) እግዚአብሔር ጥብቅ ፍርድ የፈረደባቸው ለምንድነው ?
3. በሐናንያና በሰጲራ ላይ የወረደው ፍርድ ቤተ ክርስቲያንና የማያምኑ ሰዎች ላይ ተፅዕኖ ያሳደረው እንዴት ነው?
4. ስደት በሐዋርያቱ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ አሳደረ?
5. ገማልያል ለሸንጎው የሰጠው ምክር እውነተኛነት የተገለጸው እንዴት ነው?
6. የድንቅና የተአምራት ዓላማ ምን ነበር?
7. የሸንጎው አባሎች እነማን ነበሩ?
8. ሰዱቃውያን የሐዋርያቱን መልእክት በጥብቅ የተቃወሙት ለምንድነው?
9. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሁለተኛው ችግር መንስኤ ምን ነበር?
10. ሀ) ቤተክርስቲያንን ማገልገል ያለባቸው እነማን ናቸው?
    ለ) ለአገልግሎት የሚያነሣሣቸው ሐሳብ ምን መሆን ነው ያለበት?

ለሳምንታዊው ስብሰባ ለመዘጋጀት! ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት!!

# ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊ ዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. ክለሳ
4. ውይይት፡-

ሀ) 1. በተማርናቸው ሁለት የቤተክርስቲያን ችግር ላይ ተወያይ። 2. ዛሬ በየቤተክርስቲያናቻችን ውስጥ ከሚገኙት ችግሮች ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ለ) የቤተክርስቲያን የዲሲፕሊን (የሥነ-ሥርዓት) እርምጃ፣ ለቤተክርስቲያን ዕድገት ዕንቅፋት ይሆናል ወይ? ተወያዩበት።

ሐ) 1. በኢትዮጵያ ከሚገኙት ጎሣዎች የምታውቃቸው የትኞቹ ናቸው? 2. በመካከላቸው ችግር ያለባቸው የትኞቹ ናቸው? 3. እነዚህ ችግሮች በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚታዩት እንዴት ነው? 4. ውጥረትና አለመግባባትን የሚፈጥሩት ነገሮች ምንድናቸው? 5. መፍትሔውስ ምንድነው?

መ) የእግዚአብሔር ቃል በእኛ ላይ ሥልጣን ያላቸውን ሰዎች እንድንታዘዛቸው ያስተምረናል። ልንታዘዛቸው የማንችልባቸው ወቅቶች አሉን? መቼ መታዘዝ እንዳለብንና መቼ ደግሞ መታዘዝ እንደሌለብን ምሳሌዎችን ስጥ።

ሠ) 1. በቤተክርስቲያንህ ውስጥ በአገልግሎት የዋሉትን የተለያዩ ዓይነት ስጦታዎች በዝርዝር ጻፍ። 2. እያንዳንዱ አባል ስጦታውን በሆነው ዓይነት መንገድ እየተጠቀመበት ነውን? 3. ቤተክርስቲያንህ ሁሉንም ሰው በስጦታው ተጠቅሞ ቤተክርስቲያንን የበለጠ እንዲያሳድግ ለማድረግ ስትል ተሳትፎአቸውን ልታገለብት የምትችለው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 5

የሐዋርያት ሥራ 6፡8-7፡60

## የመጀመሪያ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 6፡8-5

አንዱ የጤናማ ቤተክርስቲያን ምልክት በእግዚአብሔር ዕውቀትና በቁጥር ማደግ ነው። እንዴት አድርጋ ጌታ ኢየሱስን በተመለከተ አንዱ አባል ለሌሎች እየመሠከረ በቅፅበት የጥንቷ ቤተክርስቲያን እንዳደገች አይተናል። ሆኖም፤ ዕድገት አብሮት ችግር እንደሚያመጣም ተመልክተናል። ባለፈው ሳምንት በተለያዩ ክርስቲያኖች መካከል እንዴት ችግር እንደተነሣና መሪዎችም ችግሩን ለመፍታት ምን ነገር እንደተጠቀሙ አይተናል።

በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም ትገኝ የነበረችው ትንሿ ቤተክርስቲያን ትመራና ትተዳደር የነበረው በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ነው። የቤተክርስቲያኒቱን ሕይወት፥ የቃሉን አገልግሎትና ችግረኞችን የመንከባከቡን ሐላፊነት በሙሉ የያዙት ሐዋርያቱ ናቸው። ነገር ግን ቀደም ባለው ትምህርታችን ሐዋርያቱ እንዴት አድርገው በወንጌሉ

አገልግሎት በተለይም ዕለት በዕለት ችግረኞችን በመርዳቱ በኩል በመንፈስ የተሞሉ ሰዎችን እንዲመረጡ እንደጠየቁ አይተናል። እንደማንኛውም ጥሩ መሪ ቤተክርስቲያኒቷ ባደገችና ሊሠራ ያለው ሥራ በበዛ ጊዜ አንዳንዱ የመሪነት ሐላፊነታቸውን ለሌሎች መስጠት ጀምረዋል።

ጥያቄ 1:- ሀ) የቤተክርስቲያንህን መሪዎች ስም ዝርዝር ጻፍ። የሚሠሩት ሥራ ምንድነው? ለ) ከጥንቷ ቤተክርስቲያን ዲያቆናች ሐዋርያት የሚለዩት እንዴት ነው? የሚመሳሰሉትስ እንዴት ነው?

ጥያቄ 2:- የሐዋርያት ሥራ 6:8-7:60 አንብብ። ሀ) እስጢፋኖስ በመልእክቱ ውስጥ የጠቀሳቸውን የብሉይ ኪዳን ባህሪያት በሙሉ በዝርዝር ጻፍ። ለ) እስጢፋኖስ ምን ዓይነት ሰው ነበር?

አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት እንዲያግዙ የተመረጡት ዲያቆናት በቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረውን የችግረኞችን ፍላጎት ብቻ አልነበረም የሚቆጣጠሩት። ምንም እንኳ ይህ አንዱ የሐላፊነት ዘርፋቸው ቢሆንም ስለ ኢየሱስ በመመስከሩም ላይ ይህ ነው የማይባል አስተዋፅኦ ያደርጉ ነበር። ሉቃስ አሁን የሁለቱን ዲያቆናት አገልግሎት ሰፋ አድርጎ ይገልጻል፤ እነሱም፥ የመጀመሪያው የቤተክርስቲያኒቱ ጻድቅ ሰማዕት የሆነው እስጢፋኖስ እና ወንጌላዊው ፊሊጶስ ናቸው።

አይሁዳውያን ለብዙ ምዕተ ዓመታት እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። አምልኮአቸውም በሚያቀርቧቸው መሥዋዕቶችና በሚጥሏቸው ድግሶች ውስጥ ይታዩ ነበር። እነዚህ ልማዶች ይወክሉትና ያስተምሩት የነበረው ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው መንፈሳዊ ኅብረት ነው፤ ሆኖም ይህ ነገር በየድግሶቻቸውና በየመሥዋዕቶቻቸው ውስጥ ደብዛው ጠፍቶ ነበር፤ እና ዝም ብሎ ባዶ ዓላማ የሌለው ልማዳዊ ክብረ በዓል ሆኖ ነበር። አይሁዳውያን ደግሞ በቤተመቅደሳቸው፤ በየክብረ በዓሉ በመሰብሰባቸውና ሕጉን ሙሉ በሙሉ በመጠበቃቸው በጣም ይኮሩ ነበር። ሁሉም ክብረ በዓሎች ያከብሩ፤ መስዋዕትንም ይሠዉና ከትንሹ ሰው ጀምሮ አሥራት ይከፍሉ ነበር፤ ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት አለነበራቸውም። ኢየሱስም በምድር ላይ በነበረበት ወቅት ፈሪሳውያንንና የሕግ አስተማሪዎቹን፤ ሕጉን ስለተከተሉ ሳይሆን፤ አንዳንድ ነገሮችን ሳይሠሩ በመቅረታቸው ይገስፃቸው ነበር። በማቴዎስ 23:23 ላይ ኢየሱስ «ምሕረትን፤ ታማኝነትንም በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ ወዮላችሁ፤» ይላቸዋል።

ጥያቄ 3:- ሀ) በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ፤ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድና ሌሎች ክርስቲያናዊ ልማዶች ባዶ ትርጉም የለሽ የሚሆኑበት ጊዜ አለ ብለህ ታስባለህ? አስረዳ። ለ) በሕይወትህ ውስጥ እንዲህ ባዶ ልማድ እንዳይሆንብህ አስቀድመህ ማድረግ ያለብህ ነገር ምንድነው?

ልክ እንደ ጥንቶቹ አይሁዳውያን፤ እኛም በቀላሉ አምልኳችን «በመንፈስና በእውነት» ከመሆን ፈንታ ልማድ ሊሆንብን ይችላል። እውነተኛውን አምልኮ እንተውና በዘልማድ ማምለክ ስንጀምር፥ እግዚአብሔር እሱን የሚፈሩና ቃሉን

የሚያስተምሩ ሰዎችን ያስነሣል። ይህም ብዙ ጊዜ፤ ነባር የሆኑት መሪዎችን ተጽዕኖና ስደትም ጭምር እንዲያስነሡ ያደርጋቸዋል። ይህንን እውነታ የመጀመሪያው ጻድቅ ሰማዕት ስለሆነው ስለ እስጢፋኖስ ሕይወት ስናጠና እናየዋለን።

የዛሬው ትምህርታችን ከሐዋርያት ሥራ 6፡8-15 ላይ ነው። ይህንን ክፍል በጥንቃቄ አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 4፡- ሀ) እስጢፋኖስ የመሠከረው ለማነው? ለ) እስጢፋኖስ ከተናገረው ውስጥ በሸንጎው የነበሩትን ሰዎች ያናደደው የትኛው ነው? ሐ) በሸንጎው የተሰበሰቡት ሰዎች ከእስጢፋኖስ ጋር በሐሳብ ሲጋጩ የተፈጠረው ነገር ምንድነው? መ) ለመሪዎች ንዴት የቀሰቀሰ የእስጢፋኖስ ምላሽ ነበር?

እስጢፋኖስ በእግዚአብሔር ኃይልና ፀጋ የተሞላ ሰው ነበር። ባለፈው ሳምንት የዕለት ተዕለት የቤተክርስቲያንን ጉዳይ እንዲያስፈፅሙና ሐዋርያቱን እንዲያግዙ ከተመረጡት ዲያቆናት መካከል እንደሆነ አይተናል። እስጢፋኖስ ግን ደሃ የነበሩትን ሰዎች ብቻ አልነበረም የሚረዳው። የጥንቶቹ ክርስቲያኖች ለአይሁዳውያን ያደርጉት የነበረው ምሥክርነት ሁሌ ወንጌሉን ከብሉይ ኪዳን ጋር የሚያዛምድ ነበር። ለአይሁዳውያኑ መሢሑን በተመለከተ የሰጡትን ትንቢቶች ኢየሱስ እንዴት እንደፈጸማቸው ለማሳየት ነበር የሚፈልጉት።

በመጀመሪያ ላይ ድንቅና ተአምራትን የሚፈጽሙት ሐዋርያቱ ብቻ ነበሩ (ሐዋ. 3፡4-8) እጃቸውን ከጫኑበት በኋላ ግን እስጢፋኖስም ወንጌሉን መስበክና ተአምራትን መሥራት ጀምሯል። እጅ የመጫኑ ልማድ አይሁዳውያን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ሥልጣን ለማሸጋገርና ያንን ሰውዬ ለተለየ ሥራ እጩ ሲያደርጉት የሚፈጽሙት ነገር ነበር (ሐዋ. 13፡2-3)። የድንቅና የተአምራቱ ዓላማ ሰዎች የወንጌሉን መልእክት እንዲሰሙ ለማድረግና ሥልጣኑን ለማሳየት እንደሆነ ተመልክተናል።

እስጢፋኖስ ከፓለስታይን ውጪ የተወለደ አይሁዳዊ ነበር፤ ስለዚህም ሄለናዊ አይሁድ ነው። መስበክ በጀመረበት ጊዜም የሱ ወገን ለነበሩት ሄለናዊ አይሁዶች በጣም ይቀረቀር ነበር። በዚህም ምክንያት ሌሎች አይሁዳውያን በኢየሩሳሌም ይሰበሰቡበት ወደ ነበረው፤ የነፃ ወጭዎች ምኩራብ ወደተባለችው ሥፍራ የወንጌሉን መልእክት ይዞ ይሄዳል። ከተለያዩ የሮም ግዛቶች ይመጡ የነበሩ አይሁዳውያን ያመልኩ የነበረው በዚህ ሥፍራ ነበር።

ምኩራብ የአይሁዳውያን የመሰብሰቢያ ቦታ ነው። ብዙ አይሁዳውያን በሚኖሩበት በየትኛውም ሥፍራ ብሉይ ኪዳን ሲነበብ የሚሰሙበትንና ለአምልኮ የሚሰበሰቡበትን ቦታ ያበጃሉ። ሆኖም፤ የእንስሳ መሥዋዕትና የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓቶች ይካሄዱ የነበረው በቤተመቅደስ ውስጥ ብቻ ነው።

በኢየሩሳሌም ብዙ ምኩራቦች ነበሩ፤ ከነዚህም አንዱ «የነፃ ሰዎች ምኩራብ» ነው። «ነፃ ሰዎች» ይባሉ የነበሩት በሮም እሥረኞች የነበሩ ወይም የእነዚህ እሥረኞች ዘመዶች የነበሩ ሰዎች ናቸው። ፖምፒይ በ63 ዓ.ም ኢየሩሳሌምን በያዘ ጊዜ፤ ብዙ

አይሁዳውያንን እሥረኞች አድርጎ ወስዶ ነበር። ወደ በኋላም በሮም ውስጥ ሳሉ ነፃ ተለቀዋል። ታዲያ የእነዚህ ሰዎች ዘር የነበረባቸው ሁሉ «ነፃ ሰዎች» ተብለው ነበር የሚታወቁት፤ ምናልባትም የዚህ ምኩራብ አባላት እነርሱ ሳይሆኑ አይቀርም። የግሪክ ቋንቋን ይናገሩና ባህሉንም ያውቁ ስለነበር፤ ሄሌናውያን ተብለው ይጠሩ ነበር። ከተለያዩ አገሮች ለሚመጡ አይሁዳውያን፤ የራሳቸውን ምኩራብ የማቋቋሙ ሥርዓት የተለመደ ነበር።

ጥያቄ 5:- ሀ) ዛሬ፤ የተለያዩ ጎሳዎች የራሳቸውን ቤተክርስቲያን ያቋቁማሉን? ለ) በቤተክርስቲያንህ ውስጥ በተለያዩ ጎሳዎች መካከል የተፈጠረ ችግር አለ?

በምሥክርነቱ እስጢፋኖስ ለአይሁዳውያኑ በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተገኘውን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሚደረግበትንና ከብሉይ ኪዳን የሚበልጠውን ሥርዓት ያስተዋውቃቸውል። ይህ ነገር የተመሠረተው በእግዚአብሔር ላይ ነው፤ ሕጉንና የቀድሞውን የቤተመቅደስ አምልኮ የሚተካ ነው። አይሁዳውያን ግን ሌላ ትርጓሜ ሰጡትና፤ መልእክቱ ህጉንና የአብርሃምን አምላክ የሚቃወም ነው ብለው አሰቡ። ነፃ ወጪዎች ከእስጢፋኖስ ጋር ለመከራከር ሞከሩ፤ ሆኖም እምብዛም ውጤት አላስገኙም። በዚህ ጊዜም በጣም ተናደዱ። ምናልባትም ነገሩን አምነውበት ይሆናል። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንደ ቀፎ ባዶ እንደነበርና እውነተኛነትም እንዳልነበረው ለመቀበል አልፈለጉም።

ጥያቄ 6:- ዛሬ ወንጌል ሲሰበክ ክርክርም ግጭትን ከሌሎች ሰዎች ዘንድ የሚፈጥረው እንዴት ነው?

የአይሁድ መሪዎች የተናደዱት የእስጢፋኖስ ምሥክርነት እውነተኛ እንደሆነ ስለተገነዘቡ ነው። ሕጉ ከተደነገገ ወዲህ፤ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ችላ እንዳሉት ቆይተዋል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዙ ሥፍራ ነብያት ሕዝቡ ንስሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ሲያስጠነቅቁና ሲገስፁ ነበር። እስራኤላውያን ግን ሕጉ ከተሰጣቸው በኋላ፤ ወዲያውኑ አሮንን የሚያመልኩትን የወርቅ ጥጃ እንዲሠራላቸው ይለምኑታል (ኦሪት ዘጸአት 32:4)። ወደ ተስፋይቱ ሀገር በመሄድ ላይ ሳሉም፤ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ውስጥ ፊታቸውን ከእግዚአብሔር አዙረው የሞዓባዊያኑን አምላክ በዓልን ያመልኩ ነበር (ኦሪት ዘኁልቁ 25:1-3)። ንጉሥ አክዓብም ጣኦት ማምለክ ጀምሯል (መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 16:29-33)። እነዚህ ጥቂት ምሳሌዎች እስራኤላውያን እንዴት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመጠበቅ እንዳቃታቸውና ከሱ ጋር ኅብረታቸውን ማጽናት እንዳቃታቸው የሚያሳዩ ናቸው። እግዚአብሔር በነቢዩ አሞፅ በኩል ለእስራኤል «ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ ተጸይፌዋለሁ፤ የተቀደሰውም ጉባኤአችሁ ደስ አያሰኘኝም። ... ነገር ግን ፍርድ እንደ ወንዝ ውኃ፥ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ውኃ ይፈስሳል» ብሎ ተናግሯል፤ (አሞፅ 5:21-24)።

እስራኤላውያን መሥዋዕት ያቀርቡና ክብረ በዓላቱን ይጠብቁ ነበር፤ ነገር ግን ልባቸውና አስተሳሰባቸው ትክክለኛ አልነበረም። እግዚአብሔርም ሥርዓታችሁን ሁሉ ተጸይፌዋለሁ ይላቸዋል። ንስሐ ከመግባት ይልቅ አይሁዳውያን አምልኮአችሁ በቂ

አይደለም ወይም ልክ አይደላችሁም ብሎ በሚነግ ሰው ላይ እርምጃ ይወስዱ ነበር። የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት የእስራኤል ወገኖች ስለሆኑ በጣም ይመኩና ይኮሩ ነበር።

ጥያቄ 7፦ እግዚአብሔር ለአምልኮህ ምን ዓይነት ፍርድ የሚሰጥ ይመስልሃል? ይህን ዓይነቱ ፍርድ በእራስህ ወይም በሌሎች ቤተክርስቲያን ላይ የሚሰጥ ይመስልሃል? አብራራው።

ጥያቄ 8፦ ሀ) ቤተ ክርስቲያን መሄድ፣ በመዘምራን ውስጥ ገብቶ መዘመርና በአንድ ክፍል ውስጥ ትምህርት ማስተማር በሕግ የተደገፉ ልማዶች ሊሆኑ ይችላሉን?

ለ) ልብህን መርምር፣ አገልግሎትህ በሙሉ ባዶ ልማድ ሆኗል ወይስ እግዚአብሔርን የምታመልከው እሱን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ነው?

እስጢፋኖስ ግን እውነተኛ አምልኮ የሚጀምረው ከልብ እንደሆነ ተገንዝቧል። የሚጀመረው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ከተደረገ በኋላ ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ልማዶች በሙሉ ከልብ የመነጩ ካልሆነ ምንም ጥቅም የላቸውም። እስጢፋኖስ ከኢየሱስ መምጣት ጋር ነገሮች በሙሉ በታላቅ ሁኔታ እንደተለወጡ ተገንዝበዋል። እግዚአብሔር ዕቅድ ያወጣው ለእስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ሕዝቦችም በሙሉ ነው። አምልኮ የሚካሄደው በልብ ውስጥ ነው እንጂ፣ በቤተመቅደስ ወይም በእስራኤል አገር ውስጥ አይደለም። እስጢፋኖስ እውነቱን መናገሩ ግጭት ወይም ስደት እንደሚያስከትልበትም ያውቃል። ነገር ግን ዝም አልልም ብሎ ወሰነ፣ ለእግዚአብሔር መሠከረ።

ምንም እንኳ እስጢፋኖስን ቢከራከሩትም የነፃ ወጪዎቹ ክርክር የእስጢፋኖስን እውቀት ወይም ይናገረው የነበረውን መንፈስ ሊበግረው አልቻለም። ስለዚህም ሕዝቡን ቀስቅሰው እስጢፋኖስን ካስያዙ በኋላ፣ ሸንጎው ፊት ያቀርቡታል። የሐሰት ምሥክሮችን በማቅረብ እስጢፋኖስ ሕጉንና ቤተመቅደስን ተቃውሟል ብለው ይከሱታል።

ለአይሁዳውያን ከፍተኛው ፍርድ ቤት የነበረው ይህ ሸንጎ ነው። የተመሠረተውም በሊቀ ካህኑ፥ በሽማግሌዎችና በሕግ አስተማሪዎች ነው። ምንም እንኳ ግዙፍ ኃይል ቢኖራቸውም፣ በሮማውያን ቁጥጥር ሥር ስለነበሩ በማንም ሰው ላይ የሞት ፍርድ ሊፈርዱ አይችሉም ነበር።

በሐሰት ክስ መሐከል እንኳ ሆኖ እስጢፋኖስ በእርጋታ ውስጥ ነበር። ክሱ ከተነበበ በኋላ እስጢፋኖስ የሚሰጠውን መልስ ለመስማት ቀና ብለው ሲያዩት «እንደ መልአክ ፊት ሆኖ ፊቱን አዩት» (የሐዋርያት ሥራ 6፡15)። ዕድሉንም ሲያገኝ በግልጽ መከላከያውን ለሕዝቡ አቀረበ።

ጥያቄ 9፦ ሀ) በምሥክርነትህ ውስጥ ያለው ዕውቀትና መንፈስ ወንጌሉን የሚቃወሙትን አፋቸውን እንዴት እንደሚያስይዛቸው ሰፋ አድርገህ ግለጽ። ለ) ያለ አግባቡ ክስ ቢመሠረትብህ፣ ምላሽህ ምን ዓይነት ነበር

የሚሆነው? ሐ) ያለ አግባቡ ሲከሰስ እስጢፋኖስ ከወሰደው እርምጃ ልንማር የምንችለው ምንድነው?

ጥያቄ 10:- ሀ) እግዚአብሔርን ስናመልክ እኛና ሌሎች ሰዎች አንዳንዴ ያሉን የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ምን ምንድናቸው? ለ) አምልኮአችው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲኖረው ያሚያደርገው ነገር ምንድነው? መዝሙረ ዳዊት (51)፤ ዮሐንስ 4:24፤ እና ዕብራውያን 13:15 እንደ መልስ መስጫ አድርገህ ተመልከታቸው።

አስተውል፤ ኢየሱስ ፈሪሳውያንን የተቆጣቸው ሕጉን ስለጠበቁ አይደለም። የፈረደባቸው ዋና ዋና የሆኑት ጽድቅን ምሕረትንና ታማኝነትን ችላ ብለው በመተዋቸው ነው (ማር. 1:6)። አምልኮ ቤተክርስቲያን ሄደን የምናደርገው ነገር ብቻ ሳይሆን፤ እርሱ አኗኗራችንም ነው።

# ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 7:1-19

በትናንትናው ዕለት ኢየሱስን እንዲከተሉ እስጢፋኖስ የሰጠው ምሥክርነት ከአይሁዳውያንና ከሃይማኖት መሪዎች ተቃውሞ እንደመጣበት አይተናል። እስጢፋኖስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቀርቦ ለተመሠረተበት የሐሰት ክስ መከላከያ እንዲያቀርብ ይጠራል። የእስጢፋኖስ እውቀትና ይናገርበት የነበረው መንፈስ በሸንጎው የተሰበሰቡትን ሰዎች አሸብሯቸዋል፤ አናደ‌ቸዋልም። ሰዎቹ እስጢፋኖስ በቤተመቅደሱና በሕጉ ላይ የቅዋሜ ቃል ተናግሯል ብለው ነው የከሰሱት። ሆኖም ይህ እግዚአብሔርንና መልእክተኛውን ያለመቀበሉን ነገር በታሪክ ውስጥ ብዙ ጊዜ ደጋግመውታል።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ እምነታቸው ክርስቲያኖች ተገቢውን መስጠት እንዳለባቸው ያሳስባል፤ በሚቃወሟቸው ፊት እንኳ ቢቀርቡና ይህን አቋም መያዝ አለባቸው (1ጴጥ. 3:14-15 ተመልከት)። እስጢፋኖስም አይሁድ ሸንጎ ድረስ ቀርቦ ስለሰበከው ወንጌል ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል።

ጥያቄ 11:- አንድ ያለ አግባብ ክስ ሲመሠረትበት፤ ወንጌልን በተመለከተ መልስ ለመስጠት ዝግጁ የሚሆነው እንዴት ነው? አስተያየቶችን ስጥ።

ዛሬ እስጢፋኖስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ያቀረበውን መከላከያ እናጠናለን። እስጢፋኖስ ያለ አግባብ በቀረበበት ክስ ላይ ያቀረበው መከላከያ የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ የሚዳስስ ነበር። ዓላማው እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን ብቻ ሳይሆን ለሰዎች በሙሉ ግድ እንደሚሰጠው ለማሳየት ነው። እግዚአብሔር በእስራኤልም ውስጥ ከእስራኤልም ውጭ እንደሚሠራ ለማሳየትም ፈልጓል። በመጨረሻም፤ በኢየሱስ ላይ የወሰዱት እርምጃ ነቢያትን ይገድሉ የነበሩት አባቶቻቸውን ዓይነት ልማድ እንዲይዙ እንዳደረጋቸው ሊነግራቸው ይፈልጋል።

በብሉይ ኪዳን፤ እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ የጠራው ለተወሰነ ዓላማ ነው። መንግሥታት በሙሉ ከእግዚአብሔር እርቀው ጣኦትን ነበር የሚያመልኩት።

እግዚአብሔርም የሰጣቸውን የምሥክርነት ሥራ አቫፈረኝ ብለው ትተውታል (ሮሜ 1፡18-25)። ስለዚህም እግዚአብሔር አንድ አብርሃምን ጠራ፤ እሱና ሕዝቡ በመንግሥታቱ መካከል ቆመው ምስክሮቹ እንዲሆኑ ነገረው። አይሁዳውያንም ሁሌ በኩራት አብርሃምና ዘሩ የእነርሱ ቀደምት አባቶች እንደሆኑ ይናገራሉ። ነገር ግን ለሌሎች መንግሥታት ምሥክር መሆናቸውን ትተው፤ ትዕቢታቸው ከእግዚአብሔር ለያቸው እሱንም እንዳያዳምጡና እንዳይታዘዙ አደረጋቸው።

ጥያቄ 12፡- በሥራቸው ወይም የአንድ ጎሳ አባላት በመሆናቸው ተገልለው የሚታዩ ሰዎችን ታውቃለህን? ስማቸውን ጥቀስና ለምን ሕዝቡ በእነርሱ ላይ ጥላቻ እንዳደረበት ግለጽ።

ጥያቄ 13፡- ሀ) እግዚአብሔር ዛሬ ክርስቲያኖችን የጠራው ለምንድነው? ለ) ይህ ከአብርሃም ጥሪ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) በዘርህ ወይም በጎሳህ ላይ ያለህ መመካት በክርስቶስ ምስክርነትህ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

የሐዋርያት ሥራ 7፡1-19 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 14፡- ሀ) እስጢፋኖስ አቤቱታውን ሲያቀርብ «ወንድሞችና አባቶች ብሎ የተናገረው ለምንድነው? ለ) አብርሃም ጊዜውን በሙሉ በእስራኤል ውስጥ ነበር ወይ የኖረው? እግዚአብሔርስ ወዴት እንዲሄድ ነው የጠራው? ሐ) እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳን ምንድነው? መ) ለምንድነው ዮሴፍ ወደ ግብፅ የወረደው? ሠ) እግዚአብሔር በግብፅ ውስጥ በዮሴፍ የተጠቀመው እንዴት ነው? ረ) እስጢፋኖስ እግዚአብሔር የአይሁድ ቀደምት አባቶቻችን ከአገር ውጭ አስወጥቶ ነው ያስጨነቃቸው ብሎ የጠቀሰው ለምንድነው?

እንደምታስታውሰው በትናንትናው ዕለት እስጢፋኖስ የቀረበበት ክስ «በተቀደሰው ሥፍራ (በቤተመቅደሱ) በሕግም ላይ የስድብን ነገር ከመናገር አይተውም» የሚል ነበር። በመከላከያውም እስጢፋኖስ ለዚህ ክስ ምላሹን የሰጠው እግዚአብሔር በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ያደረገውን ነገር በመጥቀስ ነበር። በመከላከያው እስጢፋኖስ የአይሁድ ታሪክ ከሚጀምርበት ከመሶጴታምያ ይነሣና ሕጉ ለእስራኤላውያን የተሰጠበት ምድረ በዳ ላይ ያቆማል።

አይሁዶች፥ በአራት ነገሮች ትልቅ ኩራት ይሰማቸው ነበር።

1. እግዚአብሔር ይኖርና ይሠራ የነበረው በእስራኤል ውስጥ ብቻ እንደሆነና የአሕዛብ ዕጣ ፈንታ ፍርድ እንደሆነ ነበር የሚገምቱት። እስጢፋኖስ ግን እግዚአብሔር ያለማቋረጥ ከፓለስታይን ምድር ውጭ እንዲሠራ ያሳያቸዋል።

2. ለየት እንዳሉ ሰዎች፤ እግዚአብሔር ሥራውን ይሠራ የነበረው በአይሁዳውያን ብቻ እንደሆነ ይገምቱ ነበር። ሆኖም እስጢፋኖስ እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ዕቅድ እንዳለው ያሳያቸዋል።

3. አይሁዶች እግዚአብሔር ሕጉን ስለሰጣቸውና እያዳንዷን ጥቃቅን ሕግጋት የምትናገረውን ነገር በመጠበቃቸው ይኮሩ ነበር። እስጢፋኖስ ሕጉ እንኳ በእስራኤል ውጪ እንደተሰጠ ያሳያል።

4. በቤተመቅደሳቸውና በአምልኳቸው በጣም ይኮሩ ነበር፤ እስጢፋኖስ ግን የመገናኛው ድንኳን የተሰጣቸው እስራኤል ሳይገቡ ገና በምድረ በዳ ሳሉ እንደነበርና እግዚአብሔር በአንድ በተሠራ ሕንፃ ውስጥ ብቻ ሊኖር እንደማይችል ያሳስባቸዋል።

እስጢፋኖስ ተቃውሞ የደረሰበት ሄለናዊው ምኩራብ ውስጥ ይገኙ በነበሩ ሰዎች ነው። ለሸንጎው ግን «ወንድሞችና አባቶች» ብሎ ንግግሩን የከፈተው አይሁድ በመሆኑ ነው። እንደምታስታውሰው፥ ሄሌናውያን ከእስራኤል ውጭ ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን ናቸው፤ የግሪክንም ባህል ተምረዋል።

እስጢፋኖስ በመከላከያው ትልቅ ትኩረት የሰጠው፤ ከእግዚአብሔር፥ ከእስራኤል ሕዝብና ምድር ውጭ እንደሠራ ማሳመኑ ላይ ነው። የዓለም ሁሉ አምላክ ነው እንጂ የእስራኤል ብቻ አይደለም። የአይሁድ ታሪክ እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ስለሠራው ሥራ ጉልህ ማስረጃ ነው።

አይሁዳውያን በምድራቸው በጣም ይመኩ ስለነበር እስጢፋኖስ የቀድሞው አባቶቻቸው ሁሌ በእስራኤል እንዳልኖሩ ሲያሳስባቸው ይቃወሙታል። እስጢፋኖስ የታሪክ ክለሳውን የጀመረው ከአብርሃም ነው። ንግግሩንም በሚከተለው መልክ አጠር አድርገን ልናየው እንችላለን።

1. የአይሁድ አባት የሆነው የአብርሃም ታሪክ (ሐዋ. 7፡1-8)፡- አብርሃም፤ የተከበረው የአይሁድ አባት ነው። ሆኖም እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራው በመስጴጦምያ ሳለ ነው እንጂ ከነዓን ከገባ በኋላ አልነበረም። በመስጴጦምያ ሳለ እግዚአብሔር ሕዝቡንና ወገኑን ትቶ እንዲወጣ ጠራው። በመጀመሪያ ግን አብርሃም ታዛዥነቱን ለእግዚአብሔር ጥሪ ያሳየው እስከ ሃራን ድረስ በመሄድ ነበር። አባቱ ከሞተና እንደገና ሃራንን እንዲለቅ እግዚአብሔር ከጠራው በኋላ ነው፤ እሁን ከጊዜ በኋላ የእስራኤል ምድር ወደሆነችው ወደ ከነዓን የሄደው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ምድሪቱን ቃል የገባላቸው ለአብርሃምና ለዘሩ ቢሆንም፥ አብርሃም ቃል ኪዳኑን በዘመኑ አላገኘም። እሱ የነበረችው፤ ሚስቱ ሳራ ስትሞት ለመቃብር ብሎ የገዛት በኬብሮን የምትገኘው ትንሽ ቦታ ብቻ ናት (ዘፍት. 23፡17-18)። ልጁ ይስሐቅና የልጅ ልጁ ያዕቆብ ይኖሩ እንደነበረው፤ አብርሃም ይኖር የነበረው በድንኳን ውስጥ ነው። እንዲያውም እሱን የሚተካ ልጅ ከመስጠቱ በፊት እግዚአብሔር «ዘሮችህ በባዕድ አገር ስደተኞች ይሆናሉ፤ እዚያም በባርነትና በጭቆና ለአራት መቶ ዓመት ይኖራሉ» ብሎ ተናግሮት ነበር፤ (ዘፍጥ. 15፡12)። በዚህም፤ እግዚአብሔር ለአራት መቶ ዓመት ያህል በግብፅ አገር እስራኤላውያን ባሮች ሆነው የተገዙበትን ጊዜ መተንበዩ ነበር።

አብርሃም አይሁዳውያን የኛ ነው ብለው የሚፎከሩበት ምድር አግኚ ሆኖ ቀረ። የመገረዙ ቃል ኪዳን፤ አይሁዳውያን ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዳላቸው የሚያሳየው ውጫዊው ምልክት፤ የተፈጸመው እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳኑን ካደረገ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው። የግርዘቱን ምልክት እስከሰጠው ጊዜ ድረስ፤ አብርሃም አሕዛብ ነበር ልንል እንችላለን።

2. የአብርሃም ልጆች ታሪክ (ሐዋ. 7፡9-16)። እስጢፋኖስ ስለ አብርሃም ልጆች በመጥቀስ መከላከያውን ማቅረቡን ይቀጥላል። ይስሐቅ የአብርሃም ልጅ ነበር፤ የእሱ ልጅ ደግሞ ያዕቆብ ነበር፤ ያዕቆብ ደግሞ የአሥራሁለቱ ልጆች አባት ነው። እነዚህ አሥራ ሁለት ልጆች በእስራኤል ውስጥ ያሉት የአሥራሁለቱ ነገዶች መሥራቾች ናቸው። አሥራ አንዱ ልጆች በቅናት ተነሣሥተው ዮሴፍን ለባርነት ሸጡት፤ እሱም ከእስራኤል ምድር ውጭ ወደምትገኘው ወደ ግብፅ ተወሰደ። ዮሴፍን ያሰለጠኑና ያከሩት ግብፃውያን ነበሩ። በሰባቱ ዓመት የረሃብ ጊዜ አይሁዳውያንና ግብፃውያንን ከረሃብ ያዳነ ደግሞ ነበር። ዮሴፍ 75 የሚያኽሉትን አይሁዳውያን ወገኖቹን በግብፅ እንዲኖሩ አመጣቸው። በግብፅ ምድር ሞቱ፤ አስከሬናቸው ግን እንደገና ወደ ከነዓን ተወስዶ ተቀበረ።

3. የእስራኤላውያን ጭቆናና ነፃ መውጣት የሚገልፀው ታሪክ (ሐዋ. 7፡17-36)። ከብዙ ዓመታት በኋላ፤ ይላል እስጢፋኖስ፤ የእስራኤላውያን ቁጥር ወደ ታላቅ ሕዝብ አደጉ። ሆኖም፥ እስከዚሁ ጊዜ ድረስ በግብፅ ነበር የሚኖሩት። አሁን ባሮች ነበሩ። ስለ ዮሴፍ ምንም የማያውቅ አዲስ ንጉሥ፤ ሕዝቡን እየጨቆነ አዲስ የተወለዱትን ወንድ ሕፃናቶቻቸውን እንዲገድሉም አስገደዳቸው (ዘጸ. 1፡6-16)። ያለምንም ጥርጥር አንዳንዶቹ እስጢፋኖስን ይሰሙ የነበሩት ሄለናውያን የመጡት ከግብፅ ነው።

በነገው ዕለት የዚህን ክፍል ጥናታችንን የሙሴን የሕይወት ታሪክ በማጥናት እንቀጥላለን።

እግዚአብሔር፤ በአንድ አገር ውስጥ ብቻ የተወሰነ ትንሽ አምላክ አይደለም። እሱ የእስራኤል ወይም የምዕራቡ ዓለም ብቻ አምላክም አይደለም። እሱ የመላው ዓለም አምላክ ነው። እሱ ብቻውን ነው ዓለምን የፈጠረው። የነገሥታት ንጉሥና የጌቶችም ጌታ እሱ ነው። ለተወሰኑ ሰዎች ወይም ለግለሰቦች ሳይሆን ለሰዎች ሁሉ ታላቅ ዓላማ አለው። ልክ ባቢሎናውያን ገብተው እስራኤልን ሲወሩ ሕዝቡን በያለበት ሁሉ ይገኝ እንደነበረው በሌሎች ምድር የነበሩትንም ሕዝቦቹን እንደዚሁ ይገኝላቸው ነበር። እግዚአብሔር በእስራኤል ድንበር ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የቤተመቅደሱ የአምልኮ ሥርዓት ከመመሥረቱ በፊት፤ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቀጣና ይገስጽ የነበረው በሌሎች ምድሮች ውስጥ ነበር። እስጢፋኖስ እግዚአብሔር በአንድ አገር ብቻ እንዳልተወሰነ ለማስረዳት ነው የተፈለገው። እግዚአብሔር አብርሃምን ከመስጴጦምያ ምድር በጠራው ጊዜ እንኳ ስለ ስሙ ሕዝቦችን የጠራው ከአሕዛብ መካከል ነው።

ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ወይም በሕዝባችን ላይ ተመክተን፣ እግዚአብሔር የሚሠራው በኛ ውስጥ ብቻ ነው ብለን እናስብ ይሆናል። ሐዋርያቱና እስጢፋኖስ ግን፣ እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች በኩል እንደሚሠራና የጌታን ስም የሚጠሩም ሁሉ እንደሚድኑ ተገንዝበዋል።

ጥያቄ 15፡- ሀ) እራሳቸውን ከሌላው ይበልጥ ከፍ የሚያደርጉ ጎሳዎችን ወይም ቤተ ክርስቲያኖችን በኢትዮጵያ ውስጥ አይተህ ታውቃለህ? ለ) እግዚአብሔር እንደዚህ ዓይነቱን አመለካከት የሚያየው እንዴት ነው? ሐ) የአንድ ክርስቲያን ሐላፊነት ለአንድ ሕዝብ ወይም ጎሳ ሳይሆን ለዓለም ሁሉ ምንድነው?

ኢየሱስ በሐዋርያት ሥራ 1፡8 ላይ የሰጠውን ትዕዛዝ ታስታውሳለህ? ምስክሮች መሆን ያለብን ለዓለም ሁሉ ነው እንጂ በአካባቢያችን ላሉ ሰዎች ብቻ አይደለም። ሁሉ ቤተክርስቲያኖች ከተሞቻቸውን፥ ወገኖቻቸውን፣ አገራቸውንና መላውን ዓለም በወንጌል እንዴት ማዳረስ እንደሚችሉ ለማወቅ ሊጸልዩና ሊያስቡበት ይገባል። ቤተክርስቲያንህ የኢየሱስን ትዕዛዝ እየጠበቀች ነውን?

## ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 7፡20-36

እንደተማርነው፣ እስጢፋኖስ የተከሰሰው በሁለት ነገር ነው፣ እነዚህም፡- 1. ሕጉን ተቃውሟል 2. ቤተመቅደስን ተቃውሟል የሚሉ ናቸው። ትናንትና እስጢፋኖስ ታሪክን በመጥቀስ እንዴት አድርጎ የእግዚአብሔር ሥራ በአንድ ምድር ወይም ሕዝብ መሐል ብቻ እንዳልተወሰነ ሲያስረዳ አይተናል። እግዚአብሔር ከእስራኤል ውጪ መሥራቱን ለማሳየት፣ ሦስት ዋና ዋና የታሪክ ክንዋኔዎችን ይጠቅሳል። አንደኛ፣ የአብርሃምን የሕይወት ታሪክ ተመለከተ፣ ሁለተኛ የጥንቶቹን ፓትሪያርኮች ተመለከተ፣ ሦስተኛ ደግሞ የእስራኤል ሕዝብ በግብፅ ባርነት እንዴት እንደገባና እንዴት ነፃ እንደወጣ ተመለከተ። የእስራኤል ታሪክ፣ በተቀደሰችው ምድር እንደ አንድ ሕዝብ ሆኖ መታየት የጀመረው እግዚአሔር ለአብርሃም የተስፋውን ቃል ከሰጠ ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው። አይሁዶች ይህን ሊያስቡት አይፈልጉም፣ ምክንያቱም ምድራቸውን እስራኤልን እግዚአብሔር እንደሚኖርባት ምድር አድርገው በኩራት ይመለከቷት ነበርና ነው።

በኢየሩሳሌም ምኩራብ ውስጥ የነበሩት ሰዎች በእስጢፋኖስና በመልእክቱ አምፀው የተነሡት፣ እግዚአብሔር ለሌሎች ሰዎችና ሕዝቦች ዓላማ አለው በማለቱ ነው። የእስጢፋኖስ መልእክት ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው ወደ አብ የሚወስደውን ጥርጊያ መንገድ አዘጋጀ የሚል ነበር። በመንፈስ ቅዱስም ምክንያት በየትኛው ሥፍራ ሆነው እግዚአብሔርን በመንፈስ ሊያመልኩት ይችላሉ፤ (ዮሐ. 4፡23-24 ተመልከት)። «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለኛ ተናገረን» (ዕብር. 1፡1-2)። ከቤተመቅደሱ አምልኮ ጋር

ያስተዋወቀን ወይም አምልኮውን የሰጠን እግዚአብሔር ነው፤ አሁን ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተሻለ መንገድ ከፍቶልናል።

ጥያቄ 16፡- ሀ) በኢየሱስ በኩል ያለው የእግዚአብሔር መገናኛ ከብሉይ ኪዳኑ የአምልኮ ሥርዓት የሚሻሻለው በምን በምንድነው? ለ) ብዙ ሰዎች የአምልኮአቸው ሥርዓት ላይ ለውጥ ለማድረግ ወይም በሚያደርጓቸው አንዳንድ ነገሮች ላይ ለውጥን ለማድረግ የሚቃወሙት ለምንድነው?

ዛሬ፤ እስጢፋኖስ ሰፋ አድርጎ ስለ እስራኤል ልጆች በግብፅ በባርነት መያዝና እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መሥራቱን ስላተተው የመከላከያው ታሪክ እናጠናለን።

የሐዋርያት ሥራ 7፡20-36 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 17፡- ሀ) ሙሴን ወስዳ እንደ ልጇ ያሳደገችው ማን ናት? ለ) ሙሴ ወደ ምድያም የኮበለለው ለምንድነው? ሐ) በምድያም ምድረ በዳ ለ 40 ዓመት ከቆየ በኋላ፤ እግዚአብሔር ከሙሴ የተገናኘው እንዴት ነው?

አይሁዳውያን እንዴት መኖር እንደሚገባቸው የሚገልጹላቸው ሦስት ቁልፍ የሆኑ መሪዎች ነበሯቸው። አንደኛ፤ የአይሁድ ሕዝብ አባትና የእግዚአብሔር ወዳጅ የነበረው አብርሃም ነበረ። ሁለተኛ፤ እስራኤልን ከባርነት መርቶ ያወጣና ሕጉን የሰጠው ሙሴ ነበር። ሦስተኛ ደግሞ፤ የመሢሑ የዘር ግንድ የሆነው ታላቁ ንጉሥ ዳዊት ነው። እግዚአብሔር አብርሃም ከተስፋይቱ ምድር ውጪ ሳለ፤ እንዴት አድርጎ አብሮት እንደሠራ እስጢፋኖስ ሲገልጽ አይተናል። አሁን ደግሞ በመቀጠል በጭራሽ ወደ ተስፋይቱ ምድር ገብቶ የማያውቀውን ሙሴን እንዴት አድርጎ እንደጠራውና እንደተጠቀመበት እናያለን።

እስራኤላውያን ለብዙ ዓመታት በግብፅ ከኖሩ በኋላ፤ ስለ ዮሴፍ ምንም የማያውቅ ፈርዖን አዲስ ገዢ ሆነ፤ እሱም የአይሁዶችን በጣም ይጨቁናቸው ነበር። ሙሴም የተወለደው በዚሁ ጊዜ ነበር። የፈርዖን ሴት ልጅ ልጅ እንደሆነ ተደርጎ አደገ፤ ለየት ያለውንም ትምህርት እንዲማር ሆነ። የጥንቷ ግብፅ ታላላቅ ዕውቀቶችን በሙሉ ተማረ። አንዳንድ ምሁራን የግብፅን በትረ መንግሥት ቀጥሎ የሚወስደው ሙሴ ነው ብለው ያስቡ ነበር። አኳኋኑ እንደ ግብፃዊ ስለነበር፤ አይሁዳውያኑ እሱን ከግብፅ ነፃ እንደሚያወጣቸውና መሪያቸውን አድርጎ መቀበሉ በጣም አዳግቷቸው ነበር። ምንም እንኳ በኋላ ታላቅ የአይሁድ መሪ ቢሆንም፤ የእስራኤል ሕዝብ በመጀመሪያ አልተቀበለውም ነበር። ሙሴ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰማ፤ ግብፃዊ ሆኖ ከመኖርም፤ ባሮች ከነበሩት ሕዝቦቹ ጋር አንድ ሆኖ መቆጠርን መረጠ።

ጥያቄ 18፡- ሀ) ይህ ለሙሴ ከባድ ውሳኔ የነበረው ለምንድነው? ለ) እግዚአብሔርን መከተል ከፈለግን፤ እኛ ማድረግ ከሚገባን ምርጫ ጋር ይህ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

አንድ ቀን፤ በአንድ ግብፃዊ ይደበደብ የነበረን እስራኤላዊ አግዛለሁ ብሎ ሳለ ሙሴ ግብፃዊውን ይገድለዋል። ሙሴ፤ ሕዝቡ እኔን ከባርነት ያድነናል ብለው ያስቡኛል ይሆናል ብሎ ይገምት ነበር። እስራኤላውያን ግን አስተሳሰቡ አልገባቸውም ነበር።

በዚህም ምክንያት ወደ በኋላ ሁለት እስራኤላውያን ሲጣሉ አይቶ ሊገላግላቸው ቢሞክር፥ በእኛ ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው? ብለው ጠየቁት። ሙሴም፤ ለግብፃዊያኑ መሪዎች አንድ ግብፃዊ ገድሏል ብለው ይናገሩብኝ ይሆናል ብሎ ፈራ። በዚህም ምክንያት ወደ ምድያም ኮበለለ። ሙሴ፤ እግዚአብሔር እሱንና ሕዝቡን ከማዘጋጀቱ በፊት በራሱ ኃይል የእስራኤልን ሕዝብ ሊመራ ሞከረ፡፡ እንደ ብዙዎቻችን፤ እግዚአብሔር ባቀደው ጊዜ እንዲሠራ ነገሮችን ለእርሱ ከመተው ፈንታ በራሱ ኃይል እግዚአብሔርን ሊያገለግል ሙከራ አደረገ።

ጥያቄ 19:- ሀ) በራሳችን ኃይል የእግዚአብሔርን ሥራ ልንሠራባቸው የምንችልባቸውን አንዳንድ መንገዶች ግለጽ። ለ) እግዚአብሔር ከመዘጋጀቱ በፊት በምን ዓይነት መንገድ አንዳንድ ነገሮችን ልንሠራቸው እንደምንችል ግለጽ።

እስካሁን ድረስ፤ ለሕዝቦቹ ለእስራኤላውያን ሲል እግዚአብሔር የሠራውን ሥራ ተመልክተናል፤ ይህ ግን በፓለስታይን ምድር ውስጥ አይደለም። እንዲያውም፥ ይሠራ የነበረው በግብፅ ውስጥ ነው። ከዚያም ሙሴ በምድያም ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር ሙሴን ለመሪነት ለማዘጋጀት በሕይወት የዝግጅት ሥራ ይሠራ ነበር። ከ 40 ዓመት በኋላ፤ እግዚአብሔር ለሙሴ በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ተገለጠለትና የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ እንዲያወጣ ጠራው። በመጀመሪያው በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ከመደነቁ፤ ሙሴ በደንብ ለማየት ወደ ቁጥቋጦው ይጠጋል። ነገር ግን እግዚአብሔር እራሱን «የአባቶችህ የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ» ብሎ ሲያስተዋውቀው በፍርሃት ተንቀጠቀጠ፤ ሊያየውም አልደፈረም። ከዚያም ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት እንዲገልጽ እግዚአብሔር ሙሴን ጫማህን አውልቅ ይለውና፤ በግብፅ ስላሉት እስራኤላውያን ተቆርቋሪነቱን ይገልፅለታል። ሙሴ የእስራኤላውያኑ ገዢና ታዳጊ ሆኖ በእግዚአብሔር ተላከ። በመጀመሪያ ሙሴ ሊረዳቸው ቢሞክር፤ ፍጻሜው ግድያና ግዞት ሆነ። በሁለተኛው ጊዜ ግን በእግዚአብሔር ጥሪና እርዳታ፤ ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ሊያወጣና ለተቀሩት 40 ዓመታት ድንቅና ተአምራት ሊሠራ ችሏል።

ጥያቄ 20:- ሀ) አንድ ሰው ተቸግሮ አይተህ ልትረዳው ሞክረህ ታውቃለህ? ለ) ሐሳብህ ተቃናልህ ወይስ ጣልቃ በመግባትህ ሰዎች ደስ አላላቸውም? ሐ) ስለአንድ ሁኔታ እግዚአብሔርን ጠይቀህ፤ እግዚአብሔርም በተለየ መልክ በአንተ አማካኝነት በሌላ ሰው ሕይወት ውስጥ ለውጥ እንዲኖር አድርጎ ያውቃል? አብራራው።

ምንም በእስጢፋኖስ ጊዜ የነበሩት አይሁዳውያን ሙሴን በጣም ቢያከብሩትም ሕይወቱ ሙሉውን ግን የእስራኤልን ሕዝብ ተቃውሞ እንደተጋፈጠ ነው የኖረው። ልክ በአብዛኞዎቻችን እንዳለ ሁሉ እግዚአብሔር በመካከላቸው መሥራቱን አላስተዋሉም። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለውጥ ሊያስገኝላቸው ሲጥር ከግብፅ ባርነት ሊያወጣቸው ቢሞክር እንኳ፤ በሱ ላይ አምፀዋል። በነገው ትምህርታችን ይህን በሥፋት እናየዋለን።

ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር መንገድና ጊዜ እኛ የምንፈልገው ዓይነት አይደለም። ለእግዚአብሔር ሊሠራ የሚችልና የእግዚአብሔርን ጊዜ ጠብቆ ወደፊት ሊራመድ የሚችል ሰው በመንፈስ የሚመራ መሆን አለበት። ሙሴ ለ 40 ዓመት በምድረ በዳ እግዚአብሔር እንድን ሥራ የሚያከብረው በእርሱ መንገድና በእርሱ ጊዜ ሲሠራ ብቻ መሆኑን መማር ነበረበት። እኛም ብንሆን እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ለእግዚአብሔር ስንሠራ ይህንን መረዳት አለብን።

# አራተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 7:37-60

እስጢፋኖስ እንዴት አድርጎ የእስራኤልን ታሪክ በአጭሩ በማስቀመጥና ሦስት ነገሮችን በመቀስቀስ ከሳሾቹን እንዳሳመነ አይተናል። 1. ይህ በሀገርና በባህል የውሸት መመካት፤ ለእግዚአብሔር ምሥክሮች እንዳይሆኑ እንቅፋት እንደሆነባቸው 2. አምልኳቸው ባዶና ውጫዊ መልክ ብቻ የያዘ እንደሆነ 3. እስጢፋኖስ ይህን ከገለጸ በኋላ የእግዚአብሔር ክብር በቤተመቅደስ ውስጥ ብቻ ተፅዕኖ እንደማይቀር ይገልጽላቸዋል። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በተለያዩ በታዎችና አኳኋኖች ተገናኝቷል። ዛሬ፤ የእስጢፋኖስ መልእክት መደምደሚያ እናያለን።

ጥያቄ 21:- ሀ) እነዚህ ሦስት ነገሮች በክርስቲያን ውስጥ እንዴት ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ አብራራ። ለ) እግዚአብሔር እንደሚፈልገው ፀንተን ቆመን እንድንመሠክርለትና እንድናመልከው ምን ማድረግ አለብን?

ጥያቄ 22:- የአይሁድን የሃይማኖት መሪዎች የወንጌሉን መልእክት እንዲቃወሙ ያደረጋቸው ነገር ምን ይመስልሃል?

የእስራኤላውያን ታሪክ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ሳይታዘዙ የቀሩበት ታሪክ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። በታሪካቸው ውስጥ፤ በምድረ በዳ ህጉ ከተሰጣቸው ጊዜ አንሥቶ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተገዢ አልሆኑም። በምድረበዳ የተንከራተቱበትንና በተስፋይቱ ምድር የሠፈሩበትን ጊዜ ስንከታተል፤ እስራኤላውያን እራሳቸውን ጣኦት ያመልኩ ከነበሩ ጎረቤት አገሮች እንደለዩ እንመለከታለን። የእግዚአብሔር ሕዝቦች በመሆናቸው በጣም ይኮሩ ነበር፤ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ለመኖር ፈቃደኞች አልነበሩም።

ጥያቄ 23:- ሀ) ዛሬ ያለውን የክርስቲያኖች ሕይወት ከእስራኤላውያን እንዴት አድርገን ነው የምናነፃፅረው? ለ) እንደ እግዚአብሔር ልጅ በተቀደሰ ሕይወት ውስጥ ለመኖር ትጥራለህ? ከሆነስ፤ ይህ የሚታየው እንዴት ነው?

የሐዋርያት ሥራ 7:37-60 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 24:- ሀ) ሙሴ በሐዋርያት ሥራ 7:37-38 ላይ ስለ ማን ነው የሚናገረው? ለ) ሙሴ ለእስራኤላውያን ለማስተላለፍ የተቀበለው «ሕያው ቃል» የትኛው ነው? (ዘዳግም 32:45-47 ተመልከት)። ሐ) እስራኤላውያን የፈጸሟቸው ያለመታዘዝ ባህሪዎች ምን ምን ነበሩ? መ) እግዚአብሔርስ

እስራኤላውያንን የት እልካቸዋለሁ ወይም እሰዳቸዋለሁ ነው ያለው? ሠ) ከእስጢፋኖስ መልእክት የትኛው ምፍራ ላይ ሲደርሱ ነው አይሁዳውያኑ እሱን በመቃወም የተነሡት?

እስካሁን ባለው የእስጢፋኖስ መልእክት ጥናታችን ለፍርድ ሸንጎው ከአብርሃም ሕይወት፥ ከአብርሃም ልጆች ታሪክና እስራኤላውያን በግዞት በነበሩበት ወቅት ከነበረው ታሪክ ላይ በመጥቀስ፤ ብዙው የአይሁድ ታሪክ የተፈጸመው ከፓለስታይን ምድር ውጪ እንደሆነ አረጋግጧል። በዛሬው ትምህርት ደግሞ፤ እስጢፋኖስ የሚያተኩረው በምድረ በዳ የመንከራተቱ ጊዜ ከሚለው እንሥቶ ቤተመቅደሱ እስከተሠራበት ጊዜ በሚለው የእሥራኤል ታሪክ ላይ ነው።

እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ከባርነት ለማውጣት፤ በሙሴ በደንብ አድርጎ ነው የተጠቀመው። በሱ በኩል ብዙ ተአምራቶች ተሠርተዋል። ምንም እንኳ እንደ ታላቁ እስራኤላዊ ነቢይ ቢቆጠርም፥ ሙሴ ስለ ሌላ ነቢይ ትንቢት ይናገር ነበር፤ «አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል» (ዘዳ. 18፡16)። እስጢፋኖስ በሙሴ ትንቢት የተነገረለት ኢየሱስ ነው ማለቱ ነው። ነገር ግን እስራኤላውያን ኢየሱስንም ሙሴንም በአንድ መልክ ነው ያዩዋቸው፤ የሁለቱንም መሪነት አልተቀበሉትም።

እግዚአብሔር ከእስራኤል ውጪ መሥራቱን ለማረጋገጥ እስጢፋኖስ እነዚህን ሐሳቦች በማቅረብ ይቀጥላል።

4. የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ውስጥ ለሙሴ አንታዘዝም ብለው ተቃወሙ (ሐዋ. 7፡37-39)። እግዚአብሔር ከ 40 ዓመት በኋላ ሙሴን ከበረሃ የጠራው ሕዝቡ ነፃ የምታወጣን መሪያችን አንተ አይደለህም ብሎ ከወሰነበት በኋላ ነው። ከዚያም እግዚአብሔር ባሮች የነበሩትን ሕዝቦች ነፃ እንዲያወጣ ሙሴን ይልከዋል። እግዚአብሔርም ሕዝቡን የሚመራለት፤ እንደ ሙሴ የሠለጠነ መሪ ይፈልግ ነበር። ሆኖም፤ ሕዝቡ ሙሴን ተቃወመ፤ ግብፃውያንም ያመልኩት የነበረው ዓይነት አማልክት ፈለገ። የወርቅ ጥጃ አስመስለውም ጣኦት ሠሩ። እንደገና በዚህ ምፍራ እስራኤላውያን አይሁዳውያን ከመሆን ይልቅ ግብፃዊነቱ ላይ እንደሚያመዝኑ ያሳስባቸዋል።

5. ሕጉ የተሰጠው ከእስራኤል ውጭ፤ በሲና ተራራ ላይ ነበር (ሐዋ. 7፡35-43)። እስጢፋኖስ ተቃውሞታል ብለው ይሉት የነበረው በሲና ተራራ የተሰጠው ሕግ በምድራቸው በእስራኤል ውስጥ ሳይሆን በምድያም ምድረ በዳ ውስጥ ነበር የተሰጠው። እስጢፋኖስ ሕጉን «ሕያው ቃል» ብሎ ይጠራዋል፤ ምክንያቱም የተሰጠው በሕያው እግዚአብሔር ስለሆነና ይህም የእግዚአብሔር ቃል እርሱ ለሕዝቡ ያለውን ፈቃድ በመግለጹ ነው። ምንም እንኳ እስጢፋኖስ ሕጉን ተቃውሟል ብለው ቢከሱትም፥ እስራኤላውያን በታሪካቸው ሕጉን ለመቀበል አንዴም ቢሆን ፈቃደኞች አልነበሩም። የእግዚአብሔርን ሕግ ከተቀበሉ በኋላ፤ ወዲያውኑ ወደ ግብፅ ለመመለስ ፈለጉ። በሲና ተራራ ላይ ሳሉ እንኳ፤ አሮንን በወርቅ ተሠራ ጥጃ እንዲሠራላቸው ጠይቀውት ጥጃውን ሲያመልኩ ነበር።

ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር ሳይታዘዙ በመቅረታቸው እግዚአብሔር የሐሰት አማልክትን እንዲያመልኩ ፈቀደላቸው። እስጢፋኖስ የማያቋርጥ አመጸኝነታቸውን በማስረጃ ለማስደገፍ ሲል ከብሉይ ኪዳኑ ከአሞፅ ትንቢት ውስጥ ቀንጨብ አድርጎ ይገልጻል፤ (አሞፅ 5፡25-27)።

ጥያቄ 25፡- የቤተክርስቲያን ታሪክ በምን ዓይነት መንገድ ነው እንደ እስራኤላውያን ታሪክ ሕዝቡ ቅዱስ ከመሆን ይልቅ ኃጢአትን ለመሥራት የሚያዘነብለው?

በእስጢፋኖስ ላይ የተመሠረተው ሁለተኛው ክስ ቤተመቅደስን በተመለከተ ነው። እስጢፋኖስ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የምናመልክበትን አዲስ ጎዳና ከፍቶልናል ብሎ በማስተማሩ፤ በቤተመቅደስ ላይ ተናግሯል ብለው ከሰሱት። በሐዋርያት ሥራ 7፡44-50 ላይ፤ እስጢፋኖስ ቤተመቅደስን ተቃውሟል ለሚለው ክሱ፤ መከላከያ ያቀርባል።

6. መገናኛው ድንኳን የተተከለው በምድረ በዳ ውስጥ ነው እንጂ በእስራኤል አልነበረም (ሐዋ. 7፡44-47)። በሲና ተራራ በዚያ ምድረ በዳ ሳሉ ነው እግዚአብሔር መገናኛውን ድንኳን የሰጣቸው። የመጀመሪያው መገናኛ ድንኳን፤ የእግዚአብሔር ምድራዊ መኖሪያ ቦታ የነበረው፤ የተተከለው በምድረ በዳ ውስጥ ነው፤ በየሄዱበት እየተሸከሙት ይጓዙ ነበር። እስጢፋኖስ «የምሥክሩ ታቦት» ይለዋል፤ ምክንያቱም በመገናኛው ድንኳን የነበሩት ነገሮች የቃል ኪዳኑ ታቦትና አሥርቱትዕዛዛትየተጻፈበት ሁለቱ ፅላቶች ናቸው፤ እነዚህም «ምሥክር» የሚል ስያሜ ነበራቸው (ዘጸ. 25፡16-21)። በኋላ ላይም፤ መገናኛውን ድንኳን ይዘው ወደ ተስፋይቱ ምድር ገቡ። በኢያሱና በመሳፍንት ዘመን፤ የአምልኮ ሥፍራ ነበር። ዳዊት እንኳ እግዚአብሔር የሚያርፍበት ቋሚ የሆነ ቤተመቅደስ ለመሥራት የፈለገውን ሰውዬ ሊሠራ አልቻለም። የዳዊት ልጅ ሰሎሞን እስኪመጣ ድረስ ቤተመቅደስ አልተሠራም።

«እግዚአብሔር በቤተመቅደሱ ውስጥ ብቻ ነበር የሚገኘው?» ብለው አይሁዳውያን ጠይቀዋል። መልሱ ያለጥርጥር «አይደለም» ነው። እውነተኛው የእግዚአብሔር መኖሪያ ቦታ መንግሥተ ሰማያት ነው። እስጢፋኖስ ከሳሾቹን እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል የተናገረውን ነገር ያስታውሳቸዋል። «ሰማይ ዙፋኔ ነው፥ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ሥፍራ ምንድነው? እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና ... ይላል እግዚአብሔር» (ኢሳይያስ 66፡1-2)።

ጥያቄ 26፡-ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ለየት ባለ ሕንፃ ይኖራል ብለው የሚያምኑት በምን ዓይነት መንገድ ነው?

በአንድ በተወሰኑ ሰዎች የሚጠበቅ ቤተመቅደስ ውስጥ አልነበረም፤ እግዚአብሔር የሚኖረው። የሚያምረው ቤተመቅደሳቸው እንኳ ቢሆን እግዚአብሔርን ሊይዘው

አይችልም። ሁለተኛውን ክስ ቤተመቅደሱን በተመለከተ እስጢፋኖስ ያሸንፈው በጥበቡ ነው።

አይሁዶች በቤተመቅደሳቸው ላይ ያላቸው ኩራት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ከመሳብ ፈንታ ከሌሎች ሰዎችና አገሮች አለያይቷቸዋል። እራሳቸውን ከሁሉም በላይ እንደሆነ አድርገው ይመለከታሉ።

ጥያቄ 27:- ሀ) ዛሬ እግዚአብሔርን የምናገኝበት ብቸኛው ቦታ ቤተክርስቲያን ነው?
ለ) ዛሬ እግዚአብሔር የሚገኝባቸው ሌሎች ቦታዎች የት የት ናቸው?

ጥያቄ 28:- በሕንፃቸው በመመካታቸው የተነሣ፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረታቸው የተሰናከለባቸው አማኞችን ታውቃለህ?

እግዚአብሔር በሕንፃ ውስጥ ከመኖር ይልቅ፣ በሰዎች ልብ ውስጥ እንደሚኖር ያስተምረናል። ዋናው ቁም ነገሩ፣ የምንሰበሰብበት ሕንፃ ሳይሆን፣ ኢየሱስ የሚኖርበት የእያንዳንዳችን ልብ ነው (1ቆሮ. 3፡16-17፣ 6፡19)። ቅዱሱ አምላክ ይኖርበት ዘንድ፣ ልባችን ተገቢውን ያህል ንፁህ ነውን?

በሸንጎው የተሰበሰቡት ሰዎች ተናደዱ፣ የእስጢፋኖስ መከላከያ ያለ ክርክር ያስቀራቸው በሁሉም ነገር እንዲረቱ አደረጋቸው፣ ይህም እጅግ በጣም አናደዳቸው።

በመቀጠልም እስጢፋኖስ የከሰሱትን ሰዎች «እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ፥ እናንተ ሁል ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ፣ አባቶቻችሁ እንደተቃወሙት እናንተ ደግሞ ተቃወማችሁት» ብሎ ይናገራቸዋል (ሐዋ. 7፡51)። አይሁዳውያን ውጫዊ በሆነ ሥርዓትና ልማድ ታበዩ። በዚህም ምክንያት በታላቁ የተዋበው ቤተመቅደሳቸው በጣም ተመኩ። በመገረዛቸውም ተመኩ። እስጢፋኖስ ግን አንገተ ደንዳኖች በመሆናቸውና ኃጢአታቸውን ተናዘው ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ባለመፈለጋቸው ይወቅሳቸዋል። ያልተገረዘም ልብ ስላላቸው ይወቅሳቸዋል። ልክ በምድረ በዳ የነበሩት አባቶቻቸው ሙሴንና እግዚአብሔርን እንደተቃወሙ ሁሉ እነሱም በመሐከላቸው ይሠራ የነበረውን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ተቃወሙ። ነቢያትን ገደሉ፣ «ጻድቁንም» ኢየሱስ ክርስቶስን ገደሉ። ሕጉን ተቀበሉት፣ ነገር ግን አልጠበቁትም። ምንም እንኳ እንደ አባቶቻቸው ጊዜ በመላእክት በኩል ቢመጣ አልተቀበሉትም። አይሁዳውያን እግዚአብሔር በሲና ተራራ ህጉን በሰጠበት ወቅት በመጀመሪያ ለመላእክት እንደሰጠ እነሱም ለሙሴ እንደሰጡት ነው የሚያምኑት (ገላትያ. 19፣ ዕብራ. 2፡2)። ጥያቄ 29 በሕይወትህ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ኅብረት የሚያጠፉ፥ ቤተክርስቲያን እንዳትከታተል የሚያደርግህ ምሥክርነትህና ጸሎትህ ባዶ እንዲሆኑ የሚያደርግህ አመጸኝነት አለብህ?

እስጢፋኖስ፣ ጻድቁንና መሢሑን የገደላችሁ እናንተ ናችሁ ብሎ ከሳሾቹን ተጠያቂ ሲያደርጋቸው አይሁዶች ተናደዱ በእሱም ላይ ተነሡ። ይህንንም በማድረጋቸው እስጢፋኖስ የተናገራቸው እውነት እንደሆነ አሳይተዋል። ለብዙ ዓመታት እግዚአብሔርንና ሕግጋቱን መቃወማቸው ልባቸውን አደንድኖታል።

የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ካሁን ወዲህ ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ኅብረት የላቸውም። ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታዛዦች መሆን ሲገባቸው፣ ይህንን የአምልኮ ሥርዓት በመከተልና የተወሰኑ ሕግጋትን በመጠየቅ ለወጡት።

በእስጢፋኖስ ላይ በተነሡበት ወቅት እሱ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ አየ በዚህም ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር አየ፤ ኢየሱስንም በቀኝ በኩል ቆሞ አየው። ይህ መሪዎቹን የበለጠ አናደዳቸው፤ በድንጋይም ይወግሩት ዘንድ ጎትተው ከከተማ አወጡት። በድንጋይ እየወገሩትም ሳለ እስጢፋኖስ «ጌታ ኢየሱስ ነፍሴን ተቀበል ... ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው» ብሎ ጸለየ። በቤተክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው ጻድቅ ሰማዕት እስጢፋኖስ ነበር። በእግዚአብሔር ላይ የነበረው እምነትና ለቃሉ የነበረው ታዛዥነት ሞትን እንዲጋፈጥ ኃይል ሰጠው። የይቅርታ አመለካከቱ፤ ስደትንና መከራን እንዴት መቀበል እንዳለብን የሚያሳይ ለሁላችንም የሚሆን ምሳሌ ነው።

ጥያቄ 30፡- ሀ) እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎች ስለ እምነታቸው እንዲሞቱ አንዳንዶቹን ደግሞ እንዲተርፉ የሚያደርገው ለምን ይመስልሃል? ለ) የእስጢፋኖስ ቃላት መስቀል ላይ ሆኖ ኢየሱስ ያሰማቸው ከነበሩት ጋር ምን ያህል ይመሳሰላሉ? የሐዋ. 7፡59-60 ከሉቃስ 23፡32-34፤ 44-46 ጋር አነፃፅር።

በሚቀጥለው ትምህርታችን በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት ምን እንደተከሰተ እናያለን።

ምንም እንኳ ለሞት ቢጋፈጥም እስጢፋኖስ ያለምንም ማወላወል መንፈስ ቅዱስ እንዲናገር የሰጠውን መልእክት በታማኝነት ያሰማል። ክርስቲያኖች ስለ እውነት ሲሉ መቆም ያለባቸው ጊዜያቶች አሉ። ሰይጣን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት እንድንቃወም ወይም የእግዚአብሔር ቃል የሚያዘውን እንዳንከተል ያደርገንና ኅብረታችን እንዲጠፋብን ያደርጋል።

ጥያቄ 31፡- እስጢፋኖስ እስከ ሞት ድረስ፤ በክርስቶስ ያለውን እምነት ይዞ ፀንቶ መቆም የቻለው ለምንድነው?

እስጢፋኖስ የተወገዘውና የተገደለው፤ በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ በኩል ከእግዚአብሔር አዲስና ከፍ ያለ ኅብረት የማድረጊያ መንገድ በመከፈቱ ነው። እኛም ለዓለም ይህንኑ መልእክት መስጠት አለብን። የእስጢፋኖስ መልእክት ዘራቸውን፥ ያላቸውን ቦታና አምልኳቸውን በተመለከተ አይሁዶች የነበራቸውን የተሳሳተ ኩራት የሚነቅፍ ነበር። እኛስ እንደ አይሁዳውያኖቹ ነን?

ጥያቄ 32፡- ከጌታ ጋር ያለህ ኅብረት እንዴት ነው? ልብህን መርምር የሚያስፈልግህም ከሆነ እግዚአብሔርን ይቅርታ ጠይቅ።

# አምስተኛ ቀን፡-

## ትምህርቱን ከልስና የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. እስጢፋኖስ በቤተክርስቲያን የተሰጠው ሹመት ምንድነው?
2. የእስጢፋኖስ ሹመት መንፈሳዊ መሪዎች ማሟላት ካለባቸው ነገሮች ውስጥ የትኛቹን ነገር ነው የሚነግረን?
3. ኢየሱስ ፈሪሣዊያንን የገሠፀው ለምንድነው?
4. እስጢፋኖስ የተያዘው ለምንድነው?
5. «ነፃ ወጪዎች» የሚባሉት እነማን ናቸው?
6. እስጢፋኖስ ላይ የተመሠረተበት ክስ ምንድነው?
7. እስጢፋኖስ የአይሁድ መሪዎች የእስራኤልን ምድር በተመለከተ የነበራቸው መመካት ትክክለኛ እንዳልሆነ ያሳየው እንዴት ነው?
8. አይሁዶች እግዚአብሔር ለጠራቸው ብቁ ሳይሆኑ ሊገኙ የቻሉት እንዴት ነው?
9. እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝብ ያደረገው ጥሪና ኢየሱስ በሐዋ. 1፡8 ላይ ያደረገው የመጨረሻ ጥሪ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
10. እስጢፋኖስ እራሱን «ነፃ አውጪ» ምኩራብ ውስጥ ካሉት አይሁዶች ሊያመሳስል የሚችለው ለምንድነው?
11. ሀ) ባለፉት ጊዜያት እግዚአብሔር ሕዝቡን ይናገር የነበረው እንዴት ነው? ለ) ዛሬስ ሕዝቡን የሚናገረው እንዴት ነው?
12. የመጀመሪያው የአምልኮ ቤተመቅደስ የተቋቋመው የት ነው?
13. በእስጢፋኖስ ላይ የቀረበው ሁለተኛ ክስ ምን ነበር?
14. ሀ) እውነተኛ አምልኮ ምንድነው? ለ) አንድ ሰው የት ነው ማምለክ የሚችለው?
15. በእግዚአብሔር ዘንድ የሚታዩት እነሱ ብቻ እንዳልሆኑ ሲገለጽላቸው፣ አይሁዳውያን መልስ መስጠት ያቃታቸው ለምንድነው?
16. እስጢፋኖስ ባቀረበው አጠር ያለ የአይሁድ ታሪክ ክለሳ ላይ ለሸንጎውና ለከሰሱት አይሁዳውያን የሰጠውን ሦስት ዋና ዋና ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።
17. ባለፉት ዓመታት ውስጥ፣ እስጢፋኖስ ላቀረበው መልእክት፣ የአይሁዳውያንን ልብ ደንዳና እንዲሆን ያደረገው ነገር ምንድነው?

ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄዎች ተመልከትና ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ:-

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. ውይይት

ሀ) 1. ከእስጢፋኖስ ስለ ክርስቲያን መሪነት ምን ልንማር እንችላለን? 2. መሪዎችን ለመምረጥ ስትፈልግ ቤተክርስቲያንህ እንደማሟያ የምታያቸው ነገሮች ምንና ምን ናቸው? 3. መሪዎች ስንመርጥ ቅድሚያ የምንሰጠው መፈሳዊነታቸው ላይ ነው? ይህ አንዳንዴ እንዴት እንደሚፈጸም ሌላ ጊዜ ደግሞ እንዴት ችላ እንደሚባል አብራራ። ይህ ግን የሚሆነው ለምንድነው?

ለ) 1. በአገልግሎታችንና በአምልኮአችን ውስጥ ሕጋዊነትን ብቻ የምናበዛ ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? 2. እራሳችንን ከዚህ ለመጠበቅ የምንችለው እንዴት ነው?

ሐ) 1. እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው? (ዮሐ. 4፡23-24)። 2. ለአምልኮ ዕንቅፋት የሚሆኑት ነገሮች ምንና ምን ናቸው? 3. ልባችንን ለአምልኮ ዝግጁ የምናደርግባቸው መንገዶች ምንና ምን ናቸው?

ሠ) 1. በአገር፣ በዘር ወይም በትውልድ መመካት፣ በክርስቲያኖች መካከል ኅብረት እንዳይኖር ሊያደርግ የሚችለው እንዴት ነው? 2. ተገቢ ያልሆኑ አስተሳሰቦችንና ባህሎችን ከቤተክርስቲያናችንና ከአገራችን ውስጥ ልናስወግዳቸው የምንችለው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 6

## የሐዋርያት ሥራ 8፡ 1-40

## የመጀመሪያው ቀን:-የሐዋርያት ሥራ 8፡1-8

ባለፈው ሳምንት እስጢፋኖስ ችሎት ፊት ቀርቦ የሰጠውን መከላከያ አጥንተናል። በመልእክቱም፣ እስጢፋኖስ ያለፈውን የእስራኤልን ሕዝብ ታሪክ ነው ያወሳው። ለአይሁዳውያኑ፣ የእግዚአብሔር ዓላማና ሥራ በምድረ እስራኤል ላይ ብቻ የተወሰነ እንዳልሆነ ነው ማሳየት የፈለገው። እንዲያውም፣ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሠራው በአሕዛብ ምድር ሳሉ ነው። እስጢፋኖስ እነዚህ የሚመኩባቸው፣ የሙሴ ሕግ፥ አይሁዳዊነታቸውና በመካከላቸው የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ መኖሩ ሁሉ ጊዜያዊ እንደሆነ፣ ሙሉ በሙሉ ትርጉም የሚሰጡትና የተሟሉ የሚሆኑት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንደሆነ አሳይቷል። አይሁዶች ግን ኢየሱስን ሳይቀበሉ ቀርተው በመስቀል ላይ ሰቅለውታል። ልክ እንደ ኢየሱስ፣ እስጢፋኖስም እግዚአብሔርን

ተሳድቧል ተብሎ የሐሰት ምሥክሮች አቅርበውበት ነው የከሰሱት። አይሁዳውያንም በንዴት ተነሣሥተው፤ እስጢፋኖስ ወደ ጌታ ኃጢአታቸውን እንዳይዝባቸው በመጣራት ላይ ሳለ፤ በድንጋይ ወግረው ገደሉት።

ጥያቄ 1፡- ማቴዎስ 26፡25፤ ሉቃስ 22፡67-71 እና የሐዋርያት ሥራ 7፡54-60 አንብብ። በኢየሱስና በእስጢፋኖስ ላይ የቀረቡትን ፍርዶች አነፃፅር።

የእስጢፋኖስ ሞት «በኢየሩሳሌም ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ» የሚለውን የኢየሱስን ትዕዛዝ የአንዱን ምዕራፍ መጨረሻ የሚያመለክት ነው። ይህ እራሱ ደግሞ፤ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል መደምደሚያ ነው፤ ምክንያቱም ክርስትና ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ወደ ሌሎች ቦታዎች መዳረስ ጀምሮአልና ነው። ሐዋርያቱ ያለፍርሃት ይሰብኩ፤ ድንቅና ተአምራትን ያሳዩ ስለነበር በመላው ኢየሩሳሌም ሰዎች በሙሉ የወንጌሉን መልእክት ሰምተዋል። አሁን ግን፤ ምሥክሮቹ ከኢየሩሳሌም ወጥተው ወደ ሌላው ወደተቀረው ዓለም የሚሄዱበት ሰዓት ደርሷል። እዛው ኢየሩሳሌም ውስጥ ተቀምጠው ከሚሠሩ፤ እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ምሥክርነታቸውን ይዘው ለሌሎች በይሁዳና በሰማርያት ለሚገኙ ሰዎች እንዲሄዱ አደረጋቸው።

የሐዋርያት ሥራ 8፡1-40 አንብብና እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 2 ፡-ሀ) በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ላይ የሚገኙት አራቱ ዋና ዋና ሰዎች እነማን ናቸው? ለ) ወንጌሉን፤ ከኢየሩሳሌም ወጥቶ እንዲሠራጭ ያደረገው ነገር ምንድነው? ሐ) ፊሊጶስ የወንጌሉን መልእክት ያሰማባቸውን ሦስት ከተሞች ስም ግለጽ።

የሐዋርያት ሥራ 8፡ 1-8 እንደገና አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 3፡- ሀ) በምን ቀን ነው ታላቅ ስደት በቤተክርስቲያን ላይ የመጣው? ለ) አማኞች ምን ሆኑ? ሐ) ፊሊጶስ ወዴት ነው የሄደው? ከሄደስ በኋላ ምን አደረገ?

እስጢፋኖስ በድንጋይ ይወገር በነበረበት ወቅት፤ ሁኔታውን በታላቅ ደስታ ቆሞ ያይ የነበር ሳውል የሚባል ሰው ነበር። በአይሁድ መሪዎችም ዘንድ ለሕጉ ቀናተኛ እንደሆነ ነበር የሚታወቀው። እስጢፋኖስን በድንጋይ ይወግሩ የነበሩት ሰዎች ልብሳቸውን በሳውል እግር ሥር ማኖራቸው፤ ሳውል እነዚያን ሰዎች እንደሚደግፍና እንደሚያበረታታ የሚያሳይ ነው። እስጢፋኖስም ሲሞት፤ ወዲያውኑ ታላቅ ስደት በኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ላይ ወረደ። ስደቱን ይመራ የነበረው፤ በስተኋላ ዓለም ሁሉ አይቶት የማያውቀው ታላቁ የክርስትና መስካሪ ሳውል ነው። ሳውል ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት የተነሣሣው፤ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው እየሄደ ወንድና ሴቶችን ወደ እሥር ቤት በማስገባትና በመግደል ነበር። ብዙ ክርስቲያኖችም ከኢየሩሳሌም ተሰደዱ፤ በሄዱበት ሥፍራ ሁሉ ግን፤ የኢየሱስ ክርስቶስን የምሥራች ዜና ያሰሙና ይሰብኩ ነበር። እግዚአብሔር የሚቀጥለውን ዕቅዱን፤ ወደ ይሁዳና ሰማርያ የወንጌሉን ማሰራጨት እውን እንዲሆን ያደረገው ስደትን እንደመሣሪያነት ተጠቅሞ፤ ክርስቲያኖቹን ከኢየሩሳሌም በማስወጣት ነው።

ጥያቄ 4:- ከኢየሩሳሌም ሸሽተው የወጡት ሰዎች ታማኝ ምሥክሮች ሆነው ጸንተው መቆማቸውን የምናውቀው እንዴት ነው?

ጥያቄ 5:- በኢየሩሳሌም በነበሩ አማኞች ላይ በደረሰው ስደት ምን መልካም ነገር ተከሰተ?

ጥያቄ 6:- ሰማሪያዊ የሚለውን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ተመልከት። ከሄሌናዊያኑ ሰዎች ይበልጥ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ለነበሩት ኦርቶዶክስ አይሁዳውያን ሰማሪያውያኖቹንና ሌሎቹን ጎሳዎች ለመቀበል የከበደው ለምን ይመስልሃል?

ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ፤ ኢየሩሳሌም ብቻውን የወንጌሉ ምሥክሮች መከማቻ መሆኗ ቀረ። ምንም እንኳ ሐዋርያቱ በኢየሩሳሌም ቢቆዩም፤ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች በተለይም በአሕዛብ ምድር የነበሩት ሄሌናውያኑ አይሁዶች ተሰደዋል። አንዳንዶቹም ለበዓለሐምሳ መጥተው ካመኑ በኋላ ከክርስቲያኖቹ ኅብረት ጋር የቆዩ ሊሆኑ ይችላሉ። በስደቱ ምክንያትም፤ በየአካባቢው ይገኙ ወደነበሩት ከተሞች በመሄድ ወደ ቀድሞው ቤታቸው ተመልሰዋል። በሄዱበትም ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰብኩ ነበር። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በድቁና እንዲያገለግል በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን የተመረጠው ፊልጶስ ነው። ፊሊጶስም ወደ ሰማሪያ ሄዶ የክርስቶስን የምሥራች ወንጌል ሰበከ።

ሰማርያውያን የተደቀሉ ዘሮች ናቸው፤ የአሕዛብና የአይሁድ ቅልቅል ናቸው። የእስራኤል ሰሜናዊው ክፍል በሶሪያውያን እጅ ከወደቀ በኋላ በተፈጠረው ጋብቻ ምክንያት የተገኙ ናቸው። የሶሪያ መንግሥት በእስራኤል ከቀሩት አይሁዳውያን ጋር ያዳቅላቸው ዘንድ፤ አሕዛብን ወደ እስራኤል አመጣ። ዘራቸው የተዳቀለ ብቻ መሆኑ ሳይሆን፤ ይሁዳ ከነበሩት አይሁዳውያን ጋር ጠላቶች ስለነበሩም፤ የራሳቸውን ቤተመቅደስ አዋቅረው የግላቸውን የአምልኮ ሥርዓት በሰማሪያ ያቋቋሙ ናቸው። ሰማሪያውያን በሙሴ ሕግ ያምኑ ነበር፤ ሆኖም የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ነው የመጡት ብለው አያምኑም ነበር። የራሳቸውንም ቤተመቅደስ በጀሪዚም ተራራ ላይ ሠርተው በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ አያመልኩም ነበር። አንድ ጊዜ በፋሲካ በዓል ቀን በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ አጥንት በመበተን ቤተመቅደሱን አርክሰውት ነበር። ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ የነበሩትን የገሊላ አይሁዶችንም ገድለዋል። እነዚህም ሌሎች ነገሮች ተጨማምረው፤ በአይሁዶችና በሰማሪያውያን መካከል ትልቅ ቅራኔ ፈጠሩ። በዚህም ምክንያት አይሁዶች ያንቋሽሿቸው ነበር፤ ከእነርሱም ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም።

ጥያቄ 7:- ከዚህ ቀደም ብሎ በሰማርያ ወንጌሉ የተሰበከው መቼ ነው? (ዮሐ. 4 ተመልከት)።

በኢየሩሳሌም ዘወትር ይኖሩ ከነበሩት አይሁዶች ይልቅ፤ ከሌሎች ሰዎችና ባሕላቸው ጋር አብረው የኖሩት ሄለናዊ አይሁዶች ለሌሎች ጎሳዎች ያሳዩት የአቀባበል መንፈስ የተሻለ ነበር። በዚህም ምክንያት ከሰማሪያውያኑ ጋር ለመኖር ፈቃደኞች

ነበሩ፤ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመሠክሩላቸው ጊዜ ለመሥማት ፈቃደኞች ነበሩ።

በሰማርያ ከተማ ፊሊጶስ፤ ስለ ክርስቶስ እየሰበከ ሽባ፥ አንካሳና በክፉ መንፈስ ተይዘው የነበሩትን በመፈወስ ድንቅና ተአምራትን ይሠራ ነበር። እነዚህም ተአምራቶች ሰዎችን ማረካቸው። እነሱም በዚህ ተገፋፍተው መልእክቱን መስማትና በኢየሱስ ማመን ጀመሩ።

ኢየሱስ «በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳና በሰማርያ ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ» ብሎ ነበር። በስደት ምክንያት ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም በመሰደዳቸውና በታማኝነት በመመሥከራቸው ወንጌሉ በፍጥነት ተሰራጨ። ስደቱ ባይኖር ኖሮ የመልእክቱ መሰራጨት እንዲህ የፈጠነና ታላቅ አይሆንም ነበር። ሳውል ራሱ ወንጌልን ወደ ዓለም ያዳረሰበት የመጀመሪያ ምክንያት የመጀመሪያ ስደት ሆነ፤ በኋላም ሳውል ራሱ ዋና መልእክተኛ ሆኖ የተገኘበት ስደት ሆነ።

በቤተክርስቲያን ላይ የሚደርሰው ስደት ሁሌም ቢሆን የሚያሳዝን ነው፤ ሆኖም የጥንቷን ቤተክርስቲያን አላዳከማትም። ስደት ክርስቲያኖች ካሉበት እንዲፈናቀሉ አድርጓቸዋል፤ ሆኖም እንዲህ ተፈናቅለውና ተበታትነው ባይሆን ኖሮ የምሥራቹን ዜና ሊያሰሙበት ወደማይችሉባቸው ቦታዎች ድረስ ሄደው በዚያ ለሚገኙ ሕዝቦች ወንጌሉን ባላሰሙም ነበር።

ጥያቄ 8:- ስደት፤ ወንጌሉን ሰምተው ለማያውቁ ሰዎች ወንጌሉ እንዲሰበክ ያደረገበትን አጋጣሚን እንደ ምሳሌ ልትጠቅስ ትችላለህ?

ምንም እንኳ በክርስቲያኖች ኅብረት ዙሪያ ተሰብስቦ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናቱና አብሮ መጸለዩ መልካም ቢሆንም ይህ በክርስቲያኑ ላይ አደገኛ የሆነ ነገር ሊፈጥርበት ይችላል። ይህንን ብቻ እያደረጉ ክርስቲያኖች ባልሆኑ ሰዎች መካከል ወጥተው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ማካፈሉን ችላ ካሉ፤ የኢየሱስን ትዕዛዝ አላሟሉም ማለት ነው። ምንም እንኳ ክርስቲያኖቹ፤ በኢየሩሳሌም መኖርና በሐዋርያቱም መማር ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም፤ እግዚአብሔር አልፈቀደላቸውም። በእነሱ ላይ ስደትን አምጥቶ ከበተናቸው በኋላ፤ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል መስማት ለአለባቸው ሰዎች እንዲያሰሙ አድርጓል።

ጥያቄ 9:- በምን ዓይነት መንገድ ነው በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜያቸውን ለእምልኮ በአንድነት በመሰብሰብ ወደ ዓለም ወጥተው መመሥከሩን ሊረሱት የሚችሉት?

# ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 8: 9-26

የፊሊጶስ ስብከት፤ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነው፤ የመጀመሪያዎቹ [illegible]ት የሐዋርያት ሥራ ምዕራፎች ቤተክርስቲያን እንዴት እንደተመሠረ[illegible] ነው የሚያሳዩት። የመጀመሪያው ምሥክርነት የተደረገው በኢየሩሳሌም [illegible]ት ብቻ ነው አማኞቹም በሙሉ የአይሁዳውያንን አኗኗር ዘይቤ[illegible]

የሚከተሉ ነበሩ። የሚቀጥሉት አምስት ምዕራፎች ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8-12 ያሉት፣ የምሥራቹ ዜና ወደ ይሁዳና ሰማሪያ ከዚያም አልፎ አሕዛብ ቤተክርስቲያን ኅብረት ውስጥ ወደተቀላቀሉበት አንጾኪያ ድረስ እንዴት እንደ ደረሰ የሚገልጹ ናቸው። ይህም ሌላ የመሸጋገሪያ ወቅት ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 8፡9-25 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 10፡- ሀ) የሲሞን ተከታዮች ምን ሆኑ? ለ) ሲሞን ያምን የነበረው በምን ይመስልሃል? ሐ) በሰማሪያ፣ ያመኑት ሰዎች መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት መቼ ነው? መ) ሲሞን መንፈስ ቅዱስን ተቀብሏል? እንዴት እናውቃለን? ሠ) የወንጌሉን እውነታ ጠንቅቀው አውቀው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት አለማድረግ ይቻላል? ሰፋ አድርገህ አብራራው። ረ) ወደዚህ ኅብረት ውስጥ ለመግባት የሚያስፈልገው ነገር ምንድነው?

ተአምራቶች ሁሌም ሰዎችን ይማርካሉ። በሰይጣን ኃይል አማካኝነት እንደ ሲሞን ባሉ ወኪሎች በኩል የሚፈጸሙት ተአምራቶች ሰዎችን በሐሰተኞች ትምህርት እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል። በፊሊጶስ የተፈጸሙት ድንቅና ተአምራቶች ብዙ ሰዎች ወደ እውነቱ ማርከዋል።

ጥያቄ 11፡- ሀ) ጠንቋዮች ወይም ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ተአምራትን ሲፈጽሙ አይተህ ታውቃለህ? ምን እንደተደረገ ግለጽ። ለ) እግዚአብሔር በሰዎች ተጠቅሞ ተአምራትን ሲፈጽም የሚሆነው ነገር ምን ነበር?

በሰማርያ ከተማ ሲሞን የሚባል ጠንቋይ ነበር። የነበረውም ኃይል በጣም ታላቅ ስለነበር፣ ብዙ ሰዎች እንደ አምላክ ወይም ደግሞ ከአማልክት የተለየ ኃይል እንደተቀበለ አድርገው ያዩት ነበር። ሲሞንም የሚያስደንቁ ነገሮችን እያደረገ ብዙ ተከታዮችን አፍርቷል። ሆኖም ፊሊጶስ በእግዚአብሔር ኃይል ተጠቅሞ ሰዎችን ሲፈውስ አየው፣ ኃይሉንም ከገመገመ በኋላ እሱን ተከትለው መንፈስ ቅዱስ በፊሊጶስ ውስጥ አልፎ የሚሠራውን ሥራ ሲያይ፣ ለራሱ ይህን ኃይል እንዴት ማግኘት እንደሚችል ማሰብ ጀመረ። ፊሊጶስን ከሚከተሉት ሰዎች ጋር ሆኖ ክርስቲያን ለመሆን ይወስናል። ስለ እምነቱም ምሥክር ይሆን ዘንድ ከብዙ ሰዎች ጋር ተጠመቀ።

በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት ብዙ ሳምራውያን እንዳመኑ በሰሙ ጊዜ፣ ከአዳዲሶቹ ክርስቲያኖች ጋር ለመገናኘት ጴጥሮስና ዮሐንስ ተነሥተው ወደዚያ ይሄዳሉ። ጴጥሮስና ዮሐንስ በክርስቶስ ገና አዲስ አማኞች የሆኑትን ወደ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ማንነት ሊመሩዋቸው ቻሉ። ከጸለዩላቸውም በኋላ ሐዋርያት እጆቻቸውን እኖሩባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።

በማቴዎስ 16፡17-19፡- ጴጥሮስ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ማለት ወደ መንግሥተ ሰማያት ያመጣ ዘንድ ልዩ በሆነ መንገድ እንደሚጠቀምበት ኢየሱስ ቃል ገብቶለታል። እግዚአብሔር ለጴጥሮስና ለሌሎቹ ሐዋርያት አዳዲስ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር የማስገባት መብት ሰጥቷቸዋል። ስለዚህም ቤተክርስቲያን እንደዚህ

አድጎ ሳምራውያን በቤተክርስቲያን ውስጥ በዕኩል ታይተው ኅብረት እንዲኖራቸው እርምጃው ሲወሰድ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ የተላኩት የእነሱን እምነት እውነተኛነት ለማረጋገጥና እንደማንኛውም ሰው በእኩልነት በቤተክርስቲያን ውስጥ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ነው። እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ በጴጥሮስ በኩል እንዲተላለፍ ያደረገው በቤተክርስቲያን ከሌላው አይሁዳዊ እኩል መሆናቸው የተረጋገጠው፤ ሳምራውያኑ አይሁዶች በመጀመሪያ ልክ እንደተቀበሉት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ነው። በሳምራውያንና በአይሁዶች መካከል የነበረው የጥላቻና የምቀኝነት ግድግዳ፤ እግዚአብሔር በተመሳሳይ ሁኔታ ለሳምራውያኑ መንፈስ ቅዱሱን ሲሰጣቸው ፈርሷል። የመጀመሪያዎቹ ሳምራውያን ዓማኞች መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ ሌሎች ሁለተኛ የአማኞች ስብስብ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ተብሎ የተደረገ ነገር ስለመኖሩ ምንም ማስረጃ የለም። እንዲያውም ሉቃስ መንፈስ ቅዱስን ወዲያውኑ ተቀብለዋል ብሎ አለማለቱም፤ የእነሱ ነገር ለየት ያለ ነው ለማለት የፈለገ ያስመስለዋል። በልሳን ስለመናገራቸው የተዘገበ ነገር ባይኖርም፤ እግዚአብሔር ልክ እንደ አይሁዳውያኑ ሳምራውያኑን ወደ ቤተክርስቲያን መቀበሉ ግን ግልጽ ነው።

ጥያቄ 12፡- አንዳንድ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን ስለመቀበል ካላቸው አመለካከት ጋር ይህ የሚለያየው እንዴት ነው?

በዚህ ሥፍራ ላይ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብቻ በመጥቀስ ሁሉ በአንድ ክርስቲያን ላይ መንፈስ ቅዱስ የሚወርደው በኢየሱስ ካመነ ጊዜ በኋላና በተለየ ቀን ነው ልንል አንችልም። አንድ ትልቅ ሰው እጁን ጭኖ ወይም የተለየ የጾምና ጸሎት ጊዜ ተወስዶ አይደለም መንፈስ ቅዱስ የሚመጣው። መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚሰጠው ልክ እንዳመኑ ነው። በመጀመሪያዎቹ ሳምራውያን ላይ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ያልሆነው፤ እግዚአብሔር ለአይሁዳውያኑ ክርስቲያኖች ልክ እነርሱን እንደተቀበለው ሳምራውያን ክርስቲያኖችንም እንደሚቀበል ለማሳየት ስለፈለገ ብቻ ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ዘረኝነት ወይም ይህ ትልቅ ክርስቲያን ነው ይህ ትንሽ ክርስቲያን ነው የሚባል ነገር አልነበረም (1ቆሮ. 12፡13)። በእግዚአብሔር ፊት ሁሉም እኩል ናቸው። ጳውሎስም በሮሜ 8፡9 ላይ «እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» ብሎ ተናግሯል።

ስለ ፊሊጶስ ኃይል ለማወቅ ሲል ፊሊጶስን ይከተል የነበረው ሲሞን ሐዋርያቱ አዳዲሶቹን አማኞች በእጆቻቸው ሲነኳቸው መንፈስ ቅዱስ እንደወረደባቸው አየ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሲሞን መንፈስ ቅዱስን ባለመቀበሉ የእሱ እምነትና ጥምቀት እውነተኛ አለመሆኑ ግልጽ ነው።

ጥያቄ 13፡- ልክ እንደ ሲሞን የጭንቅላት እውቀት ብቻ እንጂ ከልባቸው ኢየሱስን ያልተቀበሉ ሰዎች ዛሬ በቤተክርስቲያን ይታያሉ? በሕይወታቸው ውስጥ የጎደለዉ ነገር ምንድነው?

ሲሞን በአማኞቹ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወርዶ ሲያይ፤ ያንን ኃይል ለእራሱም ፈለገ። የጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን የመስጠት ችሎታ ልክ እንደራሱ አስማት የመሥራት

ችሎታ መሰለው። በገንዘብ ሊያገኘው የሚችልና በእጁም ውስጥ አስገብቶ መንፈስ ቅዱስን ለሌሎችም በመስጠት ገንዘብ የሚያገኝም መስሎታል። በመጀመሪያ ላይም አማኝ ለመምሰል ያደረገው ሙከራ መንፈስ ቅዱስን አላሰጠውም፤ በዚህም ምክንያት እሱ በሌሎች ሰዎች ላይ እጁን ሲጭን በእነርሱ ላይ መንፈስ ቅዱስን ማውረድ የሚችልበት ኃይል ሐዋርያቱ እንዲሰጡት ገንዘብ ሊሰጣቸው ወሰነ።

በምንኖርበት ዓለም ውስጥ ሃብት ታላቅ ኃይል አለው፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ወይም የመንፈስ ፍሬዎችን ሊገዛ አይችልም። ገንዘብ አንዳንድ ምቾቶችን ሊያስገኝልኝ ይችላል፤ ሆኖም የልብ ሰላምን ወይም ዘላለማዊ ተስፋን አያቀዳጅንም። ሲሞን የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ ለመግዛት በመሞከሩ ጴጥሮስ «ምናልባትም የልብህን አሳብ ይቅር ይልህ እንደሆነ ወደ እግዚአብሔር ለምን» በማለት ይቆጣዋል (ቁ. 21)። ይህም ሆኖ ግን ሲሞን ንስሐ አልገባም። ከቤተክርስቲያን ታሪክ ደግሞ እንደምንረዳው ሲሞን «ኖትሲዝም» የሚባል ወደ በኋላ ትልቅ ችግር በክርስትና ላይ የሚፈጥር ሐሰተኛ ትምህርት ጀምሯል። ምንም እንኳ ለጊዜው በኢየሱስ ያመነ ለመምሰል ቢሞክርና ቢጠመቅም፤ ሕይወቱና ልቡ ተለውጧል ማለት አይደለም። ክርስትና፤ ሌላ ከሰዎች ገንዘብ የሚያገኝበት ዓይነተኛ መንገድ መስሎታል። ወደ በኋላ ላይ የታዩት የሕይወቱ ፍሬዎች የመጀመሪያው እምነቱ እውነተኛ እንዳልሆነ ያሳየናል። ጴጥሮስ እንዲለምንለትም ያቀረበው ምልጃ፥ ንስሐ ለመግባት ከመፈለጉ የተነሣ በንጹህ ልቡ ያቀረበው ሳይሆን ሕይወቱን ከፍርድ ለማዳን ሲል ብቻ ያደረገው ነው።

በሰማሪያ ከተማ ብዙ ሰዎች ለክርስቶስ መልእክት ተገቢ ምላሽ ሰጥተዋል። ሐዋርያቱም ወደ ኢየሩሳሌም በመመለስ ላይ ሳሉ፤ በብዙ የሰማርያ መንደሮች የወንጌሉን መልእክት ሰብከዋል። የወንጌሉ ምሥክሮች በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳና በሰማርያ ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ የሚለውን የኢየሱስን ትዕዛዝ በመጠበቃቸው እየበዙ መጡ። «እስከ ምድር ዳር» የሚለው ደግሞ፤ የሚቀጥለው የእግዚአብሔር የማዳረስ እቅድ ውስጥ የሚቃለል ነው (ሐዋ. 1፡8)።

**ጥያቄ 14፡- የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መገለጥ መመኘታችን ትክክል የሚሆነው በምን መልኩ ነው? ስሕተት የሚሆነውስ በምን መልኩ ነው?**

በአንድ መልኩ መንፈስ ቅዱስን መመኘታችን ታላቅ በሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር እውቀት ለማደግ ያለንን ፍላጎትና (ኤፌ. 3፡18-19) በኤፌሶን 5፡18 ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመጠበቅ የምናደርገውን ጥረት ያሳያል ። ነገር ግን፤ መንፈስ ቅዱስን የምንመኘው ሃብታም ለመሆን ወይም ለመታወቅ ወይም መንፈሳዊ ለመምሰል ከሆነ፤ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እየሠራን ነው። አንድን ነገር ለማግኘት የሚያነሣሣን መንፈስ ቅዱስም ይሁን ወይም ጥሩ ሥራ ወይም የትዳር ጓደኛ ወይም ማንኛውም ነገር ቢሆን፤ ይህ ሁሉ የሚያሳየው እውነተኛውን የልባችንን ሁኔታ ነው። ይህም የልባችን ምኞት፡- እግዚአብሔርን ልናከብርበት እንደሆነ ወይም የራስ ወዳድነት መንፈስን ለማራመድ እንደሆነ ለይቶ ያሳያል።

ጥያቄ 15፡- አንዳንዴ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ሰላም ለመግዛት ወይም ገንዘብን በመስጠት ውለታውን ለማግኘት የሚሞክሩት እንዴት ነው? አንተሳ እንደዚህ አድርገህ ታውቃለህ?

አንድ ወጣት እግዚአብሔር ወደሌላ አገር ሄዶ ወንጌላዊ እንዲሆን የጠራው መሆኑን ያምን ነበር። በኋላም አንዲት ሚስቱ እንድትሆን ይፈልጋት የነበረችን ልጃገረድ ያገኛል፤ እሷ ግን ወደ ሌላ አገር መሄድ አትፈልግም ነበር። ለእግዚአብሔር ታዛዥ ከመሆን ፈንታ ልጅቷን ያገባና ስላለመታዘዙ መካካሻ ይሁን ብሎ ሌሎች በዚያ ሄደው የሚሠሩበትን ገንዘብ ይከፍላል።

አለመታዘዛቸውን ለመሸፈን እያሉ ለቤተክርስቲያን ወይም ለአንድ ማኅበራዊ አገልግሎት ገንዘባቸውን የሚሰጡ ብዙ ሰዎች አሉ። ምንም እንኳ ብዙዎች በሃብታቸው ሌሎችን ለመላክ የተጠሩ ቢሆንም ይህ ለጌታ በመታዘዝ ምትክ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል ነገር አይደለም።

ጥያቄ 16፡- የፈለገውን ነገር ቢጠይቅህ፤ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ታዛዥ ለመሆን እራስህን አሳልፈህ ትሰጣለህ? አሁን ወደሚወድህ ሰማያዊው አባትህ በጸሎት ቀርበህ ሙሉ በሙሉ እራስህን አሳልፈህ ለእርሱ ስጥ።

## ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 8፡26-40

ከበዓለ ሐምሳ በኋላ ከአማኞቹ ጋር ኅብረት ለማድረግና ለማጥናት በኢየሩሳሌም ከቀሩት ሄለናዊ አይሁዳውያን አንዱ ፊሊጶስ ነው። ለመበለቶቹ ምግብ እንዲሰጡ ከተመረጡት ሰዎች መካከልም አንዱ ነበር። ሆኖም በኢየሩሳሌም የነበረው ስደት እየከረረ ሲሄድ፤ ፊሊጶስና ሌሎች ብዙ ሰዎች ከተማዋን ጥለው ወደ መጡበት የትውልድ ሥፍራ ተመልሰዋል። እግዚአብሔር እንዳዘዘውም የወንጌሉን ምሥክርነት ይዘው ወደ ይሁዳና ሰማርያ ሄደዋል። እግዚአብሔር በመልአኩ በኩል በድንገት እስከተናገረው ጊዜ ድረስ በሰማርያ ከተማ ውስጥ አገልግሎት በጣም ፍሬያማ ነበረ። መልአኩም ፊሊጶስን በደቡብ ኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚወስደው መንገድ እንዲሄድ ነገረው።

በዛሬው ዕለት፤ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲቀበል እንዴት አድርጎ የአንድ ሰውን ልብ እንዳዘጋጀ ፊሊጶስን ደግሞ ለሱ እንዲመሠክር እንዴት እንዳዘጋጀውና እንደመራውም እናያለን።

የሐዋርያት ሥራ 8፡26-40 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 17፡- ሀ) የኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ልብ እግዚአብሔር ያዘጋጀው እንዴት ነው?

ለ) ልቡ እንደተዘጋጀ የምናውቀው እንዴት ነው?

ሐ) ፊሊጶስን ወደ ኢትዮጵያዊው ለመምራት እግዚአብሔር በምንድነው የተጠቀመው?

ፊሊጶስ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ያከብራል። በጣም ያስደስተ የነበረውን የሰማርያ አገልግሎቱን ትቶ በኢየሩሳሌም በስተደቡብ በጋዛ በኩል አልፎ ወደ ግብፅ የሚወስደውን መንገድ ይዞ ይሄዳል። በጣም ረዥም ጉዞ ነበር። መጀመሪያ 40 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ወዳለችው ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ነበረበት። ከዚያም ለተወሰነ ርቀት ወደ ደቡብ መጓዝ ነበረበት። በዚያ መንገድም ላይ እየሄደ ሳለ አንድ ሰረገላ በአጠገቡ ያልፋል፤ መንፈስ ቅዱስም ፊሊጶስን» ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተገናኝ» አለው። በሰረገላውም ውስጥ የነበረው ሰውዬ ኢየሩሳሌም ደርሶ ወደ አገሩ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ነው።

የጥንቷ ኢትዮጵያ የዛሬውኑ ዓይነት ድንበር አልነበራትም። እንዲያውም ታጠቃልል የነበረው ሰሜን ሱዳንና ሰሜን ኢትዮጵያን ብቻ ነበር። ባመዛኙ ይህ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ ባለሥልጣን ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ። ከአሕዛብ ወገን ሆኖ በብሉይ ኪዳኑ አምላክ የሚያምንና አይሁዳዊ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ሳይሆን አይቀርም። አይሁዳዊ ለመሆን፤ አንድ አሕዛብ የቀድሞውን ሃይማኖቱን ትቶ በእግዚአብሔር ማመን መገረዝና ሁሉንም የብሉይ ኪዳን ሕግጋትና የአምልኮ ሥርዓት መከተል አለበት። ምንም እንኳ ከአሕዛብ ወገን ቢሆንም ይህን ከፈጸመ በኋላ ግን አይሁዳዊ ይሆናል።

ያለጥርጥር ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰው በቤተመቅደስ የአምልኮ ሥርዓት ተካፍሎ ነው። እግዚአብሔር ግን ይህ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልግ ስለነበር፤ ፊሊጶስን ልኮ ስለ ኢየሱስ እንዲነገረው ያደርጋል።

ፊሊጶስም ጠጋ ብሎ ሲሰማው፤ ኢትዮጵያዊው ድምጹን ከፍ አድርጎ ያነብ የነበረው የኢሳይያስን መጽሐፍ ነው። የሚያነበውም ክፍል ትንቢተ ኢሳይያስ 53፡7-8 ነው። ፊሊጶስም «በእውን የምታነበውን ታስተውለዋለህን?» ብሎ ይጠይቀዋል (ቁ. 30)። ምንም እንኳ ኢትዮጵያዊው ቃላቱን ቢያውቅም የመልእክቱ ትርጓሜ ግን አያውቅም ነበር። በኢየሱስ ክርስቶስም ይህ ትንቢት መፈጸሙን አያውቅም። ኢትዮጵያዊውም ሰረገላው ላይ ወጥቶ እንዲያስረዳው ፊሊጶስን ይጋብዘዋል። ትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ካለው ጽሑፍ በመጀመር ፊልጶስ ስለ ኢየሱስ ልደት፣ ሞት፣ ትንሣኤና ዳግም መምጣት ያስረዳዋል።

ጥያቄ18፡- ሀ) ለማያምን ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ማንበቡ በቂ የማይሆነው ለምንድነው? ለ) ሌላ የሚያስፈልገው ነገር ምንድነው?

የኢትዮጵያዊው ልብ የተዘጋጀው በእግዚአብሔር እጅ ነው። ለአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ነበር። ከአሕዛብም ወገን ነበር። ሆኖም ሰዎች ብዙ አማልክት በሚያመልኩበት ወቅት አንድ አምላክ ይመለክበት በነበረው በአይሁድ ሃይማኖት ተማርኮ ነበር። መጽሐፍትንም አንብቧል፤ እስከ ኢየሩሳሌምም የመጣው ለአምልኮ ነው፤ ስለዚህም፤ ምናልባት ሃይማኖቱ አይሁዳዊ ሳይሆን አይቀርም። ይህም ቢሆን፤ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስረዳው ሰው ያስፈልገው ነበር።

ፊሊጶስ ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የእግዚአብሔርን ቃል እያስረዳው ሳለ፤ ኢትዮጵያዊው «እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው?» አለው (ቁ. 36)። ኢትዮጵያዊው «ተጠመቁ» የሚለውን የኢየሱስን ትዕዛዝ ሳይሰማ አልቀረም። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ለመጠበቅ ይፈለግ ስለነበረም ቶሎ ለመጠመቅ ፈለገ። በዚህም ምክንያት ወደ ውኃው ወርደው ኢትዮጵያዊው ተጠመቀ። ከዚህም በኋላ መንፈስ ቅዱስ በድንገት ፊሊጶስን መንጥቆ ወሰደው። ኢትዮጵያዊውም ደስ ብሎት መንገዱን ቀጠለ።

ጥያቄ19፡- የኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ልብ ዝግጁ እንዲሆንና ግንዛቤ እንዲኖረው እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ነገሮች ምንና ምን ናቸው?

ጥያቄ 20፡- እግዚአብሔር በፊሊጶስ የተጠቀመው ለምንድነው?

ጥያቄ 21፡- ዛሬ የጥምቀት ዓላማ ምንድነው? በቤተክርስቲያንህ ያሉ ብዙዎች ሰዎች የተጠመቁ ናቸው? ካልተጠመቁ፤ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሆኖ ሳለ የማይጠመቁት ለምንድነው?

ምንም እንኳ እግዚአብሔር የኢትዮጵያዊውን ልብ ቢያዘጋጅ፤ ወደ ኢየሱስ እንዲመራው የተጠቀመው በፊሊጶስ ነው። ፊሊጶስም ለእግዚአብሔር ታዛዥ ለመሆንና ለእርሱ ምሥክር ለመሆን ዝግጁ ነበር። ኢትዮጵያዊው ያነበው የነበረውን ክፍል በማስረዳት ይጀምርና ኢየሱስን እንደግል አዳኙ መቀበል እንዳለበትና መጠመቅ እንዳለበትም ፊሊጶስ ሳይነግረው አልቀረም። ፊሊጶስ የእግዚአብሔርን ቃል ጠንቅቆ ያልተረዳ ቢሆን ኖሮ ለኢትዮጵያዊው ማስረዳት ባልቻለም ነበር። በተጨማሪም ፊሊጶስ በመንፈስ ቅዱስ ለመመራት ፈቃደኛና ለመታዘዙም ፈጣን ነበር።

ጥያቄ22 ፡-ሀ) አንድ ክርስቲያን ተገቢ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ሊኖረው የሚገባው ለምንድነው? ለ) የእግዚአብሔርን ቃል ባለማወቅ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ምንድናቸው?

በክርስቶስ ማመን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መጠበቅ ማለት ነው። ኢትዮጵያዊው ፊሊጶስ ያስተማረውን የኢየሱስን የምሥራች ዜና ከሰማና ከተቀበለ በኋላ ልጠመቅ ብሎ ጠየቀ። ይህ ጥምቀት ሥነ-ሥርዓት የሚካሄደው፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ባመኑ ሰዎች ላይ ሲሆን፤ ይህም ለደኅንነታቸው ነው። ኢትዮጵያዊውም የተጠመቀው፤ በክርስቶስ አምኖ ክርስቲያን ስለሆነ ነው። ጥምቀቱ አላዳነውም፤ ነገር ግን በሕይወቱ ውስጣዊ ለውጥ እንደተካሄደ የሚያሳይ ውጫዊ ምልክት ነበር።

ፊሊጶስ ወደ ጋዛ ምድረ በዳ እንዲሄድ እግዚአብሔር ትዕዛዙን የሰጠው በመልአኩ በኩል ነው። ወደ ሰረገላው ጠጋ እንዲል የመራው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው። ፊሊጶስ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ታዛዥ በመሆኑ፤ ወንጌሉን የመጀመሪያው አሕዛብ ክርስቲያን ለሆነው ለኢትዮጵያዊው የማካፈሉን አጋጣሚ ሊያገኝ ችሏል። እግዚአብሔር ያስብ የነበረው በሰማሪያ ለነበሩት ሰዎች ብቻ አልነበረም፤ የዚህን አሕዛብ ፍላጎትም አይቶ ስለነበር የፊሊጶስን ልብ ወደ ክርስቶስ እምነት እንዲመራው አድርጓል።

በምንመሠክርበት ወቅት፣ የምንጠቀምበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ኢየሱስን ለሰሚው ሰው ሊገልጽለትና ሊያሳየው ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ያሉትን ነገሮች በሙሉ ከክርስቶስ ጋር ማዛመድ አለብን፤ ምክንያቱም ከኃጢአታችን ሊያድነን የሚችለው እሱ ብቻ ነውና።

ጥያቄ 23 :-ወንጌሉን እንዲቀበል እግዚአብሔር ልቡን አዘጋጅቶት የሚያውቅ ሰውን ለምሳሌ ያህል ልትጠቅስ ትችላለህ? የወንጌሉን መልእክት ለመቀበል ልቡ ዝግጁ ወደሆነ ሰው እግዚአብሔር እንዲመራህ ጠይቀው። አንተም ለሰውዬው የምሥራቹን ወንጌል ለማካፈል ዝግጁ ሁን።

ጥያቄ 24:- ለማያምኑ ሰዎች በምትመሠክርበት ወቅት የምትጠቀምባቸውን ጥቅሶች ዝርዝር አውጣ።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ የአንድን ሰው ልብ ካላዘጋጀ ወደ ደኅንነት ልናመጣው አንችልም። በግልጽና በድፍረት ስለ ኢየሱስ ምሥክሮች እንሆን ዘንድ ነው የተጠራነው። የሰውዬውን ልብ ከፍቶ ወደ ማመን ደረጃ የማድረሱን ሓላፊነት የያዘው እግዚአብሔር ነው። የኛ ደግሞ ሐላፊነት መመሥከር ነው።

# አራተኛ ቀን:- ሳውል

እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ የወንጌሉን ምሥክርነት ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያ ብሎም ወደ አሕዛብ ለማዳረስ ሲል በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጀምሮ እያስፋፋው እንደሄደ አይተናል። ዛሬ ስለተርሴሱ ሳውል የሕይወት ታሪክ እናያለን። እግዚአብሔር በዚህ ሰውዬ ተጠቅሞ ለብዙ ሺሕ ሰዎች ወንጌሉን አዳርሷል። እንደምታስታውሰው፤ እስጢፋኖስን በድንጋይ ወግረው በገደሉት ጊዜ ሳውል በዚህ ቶሞ የነገሩን ትክክለኛነት አምኖበት ነበር። ይህ ቀናተኛ ፈሪሣዊ ጎልማሳ፤ አሁን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለአሕዛብ የሚላክ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ይሆናል።

እግዚአብሔር ብዙ ለአገልግሎቱ የሚጠቀመው ይሆናሉ ተብሎ የማይገመቱትን ነው። ወደ በኋላ ላይ እራሱን በተመለከተ ጳውሎስ «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፤ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ነኝ» ይላል (1ቆር. 15:9)። ሳውል ቤተክርስቲያንን ያሳድድ የነበረው በኋላ ላይ ደግሞ በእግዚአብሔር የተመረጠውና ጳውሎስ ተብሎ የተጠራው ሰው ለአሕዛብ የእግዚአብሔር መልእክተኛ በመሆን አገልግሏል።

ጥያቄ 25:- የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብና ስለ ጳውሎስ ሕይወት የተወሱትን ነገሮች በዝርዝር ጻፋቸው። የሐዋ. 8:1-3፤ 22:1-21፤ 25-28፤ ገላትያ 1:11-24፤ ፊሊጲስዩስ 3:4-6። ስለ ጳውሎስ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይም አንብብ።

ሳውል በኪልቂያ አውራጃ ተርሴስ በምትባል፤ በዛሬይቱ ትንሿ እስያ፥ ቱርክ ውስጥ ተወለደ። (ከዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ ካለው ካርታ ላይ ተርሴስ የት እንደምትገኝ ተመልከት)። አባቱ አይሁዳዊ ቢሆንም፤ የሮማዊ ዜግነትን አግኝቶ

የሳውል አባት ፈሪሣዊም ነበር፤ ስለዚህም ጳውሎስን የፈሪሣውያኑን ጥብቅ ሕግጋትና አስተዳደር አስተምሮታል፤ በዚህም ሥር ሆኖ እንዲያድግ አድርጓል። የአይሁድ ሕግ፤ አንድ ወንድ ልጅ ብሉይ ኪዳንን ከአምስት ዓመቱ ጀምሮ ማጥናት ይጀምር ይላል። በአሥራ ሦስት ዓመቱም «የሕግጋቱ ልጅ» ይሆናል፤ ሙሉ ለሙሉም ለአይሁድ ሕግ ሐላፊነት ይኖረዋል። ምናልባትም፤ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ፤ ያገባች እህቱ ቤት ተቀምጦ፤ በገማልያል ሥር ሆኖ ማጥናት የጀመረው በዚህ ዕድሜው ሳይሆን አይቀርም (ሐዋ. 23፡16)። ሳውል ለአይሁድ ባህል በጣም ቀናተኛ ሆነ።

ሄለናዊ የአሕዛብ ግዛት በነበረችው በጠርሴስ ማደጉ፤ ጳውሎስ ስለ አሕዛብ አኗኗር ባህል ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖረው አድርጎታል። ይህም ወደ በኋላ አሕዛብ አገር እየሄደ በሚሰብክበት ወቅት ብዙ እረድቶታል። የግሪክን፤ ዕብራይስጥንና የአረማይክ ቋንቋ በደንብ አጣርቶ ይናገር ነበር። ጳውሎስ በጣም አስተዋይ ከመሆኑ የተነሣ የዕብራይስጥንና የሄሌናዊያንን ባህል በደንብ ያውቅ ነበር።

የሳውል የቤቱ አስተዳደግና በአይሁድ ባህል መሠረት መሠልጠን ለሳውል የኢየሱስ ክርስቶንስን ወንጌል እንዲቃወምና ትክክለኛ እንዳልሆነ ነገር እንዲያየው አድርጎታል። ለአይሁድ ሃይማኖት የነበረው ቅናትና ቁርጠኝነት እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሲሞት ቆሞ እንዲመለከተውና ቤተክርስቲያንን እንዲያወድም አነሣሣው። የአይሁድን ሃይማኖት ሕግጋት በተመለከተ፤ ከሌሎቹ አይሁዳውያን የበለጠ፤ ጳውሎስ ሕጉን ያውቅና ይጠብቅ ነበር። በአይሁድ ዋነኛው ሸንጎ ውስጥም አባል እንዲሆን ተመርጧል።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 5 ላይ እንዳየነው፤ የጳውሎስ አስተማሪ ገማልያል፤ አይሁዶች በቤተክርስቲያን ላይ ያስነሡትን ስደት ጋብ እንዲያደርጉትና ትእግሥተኞች እንዲሆኑ መክሯቸዋል፤ ጳውሎስ ግን ይህን ዓይነት አመለካከት አልነበረውም። አዲሱ የወንጌል ትምህርት ከአይሁድ ሃይማኖት ጋር አለመጣጣሙን ነው ያየው። የእስጢፋኖስም መልእክት ይህን ለሳውል ግልጽ አድርጎለታል፤ ይህም ቢሆን፤ በመስቀል ላይ መሞት እርግማን በመሆኑ፤ ኢየሱስ መሢሕ ነው ብሎ ለመቀበል አልፈለገም። መሢሑም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ይሞታል ብሎ አላሰበም (1ቆር. 1፡23 ተመልከት)።

በደማስቆ መንገድ ኢየሱስ በጠራው ጊዜ ግን፤ ቀናተኛነቱ ቤተክርስቲያንን ከማጥፋት፤ የኢየሱስን የምሥራች ዜና ወደ መስበክ ተለውጧል (ሐዋ. 9)። የጳውሎስ አስተዳደግን ሥልጠና፤ ለሃይማኖት የነበረውን ቅናትና ፍቅር ያስረዳናል። ሆኖም፤ ይህ ሥልጠናው ለአይሁዳውያንና ለአሕዛብ ለሚሰጠው አገልግሎትም ዝግጁ እንዲሆን አድርጎታል። ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን እንዲመራ የሚመርጠው ዓይነት ሰው ነው። ስለዚህ ሰው ሕይወት የተሟላ ማብራሪያ ለማግኘት «የጳውሎስ ሕይወትና አገልግሎት» የሚለ‑ን መጽሐፍ ተመልከት።

ጥያቄ 26፡- ከ፡ ውሎስ ሕይወት ውስጥ፤ ለአሕዛብ ሐዋርያት እንዲሆን ዝግጁ ያደረ ትን ነገሮች ዘርዝር።

ስለዚህ ሰው ሕይወት የተሟላ ማብራሪያ ለማግኘት «የጳውሎስ ሕይወትና አገልግሎት» የሚለውን መጽሐፍ ተመልከት።

ጥያቄ 26:- ከጳውሎስ ሕይወት ውስጥ፤ ለአሕዛብ ሐዋርያት እንዲሆን ዝግጁ ያደረጉትን ነገሮች ዘርዝር።

ጥያቄ 27:- እግዚአብሔር በሕይወትህ ከሠራቸው ሥራዎች ውስጥ፤ ለእርሱ ላለኝ አገልግሎት ይጠቅማሉ ብለህ የምታስባቸውን ነገሮች ዘርዝር።

# አምስተኛ ቀን:- የክለሳ ጥያቄዎች

ትምህርቱን ከልስና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

1. የእስጢፋኖስ መልእክት አይሁዶቹን እንዲህ ያናደዳቸው ለምንድነው?
2. በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ላይ፤ ከባድ ስደት እንዲነሣ ያደረገው ክንዋኔ ምንድነው?
3. ሀ) ሳምራውያንና አይሁዳውያንን የሚያመሳስላቸው ነገር ምንድነው? ለ) የሳምራውያኖቹ አምልኮ ከአይሁዳውያኑ ይለይ የነበረው እንዴት ነው?
4. ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌሉን ይዞ ወደ ሳምራውያኑ የሄደው ማን ነው?
5. ሲሞንን መንፈስ ቅዱስን እንዲፈልግ ያነሣሣው ሐሳቡ ምን ነበር?
6. ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወንጌሉን እንዲህ በቶሎ ሊቀበል የቻለው ለምንድነው?
7. የጳውሎስ አስተዳደግና ሥልጠና ለአገልግሎቱ ምን ዓይነት ዝግጅት ነው ያስገኙለት?
8. እግዚአብሔር በአገልግሎቱ ሊጠቀምባቸው የሚችለው እነማንን ነው?

ለሳምንታዊው ስብሰባ ለመዘጋጀት ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄዎች ተመልከት።

1. የአምልኮ ጊ ዜ　　3. ክለሳ

2. ጸሎት　　4. ውይይት:-

ሀ) እግዚአብሔር ስደትን ለወንጌል ማሠራጫነት እንዴት ሊጠቀምበት እንደሚችል ተወያዩ። እንደ ምሳሌ ከቤተክርስቲያንህ ታሪክ ላይ ጥቀስ።

ለ) 1. የድንቁና የተአምራቱ ዓላማ ምን ነበር? 2. ዛሬ ተአምራት የሚሠሩ ሰዎችን በጥንቃቄ መመርመር ያለብን ለምንድነው?

ሐ) ሳምራውያኑ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን እንዴት እንደተቀበሉ ተወያዩ። 1. በጴጥሮስ በኩል ብቻ የተከናወነው ለምንድነው? 2. መጀመሪያ እንዳመኑ፤ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ያልሰጣቸው ለምንደነው? 3. መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው አንድ ሰው በክርስቲያኑ ላይ እጁን ሲጭን ነው ወይም ከደህንነት በኋላ

የሚከናወን ሁለተኛ ሥራ ነው ብለው ለሚያምኑ ክርስቲያኖች ምን ዓይነት መልሶች ነው የምትሰጡት?

መ) 1. ለማያምን ሰው፤ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበቡ ብቻ ክርስቶስን እንዲያውቅ በቂ ያደርገዋል? ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከዚህ ሌላ ምን አስፈልጎት ነበር? ይህንን ሰፋ አድርጋችሁ አብራሩት። 2. ለማያምን ሰው ስትመሠክር ልትጠቀምባቸው የሚገቡህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በዝርዝር ጻፋቸው።

5. ጸሎት፡-

# ትምህርት 7

የሐዋርያት ሥራ 9፡1-43

## የመጀመሪያ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 9፡1-18

በቤተክርስቲያን ዕድገት ላይ ትልቅ ሚና ከተጫወቱት ሰዎች አንዱ ጳውሎስ ነው። ሆኖም፤ በመጀመሪያ አካባቢ ይህ ሰው በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ላይ የተነሣውን ስደት ይመራ የነበርና፤ በየቤቱ እየሄደ በር እያንኳኳ ክርስቲያኖችን በመውሰድ ወኅኒ ቤት ያስገባ የነበረ ነው። ይህም አማኞቹን በየአጎራባቾች ከተሞች በይሁዳና በሰማርያ እንዲበታተኑ አድርጓቸዋል። ባለፈው ሳምንት ግን፤ እግዚአብሔር እንዴት በዚህ ስደት ተጠቅሞ የወንጌሉ መልእክት በይሁዳና በሰማሪያ እንዲሰብክ እንዳደረገ አይተናል። የተሰደዱትም ክርስቲያኖች በየሄዱበት ቦታ ሁሉ የወንጌሉን መልእክት ይዘው ነው የሄዱት።

በታሪክ ውስጥ ከተከናወኑት ነገሮች ዋነኛ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው። ወደ ምድር መጥቶ የሞተውና እንደገና ደግሞ ከሙታን የተነሣው የራሱ አካል የሆነችውን፤ ቤተክርስቲያንን ለመመሥረት ነው። ከሞት ከተነሣና ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ በአማኞች ልብ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መኖር ጀመረ።

ኢየሱስ በምድር ላይ ከሠራው ሥራ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ለአሕዛብ መልእክተኛ የሆነው የሳውል መለወጥ ነው። ሳውል ወይም በግሪክ ቋንቋ ሲጠራ ጳውሎስ፤ ኢየሱስን በደማስቆ መንገድ ላይ ካየ በኋላ ሙሉ በሙሉ ተለውጧል። የክርስትና ቀንደኛ ጠላት ከመሆን፤ ሐዋርያ ወደመሆንና ብሎም እርሱን አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ሊለውጥ ችሏል። ለክርስትና እምነት እውነተኛ መሆን አንዱ ማስረጃ ይህ በክርስቶስ አማካኝነት አዲስ ፍጥረት የመሆን ነገር ነው። ብዙዎቻችን ከአሕዛብ ወገን በመሆናችን፤ ጳውሎስ ደግሞ የአሕዛብ መልእክተኛ በመሆኑ በጣም ባለውለታችን ነው። በእርሱ በኩል፤ ክርስትና የአይሁድ ሃይማኖት አንድ ቅጥያ ከመሆን፤ ዓለም አቀፍ ሃይማኖት ሊሆን

ችሏል። ለዚህም ሲባል የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሕይወቱና ስለ ሥራው ዘርዝር ያለ ማብራሪያ ይሰጠናል።

የሐዋርያት ሥራ 9:1-43 አንብብና ለእነዚሕ ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጥያቄ 1 ሀ) ሳውል ወደ ደማስቆ ይሄድ የነበረው ለምንድነው? ለ) የዓይን ብርሃን ካገኘ በኋላ ሳውል ምን አደረገ? ሐ) ጴጥሮስ አገልግሎቱን ያካሂድ የነበረው የት ነው? ጥያቄ 2 የሐዋርያት ሥራ 9: 1-18 እንደገና አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ። ሀ) 1. ወደ ደማስቆ ይጓዝ በነበረበት ወቅት፣ ሳውል ምን ሆነ? 2. ክርስቶስ ለሳውል እራሱን የገለጸው እንዴት ነው? ለ) ሳውል ለሦስት ቀን ያህል ዐይነ ስውር የነበረው ለምን ይመስልሃል? ሐ) ሐናንያ የጌታን ትዕዛዝ በተመለከተ ጥያቄ ያቀረበው ለምንድነው?

እስጢፋኖስ ከሞተ በኋላ፣ ሳውል በሙሉ ኃይሉ ቤተክርስቲያንን የማጥፋት ሥራውን ቀጥሎበታል። ወደ ደማስቆ ሄዶ ክርስቲያኖቹን በሙሉ ወደ ኢየሩሳሌም ካመጣ በኋላ ወኅኒ ቤት አስገብቶ በመጨረሻ እንዲገድላቸው ከሊቀካህኑ ፈቃድ አግኝቶ ነበር። ደማስቆ ከኢየሩሳሌም በ 150 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ነበር የሚገኘው። ካሁኑ ክርስትና በአይሁዶች መካከል እስከዚህ ታላቅ ከተማ ድረስ ተዳርሶ ነበር፣ ጳውሎስም ይህንን ዕድገቱን ለማቆም ነበር የሚፈልገው።

ሆኖም፣ ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ ሲሄድ እግዚአብሔር በልብ ሳይናገረው አልቀረም። እስጢፋኖስ ለሄሌናውያኑ አይሁዶች አቅርቦት የነበረውን የመከላከያ ቃል በማሰብ ላይ ሳለ፣ ሳውል ምናልባት እስጢፋኖስ የተናገራቸውን ብዙ ነገሮች መቀበል አለብኝ ብሎ ሳያስብ አልቀረም። ይሁን እንጂ እስጢፋኖስ በሰማያት በክብር ፊቱ እንደዚያ በርቶ ሲሞት፣ ሳውል በመሞቱ ተስማምቶ ነበር። ሳውል እስጢፋኖስ በታላቅ ድምፅ «እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ ብሎ ሲጮህ ሰምቶታል። ታዲያ ይህ ሁሉ በሳውል አእምሮ የሐሳብ ፍጭት ፈጥሮበታል።

ጥያቄ 3:- ሐ) በማያምኑ ሰዎች ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንድነው? ለ) በማያምኑ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚሠራው እንዴት ነው? ሐ) መንፈስ ቅዱስ በአንተ ሕይወት ውስጥ እንዴት አድርጎ ነው የሠራው?

የደማስቆ መንገድ ከኢየሩሳሌም የስድስት ቀን መንገድ ነው፣ በዚህም ወቅት እየተጓዘ ሳለ ሳውል ብዙ ሳያስብ አልቀረም። ወደ ከተማዋ እየተቃረቡ ሳለ ታላቅ ብርሃን ከሰማያት ላይ ታየ። ሳውል መሬት ላይ ወደቀ፣ ሳውል ሳውል:- ስለምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። በማንኛውም ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሲሰደዱ፣ የቤተክርስቲያን ራስ የሆነውም ኢየሱስ ክርስቶስ ይሰደዳል። ሳውል የአብርሃምን፣ የይስሐቅንና የያዕቆብን አምላክ ለመከተል ቀናተኛ የነበረ ጎልማሳ ስለነበር፣ ይህን ሲሰማ ታላቅ መገረም ውስጥ ሳይገባ አልቀረም። ሳውልም «ጌታ ሆይ አንተ ማን ነህ?» ብሎ ይጮሃል። ድምፁም «አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ» አለ። ሳውል ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስ ክርስቶስን በራዕይ አየው፣ ይህም የሕይወቱን ዓላማ ለወጠው።

በሳውል ቁርጠኛና ዕርጋታ የሌለበት ልብና አእምሮ ውስጥ ይመላለሱ የነበሩት ሐሳቦች በድንገት ምላሻቸውን አገኙ፤ ሳውልም ያሳድደው ለነበረው ለክርስቶስ እራሱን አሳልፎ ሰጠ። ሳውል ሞቷል ብሎ ይገምተው የነበረው የናዝሬቱ ኢየሱስ ሕያው ነው፤ በዚህም የሳውል ስሕተት ቁልጭ ብሎ ተገለጸ።

ኢየሱስ ሳውልን «ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል» አለው። ኢየሱስ ሳውል ሊሄድበት ወደ አሰበው ከተማ ነው የላከው፤ አሁን ግን የተለየ ዓላማ ነው የያዘው። ሳውል ዐይነ ስውር በመሆኑም፤ ሳይደናቀፍ አልቀረም። ለእርሱ ወደ ደማስቆ መግባት ሳይከብደው አልቀረም፤ ምክንያቱም ክርስቶስን ይቃወሙ የነበሩ ብዙ ሰዎች ቤተክርስቲያንን የማሳደድ ተግባራቸው ላይ ይረዳናል ብለው ይጠብቁት ነበርና ነው። ያለምንም ጥርጥር ክርስትናን አላጠፋም ብሎ በመነሣቱ በጣም ሳይናደዱበት አልቀሩም። ይሁን እንጂ፤ ከወደቀበት ተነሥቶ፤ ለአዲሱ ጌታው በመታዘዝ መንገዱን ቀጠለ።

ለሦስት ቀን ያህል፤ አልበላም አልጠጣም፤ እንደታወረም ቆየ። እነዚያ ሦስት ቀናት ለሳውል እንደገና መለስ ብሎ የሕይወቱን ዓላማ እንዲመዝንና እንዲመረምር አድርገውታል። ምናልባትም በደንብ ያውቃቸው የነበሩትን የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች እያሰላሰለ፤ ለብዙ ዘመን ይጠበቅ የነበረው መሢሕ እውነት ኢየሱስ እንደሆነ ሳይገነዘብ አልቀረም።

ሳውል ታውሮ በጨለማ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ፤ እግዚአብሔር ወደ ጳውሎስ እንዲሄድ ሐናንያን ያዘጋጃል። ሐናንያ ሳውል ወደ ደማስቆ ስለሚመጣበት ዓላማ ሰምቶ ስለነበር፤ ተጠራጠረ። ጌታ ግን «ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእሥራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው፤ ሂድ» ይለዋል። በሐዋርያት ሥራ ጥናታችን ይህ ትንቢት በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደተፈጸመ እናያለን። እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ስም ሳውል መከራ እንደሚቀበልም ለሐናንያ ገልጾለታል። ስለ ሐናንያ ብዙም ባናውቅም፤ የእግዚአብሔር ደቀመዝሙርና በሳውል ሕይወት መልእክተኛ ነበር። ምንም እንኳ ሐናንያ ሳውልን ለመጎብኘት ጥርጣሬ ቢያድርበትም፤ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ታዛዥ በመሆን፤ ለቤተክርስቲያን ዕድገት በጣም ጠቃሚ የሆነ አስተዋፅኦ ያደረገውን ሰው ዓይን ለመክፈት የራሱን ድርሻ ተወጥቷል።

ጥያቄ 4፡- እግዚአብሔር ለአንድ ሰው እንድትመሠክር ወደ ሰው መርቶህ ያውቃል? ወይም በችግር ውስጥ ከተጠመደ አማኝ ጋር እንድትነጋገር አድርጎሃል? የሁኔታዎቹን አኳኋንና ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ታዛዥ መሆን ወይም አለመሆንን በዝርዝር ግለጽ።

ወዲያውኑም ገና ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ለሐናንያና ለሳውል ሊሠራ ያለውን ዋነኛ ሥራ ይነግራቸዋል። ለአይሁዶች ወይም የአይሁድን ሃይማኖት የሚከተሉትን ከማገልገል ፈንታ፤ ጳውሎስ አሕዛብን ነበር የሚያገለግለው። አይሁዶች አሕዛቦች ከእግዚአብሔር ዕቅድ ውጭ የሆኑ ናቸው ብለው ያስቡ ስለነበር፤ በጣም ይጠሏቸው ነበር። እንዲያውም፤ ለዘላለም ፍርድ የተጋለጡ ናቸው ብለውም ያስቡ ነበር። ነገር ግን

እግዚአብሔር የነገድ አምላክ የአይሁዶች ብቻ አምላክ አይደለም። እሱ ሁሉንም ሰው የፈጠረ አምላክ ነው እንጂ። ሁሉንም በአንድ ዓይነት መልክ ያፈቅራቸዋል። ስለዚህም፤ ወንጌሉን ለአሕዛብ እንዲከፍትለት እግዚአብሔር ጳውሎስን እንደ መሣሪያ ይጠቀምበታል። ብዙዎቻችን ዛሬ ከአሕዛብ ወገን በመሆናችን፤ በክርስቶስ ውስጥ አይሁድ ወይም ግሪክ የለም ሁሉም አንድ ነው የሚለውን ወንጌል ጳውሎስ ለኛ በማብሠሩ፥ ለኛ በጣም ባለ ውለታችን ነው። እንደ ክርስቶስ አካልነታችን ከኢኮኖሚና ከዘር ልዩነቶች በላይ ይህንን አንድነታችንን ልናንፀባርቅ ይገባናል።

ጥያቄ 5፡- ሀ) ወንጌሉ በኢትዮጵያ ውስጥ የዘርና የብሔረኝነትን ልዩነት ያስወገደው እንዴት ነው? አንዳንድ ገጠመኞችን ለማብራሪያ ያህል ጥቀስ። ለ) በቤተክርስቲያን አሁንም ገና ልናስወግዳቸው የሚገቡን፤ በዘረኝነት የመጡ ችግሮች ምንና ምንድናቸው?

ሐናንያን በተመለከተ ጳውሎስ «በዚያም የኖሩት አይሁድ ሁሉ የመሠከሩለት እንደ ሕጉም በጸሎት የተጋ ሐናንያ የሚሉት አንድ ሰው ነበር» ብሏል (ሐዋ. 22፡12)። እግዚአብሔር ባሉን ችሎታዎችና በነበረን የአስተዳደግ መሠረት ይጠቀማል። ልክ እንደ ሳውል፤ ሐናንያ ዕብራዊ ነበር እንጂ ሄለናዊ አልነበረም፤ ስለዚህም ከዕብራዊያን ዕብራዊ የነበረውን ሳውልን ሊያነጋግር ችሏል (ፊሊጵ. 5-6)።

እግዚአብሔር ሲናገረው ሐናንያ «ጌታ ሆይ እነሆኝ» ብሎ ይመልስለታል። ምንም እንኳ ስለ ሳውል የሚያውቅ፤ ወደ ደማስቆ የመጣበትን ዓላማ የተረዳም ቢሆን፤ ሄዶ የመያዝ ሁኔታ ሊያጋጥመው እንደሚችል እየተሰማው ለእግዚአብሔር ታዛዥ በመሆን ተነሥቶ ቅን መንገድ ላይ ወደሚገኘው ወደ ይሁዳ ቤት ይሄዳል። እጁንም በሳውል ላይ ጭኖ «ጌታ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው፤ ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ» ይለዋል።

ሐናንያ ይህን ነገር እንደተናገረ ሳውል የዓይኑ ብርሃን ይመለስለታል። ተነሥቶም ይጠመቃል፤ ከዚያን ጊዜ ወዲህም የጳውሎስ ሕይወት ያሳድደው ለነበረው ለኢየሱስ ሙሉ በሙሉ የተሰጠ ሆነ።

ጥያቄ 6፡- ሀ) የአንተ ሕይወት ከሐናንያ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

የእግዚአብሔር ምሪት እንዳለበት ተሰምቶህ ከፍርሃት የተነሣ ሳትታዘዘው የቀረኸው ነገር ካለ፤ አሁኑንእግዚአብሔር እንድትፈጽመው ለጠየቀህ ነገር ኃይሉንና ብርታቱን እንዲሰጥህ በጸሎት ጠይቀው። ለ) ለክርስቶስ ሕይወትህን አሳልፈህ ስትሰጥ፤ ልክ እንደ ጳውሎስ ሙሉ በሙሉ ነው አሳልፈህ የሰጠኸው? በደንብ ግለጽ። ኢየሱስን ለመከተል ሙሉ በሙሉ ሕይወትህን አልሰጠህ እንደሆን፤ እሱ የሚያዝህን ማንኛውንም ለማድረግና እሱ የሚፈልግበት ቦታ ለመሄድ በጸሎት አማካኝነት ቃል ግባ።

የጠርሴሱ ሳውል ወይም በደንብ በሚታወቅበት ስሙ የሀዋርያው ጳውሎስ መለወጥ የወንጌሉ መልእክት «እስከ ምድር ዳር» የሚሄድበትን ጊዜ ጀምሮታል። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ፤ ይህ በጣም ዋነኛ የሆነ ክንዋኔ ነው። ስለ ክርስትና

ራዕይ ነው። ዛሬ ደግሞ፣ እግዚአብሔርን በሰጠን የእምነት ስጦታ ከሙታን የተነሣውን ክርስቶስን ልናይና አዲስ ፍጡሮች ልንሆን ችለናል። ስለዚህ ለውጥ ሊያስገኝልኝ የሚችለው ክርስቶስ ብቻ ነው።

ጥያቄ 7፡- በክርስቶስ አዲስ ፍጡር ነህ? በሕይወትህ ውስጥ ለውጥን ያስገኘው እንዴት ነው?

# ሁለተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 9፡19-31

ለአይሁድ ባህልና ሕግ ቀናተኛ የነበረው ጎልማሳው ፈሪሣዊ ሳውል፣ ክርስቲያኖችን ሊይዝ ወደ ደማስቆ እያመራ ነው። በድንገት ግን፣ ከሙታን የተነሣውን ጌታ ኢየሱስን በመንገዱ ላይ ያየዋል። ሳውልም ወዲያውኑ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚዋጋ ይገነዘባል። ወደ በኋላም ኢየሱስ ለሳውል ያለውን ዕቅድ ይነግረዋል፣ ይህም የመመሥከርና መከራ የመቀበሉን ሁኔታ ነው።

ከሱ ጋር ከተገናኘን በኋላ እንደምንረዳው፣ ጌታ ለፈጠራት ሕይወት በሙሉ ዓላማ አለው። መንፈስ ቅዱስ እኛን ለማሳመን ሲል፣ ወደ ክርስቶስ እስክንመጣ ድረስ ምንም ዕረፍት አይሰጠንም። ከዚያም፣ ልክ በሳውል ሕይወት ውስጥ እንዳደረገው፣ እንቅፋት በሆኑ ነገሮች ውስጥ እንድናልፍ ያደርገናል። ሁላችንም በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ቦታ አለን፣ ልዩ በሆነ ሁኔታም ለመንግሥቱ ሊጠቀምብን ይፈልጋል። መከራ መቀበልም ቢሆን እርሱ በኛ እንዲጠቀምብን ፈቃደኞች ነን?

የሐዋርያት ሥራ 9፡19-31 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 8 ፡- ሀ) ሳውል በደማስቆ ከማን ጋር ነበር የቆየው? ለ) ሳውል የመሠከረው የት ነው? ሐ) አይሁዶች የሳውልን መልእክት እንዴት ነው የተቀበሉት? መ) ሳውል ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ፣ ደቀመዛሙርቱ የሰጡት ምላሽ ምን ዓይነት ነው? ሠ) ለደቀመዛሙርቱ ስለ ሳውል መረጃ የሰጠውና እንዲቀበሉት የጠየቀው ማነው? ረ) የእስጢፋኖስን ሥራ ሳውል የቀጠለው እንዴት ነው? (ቁ. 29)። ሰ) ክርስቲያን ወንድሞችን ወደ ቂሣርያ የወሰዱት ለምንድነው? ሸ) አብያተ ክርስቲያናትን በማበረታታትና በመርዳት እንዲታነጹና እንዲያድጉ ያደረገው ማነው?

ሳውል ከተለወጠና ከተጠመቀ በኋላ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፣ በደማስቆ ይገኙ የነበሩ ምኩራቦች ውስጥ መስበክ ጀመረ። ክርስቲያኖችን ወኅኒ አስገብቶ እንዲሰጣ የሚይፈልገው የነበረው መልእክት ይህ ነበር። ነገሮች እንዲህ መለወጣቸው አይሁዳውያኑና ክርስቲያኖቹንም በጣም አስደንቋል። አይሁዳውያን ክርስትናን ለማጥፋት የመጣ ነው የመሰላቸው። ሁለቱም ወገኖች በጳውሎስ አልተማመኑም ነበር። ሆኖም ከብዙ ቀናት በኋላ የሳውል መልእክት ኃይል ኖሮት አሳማኝነት ደረጃ ላይ መድረሱን ሲያዩ አይሁዶች ሊገድሉት ተነሡ።

ጥያቄ 9፡- ገላትያ 1፡16-18 አንብብ። በሐዋርያት ሥራ 9፡23 ላይ «ብዙ ቀን የሚለው ለምን ያህል ጊዜ ነበር? ጳውሎስ ተለውጦ ኢየሩሳሌም እስኪሄድ ድረስ ምን ያህል ጊዜ ነው የፈጀው?

ጥያቄ 10፡- 2ቆሮ. 11፡32-33 አንብብ። የጳውሎስ ጠላቶች ምን ለማድረግ ነው ያቀዱት?

በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ የሁኔታዎችን ቅደም ተከተል ለመረዳት ስንል፤ ገላቲያንና 2ቆሮ. መመልከት ይኖርብናል። በሐዋ. 9፡23 «ብዙ ቀንም» የተባለው የሦስት ዓመት ጊዜ ሲሆን፤ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ጳውሎስ ብዙ ጊዜውን ያሳለፈው በአረብ አገር ነበር። ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ ወደ ዓረብ አገር እንደሄደ ይናገራል። ከዓረብ አገርም ወደ ደማስቆ ተመልሶ እሱን ለመግደል እስካሰቡበት ጊዜ ድረስ በዚያ ሆኖ ይሰብክ ነበር። ሊገድሉት እንደተስማሙና የከተማይቱን በሮች ጠላቶቹ እንደሚጠብቁ ሲሰሙ ደቀመዛሙርቱ በቅጥሩ ላይ አሳልፈው በቅርጫት አወረዱት። ጳውሎስ ከተለወጠ ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሄደም ይናገራል።

ክርስቶስ ለሳውል የሰጠው ተልእኮ፤ በአሕዛብ በነገሥታትና በእሥራኤል ልጆች ፊት የእርሱን ስም የመሸከም ነበር (ሐዋ. 9፡ 15)። ሦስት ዓመታት አለፈዋል፤ በደማስቆ በሚገኙ ምኩራቦች ውስጥ ምሥክር ከመሆን ሌላ፤ ጳውሎስ ይህንን ተልእኮውን ሊፈጽም አልቻለም። በዓረብ አገር ሦስት ዓመት ያህል አሳልፎአል። በደማስቆም የተካሄው ተቃውሞ፤ ለሽሽቱ መንሥኤ ሆኗል። ጳውሎስ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላም ከደቀመዛሙርቱ ጋር ሊቀላቀል ሞከረ፤ ግን አሁንም እሱን ይፈሩና ምሥክርነቱን ይጠራጠሩ ነበር።

በኢየሩሳሌም የነበሩት ደቀመዛሙርት ጳውሎስ ሳይቀበሉት ሲቀሩ፤ የመጽናናት ልጅ የነበረው በርናባስ ወደ ሐዋርያቱ ይዞት ይሄዳል። ሳውል ጌታን እንዴት በደማስቆ መንገድ ላይ እንዳየውና ያለፍርሃት በኢየሱስ ስም ይሰብክ እንደነበርም ያስረዳቸዋል። በዚህም ምክንያት ሳውል ከሐዋርያቱ ጋር ሆኖ በድፍረት ይሰብክ ነበር። ከግሪክ አይሁዶችና እስጢፋኖስን ከወገሩት ሄለናውያን ጋር ይነጋገርና የጦፈ ክርክር ውስጥ ይገባ ነበር። ሄለናውያንም እራሳቸው ጳውሎስን ሊገድሉት ሞክረዋል። ክርስቲያን ወንድሞቹ ይህን ባወቁ ጊዜ ወደ ቂሣርያ ወስደው፤ ወደ ትውልድ ሥፍራው ወደ ጠርሴስ እንዲሄድ አድርገዋል። አሁንም እንደገና፤ ሳውል ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስን የመመሥከር ጥረቱ ይደናቀፍበታል። የሕዝቦቹ የአይሁዳውያን ሽብርተኛ መሆን፤ ከጊዜ በኋላ ወደ አሕዛብ አገር እንዲሄድ ያደርገዋል፤ ሕይወቱንም በሙሉ የራሱ ሕዝቦች እንደተቃወሙት ቆይተዋል።

ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ከጌታ ጋር መገናኘቱ ሦስት ነገሮችን እንዲቀበል አድርጎታል። 1. ከዚህ ቀደም ቤተክርስቲያንን የሚቃወም የነበረው ቀናተኛነት የተሣሣተ ነበር። ከመንግሥተ ሰማያት የመጣ ድምፅ አርሞታል። የመጨረሻ ሥልጣን አለው ብሎ የሚገምተው የሙሴ ሕግ ሰዎችን በእምነት ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ነው እንጂ ለደኅንነት የሚያበቃቸው አይደለም (ገላ. 3፡19-24)። 2. ሳውል ያሳድደው የነበረው ኢየሱስ ከሙታን ተነሥቷል፤ ሕያው ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱ

እንደ እርኩስ አያስቆጥረውም፤ እሱ የሰዎችን ኃጢአት ለማስወገድ በእግዚአብሔር የተመረጠና ትንቢቶችን የፈጸመ ነው። የክርስቶስ ከሙታን መነሣት እራሱ የትንቢት ፍጻሜ ሲሆን፤ ለሚያምኑት ደግሞ በክርስቶስ በኩል አዲስ ሕይወት እንደሚያገኙ ማረጋገጫ ይሆናቸዋል (1ቆሮ. 15፡1-4)። 3. ጳውሎስ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን በኢየሱስ ክርስቶስ መመረጡን በደንብ አረጋግጧል (ሮሜ 11፡ 13፤ 15፡16 ተመልከት)።

ጳውሎስ፤ አሕዛብና አይሁዶች ማዳን በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ መኖሩን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጠው ራዕይ፤ እንደገለጸለት ይናገራል (ገላ 1፡11-12 ኤፌ 3፡2-3)። ሆኖም፤ ልክ እንደ አይሁዶች አሕዛብንም በእምነት ወደ ክርስቶስ አካል ሲገቡ፤ በግልፅ ሊገነዘበው ችሏል። የሳውል የቀድሞው ጓደኞቹ ጠላት ሆነው ሊገድሉት ተነሡ፤ ያሳድዳቸው የነበሩት ጠላቶቹ ደግሞ ወዳጆቹ ሆኑ።

ጳውሎስ ወዲያውኑ መመስከሩ፤ እምነቱንና ውሳኔውን አጠንክሮለታል። አዳዲስ ክርስቲያኖችን ልናበረታታቸው የሚገባን ነገር ቢኖር ቶሎ ብለው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመሠክሩ ማድረግ ነው። ለክርስቲያኖች ኢየሱስ በሕይወታቸው ስላደረገው ነገር መናገር አለባቸው። በተጨማሪም ክርስቲያን ላልሆኑት ጓደኞቻቸውም፤ ስለ አዲሱ እምነታቸው ሊነግሯቸው ይገባል። ብዙ ጊዜ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት የሚችሉት በእነዚህ መጀመሪያ ቀናት ላይ ነው።

ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለማገልገል የነበረው ምኞት በብዙ መሰናክሎች ተደናቅፎበት ነበር። እግዚአብሔር ግን በእነዚህ መሰናክሎች በመጠቀም፤ ጳውሎስን ለታላቅ አገልግሎት እያዘጋጀው ነበር። ይህ በዓረብ በረሃ ያሳለፈው ጊዜ፤ የቀድሞውን እምነቱን ዞር ብሎ በአንክሮ እንዲያየውና ክርስቶስ በሞቱና በትንሣኤው የመሠረተው አዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስና ኢየሱስ በራዕይ በመጠቀም እሱን ያስተማሩበት ጊዜ ነው።

ጥያቄ 11፡- ሀ) እግዚአብሔር የማይጠቀምብህ መስሎህ የታየህ ጊዜ በሕይወትህ ውስጥ ተከስቶ ያውቃል? ለዚህ ያንተስ ምላሽ ምን ነበር? ለ) እግዚአብሔር ለጳውሎስ ሕይወት ካደረገው ነገር ምን ብትማር ትችላለህ?

ጳውሎስ አገልግሎቱን ይጀምር ዘንድ ለምን ይህን ያህል ጊዜ ፈጀ? ይህ ሁሉ በአገልግሎቱ መዘግየትና በሕይወቱ ላይ እንዲህ አደጋ ላይ መጋለጡ ለምንድነው? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን። እግዚአብሔር በዚህ ጎልማሳ ፈሪሣዊ ሕይወት ውስጥ ሙሉ በሙሉ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከመጠቀሙ በፊት የሚሠራባቸው ነገሮች ነበሩት። እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ያለውን ዓላማና ዕቅድ በተመለከተ የጳውሎስ ግንዛቤ በትክክለኛ አቋም ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባዋል። ጳውሎስ ይህን ተልእኮውን በብቃት ሙሉ ኃይሉን ተጠቅሞ ለሚሟላት ታጥቆ በተነሣበት ወቅት፤ ለመስበክ፥ መልእክቶቹን ላመጻፍ፥ ቤተክርስቲያኖችን ለመመሥረትና መሪዎችን በማሠልጠን የቤተክርስቲያንን ዕድገት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ ዝግጁ ነበር።

አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችን እግዚአብሔር ይህን ሥራ እንድንሠራ ነው የጠራን ብለን የምናምንበት ነገር በትዕግሥት ፀንተን ለመሥራት የማንችልበት ወቅት አለ። ነገሮች እስኪስተካከሉልን ድረስ መጠበቅ በጣም ከባድ ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያስተምረን የሚፈልገው ነገር አለ። እንድንሠራው የሰጠንን ሥራ በብቃት እንሠራ ዘንድ፤ ዝግጅት ያስፈልገናል።

ጥያቄ 12 ፡-ሀ) በዛሬ ጊዜ ክርስቲያን በመሆናችን አዳዲስ ጠላቶችና ወዳጆች ልናፈራ የምንችለው እንዴት ነው? ለ) ክርስቶስን መቀበላችን፤ የወዳጆቻችንን አመለካከት የሚለውጠው ለምንድነው? ሐ) አዳዲስ ክርስቲያኖች ወዲያውኑ ዋና ዋና የሆኑ የአገልግሎት ሐላፊነቶች ሊሰጣቸው የማይገባ ለምንድነው?

# ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 9፡ 32-43

እግዚአብሔር ባዘጋጀለት አገልግሎት ጳውሎስ ዝግጁ እንዲሆን በሕይወቱ ውስጥ ይሠራ በነበረበት ወቅት፤ በጴጥሮስም ሕይወት ውስጥ ይሠራ ነበር። ለአይሁዳውያን የተሰየመ ሐዋርያ በመሆኑ፤ የጴጥሮስ ዋነኛው አገልግሎት ለአይሁዳውያን ነበር። የዚህም ሐዋርያት የማስተማርና የመፈወስ አገልግሎት እስካሁን ድረስ በሥራ ላይ እየዋለ ነበር። በዚህ መሠረት ጴጥሮስ በይሁዳ ውስጥ በመዟዟር ክርስቲያኖችን ያበረታታና የታመሙትን ይፈውስ ነበር (ሐዋ. 2፡42)።

የጥንቷ ቤተክርስቲያን ብዙ ትግሎችና ተቃውሞዎች ደርሰውባታል። በአይሁዳውያንና በአሕዛብ መካከል የነበረውን ክፍፍል ሙሉ በሙሉ ከመወገዱ በፊት ብዙ ዓመታት አለፉ። እልባት ሊገኝላቸው የሚገቡ ሌሎች ቅራኔዎችም ነበሩ። ይህንንም በጴጥሮስ ሕይወት ጥናታችን በዛሬው ዕለት እናየዋለን። ሁሌም ቢሆን፤ በተለያዩ ቅራኔዎች ላይ በቤተክርስቲያን ውስጥ ውጥረት ነበር። በክርስቶስ ማደጋችን የሚገለጸው፤ እነዚህን ክፉ ቅራኔዎች ክርስቶስ እንደሚያያቸው አይተን ስንለወጥ ነው። የወንጌሉም እውነተኛነት የሚረጋገጠው፤ አንድ ክርስቲያን ይጠላቸው የነበሩትን ሰዎች ለማፍቀር ባለው ችሎታ ነው።

ጥያቄ 13፡- ሀ) በቤተክርስቲያንህ ወይም በምትኖርበት ኅብረተሰብ ውስጥ ምን ዓይነት ቅራኔዎች ናቸው ያሉት? ለ) ቅራኔው የቤተክርስቲያንን ምሥክርነት የሚያጠፋ ነው?

የሐዋርያት ሥራ 9፥32-43 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 14፡- ሀ) ጴጥሮስ በየቦታው ይዞር የነበረው ለምንድነው? ለ) በልዳና በሰሮና ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ወደ ጌታ ዞር ያሉት ለምንድነው? ሐ) ጣቢታ አገልግሎቷ ምን ነበር? የምትኖረውስ የት ነው? መ) በልዳ ሳለ ጴጥሮስ ሰዎች የላኩት እነማን ናቸው? ወደ እርሱ ሰዎች የላኩት ለምንድነው? ሠ) ጣቢታ በመዳኗ ምክንያት የተገኘው ውጤት ምንድነው? ረ) ጴጥሮስ በኢዮጴ ሳለ ከማን ጋር ይኖር ነበር?

ጴጥሮስ ከኢየሩሳሌም በ 20 ኪ. ሜ. ርቀት ላይ ወደምትገኘው ልዳ ወደምትባል አገር ክርስቲያኖች ለመጎብኘት ይሄዳል። በልዳም ለስምንት ዓመት ያህል ሽባ ሆኖ በአልጋ የኖረ ኤንያ የሚሉት ሰው ነበር። ጴጥሮስ ሰውዬውን ፈወሰው፤ ይህንንም ያዩ በሙሉ አመኑ ወደ ጌታም ተመለሱ። ይህ ተአምራት ለታላቅ አገልግሎት በር የከፈተና የክርስቶስን ሥልጣን የገለጸ ነው።

በልዳ ሳለም ጴጥሮስ ወደ ኢዮጴ እንዲመጣ ጥሪ ደረሰው። ኢዮጴ በሜድትራኒያን አካባቢ የምትገኝ፤ ከኢየሩሳሌም በ50 ኪ. ሜ. ርቀት ላይ ያለች ከተማ ናት። ስሟ በግሪክ ቋንቋ ትርጓሜው ዶርቃ ማለት የነበረ ጣቢታ የምትባል የክርስቶስ ደቀመዝሙር ታማ ሞታ ነበር። ክርስቲያኖቹ የታመሙትን በእምነት የመፈወስ ስጦታ ለጴጥሮስ እንደተሰጠው በሰሙ ጊዜ፤ ወደ ጴጥሮስ መልእክት ይልካሉ። ጴጥሮስ በዚያ ሥፍራ ሲደርስ፤ ሁሉም ለዶርቃ የነበራቸውን ፍቅር ያያል። ለመበለቶች ልብስ በመስፋት ታገለግል ነበር። ከጸለየም በኋላ፤ ጴጥሮስ ያፈቅሯት ለነበሩትና ሙሾ ላወጡላት ደቀመዛሙርትና መበለቶች፤ ዶርቃን ከሙታን አስነሥቶ ፊታቸው አቀረበላቸው።

ክርስትና ያስገኘው ውጤት አንዱ፤ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል የአባልነት ደረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። በሮማው መንግሥት ዘመን ሴቶች እንደ ዕቃ ነበር የሚቆጠሩት። ምንም ዓይነት መብት አልነበራቸውም፤ ይታዩ የነበረው በባሪያ ደረጃ ነው። ክርስቶስ ግን ሴቶችን ለደቀመዛሙርትነት ተቀብሏቸዋል፤ ከተከታዮቹ መካከል እነሱ ይገኙበታል። የክርስቶስን ትንሣኤ ለመጀመሪያ ጊዜ ያበሠረችው ሴት ናት (ዮሐንስ 20፡ 10-18)። ኢየሱስ ሴቶችን ፈውሷል፤ ወዳጆቹም ናቸው። በዚህም መልኩ እግዚአብሔር በሴቶችም በወንዶችም በመጠቀም ወንጌሉን ሊያሰራጭና ዓለምን ሊያዳርስ ይሻል።

ጥያቄ 15፡- ሀ) በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ሴቶች ያላቸው ድርሻ ምን ዓይነት ነው? ለ) ኢየሱስ እንደሚያደርገው፤ መብታቸው ተጠብቆ በክብር ነው የሚስተናገዱት?

ሌላኛው የክርስትና እምነት ባህሪ ፍቅር ነው፤ ይህም በውስጣችን የሚገኘው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው (ገላ. 5፡22)። ዶርቃ ሌሎችን በማገልገል በተግባር ፍቅሯን ገለጸች። በሴቷ ደቀመዝሙር ላይ ስለተነሣ ነቀፌታ ምንም ዓይነት ማስረጃ የለንም። ዶርቃ ከሞት በመነሣቷ ደግሞ በኢዮጴ የሚገኙ ብዙ ሰዎች በጌታ አመኑ። ጴጥሮስም ከፋቂው ከስምኦን ቤት ተቀምጦ በኢዮጴ ማስተማሩን ቀጠለ።

በአይሁዶች ዘንድ፤ ፋቂ የሆነ ሰው እንደ እርኩስ ሰው ነበር የሚቆጠረው። ይህም የሆነው፤ ብሉይ ኪዳን የእንስሳን በድን የነካ ማንኛውም ሰው ይረከሳል ስለሚል ነው። ስለዚህም አይሁዶች ፋቂዎችን ሊጎበኙ ወደ ቤታቸው አይሄዱም፤ ከእነርሱ ጋርም አይበሉም፤ ሁሌ ከሙሴ ሕግ ውጪ የሚኖሩ የተረገሙ ሰዎች ናቸው ብለው ነው የሚመለከቷቸው። ይህ በአይሁዶች መካከል የተለመደ ቅራኔ ነበር፤ ጴጥሮስ ግን ካሁን ወዲህ ለዚህ ልዩነት ተገዢ አልነበረም። ክርስቶስም በጴጥሮስ ልብ ውስጥ ጥያቄ የሚፈጥሩትን ልዩነቶችን በማስተካከል፤ ቅራኔዎችን እንዲፈታ አስችሎታል።

ጥያቄ 16 ፡-ሀ) ይህን ዓይነት ቅራኔ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?
ለ) ምስክርነትህ በእነዚህ ቅራኔዎች ምክንያት እንዳይገለጽ ታግዷልን?
ሐ) በዚህ ነገር ላይ ጌታ ድልን እንዲሰጥህ ትፈልጋለህን? እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ ሕይወትህ እንቅፋት ሊሆኑብህ የሚችሉትን ቅራኔዎች እንዲገልጽልህ እፊቱ በጸሎት ቅረብ።

እግዚአብሔር ለጴጥሮስ ከዚህ ይበልጥ ለአገልግሎቱ እንቅፋት ሊሆን የሚችለውን ስለ አሕዛብ የነበረውን ግንዛቤ እንዲያጤነው አድርጎታል። የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በሕይወታችን ውስጥ በዝግታ እየመራ ክርስቶስን የሚያስከብሩትን ነገሮች ያሳየናል። ለዚህ ጉዳይ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት፣ መለወጥ እንደሚገባ መገንዘብ አለብን። መንፈስ ቅዱስ ሊለወጡ የሚገቡትን ነገሮች በሙሉ፣ በአንዴ አያሳየንም፣ ነገር ግን መለወጥ የሚገባንን ነገር ተገንዝበን ለጌታ አሳልፈን ስንሰጥ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ ያደርገናል።

በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩት አንዳንድ ውጥረቶች በዛሬይቱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሚታዩት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ናቸው። በጴጥሮስ ጊዜ፡- በሥራ ኃላፊነት፥ በመደብ ልዩነት፥ በዖታና በኢኮኖሚ ደረጃ ምክንያት በጎሣዎች መካከል የጥላቻና ምቀኝነት ችግሮች እንደነበሩ ባሁኑ ጊዜም እንዳሉ ናቸው። ከነዚህ ነገሮች የሚያላቅቀን አንዱና ብቸኛው አማራጭ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወታችንን መቆጣጠር ነው።

ጥያቄ 17፡- ገላትያ 3፡ 26-28 እና ቆላስያስ 3፡11 አንብብ። ፍቅርና ሁሉንም ሕዝቦች የመቀበል ባሕሪይ በሕይወትህ ውስጥ ይንፀባረቃሉን? በሕይወትህ ውስጥ የሚገለጹት በምን መልኩ ነው?

# አራተኛ ቀን፡-

## ከሐዋርያት ሥራ 9፡ 1-43 ላይ የተወሰዱ የክለሳ ጥያቄዎች

ትምህርቱን ከልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

1. ሳውል ቤተክርስቲያንን የማውደሙ ሐሳብ ላይ ቁርጠኛ አቋም የነበረው ለምንድነው?
2. በታሪክ ውስጥ ዋነኛው ክስተት የትኛው ነው?
3. ለአሕዛቡ ዓለም ዋነኛው መልእክተኛ ማን ነበር?
4. ጳውሎስ ከተለወጠ በኋላ፣ ለሦስት ዓመት ያህል የት ነበር?
5. ሀ) በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊወገዱ የሚገባቸው ሁለት ቅራኔዎች ምንና ምን ናቸው? ለ) እነዚህ ውጥረቶች ዛሬ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያኖች ውስጥ ይታያሉን?

6. ጳውሎስ በክርስትና ሕይወቱ ከመጀመሪያ አንሥቶ ታማኝነቱን የገለፀውና ያረጋገጠው እንዴት ነው? ይህ የሕይወትህ ባሕርይ ነውን?

## አምስተኛ ቀን፡-

የሐዋርያት ሥራን ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 9 ድረስ አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ። የዛሬው ቀን ጥናት ዓላማ የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል ዋና ዋና ትምህርቶች መከለስ ነው።

# ከትምህርት 1-7

## (ሐዋ. 1-9) ክለሳ።

1. ሀ) ለሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ማጠቃለያ ሐሳብ የሚሰጠው የትኛው ትዕዛዝ ነው?

   ለ) በሐዋርያት ምዕራፍ 1-9 የዚህ ትዕዛዝ ምን ያህል ክፍል ነው የተፈጸመው.

2. በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1-9 ውስጥ፤ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የሚገልጹ የተወሰኑ ክስተቶችን በዝርዝር ግለጽ።

3. በጥንቷ ቤተክርስቲያን ወቅት የሐዋርያቱ መልእክት ውስጥ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ሐሳቦች በዝርዝር ግለጽ።

4. ጌታ በተለየ ዓይነት ሁኔታ ለቤተክርስቲያን ዕድገት የተጠቀመባቸውን አምስት ሰዎች ስም ዝርዝር ጻፍ።

5. በቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ሁለት ውስጣዊ ችግሮች ምን ነበሩ?

6. የሐዋርያት ሥራ 9፡31 ከሐዋርያት ሥራ 6፡7 ጋር አነፃፅረው። ቤተክርስቲያን ድንበሯን ያሰፋችው በምን ያህል ነው?

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ አድሮ፥ የቀድሞውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥራ ቅጥያ የያዘ ነው። «በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከምድር ዳርቻ ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ»። የሐዋርያት ሥራ 1፡8 የዚህ መጽሐፍ ማጠቃለያ ሐሳብ ነው። በአንድ በኩል ስናየው፤ ኢየሱስ ምድራዊውን አገልግሎቱን ሲፈጽም አብረውት ለነበሩና ስለ ትንሣኤው ምሥክሮች ለሆኑት ሐዋርያት የተሰጡ ልዩ ተልእኮ ነው። ሆኖም፤ ይህ አደራ ለእነርሱ ብቻ አይደለም የተሰጠው። ብዙ ሌሎች ክርስቲያኖችም ከጥንት ጀምሮ የወንጌሉን መልእክት በማሰራጨቱ ሥራ ላይ ተካፍለዋል። እኛም እራሳችን ይህንን የምሥክርነት ሥራ እንድንቀጥል ተጠርተናል።

# የወንጌል ስርጭት




ጥቁር ባሕር
ተሰሎንቄ
ፍልጵስዩስ
ቤርያ
ጥሮአዳ
አቴና
ቆሮንቶስ
ኤፌሶን
አንጾኪያ
ኢቆንዮን
ልስጥራን
ደርቤን
ጴርግያ
አንጾኪያ
ሰልማና
ሴሌውቅያ
ጳፉስ
የኤጂያን ባሕር
ታላቁ ባሕር
ቂሣርያ
ኢየሩሳሌም
የጳውሎስ
የመጀመሪያውና ሁለተኛው
የስብከት ጉዞ ።
፩ኛ የስብከት ጉዞ
፪ኛ የስብከት ጉዞ



ሦስተኛው የጳውሎስ
የስብከት ጉዞ ።


የጳውሎስ ወደ ሮሚ
ጕዞና ሰባቱ የእስያ
አብያተ ክርስቲያናት ።
ጥቁር ባሕር
ሮሜ
አፍዩስ ፋሩስ
«ሦስት ማደሪያ»
ጕቲዮሉስ
አድርያ ባሕር
ሬጊዮም
ሲሲሊ
ሰራኩስ
መላጥያ
ጴርጋሞን
ትያጥሮን
ፊልድልፍያ
ስምርኔስ
ሰርዲስ
ኤፌሶን
ሉዶቅያ
ፍጥሞ
ሙራ
ቀርጤስ
ቆጵሮስ
ሲዶና
ታላቁ ባሕር
ቂሣርያ
ኢየሩሳሌም
ግብፅ

የወንጌሉ መልእክት ምንድነው? በአጭሩ አይሁዶች የገደሉት በሦስተኛው ቀን የተነሣው ኢየሱስ፤ የሚቀበሉትን ሁሉ ከኃጢአት ያድናቸዋል የሚል የምሥራች ዜና ነው። ይህ የደኅንነት በረከት፤ የኃጢአት ይቅርታ ደስታ፤ ሰላምና በአዲስ ሕይወት ለመኖር የሚያስችለውን ኃይል የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ያካተተ ነው።

መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ፥ በኢየሩሳሌም ተሰባስበው የነበሩት ጥቂት አማኞች በቁጥር እየበዙ መጡ። የሐዋርያት ሥራ ተቀዳሚ ትኩረት የሚሠጠው ስለ ወንጌሉ መልእክት ስርጭትና ዕድገት ነው። የሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ 2-5 ያለው ክፍል በኢየሩሳሌም ስላሉ አማኞች ዕድገትና አወቃቀር የሚያትት ነው።

ጥያቄ 18:- የወንጌሉን ምሥክርነት ከኢየሩሳሌም ውጪ እንዲሠራጭ ያደረገው ነገር ምንድነው?

ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ጀምሮ ወንጌሉ በኢየሩሳሌም ለሚገኙ አይሁዳውያን ብቻ እንዳልሆነ መገንዘብ ይጀምራሉ። ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ውጪ ይኖሩ የነበሩ ብዙ ሄሌናዊ አይሁዶች ተለወጡ። እነዚህ ሄሌናዊ አይሁዳውያን ያደጉት በግሪክ ባህል ሥር ሆነው ስለነበር፤ የግሪክን ቋንቋ በደንብ ይናገሩ ነበር። በኢየሩሳሌም ይገኙ በነበሩ አርቶዶክስ አይሁዳውያን ዘንድ የበታችነት ደረጃ እንዳላቸው የአይሁድ ዜጎች ነበር የሚቆጠሩት። ታዲያ ይህም ቢሆን፥ በኢየሩሳሌም ውስጥ እስጢፋኖስን በድንጋይ በመውገር ስደቱ ሲጀመር፤ የወንጌሉን መልእክት ይዘው ወደ ሰማርያና ይሁዳ የሄዱት እነኝሁ ሄሌናዊ አይሁዳውያን ናቸው። ሙሉ በሙሉ አይሁዳውያን ያልሆኑት የመጀመሪያዎቹ አማኞች ሳምራውያን ናቸው። ወደ ምዕራፍ 9 አጋማሽ አካባቢ ደግሞ ቤተክርስቲያን በይሁዳ፥ በገሊላና በሰማርያ ሙሉ በሙሉ ስትሰራጭ፤ አንድ ኢትዮጵያዊ ተጓዥም ሳይቀር ክርስቶስን እንደ መሲሑ ተቀብሏል።

ሐዋርያቱ በመጀመሪያ መልእክታቸውን ያቀረቡት ለአይሁዳውያን ነው። ኢየሱስ ከሙታን መነሣቱን በነቢያት ይነገርለት የነበረው መሢሑ እንደሆነና የደኅንነት ምንጭና የሁሉም ጌታ እሱ የመሆኑን እውነታ ነበር ያውጁ የነበረው። ለአይሁዶች በተሠጠው መልእክት ውስጥ መሠረታዊ የነበረው ሐሳብ፤ የኢየሱስ ትንሣኤና ከፍ ከፍ ማለት ነበር። ሐዋርያቱ ለአይሁዳውያን የንስሐ ጥሪ ነው ያደረጉላቸው።

ከጳውሎስ መዳን ጋር አንዳንድ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ነገሮች መለወጥ ጀመሩ። የጳውሎስ ተልእኮ አሕዛብንና አይሁዳውያንን ያካተተ ነበር። አይሁዶቹ ወንጌሉን ሳይቀበሉ ሲቀሩ፥ ወደ አሕዛብ ይሄዳሉ (ሮሜ 1:16 ተመልከት)። በቤተክርስቲያን አሕዛብም በመግባታቸው ለእርሷ አዲስ ዘመን የመፈጠሩ አዝማሚያ ነበራት።

ከክርስትና መስፋፋት ጋር፤ የሰይጣንም ተቃውሞ አብሮ ጨመረ። ሰይጣን ዛሬም ሦስት ዋና ዋና ስልቶችን ነው የተጠቀመው። አንደኛ፤ በስደት ተጠቀመ። ሐዋርያቱ ስለ ኢየሱስ መመሥከር እንደጀመሩ፤ ወዲያውኑ የአይሁድ መሪዎች አስረው ይገርፏቸው ጀመር። ምንም እንኳ ስለ ኢየሱስ እንዳይመሠክሩ ቢታዘዙም ክርስቶስ ስላዘዛቸው መመሥከራቸውን ቀጠሉበት። ወደ በኋላም፤ ስለ ክርስቶስ በመመሥከሩ

ምክንያት የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጻድቅ ሰማዕት እስጢፋኖስ ሞተ። ከዚያም ብዙ ክርስቲያኖች ወደ ወኅኒ ገብተዋል፤ እንዳንዶቹም በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለንን እምነታችንን አንተውም በማለታቸው ተገድለዋል።

ሁለተኛ፤ ሰይጣን በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን ለመፍጠር ሞክሯል። በጥንቷ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ውስጥ ሁለት ቡድኖች ነበሩ። በይሁዳ ያደጉት ዕብራዊ አይሁዶችና ከይሁዳ ውጪ ያደጉት ሄሌናዊ አይሁዶች ናቸው። ሁለቱም ወገኖች ክርስቲያን ሲሆኑ እርስ በርሳቸው ጥርጣሬ ውስጥ ነበሩ፤ በተለይም መበለቶቹ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች ስርጭት ላይ አድሎ ያለመኖሩ ላይ ተጠራጥረዋል። ወዲያውኑም ይህ እንዲቆም፤ ሐዋርያቱ የቤተክርስቲያን ገንዘብ ላይ ሐላፊነት የሚሸከሙ ሰባት ዲያቆናትን ሾሙ።

ሦስተኛ፤ ሰይጣን የክርስቲያኖችን ቅድስና ለማጉደፍ ጥረት አድርጓል። የግብዝነት ኃጢአት በሐናንያና በሰጲራ ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ የህዝቡን ቅድስና ለማጥፋት ጥሯል። አስቸኳዩ የእግዚአብሔር ፍርድ በእነርሱ ላይ ፍርሃትንና በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና የመኖር ምኞት አሳደረባቸው።

ጥያቄ 19:- ሀ) የጥንቷ ቤተክርስቲያን መሥፋፋት በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው የክርስትና መሥፋፋት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) ወንጌልን ማሥፋፋትንና ለስደት መጋፈጥን በተመለከተ፤ ከመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ምዕራፎች የምንማረው ነገር ምንድነው? ሐ) መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ስለሚሠራው ሥራ ልንማር ልናውቅ የምንችለው ነገር ምንድነው? (የራስህን መልሶች ጻፍ። ከሌሎቹ ጋር በሳምንታዊው ስብሰባ ላይ ይህንን ነገር ትወያይበታለህ)።

ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጁ ለመሆን፤ ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄዎች ተመልከት።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

| | |
|---|---|
| 1. የአምልኮ ጊዜ | 3. ክለሳ |
| 2. የጸሎት ጊዜ | 4. ውይይት:- |

ሀ) 1. የከበረውና ከሙታን የተነሣው የእየሱስ ራዕይ፤ ለሳውል የገለጸለት ነገር ምንድነው? 2. ሐናንያ ሊሰጠው የቻለው፤ ተጨማሪ ለሳውል ያስፈልገው የነበረው ዕርዳታ ምን ነበር? 3. ጌታ በሰዎች ስለመጠቀሙ ጉዳይ ይህ የሚያሳየን ነገር ምንድነው? 4. ይህ ነገር ለሳውል ዳግመኛ ማረጋገጫ ሊሆንለት የሚችለው እንዴት ነው?

ለ) በቤተክርስቲያንህ ስላሉ የማህበራዊ የቤተሰብ ወይም የጎሳ፥ የዕድሜ፥ የዖታ ቅራኔዎች ተወያዩ። ሰዎች ሌላውን የመቀበል መንፈስ እንዲኖራቸው ምን ማድረግ ትችላለህ?

ሐ) 1. የጥንቷ ቤተክርስቲያን ስርጭት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የክርስትና ስርጭት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? 2. ከመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ የሐዋርያት ምዕራፎች የወንጌልን ስርጭትና ስደትን መጋፈጥን በተመለከተ ልንማረው የምንችለው ነገር ምንድነው? 3. ከመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ምዕራፎች፤ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ስለሚሠራው ሥራ ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው?

መ) ልክ እንደ ጳውሎስ ሕይወታቸው በሚያስደንቅ ሁኔታ የተለወጡ ሰዎችን ታውቃለህ? እስቲ ይህንን ለሌሎች ግለጽላቸው።

5. ጸሎት

# ትምህርት 8

## የሐዋርያት ሥራ 10፡ 1 - 11፡18

## የመጀመሪያ ቀን፡- መግቢያ

የእግዚአብሔር የደኅንነት መልእክት ከአይሁዶች አገር ተነሥቶ እንዴት ወደ አኅራባች አገሮች እንደተዛመተ እይተናል። ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ በመላው የአይሁድ ክፍለ ሃገራት፤ በይሁዳና በአኅራባቾቹ ነገዶች በሳምራውያን ዘንድ ተሰራጨ። በዚህ ሳምንት፤ የወንጌሉን መልእክት ወደ አሕዛብ የማሰራጨቱ የእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ በደረሰ ወቅት ስለሆነው ነገር እናያለን። እስካሁን ድረስ፤ የአይሁድ ሃይማኖት ተከታይ ሊሆን ይችላል ብለን ከምንገምተው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ በቀር፤ ቤተክርስቲያን ውስጥ ገባ ተብሎ የተመዘገበ ወይም የተገለጸ አንድም የአሕዛብ ወገን የለም።

ምናልባትም በዓለ ሐምሳ ካለፈ ስምንት ዓመቱ ይሆናል። በክርስቲያኖች ላይ የተነሣውን ስደት ይመራ የነበረው ሳውል ከተለወጠ በኋላ፤ ጊዜው ለቤተክርስቲያን የዕረፍትና የዕድገት ነበር፤ ፊሊጶስና ጴጥሮስም በይሁዳና በሰማርያ በመዟዟር ይመሰክሩና አማኞቹን ያበረታቱ ነበር። እግዚአብሔር የትዕዛዙ ሁለተኛ ክፍል የሆነውን፤ የወንጌሉን በዓለም ሁሉ የማሰራጨቱን ነገር፤ ለማስፈጸም ቅድመ ዝግጅቶችን በማድረግ ጥርጊያ መንገዱን በማዘጋጀት ላይ ነው። ከዚህ በፊት ግን በአሕዛብና በአሁዳውያን መካከል ያለው ቅራኔ በመጀመሪያ መወገድ አለበት። እግዚአብሔር ለአይሁዳውያኑ ክርስቲያኖች አሕዛብን ወደ እራሱ ቤተሰብ ልክ እንደ አይሁዳውያኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደሚቀበላቸው ማስተማር ነበረበት።

ጥያቄ 1፡- በኢትዮጵያ ውስጥ በጎሳዎች ወይም በማኅበራዊ ቡድኖች መካከል ከዚህ ቀደም ወይም አሁን ያሉ የተለያዩ ቅራኔዎች በዝርዝር ጻፍ።

ጳውሎስ የክርስቶስን ስም ይዞ ወደ አሕዛብ የመሄድ ተልእኮ ተሰጥቶታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎቱ ዝግጁ እንዲሆን እያሰለጠነው ነበር። ሆኖም፣ ለአሕዛብ በሩን እንዲከፍትለት እግዚአብሔር እንደ መሣሪያ የተጠቀመበት ጴጥሮስን ነው። ካለፈው ውይይታችን ላይ እንደምታስታውሰው ኢየሱስ በዚህች የሀዋርያው የእምነት ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኑን እንደሚመሠርት ለጴጥሮስ ነግሮት ነበር (ማቴ. 16፡17-18 ተመልከት)። እንደ ሰማሪያውያንና እንደ አሕዛብ ያሉትን ወገኖች እምነት እውነተኛነት ያረጋገጥ የነበረው የእግዚአብሔር ወኪል ጴጥሮስ ነበር። ወደ እግዚአብሔር ቤት እነሱን እንኳን ደህና መጣችሁ ብሎ የማስገባት ዕድል ተሰጥቶት ነበር። በተጨማሪም እነዚህ አዳዲስ ክርስቲያኖች ከአይሁዳውያን ጋር እኩል መታየት እንዳለባቸው ይገልጽ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ለእነዚህ አዳዲስ ቡድኖች ሲሰጥ በግንባር በመቅረብ እንዲያረጋግጥ እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል። ምንም እንኳ በቤተክርስቲያን ውስጥ ጠንካራ መሪ ቢሆንም የጴጥሮስ እምነት በየጊዜው መጠንከርና መሥፋት ነበረበት። ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ ያለው ግንዛቤ አሕዛቦችን እስኪያጠቃልል ድረስ እንዲደርስ፣ እግዚአብሔር ያስተምረው ዘንድ ይገባ ነበር።

ኤፌሶን 2፡11-22 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 2፡- ሀ) ለአሕዛብ የተሰጠው ስያሜ ምን ነበር? ለ) ተገልለው የነበሩትስ ከምንድነው? ሐ) የሌላቸው ነገር ምን ነበር? መ) ለአይሁዶችና ለአሕዛብ ክርስቶስ የፈጸመላቸው ነገር ምንድነው? ሠ) ክርስቶስ ለአይሁዶችና ለአሕዛብ የነበረው ዓላማ ምንድነው?

አይሁዶች እርሳቸውን ከአሕዛብ ጋር ሲያወዳድሩ፣ ከአሕዛብ የተሻሉ የሚያደርገን ብዙ ነገር አለ ብለው ያስቡ ነበር። አንደኛ እነርሱ ተገርዘዋል፣ አሕዛብ ግን አልተገረዙም። እንደምታስታውሰው እግዚአብሔር ይህንን የመገረዝ ምልክት ለአብርሃም እንደ ውጫዊ ምልክት አድርጎ የሰጠው ዘሮቹ ሁሉ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ኪዳን ውስጥ እንደሚሆኑ ለማመልከት ነው። ለእግዚአብሔር ዋናው ቁም ነገር የነበረው በውጫዊው መገረዝ ላይ ሳይሆን ግዝረቱ በሚያመለክተው ቁም ነገር ላይ ነው ይህም በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሥር ሆኖ የመኖር ስምምነታቸው ነው። አይሁዳውያን ግን እግዚአብሔር በትኩረት ይመለከተዋል ብለው የሚገምቱት ውጫዊውን የመገረዝ ሥርዓት ነበር። ወደ በኋላ ግን ጳውሎስ እግዚአብሔር ትኩረት የሚያደርገው የሥጋው ግዝረት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ከልብ የተገረዙት ላይ መሆኑን አስተምሯል (ሮሜ 2፡28-29)።

ጥያቄ 3 ፡-በኢትዮጵያ ዛሬ ወንዶችም ሴቶችም የሚገረዙት ለምንድነው? ምክንያቱን ከብሉይ ኪዳኑ ዓላማ ጋር አነፃፅረው።

ሁለተኛ፣ አሕዛቦች ባለመገረዛቸው ምክንያት እስራኤላዊ ከመሆን ተወግደዋል፣ ከተስፋ ቃሎቹም ውጭ ሆነዋል። አይሁዶች የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል የተሰጠው ለእኛ ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። አይሁዶች በእስራኤል ግዛት ውስጥ ነው የሚኖሩት። ከአብርሃም ጊዜ አንሥቶ እስከ ነቢያት ጊዜ የተሰጡትን የተስፋ ቃሎች የተቀበሉ

ናቸው። የተመረጡት ሕዝቦችም ናቸው፤ ይህን ስንል በሥጋ አይሁድ ያልሆኑ ሁሉ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አይቀበሉም ብለው ያምናሉ ማለት ነው። አንድ የአሕዛብ ወገን የሆነ ሰው የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ለመሆን ከፈለገ አይሁዳዊ መሆን፤ ይህም መገረዝ፣ መጠመቅና የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት በሙሉ መከተል አለበት ማለት ነው። ብዙ አሕዛብ ደግሞ እነዚህን ነገሮች እውነተኛውን አምላክ ለመከተል እንቅፋት እንደሆኑ አድርገው ነው የሚቆጥሯቸው። በዚህም ምክንያት «እግዚአብሔርን ብቻ የሚፈሩ» ይሆናሉ፤ በሌላ አነጋገር የሚያምኑት በአንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ በእርሱ ፊትም ትክክለኛ የሆነ ሕይወት ለመኖር ይጥራሉ፤ ነገር ግን ግዝረት ውስጥ በማለፍ ሙሉ አይሁዳዊ ወደ መሆኑ አይደርሱም። በዛሬው ትምህርታችን እግዚአብሔርን ስለሚፈራ ቆርኔሌዎስ ስለሚባል ሰው እናነባለን።

በመጨረሻም፤ አይሁዶች አሕዛብ ያለእግዚአብሔርና ያለምንም ተስፋ ይኖራሉ ብለው ነው የሚያስቡት። አንዳንድ አይሁዳውያን፤ አሕዛብ የእግዚአብሔር ልጆች ባለመሆናቸው በእግዚአብሔር ቤተሰብ እኩል አባልነት አይኖራቸውም ብለው ማስተማር ደረጃ ላይም ደርሷል። የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚያገኙት አይሁዳውያን ብቻ ናቸው ብለው ስለሚያስቡ ብዙ ጊዜ ይጭኑባቸው የነበሩትን አሕዛብ በጣም ስለሚጠሉ፤ አሕዛብ ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም በመጨረሻም የዘላለማዊ ፍርድ ተቀባዮች ናቸው በሚለው ሐሳባቸው በጣም ይደሰቱበትና ይመኩበት ነበር። አይሁዳውያን ግን ለአሕዛብ መብራት መሆን እንደሚገባቸው ዘንግተው ነበር (ኢሳይያስ 49፡6)።

ሆኖም፤ የእግዚአብሔር ዓላማ ይህ አልነበረም። ክርስቶስ የሞተው ለሰዎች ሁሉ ነው እንጂ፤ ለአይሁዳውያን ብቻ አይደለም። በክርስቶስ በኩልና በፈሰሰው ደሙ ምክንያት አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር ሊቀርቡ ችለዋል። ክርስቶስ በአሕዛብና በአይሁዶች መካከል ያለውን ግድግዳ አፍርሶታል። በሙትም ሕጉን ትዕዛዛቱንና መመሪያዎቹን በሙሉ ፈፅሟል። ኢየሱስ ክርስቶስ አሕዛብንና አይሁዶችን በቤተክርስቲያን አንድ አካል አድርጓቸዋል፤ ሁለቱም ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ በመካከላቸው ሰላም እንዲሰፍንም አድርጓል። በአንድ መንፈስ ሁለቱም ወገኖች ወደ አብ ሊቀርቡ ይችላሉ፤ በዚህም ምክንያት የአንድ ዜጋ አባሎችና የአንድ ቤተሰብ አባሎች ናቸው።

ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ሲሆን፤ ኢየሱስ ደግሞ ለዚህ መሠረት የማዕዘን ድንጋይ ነው። በክርስቶስ በማመን አሕዛብና አይሁዶች አንድ ይሆናሉ፤ ሙሉ በሙሉም እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱሱ አማካኝነት የሚኖርባቸው የተቀደሱ ቤተመቅደሶች ይሆናሉ።

የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እውን ሊያደርገው የቻለው ነገር ይህ ነው፤ ነገር ግን በአይሁዶችና በአሕዛብ መካከል የነበረው ግጭትና መከፋፈል አሁንም በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይታይ ነበር። ይህ በአሕዛብና በአይሁዳውያን መካከል ያለው ግጭት፤ የጥንቷ ቤተክርስቲያን ድል ልታደርገው የሚገባት አንዱ ትልቁ ትግል ነበር።

የአይሁድ ክርስቲያኖችም አሕዛቦች ሙሉውን የደህንነት በረከት ለመቀበል አይሁድ መሆን እንደሌለባቸው ለመገንዘብ ብዙ ዓመታት ፈጅቶባቸዋል።

ጥያቄ 4፡- በአሕዛብና በአይሁዶች መካከል ዛሬ ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? አይሁዶች እነማን ናቸው? አሕዛቦች እነማን ናቸው?

ጥያቄ 5፡- ሀ)) ዛሬ በዓለም ሕዝቦች መካከል ያሉ ሌሎች ክፍፍሎች የትኞቹ ናቸው? ለ) እነዚህ ክፍፍሎች በሸክላ ሠሪዎች ወይም በብረት አቅላጮችና በሌሎች የቤተክርስቲያን ሰዎች መካከል ባለው ልዩነት ላይ በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው ተግባራዊ የሚሆኑት? ሐ) የክርስቶስ ሞት ከሌሎች ጎሳዎች ወይም ማኅበረሰብ ሕዝቦች ጋር ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?

ጥያቄ 6፡- በዓለም ሕዝቦች መካከል አንድነት ሊያስገኝ የሚችለው ብቸኛው መንገድ ምንድነው? (ይህንን ጥያቄ የክርስቶስ ሞት አይሁዶችንና አሕዛብን እንዴት አንድ እንዳደረጋቸው ከሚገልጸው ሐሳብ ጋር አዛምደው)።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ምዕራፍ አሥር፤ አሕዛብ የአይሁድ ሥርዓት ተከታዮች ሳይሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዴት ወደ ቤተክርስቲያን እንደገቡ ይናገራል። የሕጉና የባህሉ ግድግዳ የአሕዛብ ከተማ በሆነችው በቂሣርያ የሐዋርያት መሪ በነበረው በስምዖን ጴጥሮስ ተገረሰሰ።

## ሁለተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 10፡1-23

በኤፌሶን ምዕራፍ ሁለት ላይ፤ አሕዛብ ከአይሁዶች የሚለያዩ አንዳንድ ነገሮችን አይተናል። ለብዙ ዓመታት ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም በይሁዳና በሰማርያ አድጋ ጥሩ መሠረት ይዛለች፤ ነገር ግን ወደ አሕዛቡ ዓለም ገና አልደረሰችም ነበር። ጳውሎስ የክርስቶስ ስም በአሕዛብ ዘንድ ይዞ እንዲሄድ ተልእኮ ተሰጥቶታል፤ ይሁን እንጂ በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ተቃውሞ ገጥሞት ወደ ትውልድ አገሩ ወደ ተርሴስ እንዲመለስ ተገደደ። ያለምንም ጥርጥር ለቤተሰቦቹ ለጓደኞቹ ሳይመሠክር አልቀረም፤ ሆኖም ስለዚህ ጉዳይ የተጻፈ ነገር የለም። እግዚአብሔር ለአሕዛብ በሩን እንዲከፍትላቸው እንደመሣሪያ አድርጎ የተጠቀመበት ጴጥሮስን ነው።

ኢየሱስ በአንድ ወቅት ስለ ሮማዊው መቶ አለቃ ሲናገር «እውነት እላችኋለሁ፤ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም። እላችኋለሁም ብዙዎች ከምስራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃም፥ ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ ብሏል (ማቴ. 1፡ 10-11)። ሰውዬው ሮማዊ በመሆኑ ኢየሱስ አላጥላላውም። ኢየሱስ አንድ ቀን ከሁሉም ባህልና ልማድ የተውጣጡ ሰዎች በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ከአይሁዳውያን ጋር እንደሚቀላቀሉ ተገንዝቧል። እግዚአብሔር የሚያየው ልብን ነው፤ በዚያም ከእያንዳንዳችን ሊያገኝ የሚሻው እምነትን ነው። አሁን ደግሞ ሌላ ታላቅ እምነት የነበረውን ሮማዊ መቶ አለቃን እናያለን።

ጥያቄ 7፡- የሐዋርያት ሥራ 10፡ 1-11፡18 አንብብ። ይህ ክፍል እግዚአብሔር አይሁዶችንና አሕዛብን የሚለየውን ግድግዳ ማፈራረሱን የሚያሳየው እንዴት ነው?

ደግመህ የሐዋርያት ሥራ 10፡ 1-23 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 8፡- ሀ) ቆርኔሌዎስ ማነው? ለ) እግዚአብሔር የተናገረው እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር የተናገረው ለምንድነው? መ) ጴጥሮስ የት ነበር? ሠ) እግዚአብሔር ጴጥሮስን የተናገረው እንዴት ነው? ረ) እግዚአብሔር ለጴጥሮስ ያስተማረው እውነታ ምንድነው?

ቆርኔሌዎስ የተከበረ የመቶ አለቃ ነበር። እርሱ ሮማዊና ጥሩ ሥነምግባርም የነበረው ሰው ነበር። በአንዱ እውነተኛ አምላክ ያምን ነበር፤ ልክ እንደ አይሁዳውያኖቹም በቀን ሦስቴ ይሰግድለት ነበር። በአካባቢው ለሚገኙ ችግረኛ አይሁዳውያን ይመፀውት ነበር። ሆኖም ሙሉ አይሁዳዊ ለመሆን፣ በመገረዝ ሂደት ውስጥ አላለፈም። አይሁዳውያን ምንም ቢያከብሩትም ከእግዚአብሔር በረከት ውጪ እንደሆነ አድርገው ነበር የሚያዩት። እንዲህ ዓይነቱን ሰው «ፈሪሃ እግዚአብሔር» ያለው ሰው ነው ብለው ነበር የሚጠሩት።

ቆርኔሌዎስ ይኖር የነበረው የሮማው ጦር ሠፈሮች ይገኙበት በነበረውና ለአይሁድ ሰዎች ዋነኛ የወደብ ከተማ በነበረችው በቂሣርያ ነበር። ምንም እንኳ አንዳንድ አይሁዳውያን በዚያ ቢኖሩም፣ ብዙ የኅብረተሰቡ ክፍል ግን ከአሕዛብ ወገን ነበር። ቆርኔሌዎስ ከአይሁዳውያን ጋር በነበረው ግንኙነት ምክንያት እግዚአብሔርን መውደድንና ማክበርን ተምሯል። ይህንንም ፍቅሩን ይገልጽ የነበረው ለተቸገሩ ሰዎች ጥሩ ለመሥራት በመጣር ነው። ሆኖም፣ ስለ ክርስቶስ ምንም አያውቅም ነበር። አንድ ቀን ቆርኔሌዎስ በዘጠኝ ሰዓት ላይ በመጸለይ ላይ ሳለ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ወደ ኢዮጴ ሰዎችን በመላክ ጴጥሮስን እንዲያስመጣ ይናገረዋል። ኢዮጴ ከቂሣሪያ በ 40 ኪ. ሜ ርቀት ላይ ነበር የምትገኘው። እግዚአብሔር የቆርኔሌዎስ ልብ ለወንጌሉ መልእክት ዝግጁ እንደሆነ ያውቃል። ስለዚህም፣ ለቆርኔሌዎስ ጥርጊያ መንገድን በማዘጋጀት ስለ ኢየሱስ ሰምቶ በማመን ለደኅንነት ብቁ እንዲሆን አደረገው።

ጥያቄ 9፡- ሀ) እግዚአብሔርን መፍራት አንድን ሰው ለደኅንነት ሊያበቃው ይችላልን? አብራራው። ለ) እግዚአብሔር መልአኩን እራሱ የወንጌሉን መልእክት ለቆርኔሌዎስ እንዲነግረው ከማድረግ ፈንታ፣ ወደ ጴጥሮስ እንዲልክ ያዘዘው ለምንድነው?

በሚቀጥለው ቀን የቆርኔሌዎስ መልእክተኛ ወደ ኢዮጴ ከተማ በመቃረብ ላይ ሳለ፣ አሕዛብን ያስተምር ዘንድ ልቡ ዝግጁ እንዲሆን እግዚአብሔር ጴጥሮስን ለዚህ ተልእኮ ማዘጋጀቱን ይጀምራል። ከዚህ በፊት እንዳየነው፣ አንዳንዶቹን የጴጥሮስ ቅራኔዎች ለማስወገድ ሲል እግዚአብሔር እንዴት በቁርበት ፋቂ ቤት እንዲመጣ እንዳደረገው አይተናል። ሆኖም፣ አሁንም ገና እግዚአብሔር ለአሕዛብ ስላለው ዕቅድ ጴጥሮስ ብዙ ማወቅ የሚገባው ነገር ነበር።

ጴጥሮስ በኢዮጴ ጣራ ላይ ወጥቶ ነበር የሚጸልየው። ብዙ ጊዜ የአይሁዳውያን ቤቶች ጣራ ጠፍጣፋ ነው። ከቤቱ ውስጥ ይልቅ በዚያ ነፋሻ ስለሚሆን አይሁዶች ብዙ ጊዜያቸውን በጣራ ላይ ያሳልፋሉ። ጴጥሮስ በጣም እርቦት ነበር፤ ምግቡ እየተዘጋጀለት ሳለ፤ በተመስጦ ሰማይ ሲከፈት አየ። ሦስት ጊዜ በብሉይ ኪዳን የምግብ ሕግ የተከለከሉ የተለያዩ እንስሳትን እፅዋትንና እንደ እባብ፥ አሞ የመሳሰሉትን ሁሉ ያያል። እነዚህን እንስሳት ገድሎ እንዲበላም ይታዘዛል። ጴጥሮስም ሦስት ጊዜ «ጌታ ሆይ አይሆንም!! አንዳች እርኩስ የሚያስጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና» በማለት እራሱን ይገታል። ምንም እንኳ ኢየሱስ ሁሉም ምግቦች ንጹሕ ናቸው ብሎ ቢያውጅም (ማርቆ. 7፡ 18-19)፤ ጴጥሮስ ሳያቋርጥ ስለንጹሕና ንጹሕ ስላልሆኑ እንስሳት የተጻፈውን የብሉይ ኪዳን ሕግ ይከተል ነበር። በአይሁድ ቤት ውስጥ የቀመሰውን የአስተዳደጉን ሥርዓት መከተሉ ስሕተት አይደለም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ራዕይ በመጠቀም ባህላዊ የሆኑ ነገሮች ለወንጌሉ ምሥክርነት ዕንቅፋት የሚሆኑ ከሆነ ስሕተት እንደሆኑ ነው የሚገልጹለት። ወደ ጴጥሮስም «እግዚአብሔር ያነፃውን አንተ አታርክሰው» የሚል ድምፅ መጣ።

በዚህ ራዕይ፤ እግዚአብሔር ለጴጥሮስ ሁለት ዋና ዋና እውነታዎችን ያስተምረዋል። አንደኛ ካሁን ወዲህ እግዚአብሔር ሰዎች የተወሰነ ምግብ ይብሉ እንደማይል ለጴጥሮስ ያስገነዝበዋል። ውጫዊ በሆኑት እንደ መብልና መጠጥ በመሳሰሉት ነገሮች ላይ ከማተኮር ይልቅ፤ እግዚአብሔር ትኩረቱን ያደረገው በልብ ውስጥ ያለውን ነው። አንድ ነገር ንጹሕ ወይም ንጹሕ ያለመሆኑን የሚወስነው ልብ ነው።

ጥያቄ 10፡- ሀ) ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የማይበሏቸው የምግብ ስም ዝርዝር ጻፍ። ሰዎች የተወሰኑ ምግቦችን አንበላም የሚሉት ለምንድነው? ለ) መብላት ስለሚገባን ወይም ስለማይገባን ምግብ በተመለከተ በማርቆስ 7፡ 18-19 ላይ ካለው የኢየሱስ ምላሽና ጴጥሮስ ካየው ራዕይ ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው?

ሁለተኛና ዋነኛው ነገር እግዚአብሔር ጴጥሮስ ንጹሕ አይደለም ብሎ የሚቆጥራቸው አሕዛቦች፤ በእግዚአብሔር እጅ የተፈጠሩ በመሆናቸው ንጹሕ መሆናቸውን ያሳየዋል። እግዚአብሔር አሕዛብን በተመለከተ በጴጥሮስ ውስጥ ያለውን ቅራኔ አስወግዶ ወንጌሉን ወደ ቆርኔሌዎስ ይዞለት እንዲሄድ ነው የፈለገው።

እግዚአብሔር ሁለቱን ሰዎች እንዴት እንዳዘጋጃቸውም ልናይ እንችላለን። ከአሕዛብ ወገን የሆነው ቆርኔሌዎስን የወንጌሉን መልእክት እንዲሰማ ዝግጁ ያደርገዋል፤ አይሁዳውያን ጴጥሮስን ደግሞ የክርስቶስ መልእክት ይዞ ወደ አሕዛቡ እንዲሄድ ያደርገዋል።

መንፈስ ቅዱስ ይህንን ራዕይ ለጴጥሮስ ካሳየው በኋላ «እነሆ፤ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል፤ ተነሥተህ ውረድ፤ እንዴም ልኬአቸዋለሁና ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ» አለው።

ጴጥሮስ ይህ ባይነገረው ኖሮ በተለምዶ ምንም ዓይነት ግንኙነት ከአሕዛብ ጋር እንዳይኖረው ነበር የሚያደርገው። የብሉይ ኪዳንን ሕጋጋት ባለመከተላቸውም አሕዛብ ንጹሕ እንዳልሆኑ ነገሮች ነበር የሚቆጠሩት፤ ታዲያ አንደይሁዳዊ ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ካለው ደግሞ ያረክሱታል። መንፈስ ቅዱስ ከተናገረው በኋላ ጴጥሮስ የቆርኔሌዎስ መልእክተኞችን በመቀበልና ከእነርሱ ጋር በመብላት ከአሕዛብ ጋር እንዳይሆን የሚያግደውን ዋነኛውን ግድብ ያፈርሰዋል።

ጥያቄ 11:- ለጴጥሮስና ለቆርኔሌዎስ ለመናገር እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ሦስት መንገዶች ምን ምንድናቸው?

ጥያቄ 12:- በዛሬው ጊዜ እግዚአብሔር አንተን የሚናገርህ በምን ዓይነት መንገድ ነው?

በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የመሆናችን እውነታ የሚገለጸው በተወሰኑ ነገሮች ላይና በሰዎች ላይ ያለን ባህላዊ አመለካከት ሲለወጥ ነው። ይህ ለውጥ ብዙውን ጊዜ በጣም አስቸጋሪ ነው። አንዳንዴ ባህላችን ይሄ ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ ከሰዎች ሁሉ የሚጠብቀው ይህ ነው ብሎ መናገሩ ያዳግታል። ከቅራኔዎችና ከማን አለብኝነት የተነሣ እኛ የተሻልን ሰዎች እንደሆንና አሠራራችንንም ትክክለኛ እንደሆነ እንቆጥረዋለን። በክርስቶስ ጎልምሰን አድገናል ስንል፤ እነዚህ በባህላችን ትዕቢትንና ልዩነትን የሚፈጥሩ ነገሮች የወንጌሉ ቀንደኛ ጠላቶች እንደሆኑ አድርገን ማየት አለብን እንጂ ልዩነቶች ናቸው ብለን ዝም ብለን ልንቀበላቸው አይገባንም። እንደ ምግብ ወይም ዘረኝነት ለወንጌሉ እንቅፋት እንዲሆኑ የምናደርግ ከሆነ ወይም ደግሞ ሌሎች ሰዎች ከእኛ በታች ናቸው ባህላቸውም ከእኛ ባህል በታች ነው ብለን የምናምን ከሆነ ጴጥሮስና አይሁዳውያን የፈጸሙትን ዓይነት ኃጢአት እየፈጸምን ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ስላለው ቅራኔ ግድ እንደሚለውም ልንገነዘብ ይገባናል። ሰዎች ምን ለብሰዋል፤ ወይም ከየትኛው ጎሳ ነው የመጡት በሚሉት ሐሳቦች ላይ ከምናተኩር እግዚአብሔር ስለ ሰዎችና በልባችን ውስጥ ስለምናምነው ነገር እንድናስብ ነው የሚፈልገው።

ጥያቄ 13:- ሀ) ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ምግብን፥ ዘርን፥ ወዘተ... በተመለከተ በምን ዓይነት ቅራኔዎች እንደሚፈጥሩ በዝርዝር ግለጽ። ለ) በእነዚህ ልዩነቶችም ላይ ክርስቲያኑ ሊኖረው የሚገባው አመለካከት ምን ይመስልሃል? ሐ) እግዚአብሔር ይህንን በሌሎች ክርስቲያኖች ያለውን ቅራኔና ትዕቢት እንድትጠቁማቸው ለበለጠ መንፈሳዊ ዕድገት እንድትገፋፋቸው፤ በአንተ እንዴት አድርጎ ነው ሊጠቀምብህ የሚችለው?

## ሦስተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 10: 24-48

ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ በራዕይ አማካይነት በሚገናኙበት ጊዜ ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርጓል። ይህ አሥረኛው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በብዙ ምክንያቶች ሲታይ

በጣም ዋነኛና አስፈላጊ ነው። 1. የእምነት በር ለአሕዛብ እንዴት እንደተከፈተ ይገልጻል። 2. ወደ በኋላ ላይ በቤተክርስቲያን ትልቅ ችግር የሚፈጥሩ ሁለት ነገሮችን ይጠቁመናል ወይም ይገልጽልናል እነዚህም ሀ) እንደ አይሁዳውያንና አሕዛብ ያሉ ጠላቶች ባህላቸው በጣም የተለያየ ሆኖ በማኅበራዊ ኑሮ ሊገናኙ የሚችሉት እንዴት ነው? ለ) አሕዛብ ወደ ቤተክርስቲያን መግባት እንዲችሉና ለደኅንነት ብቁ እንዲሆኑ እንደ መገረዝ ያሉ ማሟላት ያለባቸው ነገሮች ምንድናቸው? እነዚህን ጥያቄዎች ወደ በኋላ አካባቢ በኢየሩሳሌሙ ምክር ቤት ውስጥ የጦፈ ክርክር አድርገውባቸዋል። (ሐዋ. 15)።

ጴጥሮስ ከዚህ ቀደም ንጹሕ ያልሆኑትን ምግቦች እንዲበላ በራዕይ ያየው ነገር፤ ምግብን ከመብላት በላይ ብዙ ነገሮችን እንደሚያስገነዝብ ተረድቷል። እንዲያውም ስለ አይሁዳውያንና ስለ አሕዛብ ግንኙነት የሚናገረው ነገር አለው። ይህንንም መገንዘቡን ጉልህ የሚያደርገው የቆርኔሌዎስን መልእክተኞች ተቀብሎ ከእርሱ ጋር እንዲበሉና ምሽቱን እንዲያሳልፉ ማድረጉ ነው። ለአሕዛብ ወንጌል የሚሰሙበትና ወደ ቤተክርስቲያን ገብተው ተቀባይነት የሚያገኙበት በር እየተከፈተላቸው ነው።

የሐዋርያት ሥራ 10፡ 24-48 አንብብና እነዚህን ጥያቄዎች መልስ። ጥያቄ 14 ሀ) ጴጥሮስ ወደ ቂሣርያ ይዞት የሄደው ማንን ነው? ለ) እዚያ ሲደርሱ ጴጥሮስን ይጠባበቁት የነበሩት እነማን ናቸው? ሐ) ቆርኖሌዎስ የሰጠውን ክብር እንዳይቀበል ለጴጥሮስ ግድ የሆነበት ለምንድነው? መ) እግዚአብሔር የጴጥሮስንና የቆርኔሌዎስን ልብ ያዘጋጀው እንዴት ነው? ሠ) ጴጥሮስ መልእክቱን የጀመረው እንዴት ነው? ረ) ቆርኔሌዎስ ቤተሰቦቹና ጓደኞቹ ጴጥሮስ ያስተማረውን እውነታ ስለመቀበላቸውና ስለማመናቸው ምን ማስረጃ አለ?

ጴጥሮስ ወደ ቂሣሪያ ሲሄድ ከኢዮጴ አንዳንዶቹን አይሁድ አማኞች አብሮ ይዞ ሄዷል። በቂሣሪያም ሲደርስ ቆርኔሌዎስ ወዳጆቹና ዘመዶቹ አቀባበል አደረጉለት። ቆርኔሌዎስም የማምለክን ያህል በእግሩ ላይ ይወድቃል። ጴጥሮስም «ተነሣ እኔ እራሴ ሰው ነኝ» ብሎ አስነሳው። ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ጴጥሮስ ለእራሱ ክብር ሊያውለው ይችል ነበር፤ ነገር ግን ማምለክ የሚገባን እግዚአብሔርን ብቻ እንደሆነ ቆርኔሌዎስ እንዲረዳለት ፈልጓል። አንድ የቤተክርስቲያን መሪ ሰዎች ክብርና ሙገሳ ወደ እርሱ እንዳያመጡ ነገር ግን ለክርስቶስ እንዲሠጡ ሁሌ ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ አለበት።

ጥያቄ 15፡- ይህ ለቤተክርስቲያን መሪዎች አንዳንዴ አደገኛ የሚሆነው እንዴት ነው?

ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሲገባ፤ ብዙ በእውነተኛው አምላክ ደስ የሚሰኙ አሕዛብ ተከማችተው አገኛቸው። ጴጥሮስም ለቆርኔሌዎስ ቤት ለተሰባሰበው ሕዝብ በአይሁድ የሃይማኖት ሕግ መሠረት አንድ አይሁዳዊ ከአሕዛብ ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንደማይችል ያስታውቃቸዋል። ጴጥሮስም በመቀጠል «ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያጸይፍ ነው እንዳልል አሳይቶኛል፤ ስለዚህም ደግሞ ብትጠሩኝ ሳልከራከር መጣሁ ... አሁንም በምን ዓይነት ምክንያት አስመጣችሁኝ? ብዬ እጠይቃችኋለሁ አላቸው (ሐዋ. 10፡ 28-29)። ጴጥሮስ

ለአሕዛብ ግልጽ ሊያደርገው የፈለገው ነገር በአይሁዳውያን በአሕዛቦች መካከል ኅብረት እንዲኖር ያደረገና እንቅፋቶችን ያስወገደ እግዚአብሔር መሆኑን ነበር። እግዚአብሔር የአይሁዳውያንን ብቻ አምላክ አይደለም፤ የአሕዛብ በሙሉ እንጂ።

ቆርኔሌዎስ መልአኩ እንዴት እንደታየው ሲገልጽ እግዚአብሔር ጸሎቱንና ለደሆች የሰጠውትን ምፅዋቱን አሰበ ይላል። በመቀጠልም መልአኩ የሚኖርበትንም ሥፍራ በመናገር በኢዮጴ ወደ ስምዖን ጴጥሮስ መልእክተኞችን እንዲልክ ይነግረዋል። ቆርኔሌዎስም «እንግዲህ አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዝኸውን ሁሉ እንድንሰማ እኛ ሁላችን አሁን በእግዚአብሔር ፊት እዚህ አለን አለው (ሐዋ. 10፡33)።

ምን ዓይነት የሚያስደንቅ አጋጣሚ!! ቆርኔሌዎስ ዘመዶቹንና ወዳጆቹን ሰብስቦ በጴጥሮስ በኩል የሚተላለፈውን የእግዚአብሔር መልእክት በታላቅ ጉጉት እየተጠባበቀ ነው። እግዚአብሔር ልባቸውን ለወንጌሉ አዘጋጅቶታል።

ጥያቄ 16፡- የሐዋርያት ሥራ 2፡36 እና 3፡13-15 ከሐዋርያት ሥራ 10፡34-38 ጋር አነፃፅረው። ሀ) ጴጥሮስ ንግግሩን ሲከፍት፣ የአይሁዳውያን ሕሊና የሚነካ ሐቅ በመናገር ነገር፤ ምን ነበር እሱ? ለ) በቆርኔሌዎስ ቤት ለተሰበሰቡት ሲናገር የተጠቀመባቸው እውነታዎች ምንድናቸው?

ጴጥሮስ መልእክቱን «እግዚአብሔር ለሰው እንደሚያዳላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደሆነ በእውነት አስተዋልኩ «በማለት ከፈተ። ምንም እንኳ ነቢያት እግዚአብሔር ስለ አሕዛብ ግድ እንደሚለው ቢያስተምሩም፣ የእግዚአብሔር ወደ አሕዛብ መልአክን ያክል ነገር የመላኩ ተግባር ጴጥሮስን በጣም ሳያስገርመው አልቀረም። እግዚአብሔር ግን ለአይሁዳውያን፡- ነገሥታትም እግዚአብሔርን በማምለክ እንደሚሳተፉ ተናግሯቸዋል (ኢሳይያስ 42፡6 እና 49፡6፤ 22)።

ጴጥሮስ ከመጥምቁ ዮሐንስ በመጀመር፤ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ስለቀባው ስለ ኢየሱስ አገልግሎት መለስ ብሎ አውስቶታል።እነዚህምአሕዛብለብዙ ዘመናትበፓለስታይን በመኖራቸው፤ ስለ ኢየሱስ ወሬ እንኳ መስማታቸው የሚያጠራጥር አይደለም። የኢየሱስ ታላቅነት የተገለጸው በአጋንንት ኃይል የተያዙትን ሲፈታና በሽተኞችን ሲፈውስ ነው ከዚህም በኋላ በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩት አይሁዳውያን ኢየሱስን ገደሉት። ጴጥሮስ ጥፋተኞች አድርጎ ያቀረባቸው አይሁዳውያንን ነው እንጂ ሮማውያንን አይደለም፤ ይህም የሆነው አይሁዳውያኑ የበለጠ ስለሚያውቁ ነው። ነገር ግን ጴጥሮስ ትልቅ ትኩረት የሰጠው በአስገራሚ ሁኔታ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን ማስነሣቱ ላይ ነው። እሱና ብዙ ሰዎች ለኢየሱስ ትንሣኤ የዓይን ምሥክሮች ናቸው። ለሁሉም ሕዝቦች ምሥክሮች እንዲሆኑም ተልእኮ ተሰጥቷቸዋል። ጴጥሮስም «እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምሥክሮች፤ ... ለሕዝብም እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰኑ እርሱ እንደሆነ እንመሠክር ዘንድ አዘዘን። በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሠክሩለታል» ብሎ ተናገረ (ሐዋ. 10፡39፤ 41-43)። ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ እንደሆነና የኃጢአት

መሥዋዕትነቱም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘቱን የሚያረጋግጥልን ትንሣኤው ነው። ጴጥሮስ «በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደሆነ» ማለቱ እግዚአብሔር በሰዎች ሁሉ እንደሚፈርድ መገንዘቡን ያሳየናል። አይሁድ ይሁን አሕዛብ፤ ሁሉም በእርሱ ፊት ቀርበው ይፈረድባቸዋል። የዚህ ፍርድ ማምለጫ ብቸኛው መንገድ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው።

ጥያቄ 17፡- ከጴጥሮስ መልእክት ውስጥ፤ በእኛ ምሥክርነት ውስጥም ልናካትታቸው የሚገቡትን ዋና ዋና ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ጴጥሮስ እየተናገረ ሳለ፤ መልእክቱን በሚሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ እነዚህ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት በዚያ ክፍል ውስጥ ብቻ በመሆናቸው አይደለም። ወንጌሉ በሚብራራላቸው ወቅት፤ ወዲያውኑ እንዲቀበሉት በቅድሚያ ልባቸው በእግዚአብሔር በመዘጋጀቱ ነው እንጂ። በመጀመሪያ አይሁዳውያን ሳይሆኑ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን በመብቃታቸው ያለጥርጥር ሳይደነቁና እፎይ አረፍን ሳይሉ አይቀርም። ምንም እንኳ ባይገረዙም፤ እግዚአብሔር እንደ አይሁዳውያኑ በእኩል ዓይን አሕዛብን ወደ ቤተክርስቲያን እንደተቀበላቸው ለጴጥሮስና ለተቀሩት አይሁዳውያን ማረጋገጫ የሚሆነው በእነርሱ ላይ የወረደው መንፈስ ቅዱስ ነው። ከጴጥሮስ ጋር የነበሩት አይሁዳውያን ለአሕዛብም መንፈስ ቅዱስ በመስጠቱ በጣም ተደንቀዋል። አሕዛብ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑና በልሣን ሲናገሩ ሰሟቸው። አስተውል፤ በዚህ ሥፍራ ላይ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ፥ ጴጥሮስ እጁን በእነርሱ ላይ አልጫነም። እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ የወረደው መልእክቱን ሳይጨርስ ነው!! በበዓለ ሐምሳ ዕለት ለአይሁዳውያን የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ማስረጃ የሆናቸው በልሣን መናገራቸው ሲሆን፤ አሁን ይህንኑ ነገር እንደ ማስረጃ ይሰጣቸዋል። መንፈስ ቅዱስንም ልክ እንደ አይሁዳውያን በመቀበላቸው፤ ጴጥሮስ በኢየሱስ ስም እንዲጠመቁ ትዕዛዝ ይሰጣል። ከዚህ ጊዜ በኋላ፤ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ አሕዛብ ካመኑ በኋላ፤ በተለየ የመንፈስ ቅዱስን መቀበል ሥርዓት ውስጥ ማለፍ አለባቸው የሚል ነገር አናነብም። በምትኩ ግን ልክ እንደ ሳምራውያኑ፤ እግዚአብሔር በጴጥሮስ በመጠቀም እውነተኛ አማኞች መሆናቸውንና መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ መውረዱን ያረጋግጥ ነበር። ቆርኔሌዎስና ወዳጆቹ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት ልክ እንዳመኑ ነው። የውሃ ጥምቀትም፤ ከክርስቶስ ጋር ላላቸው አዲስ ግንኙነት ምሥክር ይሆን ዘንድ ካመኑ በኋላ የተፈጸመ ነው።

ጥያቄ 18፡- ቆርኔሌዎስ የጴጥሮስን መልእክት ከመስማቱ በፊት እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር። ታዲያ በኢየሱስ በማመኑ ያገኘው ነገር ወይም ጥቅም ምንድነው? ሐዋ. 11፡13-16።

ጥያቄ 19፡- በኢየሱስ በማመንህ ያገኘኸው ጥቅም ምንድነው? አሁኑኑ ላንድ አፍታ ቆም በልና ስለሰጠህ አስደናቂው ስጦታ እግዚአብሔርን አመስግን።

የደኅንነት በር ለአሕዛቦች ተከፈተ፤ ነገር ግን በአይሁዳውያንና በአሕዛብ መካከል የነበረው ውጥረት ቶሎ አልተቀጨም ነበር። ለብዙ ዓመታትም ይህ በአሕዛብና

በአይሁዳውያን መካከል ያለው ውጥረት በቤተክርስቲያን ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ነገር ነበር።

ጥያቄ 20:- በቤተክርስቲያን ሊወገዱ የማይችሉ አንዳንድ ታሪካዊ የሆኑ ጥላቻና ውጥረቶችን በዝርዝር ጻፍ።

# አራተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 11:1-18

እግዚአብሔር በግልጽ በክርስቶስ በኩል ያለው ደኅንነትና የመንፈስ ስጦታ ለአሕዛብና ለአይሁዳውያንም እንደሆኑ አሳይቷል። እንደ በዓለ ሐምሳውም ዓይነት ክስተት በቂሣሪያ ታይቷል። ይህም ሁሉ ሆኖ ግን፥ ብዙ አይሁዳውያን አማኞች ወደ ክርስቶስ መምጣት የሚቻለው በእስራኤላውያን ባህልና ልማድ በተለይም በመገረዝ በኩል ነው ብለው ያምኑ ነበር።

ከጴጥሮስ ጋር ወደ ቂሣሪያ አብረው ከሄዱት ደቀመዛሙርት መካከል አንዳንዶቹ አይሁዳውያን ነበሩ፥ ላልተገረዙም አይሁዳውያን መንፈስ ቅዱስ መሰጠቱ በጣም አስገርሟቸዋል። በአሕዛብ ላይ መንፈስ ቅዱስ ስለመውረዱ ምሥክሮች መሆናቸው ግን ጥሩ ነበር። ምክንያቱም ይህን ሐሳብ በተመለከተ ጭቅጭቁና ውዝግቡ ገና አልበረደም ነበርና ነው።

የሐዋርያት ሥራ 11: 1-18 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 21:- ሀ) በኢየሩሳሌም ይገኙ የነበሩት ሐዋርያትና ክርስቲያን ወንድሞች የቆርኔሌዎስንና በቂሣሪያ የሚገኙትን የሌሎቹን ሰዎች የመለወጥ ዜና የተቀበሉት እንዴት ነው? ለ) ጴጥሮስ ለፈጸመው ተግባር መከላከያ ያቀረበው እንዴት ነው? ሐ) በምን ዓይነት አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ጴጥሮስ መከላከያውን የጨረሰው? መ) ሐዋርያቱ የጴጥሮስን ማብራሪያና ሪፖርት የተቀበሉት እንዴት ነው?

ጴጥሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ከመመለሱ በፊት በኢየሩሳሌም የነበሩት አይሁዳውያን ክርስቲያኖች በእነርሱ ዓይን ሲታይ ተገቢ ያልሆነው በቂሣሪያ ስላሳየው መጥፎ ጸባይ ሰምተዋል። እንደ ወትሮው ወሬው በፍጥነት ተዛመተ። አያሌ አይሁዳውያን ክርስቲያኖችም ለእግዚአብሔር ታማኝ ባለመሆኑ ጴጥሮስን ወቀሱት። ጴጥሮስም ለትንሽ ጊዜ ያህል በቂሣሪያ ቆይቶ አዳዲሶችን የአሕዛብ አማኞች አስተምሯቸዋል። ወደ ኢየሩሳሌም እንደተመለሰ፥ «ከተገረዙት ወገን» የነበሩት ሰዎች ወዲያውኑ ጥያቄ ያቀርቡለታል። እነዚህ ሰዎች ስለ ሕጉ ቀናተኛ የነበሩ አይሁዳውያን ናቸው። ምንም እንኳ በኢየሱስ ክርስቶስ ቢያምኑም፥ ሙሉ በሙሉ ክርስቲያን ለመሆን ሰዎች መገረዝና የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት መከተል አለባቸው የሚል ግትር አቋም ነበራቸው። ጴጥሮስንም «ወዳልተገረዙ ሰዎች ገብተህ ከእነርሱ ጋር በላህ? ብለው ይነቅፉታል (ሐዋ. 11:3)። እውነተኛ አይሁዳውያን እንዳይረክሱ ሲሉ ከአሕዛብ ጋር ግንኙነት ማድረግ እንደሌለባቸው የሚጠቅሰውን ልማዳቸውን ባለመጠበቁ ነው የወቀሱት።

ጴጥሮስ በኢዮጴ ጣራ ላይ ሳለ ያየውን ራዕይና ንጹሕ ያልሆነውን ምግብ አልበላም ብሎ አሻፈረኝ ማለቱን በመናገር ስለ ምግባሩ መከላከያ ማቅረብ ነበረበት። ከዚህም በመቀጠል በቆርኔሌዎስ የተላኩት መልእክተኞች እንዴት እንደመጡና መንፈስ ቅዱስም እንዴት ሂድ እንዳለው ተናገረ። ጴጥሮስም የቆርኔሌዎስን ወደ እርሱ ሰው እንዲልክ ማድረግ እንዴት እንደተናገረው ሲሰማ፤ በእውነት እግዚአብሔር ምንም ዓይነት አድልዎ እንደማያሳይ ተገነዘበ። በመቀጠልም ጴጥሮስ ለአይሁዳውያኑ ወንድሞች በቆርኔሌዎስና በተሰበሰቡት ላይ ልክ እንደ በዓለ ሐምሳው ዕለት መንፈስ ቅዱስ እንደወረደባቸው ይገልጽላቸዋል። ጴጥሮስም መከላከያውን «እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላመንነው ለእኛ ደግሞ እንደሰጠን ያን ስጦታ ለእነርሱ ከሰጠ፤ እግዚአብሔርን ለመከልከል እችል ዘንድ እኔ ማን ነኝ?» በማለት ይደመድማል (ሐዋ. 11፡17)። እንደነዚህ ያሉ ወሬዎችን ማቆሚያው እንዱና ብቸኛው አማራጭ እውነቱን ነገር ሁሉ እንዲያውቀው ማድረግ ነው።

ጥያቄ 22፡- የጴጥሮስ መከላከያ የአይሁድ ክርስቲያኖች ክስ ሊያሸንፍ የቻለው ለምንድነው?

ጥያቄ 23፡- ሀ) ዛሬ በክርስቲያኖች መካከል የሚነሡ ክሶች ምን ዓይነት ናቸው? ለ) በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 11 ላይ እንዳለው አንዳንድ ቅሬታ የሕግን ነገር በተመለከተ ነው? አብራራው።

አንድ ክርስቲያን ብዙ ክርስቲያኖች ትክክል ነው ብለው ከሚገምቱት ነገር ውጪ ከሠራ፤ ምንም እንኳ ትንሽ መረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ቢኖረውም፤ አመኔታን ያጣል። ነገር ግን፤ እኛ የምናምነውና የምናደርገው ነገር በሙሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ እስካረጋገጥን ድረስ፤ እግዚአብሔር ለሌሎቹ ፈቃዱን እስኪያሳይ ድረስ ተቃውሞአቸውን በመጋፈጥ፤ ለእግዚአብሔር እስከመጨረሻው ታዛዥ ለመሆን፤ ፈቃደኞች መሆን አለብን።

ይህም ሁሉ ሆኖ፤ በአይሁዳውያንና በአሕዛብ መካከል የለውን ይህንን አንድነት ጴጥሮስ ሙሉ በሙሉ አልተገነዘበውም ነበር። ከጥቂት አመታት በኋላ፤ ብዙ የአሕዛብ ክርስቲያኖች ወደሚገኙባት ወደ አንጾኪያ ሄዶ ነበር። በዚያም ወቅት ከአይሁዳውያን ዘንድ ተቃውሞ ስለገጠመው፤ ጳውሎስ በግልጽ ፊት ለፊት፤ ስለ ግብዝነቱ እስከተቃወመው ጊዜ ድረስ ከአሕዛብ ጋር አልበላም፥ ኅብረት አልፈልግም ብሎ ቆይቶ ነበር (ገላ 2፡11-16 ተመልከት)።

ምንም የአይሁድ ክርስቲያኖች ለጊዜው የጴጥሮስን ቃል ቢቀበሉም፤ ሙሉ በሙሉ ከጴጥሮስ ጋር አልተስማሙም ነበር። በሐዋርያት ሥራ 15 ላይም፤ በኢየሩሳሌም የሚገኙ ክርስቲያኖች ጉባኤ አካሂደው በእግዚአብሔር ተቀባይነት ይኖራቸው ዘንድ አሕዛብ ማድረግ ስለሚገባቸው ነገር ውሳኔ አሳልፈዋል። በኢየሱስ ያመኑትን አሕዛብ እንደ እውነተኛ ክርስቲያኖች እንቀበላቸው ብላ ቤተክርስቲያን ከወሰነች በኋላ እንኳ፤ አይሁዳውያኑ በጳውሎስ ሚሲዮናዊ ጉዞ ላይ አብረውት በመሄድ፤ አሕዛብን መገረዝ አለባችሁ ብለው ያስተምሯቸው ነበር። በሮሜና በገላትያ መልእክትም ጳውሎስ ለእነዚህ አይሁዳውያን መልስ ይሰጣቸዋል።

ሰይጣን ሊያደርጋቸው ከሚፈልጋቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ወንጌልን ማጣመም ነው። ይህንንም የሚያደርገው:- ሰዎች ሊድኑበት የሚችሉት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ሆኖ ሳለ ሰይጣን ግን በዚሁም ላይ አለመጠጣትን፣ ወደ ሲኒማ አለመሄድንና የመሳሰሉትንም ማሟላት አስፈላጊ እንደሆነ ክርስቲያኖች ጨምረው ጨማምረው እንዲያስተምሩ በማድረግ ነው። እንዲሕ በማድረጉም ሰይጣን የጸጋውን ወንጌል የሥራ ወንጌል እንዲሆን ያደርገዋል ማለት ነው።

ጥ.ቁ 24:- አንድ ሰው ይድን ዘንድ፤ አንዳንድ በኢትዮጵያ የሚገኙ ክርስቲያኖች በወንጌሉ ላይ የሚጨምሯቸው ማሟያዎች ምንድናቸው?

ምንም እንኳ ብዙዎቹ በቤተክርስቲያን የተሰጡ ትዕዛዞች አስፈላጊ ቢሆኑም፤ ወንጌሉን በምናቀርብበት ወቅት ደኅንነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑን መግለጻችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል፤ በዚህም ላይ ጥንቃቄ መውሰድ አለብን። ወደ በኋላ አካባቢ ለእግዚአብሔር ቃል ወይም ለቤተክርስቲያን ሥርዓት ታዛዥ በመሆኑ ሕይወቱ እንደተለወጠ ማስረጃ ይሆነናል።

## ኦምስተኛ ቀን:-

## የሐዋርያት ሥራ 10: 1 - 11፤ 18 ክለሳ

ትምህርት ስምንትን ክልስና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥ.ቁ 1:- ሀ) የጴጥሮስ ራዕይ ትርጓሜ ምንድነው? ለ) ይህ ራዕይ፤ ጴጥሮስ ለጉብኝት ለሚመጡት ሰዎች የሚያደርገው አቀባበል ላይ ተጽዕኖ ያደረገው እንዴት ነው?

ጥ.ቁ 2:- በሐዋርያት ሥራ 10:30-33 ላይ ያለው የቆርኔሌዎስ ምሥክርነት የጴጥሮስን ግንዛቤ ያሰፋለት እንዴት ነው?

ጥ.ቁ 3:- ሀ) ቆርኔሌዎስ ምን ዓይነት ሰው ነበር? ለ) ከአገልጋዮቹ ስለ እርሱ ምን ልንማር እንችላለን?

ጥ.ቁ 4:- ሀ) ቆርኔሌዎስ እግዚአብሔርን የሚፈራ ከሆነ፤ ወደ ጴጥሮስ መልእክተኞችን መላክ ለምን አስፈለገው? ለ) ከጴጥሮስስ መልእክት ያገኘው ነገር ምንድነው?

ጥ.ቁ 5:- በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ክርስቲያኖች፤ ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሄዶ ከአሕዛብ ጋር ኅብረት ማድረጉን እንደ ትክክለኛ ነገር አድርገው እንዲቀበሉት ያደረጋቸው ምንድነው?

ጥ.ቁ 6:- የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10፡ በሐዋርያት ሥራ 1:8 መሠረት የእግዚአብሔርን ዓላማ ያስፈጸመው እንዴት ነው?

ለሳምንታዊው ስብሰባ ለመዘጋጀት ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት። ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ 3. ክለሳ

2. የጸሎት ጊዜ 4. ውይይት፡-

ሀ) 1. በኢትዮጵያ ውስጥ ትንሽ ግንኙነት ያላቸው ጎሳዎች ወይም የኅብረተሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው? 2. ብዙም ኅብረት የሌላቸው የክርስቲያን ቡድኖች የትኞቹ ናቸው? 3. ወንጌሉ በእነዚህ በተለያዩ ሥፍራዎች በምን ዓይነት መንገድ መሰናክሎቹን ማስወገድ እንዳለበት በዝርዝር ግለጽ 4. አንተና ቤተክርስቲያንህ በክርስቶስ ምንም ዓይነት ቅራኔ እንደሌለ ለማሳየት ምን ማድረግ ትችላላችሁ? 5. ምንም ዓይነት ጥላቻ እንዳይኖር ቤተክርስቲያንህ ሊታቫሸለው የሚገቧት በምን በምን ሥፍራ ነው?

ለ) 1. ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ሊነግራቸው የሚያስፈልጉ ናቸው ብሎ የተናገራቸውን ነገሮች በዝርዝር ግለጽ 2. አንዳንድ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች አንድ ሰው ይድን ዘንድ ከወንጌሉ ሌላ ማሟላት አለብህ ብለው የሚጠቅሷቸው ምን ምንድናቸው? 3. ሀ) የአንተ ቤተክርስቲያን አባሏቷ ክርስቲያኖች ይባሉ ዘንድ ማሟላት አለባቸው ብላ የምታምንባቸው ነገሮች በዝርዝር ግለጽ ለ) ከእነዚህ ውስጥ አንድ ሰው ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የምትነግረው የትኞቹን ነው? ሐ) አዲሱ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በተመለከተ አመለካከቱ ሲያድግስ የምትነግረው የትኞቹን ነው?

ሐ) በዛሬው ጊዜ አንዳንዶቹ ክርስቲያኖች መካከል ያሉት ቅራኔዎች ወይም ዕንቅፋቶች ምን ምንድናቸው? እነዚህን የምታስወግዱባቸው መንገዶች እያነሣችሁ ተወያዩባቸው።

መ) 1. በኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች ልንመገባቸው እንችላለን፤ አንችልም የሚሏቸውን ነገሮች በዝርዝር ጥቀስ። 2. ሰዎች የተወሰኑ ነገሮችን አንበላም የሚሉት ለምንድነው? 3. የተወሰኑ ምግቦችን ስለመብላትና ስላለመብላት በማርቆስ 7፡18-19 ላይ ካለው የኢየሱስ መልስና ከጴጥሮስ ራዕይ ልንማር የምንችለው ምንድነው?

5. ጸሎት ፡-

# ትምህርት 9

## የሐዋርያት ሥራ 11፡19 - 12፡25

## የመጀመሪያ ቀን፡-

## የሐዋርያት ሥራ 11፡19-30

ከዚህ በፊት እንዳየነው፤ እስጢፋኖስ ከተወገረና በሳዖል አማካኝነት ትልቅ ስደት ከተቀሰቀሰ በኋላ፤ አማኞቹ ተበታትነዋል። ከእነዚህ ከተበታተኑት ውስጥ ብዙዎች ሄሌናዊ አይሁዳውያን ነበሩ። ይኖሩባቸው ወደነበሩት እንደ አንጾኪያ፥ ቆጵሮስና ፊንቄ ወደተባሉት ሥፍራዎች በመመለስም በዚያ ለሚገኙት አይሁዳውያን መመሥከር ጀመሩ። የምሥራቹን ዜና ለቤተሰባቸውና ለወዳጆቻቸው ማካፈሉ ተገቢ ሲሆን፤ አንዳንዶቹ አይሁዳውያን አማኞች ግን ከዚህ አልፈው በቆጵሮስና በቀሬና ለሚገኙ አሕዛብ ይመሠክሩ ነበር። እነዚህ ሰዎች ያደጉት በአሕዛብ መካከል ስለነበር፤ በአሕዛብ ላይ የነበረው ጥላቻ በስፋት በተንሠራፋበት በኢየሩሳሌም ስለ ኢየሱስ ከመመሥከር በዚህ መመሥከሩ በጣም ይቀላቸው ነበር።

የዛሬው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፤ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሥር ነቀል ለውጥ የተካሄደበትን ቦታ ያሳየናል። እግዚአብሔር ጴጥሮስን መርቶ ለቆርኔሌዎስ እንዲመሠክርና በኢየሩሳሌም ለሚገኙ አይሁዳውያን ሊቀበላቸውና መንፈስ ቅዱስን ሊሰጣቸው ፈቃደኛ መሆኑ በገለጹበት በዚያኑ ወቅት፤ በስደት ምክንያት ተበትነው የነበሩት አማኞችም በአንጾኪያና በሶሪያ ለአሕዛብ መመስከር ጀመሩ። ብዙ አሕዛብ ሲያምኑ ቤተክርስቲያን በዚያው መጠን በፍጥነት አደገች። ወደ በኋላ፤ አንጾኪያ ዋነኛው የአሕዛብ ቤተክርስቲያን በመሆን ታገለግላለች፤ በተጨማሪም ወደ ተቀረው ዓለም ወንጌል ለመላክ እግዚአብሔር የሚጠቀምባት ይህችኑ ቤተክርስቲያን ነው።

የሐዋርያት ሥራ 11፡19-12፡25 አንብብና እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 1፡- ሀ) በስደቱ ምክንያት፤ ወንጌል የተሰራጨው በየትኞቹ ከተማዎች ነው?
ለ) የኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን በርናባስን ወደ አንጾኪያ የላከችው ለምንድነው?
ሐ) ንጉሥ ሄሮድስ በወንጌሉ ላይ ተቃውሞ ያስነሣው እንዴት ነው?
መ) ጴጥሮስ ወኅኒ ቤት የታሰረው ለምንድነው?
ሠ) ሄሮድስ በእግዚአብሔር መልአክ የተመታው ለምንድነው?

ጥያቄ 2፡- ሀ) እንዲመሠክሩ ወደ አንጾኪያ የተላኩት ሰዎች እነማን ነበሩ? የመሠከሩት ለማን ነው? ውጤቱስ ምን ነበር? ለ) በአንጾኪያ የበርናባስ አገልግሎት ምን ነበር? ሐ) ሳውልን በተርሴስ ለማግኘት በርናባስ ወደዚያ ያመራው ለምንድነው? በአንጾኪያ ለምን ያህል ጊዜ ኖሩ? በዚያስ ሳሉ ምን

አደረጉ? መ) አዲሷ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ነባሯን የኢየሩሳሌምን ቤተክርስቲያን የረዳችው በምን መንገድ ነው?

ቤተክርስቲያን አሕዛብን ወደ ኅብረት ማሳተፍ ከጀመረች በኋላ፤ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን በጣም በፍጥነት አደገች። እግዚአብሔርም በአሕዛብ መካከል ትልቅ የወንጌሉን ጥማት ፈጥሯል። ብዙዎች የጣዖት አምልኮ ምንም እርካታ አልሰጣቸውም። የቀደሙት አባቶቻቸው የተለያዩትን አማልክት በተመለከተ ይሰጧቸው የነበረው ትምህርት ትክክለኛ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ማሰብ ጀመሩ። እውነቱንም ለማወቅ በጣም ጥማት አደረባቸው። ብዙ አሕዛብም በአይሁዶች ሃይማኖትና የሁሉም ሕዝቦች ፈጣሪ በሆነው ጻድቅና ቅዱስ አምላክ ትምህርት ተማረኩ። ሆኖም፤ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ይፈጥሩ ዘንድ መገረዝን አልፈለጉም። ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ የሚነገሩትን እውነታዎች በሰሙና ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ለመፍጠር የግድ አይሁዳዊ መሆን እንደሌለባቸው ሲገነዘቡ ወዲያውኑ ወንጌሉን ተቀበሉ።

ብዙ አሕዛብ አማኞች ሆነዋል የሚል ወሬ በኢየሩሳሌም ሲደርስ የሚሆነውን ነገር በተመለከተ ጥርጣሬ ፈጥሯል። ቀደም ሲል የሚያምኑት አሕዛብ ብዛት ጥቂት ነበር፤ አሁን ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ከነበሩት አይሁዳውያን አማኞች እንኳ አማኞቹ በቁጥር እየበዙ መጥተዋል። የሚከናወነውን ነገር በተመለከተ ተገቢው ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ፤ ሐዋርያቱ በርናባስን ወደ አንጾኪያው ቤተክርስቲያን ይልኩታል። የአንጾኪያውን ቤተክርስቲያን የሚቆጣጠሩበት ምንም ዓይነት መንገድ ስላልነበራቸውና የትኛውም ሐዋርያ በዚያ የሚሠራውን ሥራ ስላላየ፤ ያለጥርጥር አንድ ሐሰተኛ መምህር ነው የጀመረው ብለው ሳያስቡ አልቀረም።

ከዚህ በፊት ከነበሩት ጥናቶቻችን እንደምታስታውሰው በርናባስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ከነበሩት ነባር አማኞች መካከል አንዱ ነው። በአሕዛብ መካከልም ይኖር የነበረ ሄሌናዊ አይሁድ ነበር። ይህም ቢሆን መንፈሳዊነቱን ለኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን አሳይቷል። ከዚህ ቀደም እንዳየነውም መሬቱን ሸጦ ገንዘቡን ለሐዋርያቱ ሰጥቷል። እግዚአብሔርም በዚህ ሰው ተጠቅሞ ጳውሎስን ከኢየሩሳሌም አማኞች እንዲያስተዋውቀው አድርጓል። ስለዚህም፤ ወደ አሕዛብ ከተማ ወደ አንጾኪያ እንዲላክ በርናባስ በመመረጡ ጥሩ ምርጫ ነበር። በርናባስ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ አየ፤ በዚህም በጣም ደስ ተሰኘ። አሕዛብ አማኞቹንም ለጌታ ታዛዥና ታማኝ እንዲሆን ያበረታታቸው ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ የነበረው የበርናባስ ሕይወትና አገልግሎቱ፤ ብዙ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ አምጥቷል።

ጥያቄ 3:- ሀ) በአንጾኪያ በአሕዛብ መካከል ሥራውን ይጀምር ዘንድ እግዚአብሔር በበርናባስና በጳውሎስ ከዚህ ቀደም በነበራቸው የአኗኗር መሠረት የተጠቀመው እንዴት ነው? ለ) ወንጌልን ለመዘርጋት ሲባል እግዚአብሔር እንደየአመጣጣቸው የተጠቀመባቸው አንዳንድ የቤተክርስቲያን መሪዎች የምታውቅ ከሆነ ለምሳሌ ጥቀስ።

በሮማው መንግሥት፤ አንጾኪያ ሦስተኛዋ ትልቅ ከተማ ነበረች። ከኢየሩሳሌም 500 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የምትገኘው የዚህች ከተማ ዜጎች፤ ለሥራ ትልቅ ትጉትና ፍቅር ነበራቸው ይባል ነበር። ነገር ግን በሮማው መንግሥት ውስጥ፤ በጣዖት አምልኮና በሥርዓት የለሽነት ከሚታወቁት ከተሞች አንዷ ናት። አንጾኪያ አስታርቴ የተባለችዋን ዕውቅ ጣዖት በማምለክ በጣም የታወቀች ከተማ ነበረች። ከአምልኮ ጋር የተያያዘ ዝሙተኝነትም ነበረ። ከከተማዋም አቅራቢያ ለታወቀው የግሪክ አማልክት ለአፖሎ የተሠራ ቤተመቅደስና ከአፖሎ ለማምለጥ ስትል ወደ ዛፍነት ተለወጠች ለምትባለው ዳፌን ለምትባለው አማልክት መታሰቢያ ዛፎች ተተክለው ነበር። ጳውሎስም ለአሕዛብ ክርስቶስን መስበክ የጀመረው በዚህ ከተማ ነው።

እስካሁን ጊዜ ድረስ፤ ክርስትና የአይሁዶች እምነት ክፍል ተብሎ ነበር የሚቆጠረው። ነገር ግን አይሁድ ያልሆኑ ሰዎችን ቤተክርስቲያን መቀበል ስትጀምር፤ ከቀድሞው የአይሁድ ሃይማኖት እራሷን እየለየች መጣች። የጥንቶቹም ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው «ነቢያት፤ ደቀመዛሙርት፤ ቅዱሳን» የሚል ስያሜ ይሰጣጡ ነበር። ወይም ደግሞ «መንገዱን የሚከተሉ» ተባብለው ይጠራሩ ነበር። ሆኖም በአንጾኪያ የነበሩት የማያምኑ ሰዎች ምናልባት አማኞቹ ላይ ለማላገጥ ሲሉ «ክርስቲያኖች› ብለው ጠርተዋቸው ይሆናል። መነሾው አሽሙር ይሁን እንጂ የመጥሪያው እውነት የክብር ስም ነው ትርጓሜውም ‹የክርስቶስ ወገኖች› ማለት ነው።

የጥንት ክርስቲያኖች ክርስቶስን ለመከተል ቁርጠኛ የሆነ ፍላጎት ነበራቸው። ይህንንም የማያምኑት ሰዎች እንኳ ያውቁት ነበር። ምንም እንኳ «ክርስቲያን» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ሁለቴ ብቻ ቢጠቀስም (ሐዋ. 26፡28፤ 1ጴጥ. 4፡16)፤ በጊዜው ክርስቲያን የሚለው ስም ይሰጥ የነበረው በክርስቶስ ስለሚያምኑ ነበር።

ጥያቄ 4፡- ሀ) በአንተ ኅብረተሰብ ውስጥ «ክርስቲያን» የሚለውን ስም ሰዎች የሚጠቀሙበት እንዴት ነው? ለ) ስላንተ ቢጠየቁ፤ ጎረቤቶችህ እሱ አማኝ ነው ይሉሃል? ሐ) የማያምኑ ሰዎች ዛሬ ክርስቲያኖችን ለማናደድ ሲሉ የሚጠቀሙባቸው ስሞች ምንድናቸው?

ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ የትንቢት ስጦታ ነው። ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ ነቢይ የወደፊቱን የሚናገር ሰው ነው ብለን ብናስብም፤ በብሉይ ኪዳን መሠረት ደግሞ ነቢዩ ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ መልእክት ለሕዝቡ ይዞ የሚያመጣ ሰው ነው። አንዳንድ ጊዜ፤ መልእክቱ ወደፊት ስለሚሆኑ ነገሮች የሚጠቅስ ነው። ሆኖም፤ ብዙ ጊዜ በዚያን ዘመን ለነበሩ ሰዎች ይሰጥ የነበረው መልእክት ንስሐ እንዲገቡ የሚያመለክት ነበር።

ጥያቄ 5 ፡-ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ውስጥ አምስቱን ግለጽ። ከትንቢቶቻቸው ውስጥ ስለ ወደፊቱ የማይጠቅሱ ነገር ግን ከሕዝቡ ጋር ብቻ የተገናኙ አንዳንድ ትንቢቶቻቸው ምን ምንድናቸው? (ለምሳሌ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 12፡ 1-14፤ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17፡1፤ ትንቢተ ኤርምያስ 44፡11-14)።

በጥንቷም ቤተክርስቲያን ውስጥ ነቢያት ነበሩ። በዚያን ወቅት አዲስ ኪዳን ባለመጻፉ እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች መልእክት ይሰጥ የነበረው በእነዚህ ሰዎች በኩል ነው። ከእነዚያ መልእክቶች ደግሞ ብዙዎቹ ከወደፊቱ ሁኔታ የተያያዙ አይደሉም።

ጥያቄ 6:- ሀ) በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ነቢያት አሉ? ለ) ካሉ፤ ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ነቢያት ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? ሐ) እውነተኛ ነቢያት ወይም ሐሰተኛ ነቢያት እንደሆኑ የሚታወቁባቸው አንዳንድ መለኪያዎች ምንድናቸው?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ካሉት የታወቁ ነቢያት መካከል አንዱ አጋቦስ የሚባል ሰው ነው። እሱም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ በመላው የሮማ መንግሥት ውስጥ ታላቅ ረሐብ እንደሚመጣ ተነበየ። ይሁዳ በጣም ድሃ አገር ነበረች፤ በዚህም ምክንያት በአንጾኪያ ይገኙ የነበሩት ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም የሚገኙ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው በረሐብ ላይ እንደሚወድቁ ተገነዘቡ። ምንም እንኳ በይሁዳ ይገኙ የነበሩትን ክርስቲያኖች ባያውቋቸውም፤ በአንጾኪያ ይገኙ የነበሩትም ደቀመዛሙርት በይሁዳ ይገኙ ለነበሩት ወንድሞች ዕርዳታ ለማድረግ ወሰኑ፤ ገንዘባቸውንም አሰባስበው በሳውልና በበርናባስ በኩል ለኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ይልካሉ። በስጦታቸውም በክርስቶስ ያሏቸውን አንድነትና ፍቅር ገልጸዋል። ክርስቲያኖች ሕይወታቸው መለወጡን የሚገልጹበት መንገድ አንዱ ለማያውቋቸው ሰዎች ፍቅር በማሳየት ነው።

ጥያቄ 7:- ሀ) ያንተ ቤተክርስቲያን ለማታውቋቸው ክርስቲያኖች በችግራቸው ወቅት የደረሰችላቸው እንዴት ነው? ለ) ይህን ዓይነቱን ተግባር ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ ሊፈጽም የሚችለው እንዴት ነው?

የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን አድጋ ሌሎችን ስትረዳ፤ በጊዜው ካሉት ቤተክርስቲያኖች ሁሉ የበላይ ሆነች። በዚህ ጊዜ ውስጥ ደግሞ፤ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ ነበረች። ረሐቡ ብቻ ሳይሆን፤ አዲስ የስደት ዘመቻ ተከፍቶባት ነበር። ንጉሥ ሄሮድስ ታዋቂነትንና ድጋፍን ከአይሁዶች ዘንድ ይሻ ነበር። ይህንን ነገር ለማግኛ እንደ ሁነኛ መንገድ አድርጎ የያዘው ክርስቲያኖችን ማሳደድ ነበር።

ጥያቄ 8:- ሀ) ጠንካራ የሆኑ ቤተክርስቲያኖች አንዳንዴ ገለል ተደርገው ሌሎች ቤተክርስቲያኖች የመሪነቱን ወይም የበላይነቱን ሥፍራ የሚይዙት ለምን ይመስልሃል? ለ) በአካባቢህ ይህ ነገር ሲሆን አይተህ ታውቃለህ? እንዲህ ሊሆን የቻለው ለምንድነው?

ጥያቄ 9:- ሀ) በአሁኑ ወቅት መንፈሳዊው ሕይወትህ በሰላምና በዕድገት ጊዜ ውስጥ ነው ወይስ የችግር ጊዜ ውስጥ ነው ያለው? እግዚአብሔር በሰላሙ ወይም [illegible]ግሩ ወቅት ያስተምርህ የነበረው ነገር ምንድነው? ለ) ?ቤ ክርስቲያንህና በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ በችግር ውስጥ የሚኖሩትን

አማኞች ስም ዝርዝር አውጣ። የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም የነበሩትን አማኞች እንደረዳቻቸው አንተና ቤተክርስቲያንህ ችግረኞቹን ልትረዷቸው የምትችሉት እንዴት ነው?

## ሁለተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 12፡ 1-5

እግዚአብሔር በአንጾኪያ ትገኝ የነበረችውን ቤተክርስቲያን ይባርካትና ብዙ አሕዛብ ክርስቲያኖች ይጨመሩባት ነበር። በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ነገሮችን እንዲያጣራ የተላከው በርናባስ፤ መጣር እንደሚገባቸው በብርቱ ተገንዝቧል። ይህም እርሱ ሊያደርገው ከሚችለው በላይ በመሆኑ በርናባስ ወደ ተርሴስ በመሄድ ሳውልን እንዲረዳው ይዞት ይመጣል። ብዙ ሰዎችንም እንዳስተማሩ፤ በሚቀጥለው ዓመት ውስጥ ቤተክርስቲያኒቱ እድጋ ሌሎች በችግር ውስጥ ያሉትን እስከ መርዳት ደረሰች።

በማቴዎስ 28፡ 19 ላይ፥ ኢየሱስ ታላቁን ተልእኮ ለሐዋርያቱ በሰጣቸው ጊዜ እንዲመሁከሩ ብቻ ሳይሆን ሕዝቦች ሁሉ እውነተኛ የእርሱ ደቀመዛሙርት እንዲሆኑና ትዕዛዛቱንም ሁሉ እንዲያስተምሩ ጭምር ነው። ቤተክርስቲያን የጠፉትን ፈልጎ የማግኘት ብቻ ሳይሆን፤ ለእነርሱ የእግዚአብሔርን እውነታ የማስተማር ሐላፊነትም ጭምር ነው ያለባት።

ጥያቄ 10፡- አዳዲስ ክርስቲያኖች እውነተኛ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት እንዲሆኑ፤ ቤተክርስቲያንህ የክርስትናን እውነታዎች የምታስተምራቸው እንዴት ነው?

የአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን በሚያስደንቅ ዕድገት ውስጥ በምታልፍበት በዛች ወቅት የቤተክርስቲያኖች እናት በሆነችው በኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን ላይ እንደገና ስደት ይነሣባታል። አንዳንዴ የእግዚአብሔር አሠራር እርስ በርሱ የሚቃረን ይመስላል፤ ሆኖም የእርሱ መንገድ እንደ ሰዎች መንገድ አይደለም።

ጥያቄ 11፡- ሀ) የሃይማኖት መሪዎች ሐዋርያቱን የተቃወሟቸው ለምንድነው? ለ) የአሕዛብ በቤተክርስቲያን ውስጥ መግባት በቤተክርስቲያን ላይ የተነሣውን ተቃውሞ አባብሶታልን? ለምን?

ክርስትና እየጨመረ በመሄዱ ከአይሁዶች የሚነሣው ተቃውሞ ደግሞ በዚያው መጠን አደገ። የጥንቷ ቤተክርስቲያን ቀንደኛ ጠላት የሮማው መንግሥት ሳይሆን፥ አይሁዳውያን ነበሩ። የሮማው መንግሥት ክርስቲያኖችን በፅኑ ማሳደድ የጀመረው ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው። ክርስትና የአይሁድ ሃይማኖት ክፍል ብቻ መሆኑ ሲቀርና የአይሁድ ክርስቲያኖች በግልጽ ከአሕዛብ ጋር ኅብረት ሲያደርጉ የአይሁድ መሪዎች ተቃውሞ ጨመረ።

ጥያቄ 12፡- በስደት ወቅት፤ የቤተክርስቲያን ሁነኛ መሣሪያ ምንድነው?

የሐዋርያት ሥራ 12፡ 1-5 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ። ጥያቄ 13 ሀ) በይሁዳ የነበረው ገዢ ማን ነበር? ለ) ያዕቆብን የገደለው ለምንድነው? ሐ) ጴጥሮስን

ይዞ ያሰረው ለምንድነው? መ) ጴጥሮስን ወዲያውኑ ሳይገድለው ወደ ወኅኒ ያስገባው ለምንድነው?

በአዲስ ኪዳን የሄሮድሶች ሐረግ ዘመነ መንግሥት ውስጥ ያለፉ ነገሥታት ሁሉ እውነቱን ይቃወሙ የነበሩ እርኩስ ሰዎች ነበሩ። ምንም እንኳ የተለያዩትን ሄሮድሶች ለያይቶ ማስቀመጡ ቢከብድም፤ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት ስም ዝርዝር ግን የሚከተለው ነው:-

1. የዚህ ሐረግ የመጀመሪያው ንጉሥ:- ታላቁ ሄሮድስ ኢየሱስ ሲወለድ በኢየሩሳሌም የነበረው ንጉሥ ነው። የኤዶምያስን፥ የይሁዳን፥ የሰማርያን፥ የገሊላን፥ የጥርኮዲኖስንና የዮርዳኖስን ማዶ ግዛቶች ያስተዳድር ነበር። እንደምታስታውሰውም ኢየሱስ ክርስቶስን ለመግደል ሲል፥ በቤተልሔም ይገኙ የነበሩትን ሕፃናት በሙሉ ፈጅቷል። ዘመነ መንግሥቱም ከ 37 ዓመት እስከ 4 ዓክልበ ነበር።

2. ታላቁ ሄሮድስ ሲሞት፤ ይህን ሰፊ መንግሥቱን ሦስት ወንድ ልጆቹ ይከፋፈሉታል። አርኬላዎስ የተባለው ልጁ ኤዶምያስ፥ ይሁዳንና ሰማርያን ይገዛል (ከ 4 አክልበ - 6 ዓ.ም) (ማቴ. 2፡ 19-23 ተመልከት)። የገሊላና የዮርዳኖስ ማዶ ገዢ የነበረው ሄሮድስ ደግሞ አንቲፓስ ነው (ከ 4 ዓክልበ - 39 ዓ.ም)። በአዲስ ኪዳን በብዙ ሥፍራ የሚጠቀሰው ይህ ሄሮድስ ነው፤ ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስን የገደለ እሱ ነው፤ ኢየሱስም ለፍርድ የቀረበው በዚህ ሰውዬ ፊት ነው። የጥራኮዲኖስ ገዢ የዳግማዊ ሄሮድስ ፊሊጶስ ነበር (ከ 4 ዓክልበ - 34 ዓ.ም)። ይህ ሰው በሉቃስ 3፡1 ላይ ተጠቅሷል።

3. ሌላው በአዲስ ኪዳን ያልተጠቀሰው የሄሮድስ ወንድ ልጅ አሪስቶቡለስ ሲሆን፤ ይህም ሰው የኤዶምያስ፥ የይሁዳና የገሊላ ገዢ የሆነው የቀዳማዊ ሄሮድስ አግሪጳ አባት ነው (ከ 37 ዓ.ም - 44 ዓ.ም)። ይህ፥ በዛሬው ታሪክ ውስጥ አይሁድን ለማስደሰት ሲል ያዕቆብን የገደለና ጴጥሮስን ያሳሰረው ሄሮድስ ነው።

4. ዳግማዊ ሄሮድስ አግሪጳ፥ የቀዳማዊ ሄሮድስ ልጅ ሲሆን፥ በትረ ሥልጣኑን ከአባቱ ወሰደ። ጳውሎስ በወኅኒ ሳለ መከላከያውን ያቀረበው ለዚህ ንጉሥ ነው (ሐዋ. 25፡13-26፡ 32)።

ቀዳማዊ ሄሮድስ አግሪጳ ያደገው በሮም ሲሆን፥ ከንጉሥ ቲብሪስ በኋላ በ 37ዓ.ም ንጉሥ የሆነው የግዩስ ወዳጅ ነበር። ንጉሥ ግዩስም ለሄሮድስ «ንጉሥ» የሚል ሹመት በመስጠት፥ የደቡብ ሶሪያ ገዢ ያደርገዋል። ከሁለት ዓመት በኋላም ገሊላና ዮርዳኖስ ማዶ በግዛቱ ይጨመራሉ። በ 41 ዓ.ም ላይ ቀላውኪዮስ ንጉሥ በሆነ ጊዜ ደግሞ፥ በይሁዳ በሄሮድስ ግዛት ውስጥ ትጨመራለች።

ሄሮድስ በኢየሩሳሌም በሚገኙ በአይሁድ የሃይናኖት መሪዎች መካከል ዝና ለማግኘት ሲል፤ክርስቲያኖችን ማሳደድ ጀመረ። የመጀመሪያው የሄሮድስ ሰለባ የዮሐንስ ወንድም የነበረው ያዕቆብ ነው። የሰማዕት ሞት የሞተው የመጀመሪያው

ሐዋርያ እሱ ነው። የያዕቆብ ሞት ኢየሱስ በማርቆስ 10፡ 38-39 የተናገረው ቃል ፍጻሜ ነው።

የያዕቆብ ሞት አይሁዶችን ስላስደሰታቸው፥ ሄሮድስ ጴጥሮስ እንዲያዝ ያደርጋል። ሆኖም፥ የፋሲካ በዓል ሳምንት በመሆኑ ምክንያት፥ በዓሉ እኪያልፍ ድረስ በወኅኒ እንዲቆይ ተደረገ። ከፋሲካ በኋላም ሄሮድስ በጴጥሮስ ላይ ይፋ የሆነ ክስ አቅርቦ ሊገድለው ዓቀደ።

ጥያቄ 14፡- ያዕቆብ መገደሉን በማስታወስ፥ ለጴጥሮስ እንዴት አድርገህ ነበር የምትጸልይለት?

ከፈቀድንለት ሁሉን ነገር ለክብሩና ለመንፈሳዊ ዕድገታችን ይጠቀምበታል። ስደትን መቆጣጠር ባንችልም፥ ለስደት የሚኖረንን አመለካከትና ምላሽ ልንቆጣጠር እንችላለን። በስደት ወቅት እግዚአብሔር የሚያስተምረንን ነገር በጥሞና መስማት ያስፈልገናል። በዚህም ወቅት በድፍረት ልንጠይቀውና ሙሉ በሙሉ ልንታመንበት እንችላለን። ምክንያቱም ማንኛውም የሚሰጠን ምላሽ፥ በእርሱ ታላቅ እቅድ ውስጥ እንደሆነ እናውቃለንና ነው።

ምናልባት ሄሮድስ ከዚህ በፊት ጴጥሮስ ከወኅኒ ቤት ማምለጡን ያውቅ ስለነበር፤ ከፍተኛ ጥበቃ አቁሟል። በአንድ ጊዜ የሚጠብቁት አራት ወታደሮች ነበሩ፤ በግራና በቀኝ የታሠረው ከሁለት ወታደሮች ሲሆን ሌሎቹ ሁለት ወታደሮች ደግሞ የወኅኒውን በር ይጠብቃሉ። ሆኖም፤ ጴጥሮስ እንዳያመልጥ ሲል ሄሮድስ ያደረገው ዝግጅት ፋይዳ ቢስ እንደሆነ እናያለን። እግዚአብሔር በሠንሠለት ወይም በወታደር አይገታም። ጴጥሮስ በወኅኒ ሳለም ቤተክርስቲያን አጥብቃ ትጸልይ ነበር።

ጥያቄ 15፡- ሀ) ኢየሱስ እንዲሞት እግዚአብሔር የፈቀደው ለምንድነው? ምክንያቶቹን በሙሉ እናውቃቸውም፤ ሆኖም እስቲ ሮሜ 8፡ 28-29 ተመልከት። ለ) ሁኔታዎች እንደዚህ የሚሆኑት ለምንድነው ብለን መልስ ስናጣ፥ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለኛ የተሰጠን የተስፋ ቃል ምንድነው?

ጥያቄ 16፡- ሀ) አንዳንድ በሕይወትህ ግራ የሚያጋቡህና ለምን እንደሆኑ የማታውቃቸው ነገሮች ያጋጥሙሃልን? ለ) በድፍረት መጸለይንና፥ የሚሆነው ነገር በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ እንደሆነ መረዳትን ተምረሃልን? ሐ) በዚህ በሚያደናግር ሁኔታ ውስጥ፥ እግዚአብሔር የሚያስተምርህን ነገር ለመስማት ዝግጁ ነህን?

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የሚሠራው ከምንጠብቀው ውጪ ነው። ያለጥርጥር ክርስቲያኖቹ እግዚአብሔር ያዕቆብን ከሞት ይጠብቀዋል ብለው ተስፋ ነበራቸው። ሌሎች ደግሞ፥ ምንም እንኳ ጴጥሮስ እንዲለቀቅ ቢጸልዩም፥ ይሞታል ብለው ነበር የሚጠብቁት። እግዚአብሔር ግን ጴጥሮስን ነፃ አወጣው። በሁለቱም ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር ፈቃዱን ነበረ የሚፈጽመው። በኛ ላይ ስለሚሆኑትም ብዙ ነገሮች ሙሉ የሆነ ግንዛቤ የለንም። አንዳንዴ የምንጸልይም ብንሆን እንኳ፥ እግዚአብሔር እኛ እንደጠበቅነውና እንደፈለግነው መልስ አይሰጠንም። ይህም ቢሆን፥ እግዚአብሔር

ሁኔታዎችን እንደሚቆጣጠር በማወቅ፥ እኛ የጠበቅነውን መልስ ባይሰጠን እንኳ በእርሱ ላይ መታመን አለብን። ዋናው ቁም ነገር እኛ ሁሌ ለእርሱ ታማኞች ሆነን መቆም ነው።

## ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 10፡ 6-19

ለኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን፥ ጊዜው በጣም የከፋ ነበር። የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ በሄሮድስ ተገድሏል፥ ጴጥሮስ በወኅኒ ገብቶ በሕዝብ ፊት በክስ ቀርቦ የሚሞትበትን ቀን እየተጠባበቀ ነው። የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን እንደገና በስደት ውስጥ እያለፈችና ለጴጥሮስ በጽኑ እየጸለየች ነው። የሁሉም እናት የሆነችው የኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን ገናናነቷን አጥታ እየተስፋፋች ከሄደችው ከአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን የበታች ሆናለች።

ሄሮድስ በሚቀጥለው ቀን ጴጥሮስን ለፍርድ ለማቅረብ ነበር ዕቅዱ። በዚያን ምሽት፥ ምንም እንኳ በሁለት ወታደሮች መካከል ቢታሠርም! ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ነበር የወሰደው። ከዚያም እግዚአብሔር ለጸሎቱ መልስ ይሆን ዘንድ! ኃይሉን የሚገልጽበት ሰዓት ደረሰ።

የሐዋርያት ሥራ 12፡ 6-19 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 17፡- ሀ) የጴጥሮስን ከጽኑ ጥበቃ ወኅኒ ቤት ነፃ መውጣት በስፋት አብራራው። ነፃ ያወጣው ማነው? ለ) ከወኅኒ ወጥቶ እራሱን በከተማው መንገድ ላይ ሲያገኝ ምን አለ? ምንስ አደረገ? ጴጥሮስ ወዴት ነው የሄደው? ሐ) ይጸልዩ የነበሩት ክርስቲያኖች፥ ጴጥሮስ ነፃ ይወጣል ብለው ይጠብቁ ነበር? በመጀመሪያ ወደ ቤት ውስጥ ያላስገቡት ለምንድነው? መ) ጴጥሮስ፥ እማኞቹን ምን እንዲያደርጉ ነው የጠየቀው?

እግዚአብሔር ተቃውሞችን በተለያዩ መንገዶች ያስተናግዳል። አንዳንዴ ልጆች እንዲሞቱ ይተዋቸዋል! አንዳንዴ ደግሞ አስገራሚ ተአምራትን በመሥራት ነፃ ያወጣቸዋል።

ጴጥሮስ በወኅኒ ሳለ፥ ነፃ መውጣቱን በተመለከተ ክርስቲያኖቹ በፅኑ ይጸልዩ ነበር። ብዙ ክርስቲያኖች ማርቆስ ተብሎ ይጠራ የነበረው የዮሐንስ እናት ቤት ተሰብስበው ነበር። ማርቆስ አሁን ወጣት ቢሆንም፥ ወደ በኋላ ላይ ግን እግዚአብሔር በእርሱ በጣም ይጠቀምበታል። በጳውሎስና በበርናባስ የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ ላይ ይህ ሰው አብሯቸው ሄዷል። በኋላ ላይም! እግዚአብሔር በዚህ ሰው ተጠቅሞ የማርቆስ ወንጌልን ይጽፋል።

እነሱ በሚጸልዩበት ወቅት፥ ጴጥሮስ ተኝቶ ነበር። ምንም እንኳ አሁን ሊገደል ቢዘጋጅም፥ ነፍሱ በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነች ግን በሚገባ ያምን ነበር። አእምሮን ሁሉ የሚያልፈው የእግዚአብሔር ሰላምም በእርሱ ነበር (ፊሊ. 4፡7)። ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዶት ሳለ፥ መልአክ ይመጣና ጴጥሮስን ይቀሰቅሰዋል። የታሠረበትንም ሰንሰለት ፈቶ ጴጥሮስን ወደ ውጭ ያወጣዋል። እግረ መንገዳቸውንም እየወጡ ሳለ፥

ጴጥሮስን እንዳያዩት መልአኩ የወታደሮቹን ዓይን ይጋርድ ነበር። ከወኅኒውም ወጥተው ትንሽ ራመድ ካሉ በኋላ፥ መልአኩ ጴጥሮስን ትቶት ይሄዳል።

ጴጥሮስ ይህ ሕልም አለመሆኑን ሲገነዘብ፥ ብዙ ክርስቲያኖች ተሰብስበው ይገኙበት ወደነበረው ወደ ማሪያም ቤት ያመራል። ደህና እንደሆነና እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንደሰማላቸው ሊያበሥራቸው ፈልጓል። ፅኑ ጥበቃ ካለበት ወኅኒ ቤት የጴጥሮስ በአስገራሚ ሁኔታ መውጣት፥ ይጸልዩ የነበሩትን ክርስቲያኖች በጣም አስደንቋቸዋል። ሮዴ የተባለችው ገረድ ለጴጥሮስ ልትከፍትለት ስትመጣ፥ ከደስታዋ የተነሣ በሩን ሳትከፍትለት ተመልሳ ትሄዳለች። ተሰብስበው ይጸልዩ ለነበሩትም ሰዎች፥ ጴጥሮስ በሩ ላይ ቆሟል ስትላቸው አላመኗትም። በመጨረሻም ከፍተው ሲያዩት በጣም ተገረሙ!! ጴጥሮስም ዝም እንዲሉ ምልክት ከሰጣቸው በኋላ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ከወኅኒ እንዳስወጣው ነገራቸው። ከዚያም ጴጥሮስ «ለያዕቆብና (የኢየሱስ ወንድም) ለወንድሞች ንገሩ» አላቸው። ከዚህም በኋላ ከኢየሩሳሌም ወጥቶ ወደ ሌላ ሥፍራ ሄደ። በዚህ ጊዜ የኢየሱስ ወንድም የነበረው ያዕቆብ፥ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪ ነበር። ኢየሱስም ከትንሣኤው በኋላ በተለየ መልክ ለእርሱ ከተገለጠለት በኋላ፥ እምነቱን በእርሱ ላይ ሊያደርግ በቅቷል። ወደ በኋላ ላይም የአይሁድ ቤተክርስቲያን መሪ በመሆን አገልግሏል።

**ጥያቄ 18፡- ድንቅ የሆነውን የመማለድ ጸሎት ኃይል የተለማመድከው እንዴት ነው? ኤፌሶን 3፡ 20-21 የሚነግረን ምንድነው?**

ክርስቲያኖቹ ቢገረሙም፥ በማግሥቱ ጠዋት በወኅኒ ቤት አካባቢ የነበረው መገረም ከዚህ ይበልጥ ነበር። ጴጥሮስ የት ሄደ? ሰንሰለቶቹ በወታደሮቹ እጅ ላይ እንዳሉ ናቸው። ታዲያ ከወኅኒ ቤት እንዴት ሊወጣ ቻለ? ሄሮድስ ጴጥሮስ እንዲፈለግ አዘዘ፤ ሊያገኙት ባልቻሉም ጊዜ፥ ወታደሮቹን መርምሮ እንዲገደሉ አዘዘ። በሮማው ዓለም ውስጥ፥ ከወታደሮቹ እጅ አንድ እሥረኛ ካመለጠ፥ ወታደሮቹ በሞት ይቀጡ ነበር።

**ጥያቄ 19፡- እግዚአብሔር አንዱ ሐዋርያ እንዲሞት ሌላኛው ደግሞ ነፃ እንዲወጣ ያደረገው ለምንድነው?**

በጴጥሮስ ነፃ መውጣት፥ የእግዚአብሔር ኃይል በሚያስደንቅ ሁኔታ ተገልጿል። በዚህ ተአምራት የእግዚአብሔር መሣሪያ የነበሩት፡- 1. የክርስቲያኖቹ ጸሎት፤ ቤተክርስቲያን ለጴጥሮስ በጽኑ ትጸልይ ነበር። ጴጥሮስ እንዲፈታ ነበር የሚጸልዩት ባይልም፥ ይጸልዩ ነበር (ሉቃስ 11፡9 እና ዮሐንስ 15፡7 ተመልከት)። 2. አገልጋይ መልአክ፡- «ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ፥ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን? (ዕብራውያን 1፡ 14)።

መንገዱ ድረስ እስኪወጣ፥ ጴጥሮስ መልአክ ይመራኛል ብሎ አላሰበም ነበር፤ ምንም እንኳ ባናያቸውም በመካከላችን መኖራቸውንም ባንገነዘበውም፥ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑት መላእክት አሁንም እየሠሩ ነው።

ጸሎት የእግዚአብሔር ኃይል እንዲገለጽ ያደርጋል። ጌታ ለሁሉም ዓይነት ጸሎቶች መልስ ይሰጣል! አንዳንዶቹ አዎንታዊ መልሶች ናቸው! ሌሎቹ ደግሞ አሉታዊ

ቸው። ለአንዳንድ ጸሎቶች ደግሞ መልስ ለመስጠት፥ ለትንሽ ጊዜ እንድንቆይ ይነግረናል። እነዚህ ሁሉ፥ እግዚአብሔር በወሰነው ሰዓት ለእርሱ ክብርና ለእኛ በጎነት የሚሰጡ መልሶች ናቸው። መጠየቅ አለብን፤ ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መልስ ሰጠን ብለን እግዚአብሔርን መናገር የለብንም። በእምነት መጸለይ አለብን፤ ዳሩ ግን በምንጸልይበትም ጊዜ ፈቃዱን ለማወቅ ደግሞ ማዳመጥ ይኖርብናል።

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 12፡ 20-26

ጴጥሮስ ከእሥር ቤት ካመለጠ በኋላ፥ በክርስቲያኖች ላይ የመጣው ስደት እየቀነሰ መጥቷል። ምንም እንኳ ሄሮድስ እሥረኛውን ቢያስፈልገውም፥ ሊያገኘው ባለመቻሉ፥ ወታደሮቹ እንዲገደሉ ያደርጋል። ከዚህም በኋላ ከይሁዳ ተነሥቶ ወደ ቂሣሪያ ይሄዳል። ሄሮድስ በኃይሉና በሥልጣኑ በጣም ይመካ ነበር። መሪዎችን የሚያስነሣና የሚጥል እግዚአብሔር መሆኑን ዘንግቶ ነበር። ይህም የሄሮድስ ኩራትና ግን አለብኝነት፥ የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ እንዲወርድበት አድርጓል።

የሐዋርያት ሥራ 12፤ 20-25 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 21፡- ሀ) ሄሮድስ የተጣላው ከማን ጋር ነው? አይሁድ ከንጉሥ ጋር ሰላም የፈለጉት ለምንድነው? ለ) ሄሮድስን በተመለከተ፥ ሕዝቡ ያለው ምንድነው? ሐ) በንጉሥ ሄሮድስ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ እንዲወርድበት ያደረገው ነገር ምንድነው? ፍርዱ ምን ነበር? መ) ቤተክርስቲያን በዚህ ወቅት ስለነበረበት አቋምና ሁኔታ ግለጽ ሠ) በርናባስና ጳውሎስ ምን ነበር የሚያደርጉት? አብሯቸውስ የነበረው ማነው?

እግዚአብሔር ነፃ አውጥቶት ስለነበር፥ ሄሮድስ ጴጥሮስን ለፍርድ ሊያቀርበው አልቻለም። ከዚህም በኋላ፥ ሄሮድስ ወደ ቂሣሪያ ይሄዳል። እንደምታስታውሰው፥ ነቢዩ አጋቦስ እንደተነበየው በከነዓን ምድር ውስጥ ታላቅ ረሐብ ገባ። በሰሜናዊው የከነዓን ክፍል ይኖሩ የነበሩት የጢሮስን የሲዶና ሕዝብ ለምግብ ይተማመኑት የነበረው በንጉሥ ሄሮድስ ላይና በከነዓን ምድር ላይ ነበር። በሄሮድስና በእነዚህ ሁለት ከተማዎች መካከል ደግሞ ቅራኔዎች ነበሩ። ከገሊላም ምግብ ይፈልጉ ስለነበር፥ እነዚህ ሕዝቦች ከሄሮድስ ጋር ሰላም ለመፍጠር ወሰኑ። የሚያስፈልጋቸውንም እህል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይፈልጉ ነበር።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ንጉሥ ሄሮድስ ከሲዶንና ከጢሮስ ሰዎች ጋር ተገናኝቶ የሚነጋገርበት ቀን ይወስናል። እነዚህ ሰዎች ከሄሮድስ መንግሥት ባለሥልጣን ጋር በመገናኘት ሰላምን በመፍጠር ረገድ እንዲረዳቸው አብረው መከረውበታል። እነዚህ ሰዎች ከሄሮድስ ቸር ነገር ከፈለጉ ሊያገኙት የሚችሉት ሲያሞግሱትና ከፍ ከፍ ሲያደርጉት እንደሆነ ተስማሙ። ለእርሱም ክብር ለመስጠት ተሰበሰቡ። ሄሮድስም ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ በዙፋኑ ከተቀመጠ በኋላ፤ ለሕዝቡ ንግግር አደረገ። ሄሮድስ ምን እንደተናገረ ባናውቅም፤ ሕዝቡ እርዳታን ለማግኘት ሲል «ይህ የእግዚአብሔር

ድምጽ ነው የሰውም አይደለም» ብለው ጮሁ (ቁ. 22)። ሄሮድስ የእነርሱን አክብሮት በደስታ ተቀበለ። በዚያ ዘመን ነገሥታት እንደ አማልክት ይከበሩ ስለነበር ሄሮድስ በሕዝቡ የክብር መግለጫ ኩራት ተሰማው። እንዳችም ክብር ለእግዚአብሔር ሳይሰጥ ክብሩን በሙላ ለራሱ አደረገው። ውጤቱም የእግዚአብሔር ቅጽበታዊ ፍርድ ሆነ፤ መጨረሻም ሞትን አስከተለ።

የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ ጆሲፈስ ስለሄሮድስ አሟሟት ሲናገር፥ አንዲት ጉጉት ካየ በኋላ ድንገተኛ ሕመም በእርሱ ላይ ወረደ ይላል። የእግዚአብሔር ቃል ግን «የጌታ መልአክ መታው፤ ተልቶ ደግሞ ሞተ» ነው የሚለው።

መጽሐፍ ቅዱስ «ትዕቢት ጥፋትን፥ ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል» ብሎ ያስተምረናል (ምሳሌ 16፡ 18)። አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ክብር ለእራሱ ለማድረግ ከሞከረ፥ ለእግዚአብሔር ቀጣ የተጋለጠ ይሆናል። አንድ ሰው ገዢ እንዲሆንና ለተወሰነ ጊዜ እንዲነግሥ የሚወስነው እግዚአብሔር ነው። የሰው መሪዎች ምንም እንኳ ታላቅ ኃይል ቢኖራቸውም፥ ከነገሥታት ንጉሥና ከጌቶችም ጌታ ሥር ናቸው። ኃይልን የሚሰጣቸው እሱ ብቻ ነው። ያለጥርጥር፥ እግዚአብሔር ሄሮድስ ክርስቲያኖችንም በማሳደዱ ፈርዶበታል።

ጥያቄ 22 ፡-ሀ) ጴጥሮስ ነፃ በመውጣቱ ምክንያት ክብርን የሰጠው ለማነው? ለ) ይህ ሄሮድስ ለሕዝቡ ሙገሳ ከነበረው አመለካከት ጋር የሚለየው እንዴት ነው?

ጥያቄ 23፡- ሀ) ትዕቢትና ሞገስን መፈለግ ለክርስትና ምሥክርነታችን በጣም አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው? ለ) አንዳንድ የክርስቲያን መሪዎች በዚህ ኃጢአት የሚወድቁት እንዴት ነው?

ጥያቄ 24፡- እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ወይም በመንግሥት ደረጃ በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች በትዕቢት ሲሞሉ ወይም ወንጌልን ሲቃወሙ፥ ምን ዓይነት ፍርድ እንደሰጣቸው ለምሳሌ ያህል ጥቀስ።

በሄሮድስ የተነሣው ፅኑ ስደት እንኳ፥ የቤተክርስቲያንን ዕድገት ሊገታው አልቻለም። ክርስቲያኖቹ ለምሥክርነታቸው ታማኞች ሆነው በፀኑ ቁጥር፥ እግዚአብሔርም ብዙ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያን አመጣ።

በርናባስና ሳውል ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን የሰጣቸውን ስጦታ ከሰጡ በኋላ ትንሽ ቆይተው እንደገና ወደ አንጾኪያ ተመልሰው ነበር። በዚህ ጊዜ ግን፥ በመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞአቸው የሚተባበራቸውን ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስን ይዘውት ነበር። ይህንን በሚቀጥለው ሳምንት ትምህርታችን እናጠናዋለን።

## አምስተኛ ቀን፡- ክለሳ

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

*1.* በሐዋርያት ሥራ 11፡ 26 ላይ በተጠቀሰው መሠረት፥ ክርስቲያን ማነው?

2. በርናባስ ወደ አንጾኪያ የተላከው ለምንድነው? የሄደበትስ ዓላማ በተገቢው ሁኔታ ሊፈጽም የቻለው ለምንድነው?

3. በርናባስ በአንጾኪያ መጥቶ ሳውልን እንዲረዳው የፈለገበትን ምክንያት ግለጽ። ሐዋ. 9፡ 10-19፤ 27 ተመልከት።

4. ሄሮድስን በያዕቆብና በጴጥሮስ ላይ እንዲነሣሣ ያደረገው ምንድነው?

5. ቤተክርስቲያን ለያዕቆብ ሞትና ለጴጥሮስ መታሠር የሰጠችው ምላሽ ምን ነበር? ከዚህ ምን ልንማር እንችላለን?

6. በንጉሥ ሄሮድስ ላይ ከደረሰው ነገር ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው?

ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄ በመመልከት ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

| | |
|---|---|
| 1. የአምልኮ ጊዜ | 3. ክለሳ |
| 2. የጸሎት ጊዜ | 4. ውይይት |

ሀ) 1. ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ውስጥ ስንገባ፣ አመለካከታችን ምን ዓይነት ነው መሆን ያለበት? 2. ለዕርዳታ ዓይናችንን ማንሣት ያለብን ወዴት ነው? 3. አንተ በፈለግኸው መንገድ እግዚአብሔር ጸሎትህን እንዴት ባለ ሁኔታ እንደመለሰልህ በዝርዝር አሳይ። 4. አንተ ባልጠበቅከው ወይም አንተ እንደፈለከው ባስቸኳይ ሳይሆን ዘግይቶ እግዚአብሔር ጸሎትህን እንዴት እንደመለሰልህ እስቲ በዝርዝር ተናገር። ለጸሎትህ መልስ በምትጠብቅበት ወቅት ምን ምን ነገሮችን ተማርክ?

ለ) 1. ጸሎት በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዴት ያለ ሚና ነበረው? የጥንቷ ቤተክርስቲያን ብዙ ጊዜዋን በጸሎት ያሳለፈችባቸውን አንዳንድ ወቅቶች ለምሳሌ ያህል ጥቀስ። 2. በቤተክርስቲያንህ ውስጥ እንዴት ያለ ሚና ነው ያለው? 3. በቤተክርስቲያንህ አምልኮ ውስጥ ጸሎት ዋነኛው ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

ሐ) የሐዋርያት ሥራ 11፡ 19-20 አንብብ። 1. የአንጾኪያዋን ቤተክርስቲያን ለዕድገት ያበቋት ነገሮች ምንድናቸው? 2. የቤተክርስቲያንን ዕድገት በተመለከተ ይህ የሚያስተምርህ ምንድነው? 3. ቤተክርስቲያንህ ወደ ሌሎች ሥፍራዎችና በመላው ኢትዮጵያ ሥርጭቷን ልታሰፋባቸው የምትችልባቸውን መንገዶች በዝርዝር ግለጽ።

መ) የሐዋርያት ሥራ 11፡ 23-26 አንብብ። 1. በበርናባስ ውስጥ ማየት የምንችላቸው የጥሩ መሪ ባህሪዎች ምን ምንድናቸው? 2. ስለ ጥሩ የቤተክርስቲያን መሪ ባህሪ ከበርናባስ ሕይወት ምን ልንማር እንችላለን? 3. እነዚህ ባህሪዎች ዛሬ በቤተክርስቲያንህ መሪዎች ውስጥ ምን ያህል ጎልተው ይታያሉ?

ሠ) 1. ቤተክር[illegible]ቲያንህ ችግር ላለባቸው ሰዎች ግድ እንዳላት የምትገልጸው በእንዴት ዓይነት ሁኔ[illegible] ነው? 2. ላቀፈችው ኅብረተሰብ ያላትን አስተሳሰብ ልታሰፋው

የምትችለው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? 3. ቤተክርስቲያንህ ዕርዳታ በማድረግ ፍቅሯን የገለጸችላቸው ሰዎች ወይም ቤተክርስቲያናት ካሉ ዘርዝራቸው።

ረ) ከሄሮድስ ሞት የክርስቲያን መሪዎች ሊያጤኑት የሚገባቸው ነገር ምንድነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 10

## የሐዋርያት ሥራ 13፡ 1-42

## የመጀመሪያ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 13፡ 1-3

በሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ 1-12 ላይ፥ የወንጌሉ መልእክት ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ አንጾኪያ ድረስ እንዴት እንደ ደረሰ አይተናል። እስከ እዚህ ጊዜ ድረስ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የሚያተኩረው ሐዋርያቱ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ አገሮች ስለነበራቸው አገልግሎት ነው። የሚቀጥለው የሐዋርያት መጽሐፍ ክፍል፥ ከምዕራፍ 13-28 ያለው፥ ቤተክርስቲያን ከአንጾኪያ እስከ ሮም እንዴት እንደተስፋፋች የሚጠቅስ ነው። በመጀመሪያው ክፍል መሪ ተዋናይ የነበረው የአይሁዶቹ ሐዋርያ ጴጥሮስ ነው፤ ከምዕራፍ 13 ጀምሮ ግን፥ መሪ ተዋናይ የሚሆነው የአሕዛቡ ሐዋርያ ጳውሎስ ነው። ከምዕራፍ 13-28 ውስጥ ጴጥሮስ የተጠቀሰው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ይህን ስንል ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት ወንጌልን ሌሎች መስበክ አቆሙ ማለታችን አይደለም። የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስተምረን፤ ሐዋርያቱ በሙሉ ወንጌልን ወደ ሰሜን አፍሪካና በምሥራቅ በኩል ደግሞ እስከ ሕንድ በማስፋፋት ተግባር በጣም ተጠምደው ነበር። ሉቃስ ግን የሚያተኩረው የሮማው መንግሥት መዲና ወደሆነችው ወደ ሮም ወንጌሉ የደረሰበት ታሪክ ላይ ነው።

የሐዋርያት ሥራ ሁለተኛ ክፍል፤ ከምዕራፍ 13 ጀምሮ የሚያተኩረው ወንጌል በአሕዛብ አገሮች መስፋፋት በሚለው ላይ ነው። በደማስቆ መንገድ ላይ ከጌታ በተቀበለው አደራ መሠረት ዋና መልእክተኛ ወይም ሐዋርያ ተብሎ ወደ አሕዛብ የተላከው ጳውሎስ ነበር።

ጥያቄ 1፡- ስለ ጳውሎስ አገልግሎት ኢየሱስ በሐዋርያት ሥራ 9፡ 15 ላይ የተናገረው ምንድነው?

ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ከኢየሱስ ጋር ከተገናኘና ከተመረጠ ብዙ ዓመታት አልፈዋል። በእነዚህ ዓመታት ስላደረጋቸው ነገሮች እምብዛም አናውቅም፤ ሆኖም ሳውል ሊያከናውነው ላለበት ሥራ ያዘጋጀው ዘንድ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ዓመታት በመሆናቸው ዓመታቱ በከንቱ የባከኑ እንዳልነበሩ እናውቃለን።

ጥያቄ 2፡- ሀ) ለአገልግሎት ዝግጁ መሆን አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? ለ) የቤተክርስቲያንህ መሪዎችና ወንጌላዊያን ለአገልግሎታቸው ዝግጁ

የሚሆኑት እንዴት ነው? ሐ) በተሻለ መንገድ ሊዘጋጁ የሚችሉት እንዴት ነው?

አሕዛብ ክርስቲያኖችን አብረው እንዲያስተምሩ በርናባስ ጳውሎስን ወደ አንጾኪያ ከተማ እንዳመጣው ባለፈው ሳምንት ጥናታችን አይተናል። አሁን ደግሞ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ሰዎችን የምትልክ ቤተክርስቲያን እንደሆነችና እንዲሁ ደግሞ በሮማው መንግሥት ለሚገኙት አሕዛብ ሁሉ ወንጌልን ልታደርስላቸው ትችል ዘንድ እግዚአብሔር እንዴት እንደተገለገለባት እንመለከታለን።

የሐዋርያት ሥራ 13፡ 1-52 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 3፡- ሀ) የአንጾኪያው ቤተክርስቲያን መሪዎች እነማን ነበሩ? ለ) በርናባስና ሳውል የሄዱባቸውን ሥፍራዎች በዝርዝር ግለጽ። በዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ ባለው ካርታ ላይ የተጓዙበትን መንገድ በእርሳስ አመልክት። ሐ) በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13 በየትኛው ቁጥር ላይ ነው ሉቃስ ሳውልን ጳውሎስ እያለ የሚጠራው?

የሐዋርያት ሥራ 13፡ 1-3 እንደገና አንብብና እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 4፡- ሀ) በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ውስጥ፥ የመሪዎቹ ሥራ ምን ነበር? ለ) መንፈስ ቅዱስ ሲናገራቸው፤ መሪዎቹ ምን እያደረጉ ነበር? ሐ) መንፈስ ቅዱስ የተናገረው ነገር ምንድነው?

በርናባስና ሳውል ወደ አንጾኪያ እንደገና በተመለሱ ጊዜ ማርቆስ የተባለውን የበርናባስን የአክስት ልጅ አብረው ይዘውት ሄደዋል (ሐዋ. 12፡ 25)። ሳውልና በርናባስ አገልግሎታቸውን በአንጾኪያ እንቀጥላለን ብለው ሳያስቡ አልቀሩም፤ ሆኖም እግዚአብሔር ግን ለእነርሱ የተለየ ዕቅድ ነበር። የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖች ወደ አሕዛብ አገሮች የምትልክ አዲስ የማሰራጫ ቦታ እንደሆነች እናያለን፤ በዚሁ የሐዋርያት ሥራ መሠረት የኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን በእስትራቴጂካዊ ውሳኔ ላይ ስትገባ ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ ነበር (ሐዋ. 15)።

እስጢፋኖስ ከተገደለ በኋላ በተነሣው ስደት ምክንያት ከተበታተኑት አማኞች መካከል አንዳንዶቹ የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች ነበሩ (ሐዋ. 11፡ 19-20)። እነርሱም እስከ አንጾኪያ ድረስ ለአይሁዳውያን እየሰበኩ ሄዱ። እንደምታስታውሱትም ሁሉ ወንጌሉ በአንጾኪያ ይገኙ የነበሩ አሕዛብ መካከል በፍጥነት ተሰራጨ።

አዲስ ኪዳን፥ ቤተክርስቲያን ሥራዋን በተቀላጠፈ ሁኔታ እንድትሠራ ሲባል፥ እግዚአብሔር ስጦታዎችን እንደሚለግሣት ያስተምረናል። ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችም መካከል አንዱ የመሪነት ስጦታ ነው። ለምሳሌ በአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን የማስተማርና የትንቢት ስጦታዎች የነበራቸው መሪዎች ነበሩ። በአዲስ ኪዳንም ከሐዋርያቱ ዘመን በኋላ፤ ዋነኞቹ ስጦታዎች የማስተማርና የትንቢት ስጦታዎች ነበሩ።

ጥያቄ 5:- እግዚአብሔር ዛሬም ለልጆቹ ስጦታ ይሰጣል፤ ኤፌ. 4: 11-13 አንብብ።

ሀ) እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚሰጠው ለምን ዓላማ ነው?

ለ) እግዚአብሔር የሰጠህን መንፈሳዊ ስጦታዎች በዝርዝር ጻፍ። ይህን ስጦታ ወይም እነዚህን ስጦታዎች በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው የምትጠቀምበት ወይም የምትጠቀምባቸው

የአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን አምስት ቁልፍ መሪዎች ነበሯት። እነሱም ከተለያዩ ባህሎችና ልማዶች የተውጣጡ መምህራንና ነቢያት ነበሩ። የመጀመሪያው፥ ኔገር የተባለው ስምዖን ነበር። ስምዖን የሚለው ስም፥ መሠረቱ ከአይሁድ መሆኑን ያመለክታል። ሁለተኛው ሉኪዮስ፥ ሲሆን፤ ይህም ሰው በሰሜን አፍሪካ የምትገኘው የሊቢያ ዋና ከተማ፥ የቀሬና ሰው ነበር። ምናልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ወደ አንጾኪያ ይዘው ከሄዱ ሰዎች መካከል ሳይሆን አይቀርም። ሦስተኛው፥ ለሄሮድስ አንቲፓስ ባለሟል የነበረው ምናሔ ነው። አራተኛው ሳውል ደግሞ፥ የአሕዛብ ከተማ የነበረችው የጠርሴስ ተወላጅ ሲሆን፥ በዚሁ ሥፍራ አድጎ በአይሁድ ሕግ ተገቢውን ሥልጣኔ የወሰደ ነው። አምስተኛው ደግሞ፤ ከሌዊ ወገን የነበረውና በኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን የተላከው በርናባስ የተባለው አይሁዳዊ ነበር። አንዳንድ ምሁራን፥ በሥልጣን አወራረዳቸው በቅደም ተከተል ነው የተጻፉት ብለው ይገምታሉ፤ በዚህም መሠረት ዋነኛው መሪ በርናባስ ሲሆን፤ ሳውል ደግሞ ምንም መሪ ቢሆን ከሁሉም የበታች ነበር። እነዚህ መሪዎች በሙሉ በአሕዛብ አገር ያደጉ አይሁዳውያን ይመስሉናል።

በአንጾኪያው ቤተክርስቲያን መሪነት ውስጥ፥ ጌታ ከብዙ የተለያዩ አገሮች የመጡ ሰዎችን ለአገልግሎት ጠርቷቸዋል። ይህም የቤተክርስቲያኑን መሪዎች በዚያን ጊዜ የነበረውን ዓለም ችግር በደንብ እንዲያጤኑ አስችሏቸዋል። ይህ በኢየሩሳሌም ሊሆን አይችልም ነበር፤ ምክንያቱም ብዙዎቹ መሪዎች የለመዱት የአገራቸውን ባህል ብቻ ነበርና ነው። እግዚአብሔርም ለእነዚህ ሰዎች የትንቢትና የማስተማር ስጦታ የሰጠው የአንጾኪያን ቤተክርስቲያን እንዲያንጹ ነው።

ጥያቄ 6:- ሀ) አሁን ስላለው ዓለም የበለጠ እውቀት ቢኖረን፥ ዓለምን በወንጌል የማዳረሱን ራዕያችንን ሊያሰፋልን የሚችለው እንዴት ነው? ለ) አንተ ስለዓለም ያለህን የዕውቀት አድማስ ለማስፋት ምን እያደረግህ ነው?

በአንጾኪያ የነበሩት ነቢያትና አስተማሪዎች አብረው በሚጸልዩበትና በሚጾሙበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን፥ ወንጌልን አስይዘው ወደ አሕዛብ አገር እንዲልኳቸው ይነግራቸዋል። ቤተክርስቲያኒቱም ጥሪውን ተቀብላ እንድትልካቸው ምሪቱን ተቀበለች።

ጥያቄ 7:- ሀ) ዛሬ በቤተክርስቲያንህ ወንጌላውያን የሚመረጡት እንዴት ነው? ለ) ወንጌላዊ የሚሆነውን ሰው በመምረጡ ላይ መሪዎቹ የሚጫወቱት ሚና ምንድነው? ሐ) በፈቃደኝነት መሥራትን በተመለከተ አንዳንድ ወንጌላውያን የሚፈጽሙት ምን ዓይነት ተግባር ነው? መ)

በአመራረጣቸውና በአላላካቸው ረገድ መንፈስ ቅዱስ የሚጫወተው ሚና ምንድነው?

የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን መሪዎች እዚያ የተገኙት የቤተክርስቲያንን ወይም የዓለምን ፍላጎት በተመለከተ ለማቀድ፥ ለመሰብሰብ ወይም ለመወያየት አልነበረም፤ ታዲያ በፆም ላይ ሆነው ጌታን እያመለኩ ሳለ ነው መንፈስ ቅዱስ የተናገራቸው። መንፈስ ቅዱስ ከተናገራቸው በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር እንዲሠሩ ላዘዛቸው ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለመላክ በአንድነት ይስማማሉ። በዚህም መሠረት ከጾሙና ከጸለዩ በኋላ፥ በእነሱ ላይ እጃቸውን ይጭናሉ። በርናባስና ሳውልን ለአገልግሎቱ ለመለየትና እግዚአብሔር ለሰጣቸው ልዩ ሥራ አሳልፎ ለመስጠት በተለምዶ የእጅ መጫን ባህል ነበራቸው። ቤተክርስቲያኒቱ የሚያስፈልጋቸውን ሰጥታ ሸኘቻቸው።

ጥያቄ 8፡- ሀ) እግዚአብሔር ዛሬ ወንጌላውያንን የሚጠራው እንዴት ነው? ለ) ወንጌላውያንን ለአገልግሎት ስትልክ የቤተክርስቲያን ኃላፊነት ምንድነው?

መንፈስ ቅዱስ የተናገረው እንዴት ነው? እኛ ይህን አናውቅም። ምናልባት በአንዱ ነቢይ በኩል ይሆናል፤ አለበለዚያም በጸሎት ተጠምደው አንድ ለነበሩት ሰዎች ለእያንዳንዳቸው በልባቸው ነግሯቸው ይሆናል። ዛሬ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት የምናውቀው እንዴት ነው? ብዙ ጊዜ በሚሰማ ድምጽ አይናገርም። እራሳችንንም በግድ መንፈሳዊ በሆነ መነቃቃት ውስጥ ከተን ድምጹን ሰምተናል ብለን ልናስብ አንችልም። የእግዚአብሔር ምሪት የሚመጣው ያንን ሐሳብ ይዘን በጸሎት በጌታ ፊት ጊዜ ወስደን ስንቀርብ ነው። ከእኛ ሁኔታ ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ መመሪያዎችን ከእግዚአብሔር ቃልም ውስጥ መፈለግ አለብን። እግዚአብሔር አንዳንድ ሁኔታዎችን ሊጠቀም ይችላል፤ ሆኖም በምንወስነው ውሳኔ ውስጥ ሁልጊዜ ሰላምን ይሰጠናል። ነገሩን ተገንዝበን ስንጸልይ፤ እግዚአብሔር ትክክለኛውን ውሳኔ እናደርግ ዘንድ፤ ልባችንና አእምሮአችንን ያዘጋጃል። ይህንንም ማድረግ ያለብን ለመታዘዝ ፍጹም ፈቃደኞች በመሆን ነው እንጂ፥ በአዕምሮአችን የራሳችንን ውሳኔ ይዘን ይህን ምርጫችንን ባርክልን ማለት የለብንም። በሕይወታችን ያለውንም ነገር መለስ ብለን ስናየው አዕምሯችንንና ልባችንን እግዚአብሔር እንዴት አዘጋጅቶ ሊመራን እንደቻለ ልንገነዘብ እንችላለን።

ጥያቄ 9፡- በሕይወትህ ውስጥ አንዳንድ ውሳኔዎችን እንድታደርግ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደመራህ አብራራ።

ምንም እንኳ በጣም የሚናፈቁ ቢሆኑም፤ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን በርናባስንና ሳውልን የመጀመሪያዎቹ ሚሲዮናውያን አድርጋ ላከቻቸው፤ እነርሱም ከትውልድ ቦታቸው ወደ ባዕድ አገር የተላኩ የመጀመሪያዎቹ ሆኑ። እግዚአብሔር ወንጌልን ወደአልደረሰበት ሥፍራ እንዲያዳርሱ የመረጣቸውን ሰዎች በደንብ አስተውል። ተራ የቤተክርስቲያን አባላት አይደሉም፤ እንዲያውም እግዚአብሔር የመረጣቸውና ቤተክርስቲያንም የላከቻቸው ብቁ ችሎታ ያላቸውን መሪዎችዋን ነበር። በርናባስ የቤተክርስቲያኒቱ ዋና መጋቢ ሊሆን የሚችል ነበር፤ ሳውልም ቢሆን በቤተክርስቲያን

ውስጥ መሪ ለመሆን የሚችል ነበር። ታዲያ አብዛኛው የቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚያተኩረው የጠፉትን በመፈለጉ ላይ ስለሆነ፤ ብቃት አላቸው ብለን የምንገምታቸውን ወንዶችና ሴቶች ለመላክ ፈቃደኞች መሆን ይኖርብናል። እግዚአብሔር ወንጌልን ለጠፉት ሰዎች ከማካፈል በላይ የሰጠን ሌላ ታላቅ አገልግሎት ወይም ኃላፊነት የለም። ስለዚህም በቤተክርስቲያናችን ለየት ያለ ሥልጠና የወሰዱና ብቃት አላቸው የምንላቸው አባቶቻችንን ይህን ዋነኛ የሆነ ሥራ እንዲሠሩ ልንልካቸው ይገባል።

መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ላካቸው። አንዳንዶች እዛው ቤተክርስቲያን ውስጥ ሲቀሩ፥ ሌሎች መሄድ ይኖርባቸዋል። መንፈስ ቅዱስ አንዳንዶች እንዲሄዱ፥ ሌሎች ደግሞ ለሄዱት እንዲጸልዩና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ይመራል። ሆኖም፥ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ መመራት አለባቸው። አንድ ሰው የመሄድ ጥሪ ቢሰማ በበጎ ፈቃደኝነትና በቤተክርስቲያን መሪነት መሠረት መሄድ ይገባዋል።

ጥያቄ 10:- ሀ) በሕይወትህ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ጥሪ ለመስማት በተጠንቀቅ ሆነህ ተዘጋጅተሃልን? ይህ በሕይወትህ እንዴት እንደሚገለጽ አብራራ። ለ) እግዚአብሔር ለዓለም ባለው ዕቅድ ውስጥ አንተን የሚጠቀምብህ እንዴት ነው? ሐ) ቤተክርስቲያንህ ወንጌል ወደሚያስፈልግበት አካባቢ ሥርጭቱን የምታቀላጥፈው እንዴት ነው?

## ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 13፡ 4-12

የአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያዎቹን ሚሲዮናውያን ከላከች በኋላ፥ መሠረታዊ የሆነው ወንጌሉን የማስፋፋት ተግባር ከኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን ወደ አሕዛቧ የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ይዛወራል። የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን መሪዎች በሚጾሙበትና በሚጸልዩበት ወቅት በመንፈስ ቅዱስ በመመራት፥ ሳውልንና በርናባስን ከመሪነት ኃላፊነት ላይ በማንሣት፥ የክርስቶስን ስም ወደ አሕዛቡ ዓለም ይዘው እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል። በዚህም መሠረት የአንጾኪያ ቤተክርስቲያን መሪዎች እጆቻቸውን ከጫኑባቸው በኋላ ይልኳቸዋል። የመጀመሪያው የጳውሎስ ሚሲዮናዊ ጉዞ የተደረገው ከ46 - 48 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

በርናባስና ሳውል በመንፈስ ቅዱስ ወደ ተቀሩት የሮማ መንግሥት አገሮች ሲላኩ፥ የበርናባስ የአክስት ልጅ የሆነውን ማርቆስን ከእነርሱ ጋር አብረው ይዘውት ሄዱ። የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ባልበራባቸው ሥፍራዎች ሲደርሱ፥ አዳዲስ ተቃውሞዎችና እንቅፋት ያጋጥሟቸው ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 13፡ 4-12 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 11:- ሀ) በርናባስና ሳውል መጀመሪያ የሄዱት የትኛው አገር ነው? ከዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ የሚገኘውን ካርታ በመመልከት በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱት ሥፍራዎች የት እንደሚገኙ ተመልከት። ለ) በበርናባስና በጳውሎስ ላይ የተነሣውን ተቃውሞ አብራራ። ሐ) ኤልማስ የጳውሎስን

መልእክት የተቃወመው ለምንድነው? መ) በኤልማስ ላይ የወረደው ፍርድ፥ በአገረ ገዢው ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ነበረው?

በርናባስ፥ ሳውልና ማርቆስ ወደ ሴሌውቅያ ወደብ በመሄድ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ አመሩ። የበርናባስም የትውልድ ሥፍራ በቆጵሮስ አካባቢ ስለነበር፥ ስለአካባቢውና በዚያ ስለሚኖሩት ሰዎች ግንዛቤ ነበረው። ይህም እንግዳ ለሆኑ ሰዎች ወንጌልን ከማካፈል ይልቅ ቀላል ያደርገዋል። አሁንም እንደገና፥ እግዚአብሔር የልጆቹን አስተዳደግ በመንግሥቱ ሥራ ውስጥ ይጠቀምበታል። እግዚአብሔር በአጋጣሚ ወይም እንደ ዕድል ብሎ የሚጠቀምበት አንዳች ነገር የለውም።

ቆጵሮስ የታወቀች የንግድ ቀጠና ነበረች። ከተለያዩ ቦታዎችም የሚመጡ ተጓዦች በዚህች ደሴት በኩል ያልፉ ነበር። ይህም ሁኔታ፥ በመላው ዓለም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሚሲዮናዊ አገልግሎት የሚፈጸምባት ሁነኛ ሥፍራ እንድትሆን አድርጓታል።

በቆጵሮስ ደሴት ላይ፥ አይሁዳውያንም አሕዛብም ይኖሩ ነበር። ጳውሎስና በርናባስም በደሴቷ በስተምሥራቅ አካባቢ በምትገኘው በስልማና ላይ ሥራቸውን ጀመሩ። እንደልማዳቸውም፥ በመጀመሪያ በርናባስና ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል በአይሁድ ምኩራቦች ሰበኩ። ጳውሎስ፥ ወንጌሉ መጀመሪያ ለአይሁዳውያን ቀጥሎ ለአሕዛብ ተሰጠ እንዳለው ሁሉ (ሮሜ 1፡ 16)፤ በመጀመሪያ ወደ አይሁዳውያኑ መሄድ በእነርሱ በኩል የተለመደ ነበር። አይሁዳውያንም ብሉይ ኪዳንን ስለሚያውቁ፥ የወንጌሉን መልእክት በተሻለ ሁኔታ ሊረዱት ይችላሉ። በተጨማሪም፤ በየምኩራቦቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመኑ ከእግዚአብሔር ምሕረትን እንደሚያገኙ የሚያበሥረውን የወንጌል መልእክት የሚቀበሉ ብዙ እግዚአብሔርን የሚፈሩ አሕዛብ ይገኙ ነበር።

ይህ «ምኩራብ» ተብሎ የሚጠራው የአይሁዳውያን መሰብሰቢያና ማምለኪያ ሥፍራ፤ ጳውሎስና በርናባስ ስብከታቸውን የሚጀምሩበት ሥፍራ ነበር። ብዙ ጊዜም ከእነዚህ ምኩራቦች ብዙ ሰዎች ያምኑና ቤተክርስቲያንን ይመሠርቱ ነበር።

ከሰልማናም በመነሣት ደሴቲቱን በሙሉ ዞሩ። በቆጵሮስ በስተምዕራብ ወደምትገኘው ወደ ጳፉ ሲደርሱ በርያሱስ የተባለ ጠንቋይና ሐሰተኛ ነቢይ የነበር አንድ አይሁዳዊ ሰው አገኙ። እሱም የዚያች ደሴት አገረ ገዥ የነበረው ጃንደረባ ነበር። ይህም ጠንቋይ በቶሎ የወንጌሉ ጠላት ሆነ።

ሰርግዮስ ጳውሎስ የተባለው አገረ ገዥ፥ ይህችን ደሴት እንዲያስተዳድር በሮማው መንግሥት የተወከለ ሰው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስም አስተዋይ ነበር ይለዋል። ስለ ጳውሎስና በርናባስ፥ ኢየሱስ ክርስቶስንም በተመለከተ ስለሚሰጡት ምሥክርነት ሲሰማ፥ ወደ እነርሱ ሰው ላከ። አገረ ገዥው ይህን የሚሰብኩትን የእግዚአብሔር ቃል ሊሰማ ፈልጓል። የደህንነቱን ወንጌል ለደሴቲቱ አገረ ገዥ እንዲመሠከሩ የተሰጣቸው ዕድል በጣም የሚያስደንቅ ነው።

ጥያቄ 12፡- ሀ) አንድ ሰው የኢየሱስ ክርስቶስን የምሥራች ዜና አስረዳኝ ብሎ ጠይቆህ ያውቃል? 2ኛ ጢሞ. 4፡2 እና 1ኛ ጴጥ. 3፥15 አንብብ። ለሰውዬው

ያከፈልከው ነገር ምንድነው? ለ) ስለተሰጠህ ተስፋ ለማስረዳት ዝግጁ የሆንከው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ስለእርሱ የምትመሠክርበትን አጋጣሚ እንዲያዘጋጅልህ በጸሎት ጠይቀው።

ወንጌል ወደ አዲስ ሥፍራ ሲገባ፥ ሰይጣን አርፎ አይቀመጥም። በአይሁድ የስሙ ትርጓሜ ጠንቋይ ማለት የሆነው ባርየሱስ ወይም ኤሊማስ በተባለው ሰው አማካኝነት ተቃውሞ ተነሣ። ይህ ሰው ምንም አይሁዳዊ ቢሆንም ብሉይ ኪዳን ምንም ዓይነት የጥንቆላ ሥራ የማይፈቅድ መሆኑን እያወቀ በመቃወም ጠንቋይ ሆኗል። የበርናባስንና የጳውሎስን ምሥክርነት ሲሰማም፤ በጣም ፈራ። አገረ ገዥው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበለ፥ ከእርሱ ጋር የሚኖረውን ወዳጅነት እንደሚያጣም ተገነዘበ። ስለዚህም ሰርግዮስ ጳውሎስን የበርናባስንና የጳውሎስን ምሥክርነት እንዳያምን ሊያባብለው ሞከረ። በድንገትም ሳውል በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ስለ ክፋቱ፥ ስለተንኮሉና የቀናውን የጌታ መንገድ ስለማጣመሙ ኤልማስን ይቀጣዋል። ሳውል በርያሱስ የሰይጣን መልእክተኛ እንደሆነ ተገንዝቧል። አንዳንድ ጊዜ ክፉዎች ድል የሚቀዳጁ ሊመስለን ይችላል፤ ሆኖም እግዚአብሔር ነገሮችን ሁሉ እንደሚቆጣጠርና የሚቃወሙትንም እንደሚቀጣ ሁሌ ልንገነዘብ ይገባናል።

ጳውሎስ ኤላምስን «አሁንም እነሆ የጌታ እጅ ባንተ ላይ ናት፤ ዕውርም ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም» ይለዋል። ወዲያውኑም ኤልማስ ታወረ፤ ወዲህ ወዲያም እያለ የሚመራውን ሰው መፈለግ ጀመረ (ቁ. 11)። በዚህም ጳውሎስ የክርስቶስ ኃይል ከሰይጣን ኃይል እንደሚበልጥ አሳየ። አሁንም እንደገና ይህ ተአምር የወንጌሉን እውነተኛነት የሚያሳይ ተጨባጭ ምሥክር ሆኗል።

ጥያቄ 13፡- ሀ) ለሰርግዩስ ጳውሎስና ለባለሟሎቹ እግዚአብሔር ኃይሉን የገለጸላቸው ለምን ይመስልሃል? ለ) መለኮታዊ የሆኑ ምልክቶች፥ ዓላማቸው ምንድነው?

ሰርግዩስ ጳውሎስ በኤልማስ ላይ የወረደውን ፍርድ ሲያይ፥ በጌታ ትምህርት በጣም ተገረመ። በጠንቋዩ ላይም የመጣው ፍርድ የጳውሎስን ትምህርት እውነተኛነት ገልጿል፤ የድንቅና የተአምራትም ዓላማ ይኸው ነው።

በቤተክርስቲያን ውስጥ በግብዝነትና በማታለል ምክንያት፥ በሐናንያና በሰጲራ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሲፈርድባቸው አይተሃል። አሁን ደግሞ ከቤተክርስቲያን ውጪ ባሉ የወንጌሉ ጠላቶች ላይ መንፈስ ቅዱስ ቅፅበታዊ የሆነ ፍርድ ሲሰጥ እናያለን። ሌሎች ወንጌሉን እንዳያምኑ በሚከላከሉ ሰዎች ላይ፥ የእግዚአብሔር ፍርድ ቁርጠኛና የማያወላዳ ነበር።

ጥያቄ 14፡- አንድ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው፥ የቤተክርስቲያን ጠላት በመሆኑ እግዚአብሔር እንዴት እንደተፋረደው አይተህ እንደሆነ ሰፋ አድርገህ ግለጸው።

ከአሁን ወዲህ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሳውል የሚለው ወደ ጳውሎስ ይለወጣል። ሳውል የአይሁድ ስም ነው። ሆኖም ሳውል፥ ዜግነቱ ሮማዊ ስለነበር

ጳውሎስ የሚልም ስም ነበረው (ሐዋ. 13፡ 9)። ስሙ እንዲህ የተለወጠው፥ የአሕዛብ ሐዋርያ ሆኖ ወደ አሕዛቡ ዓለም መንዝ ስለጀመረ ነው። ከዚህም ቀደም ሲል እንዳየነው፥ የጳውሎስ አስተዳደግ፥ ሥልጠናና የነበረው ስሜት የወንጌሉን ምሥክርነት ወደ አሕዛቡ ዓለም ይዞት እንዲሄድ ዝግጁ አድርጎታል። ጳውሎስ በአይሁዶች ባህልና ሕግ ሥልጠና የወሰደ አይሁዳዊ ሲሆን፥ በአሕዛብ ከተሞች ያደገም ሮማዊ ተወላጅ ነው። ታዲያ እነዚህ ነገሮች በሙሉ ተደማምረው፥ ይህን የቆጵሮስ አገረ ገዥ በሚያነጋግርበት ወቅት፥ የመሪነቱን ቦታ እንዲይዝ አድርጎታል።

የሳውልና የጳውሎስ ስም አጠራር፤ ቅደም ተከተሉም አሁንም ይለወጣል። በተጨማሪም ጳውሎስ በአገረ ገዥው ፊት መናገር ከጀመረና በአሕዛብ መካከል ለማገልገል ብቁ እንደሆነ ከተረጋገጠ ወዲህ፥ የመሪነቱን ቦታ ሊይዝ ችሏል። ስለዚህም፥ ሉቃስ የስሙን ቅደም ተከተል፤ ጳውሎስና በርናባስ በማለት ይለውጠዋል። ወደ በኋላም፥ በአይሁዳውያን መካከል ሲመጡ፥ ቅደም ተከተሉን በርናባስና ሳውል ብሎ ይለውጠዋል (ሐዋ. 15፡12)። በርናባስም ይህን የመሪነቱን ሥልጣን ለመተው ሲል እራሱን በጣም ዝቅ አድርጓል። ስለዚህም ለመሪነቱ ከመጣላት ይልቅ፤ ሥራዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲሠሩ የአበረታችነትን ሚና ይጫወት ነበር።

ጥያቄ 15፡- ሀ) ጳውሎስን ለመሪነቱ ቦታ ዝግጁ ለማድረግ፤ በርናባስ የተጫወተው ሚና ምንድነው? ለ) በርናባስ ሁለተኛውን ደረጃ መያዙ ስለበርናባስ የሚገልጽልን ነገር ምንድነው?

ጥያቄ 16፡- የሐዋርያት ሥራ 13፡ 4እና 9፤ ጳውሎስና በርናባስ ስለነበራቸው የሚያመረቃ ምሥክርነት የሚነግረን ነገር ምንድነው?

ጥያቄ 17፡- ለክርስቶስ ያለን ምሥክርነት የሚያመረቃ የሚሆነው መቼ ነው?

አንድ መሪ የሆነ ሰው፥ ከእሱ የበለጠ ስጦታ ላለው ሰው የመሪነቱን ሥልጣን ለቆ ሰውዬው እንዲመራ ለማድረግ በጣም ያዳግተዋል። ብዙ ጊዜም መሪዎች የሚሠሩትን ሥራ በተመለከተ በመካከላቸው ግጭቶች ይፈጠራሉ። ሆኖም፥ መሪዎችን የሚጠራ እግዚአብሔር እንደሆነና ሥራውም የእነሱ ሳይሆን የጌታ እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል። እግዚአብሔር መንግሥቱን ያስፋፋ ዘንድ በሌላ መሪ ቢጠቀም፥ እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን እንጂ በቅናት መንደድ የለብንም።

ጥያቄ 18፡- ሀ) ሰይጣን በቤተክርስቲያን መሪዎች መካከል ግጭት በመፍጠር፤ የእግዚአብሔርን ሥራ ለማውደም ሲሞክር ያየኸው እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር ሌላ መሪ ሲጠራ፥ በርናባስ ከነበረው አመለካከት ልንማረው የምንችለው ነገር ምንድነው?

በክርስትና ሃይማኖት ከሚነሡት ተቃውሞዎች ሁሉ አደገኛ የሆነው፥ በጨለማው ገዢዎች የሚነሣው ተቃውሞ ነው። ሰይጣን ሰዎች እንዳያምኑ ሁሉን ነገር ከማድረግ የማይቆጠብ አታላይ ፍጡር ነው። ይህ ካልሆነለት ደግሞ አማኞችን በማታለል ወደ ሐሰተኛ ትምህርት ውስጥ ይመራና፥ ከፍፍል ፈጥረው በራሳቸው ላይ ፍርድን እንዲቀልሉ ያደርጋቸዋል። ብዙ ጊዜ ደግሞ የመሪዎችን አንድነት ለማፋለስ ይጥራል።

ሥራውም እንዲቆም ከፍፍል ምቀኝነትንና ጥልን ይፈጥራል። ጳውሎስና በርናባስ ቢጣሉ ምን እንደሚሆን እስቲ አስበው። ምስክርነታቸው ምን ይሆን ነበር? ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት ከእራሳቸው ዝና ይበልጥ የእግዚአብሔርን ሥራ በማስቀደም የምስክርነታቸው ፍሬ እንዲታይና አብያተ ክርስቲያናት እንዲፈጠሩ አድርገዋል።

ጥያቄ 19፡- ኤፌ. 6፡ 10-18 አንብብ። በሕይወትህ ውስጥ፤ ይህም በቤተክርስቲያን አካባቢ ሰይጣን ድል የተቀዳጀባቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር ግለጽ። እግዚአብሔር በክፉ ላይ ድልን እንዲሰጥህ ጸልይ።

## ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 13፡ 13-41

ጳውሎስ፥ አሁን ወንጌልን ወደ አሕዛቡ ዓለም የማሰራጨቱን ሥራ የሚመራ ሰው ሆኖአል። እግዚአብሔር በጳውሎስ ልብ ውስጥ ያስቀመጠው ጥሪ ወደ እዚሁ ሥራ እየገፋፋው ነበር። ከዚሁም በተጨማሪ ጳውሎስና በርናባስ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት የመጀመሪያውን ሚሲዮናዊ ጉዞአቸውን ገፉበት።

ጳውሎስ በደማስቆ፥ በኢየሩሳሌም፥ በጠርሴስና በአንጾኪያ አስተምሯል፤ ሆኖም ከጳውሎስ መልእክተኞች ውስጥ መጀመሪያ ሆኖ የተዘገበው የሐዋርያት ሥራ 13፡16-41 ነው። ምናልባትም ለአይሁድ ዕድምተኞች ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበው መልእክት በመሆኑ ምክንያት፥ በሰፋት በዚህ ሥፍራ ሊገለጽ ችሏል። በአንዳንድ ነጥቦች የጳውሎስ መልእክት ከጴጥሮስ ጋር ይመሳሰላል። ሆኖም፥ በአንዳንድ ነጥቦች በጣም ይለያል። ይህን ክፍል ስታነብ፥ ከዚህ በፊት ካጠናናቸው የጴጥሮስ መልእክቶች ጋር አነፃፅረው።

የሐዋርያት ሥራ 13፡ 13-41 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 20፡- ሀ)ቆጵሮስ በምትገኘው በጳፉ ደሴት ከቆዩ በኋላ፥ ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች የሄዱት የት ነው? ለ) ማርቆስ ይባል የነበረው ዮሐንስ ወዴት ሄደ? ሐ) በሰንበት ዕለት፥ የምኩራቡ መሪዎች ጳውሎስና በርናባስን ምን እንዲያደርጉ ጠየቋቸው? መ) እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገላቸው የተለያዩ ነገሮች ምን ምንድናቸው? በሐዋርያት ሥራ 13፡ 17-23 ላይ የተጠቀሱት ስድስት ዋና ዋና ነገሮችን ዘርዝር። ሠ) በሐዋርያት 13፡ 26-31 ላይ ጳውሎስ ለአይሁዳውያን ሊገልጽ የፈለገው ነገር ምንድነው? ረ) በሐዋ. 13፡ 34-37 ላይ፥ ጳውሎስ ኢየሱስ ከዳዊት የሚበልጥ እንደሆነ ያሳየው እንዴት ነው? ሰ) በሐዋ. 13፡ 38-39 ላይ፥ ለሚያምኑ ሁሉ ጳውሎስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ መልእክት ምንድነው? ሸ) በሐዋ. 13፥40-41 ላይ ጳውሎስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?

ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች ከጳፉ ተነሥተው በጵንፍልያ ወደምትገኘው ወደ ጴርጌን በመርከብ አመሩ (የጳውሎስ የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ የሚያሳየውን ካርታ ተመልከት)። ምንም እንኳ ስለ ምክንያቱ የተነገረን ነገር ባይኖርም፥ ማርቆስ

የተባለው ዮሐንስ ጳውሎስንና በርናባስን ትቶ ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳል። ወደ በኋላም፥ ይህ እንዴት በበርናባስና በጳውሎስ መካከል ችግር እንደፈጠረ እናያለን።

ጳውሎስና በርናባስ ከጴርጌን አልፈው 175 ኪ.ሜ. ርቃ ወደምትገኘው የጲስዲያ ወደሆነችው ወደ አንጾኪያ በሚያስቸግር መንገድ አልፈው ይሄዳሉ (በ2ኛ ቆር. 11፡ 26 ላይ የተጠቀሱት አደገኛ ሁኔታዎች ይህን ጉዞ የሚያመለክቱ ሳይሆን አይቀርም)። ምናልባትም በዚህ ጉዞ ላይ ጳውሎስ ሳይታመም አልቀረም፤ ምክንያቱም በገላትያ 4፡ 13-14 ላይ ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለገላትያ ክርስቲያኖች የሰበከው በሕመም ላይ ሳለ መሆኑ ስለሚጠቅስ ነው።

አንጾኪያ ብዙ አሕዛብና ብዙ የአይሁድ ተወላጆች የሚገኙባት ትልቅ የግሪክ ከተማ ነበረች። ስለዚህም፥ በዚህ ሥፍራ የአይሁድ ምኩራብ ነበር (አስተውል!! ይህች አንጾኪያ ከዚህ በፊት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተጠቀሰችው አንጾኪያ አይደለችም። አንጾኪያ የሚል ስያሜ የነበራቸው ሁለት ከተሞች ነበሩ። አንደኛዋ ጳውሎስንና በርናባስን በሚሲዮናዊ ጉዟቸው ሸኝታ የላከቻቸው ቤተክርስቲያን የምትገኝባት በሶርያ ያለችው አንጾኪያ ናት። የጲሲድያዋ አንጾኪያ ደግሞ በገላትያ ክፍለ ሃገር የምትገኝ ነበረች። ጳውሎስና በርናባስ በመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዟቸው ላይ ከመሁከሩባቸው ከተሞች ውስጥ አንዷ ይህች ናት)። ሁሌ እንደሚያደርጉት፥ ጳውሎስና በርናባስ በመጀመሪያ ተነሥተው ወደ ምኩራቡ ይሄዳሉ። ብዙ ጊዜም የምኩራቡ መሪዎች መንገደኛ አስተማሪዎችን ንግግር እንዲያደርጉ ይጋብዟቸው ነበር። በዚህም መሠረት፥ የምክር ቃል እንዳላቸው ጳውሎስንና በርናባስን መሪዎች ይጠይቋቸዋል፤ የቡድኑ መሪ የሆነውም ጳውሎስ ተነሥቶ ሰበከ። ንግግሩንም «የእስራኤል ሰዎችና እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ» በማለት ከፈተ። ከተሰበሰቡት ሰዎች መሐከል ብዙዎች አይሁዳውያን ስለሆኑ፥ ምሥክርነቱ ትኩረት ያደረገው በእነርሱ ላይ ነበር። ሆኖም፥ የጣዖት አምልኮን ትተው የብሉይ ኪዳኑን አምላክ የሚከተሉ አሕዛብ እንደነበሩም ተገንዝቧል። ልክ ጴጥሮስና እስጢፋኖስ በመልእክቶቻቸው ውስጥ እንዳደረጉት፥ ጳውሎስም ወደ ኋላ መለስ ብሎ የአይሁዶችን ታሪክ በመግለጽ 1. እግዚአብሔር በግብፅ ሳሉ መሪዎችን መርጦ እንዲበለጽጉ እንዴት እንዳደረገ 2. እግዚአብሔር ከግብፅ እየመራ አውጥቷቸው ለ40 ዓመት ያህል እንዴት እንደታገሣቸው 3. ሰባቱን መንግሥታት ድል አድርገው የከነዓንን ምድር እንዴት እንደሰጣቸው 4. እግዚአብሔር በመሐከላቸው ፈራጆችን እንዴት እንዳቆመ 5. እግዚአብሔርን ንጉሥ በጠየቁት ጊዜ፥ በመጀመሪያ ሳዖልን ቀጥሎም ዳዊትን እንዴት እንደሰጣቸው 6. እንደ ተስፋ ቃሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ እስራኤል እንዴት እንደላከው ይነግራቸዋል።

ጳውሎስ ወደ ኋላ መለስ ብሎ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ የሚጠቅሰው ብሉይ ኪዳን እንዴት ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያመለክት ለማሳየት ነው። እነዚህ አይሁዳውያን የመሢሑን መመለስ የሚጠባበቁ ናቸው። ይህ መሢሕ ከዳዊት ወገን እንደሆነም ያውቁ ነበር። ስለዚህም ጳውሎስ የዳዊትን ታሪክ ከተናገረ በኋላ፥ ወዲያውኑ የመልእክቱ ዋና ሐሳብ ወደ ሆነውና ከዳዊት ወገን ስለመጣው መሢሕ መናገር ይጀምራል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሚገኘው የመጨረሻው የሚልክያስ

መጽሐፍ ላይ አስቀድሞ ይመጣል ተብሎ የተነገረለት ሰው እንኳ መጥቷል። ይህንንም የጠቀሰው እነዚህ ሰዎች ምናልባት፥ የእግዚአብሔር መንግሥት መጥታለችና ንስሐ ግቡ ብሎ ማስጠንቀቂያ ስለሚሠጠው ስለመጥምቁ ዮሐንስ ወሬ ሳይሰሙ አይቀሩም በማለት ነው። በመቀጠልም፥ ኢየሱስ ከዚህ ሰው በላይ በጣም ታላቅ እንደሆነና አንድ ባሪያ እንደሚያደርገው የኢየሱስን የጫማ ጠፍር እንኳ ሊፈታ ብቁ እንዳልሆነ ይመሰክራል።

የኢየሱስን መምጣት ከጠቀሰ በኋላም፥ በጌታ ኢየሱስ ላይ ብቻ የሚያተኩረውን ሁለተኛውን የመልእክቱን ክፍል ይጀምራል። አሁንም፥ እንደገና ወንድሞቻችን፥ የአብርሃም ዘር ልጆች ከእናንተ መካከልም እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ በማለት ይጠራቸዋል። እነዚህ አይሁዳውያን ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበርም፥ ጳውሎስ ጌታ ኢየሱስን በተመለከተ ከብሉይ ኪዳን ላይ በመጥቀስ ሊያሳምናቸው ፈልጎ ነበር። ጳውሎስ መሚሐችሁ መጥቷል፤ ነገር ግን አልተቀበሉትም ብሎ ሲናገር አይሁዶቹን ግር ሳይላቸው አልቀረም። ምናልባት ስለ ኢየሱስና ስለሞቱ ሰምተው ይሆናል። ጳውሎስ፥ አይሁዳውያን ለዘመናት ሲጠብቁት የነበረው ተስፋ የተገባለት መሚሕ፥ ኢየሱስ እንደሆነ ይናገራል። ነገር ግን የኢየሩሳሌም ሰዎችና ገዥዎችም አላወቁትም። ለሞት የሚያደርስ ምንም ምክንያት ባይኖርም፥ ይገድሉታል። ታዲያ በምግባራቸው ቢሳሳቱም፥ አይሁዳውያኑ በየሰንበቱ ሁሉ የሚያነቧቸውን ትንቢቶች እንደፈጸሙ ጳውሎስ ያሰምርበታል። የኢየሱስ ሞት ድንገተኛ ሳይሆን እግዚአብሔር የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ የነበረውን ዕቅድ የሚፈፅም ነበር። እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት አስነሣው። ስለዚህም ጳውሎስ፥ ኢየሱስ ሕያው እንደሆነና፥ ለብዙ ቀናትም እራሱን ለደቀመዛሙርቱ እንደገለጸ ይነግራቸዋል። ስለዚህም ደቀመዛሙርቱ ለትንሣኤው እውነተኛ ታሪክ የዓይን ምሥክሮች ነበሩ።

በመጨረሻም ጳውሎስ መልእክቱን የሚያገባድደው ከብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ውስጥ አንዱ በሆነውና መዝሙር (2)፡ 7-9 በመጥቀስ ነው። በዚህ መዝሙር ላይ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሲጽፍ፥ ስለመሚሑ ትንሣኤ ተንብዮአል። ዳዊት በመጀመሪያ የጠቀሰው «አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ» የሚለውን ነው። ጳውሎስ ደግሞ የሚለው እግዚአብሔር ኢየሱስን በማስነሣቱ፥ ለሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ልጁ እንደሆነ አሳወቀ ነው። ይህ ጥቅስ ግን፥ ኢየሱስ በቤተልሔም ሲወለድ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነ ብሎ አያስተምረንም። ኢየሱስ ሁሌም ቢሆን የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ማሪያም እሱን በሥጋ ከመውለዷ በፊት እንኳ፥ እሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነበር ታዲያ በዚህ ሥፍራ ትኩረት የተሰጠው ነገር እግዚአብሔር በግልጽ ለሁሉም ሰው ኢየሱስ ልጁ እንደሆነ ገለጸ የሚለው እውነታ ነው።

በመቀጠልም ጳውሎስ የዳዊት ዘር የሆነው ኢየሱስ ከሙታን እንደሚነሣ የሚተነብዩትን ጥቅሶች ይጠቅሳል። ዳዊት ሥጋው በሞት ምክንያት መበስበስን እንደማያይ ይናገራል። እነዚህ ጥቅሶች ሞቶ የተቀበረውን ዳዊት በምንም ዓይነት ቢሆን አያመለክቱም። በምትኩ ግን፥ እነዚህ ትንቢቶች ሞቶ መበስበስን ሳያይ ከሙታን የተነሳውን የዳዊትን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክቱ ናቸው።

ይህን ሁሉ ከአስረዳ በኋላ ጳውሎስ «እንግዲህ ... በእርሱ በኩል የኃጢአት ስርየት እንዲነገርላችሁ፥ በሙሴም ሕግ ትጸድቁበት ዘንድ ከማይቻላችሁ ሁሉ ያመነ ሁሉ በእርሱ እንዲጸድቅ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን» ይላቸዋል። ይህ የሙሴ ሕግ ሊያደርገው የሚችለው ነገር አይደለም፤ የሙሴ ሕግ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ብቻ ነው የሚያሳያቸው። አሁን ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታቸው ሞቷል፤ በዚህም ምክንያት ለሰው ልጅ ሁለት ዋና ዋና በረከቶች ተሰጥተውታል። አንደኛ እውነተኛና ዘላለማዊ የሆነው የይቅርታ በር በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ክፍት ሆኖለታል። ሁለተኛ የኃጢአት ይቅርታን ላገኘ ሁሉ እውነተኛውን ጽድቅ ተጎናጽፎአል።

ጥያቄ 21:- ጸድቅ ማለት ምን ማለት ነው? ይህንን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ተመልከተው።

ጳውሎስ፥ ጽድቅ የሚገኘው ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን፥ በእምነት ብቻ እንደሆአነ፥ በመጨረሻ ላይ ያስጠነቅቃቸዋል። ጽድቅ የሚለው የሕግ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም፤ ከሠራው ኃጢአት ነፃ ወጥቶ ንጹሕና ቅዱስ ሰው ነህ ተብሎ ተቀባይነት ማግኘት ማለት ነው። ጽድቅ የሚገኘው ኃጢአተኛው በደለኛ አይደለም ተብሎ ከእግዚአብሔር ሲረጋገጥለት ነው። ለኃጢአት ዋጋ ተከፍሏል፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅም ለእርሱ ተሰጥቶታል፤ አሁንም ደግሞ ኃጢአት እየሠራን ብንሆንም ኃጢአታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ስለተሸነፈልን፥ እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆንን ይቆጥራል። ጳውሎስም ትንቢተ ዕንባቆም 1፡ 5 የጠቀሰው፥ ሕዝቡ እንዲያምን በማድረግ በነቢያት የተደነገገው ፍርድ በእነርሱ ላይ እንዳይፈጸም ሲል ነው።

በአጠቃላይ ይህ ለአይሁድ የተደረገው የመጀመሪያው የጳውሎስ ንግግር፥ በብሉይ ኪዳን ትንቢት ይነገርለት የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ የሚገልጥ ነው። ሰፋ አድርጎ ሲያብራራውም፥ የእግዚአብሔር ዓላማ ኢየሱስ ስለ ኃጢአት ይሞት ዘንድ እሱን ወደ ዓለም መላክ ሲሆን የሰውም ልጅ በእርሱ አምኖ ይጸድቃል ብሏል። የኢየሱስ ትንሣኤ እሱ መሢሕ እንደሆነ፥ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና እግዚአብሔር አብ ለዓለም ኃጢአት የቀረበውን መሥዋዕት እንደቀበለው የሚያረጋግጥ ነው። በተጨማሪም ይህ፥ ከኃጢአት ደኅንነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በማመን ነው የሚለው መልእክት ለአይሁዳውያንና ለአሕዛብ የተሰጠ ነው።

ጳውሎስ ልክ እንደጴጥሮስ «እናንተ እሱን አሳልፋችሁ ከሰጣችሁ በኋላ ገደላችሁት» ብሎ አይሁዳውያኑን አልወቀሳቸውም። ጴጥሮስ «ንስሐ ግቡና ተጠመቁ» እያለ ነው የሰበከው፤ ጳውሎስ ደግሞ «እመኑ፥ የኃጢአት ስርየትንና ጽድቅን የምታገኙት በእምነት ብቻ ነው» እያለ ነው የሰበከው (ኤፌ. 2፡ 8-9)።

ጥያቄ 22:- ሀ) ከጳውሎስ መልእክት ውስጥ ለአንድ ክርስቲያን ላልሆነ ሰው ስትመሠክር ልትጠቅሳቸው የሚገቡህን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ። ለ) ጳውሎስ ከጠቀሳቸው ነገሮች ውስጥ፥ ለአይሁዳውያን ይጠቅሙ የነበር፥

ነገር ግን ለአንድ ክርስቲያን ላልሆነ ሰው ይድን ዘንድ የግድ ሊያውቃቸው የማይገቡ አንዳንድ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ጥያቄ 23፡- በእግዚአብሔር ዓይን አሁን አንተ ጻድቅ ወይም ቅዱስ ነህን? ከሆንክ፥ ይህ ለሕይወትህ ምን ዓይነት ትርጉም እንደሚሰጥህ ለአንድ ሰው አስረዳ። ካልሆንክ፥ የኢየሱስ ሞት የኃጢአትህን ዋጋ እንደከፈለልህ በመቀበል፥ እግዚአብሔር ኃጢአትህን ይቅር እንዲልህ ጸልይ። ኢየሱስም የሕይወትህ ንጉሥ ሲሆን፥ በሞቱ የከፈለልህን ነገር አትዘንጋ! አሁኑኑም ሄደህ ይህን ያደረገውን ውሳኔ ለአንድ ሰው ንገር (ሮሜ 10፡ 9-10)።

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 13፡ 42-52

ይህ የተመዘገበው የጳውሎስ መጀመሪያ መልእክት፥ በብሉይ ኪዳን ላይ ተመሥርቶ፥ ደኅንነት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንደሚገኝ በግልጽ የሚያሳይ ነው። በእየሩሳሌም የነበረው ሕዝብ እንዳደረገው፥ ኢየሱስን እንዳይቃወሙ፥ ነገር ግን ሰዎችን ሁሉ በቅዱሱ አምላክ ፊት ጻድቅ አድርጎ ሊያቀርብ የሚችለውን ክርስቶስን ብቻ እንዲያምኑ አሕዛብንና አይሁዳውያኑን በጣም ይገፋፋቸው ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል ሲከብር፥ ሰይጣን አይደሰትም። በዚህም መሠረት ጳውሎስ በመልእክቱ አይሁዶችና አሕዛብ ጽድቅንና ምሕረትን በክርስቶስ ታገኛላችሁ ብሎ ካለ በኋላ፥ ጠላት ሥራውን መሥራት ይጀምራል።

የሐዋርያት ሥራ 13፡ 42-52 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጥያቄ 24 ሀ) ሕዝቡ ለጳውሎስ መልእክት የሰጠው ምላሽ ምን ዓይነት ነው? ለ) በርናባስና ጳውሎስ ምን እንዲያደርጉ ጠየቋቸው? ሐ) ለሁለተኛ ጊዜ ሕዝቡ ሲሰበሰቡ፥ አይሁዳውያኑ የወሰዱት እርምጃ ምን ነበር? መ) ጳውሎስና በርናባስ ለአይሁዳውያኑ መልስ የሰጧቸው እንዴት ነው? ሠ) ጳውሎስና በርናባስ ከጲስዲያ አንጾኪያ ለመውጣት የተገደዱት ለምንድነው?

የጳውሎስን መልእክት በምኩራቡ የሰሙት ሰዎች፥ በመጀመሪያ ላይ በኢየሱስ በኩል ስላለው ደኅንነት ሲነገራቸው በጣም ደስ ብሏቸው ነበር። በእግዚአብሔር ፀጋ ጸንተው እንዲቆዩ ይመከራቸው በነበረውም በጳውሎስ ዙሪያ ከበውት ይሄዱ ነበር። ምንም እንኳ ብዙ አይሁዳውያን በመልእክቱ ቢሳቡም፥ እግዚአብሔርን ለሚፈሩት አሕዛብ ግን የበለጠ በጣም ጥሩ ነበር። እነሱም በሚመጣው ሳምንት ጳውሎስና በርናባስ መጥተው ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰፋ አድርገው እንዲያስረዱዋቸው ለምነዋቸዋል።

በመላዋ አንጾኪያ ስለ ጳውሎስ መልእክት ወሬው ተዛመተ፤ በሚመጣውም ሳምንት ጳውሎስ የሚናገረውን ለመስማት አብዛኛዎቹ የከተማዋ ሰዎች ተሰበሰቡ። በአሁኑም ጊዜ ብዙ አሕዛቦች የጳውሎስን መልእክት ለመስማት በምኩራቡ ተሰባስበዋል። ስለ ኃጢአት ይቅርታ የሚያወሳውን የወንጌሉን መልእክት ለመስማት ልባቸው ተዘጋጅቶ ነበር። አይሁዳውያኑ ግን፥ ልባቸው በቅናት ተሞልቶ ነበር። ብዙ

አሕዛብ መምጣታቸው አላስደሰታቸውም ነበር። በተለይም፥ አሕዛብ እንዲድኑ ሲል ልክ እንደ አይሁዳውያኑ እኩል ያያቸው ስለነበርና አይሁዳውያንም ባይሆኑ ሊቀበላቸው ዝግጁ በመሆኑ አይሁዳውያን አልተደሰቱም ነበር። የአይሁድ መሪዎችም፥ ጳውሎስንና መልእክቱን በመቃወም መናገር ጀመሩ። ልባቸውን ከፍተው መንፈስ ቅዱስንና ጳውሎስን ከመስማት ይልቅ፥ ሰይጣን በቅናታቸው ተጠቅሞ ልባቸውን እንዲደነድን አደረገ።

ጥያቄ 25፡- አንዳንድ መሪዎች፥ ከራሳቸው ይልቅ ከሌላ ጎሳ ወይም ቡድን ውስጥ ያሉ ተቀባይነት ሲያገኙ የሚቀኑት ለምንድነው?

ወንጌሉን አንቀበልም ብለው አፋቸውን ሞልተው በግልጽ ሲናገሩ ጳውሎስና በርናባስም «የእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ለእናንተ ይነገር ዘንድ ያስፈልጋል፤ ከገፋችሁትና ለዘላለም ሕይወት ብቁ አይደለንም ብላችሁ በራሳችሁ ከፈረዳችሁ ግን እነሆ ወደ አሕዛብ ዘወር እንላለን» አሏቸው። አይሁዶች በእግዚአብሔር የተመረጡ የአብርሃም ልጆች ስለሆኑ፥ መጀመሪያ ላይ የወንጌሉን መልእክት ይዘው ወደ እነርሱ መምጣት ግዴታቸው ነበር። ሆኖም፥ ሁለቱ ሚሲዮናውያን፥ አይሁዶች ልባቸውን እንደ ኢየሩሳሌሞቹ አይሁዳውያን ወገኖቻቸው እንዳደነደኑ ባዩ ጊዜ፥ ልባቸውን ከፍተው ይጠባበቁ ወደነበሩት አሕዛብ ዘወር አሉ። ጳውሎስ፥ ጀርባቸውን ለእርሱ መልእክት መስጠታቸው ዘላለማዊ ሕይወትን አንፈልግም ብሉ በራስ ላይ እንደመፍረድ እንደሆነ በብርቱ አስጠንቅቋቸዋል። አይሁዳውያን በመሆናቸውና የብሉይ ኪዳንን ሕግ በመጠበቃቸው ደኅንነትን አያገኙም። ደኅንነት የሚገኝበት አንድ ብቸኛ መንገድ አለ፤ እሱም በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው። ሌላ ሃይማኖት በመከተል ወይም ጥሩ ሥራ በመሥራት ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመድረስ የምናደርገው ማናቸውም ዓይነት ሙከራ ወደ ገሃነመ እሳት ነው የሚመራን።

ጥያቄ 26፡- ሀ) ምንም እንኳ ታማኞች ቢሆኑም ሌላ ሃይማኖት ስለሚከተሉ ሰዎች ደኅንነት፥ እነዚህ ጥቅሶች የሚያስተምሩን ነገር ምንድነው? ለ) ይህ ወንጌሉን ለእነርሱ የማካፈሉን ኃላፊነታችንን በተመለከተ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?

አይሁዳውያን ለአሕዛብ መብራት እንደሆኑ የሚገልጸውን ትንቢት ኢሳይያስ 42፡ 6-7 ጳውሎስ ጠቅሶላቸዋል። እግዚአብሔር አይሁዳውያንን የመረጠው፥ የእሱን በረከት እንዲቀበሉ ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር ሁሌም ቢሆን ስለ ዓለም ሕዝቦች በአጠቃላይ ያስብ ነበር። ዋናው እግዚአብሔር አይሁዳውያንን የመረጠበትም ምክንያት፥ የእግዚአብሔር ምርጦች እንደመሆናቸው ለአሕዛብ ሁሉ ብርሃን ይሆኑ ዘንድ ነው። የእግዚአብሔር ዓላማ መላውን ዓለም የሚያጠቃልል ነው። ሆኖም፥ አይሁዳውያን እግዚአብሔር ስለ እነርሱ ብቻ የሚያስብ ነበር የሚመስላቸው። ብርሃናቸውም ብዙ ጊዜ በሐሰት አምልኮ፥ በክፋት በተሞላ አኗኗራቸውና በትዕቢታቸው ምክንያት ይሸፈን ነበር።

ጥያቄ 27፡- ሀ) ክርስቲያኖች ለማያምኑ ሰዎች ብርሃን ሊሆኑ የሚችሉት በምን ዓይነት መንገድ ነው? ለ) ብርሃንህን በአካባቢህ ባሉ የማያምኑ ሰዎች መካከል

የምትገልጸው እንዴት ነው? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ወይም ቤተክርስቲያኖች ብርሃናቸውን የሚያጡት እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ለእነርሱ በጣም እንደሚያስብ ማወቃቸው አሕዛብን በጣም አስደስቷቸዋል። እግዚአብሔርም ቀደም ብሎ ልባቸውን አዘጋጅቶታል። የቀድሞው የአምልኮ ሥርዓታቸው ሰልችቷቸዋል፤ ለኃጢአታቸውም ይቅርታን ማግኘት ይሻሉ። ሆኖም፥ የአይሁዳውያኑ ትምህርት በእምነታቸው ላይ እንቅፋትን ፈጥሮባቸዋል። እግዚአብሔር ይድኑ ዘንድ ከእነርሱ የሚሻው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቻ መሆኑን በሰሙ ጊዜ፥ ብዙዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል በማመን በክብር ተቀበሉት፤ በዚህም የዘላለማዊ ሕይወት ስጦታ ወራሾች ሆነዋል። አይሁዳውያኑ የተቃወሙትን፥ አሕዛብ ተቀበሉት። ብዙ ጊዜም እኛ ጥሩ ሰዎች ነን ብለው የሚያስቡ ወይም መንፈሳዊ ነን የሚሉ ሰዎች፥ በቀላሉ የዘላለማዊውን ሕይወት ስጦታ አሻፈረኝ ብለው ይተዉታል። ሆኖም ዝግጁ ሆነው የሚያምኑት ኃጢአተኞች እንደሆኑ ተገንዝበው እምነታቸውን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ለማድረግ ፈቃደኞች የሚሆኑት ብቻ ናቸው።

ጥያቄ 28፡- ለሌሎች ስትመሠክር ይህንን ነገር ያየኸው እንዴት ነው?

የእግዚአብሔር ቃል በአካባቢው በሙሉ ተስፋፋ። አሕዛብ አመኑ፤ አይሁዳውያን ግን አናምንም አሻፈረኝ ብለው እውነቱን መቃወም ጀመሩ። በዚህም መሠረት የሚያመልኩትን፥ የከበሩትን ሴቶችና የከተማውን መኳንንት አወኩ። በጳውሎስና በበርናባስ ላይም የከፋ ተቃውሞ በማስነሣታቸው፥ ከተማውን ለቀው ለመሄድ ተገደዱ። በጥንቷ ቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥም ሲታይ፥ በክርስቲያኖቹ ላይ ታላቅ የሆነ ስደት ያስነሡት አይሁዳውያን ናቸው።

ጥያቄ 29፡- ሀ) በተቃውሞ ምክንያት፥ የወንጌሉ ምሥክርነት ወይም ትምህርት ቆሞ ወይም ታግዶ አይተህ ታውቃለህ? ለ) ይህ ተግባር የምሥራቹን ዜና ስለሚቃወሙት የሚገልጽልን ነገር ምንድነው?

ጳውሎስና በርናባስ ከጲስዲያ አንጾኪያ በወጡበት ጊዜ፥ ባለማመናቸው ምክንያት ለሚመጣባቸው ፍርድ ኃላፊነት የእራሳቸው የአይሁዳውያኑ እንደሚሆን የሚገልጽ ተግባር ፈጽመው ነው የወጡት። አይሁዳውያን አረመኔ ከሆኑ ሰዎች አገር ቆይተው ወደ ምድራቸው ሲመለሱ፥ የዛን አገር ትቢያ ከጫማቸው ላይ ማራገፍ የተለመደ ተግባራቸው ነበር። ይህም እግዚአብሔርን ከማያመልኩ ኃጢአተኞች እርኩሰት ሁሉ እራሳቸውን ማንጻታቸውን የሚያሳይ ተግባር ነው። የጳውሎስና በርናባስ እግሮቻቸውን የማራገፉ ጉዳይ ለአይሁዳውያን የሰጣቸው ምልክት ቢኖር በጳውሎስና በበርናባስ እንደ አረመኔ መቆጠራቸውን ነበር። ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ውጭ እንደሆኑ ተቆጥረው መለኮታዊ ፍርድን እንደሚቀበሉ ነው።

ምንም እንኳ ጳውሎስና በርናባስ ለመሄድ ቢገደዱም፥ ወደኋላ የቀሩት አዳዲሶቹ አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው በጣም ደስ አላቸው።

ጳውሎስ መጀመሪያ ለአይሁዳውያን ቀጥሎም ለአሕዛብ መሥክር ተብሎ በታዘዘው መሠረት ትዕዛዙን ይፈጽማል። ምንም እንኳ አንዳንድ አይሁዳውያን መልእክቱን

ቢቀበሉትም፥ ብዙዎቹ ግን ተቃውመውታል። እግዚአብሔርም ከምሕረቱ የተነሣ የመረጣቸውን ሕዝቦች ወደ እርሱ ለማምጣት ይጥራል፤ ነገር ግን በኋላ ላይ እንደምናየው እስከ መጨረሻው ድረስ ይቃወሙታል።

አስተውል፤ ምንም እንኳ ስደት ቢያጋጥማቸውም ጳውሎስና በርናባስ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሥራ መፈጸሙን ቀጥለውበታል። በዚህም መሠረት የምሥራቹን ዜና ለመስበክ ወደ ሌላ ከተማ ሄዱ። ተቃውሞና ስደት ቢያጋጥማቸውም እንኳ፥ እግዚአብሔር በእነዚህ ሁለት ሰዎች በኩል እንደሠራ በመጭው ሳምንት እናያለን።

ጳውሎስ በመከራና በተቃውሞ ተስፋ አይቆርጥም። የፈለገውን ያህል ዋጋ ያስከፍለው፤ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ የኢየሱስን የምሥራች ዜና የማስፋፋት ፍላጎት ነበረው። ከጥሩ ሥራ፥ ከተመቻቸ ሕይወት፥ ከስደት ነፃ ከመሆን ወይም ከማንኛውም ነገር በላይ፥ ለእርሱ ዋነኛ አድርጎ የያዘው ወንጌሉን የማስፋፋት ጉዳይ ነው።

ጥያቄ 30፡- ወንጌሉን ላልሰሙት ሰዎች ለማሰራጨትና በዛ ምክንያት የሚመጣውን መከራ ለመቀበል ምን ያህል ዝግጁ ነህ?

# አምስተኛ ቀን፡-

## የክለሳ ጥያቄዎች የሐዋርያት ሥራ 13፡ 1-52

1. ስለ ሶርያዋ አንጾኪያ ቤተክርስቲያን መሪዎች ማብራሪያ ስጥ

   ሀ) ከየት የመጡ ናቸው? ለ) አይሁዳውያን ናቸው ወይስ አሕዛብ?

2. መንፈስ ቅዱስ፥ በርናባስንና ሳውልን በመላኩ ላይ የነበረው ድርሻ ምን ነበር?
3. በርናባስንና ሳውልን በመላክ ረገድ፥ ቤተ ክርስቲያኗስ ኃላፊነቷን የተወጣችው እንዴት ነው?
4. ጳውሎስ ጠንቋዩን ኤልማስን በፅኑ የተቃወመው ለምንድነው? ኤልማስ ሊያደርግ የሞከረው ነገር ምንድነው?
5. ጳውሎስን ለመሪነት ብቁ ያደረገው ነገር ምንድነው?
6. ጴጥሮስ አይሁዳውያንን ንስሐ እንዲገቡ ገፋፋቸው። ጳውሎስስ ለአሕዛብ ያቀረበው ልመና ምንድነው?
7. ምንም እንኳ ጳውሎስና በርናባስ ከጲስዲያ አንጾኪያ ለመውጣት ቢገደዱም፥ ምሥክርነታቸው የተፈለገውን ግብ እንደመታ የምንረዳው እንዴት ነው?
8. በመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞአቸው ጳውሎስና በርናባስ የሄዱባቸው አገሮች በዝርዝር ግለጽ። እነዚህ ቦታዎች የሚገኙበትን ሥፍራ እንድታውቅ፥ ከዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ ካለው ካርታ ላይ ቦታዎቹን ፈልግ።

የመወያያ ጥያቄዎቹን በማንበብና በማሰብ ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. ክለሳ
4. ውይይት፡-

ሀ) 1. ወንጌላውያንን ወደ ሌላ ሥፍራ ወይም አገር በመላኩ ረገድ ቤተክርስቲያን ያለባት ኃላፊነት ምንድነው? 2. ቤተክርስቲያንህ የአንጾኪያዋን ቤተክርስቲያን ምሣሌነት የምትከተለው እንዴት ነው? 3. ወንጌላውያን የሚመረጡት እንዴት ነው? 4. ቤተክርስቲያንህ ከምትገኝበት ሥፍራ አልፉ ወደ ሌሎች ወንጌልን ለማዳረስ የምትጥረው እንዴት ነው?

ለ) 1. ጳውሎስን፥ ለአሕዛብ ወንጌላዊ ይሆን ዘንድ ብቁ ያደረገው ነገር ምንድነው? ሐዋ. 13፡4፤ 9፡ 47 ተመልከት። 2. ብቁ ካደረጓት ነገሮች ውስጥ ዋነኛው የትኛው ነው? 3. ዛሬ አንድን ወንጌላዊ በየከተማው፥ በየገጠሩ፥ ወዘተ... እንዲላክ ብቁ የሚያደርጉት ነገሮች ምንድናቸው? 4. ቤተክርስቲያን ወንጌላዊ ስትመርጥ፥ ሰውዬው ማሟላት ያለበት መመዘኛዎች ምንድናቸው? 5. ወንጌላውያንን በተመለከተ፥ ያመራረጡ ስልት እንዴት ሊሻሻል ይችላል?

ሐ) 1. መሪነቱ በጳውሎስ ሲወሰድ፥ ከበርናባስ ምሣሌያዊ ሥነምግባር ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው? 2. ይህ ብዙ የቤተክርስቲያን መሪዎች ካሏቸው አመለካከቶች የሚለየው እንዴት ነው?

መ) 1. የጳውሎስን ወንጌላዊ መልእክት በቤተክርስቲያንህ በኩል ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ከሚሰበኩት መልእክቶች ጋር አነፃፅር። የሚለያዩት እንዴት ነው? የሚመሳሰሉትስ እንዴት ነው? 2. የሚለያዩት ለምንድነው? 3. በሁሉም ወንጌላዊ መልእክቶች ውስጥ ሊካተቱ የሚገቡ እውነታዎች ምን ምንድናቸው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 11

የሐዋርያት ሥራ 14: 1-15:35

## የመጀመሪያ ቀን:-የሐዋርያት ሥራ 14:1-20

ከ 46-48 ዓ.ም ድረስ የተደረገውን የመጀመሪያውን የጳውሎስና የበርናባስን ሚሲዮናዊ ጉዞ ባለፈው ሳምንት አይተናል። በአሕዛቡ ዓለም በተለይም በዛሬዋ ቱርክ እንዴት ወንጌሉ እንደተስፋፋም አይተናል። በተጨማሪም የመሪነቱ ቦታ ከበርናባስ የአሕዛቡ ሐዋርያ ወደነበረው ወደ ጳውሎስ እንዴት እንደተሸጋገረ አይተናል። ከአሁን

ወዲህ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የሚያተኩረው እግዚአብሔር በጳውሎስ በኩል ወንጌሉን ያኔ በነበረው ዓለም እንዴት እንዳስፋፋው በሚተርከው ታሪክ ላይ ነው።

በጲስዲያ አንጾኪያ የመጀመሪያው የጳውሎስ መልእክት ተመዝግቦልናል። ይህም መልእክት የኢየሩሳሌም ሕዝብና ገዢዎች እንዳደረጉት፥ አይሁዳውያኑና አሕዛብ ኢየሱስን እንዳይከዱ የሚያሳስብ ነው። ከተማውም ሁሉ በሚቀጥለው ሳምንት ጳውሎስን ለመስማት ሲሰበሰብ፥ አይሁዳውያን በቅናት ተሞልተው መሳደብ ጀመሩ። በዚህን ጊዜም ጳውሎስ አይሁዳውያኑን «የእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ለእናንተ ይነገር ዘንድ ያስፈልጋል፤ ከገፋችሁት ... ወደ አሕዛብ ዞር እንላለን» ይላቸዋል። የራሱ ሕዝቦች የሆኑት አይሁዳውያን በሕይወቱ ሙሉ በጳውሎስ ላይ ያስነሡትን ተቃውሞ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነው የሚጀምሩት። አሕዛብ ደግሞ የደኅንነት በር ስለተከፈተላቸው በጣም ደስ ብሏቸዋል፤ ብዙዎቹም አመኑ፤ ወንጌሉም በአገሩ ሁሉ ተሰፋፋ።

በእርሱ ላይ የተነሣው ተቃውሞ ሲባባስ፥ ጳውሎስና በርናባስ ወደሌሎች ከተሞች ሄዱ። የእግዚአብሔር ቃል ሲከብር፥ በዚያው መጠን ተቃውሞውም ይጨምራል። ጳውሎስና በርናባስም በየከተማው ሲዟዟሩ፥ ተናደው የነበሩት አይሁዳውያን ይከታተሏቸው ነበር፤ ሆኖም የእግዚአብሔር ኃይል ይገለጥ ስለነበር ብዙ ሰዎች አምነዋል። በየከተማውም ይቀርቡ የነበሩት የጳውሎስ መልእክቶች የራሳቸው የሆነ ባህሪ ነበራቸው። የዛሬውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም ስታነብ፥ ዛሬ ወንጌልን በተቀናጀ መልክ ለመስፋፋት የሚጠቅሙ ናቸው የምትላቸውን ነጥቦች ተመልከት።

የሐዋርያት ሥራ 14፡ 1-15፡ 35 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ። ጥያቄ 1 ሀ) ጳውሎስና በርናባስ የሄዱባቸውን ከተሞች በዝርዝር ጻፍ። ሥፍራዎቹንም በካርታው ላይ ተመልከት። ለ) ጳውሎስና በርናባስ ወደ ሶርያዋ አንጾኪያ ሲመለሱ ያደረጉት ነገር ምንድነው? ሐ) በኢየሩሳሌሙ የሽማግሌዎች ስብሰባ ላይ፥ ዋና የመወያያ ጥያቄ የነበረው ምንድነው?

የሐዋርያት ሥራ 14፡ 1-20 እንደገና አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 2፡- ሀ) የጳውሎስና የበርናባስ የኢቆንዮን መልእክት ያስገኘው ውጤት ምንድን ነው?

ለ) በዚህ ሥፍራስ ችግር የፈጠረው ማነው?

ሐ) በልስጥራን የነበረው እግሩ የሰለለች ሰውዬ ሲፈወስ፥ የሕዝቡ ምላሽ ምን ነበር?

መ) ወደ ጳውሎስና በርናባስ የነበራቸው አመለካከት እንዲህ በቅፅበት የለወጠው ነገር ምንድነው?

ሠ) ሁለቱ ሰባኪዎች ከልስጥራን ተነሥተው የሄዱት ወዴት ነው?

የጲስዲያዋን አንጾኪያ ትተው፤ ጳውሎስና በርናባስ በ100 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ወደ ምትገኘው ወደ ኢቆንዮን ያመራሉ። ወንጌሉን በማስራጨቱ ረገድ ጳውሎስ የነበረው ዕቅድ፥ በትላልቅ ከተማዎች ላይ አብያተክርስቲያናትን መመሥረት ነው። ይህንንም

የሚያደርገው፥ ከእነዚህ ቦታዎች ተነሥቶ ወንጌል በአካባቢው ሥፍራዎች ይሰራጫል ብሎ ያምን ስለነበር ነው።

ጥያቄ 3፡- ዛሬ ወንጌልን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፋፋት ሲባል፥ ይህንን ዕቅድ ልንጠቀምበት የምንችለው እንዴት ነው?

በኢቆንዮን ብዙ አይሁዳውያንና አህዛብ አምነዋል። ለተወሰነም ጊዜ፥ ጳውሎስና በርናባስ በድፍረት ይናገሩና እግዚአብሔርም የመልእክቱን እውነተኛነት ድንቅና ተአምራት በመሥራት ያረጋግጥላቸው ነበር። ሆኖም፥ አንዳንድ አናምንም ብለው ያሉ አይሁዳውያን በጳውሎስና በበርናባስ ላይ ብዙ ሰዎችን አስነሡባቸው። ከተማዋም፥ የተከፋፈለች። አንዳንዶቹ አይሁዳውያንና አሕዛብ በተለይም በመሪነት ቦታ ላይ ያሉት፥ በሐዋርያቱ ላይ ተነሡባቸው። ጳውሎስና በርናባስ ሊወግሯቸው እንዳሰቡ ሲሰሙ፥ የኢቆንዮን ከተማ ትተው፥ ስለ ኢየሱስ ለመስበክ ወደ ሌላ ሥፍራ ይሄዳሉ። ይህን ሲያደርጉ ግን አዳዲስ አማኞችን ከበስተኋላቸው ትተው ነው የሄዱት።

ጥያቄ 4፡- በምትኖርበት አካባቢ ወንጌልን እንዴት ማስተማር እንደምትችል አስቲ አስብ። ስብከትህን የምትጀምረው ከየት ነው? ለሰዎች ሁሉ ለማዳረስ የምትጥረው እንዴት ነው?

ጥያቄ 5 ፡-ችግር ሲፈጠር ከዚያ ቦታ ተነሥቶ መሄድ ትክክል የሚሆነው መቼ ነው? ትክክልስ የማይሆነው መቼ ነው?

ጳውሎስና በርናባስ ኢቆንዮን ትተው ወደ ልስጥራንና ደርቤን ይሄዳሉ። በሄዱበትም ቦታ ሁሉ፥ ወንጌልን ይሰብኩ ነበር።

መጀመሪያ የሄዱት፥ ከኢቆንዮን 35 ኪ. ሜ. ርቀት ላይ ወደምትገኘው ወደ ልስጥራን ነው። በዚያም ጳውሎስ ሲሰብክ አንድ እግሩ የሰለለችበት ሰውዬ ያዳምጠው ነበር። ጳውሎስም ይህ ሰው ወንጌልን እንደተጠማና ለደኅንነት ብቻ ሳይሆን ለፈውስ የሚበቃ እምነትም እንዳለው አየ። ከዚያም ጳውሎስ «ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም» ሲለው ሰውዬውም ቃሉን በማክበር በሙሉ ልብ ታዘዘና ብድግ አለ፤ ፍጹም ድና መራመድ ጀመረ።

ጥያቄ 6፡- ይህ ተአምር በሕዝቡ ላይ ያመጣው የተሳሳተ አመለካከት ምንድነው?

ልስጥራን፥ ብዙ አማልክትን የሚያመልኩ አሕዛብ የተሰበሰቡባት ከተማ ናት። ሰዎች አንድ ተአምር ሲያዩ፥ ወዲያውኑ ያንን ነገር የሚገነዘቡት ከራሳቸው አምልኮ ጋር በማስተያየት ነው። ስለዚህም ክብሩን ለእግዚአብሔር ከመስጠት፥ ለሌሎች አማልክት ይሰጣሉ። በዚህም መልኩ፥ ጳውሎስና በርናባስ የሰውን መልክ ይዘው የመጡ ሄርሜንና ድያ የሚባሉት የግሪክ አማልክት መሰሏቸው። ሄርሜንና ድያ የሚባሉት የግሪክ አማልክት በልስጥራን የሚመለኩትና ብዙ ተከታዮች የነበሯቸው አማልክት ናቸው። ለበርናባስ የተሰጠው ድያ የሚለው ስም የዋነኛው አምላክ ስም ነበር። ለጳውሎስ የተሰጠው ሄርሜን የሚለው ስም ደግሞ፥ የድያ ቃል አቀባይ የነበረ አምላክ ነው። ይህን ዓይነቱንም ክፍፍል ያደረጉት፥ ምናልባት ብዙውን ጊዜ የተናገረው ጳውሎስ በመሆኑ ነው።

የአንካሳውን ሰውዬ መፈወስ ሲያዩ፥ አማልክት ናቸው ብለው በማሰባቸው፥ ሕዝቡና የድያ ካህናት ኮርማዎችንና የአበባ አክሊሎችን አምጥተው ሊሰዉላቸው ወደዱ። በራሳቸውም ቋንቋ ይነጋገሩ ስለነበር፥ ጳውሎስና በርናባስ የሚያደርጉትን ቶሎ አልተገነዘቡም ነበር። ከዚያም፥ ልክ ሰዎቹ የሚያደርጉትን ነገር ሲገነዘቡ በታላቅ ሐዘን ልብሳቸውን በመቅደድ፥ ሊያስቆሟቸው ወደ እነርሱ ይሮጣሉ። ከእግዚአብሔር ይልቅ እነርሱን ሊያመልኩ መነሣታቸውም በጣም አሳስቧቸዋል። የተአምራቱ ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ እንዲሰጥ በመፈለጋቸው፥ ጳውሎስ እንደገና የክርስቶስን መልእክት ማስረዳት ጀመረ።

ጥያቄ 7:- አንዳንድ የቤተክርስቲያን መሪዎች እንዴት አድርገው እግዚአብሔር በሠራው ሥራ፥ የግል ጥቅማቸውን ለማግኘት እንደሚጥሩ የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ስጥ።

የቤተክርስቲያን መሪዎችን የሚያዘናጉ ሁለቱ ዋና ዋና ፈተናዎች ክብርና ምሥጋና ናቸው። ብዙዎቹም መሪዎች ክብርና ምሥጋና የሚሰጠው ለእግዚአብሔር ሆኖ ሳለ ይህን በመዘንጋት በሚሰጣቸው ክብርና ሙገሳ ይኩራራሉ።

ጳውሎስ፥ አይሁዳውያኑን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ወደሚገኘው እግዚአብሔር ሲያመለክታቸው፥ አሕዛብን ደግሞ ስለእውነተኛውና ስለሕያው አምላክ በማስረዳት መልእክቱን መጀመር አለበት። ጳውሎስ ለተሰበሰቡት አረመኔዎች ያቀረበው መልእክት፥ ሰማይና ምድርን ወደ ፈጠረው ሕያው አምላክ ፊታቸውን እንዲያዞሩ የሚያደርጋቸው ነበር። ክብር የሚገባውም እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ አስረዳቸው። በመቀጠልም ጳውሎስ «እግዚአብሔር ባለፉት ትውልዶች አሕዛብን ሁሉ በገዛ ራሳቸው ጎዳና ይሄዱ ዘንድ ተዋቸው። ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራ እየሠራ፥ ከሰማይ ዝናብን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፥ ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለምስክር አልተወም።» ይላቸዋል (ቁ. 16-17)።

ጥያቄ 8:- ሀ) ይህን ዓይነቱን መልእክት ለአይሁዳውያኑ አላስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? ለ) ይህ ነገር፥ መልእክቶቻችን ለምንመሰክርላቸው ሰዎች እንዲገባ አድርገን በማቅረቡ ረገድ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው? ሐ) በአካባቢህ ያሉ ሰዎች፥ የወንጌሉን መልእክት በደንብ አድርገው ከመገንዘባቸው በፊት፥ ልትገልጽላቸው የሚገባህን አንዳንድ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

ምንም እንኳ ጳውሎስና በርናባስ ስለ እውነተኛው አምላክ ለማስረዳት ቢሞክሩም፥ ሕዝቡ ሊረዳቸው አልቻለም! ለእነርሱም ከመሰዋት ሰዉን ያግዱት ዘንድ አልቻሉም።

ብዙ ጊዜ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አካባቢ እንደሚሆነው፥ የሕዝቡ አስተሳሰብ ትልቅ ክብር ከመስጠት ወደ ጥላቻ ይለወጣል። ጳውሎስም ስለ ክርስቶስ የሚሰጠውን ምስክርነት ከመጨረሱ በፊት፥ አንዳንድ አይሁዳውያን ከኢቆንዮን ይመጡና ሕዝቡን በማባበል በጳውሎስና በበርናባስ ላይ እንዲነሣ ያደርጉታል! ለሁለቱ ሐዋርያት የነበረው የመስዋዕት ማቅረብ ወዲያውኑ ተለውጦ እነርሱን በድንጋይ ወደ መውገር

ይደርሳል። ሕዝቡ ከዚህ ወዲህ ጳውሎስ የሚናገረውን መስማት አልፈለገም። እነሱ የሚፈልጉት የበፊቱን የጣዖት አምልኮ ሥርዓታቸውን መቀጠል ነው።

ጥያቄ 9:- ጳውሎስ በየጊዜ ተቃውሞ ያጋጥመው ነበር። ስለ ክርስቶስ ስትመሰክር ተቃውሞ ያጋጠመህ እንዴት ነው?

ጳውሎስ፣ ምናልባት ዋነኛው መሪ በመሆኑ፣ የሞተ እስኪመስላቸው ድረስ በድንጋይ ወግረው ከከተማ ውጭ ጎትተው ያወጡታል። ከጳውሎስ ምስክርነቶች ውስጥ ተቃውሞን ካስነሱበት ከብዙዎቹ ምስክርነቶች ውስጥ አንዱ ይህ ነው። ሆኖም ስደት ለሁሉም ሕዝቦች ወንጌልን እንዲያካፍል ከተጠራበት ጥሪ፣ ጳውሎስን ፈቅ አላደረገውም።

ጥያቄ 10:- ስደት፣ አንዳንድ ክርስቲያኖችን ለክርስቶስ ያላቸውን ምስክርነት እንዲያቆሙ ያደረጋቸው እንዴት ነው?

ሕዝቡ ጳውሎስን በድንጋይ ከወገረ በኋላ፣ የሞተ መስሏቸው ትተውት ይሄዳሉ። ያለጥርጥርም፣ ደቀመዛሙርቱ የሞተ መስሏቸዋል። ሆኖም፣ ደቀመዛሙርቱ ሲከቡት፣ ተነሥቶ ወደ ልስጥራን ተመልሶ ይገባል። በሚቀጥለውም ቀን ጳውሎስና በርናባስ ከልስጥራን 100 ኪ. ሜ. ርቀት ላይ ወደምትገኘው ወደ ደርቤን ሄዱ።

የጳውሎስና የበርናባስ አገልግሎት ፍሬ የሌለው አልነበረም። ጳውሎስና በርናባስ በልስጥራን እንዴት ትንሽ ቤተክርስቲያን እስከመመሥረትም ደርሰዋል። ከዚህም ባሻገር፣ ወደበኋላ ላይ ከጳውሎስ ጋር አብሮ የሚጓዘው ሰውዬ ከልስጥራን ቤተክርስቲያን የመጣ ነው። በተጨማሪም፣ ልስጥራን የጢሞቴዎስ የትውልድ ሥፍራ ሳትሆን አትቀርም፤ ምናልባትም እሱና ቤተሰቦቹ ወደ ጌታ የመጡት በዚህ ጊዜ አካባቢ ሳይሆን አይቀርም። ወደ በኋላ ላይ፣ በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው፣ ጳውሎስ ወንጌልን በማሰራጨቱ እንዲረዳው ጢሞቴዎስን ይወስደዋል።

ጳውሎስ በግሉ፣ ወንጌልን ለማስፋፋት ሲል፣ እስከመጨረሻው ዋጋ ለመክፈል ቆርጦ የተነሣ ሰው ነው። ለእርሱ፣ ወንጌልን ማስፋፋትና ቤተክርስቲያንን መመሥረት፣ ትልቁ ሥራው ነበር። ታዲያ ምንም እንኳ በጣም መከራ ቢቀበልም፣ ሥራውን መሥራቱን አላቆመም። አንተስ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ኢየሱስን ለማያውቁ ሰዎች ይህን ያህል ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ነህ?

ጳውሎስ እሱን ለመስማት ለታደመው ሕዝብ ንግግሩን የሚያሰማው በችግራቸውና በፍላጎታቸው ላይ በመመሥረት ነው። አይሁዳውያን በፊቱንም ቢሆን፣ አንድ እውነተኛና ሕያው አምላክ እንዳለ ያውቃሉ። ለአሕዛብ ግን በመጀመሪያ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነና ከሰማይ ዝናብን በማውረድ መብልን መስጠቱ የሱንም መኖር እንደሚያመለክት ሊነገራቸው ይገባል። ምንም እንኳ ሕዝቦች በየራሳቸው መንገድ ቢሄዱም፣ እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ ራሱን ለእነርሱ መግለጡን አልተወም።

ጥያቄ 11:- ሀ) ወንጌልን መስማት የሚያስፈልጋቸውን የተለያዩ ሕዝቦችን ጥቀስ። ለ) በባህላቸውና በአምልኮ ሥርዓታቸው ያላቸው ልዩነት ምንድነው? ይህን

ስንል ወንጌሉን ለእነዚህ ሕዝቦች የምናካፍለው በተለያየ መንገድ ነው ማለታችን ነው። ሐ) የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ፣ በአካባቢህ ያሉ ሰዎች ሊያውቁ የሚገባቸው ነገር ምንድነው?

## ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 14፡ 21-28

ወንጌሉን ለማሰራጨት ሲሉ፣ ጳውሎስና በርናባስ የከፈሉት ዋጋ ከፍተኛ ነበር። ጳውሎስ መልእክቱን ከመጨረሱ በፊት የልስጥራን ሰዎች ብድግ ብለው በድንጋይ ይወግሩታል። ጌታ ግን ነፍሱን ያተርፋታል። በሚቀጥለውም ቀን ጳውሎስና በርናባስ ወደ ደርቤን ይሄዳሉ።

በዚህ የመጀመሪያው ጉዞ ላይ ጳውሎስ የወደፊቱን ሥራ የሚሠራበትን ንድፍ አውጥቷል። የድንጋዩ ውርወራም ሆነ ዛቻው ጳውሎስን ሊያስፈራው አልቻለም። ዓላማው ቤተክርስቲያኖችን መመሥረት ሲሆን፣ ለዚህም የፈለገውን ዋጋ ይጠይቀው እንጂ፣ ለዓላማው እስከመጨረሻ ድረስ ይገፋበት ነበር። በሄደበት ቦታ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ፍሬ እየሰጠው ቤተክርስቲያኖች ይመሠረቱ ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 14፡ 21-28 አንብብና እነዚህን ጥያቄዎች መልስ። ጥያቄ 12 ሀ) ጳውሎስና በርናባስ በደርቤን ያደረጉት ነገር ምንድነው? ውጤቱስ ምን ነበር? ለ) ጳውሎስና በርናባስ ከደርቤን ተነሥተው የሄዱት ወዴት ነው? ሐ) አማኞቹ እንዲያተኩሩባቸው የነገሯቸው ሁለት ነገሮች ምንድናቸው? መ) ሲመለሱ በየከተማዎቹ የነበሩትን አብያተክርስቲያናት ያጸኗቸው እንዴት ነው? ሠ) ጳውሎስና በርናባስ ወደ ሶርያዋ አንጾኪያ የተመለሱት ለምንድነው?

ጳውሎስ በደርቤን ስለነበረው አገልግሎት የምናውቀው ጥቂት ነው። በደርቤን ስለተቃውሞ የተጠቀሰ ነገር የለም። ብዙ ደቀመዛሙርት እንደሆኑና፣ ጳውሎስና በርናባስ ደግሞ ቃሉን እንዳስተማሯቸው ነው የተጠቀሰው። ወደ በኋላም አካባቢ፣ በችግር ላይ ለነበረችው ለኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን የተሰበሰበውን መባ ከጳውሎስ ጋር ይዞ የሄደው ጋይዩስ የተባለው ታላቅ መሪ የተገኘው ከዚችው ከተማ ነው (ሐዋ. 20፡ 4 ተመልከት)። ደርቤን በገላትያ በስተምሥራቅ የምትገኝ ከተማ ነች። አንጾኪያ፣ ኢቆንዮን፣ ልስጥራንና ደርቤን የተባሉት ከተሞች በሙሉ በገላትያ ክፍለ ሀገር የሚገኙ ነበሩ።

ከደርቤን በመነሣትም፣ ጳውሎስና በርናባስ ከላይ በጠቀስናቸው ከተሞች በኩል ተመልሰው ያልፉሉ። የአሁኑ ጉብኝታቸው ብዙውን ያተኮረው ለጠፉት ሰዎች ወንጌልን መስበኩ ላይ ሳይሆን፣ አዳዲሶቹን አማኞች ማበረታታቱና ማፅናናቱ ላይ ነበር።

ጥያቄ 13:- ማቴዎስ 28፡ 19-20 አንብብ። በእነዚህ ጥቅሶች ላይ በመመሥረት፣ ሁለቱ ዋና ዋና የወንጌላዊ ሥራዎች ምንድናቸው? ጳውሎስ ይህን ታላቅ ተልእኮ የፈጸመው እንዴት ነው?

ጳውሎስ ያስብ የነበረው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ለሚሉ ሰዎች ብቻ አልነበረም። ታላቁ ተልእኮ ወንጌልን መስበክ ብቻ ያካተተ አይደለም፤ የመጨረሻ ግቡ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን የሚሉ ሰዎችን በሙሉ የኢየሱስን ትዕዛዞች ማስተማርና የእሱ ደቀመዛሙርት እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ጳውሎስ ያመኑትን ሰዎች ሁሉ በመጎብኘት፥ በማጽናናት፥ የእግዚአብሔርንም ትዕዛዝ በማስተማር ይጥር እንደነበር እናያለን። በጣም ያሳሰበው የነበረውም፥ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሕይወት መኖራቸው ነበር። ጳውሎስ የጻፋቸው መልእክቶችም በሙሉ፥ ክርስቲያኖች በክርስቶስ እንዲያድጉ የሚያጽናኑ ነበሩ (ቆላ. 1፡ 25)።

ጥያቄ 14፡- ሀ) ቤተክርስቲያንህ አዳዲስ ክርስቲያኖች በእምነታቸው አድገው እንዲጎለምሱ የምታደርገው እንዴት ነው? ለ) የአዳዲስ ክርስቲያኖች እምነት ያድግ ዘንድ፥ በተሻለ መንገድ ሊያስተምራቸው የሚችሉት እንዴት ነው?

ጳውሎስ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ዋጋ እንደሚያስከፍል አስተምሯቸዋል። የደህንነትና ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስደው መንገድ ቀላል መንገድ አይደለም። ብዙ ክርስቲያኖችም አንዴ ከዳንን ምንም ችግር አይኖርብንም፥ ባለፀጎች፥ ደስተኞች፥ የተሳካልን፥ ወዘተ ... እንሆናለን ብለው ያስተምራሉ። ነገር ግን፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ይህንን አይደለም። ጳውሎስም የገላትያን ክርስቲያኖች በግልጽ «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልጋል» እያለ ያስተምር ነበር (ሐዋ. 14፡ 22)።

ጥያቄ 15፡- አንዴ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን ምንም ዓይነት ችግር፥ በሽታ፥ አያጋጥመንም፤ ባለፀጎች ነው የምንሆነው ሲሉ የሰማሃቸውን ሰዎች ስም በዝርዝር ጻፍ። ለእነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል መልስ የምትሰጣቸው እንዴት ነው?

ጳውሎስ አማኞችን ሄዶ ማፅናናት ብቻ ሳይሆን፥ አብያተክርስቲያናትንም ያዋቅር ነበር። አማኞች ተገናኝተው ኅብረት ማድረጋቸው ብቻ በቂ አይደለም፤ በቤተክርስቲያን የታቀፉም መሆን አለባቸው። ጥሩ ቤተክርስቲያናት እንዲኖሩ መሪዎች መኖር አለባቸው። ስለዚህም፥ ጳውሎስና በርናባስ ይጎበኟቸው በነበሩት ከተሞች ውስጥ ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሾመዋል። ይህ ሽማግሌዎችን የመሾም ጉዳይ በጣም ትልቅ ጉዳይ ስለሆነ ጳውሎስ፥ በርናባስና ሌሎቹም ክርስቲያኖች ምርጫቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንዲሆን፥ ጊዜያቸውን በመጾምና በመጸለይ አሳልፈዋል።

ጥያቄ 16፡- ሀ) በቤተክርስቲያንህ ሽማግሌዎች እንዴት እንደሚመረጡ አብራራ። ሟሟላት ያለባቸውን ነገሮች ምንድናቸው? ለ) ብዙ ጊዜ የሚመረጡት በጣም መንፈሳዊ የሆኑት ናቸው? ካልሆነስ፥ ለመመረጥ ያበቋቸው ነገሮች ምንድናቸው? ሐ) ቤተክርስቲያንህ የመሪዎችን አመራረጥ በተመለከተ ሁኔታዎችን ማሻሻል የምትችለው እንዴት ነው?

ጥያቄ 17፡- ቤተክርስቲያን፥ አዳዲስ አማኞችን ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ የምታስተምርና የምታሰለጥን ይመስልሃል?

ጥያቄ 18፡- ብዙ አዳዲስ ክርስቲያኖች ቀጣይ ትምህርትና አበረታች ሁኔታዎች ካልተፈጠሩላቸው ምን ይሆናሉ?

ጳውሎስና በርናባስ መሪዎቹ በእምነት የጸኑና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ፥ ተመልሰው ወደ ሶርያዋ አንጾኪያ ይመለሳሉ።ሚድኻሹ እግረመንገዳቸውንም በጴርጌን ሰብከው ወደ ኢጣልያ ወረዱ፤ ከዚያም ተመልሰው በመርከብ ወደ አንጾኪያ መጡ። ሚድኻሹ

ጳውሎስ በኋላ ላይ ለገላትያ ሰዎች የጻፈው መልእክት በነዚህ የእስያ ከተሞች ለሚገኙት አማኞች ነበር። ጳውሎስና በርናባስ ወዲያውኑ እንደሄዱ ሌሎች የአይሁድ ክርስቲያኖች ይመጡና ሐሰተኛ ትምህርቶችን ማስተማር ይጀምራሉ። በትምህርታቸውም ጳውሎስ ሐዋርያ እንዳልሆነና ለመዳን ደግሞ መገረዝና የአይሁዶችን ሕግ መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ያስተምሩ ነበር። ጳውሎስ ከየመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞው በኋላ፥ ሁለተኛ ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ክርስቲያኖቹን በኃይለ ቃል በክርስቶስ ካገኙት ነፃነት ፈቅ እንዳይሉ በምትኩ ግን ይህን ነፃነታቸውን በፅናት እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃቸዋል።

ጥያቄ 19፡- አዳዲስ ክርስቲያኖችን መከታተልን በተመለከተ የጳውሎስ ምሳሌነት ሊያስተምረን የሚችለው ምንድነው?

ጥያቄ 20፡- ተቃውሞ፥ ችግር፥ በሽታና በድንጋይ መወገር በጳውሎስ የማያቋርጥ የወንጌል ማስፋፋት ሥራ ላይ የነበረው ተፅዕኖ ምንድነው?

ቀደም ብለን እንዳየነው ጳውሎስና በርናባስ በእግዚአብሔር ከተመረጡ በኋላ የሾንቻቸውና አባሎችዋም የነበሩት የአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን ነበረች። ስለዚህም ስለ ሥራቸው ተጠያቂ የሚሆኑት በዚችው ቤተክርስቲያን ነው። በዚህም መሠረት፥ ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ሲደርሱ የቤተክርስቲያኒቱን ምዕመናን ሁሉ ሰብስበው እግዚአብሔር የሠራውን ሥራ ሪፖርት አቀረቡ። ለአሕዛብም እግዚአብሔር እንዴት የሃይማኖት ደጅ እንደ ከፈተላቸው ተናገረዋል።

ጥያቄ 21፡- ሀ) ወንጌላውያን፥ ለምትከፍላቸውና ለምትልካቸው ቤተክርስቲያን፥ ሥራቸውን በተመለከተ ተጠያቂ መሆናቸው በጣም ዋነኛ ነገር የሆነው ለምንድነው? ለ) ቤተክርስቲያንህ ሽማግሌዎችን፥ ወንጌላውያንና መጋቢዎችን ስለሚሠሩት ሥራና ስለ አገልግሎታቸው አፈፃፀም ተጠያቂ የምታደርጋቸው እንዴት ነው?

ሪፖርታቸውን ካቀረቡ በኋላ፥ ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ደቀመዛሙርቱን ለአንድ ዓመት ያህል ሲያስተምሩ ቆዩ።

የመጀመሪያውን የጳውሎስና የበርናባስ ሚሲዮናዊ ጉዞ አይተናል። ምንም እንኳ ጉዞው በተቃውሞ የተሞላ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኖችን ለመመሥረቻ

ተጠቅሞበታል። የበርናባስ የትውልድ አገር ከነበረችው ከቆጵሮስ ጀምረው፥ የዛሬዋ ቱርክ ወደምትገኝበት ወደ ገላትያ ክፍለ ሀገር ያመራሉ። በጲስዲያ አንጾኪያ፥ በኢቆንዮን፥ በልስጥራንና በደርቤን ቤተክርስቲያናት ተመሥርተዋል። ይህም ሚሲዮናዊ ጉዞ የተደረገው ከ 40-48 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር።

ጥያቄ 22፡- እስቲ መለስ ብለህ ስለ ጳውሎስ የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ አስብና ወንጌሉን ለማስፋፋት ሲል ያደረጋቸውን የተለያዩ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ። እነዚህን ነገሮች ወንጌልን ለማስፋፋት ባላት ዓላማ ውስጥ ቤተክርስቲያንህ ልታካትተው የምትችለው እንዴት ነው።

ወደ ሌላ አገር ሄደው ምሥክር የሚሆኑ ክርስቲያኖች በሙሉ አይደሉም፤ ሆኖም አንተን እግዚአብሔር የጠራህ ለዚህ ከሆነ ጸልየህ በሚያስፈልጋቸው ነገር ልትደግፋቸው ትችላለህ። ሁላችንም ደግሞ ላላመኑት ጎረቤቶቻችንና ቤተሰቦቻችን ልንመሰክር እንችላለን።

## ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 15፡ 1-35

የመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞአቸው ጳውሎስና በርናባስን በቆጵሮስ ደሴት አድርገው እስያ ወደምትገኘው የገላትያ ክፍለ ሀገር እንዲደርሱ አድርጓቸዋል። እግረ መንገዳቸውንም፥ ቤተክርስቲያናትን መሥርተዋል። በዚህም መልክ ለሁለት ዓመት ያክል ካገለገሉ በኋላ፥ ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ትገኝ ወደ ነበረችው ወደ ላከቻቸው ቤተክርስቲያን ይመለሳሉ።

ከቆርኔሌዎስ መለወጥ በኋላ፥ ባለ መገረዝና የሙሴን ሕግ ባለመጠበቅ ለአሕዛብ ደኅንነት መኖሩ እውን ሆኗል። እራሷ የኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን በእውነት እግዚአብሔር አሕዛብን እንደሚፈውስ አምናለች (ሐዋ. 11፡18)። ሆኖም፥ በጳውሎስ ጉዞ ላይ ብዙ አሕዛብ በቤተክርስቲያን ውስጥ ተጨምረዋል፤ ከኢየሩሳሌም ውጪ ያሉት ቤተክርስቲያኖች ውስጥ ብዙዎቹ አሕዛብ ነበሩ። ታዲያ ጳውሎስና በርናባስ ገና ወደ አንጾኪያ ከመመለሳቸው፥ ሐሰተኛ የአይሁድ መምህራን በየአብያተ ክርስቲያናቱ በመዘዋወር ብጥብጥ በመፍጠርና እውነተኛ አማኞች ትሆኑ ዘንድ መገረዝ አለባችሁ በማለት ያስተምሩ ነበር። በሌላ አነጋገር፥ አሕዛቦቹን ያስተምሩ የነበረ፥ በእግዚአብሔር ዓይን ተቀባይነትን ታገኙ ዘንድ መጀመሪያ ታሪክ ውስጥ፥ መመሪያ የሆኑ ትምህርቶች ላይ ግጭት ከተፈጠረ፥ እውነተኛውን ነገር ለመወሰን ሁልጊዜ ቤተክርስቲያን ሸንጎ ትሰበስብ ነበር። ዛሬ የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ሸንጎ የሆነውን የኢየሩሳሌምን ሸንጎ እናያለን። ጉዳዩ የአሕዛብን ደኅንነት በተመለከተ ነበር። አሕዛብ ሳይገረዙና የሙሴን ሕግ ሳይጠብቁ እውነተኛ አማኞች ሊሆኑ ይችላሉን? ከዚህም የበለጠ ዋነኛ የሆነ ጉዳይ እያንሠራራ ነበረ፤ እሱም «አንድ ሰው ለመዳን ምን ማድረግ አለበት?» የሚል ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን ሌላ፥ መጠበቅ የነበረባቸው ውጫዊ የሆኑ ግዴታዎች ነበሩን? ይህን ዓይነቱ ሁኔታ በማንሠራራቱ ውሳኔ ሊሰጠው ተገቢ ነበር። ታዲያ ውሳኔው አሕዛብ ለመዳን አይሁዳዊ መሆን አለባቸው፤ ከእምነታቸው በላይ ማሟላት የሚገባቸው ውጫዊ የሆኑ ነገሮች አሉ

የሚል ቢሆን ኖሮ፣ ክርስትና ከአይሁድ ሃይማኖት አንዱ ክፍል ይሆን ነበር፣ ወደ አሕዛብ ዓለም አይስፋፋም ነበር። ቤተክርስቲያንን ለውጦ እያንዳንዱ ቤተርክስቲያን ጥሩ ኅብረት እንዲኖረው የሚያደርግ ውሳኔ መደረግ ነበረበት።

ጥያቄ 23፡- ሀ) ይህንን ሐሳብ የቤተክርስቲያን መሪዎች መወሰናቸው አስፈላጊነቱ ለምንድነው? ለ) በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ዕልባት ያገኙ ዘንድ የቤተክርስቲያኒቱን ሽንነ የሚያሰባስቡ አንዳንድ ጉዳዮች ምንድናቸው?

የሐዋርያት ሥራ 15፡ 1-35 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 24፡- ሀ) ወደ አንጾኪያ መጥተው የነበሩት ሰዎች እነማን ናቸው? የሚያስተምሩትስ ትምህርት ምን ነበር? ትምህርታቸውንስ የተቃወመው ማነው? ለ) ጳውሎስና በርናባስ ወዴት እንዲሄዱ ነው የተመረጡት? በሰማሪያና በፊንቂ ሲያልፉ እየተረኩ ያለፉት ነገር ምንድነው? ሐ) በኢየሩሳሌም ይገኙ የነበሩት አንዳንድ አማኞች ምን እያደረጉ ነበር? መ) ሐዋርያቱና ሽማግሌዎቹ ክርክሩን የፈቱት እንዴት ነው? ደኅንነት በፀጋ በክርስቶስ የሚገኝ ነው የሚለውን ሐሳብ ደግፎ ያቀረበው ማነው? መከላከያውን አጠር አድርጎ ያስቀመጠውስ ማነው? ሠ) የሐዋርያቱና የሽማግሌዎቹ ሽንነ ምን ወሰነ? ረ) የሽንነውን ውሳኔ ወደ አንጾኪያ ይዘው እንዲሄዱ የተመረጡት እነማን ናቸው?

በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ ይህ የአሕዛብ መገረዝና የብሉይ ኪዳንን ሕግ የመጠበቅ ነገር፣ በአይሁዳውያን አማኞች ብዙ ግጭቶችን ፈጥሯል። አንድ የአሕዛብ ወገን የሆነ ክርስቲያን እንዲድን ከፈለገ መገረዝና የሙሴን ሕግ መጠበቅ አለበት ብለው በብርቱ የሚያስቡ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ነበሩ። በዚህም ምክንያት ከይሁዳ ተነሥተው ወደ አንጾኪያ፣ ብለውም እስከ ገላትያ ቤተክርስቲያኖች ድረስ በመሄድ አማኞች የሆኑትን የአሕዛብ ወገኖች ካልተገረዛችሁ መዳን የለም ብለው ያስተምሩ ነበር።

ይህም በየአብያተ ክርስቲያናቱ ትልቅ ግጭት ፈጥሯል። በአንጾኪያም፣ ብዙ የተለወጡ አሕዛብን ያዩ ጳውሎስና በርናባስ በእነዚህ አይሁዳውያን መምህራን ጋር የጦፈ ክርክር ይዘው ነበር። ቤተክርስቲያኒቱም በሁለት የመከፈል አደገኛ አዝማሚያ ደርሶባት ነበር። ይኸውም በአንድ በኩል አይሁዳውያን በሌላው በኩል ደግሞ አሕዛብ በመሆን ተለያይተው ነበር። ችግሩም በጣም አሳሳቢ ስለነበር፣ የአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን ጳውሎስን፣ በርናባስንና ሌሎች ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም በመላክ ነገሩን ከቤተክርስቲያኑ መሪዎች ጋር እንዲወያዩ አደረገች። ምናልባትም ጳውሎስ፣ አሕዛብ መገረዝ እንደሌለባቸው ማስረጃ እንዲሆነው ቲቶን የወሰደው በዚህ ጉዞው ላይ ሳይሆን አይቀርም (ገላ 2፡ 1-5 ተመልከት)።

ጳውሎስና በርናባስ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ በሌላ ሥፍራ ያሉትን ክርስቲያኖች በሙሉ እንደሚነካ ተገንዝበዋል። በመጀመሪያ ደግሞ ነገሩ

የተነሣው ከኢየሩሳሌም በመጡ ሰዎች ስለሆነ ሁለቱ ቤተክርስቲያኖች ችግሩን እንዲነጋገሩበት ማድረጉ ተገቢ ነው።

የአንጾኪያው ልዑካን ቡድን ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ሳለ፥ ጳውሎስና በርናባስ እግረ መንገዳቸውን ላገኟቸው ክርስቲያኖች የአሕዛብን መመለስ ይተርኩ ነበር። የፊንቄ ከተማ፥ በሶርያና በሰማርያ በስተደቡብ የምትገኝ ስትሆን፥ ወንጌል የተስፋፋበትም ወደ አንጾኪያ በገባበት ሰሞን ነበር። ከዚያ የነበሩትም ክርስቲያኖች አሕዛቦች ሳይገረዙ መለወጣቸውን ሲሰሙ፥ በጣም ደስ ተሰኙ። እነሱ እራሳቸው ከአይሁዳውያኑ ጋር በእኩል ዓይን ስለማይታዩና እንደ አሕዛብ ስለሚቆጠሩ፥ ይህ የመገረዝ ገዲታ እነሱን የሚመለከት ዋና ነገር ነበር።

ጥያቄ 25:- ከአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን የቤተክርስቲያን ግጭቶችን መፍታት በተመለከተ፥ ልንማር የምንችለው ነገር ምንድነው?

ኢየሩሳሌም ሲደርሱ፥ ጳውሎስን፥ በርናባስና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች የቤተክርስቲያኗ መሪዎች (ሐዋርያትና የኢየሱስ ወንድም የነበረው ያዕቆብ) ተቀበሏቸው። እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር እያወሩላቸው ሳለም፥ ክርክር ተነሣ። ፈሪሣዊ የነበሩት ክርስቲያኖች ተነሥተው ጳውሎስን፥ አሕዛብ ይገረዙና የሙሴን ሕግ ይጠብቁ ዘንድ ይገባል አሉት። እንደምታስታውሰውም ከአይሁድ ወገኖች ውስጥ በጣም ወግ አጥባቂ የነበሩት ፈሪሣውያን ናቸው። የብሉይ ኪዳኑን ሕግ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፥ ሕጉ በደንብ መጠበቁን የሚያረጋግጡበትን የራሳቸውን ሕግጋት ጭምር ይጨምሩበት ነበር። እነዚህ፥ ኢየሱስ መሢሕ ነው ብለው ያመኑ ክርስቲያኖች፥ ለመዳን የግድ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት መጠበቅ አለባቸው ብለው ያምኑ ነበር። በእነዚህ ሰዎችና በጳውሎስ በተመራው ልዑካን መካከል የተነሣውም ክርክር በጣም የተጧጧፈ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ምናልባትም፥ በአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ትክክል አይደለም ብለው ያዩትን ነገር ለማረም ሲሉ፥ ወኪሎቻቸውን የላኩት እነዚህ ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም።

እነዚህ ሰዎች አሕዛብ ማሟላት ያለባቸው ነገር፥ የመገረዝ ሥርዓትን ብቻ ነው አላሉም። ቢሆንም ግን፥ ዋነኛው ይህ ነበር። አንድ ሰው፥ አሕዛብ ይድኑ ዘንድ የሙሴን ሕግ መጠበቅ አለባቸው የሚል ከሆነ፥ ይህ አስተሳሰብ ሁሉንም የሕግጋቱን ክፍሎች የሚወክል ነው። የአይሁዳውያኑን አቤቱታ ካዳመጡ በኋላም፥ ሐዋርያቱና ሽማግሌዎቹ በጥያቄው ላይ ለመመካከር ይሰበሰባሉ (ሐዋ. 15: 6)። ከብዙ ክርክርም በኋላ፥ ወደ ተሰበሰበው ጉባዔ የሚመለሱ ይመስላል። ይህ በኢየሩሳሌም የተሰበሰበው ጉባዔ የኢየሩሳሌም መሪዎችን፤ እንደ ፈሪሣውያን ያሉ ቡድኖችን የሚወክሉ ተወካዮችን ጳውሎስንና በርናባስን ያሰባሰበ ሳይሆን አይቀርም፤ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚሠራውን ሥራ በተመለከተም በዚህ ጉባዔ ላይ ግልጽ ውይይት ተደርጓል።

በመጀመሪያ ጴጥሮስ ተነሥቶ የቆርኔሌዎችን ታሪክ ያስታውሳቸዋል። ወንጌልን እየሰሙ ሳለ፥ ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ ባይገረዙም፥ እሱና ሌሎቹ አሕዛብ ካመኑ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። በቆርኔሌዎስ ቤት ውስጥ፥ ጌታ በአይሁድና በአሕዛብ

መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት አላደረገም። ሁለቱም፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ልባቸው ንጹሕ ሆኗል። እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነታቸው ምክንያት ከተቀበላቸው ዘንዳ በእነሱ ላይ ሌሎች ጫናዎችን መጫኑ ትክክል አልነበረም።

ከዚህም በመቀጠል፥ ጴጥሮስ አይሁዳውያን የሙሴን ሕግ ለመጠበቅ ያላቸውን ብቃት ይመለከታል። በአይሁዳውያን ታሪክ ውስጥ እንደምናየው፥ ዕድሜ ልካቸውን ሕጉን ሳይጠብቁ ነው የኖሩት። ሕጉ እንደቀንበር ጫና ሆኖባቸዋል! ይህም የሆነው ትዕዛዙን ሊጠብቁ የሚችሉበት ችሎታ ስለሌላቸው ነው። ሆኖም፥ የሕጉ ዓላማ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር ፊቱን ዞር አድርጎ በእርሱ እንዲያምን ማድረግ ነው እንጂ፥ ሕጉን በመጠበቅ የራሳቸውን ደኅንነት ጥረው ግረው እንዲያገኙ አይደለም።

ጴጥሮስም የወንጌሉ ዋነኛ ሐሳብ የሆነውን በመጥቀስ ንግግሩን ያገባድዳል። ወንጌሉ፥ ሥራ መሥራትን እንደ አንገብጋቢ ነገር አያየውም። አንድ ሰው ለመዳን ሲልም ማድረግ ወይም መጠበቅ ያለበት ምንም መመሪያ የለም። ነገር ግን እሱ እንዳለውም «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ እንደ እነርሱ እንደምንድን እናምናለን» (ሐዋ. 15፡ 11)።

ጥያቄ 26፡- ሀ) ሰዎች የተወሰኑ ሕግጋትን በመጠበቅ ሊድኑ ይችላሉ ብለው የሚቀበሉ የአንዳንድ ሃይማኖቶችን ስም ዝርዝር ጻፍ። ለ) አዳዲስ ክርስቲያኖችን ጥሩ ክርስቲያኖች ለማድረግ ሲሉ፥ የተወሰኑ ሕግጋትን እንዲጠብቁ የሚያደርጉ አንዳንድ ቤተክርስቲያናትን በዝርዝር ግለጽ። ሐ) የጴጥሮስ ንግግር፥ ደኅንነት ያለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው ከሚለው እውነታ ላይ ሌላ ሕግ እንዳይጨመር የሚያስጠነቅቀው እንዴት ነው?

ጴጥሮስ ከጨረሰ በኋላ፥ ጳውሎስና በርናባስ ወንጌሉ በአሕዛብ መካከል እንዴት እንደተስፋፉ ተረኩ። አስተውል፥ በዚህም ሥፍራ ላይ በርናባስ ከጳውሎስ በፊት ነው የሚጠቀሰው። ይህም የሆነው ድሮ ከአይሁዳውያን ጋር ሆኖ ጳውሎስ ሳይሆን በርናባስ መሪና ቃል አቀባይ ስለነበረ ነው። በርናባስና ጳውሎስ አሕዛብ የብሉይ ኪዳኑን ሕግ መጠበቅ እንደማይገባቸው የሚገልጽ ማስረጃ ያቀረቡት እንዴት ነው? ምንም እንኳ ባይገረዙም፥ መንፈስ ቅዱስ ኃይሉን በአሕዛብ መካከል እንደገለጠ አመልክተዋል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም አሕዛብን ተቀብሎ በእነርሱ በኩል እስከሠራ ድረስ! ሌሎች አማኞች አሕዛብ የአይሁድን ልማዶች በግድ መጠበቅ አለባቸው ማለት አይገባቸውም።

በመጨረሻም፥ የኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን መሪና ከወግ አጥባቂዎች አይሁዳውያን ዘንድ ትልቅ ከበሬታ ይሰጠው የነበረው የኢየሱስ ወንድም ያዕቆብ፥ የማጠቃለያ ንግግሩን ያደርጋል። እግዚአብሔር በጴጥሮስ ተጠቅሞ እንዴት ቆርኔሌዎስ በቤተክርስቲያን ተቀባይነት እንዲያገኝ እንዳደረገ ይገልጻል። የጥንት እስራኤላውያንን «ሕዝቦች» ብሎ እንደጠራቸው ሁሉ፥ እግዚአብሔር ለራሱ የሚሆኑ ሕዝቦችን ከአሕዛብ ወገን እያሰባሰበ ነው። ያዕቆብ ትንቢተ አሞፅ 9፡ 11-12ን በመጥቀስ፥ ይህ ጉዳይ ከብሉይ ኪዳን ጋር የሚስማማ መሆኑንም ይገልጻል። አሞፅ ከ 760-750 ዓክልበ ባለው ጊዜ ለእስራኤል ሲተነብይ እንደገና በመጨረሻው ዘመን ላይ

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የሚጎበኝበትን ጊዜ አሻግሮ ያያል። እግዚአብሔር የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን እንደገና እሠራታለሁ ብሎ ቃል ይገባል፤ ይህም፥ የዳዊትን ንጉሣዊ ሐረግ ማለት ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔር ከአይሁዳውያን የተረፉትን ቅሬታዎች እሱን እንዲያመልኩ ወደ ራሱ ይመልሳቸዋል። ሆኖም፥ አሕዛብም ቢሆኑ ስሙን ያስጠሩ ዘንድ እግዚአብሔር በእነርሱም መካከል ይሠራል። ያዕቆብ፥ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት፥ የአሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን የትንቢት ፍጻሜ መጀመሪያ መሆኑን ተገንዝቧል።

በመቀጠልም ያዕቆብ አንዳንድ ምክሮችን ይለግሳል። አንደኛ በክርስቶስ ኢየሱስ ለማመን በሚሹት አሕዛብ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ይነግራቸዋል። ይህንን ሲል፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን ሲባል አስፈላጊ የሆኑ መሰናክሎችን የሚፈጥሩ ግዴታዎችን መጨመሩ ትክክል አይደለም ማለቱ ነው። አሕዛብ ለመዳን ሲሉ፥ መገረዝን፥ አይሁዳውያን ለመሆንም የአይሁድን ሕግጋት መከተል የለባቸውም።

ሆኖም፥ ያዕቆብ አሕዛብ ሦስት ዋና ዋና መመሪያዎችን ይጠብቁ ዘንድ ሊጠየቁ ይገባል፤ እነዚህም:- 1) ለጣዖታት የተሠዋን ሥጋ ከመብላት መቆጠብ አለባቸው። 2) የሕሊና ንጽሕናቸውን በመጠበቅ ከዝሙት መራቅ አለባቸው። 3) ደም ያለበትን፥ ታንቆ የሞተን እንስሳ ሥጋ መብላት የለባቸውም የሚሉ ናቸው።

አሕዛብ እነዚህን መመሪያዎች ይከተሉ ዘንድ ያዕቆብ የሰጠውን ምክንያት አስተውል። ይህ እንዲህ የሆነው፥ በሮማው ዘመነ መንግሥት ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን ያደጉት እነዚህን የሙሴ ሕግጋት በመጠበቅ በመሆኑ ያለነዚህ ሕጎች አይሁዳውያንና አሕዛብ በአንድ ቤተክርስቲያን ተሰብስበው ያምልኩ ወይም ኅብረት ያድርጉ ማለቱ በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ጠንቅቀው ከማጥናታቸው የተነሣ፥ በዚህ ሥፍራ ሁለት ዓይነት ትዕዛዞች ተሰጥተው እናያለን። አንደኛ እግዚአብሔር በሁሉም ዘመናት ያሉ ሕዝቦች እንዲጠብቋቸው የሚፈልጋቸው ዓለም አቀፍ የሆኑ ትዕዛዛት አሉ። የዝሙት ትዕዛዝ ለእነዚህ አንድ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ሴተኛ አዳሪነትን በዚያን ጊዜ በነበሩት አሕዛብ ዘንድ እንደ ሃይማኖት ክብር ተሰጥቶት በስፋት ይለመድ የነበረ ነገር ነው። ሆኖም፥ እግዚአብሔር ሕዝቦቹ ከዝሙት የፀዱ እንዲሆኑ ይፈልጋል። በብሉይም በአዲስም ኪዳን ውስጥ፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከዝሙት የፀዱ እንዲሆኑ ታዞዋል።

ጥያቄ 27:- በሁሉም ዘመናት በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ ተፈጻሚነት ያላቸውን በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ትዕዛዛትን በዝርዝር ጻፍ።

ነገር ግን፥ አንድ ቤተክርስቲያን አባላቶችዋ እንዲጠብቋቸው የምትደነግጋቸው የጊዜያዊነት መልክ ያላቸው ትዕዛዛት አሉ። እነዚህ ትዕዛዛት የሚወጡበት ሁለት ምክንያቶች አሉ። አንደኛ፥ ባልዳኑ ሰዎች መካከል የአንድን ምስክርነት ለመጠበቅ ሲባል የሚሰጡ ትዕዛዛት አሉ። እነዚህ ትዕዛዛት በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፉ ሳይሆኑ፥ ብዙውን ጊዜ የሚወሰኑት አንድ ከሚኖርበት አካባቢ ባህል ጋር በተዛመደ ሁኔታ ነው።

ጥያቄ 28፡- ቤተክርስቲያንህ አባላቷን እንዲጠብቁ የምታዛቸውን እንዲህ ዓይነቶቹን ትዕዛዛት እስቲ በዝርዝር ጻፍ።

ሁለተኛ ደግሞ፥ ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎች በበለጠ በሰላምና በፍቅር እንዲኖሩ ሲባል የሚደነገጉ ጊዜያዊ ሕግጋት አሉ። ለጣዖት የተሰዋውን ሥጋ በተመለከተ የወጡት ሕግጋትም ዓላማ ይህ ነው። ለጣዖት የተሠዋን ሥጋ ለማይበሉ አይሁዳውያን ደግሞ፥ ይህ ልማድ በጣም ትልቅ ቅሬታ ይፈጥርባቸዋል። ይህንን እነሱ፥ ከጣዖት አምልኮ ጋር እንደመተባበር ነው የሚቆጥሩት። ስለዚህም፥ አሕዛብ ክርስቲያኖች አይሁዶች የሚያምኗቸውን ነገሮች ማክበር አለባቸው። ወደ በኋላ ላይም ጳውሎስ በብዛት አሕዛብ ለነበሩት ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ ውስጥ ሌሎች መመሪያዎችን በመስጠት ይህን ሕግ ችላ ያለው ይመስላል። ለጣዖት የተሠዋን ሥጋ በተመለከተ፥ ጳውሎስ የሰጠውን ምክር የያዘውን 1ኛ ቆሮ. 8 ተመልከት።

ጥያቄ 29፡- ቤተክርስቲያንህ አባላቷን እንዲጠብቁ የምታዛቸውን እንዲህ ዓይነቶቹን ትዕዛዛት እስቲ በዝርዝር ጻፍ።

እነዚህን የተለያዩ ሕግጋት ማወቁና በየትኛው ምድብ እንደሚመደቡ መረዳቱ አስፈላጊ ነው። ሆኖም፥ እነዚህ የመጨረሻዎቹ ሕግጋት ለሁሉም ክርስቲያኖች ሊጠብቋቸው ይገባል ብሎ ማሰቡም በጣም የተሳሳተ ነው። ይህ በሥራ ላይ ወደተመሠረተ ሃይማኖት ሊያመራን ይችላል። ስለዚህም ሁለቱ የመጨረሻዎቹ ሕግጋት የሚጠብቁት፥ በማያምኑ ዘንድ የአንድን ሰው ምስክርነት በአማኞች መካከል ያለውን ኅብረት ለመጠበቅ ሲባል ነው። እነዚህም ሕግጋት የፍቅር ሕግ ነፀብራቆች ናቸው። ጊዜና ባህል በተለወጡ ቁጥርም፥ እነዚህ ሕግጋት ሊሻሩና ሊለወጡ ይችላሉ።

የያዕቆብ ምክር ከሌሎች መሪዎች ዘንድ በጠቅላላ ጉባዔው ተቀባይነት አግኝቷል። የጉባዔውን ውሳኔ በተመለከትም፥ አንድ መልእክት ለመጻፍ ፈለጉ። ይህም መልእክት በግልባጭ እየዞረ በአሕዛብ ምድር በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሚነበብ ነበር። ይህንንም ውሳኔ በይፋ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ ለመስጠት ሲባል ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የተከበሩ ሰዎች ከመልእክቱ ጋር አብረው ተልከዋል። ተወካዮቹም፥ አንደኛው ይሁዳ ሌላኛው ደግሞ ሲላስ ይባሉ ነበር። ሁለቱም በኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን ውስጥ መሪዎች የነበሩና ነቢያትም የነበሩ ናቸው። በኋላ ላይም በሁለተኛውና በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ላይ ሲላስ ከጳውሎስ ጋር ተጉዟል። ከዚያም የመከሩበትን ነገር ለአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን ሲሰጧት፥ በታላቅ ደስታ ተቀበለችው።

ጥያቄ 30፡- ነገሩን ለአንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ማሳወቅ ጥሩ የነበረው ለምንድነው?

ነቢያት የነበሩት ይሁዳና ሲላስ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ከመመለሳቸው በፊት፥ የአንጾኪያ አማኞችን መክረው አፀኑአቸው። ጳውሎስና በርናባስ ደግሞ በዚያው በአንጾኪያ ማስተማራቸውንና መስበካቸውን ቀጠሉ።

ጥያቄ 31፡- አንተ በግልህ ላደርጋቸው አይገቡኝም ብለህ የምትጠየፋቸው ግን ለአንድ ክርስቲያን እንደ ስሕተት የማይቆጠሩ፥ አንድ ወይም ሁለት ልማዶችን ጥቀስ።

ይህም ሆኖ፥ በጥንቷ ቤተክርስቲያን ይህ ሐሳብ እንዲህ በቶሎ ዕልባት አግኝቶ ክስም ብሎ አልጠፋም። በጳውሎስ አገልግሎት ጊዜ ከመጀመሪያ አንሥቶ እስከ መጨረሻ ድረስ አይሁዳውያን በአሕዛብ ላይ የብሉይ ኪዳንን ሕግ ሊጨምሩባቸው ይፈልጉ ነበር። ይህም ነገር፥ ጳውሎስ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ በጻፈው መልእክት ውስጥ ጎልቶ ሲንፀባረቅ እናያለን። እንዲያውም፥ ከዚህ ጊዜ በኋላ፥ እራሱ ጴጥሮስ በዚህ ወጥመድ ውስጥ ወድቆ ነበር። በገላትያ መልእክቱ ላይ፥ ጳውሎስ ለጴጥሮስ ሕጉ ያለውን ሥፍራ ሲያመለክተውና ለመዳንም እግዚአብሔር የሚጠይቀው እምነትን ብቻ እንጂ ሕግንም አብሮ መጠበቅ እንዳልሆነ የገለጸለትን ጊዜ ይጠቅሳል (ገላ 2፡ 11-16 ተመልከት)።

ይህ ጉዳይ የጥንቷን ቤተክርስቲያን እንዲህ እንዳስቸገራት ሁሉ፥ በየዘመናቱ ሁሉ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ይታይ የነበረውም ይኸው ችግር ነበር። ለመዳን ወይም ቅዱሳን ለመምሰል ከፈለጉ፥ ሰዎች ሊጠብቋቸው ይገባል በማለት፥ ሰይጣን የሚያደርገው ነገር ቢኖር፡- ወንጌልን በሕጎች ድርደራ በክሎ ማቅረብ ነው። አንድ ሰው ሕግን ከጥሩ መንፈስ ተነሥቶ ይጠብቀው እንደሆን ወይም ወንጌልን ለመቃወም ለማደናቀፍ ሲባል እንደሆነ ማወቁ ትልቅ ጥበብን የሚጠይቅ ነው። ይህ ነገር ከሚኖሩበት ቦታ ወጥተው በሌላ ባህል ውስጥ ገብተው የሚሠሩ ወንጌላውያን ላይ በደንብ ይታያል። የአንድ ወገን ባህላዊ እምነትን በወንጌሉ ላይ ጨማምሮ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመናቸው በፊት አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርጉ መጠየቁ በጣም ቀላል ነገር ነው። አንዳንዶችማ ዘላን የሆኑ ሰዎች ክርስቲያን ለመሆን ከፈለጉ ልብሳቸውን አውልቀው ዘመናዊ ልብስ መልበስ ይኖርባቸዋል እስከ ማለት ደርሰዋል። እንግዲህ እነዚህ ሰዎች ልክ እንደ ጥንቶቹ አይሁዳውያን፥ ሰዎች ክርስቶስን በማመን ብቻ ሳይሆን ሕግንም በመጠበቅ ክርስቲያን እንዲሆኑ በማለት በወንጌሉ ላይ ሌላ ሌላ ነገር ጨማምረዋል። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው ብለው፥ ባህላቸውን እያስለወጧቸው ነው።

ጥያቄ 32፡- ከዚህ ምዕራፍ ላይ፥ ወንጌላውያንን በጥንቃቄ ስለ ማሠልጠን ምን ልንማር እንችላለን?

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 15፡ 36-41

የኢየሩሳሌሙ ጉባዔ  ውሳኔ አሕዛብ ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ሕጎች እንዳይወስኑባቸው፥ ነገር ግን ያለምንም ችግር ወደ ቤተክርስቲያን እንዲገቡ መንገዱን ከፍቷል። ለመዳን ሲሉ፥ አይሁዳዊ መሆን የለባቸውም። ይህ ውሳኔ፥ በአይሁዳውያንና በአሕዛብ ዘንድ የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖርና፥ ወንጌሉ ያለምንም እንቅፋት በአሕዛብ ዘንድ እንዲስፋፋ አድርጓል። እንዲያውም፥ ከጥቂት ዓመታት በኋላ፥ የክርስትና

መሠረት የሚገኝበት ቦታ ከኢየሩሳሌም ወደ ሮም፥ ከአይሁዳውያን ወደ አሕዛብ ባሉበት ሥፍራ ተለውጧል።

ጳውሎስ፥ የጌታን ቃል ወደ አሕዛቡ ዓለም መውሰዱን አልዘነጋም ነበር። ለተወሰነ ያህል ጊዜም በአንጾኪያ ካስተማረ በኋላ፥ በአዳዲስ ሥፍራዎች ወንጌሉን ይዞ መሄድ እንዳለበት ይሰማዋል። ነገር ግን፥ ወዲያውኑ ያልታሰበ ችግር ውስጥ ይወድቃል። ከቤተክርስቲያን ሥራ ውስጥ አንዱ ችግር፥ በአገልጋዮች መካከል የሚፈጠረው አለመግባባት ነው። በዚህም መሠረት በጳውሎስና በበርናባስ መካከል ችግር ይፈጠራል።

ጥያቄ 33፡- ቤተክርስቲያን ውስጥ በአገልጋዮች መካከል የተነሣው ችግር፥ ለእግዚአብሔር እንዴት እንቅፋት እንደሆነ የሚገልጽ ሁኔታን ሰፋ አድርገህ አብራራ።

የሐዋርያት ሥራ 15፡ 36-41 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 34፡- ሀ) ጳውሎስ ሐሳብ ያቀረበው፥ እሱና በርናባስ ወዴት እንዲሄዱ ነው? ለመሄድ የፈለገው ለምንድነው? ለ) ያልተግባቡበት ነገር ምንድነው? ውጤቱስ ምን ሆነ? ሐ) ከጳውሎስ ጋር አብሮ የሚሄደው ማን ሆነ? ወዴትስ ነው የሄዱት? መ) ከዚህ በፊት ስለ ሲላስ የሰማነው የት ሥፍራ ነው? (ሐዋ. 15፡ 22፤ 27 ተመልከት)።

አንድ ቀን ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ እያስተማሩ ሳለ፥ ጳውሎስ በርናባስን «ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንበት በየከተማው ሁሉ ወንድሞችን እንጎብኛቸው፤ እንዴት እንዳሉም እንወቅ» ይለዋል። ጳውሎስ በእምነት ወደ ክርስቶስ የመራቸውን ሰዎች አልረሳቸውም፤ በተጨማሪም በመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞው ላይ የመሠረታቸውን ቤተክርስቲያናት እንደገና ሊጎበኛቸው ይፈልግ ነበር።

በርናባስ በነገሩ ተስማማ፤ ዘመዱንም ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስን ለመውሰድ ፈለገ። ጳውሎስ ግን በመጀመሪያው ጉዞአቸው ላይ በጵንፍልያ ትቶአቸው ስለሄደ፥ ዮሐንስ ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ አልፈለገም። መጽሐፍ ቅዱስ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ለምን እንደሄደ ባይነግረንም፥ ጳውሎስና በርናባስን ተለይቶ የሄደው ያለ እነርሱ ፈቃድ ይመስላል። ስለዚህም ይመስላል፤ ጳውሎስ በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ ላይ ከኛ ጋር ለመጓዝ ብቁ አይደለም ብሎ በማሰብ ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስን እንዳይሄድ ይከለክለዋል።

ደግና የተከበረ ሰው የነበረው በርናባስ፥ ከእነርሱ ጋር አብሮ እንዲሄድ ሌላ ዕድል ሊሰጠው ይገባል ብሎ ያምን ነበር። ለሥራው ቀናተኛ የነበረው ጳውሎስ ደግሞ፥ ማርቆስ ለአገልግሎቱ እንቅፋት ይሆናል ብሎ አሰበ። በርናባስ ግለሰቦችን የመርዳትና የማጽናናት ስጦታ ሲኖረው፥ ጳውሎስ ደግሞ መታገሥ የማይችል ነበር።

እግዚአብሔር በሁለቱም ባህሪዎች ይጠቀማል። ከዚህ በፊት፥ በርናባስ በነበረው የማጽናናት ስጦታ፥ እንዴት ቤተክርስቲያንን እንደረዳት አይተናል። እራሱ ጳውሎስ እንኳ፥ ከሐዋርያት ጋር የተዋወቀውና የማስተማር አገልግሎቱን በአንጾኪያ የጀመረው

በበርናባስ በኩል ነው። ሆኖም፥ ጳውሎስ በ ጣም ኮስታራ ሰው ነበር። ይህ ባህሪው፥ ወንጌሉን ተሰምቶባቸው ወደማይታወቁ ኦ ካባቢዎች ይዞ እንዲሄድ ት ልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ብዙ ጊ ቴም በአ ማኞች መ ካከል ግጭትን የሚፈጥረው፥ የተለያየ ባህሪያቸው ነው።

ጥያቄ 35፡- ሀ) በክርስቲያኖች መካከል ለውን ግጭት እንዴት ታየዋለህ? ወይም አልፈህበት ከሆነ እንዴት ነ ር? ለ) የሌላኛውን ሰው ሐሳብ በመቀበል ግጭቶች ሊረግቡ ይችላሉ?

ጳውሎስና በርናባስ በመካከላቸው የከረ ፡ አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። ያ ናልባትም በምዕመናኑ ዘንድ ኃዘንን ነይፈጥር አይቀ ም። ታዲያ ይህም ሁሉ ሆኖ በመጨረሻ ላይ፥ በርናባስ ማርቆስ የ ባለውን ዮ ሐን ን ወደ ቆጵሮስ ይዞት ይ ሄዳል ፡ ጳውሎስ ደግሞ ሲላስን ይመርጥና ወደ ኪልቅያ በመ ሄድ፥ በእስያ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ዳግመኛ ይጎበኛል። (የጳውሎስን ሁለተ ኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ የሚያሳየ ን ካርታ ተመልከት)።

የእግዚአብሔር ሥራ በሕዝቦቹ አለመ ስማማት ወይም ድክመቱ አይ ናቀፍም። አለመስማማቶቹን እንኳ ለውጦ ለክብሩ ሊጠቀምባቸው ይችላል። ጳውሎስና በበርናባስ መካከል የተ ፈጠረው አለመግባ ት፥ ከአንድ ወንጌላዊ ቡድን ይ ልቅ ሁለት ቡድኖች እንዲሄዱ አድርጓል። በዚህ ዞ ላይ በበርናባስና በማርቆስ ላይ ምን እንደደረሰባቸው አናውቅም፥ ይህ የ ነው ሉቃስ የጳውሎስና ሲላ ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ ላይ ትኩረት በማድረጉ ነ ።

ቤተ ክርስቲያን የጳውሎስን አዲስ ገ ዞ ደግፋለች፥ ጳውሎስና ሲላ ም ሲሄዱ ድጋፍ ሰጥታ፥ ጸልያ ው ላከቻቸው። ስ በርናባስና ማርቆስ ጉዞ ግ የተ ከቀሰ ነገር የለም፥ ታዲያ ይህን ስንል ቤተክርስቲያ ን በእነርሱ ጉዞ አልተስ ማማ ም ማለት አይደለም። ስለ በርናባስም ይሁን ማርቆ ስ ስለተባለው ዮሐንስ በሐዋ ያት ሥራ መጽሐፍ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ የተጻፈው ( ዚህ ሥ ራ ላይ ነው። ከዚህ ይ ልጥ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ የሆነው ሉ ቃስ የበለጠ ትኩ ረት የ ሰጠው ጳውሎስ በአሕዛ በ መካከል የነበረው አገልግሎት ላይ ነው።

እንደምታስታውሰው፥ የኢየሩሳሌ ም ጉባዔ ያሳለፈውን ው ሳ ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ይዞ ሲመለስ፥ ከኢየሩሳሌ አብረውት የመጡ ሁለት ሰ ች ነበሩ። ከእነዚሀ ሰዎች ውስጥ አንዱ ሲላስ ነ ር (ሐዋ. 15፡ 23-27 ። የ ላስ ስም ከኢየሩሳሌም በተላከው መልእክትም ላ ተጠቅሶ ነበር። ጳውሉስ ከ ንጾኪያዋ ቤተክርስቲያን ሲላስ ደግሞ ከኢየሩሳሌሟ ተክርስቲያን የመጣ ነው፤ በዚ ም መልኩ በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉ ላይ ሁለቱም ተክርስቲያኖች መወከላቸው ነ ገቢ ነው።

ጳውሎስና ሲላስ ሮማውያን በመሆናቸ ው በሮማው መንግሥት በተ ተ አገሮች ውስጥ የበለጠ ተቀባይነት እንዲያገኙ አድርጓቸዋል (ሐዋ. 16፡ 17-38)። በሚቀጥለው ሳምንት፥ ባቀረቡት መል ክት ምክንያት የተነሣውን ቃውሞና እግዚአብሔር በሕይወታቸ ው ውስጥ የሠራ ውን ድ ቅ ሥራ እንመለከታለን። በሶርያና

በኪልቅያ በመጓጓዝ ላይ ሳሉ፥ እግዚአብሔር የእያንዳንዳቸውን ስጦታ ለቤተክርስቲያን ማጽናኛ ተጠቅሞበታል፤ በአይሁድ ሃይማኖት ወግ አጥባቂዎች ተጽዕኖ ከተደረገባቸው ከጴጥሮስና ከበርናባስ ይበልጥ፥ ጳውሎስ በፀጋ የመዳንን የተገነዘበ መስላል (ገላ 2፡ 11-13 ተመልከት)።

ጥያቄ 36 - እግዚአብሔር የተለያዩ ስጦታዎችን ችሎታዎችን ይሰጣል። ልዩ የሆነው የጳውሎስ ስጦታ ምንድነው? የበርናባስና የሲላስ ስጦታዎች ምንድናቸው? የአንተ ስጦታ ምንድነው?

በማርቆስ ምክንያት የተነሣው አለመግባባት እስከመጨረሻ ድረስ የቆየ ችግር አልነበረም። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ ወንጌላዊ በርናባስን ሲያሞግስ እናያለን ጳውሎስ በማርቆስ ላይ የነበረውን ጥላቻ ለብዙ ጊዜ ይዞት አልቆየም፥ ምክንያቱም ጳውሎስ በሮም እሥረኛ ሳለ በአጠገቡ የነበረው ማርቆስ ነበርና ነው። እንዲያውም ጳውሎስ ከመሞቱ በፊት ማርቆስ ወደ እርሱ እንዲመጣ ጥሪ አድርጓል (ቆላ 4፡ 10 እና ጢሞ. 4፡ 11)።

በአገልጋዮች መካከል ሁሌም ቢሆን አለመስማማት ይኖራል። ሆኖም ዋናው ነገር፥ የእግዚአብሔር ሥራ እንዳይደናቀፍ በእነዚህ ችግሮች ውስጥ ማለፍ መሥራት ነው። ሰይጣን በቤተክርስቲያን ለመሥራት ፃሬቶችንና ክፍፍልን እንዲፈጥር አመቺ ሁኔታዎችን መክፈት የለብንም።

# አምስተኛ ቀን፡-

## ትምህርቱን ከልስና የመልመጃ ጥያቄዎችን ተመልከት።

የክለሳ ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ወደ አንድ አዲስ ከተማ ሲገባ፥ ለመመሥከር መጀመሪያ የሚሄደው ወደየት ነው?

2. ጳውሎስ ለአይሁዳውያንና ለአሕዛብ የሚሰጠው ምሥክርነት ልዩ መሆኑ፥ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው?

3. ይህን ታላቅና ከባድ የሆነ ወንጌልን በአለም ዙሪያ የማሰራጨት ተግባር እንዲፈጸም የረዱት የጳውሎስ ባህሪዎች ምንድናቸው?

4. ሀ) በመጀመሪያው ጉዞ ላይ፥ ጳውሎስና ተስፋ ሊያስቆርጡ ይችሉ ነበር የምትላቸውን ችግሮች በዝርዝር ግለጽ፤ ለ) አገልግሎቱ ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩትስ እንዴት ነው?

5. የጳውሎስን ቤተክርስቲያን የመመሥረትና የማነጽ ስልቶች መለስ ብለህ እያቸው።

6. ሀ) የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ጉባዔ ለምን አስፈለገ? ለ) ቤተክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ ያሳደረውስ እንዴት ነው?

7. ከጳውሎስና በርናባስ ግምት ውስጥ የተማርነውን መልካም ነገር ግለጽ።

ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጁ እንድትሆን፥ ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት።

# ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ክለሳ
4. ውይይት:-

ሀ) የጳውሎስን የቤተክርስቲያን አመሠራረት ስልት ተወያዩበትና የአንተ ቤተክርስቲያን አሠራር ከእርሱ ስልት ጋር እንዴት ሊወዳደር እንደሚችል ተመልከት።

ለ) 1. ብዙ ጊዜ በአገልጋዮች መካከል አለመግባባት የሚፈጠረው ለምንድነው?
2. እነዚህ አለመግባባቶች፥ ሁልጊዜ መጥፎ የሆነ ውጤቶችን ነው የሚያስገኙት?
3. አለመግባባቶች ለቤተክርስቲያን ጎጂ የሚሆኑት መቼ ነው?
4. ክርስቲያኖች ለልዩነቶቻቸው ዕልባትን መፍጠር ያለባቸው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

ሐ) 1. ነባር ክርስቲያኖች አስፈላጊ ያልሆኑ ባህሎችን ወይም ልማዶችን አዳዲስ ክርስቲያኖች እንዲከተሏቸው ሊያደርጉ የማይችሉት በምን ዓይነት መንገድ ነው? 2. በአዳዲስ ቦታዎች ላይ በተመሠረቱ ቤተክርስቲያኖች ውስጥ፥ ሊሟሉ ይገቧቸዋል የሚሏቸውን አንዳንድ ነገሮች በዝርዝር ጻፍ። 3. ይህ ችግሮችን የፈጠረው እንዴት ነው? 4. ቤተክርስቲያንህ ወንጌላውያኗ እንዲህ ዓይነቱን ስሕተት እንዳይፈጽሙ፥ ስትል የምታሠለጥናቸው እንዴት ነው?

መ) 1. በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚነሡ ሐሰተኛ ትምህርቶችን መዋጋት በተመለከተ፥ ከኢየሩሳሌሙ ጉባዔ ልንማረው የምንችለው ነገር ምንድነው? 2. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ወንጌላውያን ቤተክርስቲያኖች፥ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ተባብረው በመቃወሙ ረገድ አብረው የሚሠሩት እንዴት ነው? 3. ወንጌላውያን ቤተክርስቲያኖች ይህን ተግባር በተቀላጠፈ ሁኔታ ሊፈጽሙ የሚችሉት እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 12

የሐዋርያት ሥራ 16፡ 1-40

## የመጀመሪያ ቀን፡-የሐዋርያት ሥራ 16፡ 1-5

የጳውሎስ ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ የተጀመረው በተረጋጋ ሁኔታ አልነበረም። በጳውሎስና በበርናባስ መካከል የከረረ አለመግባባት ከተፈጠረ በኋላ ነበር የተጀመረው። ይህም አለመስማማት የመጀመሪያውን ሚሲዮናዊ ቡድን እንዲፈርስ አድርጎታል። በዚህም መሠረት ጳውሎስና ሲላስ ወደ ሶርያና ኪልቅያ ሲሄዱ በርናባስና ማርቆስ ደግሞ ወደ ቆጵሮስ ይመለሳሉ። አማኞችን ለማበረታታትና ለማጠናከር ከዚህ በፊት የሄዱባቸው ከተሞች ውስጥ እንዲሄዱ ዕቅዱን ያወጣው ጳውሎስ ነበር። በተጨማሪም፥ ጳውሎስ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት፥ ወደሌሎች ሥፍራዎች ወንጌልን ያደርሳሉ ብሎ ይገምት ነበር።

ወንጌሉ ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ ሲስፋፋ፥ አንዳንዶቹ ባህሎች ለደኅንነት ያስፈልጋሉ ተብሎ ትምህርት ሊሰጥ ይችላል፥ ልማዶች ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ፥ ሆኖም በክርስቶስ መዳን ላይ ሌላ ነገር ልንጨምር አንችልም። ወደ አዲስ ሥፍራ ስንገባም፥ ተገቢ ያልሆኑ ቅሬታዎች እንዳይፈጠሩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ጳውሎስም «ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ» ብሏል።

ጥያቄ 1፡- በሌላ ባህል ውስጥ የሚገኙ ለየት ያሉ ልማዶች ላይ ሊኖረን የሚገባው አመለካከት ምን ዓይነት መሆን አለበት?

ጥያቄ 2፡- የሐዋርያት ሥራ 16፡ 1-40 አንብብ። ጳውሎስ የሄደባቸውን ሥፍራዎች በሙሉ በዝርዝር ጻፍ። እነዚህ ቦታዎች ከዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ የሚገኘው ካርታ ላይ ተመልከት።

የሐዋርያት ሥራ 16፡ 1-10 እንደገና አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 3፡- ሀ) 1. ጳውሎስ በልስጥራን ያገኘው ደቀመዝሙር ማን ነበር? 2. እናቱ ማን ነበረች? አባቱስ ማን ነበር? 3. በሰዎች ዘንድ የነበረው አመለካከት ምን ነበር? ለ) 1. ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲገረዝ ያደረገው ለምንድነው? 2. ይህ ተግባር፥ በደኅንነቱ ላይ ያስገኘለት ውጤት አለን? ሐ) 1. በደርቤንና በልስጥራን ጳውሎስና ሲላስ በተለይ ያገለግሉት የነበረው እነማንን ነው 2. ያስተላለፉት መልእክት ምንድነው? 3. በቤተክርስቲያኖቹ ውስጥ የተገኘው ውጤት ምንድነው? መ) 1. መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስና ሲላስን እንዳይገቡ ያገዳቸው በየትኞቹ ሥፍራዎች ነው? 2. ጳውሎስ ራዕዩን ያየው የት ሆኖ ነው? 3. ራዕዩ ምን ነበር?

የጳውሎስ ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ ከ 49-52 ዓ.ም ድረስ የተካሄደ ነው። የመጀመሪያው ጉዞውን የጀመረው፥ በእስያ የየብስ ጉዞ እንዳደረገ ቤተክርስቲያናትን በመጎብኘት ነው። ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌምም አንጾኪያ ከመመለሱ በፊት ወደ አውሮፓ በመሄድ በግሪክ፥ በመቄዶንያና በአካያ አገልግሏል።

ጳውሎስ በገላትያ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በመጀመሪያ ያደረገው ነገር በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች የተጻፈውን መልእክት ማገበብ ነው። ይህንንም የሚያደርገው አብያተ ክርስቲያናትን በመበከል ላይ የሚገኘውን ሐሰተኛ ትምህርት በአፋጣኝ ለማቆም ነው። በተጨማሪም ይህ መልእክት፥ ከኢየሩሳሌሙ ጉባዔ በፊት ወይም ከተጠናቀቀ በኋላ ወዲያውኑ ለገላትያ ሰዎች የጻፈውን መልእክት የሚያጠናክር ነው።

ጳውሎስ በልስጥራን፥ በአማኞች ዘንድ ጥሩ ስም የነበረውን ጢሞቴዎስ የተባለ ደቀመዝሙር ያገኛል። ምናልባትም ጌታን የተቀበለው በጳውሎስ መጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ ላይ ይሆናል። የጢሞቴዎስ እናትም እውንቁ አይሁዳዊት አማኝ ነበረች። (2 ጢሞ. 1:50። አባቱ ደግሞ ግሪካዊ ሲሆን፥ ምናልባትም በእሱ ተጽዕኖ እስከ አሁን ድረስ ባህል መሠረት አልተገረዘም ነበር።

ጳውሎስ በጉዞው ላይ ጢሞቴዎስን ሊወስደው ወደደ። ጳውሎስና ጢሞቴዎስ ባለመገረዙ፥ አይሁዳውያን አይቀበሉትም ብሎም አሰበ። ይህም፥ ለወንጌሉ መስፋፋት እንቅፋት ይፈጥራል። በዚህም ምክንያት ጢሞቴዎስ ይገረዛል። ጢሞቴዎስ የተገረዘው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት እንዳልሆነ መገንዘቡ አስፈላጊ ነው። ይህ ነገር የተደረገው፥ ወንጌሉ እንዳይስፋፋ የሚያደርጉ ተገቢ ያልሆኑ እንቅፋቶች እንዳይፈጠሩ ሲባል ነው። ከዚህ ቀደም ብሎም፥ ቲቶ ለደኅንነቱ ሲባል መገረዝ አለበት ብለው አንዳንድ አይሁዳውያን ሐሳብ ሲያቀርቡ፥ ጳውሎስ ሐሳቡን አልተቀበላቸውም (ገላ. 2: 1-3)።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በመግረዙ ተቃውሞ ደርሶበታል። የጉባዔው መልእክት፥ መገረዝ ለአሕዛብ አስፈላጊ አይደለም ይላል። ይህም ቢሆን፥ የተገረዘው ለደኅንነቱ ሲባል ሳይሆን፥ እንደ አይሁዳዊ ስለሚቆጠር፥ በምኩራቡ በሚሰበሰበው ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ነው። ከወግ አጥባቂዎች የአይሁድ ክርስቲያኖች ጋር ያለውን ልዩነት ለማስወገድ ሳይሆን፥ የጢሞቴዎስን አስፈላጊነት ለማስፋት ሲባል ነው የተደረገው።

ጥያቄ 4:- ምሥክርነታችን የታለመለትን ግብ እንዲመታ ስንል መቼ የሰዎችን ባህል መቀበል እንዳለብን አንዳንድ ምሣሌዎችን ስጥ።

በጥንቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ፥ ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ጢሞቴዎስ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ልክ ማርቆስ ጳውሎስንና በርናባስን እንደሚያገለግለው በመጀመሪያ ጊዜ የጳውሎስና የሲላስ አገልጋይ ነበር። ጳውሎስም የሚተማመንባቸውና እውነተኞች የሆኑ አብረውት የሚሠሩ ሰዎች ያስፈልጉታል። በሕይወቱም ውስጥ በሙሉ፥ ጢሞቴዎስ የጳውሎስ ቅርብ ወዳጅና አገልጋይ ነበር።

ጥያቄ 5 :-ወንጌላውያን በቡድን በቡድን ሆነው መውጣታቸው ጠቃሚ የሚሆነው በምን መልኩ ስናየው ነው?

የጢሞቴዎስ አገልግሎት በትንቢቶች (1 ጢሞ. 1፡ 18) እና በሽማግሌዎች እጅ መጫን (1ጢሞ. 4፡14) የተረጋገጠ ነው። ከዚህም በመቀጠል ከጳውሎስ ጋር በሁለተኛውና በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ አብሮት ሄዷል፤ ከዚህም በላይ ወደ ሮም ሲሄድ እንኳ አብሮት ነበር። ሊሞት አካባቢም ጳውሎስ ጢሞቴዎስ አብሮት እንዲሆን ጠርቶታል። በስድስቱ የጳውሎስ መልእክቶችም ውስጥ የመክፈቻ ሰላምታ ላይ የጢሞቴዎስ ስም ተጠቅሷል።

ጢሞቴዎስ በጳውሎስ ቡድን ውስጥ አንዱ ዋነኛ አባል ነው። ብዙ ጊዜም ወደ ኋላ ቀርቶ አዳዲሶቹን ክርስቲያኖች ጥልቅ የሆኑትን የወንጌሉን እውነታዎች ያስተምርና በራሳቸው ኃይል ታንጸው እንዲንቀሳቀሱ ተገቢ ዕርዳታ ያበረክት ነበር። በውነቱ ከሆነም ጳውሎስ እሱን በማስተማርና በማሠልጠን ብዙ ጊዜ ፈጅቷል። በአዲስ ኪዳን ውስጥም በተሰሎንቄ አማኞችን እንዲያጽናና በኤፌሶን ደግሞ የሐሰት ትምህርቶችን አስወግዶ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን እንደሚመርጥ መላኩን እናያለን። ወደ መቄዶንያና ወደ ቆሮንቶስም ተልኳል (1ቆሮ. 6፡ 10-11)። በኋላም ላይ፥ በእምነቱ ምክንያት ወኅኒ ቤት ገብቷል (ዕብራ. 13፡ 23)።

ጥያቄ 6፡- ሀ) አሁን ለሚገኙ የቤተክርስቲያን መሪዎች ሐላፊነት የሚረከቡትን ሰዎች ማሠልጠኑ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? ለ) የመሪነቱን ሐላፊነት የሚተኩ ሰዎች በተመለከተ፥ ቤተክርስቲያንህ ስለምትሰጠው ሥልጠና አብራራ።

ጢሞቴዎስ ዓይነ አፋር ወጣት በመሆኑ አባቱ ጳውሎስ ተገቢውን ማበረታቻና ምክር ሊሰጠው ይገባ ነበር (2ጢሞ 1፡ 7 ተመልከት)። ሆኖም፥ አብረውት ከነበሩት ሠራተኞች ሁሉ ስለታማኝነቱ ጳውሎስ ሲያሞግሰው የነበረው ጢሞቴዎስን ነው (1ቆሮ 16፡ 10፤ ፊሊ. 2፡ 19-20)። የመጨረሻው የጳውሎስ መልእክት የሆነው 2ኛ ጢሞቴዎስም የተጻፈው ለእርሱ ነው።

እግዚአብሔር በጳውሎስ ስጦታ ተጠቅሞ ወንጌልን ወደ አዳዲስ ሥፍራዎች አስፋፋ። ጢሞቴዎስን ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንዲያንጽና እንዲመሠርት ተጠቀመበት። ቤተክርስቲያንን የመመሥረቱ ሂደት፥ ብዙ የተለያዩ ሰዎችን የሚያካትት ነው። ጳውሎስም «እኔ ተከልሁ፥ አጵሎስም አጠጣ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር ... የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው፤ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል» ብሏል (1ቆሮ. 3፡ 5-9)።

ጥያቄ 7፡- እግዚአብሔር በአንተ ሥጦታ ተጠቅሞ ወንጌልን የሚያስፋፋውና ቤተክርስቲያንን የሚያሳድገው እንዴት ነው?

በጳውሎስና በሥራ ጓደኞቹ አገልግሎት፥ አብያተ ክርስቲያናት በእምነት ይጠነክሩና በቁጥር በየጊዜው ያድጉ ነበር። ጤናማ የሆነች ቤተክርስቲያን በሁለት

ዓይነት መንገድ ታድጋለች። እንደኛ፣ የቁጥር ዕድገት አለ። ይህን ስንል፣ ሁልጊዜ ወደ ቤተክርስቲያኒቱ የሚገቡ አዳዲስ አማኞች መኖር አለባቸው ማለታችን ነው። ቤተክርስቲያኒቱ ምንም አዲስ አባል ከሌላትና በዛ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች የሚወልዷቸው ልጆች ብቻ የአባላቱን ቁጥር የሚያሳድጉት ከሆነ፣ ይህቺ ቤተክርስቲያን በጣም ደካማ ናት።

ሁለተኛ፣ ጤናማ ቤተክርስቲያን በእምነቷ ማደግ አለባት። የክርስቲያኖች በዕውቀት ረገድ በጥልቀት ማደግ አለባቸው። ጳውሎስም ሁልጊዜ ለቤተክርስቲያኖች «በእርሱ ተመላለሱ፣ ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ፣ እንደተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ ምስጋናም ይብዛላችሁ» እያለ ነበር የሚጸልየው (ቆላ 2፡7)።

ጥያቄ 8፡- ለእነዚህ ሁለቱ ዓይነት ዕድገቶች በቤተክርስቲያንህ ውስጥ እንዴት እየተከናወኑ እንደሆነ አብራራ።

## ሁለተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 16፡ 6-10

ጳውሎስ ሁለተኛው ጉዞውን ሲጀምር፣ አስቀድሞ በፊት የተመሠረቱትን አብያተ ክርስቲያናት መጎብኘት ነበር ዕቅዱ። ሆኖም ከዚህም ጋር አብሮ ወንጌልን ወደ አልደረሰባቸው ሥፍራዎች የማስፋፋት ዕቅድም ነበረው። ስለዚህም ጳውሎስ፣ ሲላስና ጢሞቴዎስ ወደ እስያ፣ ቢታንያና ሚሲያ እንሄዳለን ብለው ተስፋ በማድረግ ጉዞአቸውን ጀመሩ። መንፈስ ቅዱስ ግን፣ ወደሌሎች ሥፍራዎች መራቸው። ለእነዚህ ክፍለ ነገሮችም መንፈስ ቅዱስ የራሱ ጊዜና መንገድ ነበረው።

ጥያቄ 9 ፡-በሕይወትህ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት መወሰንን የተማርከው እንዴት ነው?

የሐዋርያት ሥራ 16፡ 6-10 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 10፡- ሀ) የጳውሎስን ሁለተኛ ሚስዮናዊ ጉዞ የሚያሳየውን ካርታ ተመልከት። በተለይም ፍርግያ፣ ገላትያ፣ እስያ፣ ቢታንያና ሚሲያ የት እንዳሉ ተመልከት። ለ) በጢሮአዳ የሆነው ነገር ምንድነው? ሐ) አሁን ከሚገኙት ክፍለ ዓለማት ውስጥ መቄዶንያ የምትገኘው በየትኛው ውስጥ ነው? መ) በሐዋርያት ሥራ 16፡ 8 ላይ «ወረዱ» ብሎ በሐዋርያት 16፡ 10 ላይ «ልንወጣ ፈለግን» የሚል ቃል የተጻፈው ለምንድነው?

የገላትያን ቤተክርስቲያን በመተው፣ ጳውሎስና፣ አብረውት የነበሩት ሰዎች ከዚህ በፊት ከተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት በስተምዕራብ በሚገኙት፣ በፍርግያና በገላትያ ክፍለ ሀገሮች በኩል ያልፋሉ። በዚህ ጊዜ በእነዚህ ሥፍራዎች ቤተክርስቲያናት ስለመመሥረታቸው በሐዋርያት ሥራ ባይጠቀስም፣ ይጓዙ በነበረበት ወቅት ያለጥርጥር የወንጌሉን መልእክት እየሰበኩ ነበር የሚያልፉት። እዚያው ድንበሩ ትገኝ ወደነበረችው ወደ እስያ ለመሄድ ፈልገው ነበር፤ ሆኖም መንፈስ ሌላ እቅድ ስለነበረው ይከለክላቸዋል። ወደ እስያ ገብተው በኤፌሶን ሥራ እንዲሠሩም የተፈቀደላቸው በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ ላይ ነው፤ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን ወደ

እስያ ሄደው አያውቁም። ወደ የትም እንደሚሄዱ ሳያውቁ፥ የምዕራቡን መንገድ በመከተል እስከ እስያ ክፍለ ዓለም ጠረፍ ድረስ ይጓዛሉ። በኋላም በሚስያ እንደደረሱ፥ «የኢየሱስ መንፈስ» የሰሜኑን አቅጣጫ ይዘው ወደ ቢታንያ እንዳይሄዱ ይከለክላቸዋል። ያለምንም ጥርጥር እግዚአብሔር የአገልግሎቱን በሮች ይዘጋባቸው ስለነበር ግራ ሳይጋቡ አልቀሩም። በመጨረሻም፥ ተነሥተው በኤጊያ ወንዝ ድንበር ላይ ወደምትገኘው ወደ ጢሮአዳ ከተማ ይሄዳሉ። ከዚህም በላይ፥ ያለ እግዚአብሔር ምሪት ወደ የትም መሄድ አይችሉም ነበር።

በጢሮአዳ ሳሉ፥ ሌሊት ላይ ጳውሎስ አንድ የመቄዶንያ ሰው ቆሞ «ወደ መቄዶንያ ተሻግረህ እርዳን» ብሎ ሲለምነው በራዕይ ያያል። መቄዶንያ በአሁኗ ግሪክ ውስጥ የምትገኝ የሰለጠነች ከተማ ነበረች። ታላቁ እስክንድርም ዓለም ድል ያደረገው ከዚህች ከተማ ተነሥቶ ነው። በተጨማሪም ይህች ከተማ የምትገኘው በአውሮፓ ክፍለ ከተማ ውስጥ ነው። ይህ ደግሞ አዲስ ክፍለ ከተማ ስለሆነ፥ ለወንጌሉ መስፋፋት አንድ ዕመርታ ነው። በተጨማሪም፥ የወደፊቱን የሚያውቀው አምላክ፥ በሚመጡት ዘመናት በአውሮፓ ውስጥ የወንጌሉ ብርሃን እንደበራ እንደሚቆይ፥ ነገር ግን በእስያና በአፍሪካ በእስልምና ሃይማኖት ምክንያት ደብዛው እንደሚጠፋ ያውቅ ነበር።

ጳውሎስ ይህን ራዕይ ካየ በኋላ፥ አብረውት ከነበሩት ሰዎች ጋር በመሆን ወደ መቄዶንያ በመርከብ ይሄዳል።

ልክ በዚህ ሥፍራ ላይ ሲደርስ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ የሆነው ሉቃስ፥ «ወደ መቄዶንያ ልንወጣ ፈለግን፤ እንሰብክላቸውም ዘንድ እግዚአብሔር እንደጠራን መስለናልና» ብሎ ይናገራል። ሉቃስ፥ ከጳውሎስ፥ ከሲላስና በጢሞቴዎስ ጋር በዚህ ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ አብሯቸው የነበረው፥ ከጢሮአዳ ተነሥተው ወደ መቄዶንያ በመርከብ ከሄዱበት ጊዜ አንሥቶ ነው። ከዚህም ጊዜ በኋላ፥ በትርፍ ጊዜው አብሮ ከጳውሎስ ጋር ይጓዝ ነበር። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ «እኛ» የሚል ቃል ካየህ፥ ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር ተጉዟል ማለት ነው።

መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን ወደ እስያና ቢታንያ እንዳይገባ አድርጎ እንዴት እንደመራው ግልጽ አይደለም። በራዕይ ነው? ድምፅ በመስማት ነው? ወይስ የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን በሚገልጹ ሁኔታዎች? ምንም የምናውቀው ነገር የለንም። እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ሊመራን ይችላል። ሆኖም፥ ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች ለመንፈስ ምሪት በደንብ የተገዙና ቶሎ ብለውም ታዛዥ ለመሆን ዝግጁ የነበሩ ናቸው። ብዙዎቹ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልጋቸው ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጠቅሰዋል። በቃሉ ላይ የገለጹልንን ነገር ሙሉ በሙሉ ከመጠበቅ ሌላም፥ እግዚአብሔር በሕይወታችን በሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮች ውስጥ ገብቶ ይመራናል ብለን ተስፋ ልናደርግ አንችልም።

ጥያቄ 11፡- እግዚአብሔር ያልጠበቅኸውን ነገር እንድትፈጽም እንዴት አድርጎ እንደመራህ የምታስታውሰው አጋጣሚ ካለህ ሰፋ አድርገህ አብራራው።

የእግዚአብሔር ጊዜ ሁልጊዜ ከእኛ አስተሳሰብ ጋር የሚጣጣም አይደለም። ጳውሎስ በዚህን ጊዜ ወደ እስያ እንዲገባ ባይፈቀድለትም በኋላ ላይ ግን በኤፌሶን ውስጥ ለሁለት ዓመት ቆየ፤ ከዚህም ሥፍራ ነበር «በእስያ የነበሩት አይሁድም የግሪክም ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ወንጌሉ ሊስፋፋ የቻለው። (ሐዋ. 19፡ 10 ተመልከት)።

አገልግሎታችን ፍሬ ሊኖረው የሚችለው፥ እግዚአብሔርን ጠብቀን በመንፈስ ቅዱስ ስንመራ ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስም ቃሉን የምናገርበትን መንገድ፥ ቦታና ጊዜ ሊያሳየን ይገባል። ዛሬ ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይበልጥ ብዙ ትኩረት የምናደርገው በአደረጃጀት፥ በግስታወቂያዎችና በየገንዘብ ድጎማ ላይ ነው። ቤተክርስቲያንን የመሠረቱት ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንዳስፈለጋቸው ሁሉ እኛም ዛሬ ያስፈልገናል። ኢየሱስ አሁንም በምድር ላይ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሥራውን እየሠራ ነው። ወንጌሉ ወደ መቄዶንያ (አውሮፓ) የሚሰበክበት ትክክለኛው ጊዜ ደርሶ ነበር፤ ለቢታንያና ለእስያ ደግሞ ጌታ ሌላ ዕቅድ ነበረው። የመጀመሪያው የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክትም፥ በጳንጦስና በገላትያ፥ በቀጰዶቅያ፥ በእስያና በቢታንያ ለተበተኑ መጻተኞች መጻፉ ጳውሎስ ወዳሰባቸው ቦታዎች በሙሉ ወንጌሉ መዳረሱን ያመለክተናል። ምናልባትም፥ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መልእክት ይዞ ወደ እነዚህ ሥፍራዎች የሄደው ጴጥሮስ ሳይሆን አይቀርም።

ጥያቄ 12 ፡-ክርስቲያኖች ዛሬ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ከመፈለግ ይልቅ ይበልጥ ወደ ሥራው ቅንጅት፥ ባጀት ማጽደቅ፥ ወዘተ... ሊያዘነብሉ የሚችሉት በምን ዓይነት መንገዶች እንደሆነ በዝርዝር ግለጽ።

ጥያቄ 13፡- በሕይወትህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምታውቅባቸውን መንገዶች በዝርዝር ግለጽ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ስትል የምትጠቀምበትን ስልት ስታወጣ በዚህ ዕቅድህ መሠረት የምታደርጋቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?

## ሦስተኛ ቀን፡-

## የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ማወቅ እንደሚቻል።

የጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች ወንጌሉን ወደ እስያ፥ ቢታንያና ሚስያ ለማስፋፋት የነበራቸውን ዕቅድ መንፈስ ቅዱስ አግዶባቸዋል፤ በኋላ ግን በጢሮአዳ ሳሉ፥ ወደ መቄዶንያ እንዲሄዱ እግዚአብሔር ጥሪውን ለጳውሎስ በራዕይ ይሰጠዋል።

ከራዕዩ ሌላ፥ መንፈስ ቅዱስ እንዴት ጳውሎስን መርቶ ወደ እነዚህ ቦታዎች እንዳይሄድ እንዳደረገው የተነገረን ነገር የለም። ሆኖም ዛሬ እንደሚያደርገው፥ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነት መንገዶች ሳይጠቀም አልቀረም። በዛሬው ጥናታችንም፥ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ምሪት እንዴት ልናውቅ እንደምንችል የሚገልጹልንን አንዳንድ መሪ ሐሳቦችን እናያለን።

ጥያቄ 14 ፡-እግዚአብሔር ይመራህ የነበረው በምን ዓይነት መንገዶች ነው?

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ስንል ልንከተላቸው የምንችላቸው አንዳንድ መመሪያዎች፡-

1. የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፡- እግዚአብሔር ፈቃዱን ቁልጭ አድርጎ የሚገልጽበት ሥፍራ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሁልጊዜ እግዚአብሔር ሲመራ፥ በቃሉ

በተነገረው ትምህርት መሠረት ነው። እግዚአብሔር ይመራናል ብለን እያሰብን ሁኔታው እግዚአብሔር በቃሉ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር የማይጣጣም ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን፤ ይህም የሚሆነው እግዚአብሔር ሐሳቡን እንደማይቀይር ወይም እንደማይዋሽ ስለምናውቅ ነው። ለምሳሌ ያህል፥ አንድ አማኝ ያልሆነችን ሴት ማግባቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ለማወቅ ብትፈልግ፥ እግዚአብሔር በግልጽ በቃሉ የማያምኑትን እንዳታገባ ትዕዛዝ ሰጥቶሃል። የምንጸልየው ጸሎት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያማይጣጣም ከሆነ፥ እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ አይሰጠንም። ቃሉን የማናውቀው ከሆነም፥ ጸሎታችን ከንቱ ነው (መዝ. (119)፡ 105 ተመልከት)። የእግዚአብሔርን ቃል እያወቅነውና እየጠበቅነው በሄድን ቁጥር፥ እግዚአብሔር የበለጠ ፈቃዱን ይገልጽልናል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ከፈለግን መጀምሪያ መውሰድ ያለብን እርምጃ፥ እግዚአብሔር በቃሉ የገለጸውን ፈቃዱን በጥንቃቄ ማጥናትና የተጻፈውንም ትዕዛዝ መጠባበቅ ነው።

ጥያቄ 15፡- ሀ) እግዚአብሔር ካንተ የሚፈልገውን ነገር ለመወሰን እንድትችል በቃሉ ላይ ያለህ እውቀት የረዳህ እንዴት ነው? ለ) የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆኑ በቃሉ በግልጽ የተቀመጡ አንዳንድ ነገሮችን በዝርዝር ግለጽ።

የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ያለብን፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመወሰን ብቻ ሳይሆን፥ እውነተኛ ያልሆነውንም ነገር ለማወቅ ስንልም ጭምር መሆን አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጡ ትምህርቶችንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ እናውቃለን ብለው የሚሉ ሰዎችን የምንመዝንበት ሚዛናችን ነው። የአንድ ሰው ትምህርት ወይም አስተሳሰብ በግልጽ ከተቀመጠው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ከሆነ፥ ነገሩ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

2. እራስን አሳልፎ መስጠት (ገር መሆን)፡- እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚገልጸው ፈቃዱን ለመጠበቅ ሙሉ ለሙሉ ፈቃደኞች ለሆኑ ብቻ ነው (መዝ. (25)፡ 9፤ የሐዋ. 9፡ 6 ተመልከት)። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚገልጸው በየደረጃው ነው። በመጀመሪያ ፈቃዱን በከፊል ይገልጽልናል። ከዚያም የገለጸልንን ነገር ተቀብለን ስንፈጽመው፥ የበለጠ ፈቃዱን እየገለጸልን ይሄዳል። መንፈስ ቅዱስም ሊመራን የሚችለው ታዛዦች ስንሆን ብቻ ነው። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ወደ ቢታንያና እስያ እንዲሄድ አለመፍቀዱን ሲያውቅ፥ አላጉረመረመም ወይም ትዕዛዙን አልቀበልም ብሎ የራሱን መንገድ አልያዘም።

ጳውሎስ እግዚአብሔር የሚፈልገውን አውቆ በመታዘዙ ግን፥ እግዚአብሔር ደረጃ በደረጃ ሊሠራበት ወደሚፈልገው ሥራ ጳውሎስን መራው።

3. ንሥሐ፡- መንፈስ ቅዱስ እንዲናገረን፥ እንዲመራን ብሎም ፈቃዱን እንዲያሳየን በሕይወታችው ያለውን ኃጢአት ሁሉ መናዘዝና መተው ይኖርብናል (መዝ. (66): 18-19፤ (139): 23-24 ተመልከት)። መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን ይጸየፋል፥ ኃጢአት በሕይወታቸው እንዲነግሥ ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር አይሠራም። መንፈስ ቅዱስም «ቅዱስ» ተብሎ የሚጠራው በዚህ ምክንያት ነው። ንስሐ ያልገባንበት ኃጢአት በሕይወታችን መኖሩን እያወቅን፥ ፈቃድህን አሳየን ብለን እግዚአብሔርን መጠየቅ የለብንም። መጀመሪያ ማድረግ ያለብን ንስሐ መግባት ነው።

ጥያቄ 16፡- ንስሐ ያልገባህበትን ኃጢአት ደብቀህ እንዳይሆን እስቲ አሁን ጊዜ ውሰድና ሕይወትህን መርምረው።

4. ጸሎት፡- እንድንጸልይ ታዝዘናል (1ተሰ. 5፡ 7፤ ዮሐ. 16፡ 24፤ 1ዜና 16፡ 11 ተመልከት)። ቆላ. 1፡ 9-10 አንብብና ልንጸልይባቸው የምንችልባቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ። ስንጸልይ፥ ልባችን እግዚአብሔርን በማዳመጥ ትዕዛዛቱንም እንዲፈጽም እናዘጋጀዋለን። ሆኖም፥ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር እንዲገልጽልን በማድረግ ፈንታ ዕቅዶቻችንን በእግዚአብሔር ፊት እናቀርብና ባርከልን እንለዋለን። ታዲያ ሁልጊዜ «የኔ ሳይሆን ያንተ ፈቃድ ይሁን» ብለን መጸለይ ያለብን ለዚህ ነው። እንደ ጌታነቱ እግዘኢአብሔር በዕቅዶቻችን ላይ የበላይነቱን እንዲይዝ መጣር አለብን እንጂ፥ ዝም ብለን ካሁን በፊት የወሰንነውን ውሳኔ እንዲባርከልን ብቻ ማድረግ የለብንም።

5 አትቸኩል፡- እግዚአብሔር ወዲያውኑ መልስ ካልሰጠህ፥ ጠብቅ! የምታምን ከሆነ አትቸኩልም። እግዚአብሔር የሚዘገይባቸው ብዙ ምክንያቶች አሉት፤ በተጨማሪም የእርሱ ጊዜ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር አንድ ዓይነት አይደለ (መዝ. (27)፡ 14፤ (130)፡ 5 ተመልከት)

6 የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለህ የምትገምተውን ነገር መሥራት ጀምር፡- እግዚአብሔር አንዳንዴ ፈቃዱን ሳይጠቅስ በደረጃ ስለሚገልጽ፥ እግዚአብሔር አንድ የሆነ ነገርን እንድሠራ ይፈልጋል ብለህ የምታምን ከሆነ፥ ጀምረው። ይህንን ነገር በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ እናየዋለን። ጳውሎስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ እንዲመሠክር ጥሪ እንዳደረገለት ያውቃል። ሆኖም የት ሄዶ እንደሚመሠክር ባያውቅም፤ ጥሪውን ተቀብሎ መፈጸም ጀምሯል። ትዕዛዙን በመፈጸም ላይ ሳለም፥ እግዚአብሔር አንዳንድ በሮችን በመክፈት ሌሎችን ደግሞ በመዝጋት ጳውሎስን እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገር አሳይቶታል። እግዚአብሔር በአንዴ ዕቅዱን ይገልጽልኛል ብለህ አትጠብቅ፤ እግዚአብሔር ይፈቅዳል የምትለውን ነገር ብቻ ዝም ብለህ ፈጽም፤ ከዚህ በኋላ በዚህ ውስጥ እያለህ እግዚአብሔር በቀላሉ፥ ሊመራህ ይችላል።

ጥያቄ 17:- አንተ ወይም ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ስትሉ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ምክሮች እንዴት እንደተጠቀማችሁባቸው አብራራ።

እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ እንዲሰጠን፥ እነዚህ ምክሮች ከተከተልን በኋላ! እግዚአብሔር አያሌ መንገዶችን በመጠቀም ፈቃዱን ይገልጽልናል። ለምሳሌ ያህል:-

ሀ) በቃሉ ሊጠቀም ይችላል:- ለዚሁም አንድን ጥቅስ ወይም መልእክት በመውሰድ ሊሆን ይችላል።

ለ) ውሳኔ ስንወስን ለልባችን ሰላምን ይሰጠናል ወይም አይሰጠንም። ቀደም ሲል የተጠቀሱትን አምስት እርምጃዎችን ጠብቀን ከሆነ እግዚአብሔር የብልህ ውሳኔዎችን ለመወሰን አእምሮ ሰጥቶናል ለማለት እንችላለን። ለልባችን ሰላሙን የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው! ስለዚህም የእርሱን ትዕዛዝ ንቁ ሆነን መጠበቅ አለብን።

ሐ) እግዚአብሔር ከሕይወታችን አጋጣሚዎችንም ሊጠቀም ይችላል። ምናልባትም አንዳንድ ነገሮችን በመስጠት ወይም በማገድ ፈቃዱን ሊገልጽ ይችል ይሆናል። የሁሉም ገገር የሆነው አምላክ፥ እንደ ፈቃዱ ከጸለይን እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ሊያስወግድልን ይችላል። ምናልባትም ጳውሎስን የመራው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሳይሆን አይቀርም። ሆኖም፥ ሁልጊዜ አጋጣሚዎችን ብቻ መመልከቱ በቂ ምሪት ሊሆን አይችልም።

መ) ማንበብ ለማይችሉ ወይም ደግሞ ቃሉን ለመስማት ዕድሉን ላላገኙ ሰዎች፥ እግዚአብሔር አንዳንዴ በራዕይ፥ በሕልም ወይም በአንዳንድ ምልክቶች በመጠቀም ይመራቸዋል። አንተ ግን እግዚአብሔር ሁልጊዜ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ይመራል ብለህ አትጠብቅ። እንዲያውም፥ እግዚአብሔር ለኛ ፈቃዱን የሚገልጸው በተለመደውና ብቸኛ በሆነ መንገድ ነው! ይህም በቃሉ ነው።

እግዚአብሔር አንድን ነገር ሲገልጽልህ፥ ያንን ነገር ለመፈጸም ወዲያውኑ ዝግጁ ሁን። ታዛዦች በሆንንም ቁጥር፥ ፈቃዱ ምን እንደሆነ የበለጠ እየገለጸልንና ግንዛቤ እየሰጠን ይሄዳል (መዝ. (32): 8-9 ተመልከት)።

እግዚአብሔር ሊመራንና ፈቃዱን ሊያሳየን ፈቃደኛ ነው! ታዲያ ይህም ቢሆን፥ እሱን መለመን ያለብን ንጹሕ ልቦና ይዘን ነው። ከዚህ በፊት ያደረግነውን ውሳኔ እንዲቀበልልን መጠየቅ የለብንም። ልክ እንደ ጳውሎስ፥ ወደ እስያ፥ ሚሲያና ቢታኒያ መሄድ እየፈለገ ሐሳቡን እንዳስለወጠው ሁሉ፥ እኛም እግዚአብሔር ሐሳባችንን ሊለውጥ ከፈለገ ፈቃደኞች ሆነን መቅረብ ይኖርብናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎትና በቃሉ አማካኝነት ከእርሱ ኅብረት እንድናደርግ ይፈልጋል። ብዙ ጊዜም ከእርሱ ጋር የሚያስፈልገውን ጊዜ እንዳናሳልፍ፥ በሥራና በሌሎች ነገሮች እንዋከባለን። በዚህም ምክንያት አብያተ ክርስቲያናትና ምዕመናን ዛሬ የእግዚአብሔር ምሪት ደብዛው ጠፍቶባቸዋል።

ጥያቄ18:- እግዚአብሔር እንዲያደርግልህ ወይም እንዲገልጽልህ የምትፈልጋቸውን ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

# አራተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 16: 11-40

እግዚአብሔር ፈቃዱን አውቀን በእርሱ እንድንመራ ይፈልጋል። እንዳየነውም፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ልንግር የምንችለው ቃሉን ስናጠናና ስንጸልይ ነው። ኃጢአታችንን ተናዝዘን ለመተውና እራሳችንን አሳልፈን ለእርሱ ለመስጠት ፈቃደኞች ስንሆን ደግሞ፥ ፈቃዱን ለኛ ሊገልጽልን ይችላል። እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ይመራናል፤ ሁሌ በተለመደው መንገድ አይመራንም። አንዳንዴ አጋጣሚዎች አመቺ ሆነው ሊታዩ ይችላሉ፥ ሆኖም እነሱ ብቻቸውን መመሪያ ሊሆኑን አይችሉም፤ ምክንያቱም እራሱ ሰይጣን አጋጣሚዎችን በመጠቀም የእግዚአብሔር ሥራ ሊያደናቅፍ ይችላልና ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ስንሆን ሁልጊዜ የምንገኝባቸው ሁኔታዎች አመቺ ይሆናሉ ማለትም አይደለም። ይህንን ነገር በጳውሎስ አገልግሎት በሰፊው እናየዋለን።

የሐዋርያት ሥራ 16: 11-40 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 19:- ሀ) 1. ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች ከጢሮአዳ ወደ ፊሊጲስዩስ የሄዱት በምንድነው? 2. ፊሊጲስዩስ ምን ዓይነት ከተማ እንደሆነች አብራራ።

ለ) 1. በሰንበት ጳውሎስ ወዴት ሄደ? 2. በዚያ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች እነማን ናቸው?

ሐ) 1. ሊድያ ማናት? 2. የምትነግደው ምን ነበር? 3. ለጳውሎስ መልእክት የሰጠችው ምላሽ ምንድነው?

መ) 1. ገረዲ ትጠነቀል የነበረው እንዴት ነው? 2. ጳውሎስን እየተከተለች ጮኻ የምትናገረው ነገር ምንድነው? 3. የጥንቆላ ችሎታዋን እንድታጣ ያደረገው ነገር ምንድነው?

ሠ) ጳውሎስ በሮማዊ ዜግነቱ ምክንያት መብት እንዳለው የገለጸው ለምንድነው?

ራዕዩን ካዩ በኋላ ወዲያውኑ ጳውሎስ፥ ሲላስ፥ ጢሞቴዎስና ሉቃስ (አብሯቸው የሆነው በጢሮአዳ ነው) ተነሥተው ወደ ፊሊጵስዩስ በመርከብ ይሄዳሉ (ይህ ጉዞ የጳውሎስን ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ ከሚያሳየው ካርታ ላይ ተመልከት)። ንፋሱ ያግዛቸው ስለነበርም፥ ከእስያ ወደ አውሮፓ ለማቋረጥ የፈጀባቸው ጊዜ ሁለት ቀን ብቻ ነው።

የክርስቶስ ወንጌል የተሰበከባት የመጀመሪያዋ የአውሮፓ ከተማ ፊሊጲስዩስ፥ መቄዶንያ ውስጥ የምትገኝ የሮማ ቅኝ ግዛት ነበረች። ይህም በመሆኑ፥ ትመራ የነበረችው በሮማውያን ነው፤ ብዙዎቹም ነዋሪዎች የሮማ ዜጎች ናቸው ማለት ነው።

በሰንበት ቀንም ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች ለአምልኮ ወደ ወንዝ ዳር ይወጣሉ። ይህም፥ በዚህ የሮማ ቅኝ ግዛት ውስጥ ጥቂት አይሁዳውያን እንዳሉና ምንም ምኩራብ እንደሌለ ይገልጽልናል። ይህ ባይሆን ኖሮ፥ ጳውሎስ ለአምልኮ ይሄድ የነበረው ወደዚያ ነበር። በወንዙ አጠገብ እንደደረሱም የተሰበሰቡ ሴቶች ያገኙና ለእነሱ ይሰብኩላቸዋል። ከእነዚህ ሴቶች ውስጥ አንዷ እግዚአብሔርን የምታመልክ ሊድያ የምትባል ሴት ነበረች። በሆነ መንገድ ስለ እውነተኛው አምላክ ሰምታ፥ የጣዖት አምልኮ የተወች ናት። ምናልባትም ስለ እግዚአብሔር የሰማችው በትውልድ አገሯ ፀትያጥሮን ሳይሆን አይቀርም። በጣም ተሰሚነት የነበራት ስመጥሩ ሴት ነበረች።

ወንጌሉን እየሰማች ሳለ፥ እግዚአብሔር ቃሉን ታዳምጥ ዘንድ ልብዋን ይከፍትላታል፥ ከዚያም እርስዋም ቤተሰቦችዋም አምነው ይጠመቃሉ። በአውሮፓ የመጀመሪያዋ ክርስቲያን ሴት ናት። የመጀመሪያዋም የአውሮፓ ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በእርሷ ቤት ውስጥ ነው። እግዚአብሔር ምንም አድልዎ አያደርግም፤ ወንዶችንም ሴቶችንም በእኩል ዓይን ነው የሚያያቸው። እግዚአብሔርም በዚህች እሱን በምትፈራ ሴት በመጠቀም፥ በፊሊጵስዩስ ለወንጌሉ በሩን እንድትከፍትና ምናልባትም ጳውሎስ ከሚወዳቸው ቤተክርስቲያን አንዱን እንድትመሠርት ያደርጋል። ዛሬም ቢሆን፥ ወንጌልን በማስፋፋት ሥራ ውስጥ፥ ለሴቶች ዋነኛዎችን ቦታዎች ይሰጣቸዋል። አብያተ ክርስቲያናት ወንጌሉን በማስፋፋቱ ሥራ ላይ ዋነኛውን ድርሻ የሚሰጡት ወንዶች ናቸው ማለት ስሕተት ነው። በቀድሞውም ጊዜ ይሁን አሁንም እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማስፋፋት በሴቶች በጣም ነው የሚጠቀመው።

ጥያቄ 20፡- በቤተክርስቲያንህ፥ ወንጌልን በማስፋፋቱ ሥራ ውስጥ፥ ሴቶች ምን ዓይነት ሚና ነው የሚጫወቱት? የበለጠ ትልቅ ድርሻ ይዘው ሊሳተፉ የሚችሉት እንዴት ነው?

በፊሊጵስዩስ፥ በእርኩስ መንፈስ ታግዛ የምትጠነቁል አንዲት ገረድ ነበረች። እርስዋም ጳውሎስንና አብረውት የነበሩትን ሰዎች ከኋላ ከኋላ እየተከተለች «የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ እነዚህ የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው» እያለች ትጮህ ነበር። ሰይጣን እንኳ በእግዚአብሔር የተመረጡትን ሰዎች ያውቃቸዋል። ምንም እንኳ የሰይጣን ተከታይ ብትሆንም፥ እንደ እግዚአብሔር መልእክተኞች ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች የነበራቸውን ሥልጣን በይፋ እንድትናገር ሆኗል።

አንድ ቀንም ጳውሎስ በልጅቷ ውስጥ ያለውን ክፉ መንፈስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲወጣ ገሰፀው። መንፈሱም ልጅቷን ትቶ ወጣ፤ ከዚያም ወዲህ መተንበይ አልቻለችም። ጌቶችዋም ትርፍ እንደማታስገኝላቸው በተረዱ ጊዜ፥ በከተማው ውስጥ ሕጋዊ ያልሆነ ሃይማኖት በማስገባታቸው ጳውሎስንና ሲላስን ይከሷቸዋል። በዚያን ጊዜ፥ በሮማው መንግሥት ሕጋዊነት ያልተሰጠው ማንኛውም ሃይማኖት አይፈቀድም ነበር። ስለዚህ የፊሊጵስዩስ ሰዎች አዲስና ሕጋዊነት የሌለውን ሃይማኖት ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች በማስተዋወቃቸው ይከሷቸዋል። ከዚያም ጳውሎስና ሲላስን ወደ ገበያ በሹማምንት ፊት ይጎትቷቸዋል፤ በዚህም ጊዜ ሕዝቡ በእነሱ ላይ ይነሣል፤

መሪዎችም ልብሳቸውን ገፍፈው በበትር ይመቷቸው ዘንድ ገዥዎቹ ያስተላልፋሉ። ከተደበደቡም በኋላ ወደ ውስጠኛው ወኅኒ ጣሏቸውና እግራቸውን ከግንድ አጣብቀው ጠረቋቸው። በዚህን ጊዜ ጢሞቴዎስና ሉቃስ ለምን ወኅኒ ቤት እንዳልገቡ አናውቅም።

ጥያቄ 21፡- ጳውሎስና ሲላስን ወደ ፊሊጵስዩስ የመራው እግዚአብሔር ከሆነ፥ ይህ ስደት እንዲደርስባቸው ያደረገው ለምንድነው?

በሰው ዓይን ሲታይ፥ በክርስቲያኖቹ ላይ ትልቅ መዓት ነው የወረደባቸው። ቤተክርስቲያን ገና መመሥረቷ ነው፥ የክፉው መንፈስ መውጣት ለበለጠ ምስክርነት በር ከፍቶ ይሆናል፤ ታዲያ ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ ጳውሎስና ሲላስ ወደ ወኅኒ ይጣላሉ። እግዚአብሔርን ሳይጠይቁ፥ ሳይፈሩና ተስፋ ሳይቆርጡ አይቀርም። ሆኖም፥ ከመደብደብ የተነሣ ሰውነታቸው ቢጎትልም ሌሊቱን በሙሉ ጳውሎስና ሲላስ በምስጋና መዝሙር ለእግዚአብሔር ሲያዜሙ ቆዩ። እምነታቸውን የመሠረቱት በእግዚአብሔር ላይ ነው እንጂ፥ አሁን በተፈጠረው አጋጣሚ ላይ አልነበረም። እግዚአብሔር ወደ ወኅኒ እንዲጣሉ ያደረገውም ለተለየ ዓላማ እንደሆነ ተገንዝበዋል።

ሲያመሰግኑም ሳሉ፥ ድንገት የወኅኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ፤ በዚያን ጊዜም ድጆቹ ሁሉ ተከፈቱ፥ የሁሉም እስራት ተፈታ። የወኅኒውም ጠባቂ እሥረኞቹ በሙሉ አመለጡ ብሎ እራሱን ሊገድል ሰይፉን መዘዘ። በሮም ሥርዓት መሠረት፥ አንድ ጠባቂ እሥረኞቹ እንዲያመልጡ ካደረገ፥ ብዙ አሰቃይተውት ይገድሉት ነበር። ታዲያ እንዲህ ዓይነት ነገር ሲሆን፥ ከመሰቃየትና ከመሰደብ ብለው ብዙ ጊዜ ጠባቂዎቹ እራሳቸውን ይገድላሉ።

ጳውሎስም ጠባቂው እራስኑ ሊገድል እንደሆነ ባየ ጊዜ፥ «ሁላችንም በዚህ አለን፤ በእራስህ ክፉ አታድርግ።» ብሎ ይጮሃል። ጠባቂው ይህንን ሲሰማ እሥረኞቹን በሙሉ እግዚአብሔር ነፃ አውጥቶአቸው እንደነበር ተገነዘበ። እግዚአብሔር ሌሎቹን እሥረኞች እንዲያመልጡ ከልክሎአቸው ነበር። ጠባቂው እራሱን ገድሎ ቢሆን ኖሮ ሰይጣን በጣም ደስ ይለው ነበር፤ ሆኖም እግዚአብሔር ሌላ አላማ ነበረው። ጠባቂው ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔር በዜማ ሲያመሰግኑ ሰምቷል፤ በዚህም ምክንያት ሮጦ መጥቶ «እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» አላቸው።

ጥያቄ 22፡- አለቀለት በለህ የገመትኸውን ነገር እግዚአብሔር ለክብሩና ለሌሎች መዳን ሲጠቀምበት ያየኸው እንዴት ነው?

ጳውሎስና ሲላስም «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፤ አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ» ብለው ይመልሱለታል። አንድ ሰው ለመዳን ሲል ሥራ መሥራት የለበትም። እግዚአብሔር ሌሎችን ትቶ ይድኑ ዘንድ የሚመርጣቸው የተለዩ ሰዎች የሉም። የእግዚአብሔር የደኅንነት ተስፋ ቃል ለሁሉም ሰው ክፍት ነው። አንድ ኃጢአተኛ የፈለገውን ያህል ኃጢአተኛ ቢሆንም በእውነት ከልቡ ካመነ፥ እግዚአብሔር እንደሚያድነውና የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጠው ቃል ገብቷል።

ጥያቄ 23፡- ይህ ቁጥር፥ የወንጌሉን ዋነኛ ሐሳብ የሚገልጸው እንዴት ነው?

የእግዚአብሔር ፀጋ የጠባቂውን ልብ ያዘጋጀዋል፥ ከዚያም እሱና ቤተሰቦቹ ያምናሉ። ይህን ስንል፥ የጠባቂው እምነት ቤተሰቦቹን በሙሉ አድኖአቸዋል ማለታችን ሳይሆን የወንጌልን ቃል ሰምቶ ቤተሰቡ በሙሉ አመነ ማለታችን ነው። ባል ካመነ ሚስቱ ክርስቲያን ሆናለች ማለት አይደለም። ልጆቹም እንዲሁ ክርስቲያን ሊሆኑ አይችሉም። እምነት የሚወረስ ነገር አይደለም። እያንዳንዱ በቤተሰቡ ውስጥ የሚገኘው ሰው የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንዲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ መቀበል አለበት።

ጥያቄ 24፡- ሀ) አንዳንድ ሰዎች ቤተሰቦቻቸው ክርስቲያኖች ስለሆኑ እኛም ክርስቲያኖች ነን ብለው የሚያስቡት ለምንድነው? ለ) ወጣቱ በኢየሱስ ክርስቶስ የማመኑን ነገር በግሉ የሚያደርገው ምርጫ እንደሆነና በወላጆቹ እምነት ላይ መተማመን እንደሌለበት ቤተክርስቲያንህ በትምህርት መልክ ለማስተማር ስትል የምታደርገው ነገር ምንድነው?

ጥያቄ 25፡- በጳውሎስና ሲላስ የተነሣው ስደት ያስገኘው ውጤት ምንድነው?

የፊሊጵስዩስ ገዢዎች እንዲፈቱ መልእክት ሲልኩ፥ ጳውሎስ «እኛ የሮሜ ሰዎች ስንሆን ያለ ፍርድ በሕዝብ ፊት ደብድበው በወኅኒ ጣሉን፥ አሁንም በስውር ይጥሉናል፥ አይሆንም፤ ራሳቸው መጥተው ያውጡን» ይላል። አንድ የሮም ተወላጅን ያልፍርድ ማንገላታት ወይም ወደ ወኅኒ መክተት ትልቅ ወንጀል ነው። ሕጉንም በመጣሳቸው ሹማምንቶቹ ፈሩ። መጥተውም ከከተማ እንዲወጡ ለመኑአቸው።

ጥያቄ 26፡- የሮም ሰዎች መሆናቸውን ጳውሎስና ሲላስ መግለጻቸው በፊሊጲስዩስ ክብራቸውን በተመለከተ ያስገኘላቸው ነገር ምንድነው? ለቤተክርስቲያንስ ያስገኘው ነገር ምንድነው?

ጳውሎስና ሲላስ ከመደብደባቸውና ወደ ወኅኒ ከመጣላቸው በፊት ለምን የሮም ሰዎች መሆናቸውን እንዳልገለጹ የምናውቀው ነገር የለም። ምናልባትም ይህን ያደረጉት፥ ከእነርሱ ጋር ከነበሩት ውስጥ የሮም ሰዎች ያልነበሩትን ከእሥር ለማዳን ይሆናል። ወይም ደግሞ አዳዲሶች አማኞች ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል እንደ ምሣሌ አይተው እንዲከተሉት ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ጳውሎስና ሲላስ መጥተው ያውጡን ያሉት ክብራቸውን ለማስጠበቅ ሳይሆን፥ ለፊሊጲስዩስ ቤተክርስቲያን ሲሉ ንጹሕ መሆናቸውን በገዢዎቹ ፊት ለመግለጽ ስለፈለጉ ነው።

ጳውሎስና ሲላስም ወዲያውኑ ከፊሊጲስዩስ አልወጡም። ወደ ሊድያ ቤት ሄደው ወንድሞችን አግኝተው ካጽናኑ በኋላ ነው የሄዱት።

ጥያቄ 27፡- ሀ) ጳውሎስን የሚያጋጥሙት ነገሮች ሁሉ የሚያስደስቱ ነበሩን? ለ) በእነዚህ ሁኔታዎች እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው? ሐ) በመታሠሩ ምክንያት የተገኘው ውጤት ምንድነው?

የመጀመሪያዋ የአውሮፓ ቤተክርስቲያን የሮማ ቅኝ በነበረችው በፊሊጲስዩስ ተቋቋመች። ምንም ትንሽ ብትሆንም፥ ጳውሎስ ከሚወዳቸው ቤተክርስቲያናት ውስጥ አንዷ ነበረች። ወደ ፊሊጵሲዩስ ሰዎች ከጻፈው መልእክት እንደምንረዳውም፥

ጳውሎስ የወንጌል ማዳረሱን ሥራ ለማስፈጸሚያ የሚሆነውን ዕርዳታ ከዚህች ቤተክርስቲያን ብቻ እንዲሰጠው አድርጓል።

## አምስተኛ ቀን፡- ክለሳ

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

1. ጳውሎስና ሲላስ ይዘው የሄዱትና ለአማኞቹ የሰጡት መልእክት የትኛው ነው?
2. ሕይወቱን ሙሉ የጳውሎስ አጋዥ ሆኖ የሠራው ወጣት ደቀመዝሙር ማነው?
3. ጢሞቴዎስ የተገረዘው ለምንድነው?
4. የጢሞቴዎስን ባሕሪ አብራራው። እግዚአብሔር በሁሉም ዓይነት ባህሪ ይጠቀማልን?
5. ጳውሎስና ሲላስ እንዳይገቡ የተከለከሉባቸው ሦስት አገሮች ምን ምንድናቸው?
6. በጢሮአዳ ሳለ ጳውሎስ የተቀበለው ምሪት ምን የሚል ነው?
7. በጢሮአዳ ሳሉ ከጳውሎስ፥ ከሲላስና ከጢሞቴዎስ ጋር አብሮ የነበረው ሰው ማነው? ስሙ ባለመጠቀሱ ምክንያት፥ ለዚህ ማስረጃ የሚሆነን ነገር ምንድነው?
8. ዛሬ ከሚገኙት ክፍለ ዓለማት ውስጥ መቄዶንያ ትገኝ የነበረው በየትኛው ክፍለ ዓለም ነው?
9. እግዚአብሔር ጳውሎስን ወደ አንዳንድ ቦታዎች እንዳይሄድ ያገደው ለምን ይመስልሃል?
10. የእግዚአብሔርን ፈቃድና ምሪት እንድናውቅ የሚረዱን አምስት ደረጃዎች ምን ምንድናቸው?
11. ከክርስቶስ ጋር በጸሎትና በቃሉ አማካኝነት ኅብረት ማድረጉ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?
12. በመቄዶንያ ውስጥ በመጀመሪያ ክርስቶስን የተቀበለው ሰው ማነው?
13. ጳውሎስ፥ እሱንና ሲላስን ገዢዎቹ መጥተው እንዲፈቷቸው የፈለገው ለምንድነው?
14. ሀ) ጠባቂውን እንዲያምን ያደረገው ነገር ምንድነው? ለ) የእርሱ ውሳኔ እውነተኛ መሆኑ በሕይወቱ የተገለጸው እንዴት ነው?
15. ደኅንነትህ በጌታ ሐሤት እንዲኖርህ ያደርግሃል ወይም?

ለሳምንታዊው ስብሰባ ለመዘጋጀት በመጀመሪያ ሳምንታዊውን የመወያያ ጥያቄ ተመልከት።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የክ፡ምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. ክለሳ

4. የመወያያ ጥያቄዎች፡-

ሀ) 1. ነባር የቤተክርስቲያን መሪዎች ወጣት መሪዎችን ማሰልጠን ያለባቸው ለምንድነው? 2. ይህ በቤተክርስቲያንህ ውስጥ የሚሠራው እንዴት ነው? 3. አንዳንድ መሪዎች በደንብ የተማሩ ወጣት መሪዎችን የሚፈሩት ለምንድነው? 4. የወደፊቶቹን መሪዎች ቤተክርስቲያንህ በተሻለ መንገድ ልታሰለጥን የምትችለው እንዴት ነው?

ለ) የቤተክርስቲያን መሪዎችን የመምረጥ፥ ወንጌላውያንን የመላክና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን ዕቅድ ማውጣትን በተመለከት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምትወስኑት እንዴት ነው?

ሐ) 1. የመጀመሪያዋ አውሮፓዊ አማኝ ሴት የሆነችው ለምንድነው? 2. በቤተክርስቲያንህ አገልግሎት ውስጥ ሴቶች የሚጫወቱት ሚና ምንድነው? 3. በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመመሥረት፥ የእነርሱን ድርሻ (አገልግሎት) ሰፋ ማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው? 5. ጸሎት

# ትምህርት 13

## የሐዋርያት ሥራ 17፡ 1-18፡ 17

## የመጀመሪያ ቀን፡-የሐዋርያት ሥራ 17፡ 1-9

ከ 49-52 ዓ.ም ድረስ የተደረገው የጳውሎስ ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ፥ ወንጌሉን በማሰራጨቱ ረገድ ትልቅ እመርታ የታየበት ጊዜ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜም ወንጌሉ በአውሮፓ ሲገባ፥ የተለወጠችው ሊድያ የምትባል ሴት ነበረች። በኋላ ላይም እግዚአብሔር ወንጌልን አጽንቶ ለመላው ዓለም እንዲዳረስ ያደረገው ከአውሮፓ ነው። ይሁን እንጂ፥ ጳውሎስና ሲላስ ታስረው ወደ ወኅኒ ሲጣሉ ተቃውሞ ተነሥቶበታል። ታዲያ ልብሳቸው ተገፎ ቢገረፉም፥ ወደ ወኅኒ ቢጣሉም፥ የወንጌሉ ምሥክርነት አልቆመም። በዚህም ምሥክርነታቸው ምክንያት ጠባቂውና ቤተሰቡ ያምናሉ። በመጨረሻም ጳውሎስና ሲላስ አገሪቷን ለቀው እንዲወጡ ቢገደዱም፥ የተወሰኑ ክርስቲያኖችን በዚያ ትተው ነው የወጡት።

ጳውሎስ በሄደበት ቦታ ሁሉ ስደት አጋጥሞታል፤ ሆኖም፥ ከአንድ ከተማ ለቆ እንዲወጣ እስከተገደደበት ጊዜ ድረስ ስደቱ ከምሥክርነቱ ገሸሽ አላደረገውም። ከማያምኑ አሕዛብ የሚነሣው ተቃውሞ፥ በግልጽ የሚደረግና ኃይለኛ የሆነ ነበር፤ ነገር ግን የራሱ ሕዝቦች ከሆኑት ከአይሁዳውያን ከተቀበለው ተቃውሞ በጣም የተሻለና ሊቋቋመው የሚችለው ነበር። ምንም እንኳ ጳውሎስ በአሕዛብ ከተሞች ውስጥ ቢሆንም፥ በከተማው አንድ ምኩራብ ካለ የእራሱን ሕዝቦች ፍለጋ መጀመሪያ ይሄድ የነበረው ወደዚያ ነበር።

ጥያቄ 1:- የሐዋርያት ሥራ 17-18፡ 17 አንብብ። ጳውሎስ የሄደባቸውን ከተሞች በሙሉ ጻፍና በየከተማዎች የተደረጉትን ዋና ዋና ነገሮች በዝርዝር ጥቀስ።

የሐዋርያት ሥራ 17፡ 1-9 አንብብና እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 2:- ሀ) በተሰሎንቄ ውስጥ ጳውሎስ መጀመሪያ ሄዶ የሰበከው የት ነው? ለ) የጳውሎስ መልእክት ይዘቱ ምን ነበር? ሐ) ጳውሎስ የተቃወመው ማንን ነው? የተቃወመውስ ለምንድነው?

ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች፥ የምዕራቡን አቅጣጫ ይዘው በአንድ በታወቀ መንገድ በኩል በመሄድ ወደ ተሰሎንቄ ይገባሉ። በአሁን ጊዜ ሉቃስ እራሱን በትረካው ላይ ስላላስገባ፥ ለሆነ ጉዳይ ወደ ኋላ በፊሊጵስዩስ የቆየ ይመስላል። ይህንንም የምናውቀው፥ ከሐዋርያት ሥራ 17፡ 17 አንሥቶ «እኛ» የሚለውን ቃል ትቶ «እነሱ» የሚል ቃል በመጠቀሙ ነው። ምናልባትም ወደ ኋላ የቀረው አዲሷን ቤተክርስቲያን ለመመሥረትና በእምነት ለማሳደግ ይሆናል።

ጳውሎስና ጓደኞቹ በአንፊጶልና በአጶሎንያ ሳይቆዩ ዝም ብለው ያለፉት ምናልባት የአይሁድ ምኩራቦች ባለመኖራቸው ይሆናል። በተሰሎንቄም ሲደርሱ ጳውሎስ በዚያ ቆም ብሎ ይሰብካል። በመጀመሪያ በሦስት ሰንበቶች ላይ በምኩራቡ በመገኘት ከብሉይ ኪዳን እየጠቀሰ ትርጉም በመስጠት ያስረዳ ነበር። በዚህም ላይ በመመሥረት ኢየሱስ እራሱ ክርስቶስ እንደሆነና መከራ ተቀብሎ ከሞተ በኋላ ከሙታን መነሣቱ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል።

ጥያቄ 3:- ለዚህ ሐሳብ እንደማስረጃ የጠቀሰው የትኛውን ጥቅስ ይመስልሃል? (እስቲ ትንቢተ ኢሳይያስ 52፡ 13-53፡ 12 ተመልከት)።

ለማያምኑ ሰዎች ስንመሠክር፥ የራሳችንን ቃል ወይም ዘይቤ ተጠቅመን ማስረዳት እንደሌለብን ልናስተውል ይገባል። የማዳን ኃይል ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ፥ የኛ ቃላት መደርደር አይደለም። ወንጌሉንም ለሌሎች ለማካፈል ሲባል፥ መጽሐፍቅዱስን በደንብ ማወቅ አለብን።

ጥያቄ 4 :-ለማያምኑ ሰዎች ስትመሠክር የምትጠቀምባቸውን ጥቅሶች እስቲ በዝርዝር ጻፍ። ከእነዚህ ውስጥ ስንቱን በቃልህ ታውቃቸዋለህ? ሁልጊዜ ለሰዎች ስለ ኢየሱስ ለመመሥከር ዝግጁ እንድትሆን ዋና ዋናዎችን ጥቅሶች ማጥናት አለብህ።

ጳውሎስ ለተወሰነ ጊዜ በተሰሎንቄ ይቆያል። ከዚያም ተነሥቶ ከሄደ በኋላ ትንሽ ቆይቶ ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ፥ ከእናንተ በአንዱ ላይ ሸክም እንዳልሆንባችሁ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በራሴ እጅ እየሠራሁ ነው የኖርኩት ይላቸዋል (ተሰ 2፡ 9)። ይህንንም ሲል፥ እንዲመግቡት፥ እንዲያለብሱትና ደመወዝ እንዲሰጡት እነሱን ከመጠየቅ፥ ይሠራ በነበረው የድንኳን ስፌት ሥራ እራሱንና አብረውት የነበሩትን ሰዎች ይደጉም እንደነበር መግለጹ ነው። ጳውሎስ በእጁ በመሥራቱ፥ ምንም ዓይነት ሐፍረት አይሰማውም ነበር።

አንዳንድ አይሁዳውያን፥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ግሪካውያንና አንዳንድ የታወቁ ሴቶች (ሃብታም የሆኑ ወይም ደግሞ የመሪዎች ሚስቶች ሆነው በሕዝቡ ዘንድ የተከበሩ ሴቶች) በኢየሱስ ሲያምኑ አይሁዳውያን በጣም ይቀኑና በክርስቲያኖች ላይ ስደት ይቀሰቅሱ ነበር።

በዚህ ጊዜ ውስጥ፥ ጳውሎስ ተቀምጦ የነበረው ኢያሶን ይባል የነበረ ሰው ቤት ውስጥ ነበር። ምናልባትም የኢያሶን ቤት ለአማኞች መሰብሰቢያ ቦታ ሳይሆን አይቀርም። ቀናተኞቹ አይሁዳውያን ሥራ ፈት የሆኑ ክፉ ሰዎችን ይሰበስቡና፥ ጳውሎስንና ጓደኞቹን የከተማውን ሰላም አውከዋል ብለው ለመክሰስ ሲሉ፥ ከተማውን አሸበሩት። ጳውሎስን ፍለጋም ወደ ኢያሶን ቤት ፈጥነው ይሄዳሉ፤ ሆኖም ጳውሎስን በዚያ ያጡታል። በዚህም ጊዜ ኢያሶንና ሌሎች ወንድሞችን ጎትተው ወደ ከተማዋ አለቆች ይወስዷቸዋል። ኢያኮንንም የሮማውን ግዛት ያወኩትን ተቀብሏል ብለው ይከሱታል። ይህ ክስ እውነት መሆኑ ከተረጋገጠ ጳውሎስንና ተከታዮቹን ለሞት ፍርድ የሚያደርሳቸው ነው። ሆኖም፥ የከተማዋ አለቆች ሐሰት እንደሆነ አረጋግጠዋል። ይህም ቢሆን ግን፥ በእነሱ የተነሣ ከአሁን ወዲያ ብጥብጥ እንዳይነሣ ሲባል፥ ኢያሶንና ሌሎች ክርስቲያኖች ዋስ አቅርበው እንዲለቀቁ አድርገዋል።

አሁንም እንደገና ጳውሎስ የገዛ ሕዝቡ በሆኑት አይሁዳውያን ተሰሎንቄን በግድ ለቅቆ እንዲሄድ ተደረገ። ምናልባትም ጳውሎስ ወገኖቹ አይሁዳውያን የገዛ መሢሐቸውን ደጋግመው ከሚክዱት ይልቅ፥ አረመኔ በሆኑ አሕዛብ መገረፉ የሚቀል መስሎ ሳይታየው አይቀርም። እስከ ዛሬ ድረስ፥ መጽሐፍ ቅዱስን መርምረው ለማወቅ የሚሹ አይሁዳውያን በጣም ጥቂቶች ናቸው። ብዙዎቹም የራሳቸው የሆነውን የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ አይቀበሉትም፤ የአይሁድ አርቶዶክሶችም ቢሆኑ መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ አያውቁትም። በአፈ ታሪክ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ባህል፥ እውነተኛውን ቃል እንዳያዩ ዓይኖቻቸውን አሳውሮታል። መረዳትም የሚችሉት፥ መንፈሳዊ ዓይኖቻቸውን የጋረደው ነገር ሲነሣ ብቻ ነው (2ቆሮ. 3፡ 13-16 ተመልከት)።

ብዙ ጊዜ ለማመን በሚፈልጉ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ የሚያሥነሡትም የገዛ ቤተሰቦቻቸውና የቅርብ ዘመዶቻቸው ናቸው።

የጳውሎስ፥ የሲላስና የጢሞቴዎስ አገልግሎት፥ ያለምንም ውጤት እንዲሁ መና አልቀረም። ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጻፈው መልእክቱ ውስጥ «ከእናንተ ወጥቶ የጌታ ቃል በመቄዶንያና በአካይያ ብቻ አልተሰማምና፤ በእግዚአብሔርም ዘንድ የሚሆን እምነታችሁ በሁሉ ሥፍራ ተወርቷል ብሎ ያሞካሻቸዋል። (1ተሰሎ. 1፡ 8)።

ጥያቄ 5፡- በሌሎች ከመነቀፍ ይልቅ፥ በራሳችን ሕዝቦች መነቀፉ በጣም ከባድ የሚሆነው ለምንድነው?

ጥያቄ 6፡- ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ የወንጌሉን ምሥክርነት የሚቃወሙ ሰዎች እነማን ናቸው? ለ) ለምን የሚቃወሙት ይመሥልሃል?

ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ለመመለስ በጣም ይፈልግ ነበር፤ ሆኖም በመልእክቱ ላይ እንደጠቀሰው «ሰይጣን አዘገይቶታል» (2ተሰ. 2፡ 18)። ምናልባትም እንዲዘገይ ያደረገው የተሰሎንቄ ጓደኞቹ አንድ እንዲፈጽሙ የሰጡት ግዴታ በመኖሩ ይሆናል።

ጥያቄ 7፡- በተሰሎንቄ አገልግሎቱ ውስጥ ጳውሎስ በ1ቆሮ 15፡ 58 ላይ የጠቀሰው ነገር እውን የሆነው እንዴት ነው?

ጥያቄ 8፡- ብዙ ጊዜ ምሥክርነታችንን የምንሰጥበት ጊዜ በጣም አጭር ስለሚሆን፥ ቀደም ብለን ማድረግ የሚገባን ነገር ምንድነው?

በአውሮፓ ውስጥ ለወንጌሉ በሮች እየተከፈቱ ነው። በፊሊጲስዩስና በተሰሎንቄ የተሰባሰቡት ጥቂት አማኞችም የቤተክርስቲያኒቱ ዋናዎች ሆነዋል። ወዲያውኑም ወንጌሉ በየአካባቢው ባሉ አገሮች ይሰራጫል። ጳውሎስ ገና ሥራውን ሊጀምር ሲል፥ እንዲወጣ በመደረጉ ተስፋ ሳይቆርጥ አልቀረም። ይህ ነገርም ብዙ ጊዜ ተደጋግሟል፤ ሆኖም፥ የወንጌሉ ኃይል የጳውሎስ ወይም የሌላ ሳይሆን የእግዚአብሔር እንደሆነ የሚያመለክት ነው። ቤተክርስቲያን እንድታድግ የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው እንጂ የሰዎች ሥራ ብቻ አይደለም።

ጥያቄ 9፡- ይህ ትምህርት፥ በሥራቸው ላይ ሳሉ፥ የቤተክርስቲያን መሪዎች ሊያውቁት የሚገባ ዋነኛ ትምህርት የሚሆነው እንዴት ነው?

## ሁለተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 17፡ 10-15

ጳውሎስ ለአይሁዳውያን ሲመሠክር፥ ከብሉይ ኪዳን ላይ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዕቅድ በመጥቀስ፥ ይህ እንዴት በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጸመ ይገልጽላቸዋል። ታዲያ ብዙ ጊዜ፥ ኢየሱስ እነዚህን ትንቢቶች ፈጽሟል ብለው አይቀበሉትም። ሆኖም፥ አሁን ደግሞ ጳውሎስ የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሉ ብሉይ ኪዳንን ለመመርመር ዝግጁ የሆኑ አይሁዳውያን ያጋጥሙታል።

የሐዋርያት ሥራ 17፡ 10-15 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 10፡- ሀ) 1. ክርስቲያን ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን ወደ የት ነው የላኳቸው? 2. በዚያ ሲደርሱ መጀመሪያ የሄዱት ወዴት ነው?

ለ) 1. ጳውሎስ ከዚህ በፊት ካስተማራቸው አይሁዳውያን የቤርያዎቹ አይሁዳውያን ለየት የሚሉት እንዴት ነው? 2. ያመኑት እነማን ናቸው?

ሐ) በቤርያ ተቃውሞ የተቀሰቀሰው ከየት ነው?

መ) 1. ጳውሎስ ምን ሆነ? 2. ጢሞቴዎስና ሲላስስ?

በተሰሎንቄ ኹከት ሲነሣ ክርስቲያን ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ይሰዷቸዋል። ይህችም ከተማ በደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ በ 80 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የምትገኝ ናት።

ቤርያ ውስጥ የሚኖሩ አይሁዳውያን ስለነበሩ ጳውሎስ በመጀመሪያ ተነሥቶ ለመስበክ ወደ አይሁዶች ምኩራብ ይሄዳል። በዚያም የነበሩት አይሁዳውያን በሌሎች ከተሞች ከነበሩት ልበ ሰፊዎች ሆነው ያገኛቸዋል። የሚናገረውን ከሰሙ በኋላ፥ ጳውሎስ የሚናገረው ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሉ፥ የተናገረውን ነገር ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጋር ያነፃፅሩ ነበር። ለጳውሎስም፥ ይህ ለየት ያለ ምላሽ ነው። እንዲያውም የቤሪያ ሰዎች ማንም ሰው መጥቶ የሚነግራቸውን ሁሉ ሰምተው የሚቀበሉ ሰዎች ሳይሆኑ የጳውሎስንም ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር መስማማቱን በማነፃፀራቸው ሉቃስ ያሞግሳቸዋል።

ጥያቄ 11፡- ይህንን ለየት ያለ ባህሪ ዛሬ እኛም መከተል ያለብን ለምንድነው?

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሳያነፃፅሩ ወንጌላውያን ወይም የቤተክርስቲያን መሪዎች የተናገሩትን ነገር ዝም ብለው ይቀበላሉ። በዚህም ምክንያት፥ በቀላሉ ሐሰተኛ አስተማሪዎች አማኞችን ከቤተክርስቲያን ይሰርቃሉ። ጥሩ ሆኖ የሚሰሟቸውን ነገር እውነትም ይሁን ውሸት ይቀበላሉ። ሰዎች ቆመው ሲያስተምሩ እውነቱን ከውሸት ለመለየት እንድንችል ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት አለብን (ዕብ 5፡ 14 ተመልከት)።

ጥያቄ 12፡- ሀ) እውነቱን ለማወቅ ስትል፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንደምታጠና ግለጽ። ለ) በዚህ የአጠናን ዘዴ በመጠቀም በቤተክርስቲያንህ ቆመው የሚያስተምሩትን ወንጌላውያንና መጋቢዎች ትምህርት የምትመረምረው እንዴት ነው? ሐ) ይህን በማድረግ ያገኘኸው የሀሰት ትምህርት አለ? መ) የሀሰት ትምህርት ሲሰበክ የምታደርገው ምንድነው?

ቤርያውያን የእግዚአብሔርን ቃል በጣም ተጠምተው ስለነበር፥ ዕለት ዕለት ተሰብስበው ጳውሎስ የሚያስተምረውን ትምህርት ይሰሙ ነበር። አንዳንድ አይሁዳውያንና የከበሩ የግሪክ ሴቶችና ወንዶችም አመኑ። ዘሩ በአንድ ሌላ የአውሮፓ ከተማ ውስጥ ተተከለ፤ ቤተክርስቲያንም ተመሥርታ ወንጌሉ እየተስፋፋ ሄደ።

ካላመኑት የቤርያ አይሁዶች መካከል በጳውሎስና በሲላስ ላይ የተነሣ ተቃውሞ ያለ አይመስልም። ዳሩ ግን ኹከት የተነሣው በተሰሎንቄ የነበሩት አይሁዳውያን ጳውሎስ በቤርያ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሰበከ ሲሰሙ ነው። ልክ በተሰሎንቄ እንዳደረጉትም እዚያ ድረስ በመምጣት ህዝቡን ቀሰቀሱና ኹከት ፈጠሩ።

አሁንም ተቃውሞ የተነሣው በጳውሎስ ላይ በመሆኑ ወንድሞች ቶሎ ብለው ወደ አቴና የሚሄድ መርከብ ወደሚያገኝበት ባሕር ዳርቻ ይልኩታል። (የጳውሎስን ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ የሚያሳየውን ካርታ ተመልከት)። እስከ አቴናም ድረስ የሸኙት ቤሪያውያን ወንድሞች ናቸው።

ሲላስና ጢሞቴዎስ ደግሞ አዳዲሶቹን ክርስቲያኖች ለማስተማርና ለማደራጀት ሲባል በዚያው በቤርያ ይቆያሉ። ጳውሎስን በአቴና ሳለ በጣም ብቸኝነት ሳይሰማው አልቀረም፤ በዚህም ምክንያት ሲላስና ጢሞቴዎስ ፈጥነው እንዲመጡ በሸኙት ሰዎች በኩል ይልክባቸዋል።

ሲላስና ጢሞቴዎስ ወደ አቴና ከሄዱ በኋላ፥ ተመልሰው ወደ መቄዶንያ፥ ምናልባትም ወደ ፊሊጵስዩስና ተሰሎንቄ ተልከው ከዚያ በኋላ ከጳውሎስ ጋር በቆሮንቶስ የተገናኙ ይመስላል (ሐዋ. 18፡ 5 እና 1ተሰ. 3፡ 1-6)።

በእነዚህ ፅኑ ተቃውሞ በነበረባቸው ከተሞች ውስጥ እንዴት ጠንካራ ቤተክርስቲያኖች ሊመሠረቱ እንደቻሉ ማየቱ የሚደንቅ ነው። ብዙ ጊዜም ቤተክርስቲያን በደንብ ጠንክራና ጥሩ ሆና የምትመሠረተው ስደት ባለበት ጊዜ እንደሆነና በሰላም ጊዜ እንዳልሆነ ይመስላል። ስለዚህም፥ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሁሌ ምንም ዓይነት ግጭት ውስጥ ሳንገባ ነገሮችን በሰላም ያሳልፈናል ማለት አይደለም።

ጥያቄ 13፡- ይህ እውነታ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያናት ሲገለጥ ያየኸቸው እንዴት ነው? አሕዛብ ወንጌሉን ለመቀበል እንደዚህ የሚጓጉት ለምንድነው?

እግዚአብሔር አሕዛብ መልእክቱን እንዲቀበሉ አዘጋጅቷቸዋል። ለብዙ ምዕተ ዓመታት ግሪኮችና አሕዛብ ከሰው የሚይሻሉ አማልክት እንዳሉ ነበር ሲማሩ የቆዩት። ብዙ ጊዜ የእነሱ ምስል ደካማና ጧች የሆኑ ሰዎችን የሚመስል ነበር፤ በተጨማሪም የሕይወት ታሪካቸው ከራሱ ከሕዝቡ የሕይወት ታሪክ ባነሰ በጉስቁልና ኑሮ የተሞላ ነበር። በዚህም ምክንያት፥ ብዙ አሕዛብ ስለ ሃይማኖታቸው እውነተኛነት ጥያቄ መጠየቅ ይጀምራሉ። ስለ አንድ ጻድቅ፥ ቅዱስና አፍቃሪ የሆነው የአይሁድ አምላክ ሲሰሙም፥ አሁን ስለ እውነተኛው አምላክ እንደሚነገር ተገነዘቡ። ታዲያ ይህም ቢሆን፥ እግዚአብሔርን ማምለክ ከፈለጉ አይሁዳውያን እንዲያሟሏቸው የሚጠይቋቸው ሕጋጋት በጣም ብዙ ስለነበሩ፥ ከአምልኮው ታገዱ። ጳውሎስ አይሁዳውያን የሚጠብቋቸውን ልማዶች እንደ ሕግ መጠበቅ እንደማያስፈልግ ገልጾ በፀጋ የተገኘውን የደኅንነት ወንጌል ይዞላቸው ሲመጣ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው አመኑ። በተለይ የከበሩት የግሪክ ሴቶች በባህላቸው ትልቅ ተጽዕኖ ይደረግባቸው ስለነበርና ወንጌሉ ደግሞ ከዚህ ነፃ አውጥቶ በመካከላቸው ፍቅር እንዲኖር ስለሚያደርግ፥ ቶሎ ብለው ወንጌሉን ተቀበሉት። በጥቂት ዓመታትም ውስጥ፥ ቤተክርስቲያን ከኢየሩሳሌም ተነሥታ ወደ ሮም ብሎም ወደ ሌሎች ቦታዎች እየተስፋፋች ሄደች።

ከመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች አንዱ፥ ሰዎች ወንጌልን እንዲቀበሉ ልባቸውን ማዘጋጀት ነው። የሰዎች ልብ ተከፍቶ እስካልለሰለሰ ድረስ፥ የፈለገውን ያህል ቢመሠክርላቸው እውነቱን አይቀበሉትም። ብዙ ጊዜም መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ልብ የሚያለሰልሰው አሁን በሚከተሉት ሃይማኖት እርካታ እንዳይኖራቸው በማድረግና ውስጣዊ ሰላማቸውን በመውሰድ ወይም ትልቅ መከራ በሕይወታቸው በማምጣት ነው። እግዚአብሔር ላዘጋጃቸው ሰዎች እንድንመሠክር፥ በሌሎች ሰዎች ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚሠራውን ሥራ ቀረብ ብለን ልንከታተለው ይገባል።

ጥያቄ 14፡- የማያምኑትን ሰዎች ገና ሳይመሠክርላቸውም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ለወንጌል ሲያዘጋጃቸው ያየኸው በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው?

ወንጌል በድል እንዳይወጣ በጣም የሚያስቸግሩ ቦታዎች:- የሚከተሉት የአምልኮ ሥርዓት በቂ ነው ብለው በሚገምቱ ሰዎች ወይም ቤተክርስቲያናት ውስጥ ነው። ይህም ነገር፥ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዦች እንሆንም ብለው ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት አማካኝነት የሚያደርጉትን ኅብረት ሲያቆሙ፥ በየትኛው ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊከሰት የሚችል ነገር ነው። ወይም ደግሞ በነገው ትምህርታችን ላይ እንደምናየው፥ በትምህርታቸው ወይም በባህላቸው በሚኮሩ ሰዎች መካከልም ሊከሰት ይችላል።

# ሦስተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 17: 16-34

በስደት ምክንያት በተሰሎንቄና በቤሪያ የነበረውን ፍሬያማ አገልግሎት በመተው፥ ጳውሎስ ወደ አቴና ከተማ ይሄዳል። በዚያም ብቻውን ቢሆንም እንኳ ዝም ብሎ አልተቀመጠም። የሚመሠክርላቸው ሰዎችጋ እየዞረ ይፈልግ ነበር። በዚህም መሠረት፥ ጳውሎስ ለግሪክ ፈላስፎች ንግግር ያደርጋል። ጳውሎስ ፈላስፎቹን ለማሳመን ሲል፥ ባደረገው ንግግርም ውስጥ ምን ያህል ዕውቀት እንዳለው በግልፅ ይታያል።

በሮማው መንግሥት ግዛቶች ብዙ የአሕዛብ አማልክት ነበሩ። ብዙ አሕዛብም አይሁዳውያን አንድ አምላክ ብቻ በማምለካቸው ምክንያት ወደ አይሁዳውያን ሃይማኖት ይገቡ ነበር። ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይዞ ሲመጣም በመጀመሪያ ያመኑት እነዚህ ሰዎች ናቸው። በዚህ ከላይ በጠቀስነው ክፍልም ውስጥ ጳውሎስ ለጥንቷ ዓለም ፈላስፎች የሰጠውን ምሥክርነትና በከተማው ውስጥ ስለነበሩት ልማዶች የሰጠውን ምላሽ እናያለን።

የሐዋርያት ሥራ 17: 16-34 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 16:- ሀ) 1. ጳውሎስ በአቴን እነማንን ነበር የሚጠብቀው?
2. ጳውሎስን ያበሳጨው ነገር ምንድነው?

ለ) 1. ጳውሎስ በምኩራብ ውስጥ ምን ነበር የሚያደርገው? 2. በገበያው ቦታስ ምን ያደርግ ነበር?

ሐ) 1. ጳውሎስ ያነጋገራቸው ሰዎች የሚያራምዱቸው ሁለቱ ፍልስፍናዎች የሚጠሩበት ስም ምንድነው? 2. ፈላስፎቹ ጳውሎስን ወዴት ወሰዱት?

መ) 1. ጳውሎስ ምን በማለት ነው መልእክቱን የሚጀምረው? 2. ጳውሎስ እነግራችኋለሁ ያላቸው ስለምንድነው? 3. ከጳውሎስ መልእክት ውስጥ እስቲ ሦስት ዋና ዋና ነጥቦችን ጥቀስ። 4. አንዳንዶቹ ያፌዙበት ሌሎቹ ደግሞ እንሰማለን ያሉት የትኛው ነጥብ ላይ ሲደርስ ነው?

ከቤሪያ ወደ አቴና ሄዶ ሲላስና ጢሞቴዎስን በሚጠባበቅበት ሰዓት፥ ጳውሎስ ለአይሁዳውያንና ለአሕዛብ መመሥከሩን አላቆመም። በምኩራቡ ውስጥ፥ ለአንዳንድ አይሁዳውያንና አብሯቸው ያመልኩ ለነበሩ አሕዛብ፥ በገበያ ቦታ ደግሞ፥ ለመስማት ፈቃደኞች ለሆኑ ሁሉ መሠከረ።

በጥንቱ ዓለም በጣም ከታወቁት ከተሞች አንዷ አቴና ናት። በግሪክ ዘመነ መንግሥት ይህቺ ከተማ ዋነኛዋ የዓለም ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ማዕከል ነበረች። ሮማዊያን የዓለም የኃይል ሚዛን ከጨበጠ በኋላም እንኳ እንደበፊቱም ባይሆን፥ ማዕከልነቷን ሙሉ በሙሉ አላጣችም። በጳውሎስ ጊዜ ደግሞ ለብዙ አማልክት የተሠሩ ውብ ሕንፃዎች-የሚገኙባት የሃይማኖት ማዕከል ነበረች። ድንገት መታወቅ ካለባቸው አማልክት የዘነጉት እንዳይኖር፥ «ለማይታወቅ አምላክ» መሠዊያ የሚል ጽሑፍ ያለበት መሠዊያም እስከመሥራት ደርሰዋል። ከዚህም በላይ አቴና በጥንቱ ዓለም ውስጥ የነበሩት ታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙባት ለዓለም የዕውቀት ማዕከል የነበረች ከተማ ናት። በዚህች ከተማ ማንም ሰው የመናገር ነፃነት ስለነበረው ብዙ ትምህርት ቤቶችና ፍልስፍናዎችን ነበሩ። እንደዛሬዎቹ ሀገሮች አቴናም ብትሆን በቅርሳ ቅርሶቹ በባህሏ በትምህርቷ ወዘተ ... በጣም ትኮራ ነበር። መንፈሳዊ ሁኔታ በተመለከተ ግን ሕዝቦችዋ ኩሩዎች ስለነበሩ የወንጌል ረሐብ የሚሰማት ከተማ አለነበረችም።

ጥያቄ 17:- ታላቅ ታሪክ፥ ብዙ ትምህርትና የሚመኩበት ነገር ያላቸው ሀገሮች ወንጌሉን መቀበል የሚከብድባቸው ለምን ይመስልሃል?

በገበያ ቦታ ከኤፊቆሮስ ወገንና ኢስጦኢኮች የተባሉ ፈላስፎች የጳውሎስን መልእክት ተጠራጠሩት።

የኤፊቆሮስ ፈላስፎች በትምህርት ቤታቸው እግዚአብሔር የለም ብለው የሚያስተምሩና በእግዚአብሔር የማያምኑ ሰዎች ናቸው። የመኖር ዋና ዓላማ እራስን ማስደሰት ነው ብለው ነበር የሚያስተምሩት። በእነርሱ መመዘኛ የሚያስደስት ነገር ጥሩ ሲሆን ችግር የሚፈጥር ነገር ደግሞ እርኩስ ነገር ነው። ዓለም አንድ አምላክ የሠራት የፈጠራ ሥራ ሳትሆን፥ በድንገት የተለያዩ ንጥረ ነገሮች በመደባለቃቸው ምክንያት የተገኘች ነገር ናት ብለው ነው የሚያስተምሩት። ከምድራዊ ሕይወታቸው በኋላ ፍርድ ወይም ሌላ ሕይወት አለ ብለው ስለማያስቡ «እባካችሁ እንብላ እንጠጣ፤ ነገ እንደሆን እንሞታለን» ነበር የሚሉት። በዚህም ላይ በጣም ኩሩዎችና እራሳቸውን ጻድቃን ነን ብለው የሚቆጥሩ ናቸው።

ጥያቄ 18:- ይህ ፍልስፍና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያራምዱ ሰዎችን ታውቃለህ?

ኢስጦኢኮች:- እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ውስጥ አለ፤ እግዚአብሔር የሚለው ሁሉም ነገር በአጠቃላይ ነው ይላሉ። ይህን ሲሉ እግዚአብሔር በድንጋይ፥ በዛፍ፥ በከዋክብት፥ ወዘተ... ውስጥ አለ ማለታቸው ነው። ይህን ካሉ ደግሞ እያንዳንዱ ነገር የእግዚአብሔር አካል ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር የዓለም መሠረት እንደሆነም ያስተምሩ ነበር። ሰው ራሱ በዓለም ውስጥ ከሚገኙት ነገሮች ውስጥ አንዱ በመሆኑ፥ እንደ አንድ የእግዚአብሔር አካል ይቆጠራል። ምድራዊና መለኮታዊ በሆኑ ነገሮች መካከል ምንም ዓይነት መለያ ነገር አያስቀምጡም። በእነርሱ አስተሳሰብ ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር አካል በመሆኑ፥ በኃጢአትና በመልካም ነገር መካከል ምንም ልዩነት የለም። በሕይወታቸው የሚመጣውን ማንኛውንም ዓይነት ነገር ይቋቋሙ ነበር።

በአሁኑ ጊዜ ይህን ዓይነት እምነት በሩቅ ምስራቅ አገሮች ውስጥ በሚገኙት ሂንዱእዝምና ቡዲዝም በሚባሉት ሃይማኖቶች ውስጥ ይታያል።

እነዚህ ፈላስፎች የጳውሎስን ንግግር ሲሰሙና የሚያስተምረው ነገር አዲስ በመሆኑ፥ ይህ ለፍላፊ (ቁ. 18) ስለ አዲስ አማልክት ያወራል ብለው ይነቅፉታል። ከዚያም በአቴና ከተማ ምሁራን አዲስን ነገር ወደሚነጋገሩበትና አንድ አዲስ ትምህርት እውነተኛ ይሁን አይሁን ወደ ሚታይበት አርዮስፋጎስ ወደ ተባለ ሥፍራ ጳውሎስን ይዘውት ይሄዳሉ። ጳውሎስን ወደዚያ ይዘውት የሄዱት የእርሱን ትምህርት ሰምተው ከተከራከሩበት በኋላ ለመወሰን ነው። ይህን ያደረጉት እርሱን ለመስማትና የተናገረውን ለማመን አይደለም። እነሱም «ይህ የምትናገረው አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ ይቻለናልን? ... እንግዲህ ይህ ነገር ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ እንሻለን» ይሉታል።

ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ ቆሞ የተናገረው ንግግር በብዙ ጥበብና ብልሃት የተዘጋጀ ነው። እንደምታስታውሰውም ጳውሎስ ያደገበት የተሬስ ከተማ ዩኒቨርሲቲ ነበራት። በዚያም ሳለ ያለምንም ጥርጥር የኤፊቆሮሶችንና የኢስጦኢኮችን ትምህርቶች በደንብ ያውቅ ነበር። በዚህም መሠረት እራሱን እንደ ፈላስፋ አድርጎ በማቅረብ የወንጌሉን ምስጢር ለማብራራት ሲል አንዳንድ የእነሱን አስተሳሰቦች በማከል እሱ የሚናገረው ነገር ለማወቅ ችግር ያጋጠማቸውን ሰዎች ያነጋግራቸዋል።

የጳውሎስን መልእክት በሶስት ቦታ ልንከፍለው እንችላለን።

ሀ) መግቢያ (የሐዋ. 17፡20-23)። የተሳሳተ አምልኮ እያላቸው ነቀፋ ከመሰንዘር ይቆጠብና መንፈሳዊነታቸውን በመጥቀስ ያሞግሳቸዋል። በዙ የተለያዩ አማልክትን የሚወክሉ ጣእቶችን በማየቱም አማልክትን የምትፈሩ ናችሁ ይላቸዋል። በመቀጠልም አንድ ለማይታወቅ አምላክ የሚል ጽሑፍ ያለበት መሠዊያ አየሁኝ ስለዚህም ይህን የማታውቁትን አምላክ እኔ አስታውቃችኋለሁ ይላቸዋል።

ጳውሎስ ያለ በቂ ምክንያት ወንጌሉ ላይ ተቃውሞ እንዲሰነዘሩ አልፈለገም። ስለዚህም፥ የተሳሳተ አመለካከታቸውንና እነሱን ከመቃወም ይልቅ እነሱን በማሞገስ ይጀምራል። በሌላ እምነት ውስጥ ላሉ ሰዎች ስንመሰክር ይህ ልንከተለው የሚገባን ጥሩ መመሪያ ነው። በመጀመሪያ ላይ ማድረግ ያለብን እምነታቸውን መቃወም መንቀፍ ሳይሆን የእነሱን ሐሳብ ወደ እኛ ለመሰብሰብና ተቀባይነትን ለማግኘት የእነሱን ሕይወትና ሃይማኖት በተመለከተው ጥሩ ነው የምንለውን ነገር መጥቀስ ነው።

ጥያቄ 19፡- የወንጌሉን መልእክት ለአርቶዶክስ ወይም ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ለመግለጽ፥ በመጀመሪያ ላይ እነርሱ ከሚያደርጉት ነገር ውስጥ የምትጠቅሳቸው መልካም ነገሮች ምንድናቸው?

ለ) ሳያውቁ የሚያመልኩትን አምላክ መግለጽ (ሐዋ. 17፡ 24-29)፡- ይህ የማይታወቀው አምላክ የራሱ የሆነ ስም ስለሌለው ጳውሎስ ስለ እውነተኛው አምላክ በሚያስረዳበት ወቅት ይህ ጉዳይ ችግር ፈጥሮበታል። እንደምታየውም እነዚህ ሰዎች ስለ አንዱ አምላክ የሚያውቁት ምንም ነገር ስላልነበራቸው፥

ጳውሎስ ምስክርነቱን ወዲያውኑ ቶሎ ብሎ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመናገር አይጀምርም። በመጀመሪያ መጀመር ያለበትም እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በመግለጽ ነው። በዚህ መሠረት ይህ ሳያውቁት የሚያመልኩት አምላክ ዓለምንና በእርሷ ውስጥ ያለውን ነገር የፈጠረ ነው በማለት ይጀምራል። በመቀጠልም እግዚአብሔር የሁሉም ፈጣሪ ስለሆነ የሰው እጅ በሠራው መቅደስ ውስጥ አይኖርም ይላቸዋል። ልክ ሁሉ ነገር እንደሌለው ተቆጥሮ በሰው እጅ አይገለልገልም። እግዚአብሔር የመንግሥታት ሁሉ ፈጣሪም ገዥም ወይም ተቆጣጣሪም ነው። በተጨማሪም እርሱ ሰዎች እየመረመሩ ያውቁት ዘንድ በምድር ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ በአንድ ፈጠረ፤ የተወሰኑም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ሥፍራ ዳርቻ መደበላቸው።

ጳውሎስ በዚህ ትምህርቱ ከኤፊቆሮስና ከኢስጦኢኮች አስተሳሰብ የሚቃረን ነገር ነው የሚናገረው። እግዚአብሔርን ከፍጥረታት ሁሉ በመለየት፥ ከፍጥረታት ሁሉ የበላይ አድርጎ በማቅረቡ የተፈጠሩ ነገሮች በሙሉ የእግዚአብሔር አካል ናቸው የሚል እምነት ካላቸው ከኢስጦኢኮች ጋር ይቃረናል። ለሚሠሩት ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ተጠያቂ እንደሚሆኑም በማሳየት እግዚአብሔር የለም የሚለውን የኤፊቆሮሶች ትምህርት ውድቅ እንደሆነ ይገልጻል።

ጳውሎስ ላስተማረው ትምህርት ማስረጃ እንደሆነው፥ «እኛ ትውልዶቹ ነን» ብለው የተናገሩትን እንደዚህ ብለው ከተናገሩት ባለቅኔዎች አንዱ የኢስጦኢኮች ፈላስፋ የነበረው አራቱስ ነው። እንግዲህ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከራሳቸው ባለቅኔዎች ንግግር ላይ በመጥቀስ ይቃወማቸዋል። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ የራሱ የእግዚአብሔር ፍጥረት እንደሆነና ይህ አምላክ በሰው እጅ በብልሃት በተሠራ በወርቅ ወይም በድንጋይ ምሥል ውስጥ እንደማይገኝ ያሳያቸዋል። ይህን ዓይነቱን አምልኮ አምላክን የማያውቁ አሕዛብ የሚያደርጉት ነው።

ጥያቄ 20፡- ጳውሎስ ስለ ወንጌሉ ለመግለጽ ሲል በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የጀመረው ለምን ይመሥልሃል?

ሐ) ከእግዚአብሔር የተላከ መልእክት (17፡ 30-34)። ጳውሎስ ያለፉት የእምነታቸውን ጊዜዎች የድንቁርና ወራት ይላቸዋል። ይህ አባባሉ ለአቴና ሰዎች የተሰጠ ታላቅ ስድብ መሆኑ ነው። ለነገሩማ የባህልና የዕውቀት ማዕከል ነበሩ። በትምህርታቸውና በእውቀታቸው ይኮሩ ነበር ሆኖም ጳውሎስ ይህን ሁሉ በድንቁርና ወራት ውስጥ ያካትተዋል። ጳውሎስ ይህን ሲል ለፍልስፍናቸው ምሪት የሚሰጥ የእግዚአብሔር ቃል ስላልነበራቸው ባለማወቃቸው ተጠያቂ አያደርጋቸውም ማለቱ ነው። በዚህም መሠረት እግዚአብሔር እነዚህን ዓመታት የእግዚአብሔር ቃል ያልታወቀበት ዘመናት በማለት አልፎአቸዋል። አሁን ግን፥ እውነቱ ስለተገለጸላቸው፥ ለሚያደርጉት ነገር ሁሉ ተጠያቂ ሆኑ። ይህም ማለት እግዚአብሔር አይፈርድባቸውም ማለቱ አይደለም። ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክት እንደገለጸውም ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የሚመሰክሩላቸው ፍጥረታትና ሕሊና አላቸው። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ሆን ብለው

ባለመቀበላቸው ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚያመልጡ አይሆኑም። እግዚአብሔርም በተለየ ራዕይ በቃሉ በሚገልጸው ነገር ላይ ተጠያቂ ናችሁ ብሎ በኃላፊነት አልያዛቸውም። እንግዲህ እግዚአብሔር የድንቁርናን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ ቀን ቀጥሮአልና በዚያም ቀን ባዘጋጀው የሰው ልጅ በዓለሙ ላይ በጻድቅ ሲፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሳቱ ሁሉን አረጋግጧል። እንዲ እውነቱን ከሰሙ የመቀበሉ ኃላፊነት የራሳቸው ነው። ጳውሎስም ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መግለጽ የሚጀምረው ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛ ባሕርይ በደንብ ካስረዳ በኋላ ነው።

ከሙታን የመነሣትን ነገር ሲሰሙ፥ ብዙዎች በጳውሎስ ላይ አፌዙበት። ግሪካውያን ከሞት መነሣት አለ ብለው አያምኑም። በተለይም በዚህ ምድራዊ ኑሮአችን፥ አንድ ሰው ከሙታን ይነሣል ብለው አያምኑም። ይህም ሆኖ የተቀሩት ሰዎች ስለዚሁ ርዕስ እንደገና ልንሰማህ እንሻለን አሉት።

ጳውሎስ ወንጌሉን ሰፋ አድርጎ በማቅረብ የኃጢአት ይቅርታ እንዳለ ያልገለጸው ለምንድነው? በእርግጥ አቴናውያን ለዚህ ጉዳይ ዝግጁ አልነበሩም። የሚናገረው ብዙው ነገር ለእነርሱ አዲስ ነበር። ጳውሎስም ወደ በኋላ ላይ ሰፋ ባለ ሁኔታ ስለ ኢየሱስ ለማስረዳት የሚችልበትን መሠረት እየጣለ ሄደ። ምንም እንኳ በጳውሎስ ላይ ቢያፌዙም፥ ብዙ የሚያሳስቡ ነገሮችን ጠቅሶላቸዋል።

ጥያቄ 21፡- ከጳውሎስ መልእክት ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቃሉ ምንም ዓይነት ግንዛቤ ለሌላቸው መመስከርን በተመለከተ የምንማረው ነገር ምንድነው?

የጳውሎስ መልእክት እንዲሁ መና አልቀረም፤ አንዳንዶች በእግዚአብሔር አምነዋል። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ፥ በአርዮስፋጎስ ያለው ፍርድ ቤት ፈራጅ የነበረው ዲዮናስዮስ የተባለው ሰውዬ ነው (ከቤተ ክርስቲያን የታሪክ መጻሕፍት እንደምንረዳው፥ ይህ ሰው በኋላ ላይ በአቴና የነበረችው ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኗል)። ሌላም ደማሪስ የሚሏት ሴት አምናለች። ወደ ቆሮንቶስ ከመሄዱም በፊት፥ ጳውሎስ ለእነዚሁ አዳዲስ ክርስቲያኖች ሰፋ ያለ ትምህርት ሳይሰጣቸው አልቀረም።

አንዳንድ ምሁራን ጳውሎስ ከፈላስፎች ጋር የፍልስፍናን ጽንሰ-ሐሳብ ይዞ በወንጌሉ ላይ መከራከሩ ምንም ዋጋ የሌለው ነገር እንደሆነ ተገንዝቧል ብለው ያስባሉ። ቆሮንቶስ እንደደረሰም፥ «ለማጥመቅ ክርስቶስ አላከኝምና ወንጌልን ልሰብክ እንጂ፤ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን በቃል ጥበብ አይደለም» ብሎ ይናገራል። ቀጥሎም የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።» ይላል። (1ኛ ቆሮ 1፡ 17 እና 18)።

ጥያቄ 22፡- 1ቆሮ !፡ 17-2፡ 5 አንብብ። ከዚህ ክፍል በምሥክርነታችን ወቅት በሰው ጥበብ ላይ ለመመካት ስለ መሞከር የምንማረው ነገር ምንድነው?

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 18፡ 1-17

ጳውሎስ አቴና በሚገኘው ፍርድ ቤት ሄዶ ለተሰበሰበው ሕዝብ ያደረገው ንግግር፥ አንዳንዶችን ለማሳመን ሲል የማይሆነው ነገር እንደሌለ የሚያሳየን ነው። እንደ ፈላስፋ በመሆን ከራሳቸው ቅኔ ተናጋሪዎች ንግግር ላይ በመጥቀስ፥ የእነሱን ሐሳብ እንደሚቃወም አድርጎ ያቀርበዋል። ስለ ፍርድና ስለሙታን ትንሣኤ ሲናገር ብዙዎች አፈዙበትም ትተውት ሄዱ። ጳውሎስም አቴናን ትቶ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን በጥቂት ሰዎች ሕይወት ውስጥ ሆኖ ፍሬም እያፈራ ነው። ብዙዎች ቢያፌዙም፥ በአቴና ምሥክሮች አልታጡም። ሆኖም የአቴና ቤተ ክርስቲያን በሌሎች ቦታዎች ላይ እንደተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት በጣም አላደገችም።

የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ ይህን ሁሉ የጻፈው የኢየሱስ የመጨረሻ ትዕዛዝ የነበረችውን ከኢየሩሳሌም ወደ ዓለም ሁሉ ወንጌልን አዳርሱ የምትለው ትዕዛዝ እንዴት እንደተፈጸመች ለማሳየት ነው (ሐዋ. 1፡ 8)። ሉቃስ ይህን የማስፋፋት ሥራ ለመግለጽ ሁለት ቁልፍ የሆኑ ሰዎች ሕይወት ይከታተላል፤ እነዚህም ሰዎች ጳውሎስና ጴጥሮስ ናቸው። በራዕይ ምክንያት ጴጥሮስ ወንጌሉ ለአይሁዳውያንም ለአሕዛብ እንደሆነ ይገነዘባል። የእርሱም ልዩ አገልግሎት ይህንን ለአይሁዳውያን ማሳወቅና ማሳመን ነው። ጳውሎስ ደግሞ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን በማየቱ፥ ክርስቶስን ለአሕዛብ እንዲያሳውቅ ጥሪ ይደርሰዋል። በዚህ ውስጥ ግን ከጳውሎስ ጋር አብረውት የሚሠሩ ሰዎች እንዳሉ እናያለን።

የሐዋርያት ሥራ 18፡ 1-17 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 23፡- ሀ) 1. ጳውሎስ ቆሮንቶስ ሲገባ ከማን ጋር ነው የተገናኘው? 2. ወደ ቆሮንቶስ የሄደው ለምንድነው? 3. ጳውሎስ አብሯቸው ይሠራ የነበረው ሥራ ምንድነው?

ለ) 1. ጳውሎስ በየሰንበቱ ንግግር ያደርግ የነበረው የት ነው? 2. የአይሁዳያኑ ምላሽ ምን ነበር?

ሐ) 1. ኢዮስጦስ ማነው? 2. ቀርስጶስ ማነው?

መ) 1. ለጳውሎስ በራዕይ የተነገረው ነገር ምንድነው? 2. አይሁዳውያን ሲቃወሙት ከጳውሎስ ጎን በመቆም የተከላከለው ማነው? 3. በጳውሎስ ላይ የተነሣው ክስ ለመርታት እንዴት ነበር የተሟገተው?

ጢሞቴዎስና ሲላስ አቴና ከመድረሳቸው በፊት ጳውሎስ በስተደቡብ በ 80 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ወደምትገኘው የቆሮንቶስ ከተማ ለመሄድ ይወስናል።

ቆሮንቶስ በዛሬዋ ግሪክ በምትገኘው አካያ በምትባለው ክፍለ ሀገር ውስጥ የምትገኝ ትልቅ ከተማ ነበረች። ብዙ ለንግድ የሚመጡ ነጋዴዎች የሚሰበሰቡባት የነጋዴ ከተማ ነበረች። ከእስያ ወደ ሮም በሚወስደው አውራ ጎዳና ላይም የምትገኝ ከተማ ናት። በብዙዎቹ የነጋዴ ከተማዎች ውስጥ እንደሚታየው፥ ብዙ አምልኮና ዝሙት የበዛባት አገር ነበረች። ለአምልኮ ከ 1000 በላይ ሴተኛ አዳሪዎችን የሚጠቀሙበት አፍሮዲት

የሚባል የአሕዛብ ቤተመቅደስም በዚች ከተማ ይገኝ ነበር። እንዲያውም ከተማዋ በመጥፎነቷ በጣም ከመታወቋ የተነሣ፥ ሰዎች በጣም እርኩስ እየሆኑ ሲመጡ ከቆሮንቶስ ሰዎች ጋር ይነፃፀሩ ነበር። የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያንም ቅድስናዋን ለመጠበቅ የገጠማትን ችግር ልንገነዘብ የምንችለው፥ ይህን ዓይነቱ ሊዋጉት የሚገባ የሠረፀ ርኩሰት መኖሩን ስናውቅ ነው።

ጳውሎስ ቆሮንቶስ እንደ ደረሰ ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር ይገናኛል። እነዚህ ሁለት አይሁዳውያን በሮም ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን ናቸው። ስለ ክርስቶስ እንዴት እንደሰሙ ባናውቅም ምናልባት ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ወደ ሮም የተመለሱ አንዳንድ ክርስቲያኖች ሳይመሰክሩላቸው አይቀርም። ምንም እንኳ ሙሉ ጊዜያቸውን በቤተ ክርስቲያን ሥራ ላይ ባያውሉትም፥ እግዚአብሔር በቆሮንቶስና በኤፌሶን ቤተክርስቲያኖች ውስጥ በእነርሱ በጣም ተጠቅሞባቸዋል። ከሮም የወጡትም፥ ንጉሥ ቀላውዴዎስ አይሁዳውያን በሙሉ ከሮም እንዲወጡ ካዘዘ በኋላ ነው። አቂላና ጵርስቅላ ድንኳን ሰፊዎች ነበሩ። ከጳውሎስም ጋር ተመሳሳይ ሙያ ስለነበራቸው ጳውሎስ ከእነርሱ ጋር አብሮ ይሠራ ነበር። አይሁዳውያን በባህላቸው መሠረት ልጆቻቸውን የእጅ ሙያ ያስተምሯቸው ነበር። እንደ ፈሪሣውያን ያሉ የሃይማኖት መሪዎች እንኳ ሠርተው መተዳደሪያቸውን ያገኙ ዘንድ ለየት ያለ የእጅ ሙያ እንዲኖራቸው ያስፈልግ ነበር። ብዙ ጊዜም ጳውሎስ ይህን ሙያውን ይጠቀምበት የነበረው በሚሲዮናዊ ጉዞዎቹ ላይ ነው። ይህን ሥራ ይሠራ የነበረው፥ በሚመሠክርላቸው ሰዎች ላይ ሸክም ላለመሆን ሲል ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ ሲመጡ ከፊሊጲስዩስ ክርስቲያኖች የተላከ ስጦታ ይዘውለት ይመጣሉ (ሐዋ. 18፡ 5፤ 2ቆሮ. 11፡ 8-9 እና ፊሊጵ. 4፡ 15 ተመልከት)። ጳውሎስ ይህን ስጦታ ከተቀበለ በኋላም ሙሉውን ጊዜውን በስብከት ላይ ሊያውለው ቻለ።

ጥያቄ 24፡- ለወንጌላውያን መደረግ ያለበት ድጋፍ በተመለከተ ይህ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?

የጢሞቴዎስና የሲላስ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አልተጠቀሰም። ስለ እነርሱ ብዙ የምንማረው ጳውሎስ በጻፋቸው መልእክቶች ውስጥ ነው። በየቤተክርስቲያኑ እየሄደ ሲያገለግል አብረውት ያገለግሉ እንደነበር መገንዘቡ በጣም አስፈላጊ ነው። ለመጥቀስ ያህል የሚከተሉትን ተመልከት፡-

1. ጳውሎስ ወደ አቴና ሲሄድ ሲላስና ጢሞቴዎስ በቤርያ ቆዩ (ሐዋ. 17፡ 14-15)

2. ከጳውሎስ ጋር በአቴና ከተገናኙ በኋላ አማኞቹን በእምነታቸው ያበረታቱና ያጽናኗቸው ዘንድ ወደ ተሰሎንቄ ይልካቸዋል። (1ተሰ 3፡ 1-2)

3. ጢሞቴዎስና ሲላስ፥ ጳውሎስ ወዳለበት ወደ ቆሮንቶስ የሥራ ሪፖርትና ከፊሊጵሲዩስ ሰዎች ስጦታ ይዘው ይሄዳሉ (1ተሰ 3፡ 6)። በፊልጵሲዩስ 4፡ 15-16 ላይ የፊሊጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ስጦታ በማመስገን ከቆሮንቶስ ክርስቲያኖችም ምንም እንዳልወሰዱ ይገልጽላቸዋል። (2ቆሮ. 11፡ 8-9)።

የጢሞቴዎስንና የሲላስን አገልግሎት እንደምናየው፥ በየአብያተ ክርስቲያናቱ እየሄዱ ያገለግሉ የነበረው አብረው እንደሆነ እንገነዘባለን።

**ጥያቄ 25:- የጢሞቴዎስና የሲላስ አገልግሎት በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ አብሮ በቡድን ስለመሥራት አስፈላጊነት የሚገልጽልን ነገር ምንድነው?**

ጳውሎስ በሕይወቱ አንዳንድ አሳሳቢ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙት ጌታ በራዕይ ይገለጥለት ነበር። በአሁን ጊዜም ጳውሎስ ለምን ራዕይ እንዳስፈለገው አናውቅም። ሆኖም፥ ጳውሎስ በየሄደበት ቦታ ሁሉ መከራ ተቀብሏል፤ በ1ኛ ቆሮ. 1፡ 3 ላይም «እኔ በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርሁ» ይላል። ጌታም ለጳውሎስ ያስፈልግ የነበረውን ነገር ያውቅ ስለነበር በራዕይ «እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፤ ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፤ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና» ይለዋል።

**ጥያቄ 26:- እግዚአብሔር በችግር ውስጥ ሳለህ ያጽናናህ እንዴት ነው?**

ጳውሎስም በቆሮንቶስ አንድ ዓመት ከስድስት ወር በመቆየት የእግዚአብሔርን ቃል አስተማረ። በመጀመሪያ ትኩረት ያደረገው በአይሁዳውያኑ ላይ ነበር። ነገር ግን አይሁዳውያኑ ወንጌሉን በተቃወሙ ጊዜ፥ ጽኑ የሆነ የአይሁዳውያን ዕርግማን ይወርድባቸዋል። የጳውሎስ ልብስ ማራገፍ፥ አይሁዳውያን አንድ የአሕዛብ ቤትን ትተው ሲወጡ የሚያደርጉት ሥርዓት ነው። ይህም የሚያመለክተው፥ በአሕዛብ እርኩስ ነገር ለመርከስ አለመፈለጋቸውን ነው። ጳውሎስም ይህን ዓይነቱን ተግባር የፈጸመው ወንጌሉን በመቃወማቸው፥ ልክ እንደ አሕዛብ ንጹሕ ያልሆኑ መሆናቸውንና ላለማመናቸውም በእነርሱ ላይ ለሚወርደው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ፍርድ ኃላፊነቱን እነሱ እንደሚወስዱ ለማሳየት ነው (ማቴ. 10፡ 14)። ከዚህም በኃላ ጳውሎስ አሕዛብ ላይ ያተኩራል። ታዲያ ይህ ሁሉ ቢሆንም፥ የምኩራብ አለቃ እንደነበረው እንደ ቀርስጶስ ያሉ አንዳንድ አይሁዳውያን በኢየሱስ አምነዋል።

ጳውሎስ ከምኩራብ ይወጣና ኢይስጦስ ወደሚባል እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ ሰው ቤት ውስጥ ገብቶ በዚያ መስበክ ጀመረ። ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር ያህል ጳውሎስ በቆሮንቶስ ካስተማረ በኋላ ብዙ አሕዛብ ያምናሉ፤ ቤተክርስቲያንም ይቋቋማል። በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ላይ ጳውሎስ ብዙ ጊዜውን ያሳለፈው እዚሁ ቆሮንቶስ ውስጥ ነው።

በመጨረሻም አይሁዳውያን እንደገና ይነሡበትና ወደ ፍርድ ወንበር ያቀርቡታል። ከዚያም ጳውሎስ ከሮም ሕግ ውጪ ሰዎችን እያባበለ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩት ያደርጋል ብለው ይከሱታል። እንደምታስታውሰው የቀድሞው የአይሁዳውያን ሃይማኖት ሕጋዊ ነው፤ ሆኖም ክርስትና ከዚህ ሃይማኖት ውጪ ሕጋዊነት አይኖረውም። ታዲያ ጋልዮስ የተባለው የአካይያ አገረ ገዥ፥ ይህን ክስ በቅናት ተነሣሥተው እንዳቀረቡ ተገንዝቧል። አይሁዳውያኑም ከሳችሁ ከዓመፃ ወይም ከክፉ በደል የተነሣ አይደለም ይላቸዋል። የራሳቸውን ሕግ በተመለከተ ከሆነ ግን እራሳቸው እዚያው ለነገሩ እልባት መፍጠር አለባቸው። በዚህም ምክንያት ጋልዮስ ፈራጅ

አልሆንም ይላቸዋል። በዚያን ጊዜም የክርስትና እምነት፥ የአይሁድ ሃይማኖት አንድ ክፍል እንደሆነ ተደርጎ ነበር የሚቆጠረው፤ በመጨረሻም ጋልዮስ ከሳሾቹንም ከፍርድ ወንበሩ ፊት ያስወጣቸዋል።

ጥያቄ 27፡- ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ጥበቃ የሚያሳየን እንዴት ነው?

በዚህ ምዕራፍ ላይ ጋልዮስ በመጠቀሱ፤ የታሪክ ጠበብት በትክክል ይህ ታሪክ የተከናወነበትን ጊዜ ለማመልከት ይችላሉ። ጋልዮስ የቆሮንቶስ አገረ ገዥ የነበረው ከ51 - 52 ዓ.ም ብቻ ነው። ስለዚህም፤ ይህ ከላይ የተጠቀሰው ታሪክና የተፈጸመው 1ኛ ና 2ኛ ተሰሎንቄ የተጻፈው በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ነው።

ክርስቲያኖቹን ከመደብደብ ፈንታ የማያምኑት የግሪክ ሰዎች የምኩራብ አለቃ የነበረውን ሶስቴንስን ይደበድቡታል፤ ይህም ሲደረግ ጋልዮስ ምንም አላለም። ምናልባትም ሶስቴንስን ክርስቲያን የሆነው ከተደበደበ በኋላ ይሆናል፤ ምክንያቱም ለመጀመሪያ ጊዜ ሶስቴንስን እንደ ወንድም የሚጠራው በ1ኛ ቆሮ 1፡ 1 ላይ ነው።

# አምስተኛ ቀን፡- የክለሳ ጥያቄዎች

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

1. ቤሪያውያን ከተሰሎንቄ ሰዎች የሚለዩት እንዴት ነው?
2. እስከ ዛሬ ድረስ አይሁዳውያን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የሚቃወሙት ለምንድነው? (2ቆሮ. 3፡ 13-16)
3. በሮማው ዘመነ መንግሥት ብዙ አሕዛብ በመጀመሪያ ወደ አይሁዳውያን ቀጥሎም ወደ ክርስትና እምነት የመጡት ለምንድነው?
4. የአቴና ከተማንና የሰዎቹን አኗኗር አብራራ።
5. ጳውሎስ አብረውት ከነበሩ አገልጋዮች ጋር እንዴት ይሠራ እንደነበር አብራራ።
6. ሀ) የጳውሎስ መልእክት በአቴና ለሚያደምጠው እንደሚገባ ሆኖ ሊቀርብ የቻለው እንዴት ነው? ለ) ይህ እኛ ማቅረብ ስለሚገባን መልእክት የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
7. በአርዮስፋጎስ በቀረቡ መልእክቶች በጳውሎስ ያፌዙበት በምን ነጥብ ላይ ነው?
8. እግዚአብሔር ለጳውሎስ በቆሮንቶስ ሳለ ራዕይ የሰጠው ለምን ይመስልሃል?
9. ክስ መሥርተውበት በቆሮንቶስ ወደሚገኘው የፍርድ ወንበር ባቀረቡት ጊዜ የእግዚአብሔር ጥበቃ የተገለጸው እንዴት ነው?

ሳምንታዊዎቹን የመወያያ ጥያቄዎች ተመልከትና ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

*1.* የአምልኮ ጊዜ    3. ክለሳ

2. የጸሎት ጊዜ    4. የውይይት ጊዜ፡

ሀ) ኢየሱስ መሲሕ እንደሆነ እንደ ማስረጃ ሊገልጹ የሚችሉ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን በዝርዝር ጻፍ።

ለ) 1. የቤርያውያን ልንማረው የምንችለው ትልቅ ትምህርት ምንድነው? 2. አንተና ሌሎች ሰዎች ወንጌላውያንና መጋቢዎች የሚያስተምሩት ትምህርት ላይ በእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም ፍርድ ለመስጠት ዝግጁ ልትሆኑ የምትችሉት እንዴት ነው? 3. በቤተክርስቲያንህ ሐሰተኛ የሆኑ ትምህርቶች የተሰጡባቸው አጋጣሚዎች አጋጥመውህ ከሆነ እንዴት እንደነበሩ አብራራ። 4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሀሰት ትምህርት ከተሰማ፥ በዚህ ውስጥ ያንተ ኃላፊነት ምንድነው.

ሐ) 1. ጳውሎስ በአቴና ያቀረበው መልእክት መልእክቶቻችንን ለታዳሚው ሕዝብ በሚገባ ሁኔታ ስለማቅረብ ያሚያስተምረን ነገር ምንድነው? 2. በአእምሮ ጥበብ ተጠቅመን ለምሥክርነታችን መከላከያ እንዴት ልናቀርብ እንደምንችል ግለጽ። 3. ይህ ለምሥክርነታችን አደገኛ የሚሆነው መቼ ነው? 4. ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ጥበብና ስለ ዓለም ጥበብ የሚናገረው ነገር ምንድነው? (1ቆር. 1፡ 18-2፡7)

5. ጸሎት

# ትምህርት 14

የሐዋርያትሥራ18፡ 18-20፡ 12

## የመጀመሪያ ቀን፡-

## የሐዋርያት ሥራ 18፡ 18-28

በሁለተኛው ጉዞው ላይ እግዚአብሔር በጳውሎስ ተጠቅሞ በአዳዲስ ሥፍራዎች ውስጥ ወንጌልን ያስፋፋል። በገላትያ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ከጎበኘ በኋላ ወደ አውሮፓ በመዝለቅ በዛሬዋ ግሪክ ውስጥ የሚገኙ ምኩራቦች ውስጥ መስበክ ይጀምራል። በሄደበት ቦታ ሁሉ አይሁዳውያንና አሕዛብ ያሳድዱት ነበር። ሆኖም ታማኝ ምሥክር ሆኖ በመጽናቱ አብያተ ክርስቲያናት ሊመሠረቱ ችለዋል። ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር ያህል በቆሮንቶስ ካገለገለ በኋላም፥ ሁለተኛውን ጉዞ የሚያጠናቅቅበት ጊዜ እየተቃረበ ይሄዳል።

# ትምህርት 14

የሐዋርያትሥራ18፡18-20፡12

## የመጀመሪያ ቀን፡-

## የሐዋርያት ሥራ 18፡18-28

በሁለተኛው ጉዞው ላይ እግዚአብሔር በጳውሎስ ተጠቅሞ በአዳዲስ ሥፍራዎች ውስጥ ወንጌልን ያስፋፋል። በገላትያ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ከጎበኘ በኋላ ወደ አውሮፓ በመዝለቅ በዛሬዋ ግሪክ ውስጥ የሚገኙ ምኩራቦች ውስጥ መስበክ ይጀምራል። በሄደበት ቦታ ሁሉ አይሁዳውያንና አሕዛብ ያሳድዱት ነበር። ሆኖም ታማኝ ምሥክር ሆኖ በመጽናቱ አብያተ ክርስቲያናት ሊመሠረቱ ችለዋል። ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር ያህል በቆሮንቶስ ካገለገለ በኋላም፥ ሁለተኛውን ጉዞ የሚያጠናቅቅበት ጊዜ እየተቃረበ ይሄዳል።

ጥያቄ 1:- የሐዋርያት ሥራ 18፡ 18-20፡ 12 አንብብ። ሀ) ወንጌሉ በኤፌሶን እንዴት እንደተስፋፋ ግለጽ። ለ) ካርታውን በመመልከት ጳውሎስ በሶስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው የሄደባቸውን ሥፍራዎች በዝርዝር ጻፍ።

የሐዋርያት ሥራ 18፡ 18-28 እንደገና አንብብና እነዚህን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 2 :-ሀ) 1. ከቆሮንቶስ በኋላ ጳውሎስ የሄደው ወዴት ነው? 2. አብሮት የሄደው ማነው? 3. ጳውሎስ ጠጉሩን የተቆረጠው ለምንድነው?

ለ) 1. አቂላና ጵርስቅላ በየት ቆዩ? 2. በኤፌሶን የነበሩ አይሁዳውያን ጳውሎስን እንዲቆይ ሲለምኑት የሰጣቸው ተስፋ ምንድነው?

ሐ) 1. ቂሳሪያ ከደረሰ በኋላ ጳውሎስ የጎበኛቸው ሁለት ከተሞች እነማን ናቸው?

መ) ጳውሎስ ሶስተኛው ጉዞውን የጀመረው የት በመሄድ ነው?

ሠ) 1. አጵሎስ ማነው? 2. ያንሰው የነበረው እውቀት ምንድነው? 3. ሙሉ በሙሉ በደንብ አድርገው ያስተማሩት እነማን ናቸው.

ጳውሎስ ብዙውን ጊዜውን ያቃጠለው በቆሮንቶስ ነው። እግዚአብሔር በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረትም ለተወሰነ ጊዜ ያህል አገልግሎቱን በቆሮንቶስ ሊቀጥል ችሏል። በዚህም ምክንያት የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን በደንብ ሥር ሰዳ ተመሠረተች። ለብዙ ጊዜ በዚህ ሥፍራ ካገለገለ በኋላም አንጾኪያ ወደምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ስለ አገልግሎት ሥራ ሪፖርት ማቅረብ አለብኝ የሚል ስሜት ተሰማው።

ጳውሎስ አብረውት ከነበሩት ሰዎች ጋር በመርከብ ከቆሮንቶስ ከመነሳቱ በፊት ስለት ስለነበረበት ራሱን ይላጫል። ለምን ስለት እንዳደረገ የምናውቀው ነገር የለንም። አንዳንዶች ግን ይህ የናዝራዊ ስለት ነው ይላሉ። አንድ ናዝራዊ ስለት የሚሳል ሰው (ዘኁ. 6፡ 1-6) ከወይን ጠጅና ከሚያሰክር መጠጥ ራሱን ማግለል አለበት፤ ጸጉሩን መቆረጥ የለበትም፥ ወደ ሬሳ አይቀርብም፥ ወራቱም እስኪያልቅ ድረስ እራሱን ለይቶ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መሆን አለበት። ይህ የመለየት ወራት ካለቀ በኋላ ጸጉሩን ይላጫል። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ይህን ስለት የሚያደርጉት እግዚአብሔር በሚያስገርም ሁኔታ ስለታደጋቸው ምስጋና ለማቅረብ ሲሉ ነው። ምናልባትም ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቆይታው እግዚአብሔር ስለጠበቀው ወይም በአውሮፓ ስለ አሳለፈው ጊዜ ማመስገኑ ይሆናል። ጸጉሩንም በመላጨት የስለቱን መጨረሻ ይገልጻል።

ጥያቄ 3 :-ለእግዚአብሔር ምስጋናህን የምትገልጸው እንዴት ነው (ዕብ. 13፡ 15)?

ከአቂላና ከጵርስቅላ ጋር በመሆን፤ ጳውሎስ በመርከብ ወደ ኤፌሶን ይጓዛል። ይህቺ ከተማም በእስያ ክፍለ አህጉር ዋነኛዋ ከተማ ስትሆን፥ አቂላና ጵርስቅላ መጨረሻ ላይ የቀሩት ከዚችው ከተማ ነው። እንደምታስታውሰውም የሮማው ንጉሥ አይሁዳውያንን ከማባረሩ በፊት በመጀመሪያ አቂላና ጵርስቅላ ይኖሩ የነበሩት በሮም ነው። ከዚያም ወደ ቆሮንቶስ ሄደው ከጳውሎስ ጋር ይገናኛሉ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይሆናሉ። ለምን እንደሆነ ባናውቅም ጳውሎስ ተነሥቶ ወደ አንጾኪያ ሊመለስ ሲል፥ እነዚህ ሰዎች ከእርሱ ጋር አብረው እስከ ኤፌሶን ድረስ ይሄዳሉ። እግዚአብሔር

በእነርሱ ተጠቅሞ በኤፌሶን የምትገኘውን ትንሽ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደመሠረተ እናያለን።

ኤፌሶን እንደ ደረሱ፣ ጳውሎስ ወደ ምኩራብ ገብቶ ምናልባትም ወንጌሉን በተመለከተ ከአይሁዳውያን ጋር ይነጋገር ነበር። እነሱም በእርሱ ደስ ስለተሰኙ ለጥቂት ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንዲቀመጥ ይለምኑታል። ምንም እንኳ ጳውሎስ እሺ ባይላቸውም፣ እግዚአብሔር ከፈቀደ ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል ይገባላቸዋል። ከዚያም በመርከብ ወደ ቂሣሪያ ይሄዳል።

ጳውሎስ በቂሣሪያ እንደ ደረሰ፣ በመጀመሪያ ሄዶ ለኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ያቀርባል። «ወጥቶ» የሚል ስያሜ ለኢየሩሳሌም የተሰጣት በተራራ ላይ ስለነበረች ነው። ከዚያም በሚሲዮናዊ ጉዞው ሸኝታ ወደ ላከችው ወደ አንጾኪያዋ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል። በዚህም ለምን ያህል ጊዜ እንደ ቆየ ባናውቅም ለብዙ ቀናት የቆየ አይመስልም። እንግዲህ ይህ የጳውሎስ ሁለተኛ ጉዞ መጨረሻ ነው።

**ጥያቄ 4፡- የጳውሎስን ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ የሚያሳየውን ካርታ ተመልከትና ከ 49 -52 ዓ.ም ድረስ የሄደባቸውን አገሮች በድጋሚ አጥናቸው።**

በአንጾኪያ ለጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ ጳውሎስ ሦስተኛውን ጉዞ ይጀምራል። ይህን ጉዞውን ያከናወነው ከ 53 - 57 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ላይ ጳውሎስ ብዙውን ጊዜውን ያሳለፈው በፊት የተመሠረቱትን ቤተክርስቲያናት በመጎብኘት ነው። በመጀመሪያው ጉዞ ላይ የመሠረታቸውን የገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደገና ይጎበኛቸዋል። በመቀጠልም ወደ ኤፌሶን ይሄድና ለሁለት ዓመት ያህል በዚያ ሲያገለግል ይቆያል። በመጨረሻም ወደ ኢየሩሳሌም ከመመለሱ በፊት መቄዶንያና አካያ የሚገኙትን ቤተክርስቲያናት ይጎበኛል።

ጳውሎስ ከኤፌሶን ከሄደ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ከእስክንድርያ ወገን የነበረ አንድ አጵሎስ የሚባል ነገር አዋቂ ወደ ኤፌሶን ይመጣል። እስክንድርያ በሮሚው ዘመነ መንግሥት ጊዜ ሁለተኛዋ ታላቅ ከተማ ነበረች። ይህቺ በግብፅ የምትገኝ ከተማ፣ ታላቅ የእውቀት ማዕከል በነበረው ዩኒቨርሲቲዋ በጣም ትታወቅ ነበር። አጵሎስ ደግሞ ከፓለስታይን የመጣ አይሁዳዊ ባለመሆኑ ከኢየሱስ ወይም ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር አልተገናኘም። ሆኖም ባመዛኙ ሲታይ የኢየሱስን የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎት በወሬ ወሬ በእስክንድርያ ሰምቶ ካመነ በኋላ የሰማውን የሚመሰክር ይሆናል። ያም ሆነ ይህ እውቀቱ በከፊል ነበር። እንዲያውም አንዱ የሚያውቀው ጥምቀት የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ ነበር። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅን አያውቅም። የቤተክርስቲያንን መጀመርና የመንፈስ ቅዱስን በአማኞች ላይ መውረድ አልሰማም። ስለዚህም የእርሱ መልእክት ትክክል የነበረው በከፊል ነው።

አጵሎስ የሚያውቃትን እውነት ይመሠክር ነበር። በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ስለነበር ይጠብቁት የነበረው መሢሕ ኢየሱስ እንደሆነ ሰዎችን ያሳምን ነበር። አጵሎስ በትክክል ያስተምር የነበረ ሰው ነው! በምኩራብም በደንብ ገልጦ አስተምሯል።

ጥያቄ 5:- ሀ) አንዳንዴ ያልሠለጠኑ ወንጌላዊያን ወጥተው ወንጌልን እንዲሰብኩ ማድረጉ አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው? ለ) የሚያስተምሩት ትክክል ካልሆነ ምን ዓይነት ነገር ሊከሰት ይችላል?

ጵርስቅላና አቂላ በምኩራብ ሲያስተምር ሰሙት። (ማሳሰቢያ፡- አንዳንዶች የጵርስቅላ ስም መጀመሪያ መጻፉ በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እሷ ከአቂላ የበለጠ አገልግሎት እንደነበራት የሚገልጽ ነው ብለው ያስባሉ)። በምታስተምርበት ወቅት አስፈላጊውን ያህል ብቃት አልነበረህም ብለው አልተቃወሙትም። የእግዚአብሔርን መንገድ በተመለከተ በቂ እውቀት እንደሌለው ከተገነዘቡ በኋላ ወደ ቤታቸው በመጋበዝ እሱ ከሚያውቀው በላይ በደንብ አድርገው ወንጌሉን ይገልጡለታል። ሆኖም በሐዋርያት ሥራ 19፡ 1-7 ላይ ባለው ታሪክ ላይ እንደምናየው አጵሎስ እስከአሁን ተገቢውን ግንዛቤ ያገኘ አይመስልም፤ ምክንያቱም የእሱ ደቀመዛሙርት ስለ መንፈስ ቅዱስ አያውቁም ነበርና ነው።

አጵሎስ ሌላው የጌታ ጠንካራ ምሥክር ነበር። ወደ አካይያ ሄዶ ለማገልገል የፈለገውም ስለ ቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ሰምቶ ይሆናል። ጵርስቅላና አቂላም በክርስቲያኖቹዘንድ የታወቁ ስለነበሩ ይቀበሉት ዘንድ ወደ ደቀመዛሙርቱ ጻፉለት። በቆሮንቶስም ሳለ ፍሬያማ የሆነ አገልግሎት ነበረው። በሕዝብ ፊትም ክርክር ተነሥቶ አይሁዳውያን የተሳሳተ አመለካከት እንደያዙ በግልጽ ሊያሳይ ችሏል። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ግን በእሱ የሚሠራውን ጌታ ከማየት ይልቅ የእሱን ችሎታ ማድነቅ ጀመሩ። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ በግልጽ እንደሚታየው አንዳንድ ክርስቲያኖች የአጵሎስ ደቀመዝሙር ነኝ፤ ሌሎች ደግሞ የጳውሎስ ደቀመዝሙር ነኝ በማለት ጉራቸውን ይነዙ ነበር። ጳውሎስም «እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር» በማለት ይቆጣቸዋል (1ቆሮ. 3፡ 3-7፤ 1ቆሮ 16፡ 12)። ለሰዎች ተገቢ ያልሆነ ክብር እንዳንሰጥ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። የፈለገውን ያህል ስጦታ ቢኖረው መከተል ያለብን ያዳነንን ኢየሱስን ነው።

ጥያቄ 6 :-አይንን በእግዚአብሔር ላይ ከማድረግ ይልቅ አንድን መሪ መከተል ወይም በመሪዎች መመካት አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው?

የጳውሎስ ስብከት እንደ አጵሎስ በጣም ግሩም ባይሆንም፥ በኃይልና በመንፈስ የታገዘ በመሆኑ ብዙ ነፍሳት እንዲድኑ አድርጓል። ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ «... ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር ምሥክርነቴ በእናንተ እየተናገርሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደ ተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበርና ብሏል (1ቆሮ. 2፡ 1-2)።

ጳውሎስ በዚያን ጊዜ በነበረው ዓለም የእግዚአብሔርን ቃል ዘር ዘራ። ከዚያም እግዚአብሔር የተዘራውን ዘር ውሃ የሚያጠጡና የጀመረውን ሥራ የሚቀጥሉ እንደ አጵሎስ ጵርስቅላ፥ አቂላ፥ ጢሞቴዎስ ያሉትን ሰዎች አስነሣ። የእግዚአብሔር ቃል ከአንድ ታማኝ ምሥክር ጋር ተነሥቶ ምን ያህል ቦታ ሊያዳርስ እንደሚችል መገመቱ በጣም አዳጋች ነው። እኛ ማድረግ ያለብን አንድ ነገር ታማኞች መሆን ነው። ብዙ በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ልባቸውን ነክቶ አንድ ውሳኔ ላይ

እንዲደርሱ ከማድረጉ በፊት የብዙ ሰዎችን ምሥክርነትና ትምህርት ሰምተዋል። ሆኖም መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ ሰው በመጠቀም ያንን ሰው በእምነት ወደ ጌታ እንዲመጣ ያደርጋል። እኛ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ሆነን እርሱ በፈለገው መንገድ እንድንሠራ የምንደረግ መሣሪያዎች ነን።

ጥያቄ 7፡- እግዚአብሔር አጋጣሚውን ባመቻቸልህ በማንኛውም ጊዜ ቃሉን በመዝራት ይሁን በማጠጣት ሥራህን በታማኝነት እየፈጸምክ ነው?

# ሁለተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 19፡ 1-7

ጳውሎስ ለጥቂት ቀናት በአንጾኪያ ከቆየ በኋላ ሶስተኛውን ሚሲዮናዊ ጉዞውን በገላትያና በፍርግያ አገሮች በመሄድና ደቀመዛሙርቱን በማበረታታት ይጀምራል (ሐዋ. 18፡ 23)። በእርሱ ጸሎት አማካኝነት የተመሠረቱትን አብያተ ክርስቲያናት ምንም ቢሆን አይረሳቸውም፤ አመቺ ሁኔታም ባጋጠመው ጊዜ ሳይጎበኛቸው አያልፍም። ከዚህም በኋላ ከፍርግያ በመነሣት ወደ ኤፌሶን ይሄዳል።

ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ጊዜና የሰው ጊዜ አንድ ዓይነት አይደሉም። ከብዙ ዓመታት በፊት ጳውሎስ በእስያ ክፍለ ሀገርና ዋና ከተማዋ በሆነችው በኤፌሶን ለመሥራት ይፈልግ ነበር። ሆኖም መንፈስ ቅዱስ እንዳይሄድ ይከለክለዋል። ይህም የሆነው ምናልባት የሰዎቹ ልብ ለወንጌል ገና ያልተዘጋጀ ሆኖ ይሆናል። ልባቸው ዝግጁ ሆኖ ሲገኝ መንፈስ ቅዱስ በኃይል ይሠራል። ሰይጣንም የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሥፋፋ እንቅፋቶችን ይፈጥራል። እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ እንደሚ6ሰራ የሚገልጽልን አንዱ ነገር የጠላት ተቃውሞ ነው። ይህን ተቃውሞ ጳውሎስ ከእዚህ ወደ ኤፌሶን በሚያደርገው ጉዞ በጉልህ እናየዋለን።

የሐዋርያት ሥራ 19፡ 1-7 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ

ጥያቄ 8፡- ሀ) በኤፌሶን ያገኛቸውን ደቀመዛሙርት ጳውሎስ ምን ብሎ ነው የጠየቃቸው? ለ) የዮሐንስ ጥምቀት ምንድነው?

ጥያቄ 9፡- 1ቆሮ. 11-14 አንብብ። ሀ) በልሳን መናገር ጥቅሙ ምንድነው? ለ) በልሳን ከመናገር በላይ የሆነው ነገር ምንድነው? ሐ) በቤተክርስቲያን ጉባዔ ውስጥ በልሳን ስለ መጠቀም ጳውሎስ ያወጣቸውን ድንጋጌዎች በዝርዝር ጻፍ።

ጳውሎስ ሶስተኛውን ሚሲዮናዊ ጉዞውን የጀመረው ከአንጾኪያ በመነሣት ነው። ከእርሱ ጋር ማን እንደሄደ ባይጠቀስም ጢሞቴዎስና ሲላስ አብረውት የነበሩ ይመስላል። በዚህ ጉዞ ላይም በጻፋቸው መልእክቶቹም ውስጥ በገላትያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በጣም ያስብ ነበር። ይህም የሆነው በቤተክርስቲያኑ የሐሰት ትምህርት በመግባቱና በዙዎች የጳውሎስ ሐዋርያ መሆን አጠያያቂ ስለሆነባቸው ነው (ገላ 1፡ 6-12 ተመልከት)።

ጳውሎስ ቃል በገባው መሠረት ወደ ኤፌሶን ተመልሶ ለማገልገል ይፈልግ ነበር። በዚህም መሠረት ረጅሙን የንግድ ቀጠና የሆነውን መንገድ በመተው፥ በገላትያ በኩል ያለውን አቋራጭ መንገድ ይዞ ይሄዳል። በሁለተኛውና በሶስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ መካከል በነበረው ጊዜ ውስጥም አጵሎስ ወደ ኤፌሶን ሄዶ አንዲት ትንሽ ቤተክርስቲያን ሳያቋቁም አልቀረም።

ጳውሎስ ኤፌሶን ሲደርስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምንም ግንዛቤ ያልነበራቸውን አሥራ ሁለት ደቀመዛሙርት ያገኛል። በአመዛኙም እነዚህ ደቀመዛሙርት የአጵሎስ ሳይሆኑ አይቀርም። እነዚህ ሰዎች የተጠመቁት ወደ ኢየሱስ ያመለከት በነበረው በዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት ነው። ጳውሎስም መንፈስ ቅዱስ ተቀብለው እንደሆነ ሲጠይቃቸው መንፈስ ቅዱስ የሚባል ነገር ምንም እንዳልሰሙ ይነግሩታል። ጳውሎስ ስለዚህ ነገር በደንብ ካስረዳቸው በኋላም እነዚህ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይጠመቃሉ። መንፈስ ቅዱስንም፥ ልክ እንደ ሳምራውያኑ እንደ ቂሣርያ አሕዛብ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተቀብለው በልሳን ይናገሩና ትንቢትን ይተነብዩ ነበር። አሁንም እንደገና የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በማይታወቅበት ቦታ በድንቅ ይገለጣል። መንፈስ ቅዱስም ከልሳን ስጦታ ጋር አብሮ ድንቅ በሆነ ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን ጋር ለመጨረሻ ጊዜ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ መሰጠቱ የተጠቀሰው በዚህ ሥፍራ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ዛሬ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበላቸው ማስረጃ የሚሆናቸው በልሳን መናገራቸው ነው። ሌሎች ደግሞ የእጅ መጫኑ ሥርዓት አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። ሆኖም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉትን ድንቅ ለውጦች ካጠናን ይሄ ነው ብለን ልንከተለው የሚገባን ሥርዓት አናገኝም። አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ እጃቸውን በሰዎቹ ላይ የጫኑት ጴጥሮስ፥ ዮሐንስና ጳውሎስ ብቻ ናቸው። እስቲ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ላይ የወረደባቸውን አራት ጊዜያቶች መለስ ብለን እንያቸው።

*1.* በበዓለ ሐምሳ ዕለት 120 አይሁዳውያን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በአካባቢው ተሰብስቦ ያዩዋቸው በነበረው ሕዝብ ፊት ልሳኖች ይናገሩ ነበር። በዚህ ጊዜም እጅ አልተጫነባቸውም (ሐዋ. 2፡ 1-13)።

*2.* በሰማሪያ ይገኙ የነበሩ አማኞች አምነው በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠመቁ! ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን አልተቀበሉም ነበር። ከዚያም ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃቸውን ይጭኑባቸውና መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ። በልሳን ስለ መናገር የተጠቀሰ ነገር የለም (ሐዋ. 8፡ 14-17)። ሳምራውያኑ መንፈስ ቅዱስን ልክ እንደ አይሁዳውያኑ መቀበላቸው ለሐዋርያቱና ለአይሁዳውያን አሕዛብ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ልክ እንደ እነሱ እኩል እንደሚታዩ እንደ ማስረጃ ሆኗቸዋል።

*3.* ቆርኖሌዎስና በቤቱ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎቹ ጴጥሮስ ወንጌልን እየሰበከላቸው ሳለ መንፈስ ቅዱስ በእነሱ ላይ ይወርድና በልሳን መናገርና እግዚአብሔርን ማመስገን ይጀምራሉ (ሐዋ. 10፡ 1-6)። በእነዚህ ሰዎች ላይ እጅ አልተጫነም! በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቁ ሁኔታ አሁንም ከማመን ጋር የተያያዘ ነው! ምክንያቱም ሁለቱም የተከናወነው በአንድ ጊዜ ነው። አሁንም ይህ ለሐዋርያትና

ለአይሁዳውያን አሕዛብም ሆኑ ሳምራውያን ልክ እንደ አይሁዳውያን በተመሳሳይ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ በመቀበላቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ በእኩል ዓይን መታየት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው።

ከላይ በተጠቀሱት ሶስት የተለያዩ ወቅቶች መንፈስ ቅዱስ በዘር በጎሳ የተለያዩ ሕዝቦች አንድ መሆናቸውን ሲገልጽ እናያለን። እስቲ አሁን እነዚህ የተለዩት ሶስት ጊዜዎች ከሐዋርያት 1፡ 8 ጋር እናነፃፅራቸው። ኢየሱስ በመጨረሻ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ትዕዛዝ በሶስት ደረጃዎች ከፋፍሎ ወደ ዓለም ሁሉ ወንጌልን አዳርሱ የሚል ነው።

ሀ) በኢየሩሳሌምም በይሁዳም በዚህ ሥፍራ የሚገኙት ሕዝቦች የአብርሃም ልጆች የሆኑት እውነተኞቹ አይሁዳውያን ናቸው። እነዚህ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ፤ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው በልሳን መናገራቸው ነው። በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የሚገኙ ሌሎቹ አይሁዳውያን በእነዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ውስጥ ስለማለፋቸው ምንም ዓይነት ማስረጃ የለንም። በምትኩ ግን እግዚአብሔር አይሁዳውያን ሲያምኑ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው ጀመር።

ለ) በሰማርያ፡- ግማሽ ወገናቸው ከአሕዛብ ሌላኛው ደግሞ ከአይሁድ የነበሩት ሳምራውያን የአይሁዳውያን ጠላቶች ነበሩ። ምንም እንኳ የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቢከተሉም ከዚያ ወዲያ ያለውን አያምኑበትም ነበር። ይህም ቢሆን፥ በጴጥሮስና በዮሐንስ በኩል እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ለእነዚህ ሰዎች በመስጠት በእርሱ ቤት አይሁዳውያንና ሳምራውያን እኩል መሆናቸውን በማያሻማ ሁኔታ ገልጿል። ከዚህም በኋላ እንደቀድሞዎቹ ሌሎች ሳምራውያን መንፈስ ቅዱስ ተቀብለዋል የሚል ነገር አናነብም።

ሐ) እስከ ምድር ዳር ይህም አሕዛብ የሚኖሩበት ዓለም ነው። አይሁዳውያን ከሳምራውያን በላይ አሕዛብ ከደኅንነት ተስፋ ውጪ ናቸው ብለው ነበር የሚገምቱት። ከዚያም እግዚአብሔር ያለ ጴጥሮስ ዕርዳታ መንፈስ ቅዱሱን ለአሕዛብ ሲሰጥ እነሱም በእግዚአብሔር ቤት ልክ እንደ እነርሱ እኩል ተቀባይነት እንዳላቸው አሳይቷል። በተጨማሪም በቆርኔሌዎስ ቤት የነበሩት የመጀመሪያዎቹ አሕዛብ ያለፉበት ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ያለፉ ሌሎች አሕዛብ በአዲስ ኪዳን አልተጠቀሱም።

4. በኤፌሶን የነበሩት አስራ ሁለቱ ሄለናዊ አይሁዳውያን ጳውሎስ እጁን ሲጭንባቸው መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ (ሐዋ. 19፡ 1-7)። እነዚህ ሰዎች ከሌሎች በጣም ለየት ይላሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን እየኖሩ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ምን እንደሆነ አላወቁም። ይህም ከክርስቲያኖች ጋርም ሆነ ከቤተክርስቲያን ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች የሚያውቁት ስለ ዮሐንስ ጥምቀት ብቻ ነው። ይህም ሆኖ ንስሐ ግቡ መሢሑን ኢየሱስ ክርስቶስን ጠብቁ የሚለውን የዮሐንስን መልእክት ያምኑበት ነበር። እግዚአብሔርም በጳውሎስ

በመጠቀም እነዚህን የብሉይ ኪዳን ዘመን ቅሪቶች (ልክ ከመከሩ ጊዜ በኋላ እንደሚቀየር እህል የነበሩ) ወደ ቤተክርስቲያን በማምጣት የአዲስ ኪዳን ተከታዮች ያደርጋቸዋል።

ምናልባት ይህ ነገር የሆነበት ሌላ ሁለተኛ ምክንያት ሳይኖር አይቀርም። በዚህ ጊዜ አንዳንድ በገላትያና በእስያ የነበሩ ሰዎች የጳውሎስን ሐዋርያነት ተጠራጥረው ነበር። ሆኖም ልክ እንደ ጴጥሮስና ዮሐንስ ጳውሎስ እጁን ሲጭንባቸው መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ። ስለዚህም በኢየሩሳሌም ከሚገኙት አሥራ ሁለት ሐዋርያት ጋር እኩል ሆነ።

በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ዋነኛው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ በእምነት መቀበሉ ነበር። የዮሐንስ ጥምቀት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት የሚያመለክት ነበረ፤ ስለዚህ ብቻውን ብቃት አልነበረውም። የመንፈስ ቅዱስ መውረድም የእምነታቸው መረጃ ነበር። በተጨማሪም ከላይ ያየናቸው አራቱ ሁኔታዎች አንድ ሰው አይሁዳዊ ይሁን ሳምራዊ ወይም ሄለናዊ አይሁድ ወይም አሕዛብ በክርስቶስ ካመነ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚሰጠው የሚገልጹ ናቸው።

ይህን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጥናታችን እየገፋንበት ስንሄድ በሁሉም የመለወጥ አጋጣሚዎች ላይ በልሳን የመናገር ወይም እጅ የመጫን ሥርዓት እንደተደረገ የሚገልጽልን ምንም ማስረጃዎች አናገኝም። በተጨማሪም እጃቸውን ይጭኑ የነበሩት ሐዋርያት ብቻ ነበሩ።

መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል መጸለይ አለባቸው አይልም። በምትኩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ለሁሉም ክርስቲያኖች ሲያምኑ እንደ ስጦታ እንደሚሰጥ ነው የሚያሳየን። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ ለመንፈስ ቅዱስ መኖር ማስረጃ የሚሆነው በልሳን የመናገር ስጦታ ሲታይ ነው አይልም። መንፈስ ቅዱስ እራሱ በፈለገው መንገድ ለተለያዩ ግለሰቦች የተለያዩ ስጦታዎችን ይሰጣል። በልሳን መናገርም አንድ ክርስቲያን ከሌላው ክርስቲያን ይበልጥ ቅዱስ መሆኑን የሚገልጽ አይደለም። ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ በልሳን መናገርን ቢፈቅድም ከስጦታዎች ሁሉ የመጨረሻው ትንሹ እንደሆነና በአግባቡ መጽሐፍ ቅዱስ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ልንጠቀምበት እንደሚገባ ግልጽ ነው። በልሳን የመናገር ስጦታ ላይ በጣም ትኩረት ከማድረግ የመንፈስ ፍሬ የሆነው ፍቅር ላይ ማተኮሩ ዋነኛ መልካምና የተሻለ ነው።

ጥያቄ 10:- 1ኛ ቆሮ. 12-14 አንብብ። በልሳን ስለ መናገር ጳውሎስ የገለጻቸውን ነገሮች በሙሉ በዝርዝር ጻፋቸው።

ጥያቄ 11:- ገላትያ 5፡ 22-23 አንብብ። በብዙ መንገድ ስናየው እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች በልሳን ከመናገር ይበልጥ በጣም አስፈላጊ ዋነኛ ስጦታዎች የሚሆኑት እንዴት ነው?

ምንም እንኳ ክርስቲያኖች በልሳን በመናገሩ አስፈላጊነት ላይ የተለያየ አመለካከት ቢኖራቸውም እምነታችንን በስሜታችን ላይ ሳይሆን ግልጽ በሆኑት የመጽሐፍ ቅዱስ

ትምህርቶች ላይ ማድረጋችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል። ይህንን ጉዳይ በተመለከተም ከእኛ አስተሳሰብ ጋር የማይስማሙ ክርስቲያኖችን መታገስ አለብን። ጳውሎስ እንዳለውም «ዛሬ በመስታወት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ፤ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ» (1ቆሮ. 13፡ 12)። ደኅንነትንና ኢየሱስን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረውን ነገር አጥብቀን እንያዝ። ግልጽ ያልሆኑልን ነገሮች አሁንም አሉ በእነዚህ ልዩነቶቻችን ደግሞ እርስ በርሳችን በትዕግሥት እንተያይ። እንተንም ከሌሎች ክርስቲያኖች እሻላለሁ የሚል መንፈሳዊ ኩራት እንዳይዝህ ተጠንቀቅ። የፈሪሳውያን ኃጢአት የነበረውም ይህ ነው።

## ነሥስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 19፡ 8-41

የሐዋርያት ሥራ 19፡ 8-41 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 12፡- ሀ) 1. በኤፌሶን በምኩራብ ውስጥ የነበሩ አይሁዳውያን ለወንጌሉ የሰጡት ምላሽ ምን ዓይነት ነው? 2. ጳውሎስ ማስተማሩን የቀጠለው በየት ነው? 3. ጳውሎስ በኤፌሶን በሰጠው ትምህርት ምክንያት ወንጌል እስከየት ድረስ ተስፋፋ?

ለ) 1. ስለ ጳውሎስ በኤፌሶን ስለነበረው የፈውስ አገልግሎት ገለጻ አድርግ። 2. የአስቄዋ ልጆች ምን ሆኑ? 3. ይህስ በኢየሱስ ስም ላይ ምን ዓይነት ለውጥ አመጣ?

ሐ) 1. ጳውሎስ በኤፌሶን ያገኛቸውን አሥራ ሁለት ደቀመዛሙርት ያስተማራቸው ነገር ምንድነው? 2. እውነተኛ እምነት እንደነበራቸው ምን ማስረጃ ነበር?

መ) 1. ጳውሎስ ኤፌሶን በሚገኘው ምኩራብ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ነው ያስተማረው? 2. በምኩራብ ማስተማሩን ያቆመው ለምንድነው? 3. ከዚያስ ያስተምር የነበረው የት ነው? 4. ለምን ያህል ጊዜ ነው ጳውሎስ በኤፌሶን የቆየው.

ሠ) 1. በአይሁዳውያንና በግሪኮች ላይ ፍርሃት የጣለባቸው ነገር ምንድነው? 2. እሱ ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ ወደ መቄዶንያ የላካቸው እነማንን ነው?

ረ) 1. በኤፌሶን ሁከት እንዲነሣሣ ያደረገው ነገር ምንድነው? 2. ሁከቱ የበረደው እንዴት ነው? ሰፋ አድርገህ አብራራው።

ሰ) 1. የኤፌሶንን ሰዎች በጳውሎስ ላይ እንዲነሡ ያደረጋቸው ማነው? 2. የተናደዱት ለምንድን ነው? 3. ምን እያሉ ነው የጮኹት?

ሸ) 1. ሕዝቡ እነማንን ነው የያዘው? 2. ጳውሎስ ሰዎቹን ያላናገራቸው ለምንድነው?

ቀ) 1. ሕዝቡን ጸጥ ያሰኘው ማነው? 2. ይጮኹ ለነበሩት ሰዎች የነገራቸው ነገር ምንድነው? 3. ክሳቸውን ወዴት ይዘው እንደሄዱ ነው የነገራቸው?

ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ተመልሶ፥ በምኩራብ ውስጥ ለሦስት ወር ያህል ሊያስተምር ችሏል። ልክ እንደ አጵሎስ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ለመግለጽ ከብሉይ ኪዳን ላይ

ይጠቅስ ነበር። ታዲያ እንደተለመደው ይህ ትምህርት በአይሁዳውያን መካከል ክፍፍል ይፈጥራል። አንዳንዶች የጳውሎስ መልእክት ትክክል ነው ብለው ተቀብለውታል፤ ሌሎች ግን አናምንም ብለው «መንገዱን» ወይም ክርስትናን መስደብና ማጥላላት ይጀምራሉ። በዚህም ጊዜ የከረረ ክፍፍል እንዳይፈጥር ብሎ ጳውሎስ ደቀመዛሙርቱን ወደጢራኖስ የሚባል ትምህርት ቤት ይወስዳቸዋል። ጢራኖስ ማን እንደሆነ አናውቅም፤ ግን የታወቀ ፈላስፋ ወይም የትምህርት ቤቱ ባለቤት ሊሆን ይችላል። ከሁኔታዎች እንደሚታየው ይህን ትምህርት ቤት ይጠቀሙበት የነበረው ጠዋት ላይ ገና ፀሐዩ ሳያይል ይመስላል። ነገር ግን ጳውሎስ ኃይለኛ ሙቀት በነበረበት ጊዜ እንዲጠቀምበት ፈቀዱለት። ጳውሎስም ጠዋት ጠዋት ድንኳን እየሰፋ ከሰዓት ሕዝቡን ሰብስቦ የእግዚአብሔርን ቃል ሳያሰማቸው አይቀርም። በዚህም ዓይነት ጳውሎስ ለሁለት ዓመት ያህል አስተማረ። እነዚህ ዓመታት በጣም ፍሬ የተገኘባቸው ናቸው። ምክንያቱም በእስያ የኖሩት አይሁድና የግሪክ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ሰምተዋልና ነው። ምናልባትም ሰዎቹ በሙሉ ከጳውሎስ ሳይሆን ከሚያስተምሯቸው ሰዎች አንደበት ይሆናል የሰሙት።

ጥያቄ 13፡- ወንጌላውያን ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ክርስቲያኖች ወንጌልን የማስተላለፍ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይህ ክፍል የሚያስተምረን እንዴት ነው? በቆላስያስ፥ በኢያራ፥ በሎዶቂያና በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 2 እና 3 ላይ የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የተመሠረቱት በዚህ ጊዜ ውስጥ ነው (ቆላ 2፡ 1 እና 4፡ 13)። የጳውሎስ አገልግሎትም በጣም ግቡን የመታ ስለነበር፥ ኤፌሶን ለብዙ መቶ ዓመታት የክርስትና መዲና ልትሆን ችላለች።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደምናየው፥ ጳውሎስ በኤፌሶንም ያገለግል በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር የመልእክቱን እውነተኛነት ተአምራትን በእርሱ በኩል በመፈጸም ያረጋግጥለት ነበር። ጳውሎስ የነካው ልብስ ወይም ጨርቅ በሽተኞችን ይፈውስ ነበር፤ ይህም የኢየሱስን ልብስ ከኋላው መጥታ ከነካች በኋላ የተፈወሰችውን ሴትዮ አይነት ፈውስ ነው (ማር. 5፡ 27-29፤ 6፡ 56)። የኢየሱስም ስም አጋንንትን በማውጣት ትልቅ ኃይል ስለነበረው ሌሎች አጋንንት የሚያስወጡ ሰዎችም «ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ ስም እናምላችኋለን» እያሉ ክፉ መናፍስትን በኢየሱስ ስም ለማውጣት ይሞክሩ ነበር።

ሥራቸው አጋንንትን ማስወጣት ከነበሩት ሰዎች ውስጥ ሰባቱ የካህናት አለቃ የአስቄዋ ልጆች ይገኙበታል። ይህ ሰው አይሁዳዊ ነኝ እያለ በአስማት ክፉ መናፍስትን የሚያስወጣ ሳይሆን አይቀርም። ይተዳደርም የነበረው በዚሁ ነው። የኢየሱስ ስም አጋንንትን በማውጣት የነበረውን ኃይል ሲያዩ የአስቄዋ ልጆች «በኢየሱስ ስም ተጠቅመው አጋንንትን ለማውጣት ሞከሩ። አንድ ቀንም ክፉ መንፈስ መልሶ «ኢየሱስን አውቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፤ ለእናንተስ እነማን ናችሁ?» አላቸው። ከዚያም በክፉ መንፈስ ተይዞ የነበረው ሰውዬ በሰባቱ የአስቄዋ ልጆች ላይ

ዘሉ ይወጣባቸዋል፤ ያቆስላቸዋል፤ ዕራቁታቸውን ሆነው እስኪያመልጡ ድረስም ይበረታባቸዋል።

ጥያቄ 14፡- ሀ) ክፉው መንፈስ ያጠቃቸው ለምን ይመስልሃል? ለ) ይህ ታሪክ በኢየሱስ ስም ስለሚጠቀሙ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?

ይህ በአስቄዋ ልጆች ላይ የሆነው ነገር ሲሰማ በኤፌሶን ይኖሩ የነበሩት አይሁዳውያንና የግሪክ ሰዎች ላይ ፍርሃት ጣለባቸው፤ የኢየሱስንም ስም አከበሩ። በዙዎችም በኢየሱስ ያመኑ የእምነታቸውን እውነተኛነት ድሮ ያደርጉ የነበረውን ነገር በመተው በግልጽ አሳይተዋል። አስማተኞችም የነበሩት መጽሐፍቶቻቸውን በሰው ሁሉ ፊት በማቃጠል፥ በሕዝብ ፊት ንስሐ ገብተዋል። የእነዚህ መጻሕፍት ዋጋም ወደ ሃምሳ ሺህ ብር ይጠጋ ነበር። አስተውል፤ ይህ ሁሉ ታላቅ ነገር ሲደረግ ክብር የተሰጠው ለጳውሎስ አልነበረም። ክብር ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሆን ብርቱ ጥንቃቄ ያደርግ ነበር። ሰዎችም በጌታ ኢየሱስ ስም ኃይል ተገረሙ፤ የጌታም ቃል በኃይል እያደገ በከተማዋና በመላው እስያ ተሰራጨ።

ይህ ታሪክ የእግዚአብሔር መንፈስ በሚያስደንቅ ሁኔታ በአንድ አካባቢ እንዴት እንደሚሠራ የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ እየሠራ ለመሆኑ ማስረጃ የሚሆኑን ብዙ ነገሮችን ልንዘረዝር እንችላለን፡-

1. ፍርሃት ይኖራል፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ደግሞ ይከበራል።

2. በሕዝብ ፊት በግልጽ ንስሐ መግባት ይኖራል።

3. ሰዎች ንስሐ በመግባት የድሮውን አኗኗርና የአምልኮ ሥርዓትን ለመተዋቸው በተግባር ይገልጹታል።

4. የእግዚአብሔር ቃል በሁሉም ቦታ እንዲዳረስ ምስክር ሆኖ የመቅረብ ድፍረት ይኖራል።

እነዚህ አራት ነገሮች ሲታዩ የመንፈሳዊ መነቃቃት ጊዜ ነው እንለዋለን። የእግዚአብሔርም መንፈስ በታላቅ ኃይል እንዲሠራ ሌሎች ሁለት አስፈላጊ ነገሮች አሉ። አንደኛ የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽና በድፍረት የማቅረብ ሂደት አለ። ሁለተኛ የእግዚአብሔር ሕዝብ በጸሎት የመትጋት ሁኔታም አለ። እነዚህ የመነቃቃት ጊዜዎች ሲመጡ፥ አንድን ከተማ፥ አንድን ክፍለ ሀገር አንድን አገር እስከ መቀየር ይደርሳሉ። ታዲያ መንፈሳዊ መነቃቃት በኢትዮጵያ እንዲኖር መጸለይ ያለብን አይመስልህም?

ጥያቄ 15፡- ይህ ዓይነቱ መነቃቃት በትንሹም ቢሆን በቤተክርስቲያንህ ወይም በከተማህ ውስጥ የታየው እንዴት ነው? ይህ ካልሆነ አንተና ቤተክርስቲያንህ እግዚአብሔር ልክ በኤፌሶን እንደሠራው በእናንተ መካከልም እንዲሠራ መጸለይ ያለባችሁ መስሉ አይታይህም?

ጳውሎስ ለሁለት ዓመት ያህል በኤፌሶን ያገለግላል፤ በዚህ ጊዜ መስበክ ብቻ ሳይሆን፥ እንደ 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ ያሉትን መጻሕፍት የጻፈበት ጊዜ ነው። ከዚህም በኋላ፥ ወደ ሌሎች ከተሞች ለመሄድ ይዘጋጃል። ከሁሉም በላይ የሮሜው መንግሥት መዲና ወደ ነበረችው ወደ ሮም ለመሄድ በጣም ይፈልግ ነበር። ከዚህም ሌላ በሮሜው መንግሥት ክልል ውስጥ ርቃ ትገኝ ወደ ነበረችውም ወደ እስፓኝ መሄድ ይፈልግ ነበር (ሮሜ 16፡ 19-29)። ለሮሜ ሰዎች እንደተናገረውም ምኞቱና ፍላጎቱ ክርስቶስ ተሰብኮባቸው በማይታወቁ ቦታዎች ሁሉ ሄዶ መስበክ ነው። ነገር ግን ወደ ሮም ከመሄዱ በፊት በመቄዶንያና በአካይያ አልፎ አብያተ ክርስቲያናትን ጎብኝቶ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ይፈልግ ነበር። ጳውሎስ ለጊዜው በእስያ መቆየቱን ቀጥሎ፥ ጢሞቴዎስንና እርስጦስን ግን ወደ መቄዶንያ ላካቸው። እነርሱም እዛው ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ምናልባት ጳውሎስ ሳይመጣ ለኢየሩሳሌም አብያተ ክርስቲያናት ሊያደርጉት ያሰቡትን የገንዘብ እርዳታን ይሰበስቡ ዘንድ 2ኛ የቆሮንቶስ መልእክቱን ይዘው ሳይሄዱ አይቀሩም የሚል ግምት አለ።

በአንድ አካባቢ የእግዚአብሔር ኃይል በሙላት ሲገለጥ፥ የሰይጣን ተቃውሞም በዛው መጠን ይጨምራል። የጳውሎስ ትምህርት ብዙዎቹን በኤፌሶን የነበሩትን ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ አድርጓቸዋል። በዚህም ምክንያት አርጤምስን ማምለካቸውን አቁመዋል፤ አርጤምስም የሚባለው የግሪክ ስም ለሮማው ዲያና ለተባለችው የጣኦት አምላክ የተሰጠ ስም ነበር። ታዲያ በድንገት በጳውሎስና በቤተክርስቲያን ላይ ያልተጠበቀ ተቃውሞ ይነሣል።

በኤፌሶን አንድ ድሜጥሮስ የተባለ የብር አንጥረኛ ነበር። ለአርጤምስ የቤተ መቅደስ ምስሎችንም እየሠራ ብዙ ትርፍ ያገኝ ነበር። ታዲያ ብዙ ሰዎች በእስያና በኤፌሶን ዓይናቸውን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማቅናታቸውን ሲያይ ሥራው ተንቆ ምንም ንግድ አይኖረኝም ብሎ ፈራ። በዚህም መሠረት የብር አንጥረኞችን በሙሉ ይሰበስብና፥ የጳውሎስ ስብከት ንግዳቸውን እያመከነው እንደሆነ ይነግራቸዋል። በዚህ ጊዜ አንጥረኞቹ በጣም ይናደዱና «የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት» እያሉ መጮህ ይጀምራሉ። ከዚያም ይህ ጩኸት አንዱ ከተማዋን በሙሉ ይደበላልቃታል።

ጥያቄ 16፡- ሰይጣን የተወሰነ ሰዎችን ስስታምነት ተጠቅሞ የወንጌሉን ሥርጭት ለማደናቀፍ ይሠራ የነበረው እንዴት ነው?

በከተማዋ እየዞሩ ሲጮኹ፥ ብዙዎቹ ለምን እንደሚጮኹ ሳያውቁ ዝም ብለው በስሜት ከእነርሱ ጋር ተደባልቀው መጮህ ጀመሩ። ከመቄዶንያ ቤተክርስቲያን የመጡትን የጳውሎስ ጓደኞች ጋዩስንና አርስጥሮኮስን ይዘው ለፍርድ የሚያቀርቧቸው ይመስላል። ወደ አንድ ቴአትር ቤት ይከቷቸዋል። ጳውሎስ ከዚህ ሁሉ ቢያመልጥም ለተሰበሰበው ሕዝብ ገብቶ ንግግር ማድረግ ፈልጎ ነበር። ሆኖም፥ በኤፌሶን የነበሩት አማኞች እንዳይገባ ከለከሉት። ከዚህም ሌላ አንዳንድ ወዳጆች የነበሩ ባለሥልጣኖች ወደ እርሱ ልከው ወደ ቴአትር ቤት እንዳይገባ ለምነውታል።

ጳውሎስን ይጠሉት የነበሩት አይሁዳውያንም እሱንና ተከታዮቹን ለመቃወም ቆርጠው ተነሥተዋል። በዚህም መሠረት በሕዝብ ፊት የተሰበሰበውን ሰው ወክሉ

እንዲናገር እስክንድርስን ወደ መድረኩ ይገፋታል። ሆኖም፥ አይሁዳውያን ይህን የጣኦት አምልኮትን ይጠሉ ስለነበር በአሕዛብ ዘንድ ምንም ተወዳጅነት አልነበራቸውም፤ ስለዚህም ሕዝቡ አይሁዳዊንም ለመስማት አሻፈረኝ አለ።

ከቁጥጥሩ ውጪ የወጣውም ሕዝብ ለሁለት ሰዓት ያኀል «የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት» እያለ ጮኸ። በመጨረሻም የከተማይቱ ጸሐፊ ሕዝቡን ጸጥ ሊያሰኝ ችሏል። ከዚያም በመቀጠል ትንሽ እነሱን አጥግሶ ከአረጋጋቸው በኋላ፥ ሁከት ብናስነሣ ምንም የምንሰጠው መልስ ስለሌለ ምንም ዓይነት አመፃ እንዳታስነሡ ብሎ ያስጠነቅቃቸዋል። ይህም ድርጊት እራሱ በሮማውያን ላይ የተሸረበ ትልቅ ድፍረት እንደሆነ ተደርጎ ስለሚቆጠር ከተማይቱን የሮሜ ወታደሮች መጥተው ሊያጠፏት ይችላሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች የመቅደስን ዕቃ አልሰረቁም አምላካችንንም አልሰደቡም ይላቸዋል። በመቀጠልም፥ አንጥረኞች በደል ፈጽመዋል የሚሉ ከሆነ ክሳቸውን በፍርድ ቤቱ ያቅርቡ አለ። በመጨረሻ ሕዝቡ ጸጥ እንዲል ተደርጎ በሰላም ወደየቤቱ ገባ።

ጳውሎስ አሁንም እንደገና አገልግሎቱን ይቀጥል ዘንድ የእግዚአብሔር ጥበቃ አልተለየውም። እግዚአብሔር በወዳጆቹና በሹማምንቶች በመጠቀም፥ በሕይወቱ ከመጡበት ሰዎች ሊያድነው ችሏል።

ጥያቄ 17:- ወንጌሉ በባህልህ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ልማዶች የለወጠው እንዴት ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ባህላዊ ከሆኑ ልማዶች ጋር በሚገናኝበት ጊዜ ምርጫ ማድረግ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ልጅ መንፈስ ቅዱስን ሲሰማና ቃሉን ሲጠብቅ፤ ነገሮችን ይገነዘብና አንዳንድ እግዚአብሔርን የማያስከብሩ ልማዶችን ይተዋቸዋል። ልክ በኤፌሶን እንደተከሰተው በአንዳንድ ንግዶች ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ሰይጣን ለብዙ ምዕተ ዓመታት ባህልን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ይዟል። ወንጌልንም አንዳንድ ለውጦች ሲያስከትል በጣም በብርቱ ይቃወማል። ብዙ ጊዜ፤ ሁከትን ያስነሣል። ታዲያ ይህም ሁሉ ቢሆን፥ የወንጌሉ ኃይል ከሰይጣን ይበልጣል።

ጥያቄ 18:- ማንም እንኳ ሌሎች ክርስቲያኖች ቢያደርጓቸውም፥ መንፈስ ቅዱስ አንተን እንዴት አድርጎ አንዳንድ ልማዶችን እንድትተው እንዳደረገህ ሰፋ አድርገህ አብራራ።

# አራተኛ ቀን:- ሐዋርያት ሥራ 20: 1-12

በኤፌሶን የሁለት ዓመት አገልግሎት ውስጥ ወንጌል በእስያ በሙሉ ተስፋፍቶ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተቋቁመዋል። በዚህም ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ ተነሥቶ ነበር፤ ሆኖም እግዚአብሔር ሁኔታውን አረጋግቶ ቤተክርስቲያን ከችግር ሊያድናት ችሏል።

ምንም እንኳን ጳውሎስ በየሄደበት ሁሉ ብዙ ጉዳት ቢያጋጥመውም በጣም ያሳስበው የነበረው የቤተክርስቲያናት ሁኔታ ነበር (2ቆሮ. 11፡ 23-28)። እራሱ ጳውሎስ እንደተናገረውም «ዕለት ዕለት የሚከብድኝ የአብያተ ክርስቲያናት አሳብ ነበር»። ሐዋርያቱን በመጠራጠር ስለ አስፈላጊ የሆነ ክስ ሲቀርብበትም፣ ብዙዎች የክርስቶስን ወንጌል ተጠራጥረውታል። በዚህም ምክንያት አንዳንዴ የሐዋርያቱን ሥልጣን ማስከበር ነበረበት፤ በተለይም በቆሮንቶስና (2ቆሮ. 11፡ 1-3)፣ በገላትያ (ገላ. 1፡ 6-12) ጳውሎስ የሰበከው ወንጌል እውነተኛ መሆኑን በማስረጃ አስደግፎ ማቅረብ ግድ ሆኖበት ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 20፡ 1-12 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 19፡- ሀ) በመቄዶንያ በነበረበት ወቅት ጳውሎስ ያቀረበው መልእክት ምን ነበር? ለ) 1. ጳውሎስ ለሦስት ወር ያህል የቆየው የት ነው? 2. በመቄዶንያ በኩል ተመልሶ ለመሄድ የፈለገው ለምንድነው? ሐ) 1. ጳውሎስን የሸኙት እነማን ናቸው? 2. ጳውሎስን የሚጠብቁት የት ነበር? 3. ከፊሊጵስዩስ ወደ ጢሮአዳ በአደረገው ጉዞ ላይ አብሮት የነበረው ሰው ማነው? በሐዋርያት ሥራ 20፡ 6 ላይ «እኛ» የምትለውን ቃል በደንብ አስተውሉት።

መ) 1. ጳውሎስ በጢሮአዳ ለምን ያህል ጊዜ ነው ንግግር ያደረገው? 2. ጳውሎስ ንግግር እያደረገ ሳለ፣ አንድ ሰውዬ ምን ሆነ?

ከሁከቱ በኋላ ጳውሎስ በኤፌሶን የነበሩትን አማኞች ካጽናናቸው በኋላ ወደ መቄዶንያና አካይያ ይሄዳል። ምናልባትም እስከ እልዋሪቆን ድረስ (የዛሬዎቹ አልባንያና ዩጎዝላቪያ) የሄደው በዚህ ጊዜ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም (ሮሜ 15፡ 19)።

ጳውሎስ ከኤፌሶን በየብስ ወደ መቄዶንያና አካይያ ተጓዘ። ወደ መቄዶንያ ሲያቀና እግረ መንገዱንም አብያተ ክርስቲያናትን ፤ በተለይ ችግር የነበራትን የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያንን ለመጎብኘት ፈለገ፤ ዋና አላማውም በአሕዛብ አገሮች ካሉት አብያተ ክርስቲያናት፣ በኢየሩሳሌሟ ለነበሩት አይሁድ ክርስቲያኖች ሊሰጥ የተሰበሰበውን ምፅዋት ይዞ ለመሄድ ነበር። በቆሮንቶስ ለሦስት ወር ያህል ቆይቶአል። ለሮሜ ሰዎችም ላያችሁ ዓቅጃለሁ ብሎ መልእክቱን የጻፈላቸው ከዚሁ ሆኖ ሳይሆን አይቀርም።

በመጨረሻም ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ተሰናዳ። ስጦታውን በሙሉ እሱ ብቻውን ይዞት ከሚሄድ የየቤተክርስቲያኑ ተወካዮች አብረውት እንዲሄዱ አደረገ። የእነዚህ ተወካዮችም ስም እንደሚከተለው ነው (ሐዋ. 20፡ 4)፡- የቤርያው ሱሲጳጥሮስ፣ የተሰሎንቄዎቹ አርስጥሮኮስና ሲኮንዱስ፣ የደርቤኖቹ ጋይዮስና ጢሞቴዎስ፣ በመጨረሻም ጥሮፊሞስ ከእስያ ናቸው (1ቆሮ. 16፡ 1-5)። እንዲሁም የሐዋርያት ሥራ ደራሲ ሉቃስና በጢሮስ ሲጠብቁት የነበሩትም ሌሎች ተወካዮች ከጳውሎስ ጋር አብረው ነበሩ።

ጥያቄ 20፡- ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ አብሮ የየአብያተ ክርስቲያናቱን ወኪሎች ይዞ መሄዱ ጥሩ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል?

ሰይጣን የቤተክርስቲያን መሪዎችን የሚጥልበት አንዱ መንገድ የቤተክርስቲያንን ገንዘብ በተገቢው መንገድ እንዳይጠቀሙበት በማድረግ ነው። አንድ መሪ ከዛ ገንዘብ ላይ ባይሰርቅም እንኳ መሪው ላይ ጥርጣሬ ሊፈጥሩ የሚችሉ ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ። ጳውሎስም ይህን ያውቅ ስለነበር የየቤተክርስቲያኑ ወኪሎች አብረውት መጥተው ስጦታቸውን ለኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን እንዲሰጡ ያደርጋል። ይህ ድርጊት ሁለት ዓላማዎችን ያካተተ ነው። አንደኛ፥ ይህን በማድረግ ማንም ሰው ለግል ጥቅሙ አዋለው ብሎ አይከሰውም። ሁለተኛ ደግሞ ጳውሎስ ይህን ያደረገው የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ከአይሁድውያኑ ወንድሞቻቸው ጋር ተዋውቀው አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ ሲል ነው።

ጥያቄ 21፡- ሀ) የምታውቃቸው የቤተክርስቲያን መሪዎች ገንዘብን በተገቢው መንገድ ካለመጠቀማቸው ምሥክርነታቸው የተበላሸው እንዴት ነው? ለ) በመሪዎቹ ላይ ተቃውሞ እንዳይነሣ መሪዎቹም ገንዘቡ እንዳይፈታተናቸው ለማድረግና ሁሉም ሰው ገንዘቡን በተገቢው መንገድ ይጠቀሙበታል ብሎ ሙሉ አመኔታ እንዲኖረው የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ማድረግ ያለባቸው ነገር ምንድነው?

በመጨረሻም ጳውሎስና አብረውት ወደ ጢሮአዳ ሄደው ለሰባት ቀን በዚያ ይቆያሉ። በመጨረሻውም ምሽት ጳውሎስ ስብሰባ ይጠራል፤ አብረውም የጌታን እራት ይወስዳሉ (እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን የሚለው ይህን ማለቱ ነው)። ከዚያም ጳውሎስ ዳግመኛ አላያቸውም ብሎ ይሆናል፤ አናውቅም ነገር ግን ለረጅም ጊዜ ንግግር ያደርጋል። ይህን ንግግሩንም እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ቀጠለ ይህም ሲሆን አንድ በመስኮት አካባቢ ተቀምጦ የነበረ ሰው ከዕንቅልፍ ብዛት ከሦስተኛው ፎቅ መስኮት ላይ ይወድቅና ይሞታል። ጳውሎስም ሮጦ በመውጣት «ነፍስ አለችበትና አትንጫጩ» ይላቸዋል። ከዚያም ወደ ላይ ይወጣና እንጀራ ቆርሶ ከበላ በኋላ እስኪነጋ ድረስ ይናገራል። ከዚያም ጉዞውን ይቀጥላል።

የጳውሎስም ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ አሁን ወደ መጨረሻው አካባቢ ደርሷል። ከ53-57 ዓ.ም ድረስ ጳውሎስ ያገለገለው በኤፌሶንና የዛሬዋ ቱርክ በምትገኝበት በእስያ ነው። አሁን ደግሞ ወደ እየሩሳሌም በመመለስ ላይ ሳለ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ለመጎብኘትና ለማጽናናት ይፈልግ ነበር። ሆኖም፥ አሁን እንደምናየው ወደ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እንዳይሄድ ያሚያደርግ አንድ ነገር ይፈጠራል። በሚቀጥለው ሳምንት ይህንን ሰፋ ባለ ሁኔታ እናጠናዋለን።

# አምስተኛ ቀን፡- ክለሳ

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

*1.* ሀ) ጳውሎስ ራዕዩን የተቀበለው በየት ሳለ ነው? ለ) እግዚአብሔር በእዚህ ራዕይ ውስጥ የተናገረው ነገር ምንድነው?

2. ሀ) አቂላና ጵርስቅላ እነማን ናቸው? ለ) ከጳውሎስ ጋር ያገለግሉ የነበረው እንዴት ነው?

.3 ሀ) አጵሎስ ማነው. ለ) በቆሮንቶስ የነበረውን አገልግሎት አመርቂ እንዲሆን ያደረገው ነገር ምንድነው?

4. ሀ) በኤፌሶን የነበሩ ደቀመዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበሉት ለምንድነው? ለ) መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት መቼ ነው?

5. በኤፌሶን የነበሩ ሰዎች ፍርሃት እንዲወድቅባቸውና የኢየሱስን ስም እንዲያከብሩ ያደረገው ነገር ምንድነው?

6. የጳውሎስ የኤፌሶንን ሁለት ዓመት ቆይታ ምን ዓይነት ውጤት ነው ያስገኘው?

7. ሀ) ጳውሎስ መቄዶናያና አካይያ ከደረሰ በኋላ ወዴት ለመሄድ ነበር ያሰበው? ለ) አብሮት ይሄድ የነበረውስ ማነው?

8. በጢሮአዳው የመጨረሻ ምሽት ላይ የሆነው ነገር ምንድነው?

ሳምንታዊዎቹን የመወያያ ጥያቄዎች በመመልከት ለስብሰባው ተዘጋጅ።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. ክለሳ
4. ውይይት

ሀ) 1. እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ለመመሥረትና ለማሳደግ የተለያዩ ሰዎችን እንዴት አድርጎ እንደሚጠቀም ከአጵሎስና ከጳውሎስ አገልግሎት የምንማረው ነገር ምንድነው? 2. እግዚአብሔር የተለያዩ ስጦታ ባላቸው ሰዎች ቤተክርስቲያንህ ውስጥ የተጠቀመው እንዴት ነው? 3. ከዚህስ አንዱ መሪ በሌላኛው ላይ መቅናት እንደሌለበት የሚገልጽ ምን ዓይነት ትምህርት ነው ልንቀስም የምንችለው?

ለ) 1. ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በልሳን ስለ መናገር ከሐዋርያት ሥራ ጥናታችን የምንማረው ነገር ምንድነው? 2. ይህ አንዳንድ ክርስቲያኖች ከሚያስተምሩት የሚለየው እንዴት ነው? 3. 1ቆር. ከምዕራፍ 12-14 አንብብና በቤተክርስቲያን ውስጥ የልሳንን አጠቃቀም በተመለከተ የተሰጡትን መመሪያዎች በቅደም ተከተል ጻፋቸው።

ሐ) 1. በኤፌሶን የአንጥረኞቹን ንግድ ትርፍ እንዳደረገው ሁሉ በኢትዮጵያም ውስጥ ክርስትና ተጽዕኖ የሚያደርገው ምን ዓይነቶቹ ነገሮች ላይ ነው? 2. ክርስቲያን መሆን አሠራርህን፣ አኗኗርህን፣ ወዘተ.. እንዴት እንደሚለውጠው አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ። 3. ክርስቲያኖች አኗኗራቸውን ቢለውጡ በኅብረተሰቡ ላይ የበለጠ ተጽዕኖ ሊኖራቸው የሚችለው በምን ዓይነት መንገዶች ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 15

የሐዋርያትሥራ20፡13-21፡26

## የመጀመሪያ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 20፡13-38

ከ 53 - 57 ዓ.ም ድረስም ጳውሎስ ያደረገውን ሦስተኛውን ሚሲዮናዊ ጉዞ አይተናል። ከዚህ በፊት ካደረጋቸው ጉዞዎች ሁሉ ብዙ ጊዜ የቆየበት ይህ ጉዞው ነው። በዚህም ጊዜ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ያሳለፈው በኤፌሶን ነው። ይህም በመሆኑ ኤፌሶን ለመላው ለእስያ ክፍለ ዓለም የክርስትና መዲና ሆነች፤ ወንጌልም ከዚህችው ከተማ ወደ ሌሎቹ የእስያ ከተሞች በምሥክሮች አማካኝነት ተስፋፋ። ጳውሎስም ብዙዎቹን መልእክቶቹን የጻፈው በዚህ በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ላይ ነው። በዚህም መልኩ ስናየው የ1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ መልእክቶቹን በኤፌሶን ለሮሜ ሰዎች መልእክቱን በቆሮንቶስ ሳለ የጻፈ ይመስላል። ለሁለት ዓመትም እንዲህ ከመሰከረና ካስተማረ በኋላ ጌታ ወደ ሌሎች ቦታዎች እንዲሄድ አድርጎታል። እሱም እራሱ ወደ ሮምና ወንጌሉ ወዳልደረሰበት ወደ እስፓኝ የመሄድ ፍላጎት ነበረው።

ጳውሎስ ከኤፌሶን በመነሣት በመቄዶንያና በግሪክ በኩል በማለፍ ለሦስት ወር ምናልባት በቆሮንቶስ ሳይቀር አልቀረም። ከዚህ በኋላ ወደ ሶሪያ በመርከብ ለመሄድ ሲያስብ አይሁዳውያን ሊገድሉት ሴራ እንደጠነሰሱ ይሰማል። በዚህም ምክንያት ወደ መቄዶንያ በእግሩ ይሄዳል። ከዚያም በጢርአዳ አብረውት ወደ ኢየሩሳሌም ስጦታቸውን ይዘው የሚወርዱ የአብያተ ክርስቲያናት ወኪሎችን ያገኛቸዋል። በመጨረሻም ጳውሎስ በጢርአዳ የነበሩትን ክርስቲያኖች ሌሊቱን በሙሉ ሲመክራቸው አድሮ ከወኪሎቹ ጋር ጉዞውን ወደ ኢየሩሳሌም ይቀጥላል።

ጥያቄ 1፡- የሐዋርያት ሥራ 20፡ 13 - 21-26 አንብብ። ከዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት። ወደ ኢየሩሳሌም ባደረገው ጉዞ ላይ እግረ መንገዱን የቆመባቸውን ሥፍራዎች በዝርዝር ጻፍ።

የሐዋርያት ሥራ 20፡ 13-38 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 2፡- ሀ) 1. ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን የሄደው እንዴት ነው? 2. አብረውት የነበሩትስ ሰዎች በምንድነው የሄዱት?

ለ) ጳውሎስ በኤፌሶን በኩል ማለፍ የፈለገው ለምንድነው? 2. ከኤፌሶን ሽማግሌዎች ጋር ሊገናኝ የቻለው እንዴት ነው?

ሐ) 1. ጳውሎስ በኤፌሶን የነበረውን አገልግሎቱን እንዴት አድርጎ ነው የገለጸው? 2. ለአይሁዳውያንና ለግሪክ ሰዎች ያስተማረው ነገር ምንድነው? 3. ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄደው ለምን ነበር? 4. ጳውሎስ ከነፍሱ አስበልጦ የሚያየው ነገር ምንድነው? 5. ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው?

መ) ጳውሎስ ለሽማግሌዎቹ የሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ምንድነው?

ሠ) 1. ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች በኤፌሶን ሰዎች ላይ ጥገኛ ነበሩን? 2. ምግባቸውን ያገኙ የነበረው እንዴት ነው?

ረ) ጳውሎስ ስለመስጠት የተናገረው ነገር ምንድነው?

ሰ) የኤፌሶን ሽማግሌዎች እጅግ ያዘኑት ጳውሎስ ምን ሲላቸው ነው?

ሸ) 1. ከእነዚህ ጥቅሶች የምንማረው አንድ መሪ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዴት መሥራትና መኖር እንዳለበት ነው? 2. ከእነዚህ ጥቅሶች ሐሰተኛ መምህራን እንዴት እንደሚሠሩ ነው የምንማረው?

ከቆሮንቶስ በመነሣት ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ያቀናሉ። ጳውሎስም ሉቃስና ሌሎች የቤተክርስቲያን መሪዎች ይጠብቁት ወደ ነበረው መርከብ ድረስ በእግሩ ይሄዳል ከዚያም ተነሥተው ወደ ሚሊጢን፥ ኪዩ፥ ሳሞንና ትሮጊሊዮን አብረው በመርከብ ይሄዳሉ (የጳውሎስ ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ የሚያመለክተውን ካርታ ተመልከት)። ወደ ኤፌሶን ከገባ ሊያቆዩትና ለበዓለም ሃምሳ ላይደርስ ስለሚችል ወደዚያ ማምራቱን ይተዋል። ሆኖም መርከቧ በሚሊጢን በመቆሟና ይህችም ከተማ ከኤፌሶን በ50 ኪ.ሚ. ርቀት ላይ ስለምትገኝ ሽማግሌዎቹ ወደ እርሱ እንዲመጡ መልእክት ይልክባቸዋል።

በሚሊጢንም ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች የመጨረሻውን ምክሩን ይለግሳቸዋል። እስካሁን ድረስም የተመዘገቡት የጳውሎስ መልእክቶች ለማያምኑ አይሁዳውያንና አሕዛብ የተሰጡ ነበሩ። ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ያቀረበው መልእክት ግን ለየአብያተ ክርስቲያናቱ ከጻፋቸው መልእክቶች ጋር ይመሳሰላል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ይህንን ክፍል ማወቅ አለባቸው። ለምን ቢባል፥ በዚህ ውስጥ እንደ ቤተክርስቲያን መሪ ለመኖር የሚያስችሏቸውን መመሪያዎች ያገኛሉና ነው። በተጨማሪም ሐሰተኛ መምህራን እንዴት እንደሚነሡ ቤተክርስቲያንንም ለማጥፋት እንዴት እንደሚጥሩ በማስጠንቀቂያ መልክ በደንብ ይገልጻል።

የጳውሎስ መልእክት የመጀመሪያው ክፍል በኤፌሶን በነበረበት ወቅት አገልግሎቱ ትክክለኛ እንደነበር የሚገልጽ ነው። ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ለሽማግሌዎች ሊያስተላልፈው የፈለገው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ነበሩ። አንደኛ በእነርሱ ፊት ለእራሱ መከላከያ ማቅረብ ይፈልጋል። እንደሚታወሰውም በመላው እስያ የነበሩ ጠላቶቹ የጳውሎስን ምሥክርነት ለማበላሸት ያላደረጉት ነገር የለም። ስለዚህም ባለፉት ሦስት ዓመታት በእነርሱ ዘንድ ሳለ የእርሱ አገልግሎት ምን ይመስል እንደነበር ሊያስታውሳቸው ፈልጓል። ሁለተኛም ያስተማረው ወንጌል ትክክለኛ መሆኑን ለማሳየት ይፈልግ ነበር። ይህንንም ያደረገው፥ ሐሰተኛ መምህራን ልክ እንደ ተኩላ መጥተው መንጋውን ከእውነቱ እንደሚያርቁ ያውቅ ስለነበር ነው። ከእነዚህ መምህራን አዳንዶችም ከራሳቸው ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚነሱ ናቸው።

ጥያቄ 3:- ይህ ነገር ዛሬ ሰይጣን ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ካለው ምኞት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

የጳውሎስ መልእክት የመጀምሪያው ክፍል በኤፌሶን የነበረው አገልግሎቱ ትክክለኛ መሆኑን የሚያስረዳበት ነው። እስቲ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንዴት መምራት እንደሚገባን ከጳውሎስ ሕይወት እንደ ምሣሌ ሊሆኑን የሚችሉትን የሚከተሉትን ነገሮች እናጢናቸው፡-

1. ጳውሎስ በሕይወቱ ውስጥ ከሕዝቡ የደበቀው ነገር የለም፤ በግልጽና በታማኝነት ነበር የሚኖረው። ጳውሎስ ሌሎች ሰዎች እንዲያዩት እንዲመረምሩትና እንዲከተሉት ራሱን አሳልፎ ሰጠ።

ጥያቄ 4፡- ይህ የቤተክርስቲያን መሪዎች ሊከተሉት የሚያስፈልግ ጥሩ አርአያ የሚሆነው ለምንድነው?

2. ጳውሎስ መሪ ለመሆን ሳይሆን እራሱን ዝቅ አድርጎ ለማገልገል ነው የመጣው።

ጥያቄ 5 :-ይህ አመለካከት ዛሬ የሚገኙ መሪዎች ካላቸው አስተሳሰብ ጋር የሚለየው እንዴት ነው።

3. ጳውሎስ ሁለንተናውን ለወንጌሉ ሥራ አሳልፎ ሰጥቷል። ያገለግልም የነበረው በእንባ ነው። እሱ እንዳለውም ቤተክርስቲያን ትመሠረት ዘንድ በእነርሱ መካከል ሌትና ቀን ሰርቷል።

4. ጳውሎስ ለወንጌሉ ሲል በብዙ ችግርና መከራ ውስጥ ለማለፍ ፈቃደኛ ነበር። ይህ ስደት በተለይ ይቀሰቀስ የነበረው በአይሁዳውያን ነው። ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ጳውሎስን ከዚህ በኋላ ብዙ መከራ ይቆይሃል ብሎታል። ታዲያ ይህም ሁሉ ቢሆን፥ ለአይሁዳውያንና ለአሕዛብ ወንጌሉን በየጉባዔውና በየቤታቸው መስበኩን አላቆመም። ይህንንም ነገር በተመለከተ ይሰማው የነበረውን ሸክም፥ ከኤፌሶን ሽማግሌዎች ጋር ከመሰብሰብ ከትንሽ ወራት ቀደም ብሎ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ውስጥ ጠቅሶታል (ሮሜ 9-11)።

5. ጳውሎስ ለገንዘብ የሚስገበገብ አለነበረም። ሽማግሌዎቹንም ከእነርሱ ምንም ገንዘብ ጠይቆ እንደማያውቅ ያስታውሳቸዋል። እራሱንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ያስተዳድር የነበረው እርሱ እየሠራ ነበር። በምሣሌም አማኞቹን ደካሞችን እንዲረዱ መሥራት እንዳለባቸው አሳይቷቸዋል፤ ኢየሱስም ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብጹዕ ነው» ብሎ ያስተማረው ለዚሁ ነው ። እሱም ይሠራ የነበረው ገንዘብ ለማግኘት ሲል ሳይሆን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ነው። ክፍያ ተቀበለ ወይም አልተቀበለም ምንም ደንታ አይሰጠውም ነበር። እንዲያውም ማንም ሰው የሚሠራው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ነው ብሎ እንዳይወቅሰው ሲል፥ ክፍያ መቀበልን አይፈልግም ነበር።

ጥያቄ 6፡- ይህ ዛሬ ለመሪዎች ጥሩ ማስጠንቀቂያ የሚሆነው እንዴት ነው?

6. ጳውሎስ ያስብ የነበረው ለሌሎች መመሥከሩንና ወደ ክርስቶስ ማምጣቱ ብቻ ሳይሆን እነሱን በእምነት ማሳደጉንም ጭምር ነው። ከዚህም በላይ «የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁ ምንም አላስቀረሁባችሁም» ይላቸዋል።

ጥያቄ 7፡- «የእግዚአብሔር ምክር» በሚለው ውስጥ ይጠቃለላሉ ብለህ የምትገምታቸውን ነገሮች በሙሉ በዝርዝር ጻፍ።

7. ጳውሎስ በሕይወቱ ውስጥ የሚሠራበት ዋና ዓላማ ነበረው። ይህንንም ዓላማውን «ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልኩትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ፀጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደሚትከብር እንደ ከንቱ እቆጥራታለሁ» በማለት ገልጾታል (ሐዋ. 20፡ 24)።

ጥያቄ 8፡- በሕይወትህ ውስጥ ዋናው ዓላማዬና ግቤ ነው የምትለውን ነገር ጻፍ። የጳውሎስ ዓላማ ብንከተለው ለሁላችንም ጥሩ ሊሆንልን የሚችለው እንዴት ነው?

የጳውሎስ መልእክት ሁለተኛ ክፍል ሐሰተኛ መምህራንን በተመለከተ ለመሪዎቹ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነበር። ለቤተክርስቲያን ትልቁና አደገኛው ነገር ከወጪ የሚነሣው ስደት ሳይሆን፥ ከውስጥ የሚቀሰቀሰው ሐሰተኛ ትምህርት ነው። ብዙ ቤተክርስቲያኖችም ከስደት ይልቅ በሐሰተኛ ትምህርት እየጠፉ ነው። ከጳውሎስም መልእክት ሐሰተኛ መምህራንን በተመለከተ ብዙ ነገሮችን ልንማር እንችላለን።

1. ሐሰተኛ መምህራን ብዙ ጊዜ የመሪዎችን ወይም የቤተክርስቲያኒቱን ስም ለማጥፋት ነው የሚነሡት።

ጥያቄ 9፡- ይህ ነገር በቤተክርስቲያንህ ውስጥ እንዴት እንደተከሰተ ግለጽ።

2. ብዙ ጊዜም የሐሰተኛ መምህራን የሚነሡት ከክርስቲያኖች መካከል ነው እንጂ፥ ክርስቲያን አይደለንም ብለው ከሚሉት ሰዎች ውስጥ አይደለም።

3. ሐሰተኛ መምህራን ልክ እንደ ተኩላ ለማፍረስ ነው እንጂ ለመገንባት አይፈልጉም።

4. ሐሰተኛ መምህራን ልክ እውነቱን ማጣመም ይቀናቸዋል። ታዲያ ክርስቲያኖችን ለውድቀት የሚያበቃው ከእውነቱ ጋር አብሮ የተቀመመው ሐሰተኛ ትምህርት ነው እንጂ ለብቻው ሐሰተኛ ትምህርት አይደለም። ልዩነቱንም ልናውቅ የምንችለው፤ እውነቱን ስናውቅ ብቻ ነው። ሐሰተኛ ትምህርት በቤተክርስቲያናችን እንዳይስፋፋ ማድረግ የምንችለው፥ አባላቶቻችንን እውነቱን በግልጽ ስናስተምራቸው ነው።

ጥያቄ 10፡- ሀ) በቤተክርስቲያህ ላይ ጉዳት በማድረስ ላይ ያሉት አንዳንድ የሐሰት ትምህርቶች ምን ምንድናቸው? ለ) ሰዎች በእነዚህ ትምህርቶች ተሰናክለው እንዳይወድቁ ቤተክርስቲያንህ ምን እያደረገች ነው?

5. ሐሰተኛ መምህራን ለመንጠቅ የሚፈልጉት ክርስቲያን የሆኑትን ነው እንጂ፥ ያልዳኑትን ሰዎች አይደሉም። በተለይም በጣም ትኩረት የሚያደርጉት ከሌላ ቤተክርስቲያን በመጡት ላይ ነው።

አንድ ቤተክርስቲያን እራስዋን ከሐሰተኛ ትምህርት መከላከል የምትችለው እንዴት ነው? ጳውሎስ ትልቁን የሥራ ጫና የሚጥለው በቤተክርስቲያን መሪዎች ላይ ነው። አንደኛ፥ ጳውሎስ መሪዎችን ለራሳቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያስጠነቅቃቸዋል። አንድ መሪ በሐሰተኛ ትምህርት ከተጠመደ፥ ብዙዎችን ከራሱ ጋር

አብር ይዞ ይሄዳል። ስለዚህም እንደ መሪ፥ እውነቱን በደንብ ማወቅና እራሳችንን ከሐሰት ትምህርት መጠበቅ አለብን።

ሁለተኛ፥ አንድ እረኛ ከብቶቹን እንደሚጠብቅ ሁሉ መሪዎቹም አማኞቹን እንዲጠብቁ አደራ ይሰጣቸዋል። ይህም፥ አማኞች ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ማሰብ አለባቸው ማለት ነው። በተለይም ከሐሰተኛ መምህራን ሊጠብቋቸው ይገባል።

በመጨረሻ ጳውሎስ ያድናቸው ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣቸው ዘንድ ለሚችል ለእግዚአብሔርና ለፀጋው ቃል አሳልፎ አደራ ይሰጣቸዋል።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች አማኞችን የመምራቱንና የመጠበቁን አደራ ከሰጣቸው በኋላ፥ አብረው ተንበርክከው ይጸልያሉ። ከዚያም ጳውሎስ ካሁን ወዲህ እንገናኝም ብሏቸው ስለነበር፥ ሲሰናበቱት በጣም አለቀሱ።

የጳውሎስ ምኞት የእግዚአብሔርን የፀጋ ወንጌል እግዚአብሔር እንደላከው ለአይሁዳውያንና ለአሕዛብ ሰብኮ ሩጫውን መጨረስ ነው። ይህንንም ሥራ ለመጨረስ ሲል፥ በደማስቆ መንገድ ከተቀየረበት ጊዜ አንሥቶ እራሱን ሙሉ በሙሉ ለጌታ አሳልፎ ሰጥቷል። ይህም ነገር ነበር ጳውሎስን በድብደባው፥ በተቃውሞው፥ በሐሰት ክሶች ውስጥና በወኅኒ ቤት መግባት ውስጥ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን ከነበረው ሐሳብ ውስጥ በሙሉ ጸንቶ እንዲቆም ያደረገው።

ጥያቄ 11:- ለክርስቶስ ሕይወትህን የሰጠህበት አኳኋን ከዚህ ጋር የሚመሳሰለው ወይም የሚለያየው እንዴት ነው?

ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን የነበረው ፍቅር አንድ አባት ለልጁ እንደሚኖረው ዓይነት ነው። ችግርና አደጋ እንደሚያጋጥማቸው እያወቀ ጥሏቸው መሄዱ ከባድ ነው፤ ሆኖም ሌሎች የመሪነቱን ቦታ የሚይዙበት ጊዜ ደርሶ ነበር።

ጥያቄ 12:- ክርስቲያን መሪዎች የተሻለ ሥልጠና ለተሰጣቸው ሰዎች የመሪነታቸውን ቦታ የሚያስረክቡበት ጊዜ ይመጣል። ታዲያ ቅድሚያ ለቤተክርስቲያኒቱ ደኅንነት በመስጠት ይህንን ለማድረግ ዝግጁ ነህን?

## ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 21: 1-16

በሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞው ማገባደጃ ላይም የጳውሎስ አገልግሎት ወደ ፍጻሜው ተቃረበ። ካሁን ወዲህም የተመሠረቱትን ቤተክርስቲያኖች የሚያስታውሳቸው በጸሎቱ ብቻ ነው። የየቤተክርስቲያኖቹን ምዕመናችና ሽማግሌዎች መሰናበቱም ለጳውሎስ በጣም ከብዶበት ነበር። ታዲያ መከራና እስራት ይጠብቅሃል ቢባልም፥ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ተገድዶ ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 21: 1-16 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 13:- ሀ) የጳውሎስን ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ በሚያሳየው ካርታ ላይ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ የሄደበትን መንገድ በእርሳስ አመልክት። ከዚህ በፊት በሦስት ጉዞዎች ያስጎበኛቸውን የትኞቹን አገሮች ነው በዚህ

የመልስ ጉዞ ላይ የጎበኘው? በዝርዝር ጻፋቸው። ለ) ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ለለመኑት ሰዎች የሰጠው መልስ ምንድነው? ሐ) ጳውሎስ ለመሞት ዝግጁ ነኝ ያለው ለምንድነው.

ጳውሎስና አብረውት የነበሩት ሰዎች የኤፌሶን ሽማግሌዎችን ተሰናብተው በመርከብ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞአቸውን ይጀምራሉ። በመጀመሪያም ወደ ቆስ፥ ከዚያም በማግሥቱ ወደ ሩድ ይሄዳሉ። በመቀጠልም ወደ ጳጥራ ይሄዱና ፊንቄ ድረስ በሚወስዳቸው መርከብ ይሳፈራሉ። ከዚህም በኋላ ቆጵሮስን በስተግራቸው በመተው ወደ ሶርያ ያልፉና መርከቧ ጭነቷን በጢሮን ታራግፋለች። ጳውሎስናጓደኞቹም በዚያ ክርስቲያኖችን ያገኙና ለሰባት ቀን ያህል ይቆያሉ። ይህቺ ቤተክርስቲያንም የተመሠረተችው ክርስቲያኖች በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት በተበታተኑ ጊዜ ነው (ሐዋ. 11፡ 19)።

በጢሮን አንዳንድ ደቀመዛሙርት በመንፈስ ቅዱስ ተነግሯቸው ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም እንዳትሄድ ይሉታል። ሌሎቹም አማኞች ይህን ሲሰሙ ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ይለምኑታል። ጳውሎስ ግን በጣም መሄድ ይፈልግ ስለነበር ጊዜያቸውን እንደፈጸሙ ቶሎ ብሎ ተነሥቶ ወደ አካ ይሄዳል። በዚህም ሥፍራ ለወንድሞች ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ፥ ለአንድ ቀን ይቆያሉ! ከዚያም የመርከብ ጉዞአቸውን ወደሚያገባድዱበት ወደ ቂሣሪያ ይሄዳሉ።

በቂሣሪያም ሳሉ አርፈውበት የነበረው የወንጌላዊው የፊሊጶስ ቤት ነው። እንደምታስታውሰውም፥ በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ ከተመረጡት ሰባት ሰዎች መካከል አንዱ ፊሊጶስ ነበር (ሐዋ. 6፡ 3)። ወንጌልን ለሳምራውያን ያሰማና ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ወደ ጌታ ያመጣ ይህ ሰው ነው። በቂሣሪያም ሲኖር ሃያ ዓመት ይሆናል! በዚህም ጊዜ ውስጥ ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴት ልጆችን አፍርቷል። እነዚህም ልጆች ከእግዚአብሔር የሚላከውን መልእክት ለሕዝቡ ያሰሙ ነበር። ከእነዚህም መልእክቶች ውስጥ የወደፊቱ ሁኔታ የሚነገርባቸው ትንቢቶች ይገኙባቸዋል።

ጥያቄ 14፡-ይህ ክፍል ሴቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ የመሥራት ችሎታ የሚናገረው ነገር ምንድነው?

ጳውሎስና ከእሱ ጋር የነበሩት በሙሉ በቂሣሪያ ሳሉ፥ አንድ ነቢይ ከይሁዳ ወደ እነርሱ ይመጣል። በሐዋርያት ሥራ 11፡ 27 ላይም አጋቦስ በ46 ዓ.ም ላይ ረሃብ እንደሚኖር ተንብዮአል። አሁን ደግሞ አይሁዳውያን ጳውሎስን አስረው ከአሕዛብ እጅ አሳልፈው እንደሚሠጡት ይናገራል። ይህም እንዴት እንደሚሆን አጋቦስ የገለጸው እጁንና እግሩን በጳውሎስ መታጠቂያ በማሰር ነው። ታዲያ ይህንን ነገር በዚያ የነበሩት በሙሉ ሲሰሙ ጳውሎስን እንዳይሄድ ይለምኑታል።

ጥያቄ 15፡- መንፈስ ቅዱስ በተደጋጋሚ ጳውሎስን በኢየሩሳሌም ያጋጥመው ስለነበረው እሥር ያስጠነቅቀው የነበረው ለምን ይመስልሃል?

ጳውሎስ ብዙ ወዳጆቹ እንዲቀር ቢለምኑት ስለእሱም ትንቢት ሲነገር ከኢየሩሳሌም በጭራሽ ሊያስቀሩት አልቻሉም። መንፈስ ቅዱስም በተደጋጋሚ ለምን እንደዚህ ያስጠነቀቀው እንደነበር አናውቅም። ሆኖም፥ አንዳንድ ሰዎች ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ወጥቶ ተገቢ ያልሆኑ አመታትን በእሥር ቤት ውስጥ አሳልፏል ብለው ይገምታሉ። ይህም እውነት ከሆነ፥ እግዚአብሔር ሁኔታዎቹን በቁጥጥር ሥር በማድረግ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለአሕዛብ ንገሮች እንዲመሰክር አድርጓል። የጳውሎስም መልስ «እያለቀሳችሁ ልቤንም እየሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔ ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳ ተሰናድቼአለሁ እንጂ ለእስራት በቻ አይደለም» የሚል ነው።

ደቀመዛሙርቱም ጳውሎስን ከመሄድ ሊገቱት ባለመቻላቸው ጳውሎስና አብረውት የመጡት ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ይዘጋጃሉ። ከዚያም ወደ ቀድሞው የቆጵሮስ ደቀመዝሙር ወደ ምናሶን ቤት ሄደው ያድራሉ።

ጥያቄ 16፡-ጳውሎስ በሄደበት ቦታ ሁሉ ትታሠራለህ የሚል ማስጠንቀቂያ እየተሰጠው፥ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ለምን ይመስልሃል?

አጋቦስ ለጳውሎስ የነገረው ስለ መታሠሩ ነው እንጂ፥ አትሂድ ብሎ አልተናገረውም። ጳውሎስ ደግሞ ይህን ጉዞ ሊጀምር ካሰበበት ጊዜ ጀምሮ ምን እንደሚያጋጥመው ያውቅ ነበር! ሆኖም አንዱ ልሂድ ብሎ ቆርጦ በመነሣቱ ይህን ሐሳቡን አንዳች ነገር እንዳይደናቀፍበት አድርጓል። በተጨማሪም በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም፥ መንፈስ ቅዱስ በሚመራኝ መንገድ ነው የምሄደው ብሎ ያምን ነበር።

ጥያቄ 17፡-ሰዎች ወይም አንዳንድ ችግሮች ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ እንዲያደርጉህ እራስህን ለእነዚህ ነገሮች አሳልፈህ ትሰጣለህን?

# ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 21፡ 17-27

ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም በሚሄድበት ወቅት መርከቢ በቆመችበት ሥፍራ ሁሉ ከክርስቲያኖች ጋር ይገናኝ ነበር። እስከዚህን ጊዜድረስም፥ ክርስትና ከአይሁድ ሃይማኖት እንደ አንድ ክፍል ነበር የሚቆጠረው። ጳውሎስም አይሁዳውያንን እንዳያሰናክላቸው በማለት ከአይሁዳውያን ጋር እንደ አይሁዳዊ ይሆን ነበር (1ቆር. 9፡ 20-21)። ወንጌሉንም ለእነዚህ ሰዎች ሲሰብክ ለእነርሱ እንዲገባቸው አድርጎ ነበር የሚያቀርበው። ሆኖም አይሁዳውያኖች ደስ እንዲላቸው ብሎ የወንጌሉን መልእክት አይለውጥም ወይም አያዛባም ነበር። በኢየሩሳሌምም፥ በአይሁዳውያንና በአሕዛብ መካከል ተገቢ ያልሆኑ ልዩነቶችን ለማስወገድ ሲል ጳውሎስ ያደርገው የነበረውን ነገር እናያለን።

የሐዋርያት ሥራ 21፡ 17-26 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 18:- ሀ) 1. በኢየሩሳሌም የሚገኙት ወንድሞች ለጳውሎስ ያደረጉት አቀባበል እንዴት ዓይነት ነው? 2. በነጋታው ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ ሪፖርት ያቀረበው ለእነማን ነው?

ለ) 1. አይሁዳውያን አማኞች ስለ ጳውሎስ ይናገሩ የነበረው ነገር ምንድነው? 2. ያዕቆብና ሽማግሌዎቹ ስለ ጳውሎስ በጣም ያስቡ የነበረው ለምንድነው?

ሐ) ጳውሎስን ምን እንዲያደርግ ነው የጠየቁት? ለምን?

መ) 1. አሕዛብ አማኞች ላይ ከዚህ በፊት የተደነገገው ነገር ምንድነው? 2. ይህ ውሳኔ የተደረገው መቼ ነው? (ሐዋ. 15)

ሠ) ይህ የመንጻት ስለት ለአይሁዳውያኑ ስለ ጳውሎስ የሚገልጽላቸው ነገር ምንድነው.

ጳውሎስ ከእስያ፥ ከመቄዶንያና ከአካይያ ከመጡት ተወካዮች ጋር ኢየሩሳሌም ሲደርስ ያዕቆብና የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ሞቅ ያለ አቀባበል አድርገውላቸዋል። በዚያም ጳውሎስ ወንጌሉ በአሕዛቡ ዓለም ውስጥ እንዴት እየተስፋፋ እንዳለ ገለጻ ያደርጋል። እነሱም ለሰሙት ነገር እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። ከዚህም በኋላ የየአብያተ ክርስቲያናቱ ተወካዮች ስጦታቸውን ለኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ያበረክታሉ (ሉቃስ ይህንን ነገር እስከ ሐዋርያት ሥራ 23፡ 7 ድረስ አይጠቅሰውም)።

በኢየሩሳሌም የነበሩ መሪዎች በጣም ችግር ላይ ይወድቃሉ። ከብዙ ዓመታት በፊትም፥ ከጳውሎስ የመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዞ በኋላ፥ አሕዛብ ለመዳን የሙሴን ሕግ መጠበቅ ወይም መገረዝ የለባቸውም ብለው ወስነው ነበር። ሆኖም ብዙዎቹ ወግ አጥባቂና አይሁዳዊ ክርስቲያኖች በዚህ ውሳኔ አልተስማሙም ነበር። በዚህም መሠረት በጳውሎስ ጉዞዎች ላይ በሙሉ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ አይሁዳውያን ጳውሎስን ለመከተል አሕዛብ የሙሴን ሕግ መጠበቅ አለባችሁ ብለው ያስተምሩ ነበር። በተጨማሪም እነዚህ አይሁዳውያን በኢየሩሳሌም ይኖሩ በነበሩት ክርስቲያኖች መካከል የጳውሎስን ምስክርነት የሚያጎድፍ ወሬዎች ያወሩ ነበር።

ምንም እንኳ ሽማግሌዎቹ የጳውሎስን አገልግሎት ቢደግፉም፥ የአይሁድ ክርስቲያኖች ያስነሡበት ተቃውሞ በጣም አሳስቧቸው ነበር። እነዚህ አይሁዳውያን በምድራቸውና በባህላቸው ይኮሩ የነበሩ ናቸው። በዚህም መሠረት አንዳንዶች የኢየሩሳሌሙ ጉባዔ አሕዛብ አይገረዙ ብሎ ባስተላለፈው ውሳኔ ጳውሎስ አልተደሰተም ብለው ያወሩ ነበር። ከዚህም ጋር አስታከው፥ ጳውሎስ አይሁዳውያንን የሙሴን ሕግ መጠበቁ፥ መገረዙና ሌሎች ባህሎችን መጠበቁ አስፈላጊ አይደለም ብሎ ያስተምራል ብለው ይናገሩ ነበር። ጳውሎስ ግን በጭራሽ እንዲህ ብሎ አላስተማረም።

ጥያቄ19:- ሀ) ሐሰተኛ ወሬዎች የአንድን ሰው ምሥክርነት ሲያጎድፉ ወይም በቤተክርስቲያን ላይ ችግር ሲፈጥሩ ያየኸው እንዴት ነው? ለ) በቤተክርስቲያን ላይ የሚፈጥረው ችግር ምን ዓይነት ነው? ሐ) እውነቱን ለማወቅና ብሎም ወሬውን ለመግታት ስትል ያደረግኸው ነገር ምንድነው?

ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፥ በአይሁዳውያኑ ክርስቲያኖች እና በጳውሎስ መካከል ግጭት እንደሚኖር ሽማግሌዎቹ ያውቁ ነበር። ስለዚህም ጳውሎስ ለአይሁድ ባህል ተገዢ መሆኑን የሚያረጋግጥ አንድ ነገር እናድርግ ብለው ያቅዳሉ። በዚህም መሠረት ወደ ቤተመቅደስ ገብተው የሚነጹ አራት ክርስቲያኖች ነበሩ። ምናልባትም እነዚህ ሰዎች የናዝራዊ ስለት ነው የተሳሉት። ይህ ስለት፥ አንድን ሰው ለተወሰነ ጊዜ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለየ እንዲሆን የሚደረግበት ነው (ይህን ስለት ለማድረግ መሟላት ያለባቸውን ነገሮች በኦሪት ዘኁልቁ 6፡ 1-24 ላይ ተመልከት)። ለምን እነዚህ ሰዎች ይህን ስለት እንደገቡም አልተጠቀሰም። ሆኖም የስለታቸው ጊዜ ከመፈጸሙ በፊት ሳይረክሱ አልቀረም (ምናልባትም በድን የሆነ ነገር በመንካት ይሆናል)።

ጳውሎስ የአይሁድን ባህል የሚከተሉትን አይሁዳዊ ክርስቲያኖችን እንደማይቃወም ለማረጋገጥ ጳውሎስ ከአራቱ ሰዎች ጋር እንዲነጻ ይጠየቃል። የእነዚህንም ሰዎች ወጪ (በዚህ የስለት ጊዜ ውስጥ መርከስ የሚያስወጣው ወጪ በጣም ብዙ ነበር) ይሸፍን የነበረው እሱ ነበር። ይህ የመንጻቱ ጊዜ ሲያልቅም፥ ለእያንዳንዱ ሰው መስዋዕት ይቀርብ ነበር።

ጳውሎስ በግልጽ ከሕግ በታች አይደለሁም ብሎ ያስተምር ነበር። ይህንንም ሲል፥ ከእግዚአብሔር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዲኖረኝ የግድ የብሉይ ኪዳንን ሥርዓተ ሕግ መከተል የለብኝም ማለቱ ነው። አትግደል፥ አትስረቅ፥ ዝሙት አትፈጽም ወዘተ ... የሚሉትን የግብረ ገብ ሕግጋት ግን ይጠብቅ ነበር። ስለዚህም የአይሁዳውያኑ እነዚህን ሕግጋት መጠበቅ፥ ደኅንነትን ለማግኘት ወይም እሕዛብን ለማስገደድ ተብሎ እስካልሆነ ድረስ ምንም ስሕተት የለበትም። አንድ ኃጢአተኛ ኢየሱስ ስለ እርሱ እንደሞተ ካመነ፥ የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን ደኅንነትን ያገኛል ማለት ነው። በዚህም መሠረት የብሉይ ኪዳንን ሕግ እንዲጠብቅ መደረጉ ለደኅንነት የሚጨምርለት ወይም የሚቀንስበት ነገር ባለመኖሩ፥ ጳውሎስ ሽማግሌዎቹ ላቀረቡለት ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ይሰጣል። በ1ቆር. 9፡ 20 ላይም «ከሕግ በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ፥ እኔ ራሴ ከሕግ በታች ሳልሆን፥ ከሕግ በታች ላሉት ከሕግ በታች እንዳለሁ ሆንሁ» ብሎ ጽፏል።

ጥያቄ 20፡- ሀ) በቤተክርስቲያን ውስጥ በሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች መታዘዝ እንዳለብን የሚያሳይ ከዚህ ሥፍራ ልንቀስመው የሚገባን ትምህርት ምንድነው? ለ) ከዚህ በፊት ወንጌሉ እንዲስፋፋ ወይም ሰላም እንዲኖር ሲባል አኗኗራችንን እንድንለውጥ የሚያደርጉ ሰዎችን በተመለከተ፥ ሊከተሉት የሚገባቸው መመሪያ ምንድነው? ይህ ነገር ቤተክርስቲያንህ ውስጥ ባሉ ሰዎች ዘንድ እንዴት እንደሚሠራ አንዳንድ ሁኔታዎችን እንደምሳሌ ጥቀስ።

ጳውሎስ ለመሥዋዕት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ለአራቱ አይሁዳዊ ክርስቲያኖች ይከፍላል። የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች ይህ ድርጊት ጳውሎስ ለሕጉ ታማኝ እንደሆነ ለአይሁዳውያን ያሳያቸዋል ብለው ገምተው ነበር። ጳውሎስም እኔ ለክርስቶስ

ታማኝ ነኝ ብሎ ጣጣ ሳያበዛ ሽማግሌዎቹ እንዳዘዙት ያደርጋል። በዚህም መሠረት አብሮ ከሰዎቹ ጋር ሄዶ እራሱን ያነጻል። ከዚህም በኋላ ወደ ቤተመቅደስ በመሄድ የመንጻታቸው ጊዜ መቼ እንደሚገባደድና እያንዳንዱ መቼ መሥዋዕት እንደሚያቀርቡ ያሳውቃል።

ጥያቄ 21፡- 1ቆሮ. 9፡ 20-23 እና 10፡ 32-33 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች በሌሎች ያለህን አመልካከት ሊለውጡት የሚችሉት እንዴት ነው?

የሌሎችን ሰዎች እምነት በጥሞና መገንዘብ ይኖርብናል፤ ሆኖም ይህንን ስናደርግ እምነታችን ላይ አንዳች የሆነ ለውጥ እንዳያመጣ መጠንቀቅ ይኖርብናል። ሰዎችን ደስ ማሰኘቱም ለእግዚአብሔር ቃል ከመታዘዙ መቅደም የለበትም።

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 21፡ 27-40

ጳውሎስ በኢየሩሳሌም መከራና ችግር ያጋጥምሃል ተብሎ በተሰጡት ማስጠንቀቂያዎችም መሠረት፥ በእሱ ላይ ተቃውሞቹ መጽናት ይጀምራሉ። የቤተክርስቲያኒቷ ሽማግሌዎች እግዚአብሔር በጳውሎስ በኩል በሠራው ሥራ ደስ ይሰኛሉ። ሆኖም፥ ክርስቲያን በሆኑትና ባልሆኑት አይሁዳውያን ዘንድ በጳውሎስ ላይ የነበረውንም ጥላቻ ያውቁ ነበር። ስለዚህም ለጳውሎስ በማሰብና ሰላምን ለማውረድ ሲሉ ከሌሎች አራት አይሁዳውያን ጋር የመንጻቱ ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፍ ያደርጉታል። ጳውሎስም ይህንን ነገር በአሕዛብ ፊት መፈጸሙ በአይሁዳውያን ዘንድ ተቀባይነት ያስገኝለታል፤ ለአይሁድ ሕግም ታማኝ መሆኑን ያረጋግጥለታል ብለው ይገምቱ ነበር። ታዲያ ይህም ቢሆን፥ የአንዳንዶቹን ክርስቲያኖች አእምሮ ለውጦ ይሆናል እንጂ ሙሉ በሙሉ ወግ አጥባቂ የነበሩትን አይሁዳውያን አላሳመነም ነበር።

አንዳንድ ጊዜ፥ አንድ ችግር ለመግታት የሚደረግ ሙከራ የባሰ ችግርን ያስከትላል። ጳውሎስ የሽማግሌዎቹን ትዕዛዝ ፈጽሟል፤ ሆኖም ይህንን በማድረጉ ለጳውሎስ ያስገኘለት ጥቅም እንዳለ የሚገልጽ አንድ ማስረጃ የለም። አሁን ቀጥሎ እንደምናየውም፥ በኢየሩሳሌም ውስጥ በእሱ ላይ የተነሣው ተቃውሞ የሚነሣው ወደ ቤተመቅደስ ቢሄድ ነው።

የሐዋርያት ሥራ 21፡ 27-40 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ጥያቄ 22፡- ሀ) 1. በጳውሎስ ላይ ተቃውሞውን የቀሰቀሱት እነማን ናቸው? 2. በጳውሎስ ላይ የቀረቡት ክሶች ምን ምንድናቸው? 3. ጥሮፊሞስ ማነው?

ለ) 1. ሕዝቡ ጳውሎስን ምን አደረገው? 2. ከሕዝቡ እጅ ጳውሎስን ያዳነው ማነው? 3. ጳውሎስ ማን መሰላቸው? 4. ጳውሎስን ወዴት ወሰዱት?

ሐ) 1. ጳውሎስ ሻለቃውን ምን ብሎ ነው የጠየቀው? 2. ሻለቃው ጳውሎስ ማንን ነበር የመሰለው? 3. ጳውሎስ ለሕዝቡ ንግግር ያደረገው በምን ቋንቋ ነው?

የመንጻቱ ጊዜ ሊገባደድ አንድ ቀን ሲቀረው ጳውሎስ ለአምልኮ ወደ ቤተመቅደስ ሄዶ ነበር። አብረውትም ሌሎች አይሁዳውያን ነበሩ። ከእነዚህም ሰዎች መካከል

በኤፌሶን ከተማ ጥሮፊሞስ ከተባለ ሰው ጋር ያዩት ከእስያ የመጡ አይሁዳውያን ነበሩ። በዚህ ጊዜ ውስጥም በኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁዳውያን የነበራቸውን ስሜት ለመገንዘብ ስንል የቤተመቅደሱን አቀማመጥ ማወቅ ይኖርብናል። ስለዚህም የቤተመቅደሱን አቀማመጥ የሚያሳየውን ሥዕል ተመልከት።

ቤተመቅደስ መሠዊያ የወንዶች መሰብሰቢያ የሴቶች መሰብሰቢያ የአሕዛብ መሰብሰቢያ

በጳውሎስ ጊዜ ቤተመቅደሱ በጣም ሰፊ በሆነ ግቢ ውስጥ የተሠራ ነበር። በዚህ ግቢ ዙሪያ ትልቅ ግንብ አለ! በውስጡም አንድ ትልቅ መሰብሰቢያ ቦታ አለ። ይህም የአሕዛብ መሰብሰቢያ ነው። ይህን ዓይነቱንም ስያሜ የተሰጠው አሕዛብ መሄድ የሚችሉት እስከዚህ ክልል ድረስ ብቻ በመሆኑ ነው። ቤተመቅደሱ ያለበትም አንድ በትንሹ የተከለለ ሥፍራ አለ። በዚህም ሥፍራ ሁለት መሰብሰቢያ ቦታዎች አሉ። እነዚህም የሴቶችና የወንዶች መሰብሰቢያ ናቸው። ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሁሉም ወደ እነዚህ ቦታዎች መግባት አይፈቀድላቸውም ነበር። ውስጠኛውን ግቢ ከአሕዛቡ መሰብሰቢያ በሚለየው በር ላይም አሕዛብ ወደ ውስጥ እንዳይገቡ የሚያስጠነቅቁ ማስታወቂያዎች ነበሩ። «ወደ እስራኤላውያን መሰብሰቢያ» የገባ ከአሓዛብ ወገን የሆነ ማንኛውም ሰው በሞት እንደሚቀጣ የሚጠቅሱ በላቲንና በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ማስታወቂያዎችም ነበሩ።

ምናልባት ጳውሎስ ጥሮፊሞስን ወደ አሕዛብ መሰብሰቢያ ይዞት ሲገባ ሳይታይ አልቀረም። በቤተመቅደስም ውስጥ ለበዓለ ሐምሳ ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ በእስያ ነዋሪ የነበሩ አይሁዳውያን ነበሩ። ጳውሎስንም ከብዙ ሰዎች ጋር በቤተመቅደስ ውስጥ ሲያዩት፥ ወዲያውኑ ወደ ውስጠኛው ግቢ አሕዛብን ይዞ ገብቶአል ብለው ይገምታሉ። በመቀጠልም፥ አሕዛብ ወደ ውስጠኛው ግቢ ገብተዋል ብለው ይጮሃሉ። ለዚህም ድርጊት የወቀሱት ጳውሎስን ነው። ከዚህም ሌላ፥ በሮማው መንግሥት ወደሚገኙት ወደተለያዩ ሥፍራዎች በመሄድ ሕዝቡን የሚቃወሙ ትምህርቶችን ያስተምራል ብለው ተቃውመውታል። በዚህን ጊዜም፥ ከተማው ይታወክና ሕዝቡ ጳውሎስን ለመግደል ይነሣል።

ሕዝቡም ጳውሎስን ይዘው ከመቅደስ ውጭ ይጎትቱታል። ከቤተመቅደሱም ጎን፥ የሮም ወታደሮች የሚኖሩባት ክፍል ጦር ይገኛል። የዚህም ጭፍራ ሻለቃ፥ ከተማዋ እንደታወከች ይሰማል። በዚህም ጊዜ ወታደሮችንና መቶ አለቆችን ይዞ ወደ ሕዝቡ ይወጣል። ሕዝቡም ሻለቃውን ሲያይ፥ ጳውሎስን መደብደቡን ያቆማል! ሻለቃውም ጳውሎስን በሰንሰለት ያስረዋል። እርግጠኛውን ክስ ከጫጫታው የተነሣ ሊያውቅ ባለመቻሉም፥ ወደ ወታደሮቹ ሠፈር ይዘውት እንዲሄዱ ያደርጋሉ። ሕዝቡም በጣም ይጋፉ ስለነበር፥ ጳውሎስን ተሸክመውት ነበር የሄዱት።

ወደ ሰፈሩም እንደተቃረቡ፥ ጳውሎስ ሻለቃውን በግሪክ ቋንቋ፥ «አንድ ነገር ብነግርህ ትፈቅዳለህ?» ብሎ ይጠይቀዋል። ሻለቃውም፥ አራት ሺህ ያህል ነፍስ ገዳዮችን ያሸፈተ የግብፅ ሰው አድርጎ ይቆጥረው ስለነበረም በግሪክ ቋንቋ ሲናገር ይገርመዋል። ይህ የግብፅ ሰው እንደ አደገኛ ወንጀለኛ ይታደን የነበረ ሰው ነው።

ጳውሎስም አይሁዳዊ መሆኑን ሲናገር ለሕዝቡ ንግግር እንዲያደርግ ይፈቅድለታል። ሕዝቡም፥ ጳውሎስ በዕብራይስጥ ቋንቋ መናገር ሲጀምር ጸጥ ብሎ ይሰማው ነበር።

ለጳውሎስ ከራሱ ሕልውና ይበልጥ ለጠላቶቹ ስለ ክርስቶስ መመስከሩ ትልቁን ሥፍራ ይይዝ ነበር። እግዚአብሔርም በዚህ አደገኛ ሕዝብ ፊት መናገር የሚችልበትን ድፍረት ይሰጠዋል። በሚቀጥለው ሳምንትም ጳውሎስ ያቀረበውን መልእክት እናያለን።

ጥያቄ 23:- ይህ ሁኔታ ለክርስቶስ ስላለው ቁርጠኛ አቋም የሚገልጽልን ነገር ምንድነው?

ጥያቄ 24:- የጳውሎስንና ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት እንዳደረጓቸው አነፃፅር። ተመሳሳይ የሆኑትንም ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

# አምስተኛ ቀን:- ክለሳ

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

1. ጳውሎስ የየአብያተ ክርስቲያናቱን ሽማግሌዎች እግረ መንገዱን ሲሰናበት፥ ምን ዓይነት ተልእኮና ማስጠንቀቂያ ነው የሰጣቸው? ለምናስተምራቸው ሰዎች ስላለን ኃላፊነትስ እኛን የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
2. ሀ) ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም አልሄድም ብሎ ጥርጣሬ ውስጥ ገብቶ ነበርን? ለ) ወደዚያ ለመሄድ ያነሣሣው ነገር ምንድነው? ሐ) እንዳይሄድ ለማድረግ የሞከሩት እነማን ናቸው?
3. ምንም እንኳ ከሕግ በታች ባይሆንም ጳውሎስ እንዴት በመንጻቱ ሥርዓት ለማለፍ ፈቃደኛ ሊሆን እንደቻለ አብራራ።
4. ሀ) በጳውሎስ ላይ ተቃውሞ የተነሣው እንዴት ነው? ለ) ክሳቸውና ድርጊታቸው ሕጋዊ ነበርን?
5. ያዕቆብና ሽማግሌዎች ጳውሎስን ፊት ለፊቱ ተደቅኖበት ከነበረው ችግር ለማውጣት ሲሉ የረዱት እንዴት ነው?

የመወያያ ጥያቄዎችን በመመልከት ለሳምንታዊው ስብሰባ ተዘጋጅ።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. ክለሳ
4. ውይይት:-

ሀ) 1. አንድ ጥሩ የቤተክርስቲያን መሪ መመሪያው ሊሆኑት የሚገባውን ነገሮች ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በሰጠው መልእክት ላይ በመመርኮዝ ዘርዝራቸው። 2. እነዚህ ነገሮች በቤተክርስቲያንህ መሪዎች ውስጥ የሚታዩት እንዴት ነው? 3. ጠንክር የሚሉበት በየትኛው ቦታዎች ነው? ደከም የሚሉትስ?

4. አንድ ጥሩ መሪ ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ካለን ልማዳዊ አመለካከት ጋር የጳውሎስ መልእክት የሚወዳደረው እንዴት ነው?

ለ) 1. ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ካቀረበው መልእክት ስለ ሐሰተኛ መምህራን የምንማረው ነገር ምንድን ነው? 2. ቤተክርስቲያንህን በመጉዳት ላይ ያሉ አንዳንድ የሐሰት ትምህርቶች ምን ምንድን ናቸው? 3. ለኤፌሶን ሽማግሌዎች የተሰጠው ማስጠንቀቂያ በቤተክርስቲያንህ ከሚደረገው ነገር ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? 4. አንተና ሌሎች የቤተክርስቲያን መሪዎች በቤተክርስቲያናችሁ ያሉ ሰዎች በሐሰተኛ ትምህርት እንዳይጠመዱ ማድረግ ያለባችሁ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

ሐ) ምንም እንኳ እንዳይሄድ ቢነገረውም፥ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ያደረገው የጳውሎስ ባሕሪ ምን ነበር?

መ) የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉን ነገር ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ያለምንም ችግር የሚያስፈጽም ሁኔታ ነውን? ካልሆነስ የእጊዘብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆናችንን የምናውቀው እንዴት ነው?

ሠ) ለእግዚአብሔር ታዛዥ አለመሆናችን የአንድን ሰው ታዛዥነት ሊያሰናክልበትና በዚያ እንዳይገፋበት ሊያደርገው የሚችለው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 16

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 1-23፡ 11

## የመጀመሪያ ቀን፡-
## የሐዋርያት ሥራ 22፡1-21

የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የአይሁድን ክርስቲያኖች ያስነሡትን ውጥረት ለማርገብ ሲሉ ያቀዱት ዕቅድ ግቡን ሳይመታ ቀርቶ፥ ጳውሎስን እስከ መታሠር አድርሶታል። በዚህ ውስጥ ሳለም ጳውሎስ ለራሱ መከላከያ ማቅረብ ይፈልግ ነበር። ስለዚህም፥ ለአይሁዳውያኑ ንግግር እንዲያደርግ የሮማውን ሻለቃ ፈቃድ ይጠይቃል። ሉቃስም ከዚህ ክፍል አንስቶ እስከ መጽሐፉ መጨረሻ ድረስ ጳውሎስ በተለያዩ ሰዎች ፊት ቀርቦ የሰጠውን ምሥክርነት መዝግቦልናል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በአይሁዳውያን ፊት ያቀረበውን ምሥክርነቱን እናያለን። ወደ በኋላ ላይ ደግሞ

በተለያዩ መሪዎች ፊት ያቀረበውን እናያለን። ምንም እንኳ ተመሳሳይ ቢሆኑም፥ በተለያዩ ጊዜያት ምሥክርነቱን ለታደመው ሕዝብ ያቀርብ የነበረው ለእነርሱ በሚገባ አኳኋን ነበር።

ጳውሎስ ስለሚሠራው ሥራ እንደ መከላከያ አድርጎ የሚያቀርበው ስለ ጥሪውና ጌታ ስለሰጠው ተልእኮ በማስረዳትና ከዚህ በፊት ይጠላው የነበረውን ክርስትና እንዲከተል እግዚአብሔር ሕይወቱን እንዴት እንደለወጠው በመግለጽ ነው። የአንድ ክርስቲያን አስተማማኝ ምሥክርነት ኢየሱስ በሕይወቱ የሚያገኘው ለውጥ ነው። ሆኖም አይሁዶች በጳውሎስና በአሕዛብ ላይ የነበራቸው ጥላቻ የመልእክቱን እውነተኛነት እንዳያዩ አድርጓቸዋል።

ጥያቄ 1:- የሐዋርያት ሥራ 22: 1-23: 22 አንብብ።

ሀ) በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ጳውሎስ መከላከያውን ያቀረበው በእነማን ፊት ነው? ለ) በሁለቱም ጊዜያት የሰሚዎቹ ምላሽ ምን ነበር? እንዴት ነበር የሚለያዩት? እንዴት ነበር የሚመሳሰሉት?

የሐዋርያት ሥራ 22: 1-21 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 2:- ሀ) 1. ተሰብስበው የነበሩትን ሰዎች ጳውሎስ ምን ብሎ ነው የጠራቸው?
2. ሕዝቡ ጸጥ ያለው ለምንድነው?

ለ) 1. ስለ ጳውሎስ የትውልድ ቦታና ትምህርት አጠር ያለ ማብራሪያ ስጥ። 2. በመጀመሪያ ለክርስትና የነበረው አመለካከት ምን ነበር? 3. ጳውሎስን በክርስትና ላይ የነበረውን ጥላቻ እንዲለውጥ ያደረገው ነገር ምንድነው?

ሐ) 1. ጳውሎስ ለየት አድርጎ ስለ ሐናንያ የጠቀሰው ለምንድነው? 2. ጳውሎስ ለሁለተኛ ጊዜ ከጌታ ጋር የተገናኘው የት ነው? 3. በዚህ ጊዜስ ጌታ ምን ዓይነት ትዕዛዝ ነው የሰጠው?

ጳውሎስ ከሻለቃው ፈቃድ ካገኘ በኋላ፥ ለሕዝቡ በዕብራይስጥ ቋንቋ ንግግር ያደርጋል። በይሁዳ ይገኙ የነበሩ አይሁዳውያንም ይነጋገሩ የነበረው በዚህ ቋንቋ ነው።

የጳውሎስ ንግግር ያተኮረው በራሱ ምሥክርነት ላይ ነው። ከእዚህ በፊትም ስለ ኢየሱስ ሳይሰሙ ስለማይቀር፥ ስለ እርሱ ገለጻ ሊያደርግላቸው አልሞከረም። ዋናው ጳውሎስ የፈለገው ነገር በቤተመቅደስ ይኖሩ የነበሩት አይሁዳውያን በፓለስታይን ምድር ይኖሩ የነበሩ ሁሉና ከሌላ ሥፍራ የመጡት አይሁዳውያን ስለማንነቱ እንዲረዱና፥ ለምን እንዲህ እንደሚያስተምር እንዲገነዘቡለት ነው።

ጳውሎስ ምሥክርነቱን የሚጀምረው አይሁዳዊ መሆኑን በመጥቀስ ነው። አይሁዳውያንም በዘራቸው በጣም ኩራት ይሰማቸው ነበር። ንጹሕ አይሁዳዊ መሆናቸውንም ለመግለጽ እስከ አሥራ ሁለት ትውልድ ወደ ኋላ በመሄድ ሊጀምሩቸውን ያላውቁ ነበር። ወግ አጥባቂ የነበሩት ደግሞ የፈሪሳውያንን ሕግ እንደሚጠብቁ ማሳየት ነበረባቸው። በዚህም መሠረት ጳውሎስ ስለ ትውልድ ቦታውና እንደ አይሁዳዊ ስለተቀበለው ትምህርት ይናገራል።

**ጥያቄ 3:- በኢትዮጵያ ውስጥ መንፈሳዊ ሰዎች ከሚያተኩሩባቸው ነገሮች ጋር ይህ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?**

ተሰብስበው እንደሚሰሙት እንደ ብዙዎች አይሁዳውያን ጳውሎስ ከይሁዳ የመጣ አይሁዳዊ ሳይሆን ከይሁዳ ውጪ የምትገኝ የሮም ቅኝ ግዛት የነበረች አገር ውስጥ የመጣ አይሁዳዊ ነው። በይሁዳ ባደጉትና በሌሎች ከተሞች ባደጉት አይሁዳውያን መካከልም ጥላቻ ስለነበር፥ ምናልባት ይህን ሲናገር አንዳንዶቹ ሄሌናዊ አይሁዳውያን የእሱ ደጋፊዎች ሳይሆኑ አልቀረም።

ምንም እንኳ በአሕዛብ ከተማ ውስጥ ቢወለድም፥ ጳውሎስ ይከተል የነበረው የወግ አጥባቂዎቹን የፈሪሳውያንን ሥርዓት ነበር። ገና ልጅ ሳለም ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ በዚያን ጊዜ ከነበረው ትልቁ መምህር ከገማልያ እግር ሥር ሆኖ ይማር ነበር። እሱም ልክ አሁን ከፊቱ እንደ ቆሙት ሰዎች ቀናተኛ እንደነበረም ይነግራቸዋል።

ለቀናተኛነቱም ማስረጃ ይሆነው ዘንድ እንዴት አድርጎ ክርስቲያኖችን ያሳድድ እንደነበር ይጠቅሳል። ያለ አንዳች ጥርጥር ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከልም የጥንቷ ቤተክርስቲያን ሲያጠፉ የተነሣውን ታላቁን ሳውል የሚያውቅ ሰው አይታጣም። ታሪኩ እንዴት እንደተለወጠ ይነግራቸው ዘንድ መጀመሪያ በደማስቆ መንገድ ላይ ስለገጠመው ነገር መናገሩ ግድ ሆኖበታል። ከሊቀ ካህኑ ፈቃድ ተቀብሎ በደማስቆ የነበሩትን ክርስቲያኖች ለቅጣት ወደ ኢየሩሳሌም ሊያመጣ ወደዚያ በሚያመራበት ወቅት በድንገት በዙሪያው ታላቅ ብርሃን ያንፀባርቅና ምድር ላይ ይወድቃል። ከዚያም «ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ?» የሚል ድምፅ ይሰማል። እንዲህም ከልቡ ሆኖ ይዋጋ የነበረው እምነቱ ከሚለው እምነት ጋር እንደሆነና ሐዋርያት ከሙታን ስለተነሣው ኢየሱስ የሰጡትም ምሥክርነት እውነተኛ እንደሆነ ይገነዘባል። ይህም የሆነው በዚያን ሰዓት ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር በመገናኘቱ ነው። ስለዚህም ለአይሁድ ባህል ቀናተኛ መሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር ከመጣላት ሌላ ያስገኘለት ምንም ጥቅም የለውም።

**ጥያቄ 4:- ሰዎች ዛሬ ታላቅ የሆነ መንፈሳዊ ቅናት ኖሯቸው እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ሊዋጉ እንደሚችሉ አብራራ።**

ኢየሱስም ጳውሎስን ተነሥተህ ወደ ደማስቆ ሂድ ታደርገው ዘንድ ስለታዘዘው ሁሉን በዚያ ይነግሩሃል ይለዋል። ከብርሃኑም የተነሣ በመታወሩ ሰዎች ወደ ደማስቆ እየመሩ ይወስዱታል። ምንም ማድረግ በማይችልበት ሁኔታ ላይ በመድረሱም የነበረው አማራጭ እራሱን ዝቅ አድርጎ እግዚአብሔር ከዓይነ ሥውርነቱ እስኪፈውሰው እሱን መጠበቅ ብቻ ነበር።

**ጥያቄ 5:- እግዚአብሔር የጳውሎስን ዓይነ ለሦስት ቀን ያሳወረው ለምን ይመስልሃል?**

በመቀጠልም ጳውሎስ እግዚአብሔር ሐናንያ በሚባል ሰው ተጠቅሞ እንዲያይ እንዳደረገው ይጠቅሳል። ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከልም ሐናንያን የሚያውቅ አይታጣም፤ ምክንያቱም ሕጉን ይጠብቅና በአይሁዳውያን ዘንድ ትልቅ ከበሬታ ይሰጠው የነበረ መንፈሳዊ ሰው ነበርና ነው። ወደ ጳውሎስም መጥቶ እይ ይለዋል።

ከዚያም የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድና ጽድቁን ታይ ዘንድ ከአፉም ድምጹን ትሰማ ዘንድ አስቀድሞ መርጦሃል፤ ይህን ያደረገውም ባየኸውና በሰማኸው በሰው ፊት ሁሉ ምሥክር ትሆንለት ዘንድ ነው ብሎ ይነግረዋል። በመጨረሻም ሐናንያ ተነሥቶ እንዲጠመቅና ከኃጢአቱ እንዲነጻ ይነግረዋል።

ጥያቄ 6:- ሐ) ጳውሎስ ሲመሠክር ከኢየሱስ ጋር በደማስቆ የተገናኘበትን ጊዜ ሁልጊዜ የሚጠቅሰው ለምን ይመስልሃል? ለ) በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደተገናኘንና በሱ ልናምን እንደቻለን መጥቀሱ ጥሩ የሚሆነው ለምንድነው? ሐ) ለሌሎች ስትመሠክር የራስህን ምሥክርነት ያሰማኸው በምን ዓይነት ሁኔታዎች ላይ እንደሆነ ማብራሪያ ስጥ።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳል። በዚህች አሁን በነበረበት ቤተመቅደስ ውስጥም ሳለ፥ ጌታ እንደገና ይገናኘውና «ፍጠን ከኢየሩሳሌምም ቶሎ ውጣ ስለ እኔ የምትመሠክረውን አይቀበሉህምና» ይለዋል።

ጳውሎስም ለጌታ መልስ ይሰጣል፤ በአይሁድ ሃይማኖት ውስጥ መሪ ስለነበር፥ አይሁዳውያን ይቀበሉኛል ብሎ ያስብ ነበር። በቤተክርስቲያን ተቃዋሚነቱም የታወቀ ነበር። ከዚህም ሌላ በየምኩራቡ እየሄደ ክርስቲያኖችን እየጎተተ በመደብደብ የእስጢፋኖስን መሞት እንዳጸደቀ አይይሁዳውያን በደንብ ያውቃሉ። አሁን ደግሞ ክርስቲያን በመሆኑና እንዲህ በአስገራሚ ሁኔታ በመለወጡ ያለጥርጥር ያዳምጡታል ተብሎ ነው የሚገመተው። ሆኖም ሁኔታው እንዲህ አልነበረም፤ እግዚአብሔር ለእርሱ የተለየ ዓላማ ስለነበረው። በዚህም መሠረት ጌታ «ሂድ እኔ ወደ አሕዛብ ከዚህ ወደ ሩቅ እልክሃለሁ» ይለዋል። ጳውሎስም ይህ ተልእኮውን ተቀብሎ ወንጌሉን ይዞ ወደ አሕዛብ ከተሞች ይሄዳል።

ስለ አሕዛብ እስከጠቀሰበት ጊዜ ድረስ ዝም ብለው ከሰሙ በኋላ እንደ ጳውሎስ ያለው መኖር አይገባውም ብለው ይጮሃሉ።

ጥያቄ 7:- በሐዋርያት ሥራ ጥናትህ ላይ በመመርኮዝ፥ ያለበቂ ምክንያት አይሁዳውያን ለምን በጳውሎስና በአሕዛብ ላይ ጥላቻ እንደነበራቸው አብራራ።

ጳውሎስ ሕጉን በሚጠብቀውና የእግዚአብሔር መልእክተኛ በሆነው በሐናንያ በኩል እግዚአብሔር ብርሃኑን እንደሰጠውና ወደ አሕዛብ ወንጌሉን ይዞ የመሄድ ተልእኮ እንደሰጠው በግልጽ ያስቀምጠዋል። በተጨማሪም እግዚአብሔር ጳውሎስን እንደተቀበለው የተረጋገጠው፥ ብርሃኑ ሲመለስለት ነው።

ጳውሎስ የአዲስ ኪዳኑን ራዕይ ከብሉይ ኪዳኑ ጋር ለማያያዝ ሞክሯል፤ ሆኖም አይሁዳውያኑ ማሳመኛውን ሲሰሙ ይህን አንቀበልም ብለው አሻፈረኝ ይላሉ። ከዚህም ሌላ በቤተመቅደስ እየጸለየ ሳለ ተመስጦ እንደመጣበት ይጠቅሳል። ይህንንም በማለት ለአይሁዳውያኑ ሊያሳያቸው የፈለገው አሁንም በቤተመቅደስ እንደሚያመልክና እንደገናም ክርስቶስ ያየው በዚህ ሥፍራ መሆኑን ነው።

አይሁዳውያኑም እንደገና ይህንን ማስረጃ አይቀበሉም። ከዚያም ወዲያውኑ ስለ አሕዛብ መጥቀስ ሲጀምር በንዴት ሆ! ብለው ይነሣሉ።

ይህ የጳውሎስ መለወጥ ገለጻ በሐዋርያት ሥራ ተጽፎ የሚገኘው ሁለት ጊዜ ነው። ሉቃስ ለመጀመሪያ ጊዜ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 9 ላይ ገልጾታል። እኛም ለዓለም ከምናቀርበው ምሥክርነት ውስጥ አንዱና ታላቁ:- ክርስቶስ እንደ ጳውሎስ ዓይነቱን የሕይወት ለውጥ በሰው ሕይወት የማምጣት ችሎታ ያለው መሆኑን ነው።

ጥያቄ 8:- ሀ) በምን ዓይነት መንገድ ነው የተለወጠ ሕይወት ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትልቅ ምሥክር የሚሆነው? ለ) ሕይወትህ እንዴት እንደተለወጠና ለማያምኑ ሰዎች ያለህ ምሥክርነት እንዴት ሊሻሻል እንደቻለ ማብራሪያ ስጥ።

# ሁለተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 22፡ 22-29

ጳውሎስ ለአይሁዳውያኑ ባሰማው ንግግር ውስጥ ቤተ መቅደስን ወይም ሕግጋትን እንደማይቃወም ነገር ግን ልክ እንደ አንድ የብሉይ ኪዳን ነቢይ እግዚአብሔር ለአሕዛብ እንዲመሠክርላቸው እንደጠራው ሊያስረዳቸው ሞክሯል።

ጥያቄ 9:- ወደ አሕዛብ የተላከ አንድ የእስራኤል ነቢይ ጥቀስ።

ጳውሎስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ያቀረበው መከላከያ የአሕዛብን ስም ሲያነሣ ውድቅ ሆኖበታል። ለአሕዛብ የነበራቸው ጥላቻ ልክ እንደ ዛሬው ጊዜ እንዳለው ጥላቻና ምቀኝነት የመጻሕፍትን እውነታ እንዳያዩ አድርጓቸዋል። ከጌታ የተሰጠውን ተልእኮ በጥሞና ካደመጡ በኋላ፣ በአሕዛብ ላይ የነበራቸውን ጥላቻ ጳውሎስ የሚነግራቸው በደንብ እንዲያጤኑት አድርጓቸዋል።

ጌታ ሰዎችን ከጥፋት የሚከልልበት የተለያዩ መንገዶች አሉት። አንዳንዴ ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ ይጠቀማል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአጋጣሚዎች ይጠቀማል። ጳውሎስም፣ ለሕይወቱ አስጊ ከሆነ ሁኔታ ውስጥ ሊወጣ የቻለው የሮም ተወላጅ በመሆኑ ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 22-29 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 10:- ሀ) በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ በቅጽበት በጳውሎስ ላይ ያለውን ጥላቻ የገለጸው እንዴት ነው?

ለ) 1. ጳውሎስን በተመለከተ ሻለቃው የሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው? 2. ጳውሎስን እንዴት አድርገው ሊመረምሩት እንዳሰቡ ግለጽ።

ሐ) 1. ጳውሎስ ከመገረፍ ሊድን የቻለው እንዴት ነው? 2. ይህ ጉዳይስ ሮማውያኑ ሊያስደነግጣቸው የቻለው ለምንድነው?

እንደምታስታውሰው በመጀመሪያ ጳውሎስን የከሰሡበትና ሁከት ያስነሡበት ጉዳይ አንድ አሕዛብ ሰው ወደ ቤተመቅደስ ውስጠኛ ክፍል ይዘህ ገብተሃል የሚል ነበር። ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ወደ አሕዛብ ልኮኛል ብሎ ሲናገር ሕዝቡ በንዴት

መምህ፥ ልብሳቸውን መቅደድ፥ ጳውሎስን አለመቀባላቸውንና በእሱም በጣም መናደዳቸውን ለመግለጽ ትቢያ መበተን ይጀምራሉ።

በዚያ የተሰበሰበው ከቁጥጥር ውጪ በመሆኑ ሻለቃው ወደ ሠፈሩ ይዘውት እንዲገቡና እየገረፉ እንዲመረምሩት ያዛል። ጳውሎስም ሥጋን የሚበሉ ሹል አጥንት ወይም ብረት ባለባቸው መግረፊያዎች ሊገረፍ በጠፍር ጥብቅ ተደርጎ ይታሠራል። ይህን ዓይነቱ ግርፋትም ሰውዬውን ካልገደለው፥ ሽባ አድርጎ ያስቀረው ነበር። ጳውሎስ ይህን ዓይነቱን ግርፋት በፊሊጵስዩስና በሌሎች ቦታዎች እንደተቀበለ የሚታወስ ነው።

ምንም እንኳ ጳውሎስ ሞትን ባይፈራም ያለ በቂ ምክንያት መገረፉ ግን ተገቢ አልነበረም። ስለዚህም ጳውሎስ ሊገርፈው በአጠገቡ ቆሞ የነበረውን መቶ አለቃ «የሮሜ ሰው ያለ ፍርድ ትገርፉ ዘንድ ተፈቅዶላችኋልን?» ብሎ ይጠይቀዋል።

በሮም ሕግ የሮም ተወላጅ የሆነን ሰው በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መመርመር ሕገ ወጥ ድርጊት ነበር። በዚህም መሠረት የሮም ተወላጆች ከመቀጣታቸው በፊት በደንብ በሕግ ፊት የመቅረብ መብት ነበራቸው። ታዲያ አንድ ሌላ ባለሥልጣን ይህን መብት ቢተላለፍ ትልቅ ቅጣት ከሮም ባለሥልጣኖች ይጠብቀዋል (በፊሊጵስዩስ የነበሩት ባለሥልጣኖች ጳውሎስ የሮም ተወላጅ መሆኑን ሲነገራቸው እንዴት እንደደነገጡ አስታውስ)።

ጳውሎስን ሊገርፍ ተዘጋጅቶ የነበረው መቶ አለቃ፥ ቶሎ ብሎ ይሄድና ይህን ነገር ለሻለቃው ይናገራል። ሻለቃው ወደ እርሱ ቀርቦ ስለ ዜግነቱ ይጠይቀዋል። አንድ ሰው የሮም ተወላጅ ሊሆን የሚችለው በሦስት ዓይነት መንገድ ነው። ሆኖም ከዚህ ሁሉ በላይ የሆነው በትውልድ የሮም ተወላጅ መሆን ነው። ሁለተኛ ደግሞ አንድ ሰው ለሮም መንግሥት አንድ ትልቅ ሥራ ከሠራ ይህን ዜግነት ሊያገኝ ይችላል። ይህ የዜግነት መብት የሚሰጠውም በሮም ጥሩ ሰዎች ናቸው ተብለው በጥንቃቄ ለተመረመሩ ሰዎች ነው። በተለይ ደግሞ ለሮማው መንግሥት ግዛቱን እንዲያስፋፉ አስተዋጽኦ ላደረጉ ሰዎች ይህ መብት ይሰጣል። ሦስተኛ አንድ ሰው ይህን ዜግነት ብዙ ገንዘብ በመስጠት ሊያገኘው ይችላል።

ጳውሎስ የተወለደው በተርሴስ ቢሆንም ይህ የሮምን ዜግነት አያስገኝለትም። ተርሴስ በሮም ቅኝ ግዛት ውስጥ ያልነበረች ነጻ ከተማ ነበረች። ስለዚህም ጳውሎስ ይህን የዜግነት መብት ሊያገኝ የቻለው ምናልባት አባቱ የሮማውን መንግሥት በማገልገሉ ይሆናል። በዚህም ዓይነት ጳውሎስ የሮም ዜጋ ሊሆን የቻለው አይሁዳዊ የነበረው አባቱ ይህን የዜግነት መብት በማግኘቱ ነው። ጳውሎስ ይህንን የዜግነት መብት በማግኘቱም ከአረመኔያዊው ድብደባ ሊድን ችሏል። ወደ በኋላም እንደምናየው ይህን ዜግነት በመያዙ ወደ ሮም ሄዶ ለፍርድ እንዲቀርብ ይደረጋል።

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው አንሥቶ ጳውሎስ የሮም ዜግነት መብት ካለው ቤተሰብ ውስጥ እንዲወለድ አድርጓል። ይህም ለአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን ብቁ አድርጎታል። ለእግዚአብሔር ገና ከመዳናችን በፊት በእኛ ውስጥ ያሉትን የቀድሞ

ነገሮች መንግሥቱን ለማስፋፊያ ይጠቀምባቸዋል። እግዚብሔር በእኛ ትምህርት፥ በቤተሰባችን ካገኘነው ውርስ፥ በቤተክርስቲያን ውስጥ ካገኘነው ልምድና በምናልፍባቸው ችግሮች በመጠቀም የበለጠ ብቁ ሆነን እሱን እንድናገለግል ያደርጋል።

ጥያቄ 11፦ ሀ) በሕይወትህ ውስጥ ከወንጌሉ መስፋፋት ጋር ብዙ ግንኙነት የሌለው እግዚአብሔር የተጠቀመበት ነገር ምንድን ነው? ለ) እራስህን በበለጠ ሁኔታ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ዝግጁ የምታደርገው እንዴት ነው?

# ሦስተኛ ቀን፦የሐዋርያት ሥራ 22፡ 20-23፡ 11

በትናንትናው ዕለት፥ የጳውሎስ የሮም ዜግነት እንዴት ከግርፋት እንዳዳነውና በሻለቃው ዘንድ ከበሬታን እንዳስገኘለት አይተናል። ዛሬ ደግሞ እንደ ፈሪሣዊ የነበረው ዕውቀት እንዴት ከአይሁድ ከፍተኛ ሸንጎ ፍርድ ሊያድነው እንደቻለ እናያለን። አሁንም እንደገና ጳውሎስ ጠላቶቹን ለማሸነፍ ባለፈው ጊዜ የነበረውን ልምድ እንደ መሣሪያ ይጠቀምበታል።

የሐዋርያት ሥራ 22፡ 30-23፡ 11 አንብብና ለሚቀጥሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 12፦ ሀ) ሻለቃው የካህናት ሸንጎው እንዲሰበሰብ ያዘዘው ለምንድነው?

ለ) 1. ሊቀካህኑ ጳውሎስን አፉን እንዲመቱት ያዘዘው ለምንድነው?

2. ጳውሎስ ሊቀ ካህኑን ይቅርታ የጠየቀውስ ለምንድነው?

ሐ) 1. ሸንጎውን የወከሉት ሁለት ቡድኖች ማንና ማን ነበሩ?

2. ጳውሎስ የየትኛው ቡድን አባል ነበርኩ ነው የሚለው?

መ) 1. ጳውሎስን የደገፉት እነማን ናቸው?

2. የተናገሩትስ ነገር ምንድነው?

3. የሻለቃው ጭፍሮች ጳውሎስን ለማዳን የተላኩት ለምንድነው?

ሠ) ጳውሎስ ከጌታ የተቀበለው መልእክት ምን የሚል ነው?

ሻለቃው ለምን አይሁዳውያኑ በጳውሎስ ላይ እንዲህ ንዴታቸውን እንደሚገልጹ አላወቀም። በዚህም ምክንያት እውነተኛውን ነገር ለማወቅና ጳውሎስን እንዲህ ዓይነት ጥፋት ፈጽመሃል ለማለት ሲል የካህናት አለቆች ሸንጎ እንዲሰበሰብ ያዛል።

ጳውሎስም በሸንጎው ፊት ቀርቦ «እስከዚያ ቀን ድረስ በመልካም ሕሊና በእግዚአብሔር ፊት ኖሬአለሁ።» በማለት መከላከያውን ይጀምራል። ይህን ዓይነቱም አነጋገር በጣም የድፍረት አነጋገር ነው። ጳውሎስ ደግሞ ሕይወቱን አሳልፎ ለኢየሱስ በመስጠቱና ሙሉ ኃይሉን ክርስትናን ከማውደም ይልቅ ለወንጌል መስፋፋት ስለሰጠ በእሱና በእግዚአብሔር መካከል ሁሉ ነገር ትክክል እንደሆነ የሚያረጋግጥለት ሰላም በውስጡ ነበር። ስለዚህም ጳውሎስ ይህን ዓይነት ድፍረት ሊኖረው የቻለው በውስጡ የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ ተስፋ ስለነበር ነው። መልካም ሕሊና ነበረኝ ሊልም የቻለው በራሱ ጽድቅ ሳይሆን በክርስቶስ ባገኘው ጽድቅ ምክንያት ነው።

ጥያቄ 13፦ በንጹሕ ሕሊና ይህን ዓይነት ንግግር ስለ እራስህ ልትናገር ትችላለህን? ካልሆነ የሚያሳፍሩህን ነገሮች በዝርዝር ጻፍና በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ግባ።

ይህን ዓይነት ንግግር የተለመደ ባለመሆኑና የሊቀ ካሕንና የሌሎችን ሕሊና የሚነካ በመሆኑ ሊቀ ካህኑ ሐናንያ ቆመው የነበሩትን የጳውሎስን አፍ እንዲመቱ ትዕዛዝ ይሰጣል። ሐናንያ በጨካኝነቱ የታወቀ ነበር። ምንም እንኳ የአይሁዳውያን ሃይማኖት መሪ ቢሆንም፥ ያገለግል የነበረው የራሱ ሀብት ለማካበት ብቻ ነበር። እንዲያውም ከአሥር ዓመት በኋላ አይሁዳውያን በርም ላይ ሲያምጹ በመጀመሪያ ካደረጓቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ሐናንያን መግደል ነበር።

ጳውሎስ በፍርሃት መልክ የተወሰነበትን ውሳኔ ይቃወማል። እንደ ትንቢትም አድርጎ በእርሱ ላይ የሚወርደውን የእግዚአብሔርን ፍርድ አስቀድሞ ይናገራል። በተጨማሪም በኖራ የተለሰነ ግድግዳ ተመስላለህ ብሎ ይከሰዋል። ምንም እንኳ ኖራው ከውጪ ሲታይ ቢያምርም፥ የግድግዳውን ቆሻሻና ስንጥቅ ይሸፍን ነበር። ልክ እንደዚሁ ሊቀ ካህኑም ባደረገው ልብስ ከውጪ ሲታይ ሰውን ቢማርክም ውስጡ በክፋት በቆሻሻ የተሞላና ሊወድቅ የተቃረበ ነበር። በሌላ አነጋገር ሊቀ ካህኑ ግብዝ ነበር። ሊቀ ካህኑም ጳውሎስን በጥፊ ሊያስመታው የቻለው የብሉይ ኪዳንን ሕግ ተላልፈሃል ብሎ ነው።

ጥያቄ 14፦ ሲታዩ ለዓይን የሚማርኩ፥ ውስጣቸው ግን በክፋት የተሞላ መንፈሳዊ መሪዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ ግለጽ።

ጳውሎስ ለምን ሊቀ ካህኑን ሊያውቅ እንዳልቻለ አናውቅም። ሆኖም አንዳንዶች ዓይኑ በደንብ አያይ ይሆናል ብለው ይገምታሉ። ያም ሆነ ይህ ከመካከል አንዱ ተነሥቶ ሊቀ ካህኑን ትሳደባለህ ሲለው ቶሎ ብሎ ይቅርታ ይጠይቃል። ሊቀ ካህኑ የፈለገውን ያህል ጨካኝ ቢሆንም መሪ ሆኖ ሊያስተዳድር የሚችለው እግዚአብሔር በሰጠው ሥልጣን እንደሆነ ጳውሎስ ተገንዝቧል። ስለዚህም ሊቀካህኑ ሊከበር ይገባዋል።

ጳውሎስ መከላከያውን ያቀረበው ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለጌታም ጭምር ነው። ካህኑን በኖራ የተለሰነ ግድግዳ ብሎ መጥራቱ ካህኑን ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሥርዓተ ሕጉን የሚነቅፍ ስድብ ነው። ጳውሎስን አፉ ላይ መምታት ሕጋዊ አይደለም! ስለዚህም ጳውሎስ ሊቀ ካህኑ በሕጉ መሠረት አይፈርድም ነበር የሚለው። በአይሁድ ሸንጎ ፊት ክስ የቀረበበት ሰውዬ መብት በደንብ ይጠበቅ ነበር! በተጨማሪም ሰውዬው ወንጀለኛ ሆኖ እስከ አልተገኘ ድረስ እንደ ንጹሕ ሰው ነበር የሚቆጠረው።

ጳውሎስ ይህን መልስ ሰጥቶ የነበረው በንዴት ስለነበር የሕዝቡ ገዢ የሆነውን በመሳደቡ ይቅርታ ለመጠየቅ ጥፋተኛነቱን ለማመን ምንም ጊዜ አልወሰደበትም። ሁላችንም ስሕተት እንሠራለን፤ ሆኖም፥ ሁላችንም ዝቅ ብለን ጥፋተኛነታችንን አምነን ነገሮችን ትክክል ለማድረግ ዝግጁ ነን?

ጥያቄ 15:- ሀ) ስሕተት ስንፈጽም ያንን ነገር ተረድቶ ይቅርታ መጠየቁ ድክመት ሳይሆን የማወቅ ዝንባሌ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) አንድ ሰው እስቀይሞህ ይቅርታ የጠየከበት አጋጣሚ ካለ እስቲ ሰፋ አድርገህ ግለጽ።

ስሕተታችንና ድክመቶቻችንን ሸፍነን እንድንቆም የሚያደርገን ትዕቢት ነው። ስሕተተኞች መሆናችንን ማመኑና ይቅርታን መጠየቁ ራስን ዝቅ ማድረግን ይጠይቃል።

ጳውሎስ በሸንጎው ፊት ባቀረበው መከላከያ ላይ ለአይሁድ እምነት ታማኝ እንደሆነና ክርስትናም የጥንቱ የአይሁድ ሃይማኖት ቅጥያ እንደሆነ ይገልጻል። በመቀጠልም በሰዱቃውያንና በፈሪሳውያን መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት ይጠቅሳል። የክርስትና መሠረት ወደ ሆነው ወደ ሙታን ትንሣኤ ዞር በማለት ክስ የተመሠረተበት ይህን በማመኑ እንደሆነ ያመለክታል።

ጳውሎስ በሙታን ትንሣኤ በማመኑ ከፈሪሳውያን ጋር ይመሳሰላል። እንዲያውም እራሱ ፈሪሳዊ እንደሆነ አባቱም ፈሪሳዊ እንደሆነና አንድ ፈሪሳዊ ክርስቲያን ቢሆን እንደሚችል ነበር የሚገልጸው። በሌላ አነጋገርም አንድ ሰው እውነተኛ ፈሪሳዊ ሊሆን የሚችለው ክርስቲያን ከሆነ ነው ማለቱ ነው። ሊቀ ካህኑ ይመረጥበት የነበረው የሰዱቃውያን ክፍል ደግሞ ትንሣኤ መልአክና መንፈስ የለም የሚሉ ነበሩ። የጳውሎስ ንግግርም በሰዱቃውያንናአ በፈሪሳውያን መካከል ጥል ያስነሣል። አንዳንዶቹም ፈሪሳውያን «በዚህ ሰው ላይ ምንም ክፉ ነገር አላገኘንበትም» አሉ። ጥሉም በጣም እየከረረ በመሄዱ፥ ሻለቃው ጳውሎስን ይገነጣጥሉታል ብሎ አሰበ። በዚህም ምክንያት ጭፍሮቹ ጳውሎስን ይዘው ወደ ሠፈሩ እንዲያገቡት ያዝዛል። በጳውሎስ የቀረበውን ክስ መረዳትም አልተቻለም፤ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር የጳውሎስን ሕይወት ለማዳን እንደገና በሻለቃው በኩል ሆኖ ይሠራል።

የሙታንን ትንሣኤ ለመከላከያው መሠረት አድርጎ ጳውሎስ ያቀረበው ለምንድነው? ይህንን ሰፋ አድርጎ ሲያብራራው በ 1ኛ ቆር. ምዕራፍ 15 ላይ ለሚያምኑ ሰዎች የትንሣኤ መሠረት የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ እንደሆነ ይናገራል። ጳውሎስ ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስን በደማስቆ መንገድ ላይ ተገናኝቶታል። ይህንንም ካየ በኋላ፥ በኢየሱስ ያመኑ ሁሉ ከሞት እንደሚነሡ ተገንዝቧል። የሙታን ትንሣኤን መካድ ኢየሱስ ከሙታን አልተነሣም ብሎ እንደማመን ነው። ያለ ክርስቶስ ትንሣኤ ደግሞ ክርስትና ባዶ ሰው ሠራሽ ሃይማኖት ይሆናል። ስለዚህም ክርስትና የተመሠረተው በሙታን ላይ ነው።

ጥያቄ 16:- ከሞት የመነሣቱ ተስፋ ለአንተ ትልቅ ማጽናኛ የሚሆነው ለምንድነው?

አይሁዳውያን ጳውሎስን በተገቢው መንገድ መመርመሩን እንደ ቁም ነገር አልቆጠሩትም። የእነርሱ ዋና ዓላማቸው በጳውሎስ ላይ መፍረድና ለሕጋቸውና ለባሕላቸው ቀናተኛ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸውን የጳውሎስን መልእክት ማቆም ብቻ ነው።

ስለ ጳውሎስ የተናገሩ ትንቢቶችና ማስጠንቀቂያዎች በኢየሩሳሌም በመፈጸም ላይ ናቸው። ወደ ሮምና ወደ እስፓኝ የመሄዱ ተስፋውም ደብዛው እየጠፋ ነው። ሆኖም፥ ይህ በእንዲህ እንዳለ በሁለተኛው ሌሊት ጌታ እንደገና ይገለጥለትና «ጳውሎስ ሆይ፥ በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሠከርህ እንዲሁ በሮሜም ትመሠክርልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ» ይለዋል። ይህም ገና ወደፊት የሚገጥመውን ችግር በድፍረት እንዲጋፈጠው አድርጎታል።

# አራተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 23፡ 12-22

ምንም እንኳ ሻለቃው በጳውሎስ ላይ የቀረበውን ክስ መርምሮ እሱን ለመልቀቅ ወይም በግልጽ ለመወንጀል ቢዘጋጅም የካህናቱ ሸንጎ በምንም ዓይነት ክስ ላይ ሊስማማ አልቻለም። አንዳንዶች ጳውሎስን ነፃ ለመልቀቅ ፈልገዋል! ሌሎች ደግሞ ለፍርድ ሊያቀርቡት ይፈልጉ ነበር። ምናልባትም በከንቱ ካባከነው ጊዜና ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ ይመሥላል! ጳውሎስ ወደ እሥር ቤቱ እንዲመለስ ይደረጋል። ጌታ ደግሞ ጳውሎስ መጽናናት ያለበትን ጊዜ ያውቅ ስለነበር፥ አይዞህ ብሎ በማጽናናት በመጨረሻ ላይ ወደ ሮም እንደሚሄድ ይነግረዋል። ሆኖም ጳውሎስ ሮም እስከሚሄድበት ጊዜ ድረስ ሁለት ዓመት ያልፋል ብሎ አላሰበም ነበር።

ምንም እንኳ ጳውሎስ ወደ ሮም እንደሚሄድ ከጌታ ማረጋገጫ ቢሰጠውም፥ ወደዚያ ለመሄድ የሚያልፍበት ውጣውረድ ግን ገና መጀመሩ ነበር። የሁኔታዎችም አለመረጋጋት ለአንድ ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ አለመሆኑን የሚገልጹለት ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ ጌታን ይጠራጠር ነበር። ሆኖም ተቃውሞና ግጭቱ ከጳውሎስ ጋር አልተለዩም ነበር። ከዚህም የምናየው እነዚህ ነገሮች እራሳቸው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንደሆንን የሚገልጹ ሳይሆኑ አለመቅረታቸውን ነው።

የሐዋርያት ሥራ 23፡ 12-22 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 17:- ሀ) 1. አይሁዳውያን በጳውሎስ ላይ የዶለቱት ነገር ምን ነበር? 2. በዚህ ሴራ ውስጥ የተካፈሉት ሰዎች ምን ያህል ናቸው? 3. ይህንን ዕቅዳቸውን በተግባር ለመፈጸም ሲሉ ስምምነት ላይ የደረሱት እንዴት ነው?

ለ) 1. ይህን የአይሁዶች ደባ የሰማው ማነው? 2. ይህ የአይሁዳውያን ደባ ለሮማዊው ሻለቃ የተገለጸለት እንዴት ነው?

ሐ) ሻለቃው የጳውሎስን የእህት ልጅ ምንድነው ያለው?

አይሁዳውያን ጳውሎስን በሚከሱበት ጉዳይ ባለመስማማታቸው ምክንያት፥ ጳውሎስ ባይፋ አልተከሰሰም። ስለዚህም አይሁዳውያን ጳውሎስን የሚያስወግዱበትን ደባ ይዶልታሉ። በጳውሎስ ላይ የነበራቸውም ጥላቻ የሚታየው የጳውሎስን ሕይወት ለማጥፋት ባቀዱት ሴራ ውስጥ ነው። ከአርባ የሚበልጡም አይሁዳውያን ጳውሎስን እስከንገድል ድረስ ምንም አንበላም ምንም አንጠጣም ብለው መሐላ ያደርጋሉ። ይህም በጥቂት ቀናት ውስጥ ጳውሎስን ለመግደል ተስማምተዋል ማለት ነው። ለአይሁዳውያን መሐላ በጣም ትልቅ ነገር ነው! ስለዚህም ግዴታ ይፈጽሙት ነበር።

በዚህም መሠረት ይህን መሐላ ያደረጉ ሰዎች ሄደው በሸንጎው ለተሰበሰቡት ካህናት ይነግራቸዋል። ሸንጎውንም ጠበቅ ላለ ምርመራ ጳውሎስን እንፈልገዋለን ብለው እንዲጠይቁ ያደርጋሉ። ከዚያም ለፍርድ ሳይቀርብ እነዚህ አይሁዳውያን ይገድሉታል። ሸንጎውም በጭቅጭቅ ምክንያት በጳውሎስ ላይ ሊመሠርቱት ያሰቡት ክስ በመከሸፉ ይህን ደባ ተግባራዊ ለማድረግ ይሳማማሉ።

እግዚአብሔር የክፉ ሰዎችን ደባ የሚያከሽፍበት የራሱ የሆነ መንገድ አለው። በዚህም መሠረት በሆነ ዓይነት መንገድ የጳውሎስ የእህቱ ልጅ ጳውሎስን ለመግደል እንደ ዶለቱ ይሰማል። ከዚያም ወደ ጳውሎስ በመሄድ ያስጠነቅቀዋል። ጳውሎስም ይነግረው ዘንድ የእህቱን ልጅ ወደ ሻለቃው ይሰደዋል። ስለ ደባቸውም ሲሰማ ይህን ነገር ለእኔ ማመልከትህን ለማንም እንዳትገልጽ ብሎ ያዘዋል።

ጥያቄ 18፡- እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የራሱን ሰዎች ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት ሁኔታ ከጠላት እጅ ያዳናቸው እንዴት ነው?

ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ውስጥ ዘመድ እንዳለው ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዚህ ሥፍራ ነው። እህቱና ልጇ ክርስቲያኖች ይሁኑ ወይም በዓለ ሃምሳን ለማክበር የመጡ ታማኝ አይሁዳውያን የምናውቀው ነገር የለንም። ሆኖም፥ የእህቱ ልጅ በኢየሩሳሌም ተማሪ በመሆኑ በጳውሎስ ላይ የተሸረበውን ደባ ሊሰማ የቻለ ይመስላል። ታዲያ ምንም እንኳ ልጁ እንዴት እንደሰማ ባናውቅም፥ እግዚአብሔር ጳውሎስን ለማዳን እጁን እንዳስገባ ግን እንረዳለን። እግዚአብሔር የራሱ የሆኑ ሰዎችን ወይም ደግ የሆኑ ሰዎችን ዓላማውን እንዲፈጽም ያመቸው ዘንድ በተለያዩ ከፍተኛ በታዎች ላይ ያስቀምጣቸዋል።

ጥያቄ 19፡- በአንድ ፍርድ ውስጥ እግዚአብሔር ጣልቃ ሲገባ አይተህ ወይም መግባቱን ተገንዝበህ ታውቃለህ?

ጌታ ወደ ሮም ትሄዳለህ ብሎ የሰጠው የተስፋ ቃል ያለምንም ችግር ወደዚያ ትደርሳለህ ማለት አይደለም። ያውም ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ነገር የሚፈጸመው በብዙ ፈተናዎችና መከራዎች ከታለፈ በኋላ ነው። እግዚአብሔርም የልጆቹን እምነት ለማጠንከር ሲል፥ በብዙ ችግር ውስጥ ያሳልፋቸዋል። በችግር ውስጥም በተገኙት ድሎች በመጠቀም፤ ኃይሉን ያሳያል፤ ያልዳኑትም ሰዎች ይናገራቸዋል።

ጥያቄ 20፡- እግዚአብሔር አንተን በፈተና ውስጥ በማሳለፍ እንዴት እምነትህን ሊያጠነክርልህ እንደቻለ አብራራ።

# አምስተኛ ቀን፡- ክለሳ

የዚህን ሳምንት ትምህርት ክልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

*1.* እነዚያ በኢየሩሳሌም ውስጥ በጳውሎስ ላይ ጥቃትን የጀመሩ አይሁዳውያን ከየት የመጡ ነበሩ?

2. ጳውሎስ ብዙ ጊዜ በንግግሩ ውስጥ እንዴት እንደተለወጠ የሚናገረው ለምንድነው?

3. ጳውሎስ ፈሪሣዊ ነኝ ሕጉንም እጠብቃለሁ ሲል፥ ለአይሁዳውያኑ ሊገልጽላቸው የፈለገው ነገር ምንድነው?

4. ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ከመገረፍ ያዳነው ነገር ምንድነው?

5. በሸንጎው ፊት ሲቀርብ፥ የጳውሎስን ሕይወት ከፍርድ ያዳነው ነገር ምንድነው?

6. ሰዱቃውያንና ፈሪሣውያን በየትኛው ዋነኛ ሐሳብ ላይ ነው ያልተስማሙት?

7. የሊቀ ካህኑን ድርጊት በመቃወሙ ጳውሎስ ይቅርታ የጠየቀው ለምንድነው?

8. ጳውሎስን ከአይሁዶች ደባ ያዳነው ማነው?

9. ሀ) ሕዝቡ የጳውሎስን ንግግር ይሰማ ዘንድ ጸጥ ያሰኘው ነገር ምንድነው?
ለ) እንደገና ሕዝቡን እንዲጮኹ ያደረገው የትኛው ንግግሩ ነው?

10. ጳውሎስ ሻለቃውን በግሪክ ቋንቋ ከማናገሩ በፊት ማን ነበር የመሰላቸው?

ለሳምንታዊው ስብሰባ ለማዘጋጀት እነዚህን የመወያያ ጥያቄዎች ተመልከት።

1. የአምልኮ ጊዜ 3. ክለሳ

2. ጸሎት 4. ውይይት

ሀ) 1ቆሮ. 9፡ 19-23 አንብብ 1. በክርስቶስ ያላችሁን እምነት ሳትለውጡ ለሁሉም ሰው በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ እንዴት መሆን እንደምትችሉ ተወያዩ። 2. ይህን ነገር በሥራህ ወይም በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ተግባራዊ ልታደርገው የምትችለው እንዴት ነው? 3. በዚህ ነገር በመጠቀም እንዴት አድርገህ የወንጌል ምሥክርነትህን ልታሰፋ እንደምትችል አንዳንድ መንገዶችን ግለጽ።

ለ) 1. አንድ ፍርድ እንዴት የአንተንም ሆነ የሌሎችን እምነት ሊያጠነክር እንደቻለ የምታውቀው አጋጣሚ ካለ ግለጸው። 2. እግዚአብሔር ፈተናዎች በሕይወታችን እንዲያልፍ የሚያደርገው በምን በምን ምክንያቶች ነው (ያዕቆብ 1፡ 12-14 ተመልከት)። 3. እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስጥ ልዩ ጥበቃውን የገለጸልህ እንዴት ነው?

ሐ) 1. እግዚአብሔር ጳውሎስ በእሥራት ውስጥ እንዲያልፍ ያደረገው ለምን ይመስልሃል? 2. እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች መከራን እንዲቀበሉ የሚያደርገው ለምንድነው?

መ) ጳውሎስ አሁን በሚያልፍበት ሁኔታ ውስጥ በሐዋርያት ሥራ 9፡ 15-16 ላይ ተሰጥቶት የነበረውን ተልእኮ ይፈጽም የነበረው እንዴት ነው?

5. ጸሎት፡-

# ትምህርት 17

የሐዋርያት 23፡ 23-25፡ 12

## የመጀሪያ ቀንየሐዋርያት ሥራ 23፡ 23-35

ሉቃስ ይህን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከጻፈበት ዓላማ አንዱ፡- ወንጌሉ ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ እንዴት ወደ ጥንቱ ዓለም መዲና ወደ ሆነችው ወደ ሮም እንደደረሰ ለማሳየት ነው። ጳውሎስም ወደ ሮም ሄዶ ከክርስቲያኖች ጋር ከተገናኘ በኋላ ወደ እስፓኝ ሄዶ ስለ ክርስቶስ መመሥከር ይፈልግ ነበር። ሆኖም ወደ ሮም እስኪደርስ ድረስ ለረጅም ጊዜ በእሥር ቤት ውስጥ እንደሚሆን አልተገነዘበም ነበር። በዚህ ሳምንት የጳውሎስ ወደ ሮም የመሄድ ምኞት ከመፈጸሙ በፊት ያሳለፈውን የእሥራት ጊዜ እናያለን። በዚህ ጊዜ ውስጥም የእግዚአብሔር እጅ ጳውሎስን ያጽናናው፥ ይጠብቀውና ከከፍተኛ ባለሥልጣኖች ፊት ስለ ጌታ እንዲመሠክር ድፍረትን ይሰጠው ነበር። እግዚአብሔር ዓላማውን ለማስፈጸም ሲል በማያምኑ መሪዎች በኩል እንኳ ይሠራል። «ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና» (ሮሜ 13፡ 1)። እግዚአብሔርም ጳውሎስ ሮም እስኪደርስ ድረስ በከፍተኛ ባለሥልጣኖች ደኅንነቱ እንዲጠበቅ አድርጓል።

ጥያቄ 1፡- የሐዋርያት ሥራ 23፡ 23-25፡ 15 አንብብ። ጳውሎስ የመሠከረላቸውን ባለሥልጣኖች ስም ዝርዝር ጻፍና ምላሻቸው እንዴት እንደነበር ግለጽ።

የሐዋርያት ሥራ 23፡ 23-35 አንብበህ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 2፡- ሀ) 1. ሻለቃው በጳውሎስ ላይ ስለተጠነሰሰው ደባ ሲሰማ ለመቶ አለቆቹ የሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው? 2. ምን ያህል ሠራዊት ነበር አብሮት የተላከው? 3. ሻለቃው ደብዳቤ የጻፈው ለማን ነው?

ለ) 1. በዚህ ደብዳቤ ላይ በጳውሎስ ላይ ካደረገው ነገር ውስጥ የትኛውን ነው ሻለቃው ያልጠቀሰው? 2. ጳውሎስ በቂሣርያ ሲደርስ ምንድነው የተደረገው? ሐ) እግዚአብሔር በማያምኑ ሰዎች በኩል ጳውሎስን ከጠላቶቹ እጅ የጠበቀው እንዴት ነው?

ሸንጎው ጳውሎስን የሚከስበት ጉዳይ ላይ ስምምነት ላይ ባለመድረሱ ምክንያት የተማለሉ አይሁዳውያን ጳውሎስን ለመግደል ቃል መሐላ ያደርጋሉ። በዚህም ጉዳይ ላይ ሸንጎው ከእነዚህ ሰዎች ጋር ይስማማል። ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ የጳውሎስ የእህቱ ልጅ ይህን የሸረቡትን ደባ ይሰማና ለሻለቃው ይነግረዋል። ሻለቃው ይህንን ሲሰማ በይሁዳ ከተማ ዋናው የሮም መንግሥት ባለስልጣን ወደሚገኝበት ወደ ቂሣርያ ወታደሮቹ ጳውሎስን ይዘውት እንዲሄዱ ትዕዛዝ ይሰጣል። ይህቺ የቂሣርያ ከተማም

ከሜዲትራኒያን ባሕር ጋር የምትዋሰንና ከኢየሩሳሌም በ1[illegible] ቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት። በዚያም ሌሊት ወደዚች ከተማ ጳውሎስን የ[illegible] መቶ ወታደሮች ሰባ ፈረሰኞችና ሁለት መቶ ባለጦር መሣሪያ አንጋቾች ነበሩ። ጳውሎስ የሚሄድበትን ከብት ካዘጋጁለትም በኋላ ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት ላይ ጉዞአቸውን ይጀምራሉ።

ይህ ሠራዊት ከኢየሩሳሌሙ ሻለቃ የይሁዳና የሰማርያ ገዢ ለነበረው ለፊልክስ የተላከ ደብዳቤ ይዞ ነበር የሄደው። ሻለቃውም በደብዳቤው ጳውሎስን ወደ እርሱ ለምን ለፍርድ እንደሚልከው ገልጿል። ከዚህም በላይ አይሁዳውያኑ ጳውሎስን በቤተመቅደስ እንዴት እንደያዙትና የእሱ ወታደሮች ከሕዝቡ እጅ እንዴት እንደዳኑ ይገልጻል። በመቀጠልም ሻለቃው የሚከሰስበትን ምክንያት አውቅ ዘንድ አስቤ ወደ ሸንጎው ባወርደው ለሞት የሚያደርስ ጥፋት አላገኘሁበትም ይላል። በመጨረሻም ጳውሎስ የሮም ተወላጅ መሆኑን ሲያውቅ ለፍርድ ወደ ፊልክስ ይልከዋል (እዚህ ላይ ግን ሻለቃው ጳውሎስ ሮማዊ መሆኑን እንዴት እንዳወቀ አይገለጽም)። ከፈለጉም ከሳሾቹ ወደ ቂሣርያ ወርደው ክሳቸውን በፊልክስ ፊት ማቅረብ እንደሚችሉ ገልጾላቸዋል።

በዚያን ሌሊት ወታደሮቹ ጳውሎስን ከኢየሩሳሌም በ50 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እስከምትገኘው እስከ አንቲጳጥሪስ ድረስ ይሸኙታል። ሲነጋም ፈረሰኞቹ እርሱን እንዲወስዱና ለፌሊክስ እንዲሰጡ ካደረጉ በኋላ እነርሱ ወደ ሠፈር ይመለሳሉ። አገረ ገዢውም ጳውሎስን የየት አገር ሰው እንደሆነ ይጠይቀዋል። ጳውሎስም የኪልቅያ ሰው መሆኑን ሲናገር ከሳሾች እስኪመጡ ድረስ በሄሮድስ ግቢ እንዲቀመጥ ይደረጋል።

መሪዎችን ከፍና ዝቅ የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው! በዚህም መሠረት መሪዎች ጳውሎስን እንዲጠብቁት ያደርጋል። እስቲ እንዴት አድርጎ ጳውሎስን ይጠብቁት ዘንድ በእህቱ ልጅ በሻለቃው በ470 ወታደሮችና የይሁዳ አገረ ገዥ በሆነው በፊልክስ እንደተጠቀመ አስተውል። ጥያቄ 3 ሀ) በማትጠብቀው ሰው አንተም ሆነ ሌሎች ሰዎች ጥበቃ ሲደረግላቸው ያየኸው እንዴት ነው? ለ) ከጥበቃው በስተኋላ የሚሆነው ማነው?

ጳውሎስ ወደ ሮም ያደረገው ጎታታ ጉዞ የተጀመረው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር በቂሣርያ ለጳውሎስ የተለየ ዓላማ ነበረው። እግዚአብሔር ለጳውሎስ ተልእኮውን ሲሰጠው፥ «ይህ ሰው በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው» ብሎት ነበር (ሐዋ. 9፡ 15)። ይህም የእሥር ቤት ኑሮ፥ ለሮማውያን አዛዦች፥ ለባለሥልጣናትና ለብዙ ወታደሮች እንዲመሠክር ለጳውሎስ አመቺ ሁኔታን ፈጥሮለታል።

ጥያቄ 4:- ሀ) የባለሥልጣኖች ወንጌልን መስማትና ለደህንነት መብቃት አስፈላጊ የነበረው ለምንድነው? ለ) እግዚአብሔር ወንጌሉን ለማስፋፋት በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት ክርስቲያን ባለሥልጣኖች የተጠቀመው እንዴት ነው?

አገረ ገዢዎችና ባለሥልጣናት በአንድ አገር ውስጥ በሚሆኑ ነገሮች ቀጥተኛ የሆነ ተሳትፎ ቢኖራቸውም፥ ውሳኔዎቻቸውንና እቅዶቻቸውን እግዚአብሔር እንደሚቆጣጠረው አይገነዘቡም። ጳውሎስ ደግሞ መሪዎች ካሙኑ ለወንጌሉ መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተገንዝቧል።

ጥያቄ 5:- ሀ) ለባለሥልጣናት መጸለዩ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? ለ) ልክ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ለእነርሱ ሥልጣን መገዛቱ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው?

ሁለተኛ ቀንየሐዋርያት ሥራ 24: 1-21

ጳውሎስ ወደ ሮም ሄዶ ከማገልገሉ በፊት ሁለት ዓመት በቂሣርያ እሥር ቤት ውስጥ አሳልፎ ነበር። በዚህም መሠረት መጀመሪያ ከሳሾቹ እስኪመጡ ድረስ በሄሮድስ ግቢ ነበር የታሠረው። የሮም ባለሥልጣናትም ምንም ወንጀል ባይኖረውም፥ በሕግ ክርክር ምክንያት ብቻ ለአይሁዳውያን አሳልፈው ሊሰጡት አልፈለጉም፤ ይህም የሆነው ዜግነቱ ሮማዊ በመሆኑ ነበር።

ጳውሎስ በቂሣርያ ለአምስት ቀን ያህል ከቆየ በኋላ ከሳሾቹ የሆኑት የአይሁድ መንፈሳዊ መሪዎች ከኢየሩሳሌም ተነሥተው ወደዚያ ይመጣሉ። ከመጡት ሰዎች መካከልም ሊቀ ካህኑ ሐናንያና የታወቀው ጠበቃ ጠርጠሉስ ይገኙበታል። ለአንድ ሊቀ ካህን ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ይህን ያህል መንገድ መሄድ የተለመደ ባይሆንም ይህን ማድረጉ እነዚህ መንፈሳዊ መሪዎች ምን ያህል ለጳውሎስ ጥላቻ እንደነበራቸው ያሳየናል። በዚያም እንደደረሱ በሚያባብል ቃል ጳውሎስ ላይ ክሳቸውን በማቅረብ በፊልክስ ፊት ሞገስ ለማግኘት ይሞክራሉ። ሆኖም ይህ ክሳቸው ፊልክስንም ሆነ የሮምን መንግሥት የሚመለከት አልነበረም።

የሐዋርያት ሥራ 24: 1-27 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 6:- ሀ) 1. ጠርጠሉስ ማነው? 2. በፊልክስ ፊት ሞገስ ለማግኘት ሲል ጠርጠሉስ የተጠቀመው ምን ዓይነት ቃላትን ነው?

ለ) በጳውሎስ ላይ የቀረቡት ሦስት ክሶች ምን ነበሩ?

ሐ) ጳውሎስ በመከላከያው ለእነዚህ ሦስት ክሶች መልስ የሰጠው እንዴት ነው?

መ) 1. ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ለምንድነው?
2. በመጀመሪያ ላይ ጳውሎስን የከሰሱት አይሁዳውያን የትኞቹ ናቸው?

ሠ) በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሕሊና እንዲኖረው ጳውሎስ ይተጋ የነበረው ለምንድነው?

ረ) አይሁዳውያን ለክርስትና እምነት የሰጡት ስም ምን ነበር?

ሰ) ጳውሎስና ከሳሾቹ የተስማሙባቸው ነጥቦች ምንድናቸው?

ጳውሎስ ወደ ቂሳርያ ከሄደ በኋላ ነገሩ ውሉ ሳያድር ከሳሾቹ ከበሬቱ በይበልጥ ተዘጋጅተው ሊከሱት ወደዚያ ይወርዳሉ። ሊቀ ካህኑ ሐናንያና አንዳንድ የሸንጎው ተወካዮች የታወቀውን አይሁዳዊ ጠበቃ ጠርጠሉስን ይዘው ይመጣሉ። ጠርጠሉስም በሮም ሥርዓተ ሕግ የሰለጠነና በሮም ባለሥልጣኖች ክሱን በደንብ አቅርቦ ድል ለማድረግ የሚችል የግሪክ አይሁድ ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስ ተጠርቶ ሲገባም በፊልክስ ፊት ሞገስን ለማግኘት ሲል ጠርጠሉስ ክሱን በሚያባብሉ ቃላት ይከፍታል። ፊልክስ ሰላምን ስላስገኘና አንዳንድ ሁኔታዎችን ስላሻሻለ ያመሰግነዋል። ሆኖም ይህ ነገር እውነት አልነበረም። የፊልክስ አስተዳደር በአይሁዶችና በሮማውያን መካከል ያለው ግንኙነት የባሰ ውጥረት የተሞላ እንዲሆን ያደረገ እንጂ ግንኙነታቸውን በምንም ዓይነት መንገድ ያሻሻለ አልነበረም። ሆኖም፥ ጠርጠሉስ ጳውሎስን ማቅረብ የፈለገው የአገሪቱን ሰላም እንደሚያውክ እንደ አንድ አሸባሪ ሰው አድርጎ ነበር እንጂ፥ በሃይማኖት ላይ በተመሠረት ጉዳይ ላይ አልነበረም።

ጠርጠሉስ ከዚህ በመቀጠል በጳውሎስ ላይ የተለያዩ ክሶችን ይመሠርታል። የመጀመሪያው ክስ ይህ ሰው ችግር ፈጣሪ በሮሚ ግዛቱ ሁሉ ሁከት የሚያነሣሣ ሰው ነው የሚል ነበር። ይህንንም ያለው፥ ፊልክስ ጳውሎስን እንደ ለውጥ ፈላጊ ፖለቲከኛና መንግሥት ገልባጭ አድርጎ እንዲያየው ስለፈለገ ነው።

ሁለተኛው ክስ ደግሞ ጳውሎስ ናዝራውያን ወገን መሪ ነው የሚል ነበር! ይህም የናዝሬቱ ኢየሱስ ተከታዮች ማለት ነው። አይሁዳውያን ወደ ኢየሱስ የነበራቸውን አመለካከትም የዮሐንስ ወንጌል 1፡ 46 «ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን?» በሚል ዓይነት ዐረፍተ ነገር ይገልጸዋል። በሮማውያን ዘንድም ሕጋዊነት የነበረው የአይሁድ ሃይማኖት ስለነበር፥ ክርስትና ሕገ ወጥ መሆኑን ለማመልከት ይፈልጉ ነበር።

ሦስተኛ ክስ መቅደስን ሊያረክስ ሲሞክር ያዝነው የሚል ነው (ጳውሎስ የግሪክ ሰዎችን ወደ ቤተመቅደስ ይዞ ገብቷል ተብሎ ነበር የተከሰሰው። ሐዋ. 21፡ 29)። ጠርጠሉስ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም የተነዛው በዚህ ምክንያት ነው! ነው የሚለው። በመጨረሻም አይሁዳውያኑ ይህ ክስ ትክክለኛ ነው ብለው ይስማማሉ።

**ጥያቄ 7፡- የማያምኑ ሰዎች በክርስቲያኖች ላይ የሚሰነዝሯቸው አንዳንድ ተገቢ ያልሆኑ ክሶች ምን ምንድናቸው?**

ፊልክስም በጳውሎስ ላይ የቀረበውን ክስ ካዳመጠ በኋላ ጳውሎስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ይጠይቀዋል።

ጳውሎስ የአይሁድ ሥርዓትንና የአሕዛቡን ዓለም ትምህርት በደንብ ያውቅ ስለነበር፥ ስነዚህ በእሱ ላይ የተመሠረቱት ክሶች በጣም ከባድ እንደሆኑ ተገንዝቧል። በዚህም መሠረት፥ በመዋሸታቸው ምክንያት የአይሁድን መሪዎች ከመውቀስ ፈንታ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም የተፈጸመውን እውነቱን በመናገር እውነቱ እራሱ የእኔን ንጽሐና ያሳይ ብሎ እራሱን አሳልፎ ለእግዚአብሔር ይሰጣል።

ጥያቄ 8:- ሀ) አንድ ክርስቲያን በሐሰት ሲከሰስ እግዚአብሔርን እንዲያስከብር አድርጎ መልስ መስጠት ያለበት እንዴት ነው? ለ) ክርስቲያኖች መጠቀም የሌለባቸው የአመላለስ ዘይቤዎች ምን ምንድናቸው?

የጳውሎስ መልስ በጣም ቀልጥ ያለች ነበረች። በመጀመሪያ ከመጣ ገና አሥራ ሁለት ቀኑ ስለነበር፥ ይህን ያህል ሁከት በዚህ ጊዜ ውስጥ በኢየሩሳሌም ሊፈጠር እንደማይችል ይናገራል።

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ከብዙ ዓመታት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው ለሕዝቡ ምጽዋትና መሥዋዕት ለማቅረብ እንደሆነ ይናገራል። ጳውሎስ ለብዙ ዓመታት ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ አያውቅም። ወደ ኢየሩሳሌም የመጣው፥ የተቸገሩ ሰዎችን የሚረዳበትን ገንዘብ ይዞ ነው። በሥርዓታቸውም መሠረት ንጹሕ ስለነበር፥ ቤተክርስቲያንን አላረከሰም። ከዚህም በላይ ከሳሾቹ ከአንድ ሰው ሲጣላ ወይም ሕዝቡን በምኩራብም ይሁን በቤተመቅደስ ሲሰበስብ አላገኙትም። ስለዚህም አሁንም ስለሚከሡኝ ያስረዱህ ዘንድ አይችሉም» ይለዋል (ሐዋ. 24፡ 13)። ሦስተኛ፥ ጳውሎስ በእኔ ላይ ነገር ካላቸው በፊትህ መጥተው ሊከሱኝ የሚገባው ከእስያ የመጡት አይሁዳውያን ናቸው ይላል። ይህንንም ያለው፥ በመጀመሪያ ሁከት የፈጠሩት እነሱ በመሆናቸው ነው።

በመጨረሻም፥ ጳውሎስ እሱን ለመክሰስ ወደ አነሣሣቸው እውነተኛ ምክንያት ዞር ይላል። የአይሁድ መሪዎች የጠሉት «የመንገዱ» ተከታይ በመሆኑ ብቻ ነው። በይሁዳ ምድር ክርስትና «መንገዱ» በመባል ነበር የሚታወቀው። ጳውሎስም በሕጉ ያለውን በነቢያትም የተጻፉትን ሁሉ አምኜ «የአባቶቼን አምላክ እነርሱ ኑፋቄ ብለው እንደሚጠሩት መንገድ አመልካለሁ» ብሎ ይናገራል። ጳውሎስ እሱ የሚከተለው እምነት ከሥር መሠረቱ ከእነርሱ ጋር አንድ ዓይነት እንደሆነና እነርሱንም እንደማይቃወም ይናገራል። እንግዲህ አንዳች ነቀፌታ በጳውሎስ ላይ ቢኖራቸው፥ ከመንፈሳዊ ነገር ጋር የተያያዘ መሆን እንዳለበት ነው የሚያስገነዝባቸው። በሸንጎው ውስጥ እንዳሉት እንደ ብዙዎቹ ካህናትም ጻድቃንና ዓመጸኞች ከሙታን ይነሣሉ ብሎ ያምናል። ጳውሎስ በትንሣኤ ስለሚያምን «በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለበት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ» ይላል። በአጭሩም ጳውሎስ ካቀረቡብኝ ክስ ነፃ ነኝ፥ በእግዚአብሔርም ፊት ንጹሕ ነኝ ነው የሚለው። ከዚህም በላይ ነገር አለን ብለው ክስ መመሥረት የሚችሉት ሌሎች እንደሆኑና ይህ የክስ አቀራረብ ትክክል እንዳልሆነ ይጠቅሳል።

እሱም ከሳሾቹም የሚስማሙባቸው የተወሰኑ ነገሮች አሉ። እነዚህም፥ ጳውሎስ እስራኤልን እንደሚወድ የአባቶቻቸውንም አምላክ እንደሚያመልክና በነቢያትና በሕግጋት እንደሚያምን ናቸው። ስለዚህም ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች ከጠቀሰ በኋላ፥ እንደ ተከሰሰበት ጉዳይ አድርጎ የሚያቀርበው በሙታን ትንሣኤ የማመኑን ጉዳይ ነው። ይህ የአመለካከት አለመጣጣም ደግሞ የሮምን ፍርድ ቤት የሚያገባው ነገር አይደለም። ስለዚህም፥ ፊልክስ በኢየሩሳሌም የሚገኘው ሻለቃ ሉስዮስ እስኪመጣ ድረስ

ለነገራችሁ እልባት አልሰጥም ብሎ ይበትናቸዋል። ጳውሎስንም ደግሞ በጥበቃ ሥር እንዲቆይና ወዳጆቹ ከመጡ ወደ እርሱ እንዲገቡና እንዲያገለግሉት ፍቃድ ይሰጣል።

ጥያቄ 9:- ሀ) ክርስቲያኖች በሐሰት ሲከሰሱ፥ የጳውሎስን መልስ እንደምሳሌ ቢጠቀሙበት ጥሩ የሚሆንላቸው እንዴት ነው? ለ) ዛሬ ለራሳችን መከላከያ ለማቅረብ ስንል ልንከተላቸው የሚገቡን መርሆዎች ምን ምንድናቸው?

## ሦስተኛ ቀን:- የሐዋርያት ሥራ 24: 22-27

ከሊቀ ካህናቱ ጋር የመጣው ጠበቃ በጳውሎስ ላይ ያቀረበው ክስ፥ የፊልክስ ዓይን ጳውሎስን ወንጀለኛ ሊያሰኘው አልቻለም። የይሁዳ አገረ ገዥ የነበረውም ፊልክስ፥ ለጳውሎስ ጉዳይ ፍርድ ሰጥቶ ጳውሎስን በነፃ መልቀቅ ይችል ነበር። ሆኖም ጳውሎስን በቂሣሪያ የሚያቆይበት ሌላ የራሱ ምክንያት ስለነበረው ይህን አያደርግም።

የሐዋርያት ሥራ 24-27 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 10:- ሀ) ምንም እንኳ ጳውሎስ በጥበቃ ላይ ቢሆንም፥ ፊልክስ ምን ዓይነት ነፃነት ነበር የሰጠው?

ለ) 1. ከፊልክስ ጋር በመሆን ጳውሎስን ያስጠራችው ማናት?
2. ስለማን ነበር የሚነጋገሩት?

ሐ) 1. ጳውሎስ ያስተማራቸው ሦስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
2. ፊልክስ ለጳውሎስ ትምህርት ምን ዓይነት ምላሽ ነው የሰጠው?
3. ፊልክስ ጳውሎስን እስልኪ እጠራሃለሁ ያለው መቼ ነው?

መ) 1. ለምንድነው ፊልክስ ጳውሎስን በእሥር ቤት ያቆየው?
2. ጳውሎስ በቂሣሪያ በእሥር ላይ ለምን ያህል ጊዜ ነው የቆየው?
3. ከፊልክስ በኋላ የይሁዳ አገረ ገዥ የሆነው ማነው?

ታሪክ ስለ ፊልክስ የሚናገረን ብዙ ነገሮች አሉት። ፊልክስ የይሁዳ ገዢ የነበረው ከ 52-59 ዓ.ም ድረስ ነበር። በመጀመሪያም ፊልክስ ባሪያ ነበር። ከዚያም ከዕለታት አንድ ቀን ባሪያ የነበረው ወንድሙ ፓለስ በዚያን ጊዜ የሮም ገዢ በነበረው በንጉሥ ገላውዴዎስ ፊት ሞገስ ያገኛል። በዚህም በመጠቀም ወንድሙን ፊልክስን የይሁዳ አገረ ገዥነትን ሥልጣን ያሰጠዋል። አገረ ገዢ ከሆነ በኋላም የአይሁዳውያን ተቃውሞዎችን በሚያቆምበት ወቅት ጨካኝ መሆኑን አሳይቷል! በዚህም ምክንያት አይሁዳውያን በእርሱ ላይ ተነሡ። ኃይል እንዲኖረውም በጣም ይመኝ ስለነበር፥ ይህንን ለማግኘት ሲል ሦስት ጋብቻዎችን ፈጽሟል። በመጨረሻም ጳውሎስ ለፍርድ ባቀረቡት ጊዜ፥ ያዕቆብን የገደለውን የሄሮድስን ልጅ ድሩሲላን ነበር ያገባው። ይህም ምኞቱ ከብዙ ሰዎች ጋር ጠላት እንዲሆን አድርጎታል።

በዚህ በሐዋርያት ሥራ ላይ በተጠቀሰው ዘገባም መሠረት ፊልክስ እንዲሁ በቀላል ልምምጥ ሊለወጥ አልቻለም። ምናልባትም ከዚህ በፊት ዛሬ ክርስትና ተብሎ

የሚጠራውን ሃይማኖት ይከተሉ ከነበሩ ሰዎች ጋር ሳይጋጭ አይቀርም ይሆናል። ወይም ደግሞ ከአይሁዳውያኑ ይበልጥ ስለ ክርስትና ተገንዝቦ ይሆናል። የጳውሎስንም ድፍረት ሲያይ ግን ስለ እምነቱ ብዙ ለመስማት ጉጉት አደረበት። ከዚህም ሌላ ጳውሎስ ጉቦ ይሰጠኛል ብሎ ተስፋ አድርጎ ነበር። ይህም የሆነው እሱ ያስብ የነበረው ትክክለኛ ፍርድን ሳይሆን ኃይልንና ምድራዊ ሃብት ስለነበር ነው። ጳውሎስን ወዲያውኑ መፍታት ይችል ነበር፤ ነገር ግን ሆነ ብሎ ለሁለት ዓመት ሙሉ በእሥር ቤት እንዲቆይ አደረገ።

ጥያቄ 11፡- ሀ) አንድ እንደ ጳውሎስ ንጹሕ የነበረ ሰው በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ላይ ምን ዓይነት አቋም ነበር የሚወስደው? ለ) ጳውሎስ ጉቦውን ከፍሎ በሮም አገልግሎቱን ያልቀጠለው ለምን ይመስልሃል?

ፊልክስና ድሩሲላ የተባለችው አይሁዳዊት ሚስቱ ስለ ወንጌል ብዙ መስማት ይፈልጉ ነበር። ለዚህም ያነሣሣቸው በነገሩ ተማርከውበት ሳይሆን እንዲያው ወንጌሉ ምን እንደሚል ለመስማት ያህል ነበር። ለጳውሎስ ግን በሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች ወንጌሉን የሚያካፍልበት አንድ ጥሩ አጋጣሚ ከፍቶለት ነበር።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ክርስቲያን በሆኑ ባለሥልጣኖች በመጠቀም አዳዲስ የአገልግሎት በሮች እንዲከፈቱና ወንጌሉ በተሻለ ሁኔታ እንዲስፋፋ ያደርጋል። ጳውሎስም ይህን ያውቅ ስለነበር፥ ለባለሥልጣኖች በድፍረት ግልጽ አድርጎ ይመሠክርላቸው ነበር። ምንም እንኳ ጳውሎስ ወንጌሉን ለመሪዎቹ እንደሚስማማ አድርጎ ማቅረብ ቢችልም፥ ለእነሱ ግን ምንም ዓይነት ማስፈራራት እንዲደርስበት አይፈልግም ነበር። እርሱ በፈቀደውም መሠረት በተቻለውም መጠን ግልጽ አድርጎ ወንጌሉን ለፊልክስና ለሚስቱ አካፈላቸው።

ሉቃስ ጳውሎስ የተናገረው ስለ ጽድቅ፥ ራስን ስለ መግዛትና ስለሚመጣው ፍርድ እንደነበረ ይናገራል።

ጥያቄ 12፡- ሀ) ፊልክስ ስለ ጽድቅ ራስን ስለመግዛትና ስለ ፍርድ መስማት ያልፈለገው ለምን ይመስልሃል? ለ) ዛሬ ብዙ ሰዎች ክርስቲያኖችንም ጨምሮ ስለ እነዚህ ነገሮች መስማት የማይፈልጉት ለምንድነው?

ጳውሎስ ስለ ጽድቅ ተናገሯል፡- ይህም ጽድቅ የሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንና እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲያደርጉት የሚጠይቀውን ነገሮች በማድረግ ነው። በተለይ መሪዎች ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግንኙነት ይኖራቸው ዘንድ ይህን ማድረግ አለባቸው። እንደ ፊልክስ ሌላ ጨካኝ መሪ ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን ግንኙነት ለመቀበል በጣም ያዳግተዋል።

ጳውሎስ ስለ ራስ መግዛት ተናገሯል፡- ይህም የራስን ንዴትና ምኞት መቆጣጠርን የሚያካትት ነው። በሮማው ዘመነ መንግሥት የነበሩት መሪዎች በማንኛውም ዓይነት በተለይ በዝሙት እራሳቸውን በማስደሰት የታወቁ ነበሩ። በዚህም ምክንያት በሌሎች ሰዎች ላይ እንኳ ጉዳት ቢያደርሱም እራሳቸውን መቆጣጠር እስኪሳናቸው ድረስ ምኞታቸው እንዲገዛቸው ያደርጉ ነበር። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ጋር

ሙሉ በሙሉ የሚቃረን ነው። በዚህም መሠረት ፊልክስም ሆነ ሌሎቻችንም እንደበታችንን፥ ስሜቶቻችንን፥ ወዘተ. ገትተን እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን ነገር መፈጸም ይኖርብናል።

ጥያቄ 13፡- በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ራስን የመግዛት ነገር ጉልህ ሆኖ የሚታየው እንዴት ነው?

ጳውሎስ ስለሚመጣውም ኩነኔ ተናገሯል፡- በዓለም ላይ ያሉ መሪዎች እንደዚህ ጨካኝና ክፉ የሚሆኑበት አንዱ ምክንያት፥ ወደፊት የፍርድ ጊዜ ይመጣል ብለው ስለማያምኑ ነው። የሙታን ትንሣኤና ስለ ኃጢአት መጠየቅ ከሌሉ፥ አንድ ሰው ሌላ ደግ ሥራ የሚሠራበት ምንም ምክንያት የለውም። ጳውሎስ ግን ከመሪዎች እንሥቶ እስከ ተራው ሕዝብ ድረስ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ መቅረባችን ግድ እንደሆነ ይናገራል። ይህ ፍርድ የተመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ላይ ነው። በዚህም መሠረት አንድ ሰው በኢየሱስ ካመነ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል፤ ካላመነ ደግሞ ወደ ገሃነመ እሳት ይገባል። ሆኖም፥ ይህ ፍርድ በምድራዊ ሕይወታችን የሠራናቸውንም ሥራዎች ያካትታል። በዚህም መሠረት አንድ ሰው እግዚአብሔርን አስከብሮ ከኖረ፥ ዋጋውን ይቀበላል። እንደ መሪዎች ደግሞ ብዙ ሥልጣን ኖሮት፥ በሥልጣኑ የሚባልግና ክፉ የሆነ፥ ከእግዚአብሔር ቅጣቱን ይቀበላል። ወንጌሉን እንዲህ ግልጽ አድርጎ አቅርቦ አንድ ሰው ለራሱ ያለውን ኃላፊነት ሲያሳየው ፊልክስ ይፈራል። ጳውሎስንም «አሁንስ ሂድ በተመቸኝ ጊዜ ልኪ አስጠራሃለሁ» ብሎ ይመልሰዋል።

ጳውሎስም በቂሣሪያ ለሁለት ዓመት ይቆያል። ፊልክስ ወይ አልለቀቀው ወይ ለአይሁዳውያን አልፈረደ፥ ዝም ብሎ ውሳኔውን አዘግይቶ ያስቀምጠዋል። ብዙ ጊዜም ጳውሎስን እያስጠራ ያነጋገረው ነበር።

በ 62 ዓ.ም ጶርቅዮስ ፊስጦስ በፊልክስ ፈንታ ይተካል። በዚህም ጊዜ ጳውሎስ በቂሣሪያ ወኅኒ ቤት ታሥሮ ነበር። ፊልክስም ጳውሎስ ምንም ወንጀል እንዳልፈጸመ ያውቃል፤ ሆኖም አይሁዳውያንን ላለማስከፋት ሲል ሊፈታው አልፈለገም።

ጥያቄ 14፡- ሀ) በሥልጣን ያሉ ሰዎች እውነቱን መቀበሉ እንዲህ የሚያዳግታቸው ለምንድነው? ለ) ብዙ የቤተክርስቲያን መሪዎች ስሕተታቸው ሲነገራቸው ምን ዓይነት ምላሽ ነው የሚሰጡት?

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 25፡ 1-12

ጶርቅዮስ ፊስጦስ በፊልክስ ፈንታ ይተካል። አይሁዳውያን ቅር እንዳይሰኙ ብሎ ፊልክስ ለሁለት ዓመት ያክል ጳውሎስን በእሥር ቤት ያቆየዋል።

ጳውሎስ አዲስ ገዢ ሲመጣ ንጹሕ ተብሎ እንደሚለቀቅ ተስፋ አድርጎ ሳይሆን አይቀርም። ሆኖም የአዲሱ ገዢ መምጣት ለጳውሎስ ያስገኘለት ምንም ጥቅም የለውም። ሁለት ዓመት ቢያልፍም፥ አይሁዳውያን ጳውሎስን ለመግደል የነበራቸውን

ቁርጠኛ ውሳኔ አልረሱም ነበር። በዚህም ጊዜ ጳውሎስ ወደ ሮም የመሄድ አንዲት አማራጭ ነበረችው፤ ይህችን አማራጭ ይጠቀምባታል።

የሐዋርያት ሥራ 25፡ 1-22 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 15፡- ሀ) 1. ፊስጦስ በኢየሩሳሌም እንደገባ የማን ግመልከቻ ነበር የቀረበለት?

2. ግመልከቻውን ያስገቡት እነማን ናቸው?

3. ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ የፈለጉት ለምንድነው?

4. ፊስጦስ ለጥያቄአቸው ምን ዓይነት ምላሽ ነው የሰጣቸው?

ለ) 1. ፊስጦስ ጳውሎስን ኢየሩሳሌም ሄዶ ሊፋረዳቸው ይፈልግ እንደሆነ የጠየቀው ለምንድነው?

2. የጳውሎስ መልስ ምን ነበር?

ሐ) የጳውሎስ ይግባኝ ወደ ሮም መሄዱን እርግጠኛ እንዲሆንለት ያደረገው እንዴት ነው?

አዲሱ የይሁዳ አገረ ገዥ ፊስጦስ ለሦስት ቀን ያህል በቂሣሪያ ከቆየ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዳል። እንደ አገረ ገዥነቱም የየአካባቢው መሪዎች ከነበሩት አይሁዳውያን ጋር መገናኘት ነበረበት። እነዚህም መሪዎች በካህናት ሸንጎ ውስጥ ያሉት ሰዎች ናቸው።

እነዚህ የአይሁድ መሪዎች የጳውሎስን ጉዳይ አልረሱትም ነበር። በዚህም መሠረት ቶሎ በፊስጦስ ፊት የጳውሎስን ጉዳይ ያቀርቡና ለፍርድ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ ይጠይቃሉ። አዲስ አገረ ገዥ እንደመሆኑም፥ አይሁዳውያኖች ያለጥርጥር ማስደሰት ይፈልግ ነበር። ሆኖም ከዚህ ቀደም ሲል ስለጳውሎስ ሳይሰማ አይቀርም የሮም ዜግነት እስካለውም ድረስ በትክክለኛ ፍርድ መቀበል መብቱ ነበር። ስለዚህም ፊስጦስ ወደ ቂሣሪያ እንደሚሄድና በዚያም መጥተው ለፍርድ ሊያቀርቡት እንደሚችሉ ይነግራቸዋል። አሁንም እንደገና አይሁዳውያኑ በመንገድ ላይ ሸምቀው ጳውሎስን ለመግደል ሲያስቡ እግዚአብሔር በዚህ አገረ ገዥ ተጠቅሞ ያድነዋል።

ፊስጦስና የሊቀ ካህናቱ ሸንጎ አባላት በቂሣሪያ ሲደርሱ፥ ጳውሎስ ክሱን እንዲሰማ ወደ ፍርድ ቤቱ ይጠራል። ከዚያም በኋላ አይሁዳውያን ሊረቱበት የማይችሉትን ብዙና ከባድ ክስ ያነሡበታል። አሁንም ልክ እንደ ፊልክስ ጊዜ፥ ምንም ማረጋገጫ ስላልነበር፥ ጳውሎስ ነፃ መለቀቅ ነበረበት። ሆኖም ፊስጦስ በአይሁዳውያን ዘንድ ሞገስን የሚያገኝበትን አጋጣሚ ያገኛል፤ ስለዚህም ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተህ ስለዚህ ነገር እዚያው በፊቴ ትፋረድ ዘንድ ትወዳለህን ብሎ ይጠይቀዋል።

ጳውሎስም «የአይሁድን ሕግ ቢሆን መቅደስንም ቢሆን ቄሣርንም ቢሆን አንዳች አልበደልሁም» በማለት ይሟገታል። ፊስጦስም አይሁዳውያኑን ለማስደሰት ብሎ፥ ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ እንደገና እንዲፋረዳቸው ቢጠይቀው፥ እንቢ ይለዋል። ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ቢመለስ ሞት እንደሚጠብቀው በደንብ ያውቅ ነበር። ምንም እንኳ ሞትን ባይፈራም፥ ያለምንም አጥጋቢ ምክንያት ዝም ብሎ እራሱን ለሞት አሳልፎ መስጠቱን አልፈለገውም። በድሉ ቢሆን ኖሮ ለመሞት ዝግጁ ነበር።

ስለዚህም ጳውሎስ የሮም ዜግነት ላላቸው ሰዎች ወደ ቆመው ወደ መጨረሻው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ይላል። ፊስጦስንም «ወደ ቄሣር ይግባኝ ብዬአለሁ» ይለዋል።

ፊስጦስም ከአማካሪዎቹ ጋር በጉዳዩ ላይ ከተማከረ በኋላ፥ «ወደ ቄሣር ይግባኝ ብለሃል፤ ወደ ቄሣር ትሄዳለህ» ብሎ ይመልስለታል።

ጳውሎስ ሞትን በጭራሽ አይፈራም ነበር። ለፊሊጵስዩስ ሰዎችም በጻፈው መልእክቱ «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅሜ ነውና» ብሏል (ፊል. 1፡ 21)። ሆኖም እግዚአብሔር ወደ ሮም ሄዶ የእርሱ ምሥክር እንዲሆን ያቀደው በእንዲህን ዓይነት ሁኔታ ነበር።

ፊስጦስ ጳውሎስ ወደ ሮም ይግባኝ በማለቱ ደስ ሳይሰኝ አልቀረም። ምክንያቱም ካሁን ወዲህ ከአይሁዳውያኑ ጋር ስለ ጳውሎስ አይነጋገርምና ነው። ጳውሎስም ይህንን በማድረጉ ከሚከሱት አይሁዳውያን ጫንቃ ነፃ ሊወጣ ችሏል።

ጳውሎስ፥ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ይህን ዓይነቱን ውሳኔ ያደርጋል። ጌታም ቃል እንደገባለት ይህ ውሳኔው ወደ ሮም እንዲደርስ ያደርገዋል። ሆኖም፥ ጳውሎስ እግረ መንገዱን በሮም ሲደርስ ስለሚያጋጥመው መከራ ምንም ያወቀ አይመስልም።

ለቃሉ ታዛዦች ሆነን ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ኅብረት የሚኖረን ከሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ ውሳኔዎቻችንን ሊመራልን ይችላል። ጳውሎስ ምንም እንከን የሌለበት ሰው አልነበረም፤ ሆኖም ለመኖር ይፈልግ የነበረው ለክርስቶስ ብቻ በመሆኑ፥ መንፈስ ቅዱስ በውሳኔዎቹ ሊመራው ችሏል። ፊልክስና ፊስጦስ አይሁዳውያንን ለማስደሰት ከነበራቸው ፍላጎት የተነሣ፥ ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን አቅቷቸዋል። ይህን ዓይነትም ነገር በብዙ የፖለቲካ መሪዎችና በማያምኑ ሰዎች ዘንድ የተለመደ ነው።

ጥያቄ 16፡- የአንተ ውሳኔ ወይም የሌሎች ቤተክርስቲያን መሪዎች ውሳኔዎች እግዚአብሔርን ደስ ከማሰኘት ይልቅ ለሰው ተብለው የሚወሰኑት እንዴት ነው? እስቲ ምሳሌዎችን ስጥ።

ሉቃስ ስለ ጳውሎስ መታሠር ይህን ያህል ሰፋ አድርጎ የሚያትተው ለምንድነው? እንደምታስታውሰው ይህ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተጻፈው ቴዎፍሎስ ለተባለ ሰው ነበር። ሉቃስም ለዚህ ሰውዬና ለሌሎች አሕዛብ ጳውሎስ ለምን እንደታሰረ ማስረዳት ይፈልግ ነበር። ስለዚህም ጳውሎስ የታሠረው በፈጸመው ወንጀል ምክንያት ሳይሆን፥ አይሁዳውያን ስለቀኑበትና የሮም መሪዎች በፍርሃት ስለተዋጡ ነበር። ከዚህም ሌላ ሉቃስ ክርስትና እንዴት ከትንሿ ከተማ ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ በዚያን ዘመን ኃይል ወደነበረው መንግሥት መዲና ወደ ሮም እንደደረሰ ለማመልከት ፈልጓል።

# አምስተኛ ቀን:-　　　　ክለሳ

ያለፈውን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

1. ሀ) ቀላውዴዎስ ሉስዩስ፥ አይሁዳውያን በጳውሎስ ላይ የሸረቡትን ደባ ሊያውቅ የቻለው እንዴት ነው? ለ) ደባውስ ምን ነበር?

2. ሀ) ጳውሎስ ከአይሁዳውያኑ እጅ ሊድን የቻለው እንዴት ነው? ለ) ጳውሎስን የሸኙት እነማን ናቸው?

3. በጳውሎስ ላይ ክስ ለመመሥረት ከአይሁዳውያኑ ጋር የመጣው ማነው?

4. ሀ) ፊልክስ ለጳውሎስ ጉዳይ እልባት ያልሰጠው ለምንድነው? ለ) ጳውሎስን በቂሣሪያ የቆየው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

5. ሀ) ለፊልክስና ለድሩሲላ፥ ጳውሎስ ስለ እምነቱ ይነግራቸው በነበረበት ወቅት፥ ንግግሩ በፊልክስ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ነበረው? ለ) ለጳውሎስ ምን ብሎ ነው የተናገረው?

6. ሀ) በፊልክስ ፈንታ የይሁዳ አገረ ገዥ የነበረው ማነው? ለ) የካህናቱ ሸንጎ ለፊስጦስ ያመለከቱት የመጀመሪያው ምን ነበር?

7. አይሁዳውያኑ ጳውሎስ እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ለፍርድ እንዲቀርብ የፈለጉት ለምንድነው?

8. ሀ) የጳውሎስን ጉዳይ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይመለስ ያደረገው ነገር ምንድነው? ለ) ጳውሎስ ይህን ዓይነት ውሳኔ ያደረገው ለምንድነው?

እራስህን ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጁ ለማድረግ፥ የመወያያ ጥያቄዎቹን ተመልከት።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ　　　　3. ክለሳ

2. የጸሎት ጊዜ　　　　4. ውይይት:-

ሀ) 1. እግዚአብሔር፥ ጳውሎስ በባለሥልጣኖች ፊት እንዲመሠክርለት የፈለገው ለምንድነው? 2. ክርስቲያን የነበሩ ባለሥልጣኖች በኢትዮጵያ ውስጥ ወንጌሉን በማስፋፋት ረገድ የተጫወቱት ሚና ምንድነው? 3. ጳውሎስ ለባለሥልጣኖች ካቀረበው ምሥክርነት፥ ለባለሥልጣኖች እንዴት መመሥከር እንዳለብን ነው የምንማረው?

ለ) 1. አንድ ክርስቲያን በሐሰት ሲከሰስ እንዴት አድርጎ ነው መልስ መስጠት ያለበት? 2. አንድ ክርስቲያን ጉቦ መስጠት አለበት? ለምን?

ሐ) 1. እግዚአብሔር ጳውሎስን ይህን ያህል ጊዜ በእሥር ቤት እንዲያሣልፍ ያደረገው ለምንድነው? 2. ከዚህስ ልንማረው የምንችለው ነገር ምንድነው?

መ) ጳውሎስ ለፊሊክስ ንግግር ያደረገው ስለ ጽድቅ ራስን ስለመግዛትና ስለሚመጣው ፍርድ ነው።

1. ክርስቲያን ላልሆኑ ሰዎች በምንመሠክርበት ወቅት፣ ለሦስቱ ሐሳቦች ምን ያህል ትኩረት ነው የምንሰጠው?

2. እነዚህ ሦስት ነገሮች በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚገለጹት እንዴት ነው?

3. በአንዳንድ ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ እነዚህ በምን ዓይነት መንገድ ነው ጎልተው የማይታዩት?

5. ጸሎት

# ትምህርት 18

## የሐዋርያት ሥራ 25፡ 13-27፤ 26

## የመጀመሪያ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 25፡ 13-27

ጳውሎስ ለሁለት ዓመታት ያህል በቂሣሪያ እሥር ቤት ውስጥ ቆይቶ ነበር። ጉዳዩም በሁለት ሮማውያን ባለሥልጣኖች ከታየ በኋላ፥ ምንም ወንጀል ባይገኝበትም፥ ነፃ ሊለቁት አልፈለጉም ነበር። በመጨረሻም አገረ ገዥው ፊስጦስ ትክክለኛ ፍርድ ባለመስጠቱ ጳውሎስ ሮም ወደሚገኘው የቄሣር ፍርድ ቤት ይግባኝ ይላል።

እግዚአብሔር ለምን ለዚህን ያህል ጊዜ ጳውሎስ በእሥር ቤት ውስጥ እንዲቆይ እንዳደረገ ማወቁ በጣም ያዳግተናል። ሆኖም፥ ይህ ነገር የእግዚአብሔር ዕቅድ እንደነበር ነው። ምክንያቱም በምንም ዓይነት መንገድ የወንጌሉን መልእክት ሊሰሙ የማይችሉ ባለሥልጣኖች በዚህ አጋጣሚ ውስጥ ሰምተዋልና ነው። ጌታም ጳውሎስ ወደ ሮም ሄዶ ስለ እርሱ እንደሚመሠክርለት የተስፋ ቃል ሰጥቶት ስለነበር፥ ይህ ለጳውሎስ እስከመጨረሻው እንደ ጌታ ምሥክር ሆኖ እንዲቆም ድፍረትና መተማመኛ ይሰጠዋል። ጥያቄ 1 የሐዋርያት ሥራ 15፡ 13-27፡26 አንብብ። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተካሄዱትን አበይት ሁኔታዎች በዝርዝር ጻፍ።

የሐዋርያት ሥራ 25፡ 13-27 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 2፡- ሀ) 1. ለፊስጦስ ሰላምታ ለማቅረብ ወደ ቂሣሪያ የመጣው ማነው?

2. ፊስጦስ ከዚህ ሰው ጋር ስለምንድነው የተነጋገረው?

ለ) በአንድ ወንጀለኛ ላይ የሚሰጠውን ፍርድ በተመለከተ ፊስጦስ ለአይሁዳውያኑ የነገራቸው ነገር ምንድነው?

ሐ) ጳውሎስ በእሱና በአይሁዳውያኑ መካከል የነበረውን አለመግባባት እንዴት አድርጎ ነው የገለጸው?

መ) ፊስጦስ ከአግሪጳ ምን ዓይነት ዕርዳታ ነበር የፈለገው?

ጳውሎስ ወደ ሮም ይግባኙን ከጠየቀ ከጥቂት ቀናት በኋላ፥ ፊስጦስ አንድ ትልቅ እንግዳ ይቀበላል። አንድ አዲስ አገረ ገዥ ሲሾም፥ በአጎራባች አገሮች ያሉት ገዥዎች ከእርሱ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ለመፍጠር ሲሉ ሄደው ይጎበኙት ነበር። በዚህም መሠረት፥ በይሁዳ በስተሰሜን የሚገኘውን አገር ገሊላንና ፔሪያን ይገዛ የነበረው ዳግማዊ ሄሮድስ አግሪጳ ከእህቱ ከቤርኒቄ ጋር በመሆን ፊስጦስን ለመጎብኘት ይመጣል።

ሄሮድስ በአንድ ጎኑ አይሁዳዊ ስለነበርና የአይሁድ ባህልን በደንብ ያውቅ ስለነበር፥ ፊስጦስ ለአግሪጳ ስለ ጳውሎስ ይነግረዋል። በዚህም መሠረት፥ የኢየሩሳሌም ሽማግሌዎች እንዴት ሞት እንዲፈረድበት እንደጠየቁ ይነግረዋል። ፊስጦስም ተከሳሹ በከሳሾቹ ፊት ለፊት ሳይቆም፥ ለተከሰሰበትም መልስ ለመስጠት ዕድሉን ሳያገኝ ማንንም ቢሆን አሳልፎ መስጠት የሮማውያን ሥርዓት እንዳልሆነ ይነግራቸዋል። አይሁዳውያኑም ወደ ቂሣሪያ መጥተው በከሳቸው ላይ ስለ እርሱ ምንም ክፉ ነገር አላነሡም ብቻ ዝም ብለው ጳውሎስ ሕያው ነው ይለው ስለነበረው ስለአንድ ኢየሱስ ስለተባለ የሞተ ሰው ነበር የሚከራከሩት። ከዚህም በኋላ አይሁዳውያኑ ጳውሎስ ኢየሩሳሌም ድረስ መጥቶ ፍርድን እንዲቀበል ይጠይቃሉ፤ ጳውሎስም በነገሩ ሳይስማማ ይቀርና ወደ ቄሣር እንዲላክ ይጠይቃል፤ ፊስጦስም እሱን ለመላክ አመቺ ሁኔታን ይጠብቅ ነበር።

ንጉሥ አግሪጳ ጳውሎስ በቂሣሪያ እንዳለ ሲሰማ ከዚህ በፊት ስለዚህ ታላቅ ሰው ሰምቶ ስለነበር፥ ባገኘው ደስ ይለኛል ብሎ ይናገራል። ያለምንም ጥርጥር፥ የታወቀው የአይሁድ መሪ ስለነበረውና ዓለምን በወንጌል ሊያዳርስ ታጥቆ ስለተነሣው ስለ ጳውሎስ የአይሁድ ሕዝብ ሳይሰማ አይቀርም። በመጨረሻም ፊስጦስ ንጉሥ አግሪጳን ነገ ጳውሎስን ትሰማዋለህ ብሎ በነገሩ ይስማማል።

በሚቀጥለውም ቀን አግሪጳና በርኒቄ በብዙ ግርማ መጥተው ከሻለቆችና ከከተማው ታላላቆች ጋር ወደ ፍርድ ቤት ይገባሉ። ልክ ለንጉሡ ሄሮድስ ክብር እንደተዘጋጀ ትልቅ ድግሥ ነበር የሚመስለው። በተጠየቀውም መሠረት፥ ፊስጦስ ወደ ጳውሎስ ያስልካል። በመቀጠልም በኢየሩሳሌምና በእዚሁ በቂሣሪያ አይሁዳውያን እንዴት አድርገው ይህ ሰው እንዲሞት እንደጠየቁ ያስረዳል። ለሞት የሚገባውን ነገር አለማድረጉን ሲረዳም ጳውሎስ ወደ ቄሣር ይግባኝ ብሎ ስለነበር ወደዚያ እንዲሄድ ይፈቅድለታል። ይህንንም በመናገር ፊስጦስ የአይሁዳውያን ጠላት እንዳልሆነና ንጹሕ ሰው እንደሆነ ለማገለጽ የፈለገ ይመስላል። በመጨረሻም ከተመረመረ በኋላ የተሰበሰቡትን ሰዎችና በተለይ ንጉሥ አግሪጳን ወደ ሮም ሲልከው አንድ ነገር ጽፈው እንዲልኩት ይጠይቃል።

እንደ ታሪክ ጸሐፊው እንደ ዮሴፍ፥ ፊስጦስ በጣም ጥሩ አገረ ገዥ ነበር። በዚህ ነገር ላይም የአይሁድን ሃይማኖት ይከተል የነበረውን የንጉሥ አግሪጳን አስተያየት ይፈልግ ነበር። የአይሁድ ሃይማኖት በተመለከተ ደግሞ አግሪጳ አዋቂ እንደነበር ይነገርለት ስለነበር ፊስጦስ የእርሱን ዕርዳታ ይጠይቃል።

ጥያቄ 3፡- ይህ ጊዜ ጳውሎስ ወንጌሉን የሚናገርበት ጥሩ አጋጣሚ የሆነለት ለምንድነው?

# ሁለተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ26፡ 1-32

ሄሮድስ አግሪጳና ሌሎች ሹማምንቶች ከተሰበሰቡ በኋላ ጳውሎስስለ እራሱ እንዲናገር ዕድል ይከፈትለታል። በዚህም አጋጣሚ ፊስጦስ ጳውሎስን ወደ ሮም ሲልክ በእሱ ላይ ያለውን ክስ በደንብ ጥርት አድርጎ መጻፍ ይፈልግ ነበር።

ኢየሱስ በማቴ. 10፡ 17-19 ላይ እንደተነበየው፥ ሐዋርያው ጳውሎስ በሸንጎ፥ በገዢዎች፥ በምኩራቦችና ብሎም በነገሥታት ፊት ይቀርባል። ወደ ወኅኒ ቢጣልም፥ ጳውሎስ ለአይሁዳውያንና ለአሕዛብ ከሙታን ስለተነሣው ኢየሱስ መመስከሩን አላቆመም።

የሐዋርያት ሥራ 26፡ 1-32 አንብበሀ ለጥያቄዎቹ መልስ ስጥ።

ጥያቄ 4፡- ሀ) 1. ጳውሎስ የሱን ጉዳይ ወደ አግሪጳ በማቅረቡ ደስ የተሰኘው ለምንድነው? 2. ጳውሎስ ንግግሩን ከቀድሞው ሕይወቱና ከነበረው የሃይማኖት ልምምድ የጀመረው ለምንድነው?

ለ) 1. ጳውሎስ፥ በምን ምክንያት ነው ለክስ ቀረብኩ የሚለው? 2. ጳውሎስ ተስፋዬ ነው ብሎ የጠቀሰው ነገር ምንድነው?

ሐ) ጳውሎስ በሕይወቱ ስላደረጋቸው ስለ ሦስት ነገሮች ተናግሯል እስቲ እነዚህን ሦስት ነገሮች በዝርዝር ጻፍ።

መ) 1. በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ ለውጥ እንዲኖረው ያደረገው ነገር ምንድነው? 2. ጳውሎስ ከጌታ የተሰጠውን አደራ እንዴት አድርጎ ነው የገለጸው? (ወዴት ነው የተላከው? ለምንስ ምክንያት ነው) (ሐዋ. 26፡ 15-19)።

ሠ) ፊስጦስ ጣልቃ ገብቶ ንግግሩን ከማስቆሙ በፊት ጳውሎስ ስለምን ነበር የሚናገረው?

ረ) 1. ጳውሎስ ለንጉሥ አግሪጳ የቀረበው ጥያቄ ምንድነው? 2. አግሪጳ ምን ዓይነት መልስ ነው የሰጠው?

ሰ) 1. ስለ ጳውሎስ ምን ዓይነት ፍርድ ነው የሰጡት? 2. የጳውሎስን ጉዳይ በተመለከተ ንጉሥ አግሪጳ ምንድነው ያለው?

ጳውሎስ በንጉሥ አግሪጳ ፊት ቆሞ ያደረገው ንግግር በኢየሩሳሌም ካደረገው ጋር በጣም ይመሳሰላል። ይህም የሆነው የሚያዳምጡት ሰዎች ስለ አይሁድ ሃይማኖት በቂ

ግንዛቤ ስላላቸው ነው። በእዚህኛው ንግግሩም ብዙ ትኩረት ይሰጠው የነበረው ወደ አግሪጳ ነው። ሊያሳይ የሞከረውም አኗኗሩ ሆነ የሚያስተምረው ትምህርት፥ ከአይሁዳውያን ግጭት ሊፈጥርበት እንደማይችል ነው።

ጳውሎስ በሄሮድስ ፊት ቀርቦ ንግግር በማድረጉ ደስ የተሰኘው፥ ሄሮድስ ስለ አይሁድ ሃይማኖት በቂ ግንዛቤ የነበረው ሰው በመሆኑ ነው። ይህ ሰው ያለምንም ጥርጥር ስለ ኢየሱስ ስለ ሞቱና ትንሣኤው ሰምቷል። ከዚህም ሌላ፥ ሊቀ ካህናቱና የሃይማኖት መሪዎቹ ቀናተኞች እንደሆኑና በፈሪሣውያንና በሰዱቃውያን መካከል ደግሞ ልዩነት እንዳለ ያውቃል። በይሁዳ ምድርም ለጳውሎስ ጉዳይ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ብቁ የሆነው መሪ ሄሮድስ ብቻ ነው።

ጳውሎስ ንግግሩን የሚጀምረው፥ ከመለወጡ በፊት ስለነበረው ሕይወት በመናገር ነው። በዚያን ጊዜም ቢሆን ጳውሎስ ሕጉን የሚቃወም ሰው አልነበረም። እንዲያውም ወግ አጥባቂ ከነበሩት ከፈሪሣዊያን ወገን ነበር እንጂ። ጳውሎስ ሲናገርም አሁን ለፍርድ የቀረብኩት እግዚአብሔር ለአባቶቻችን የሰጠውን የተስፋ ቃል እንደአለኘታ በመያዜ ነው ይላል። ይህን ሲል፥ ስለሚመጣው መሢሕ፥ በምድር ላይ ስለምትመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት፥ ስለሙታን ትንሣኤ፥ ወዘተ.... መናገሩ ነው። ይህ ደግሞ፥ በጣም ልዩ የሆነ እምነት አይደለም፥ ምክንያቱም ሁሉም አይሁዳውያን ተስፋ የሚያደርጉት እነዚህኑ የተስፋ ቃሎች ነው። ሆኖም ልዩነታቸው ያለው ጳውሎስ እነዚህ ነገሮች መሢሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ተፈጻሚነት አግኝተዋል በማለቱ ብቻ ነው። ስለዚህም ጳውሎስን የቸገረው ነገር አይሁዳውያን በሙታን ትንሣኤ እስካመኑ ድረስ ለምን በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ማመን ተሳናቸው የሚለው ነገር ነው።

ጳውሎስ ፈሪሣዊ ሳለ ቤተክርስቲያንን በጽኑ ከሚያሳድዱት ሰዎች አንዱ ነበር። ለሄሮድስና ለሌሎችም፥ ጳውሎስ ከመጀመሪያው ጀምሮ የክርስትና ተከታይ አለመሆኑን ሊገልጽላቸው ፈልጓል። በዚያን ጊዜም ከካህናት አለቆች ክርስቲያኖችን ለማሳደድ ሥልጣንና ትዕዛዝ የተሰጠው ጳውሎስ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ የእሱ ምኞት አይሁዳውያን ላይ ትልቅ ውርደት ያስከተለውን የክርስቲያን ሃይማኖት ከምድረ ገጽ ማጥፋት ነበር። ታዲያ ጳውሎስ ስለዚህ ጊዜ የተናገረበት ሌላው ምክንያት እሱን የመሰለ ሰው እንዲህ በቅጽበት መለወጡ አስገራሚ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ይህ ለውጥ ደግሞ ጳውሎስ በራሱ ችሎታ ያመጣው ሳይሆን እራሱ እግዚአብሔር ያደረገው ነገር ነው።

ጥያቄ 5፡- ይህ ለውጥ፥ በአንተ ሕይወት ውስጥ በገሃድ የታየው እንዴት ነው?

ጳውሎስ ስለመለወጡ ከተናገረ በኋላ ኢየሱስ እንዲያገለግለው ጥሪ እንደሰጠው ይናገራል። ከዚህም በፊት ጳውሎስ በካህናት አለቆችና ትዕዛዝ መሠረት ወደ ደማስቆ እየሄደ ነበር። ዓላማውም ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ነበር። ሆኖም፥ ወደዚያ እያመራ ሳለ ጳውሎስ በሚያስገርም ዓይነት ሁኔታ ከኢየሱስ ጋር ይገናኛል። ከዛም ይህ አሳዳጅ ሰው ክርስቲያን ይሆናል። በመጨረሻ ላይም ለአይሁዳውያንና ለአሕዛብ መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው እንዲከፈቱ ከጨለማ ወደ ብርሃን እንዲመጡና የኃጢአት ይቅርታን

እንዲያገኙ በኢየሱስ ማመን እንዳለባቸው እየሄድ እንዲናገር በዚሁ መንገድ ላይ የአገልግሎት ጥሪ ይሰጠዋል።

ጥያቄ 6:- ሀ) ይህ በመጨረሻ ላይ ያለው ዐረፍተ ነገር የወንጌሉን መልእክትና በኃጢአተኛ ሰው ላይ ያስገኘውን ለውጥ ባጭሩ ያስቀመጠው እንዴት ነው?

ለ) እኛም እንደ ጳውሎስ ዓይነት ኃላፊነት ያለን በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው?

ሐ) ኃላፊነትህን እንዴት እየተወጣኸው እንዳለህ አብራራ።

ጳውሎስ ይህን ከሰማይ የታየውን ራዕይ እንቢ አላለም። ከደማስቆ በመነሣት፥ ወደ ኢየሩሳሌምና ይሁዳ ብሎም ወደ አሕዛቡ ዓለም በሙሉ በመሄድ የወንጌሉን መልእክት አሰምቷል። ሁሉም ወደ እግዚአብሔር በንስሐ መቅረብ እንዳለበትና ይህን ማድረጉንም በሕይወቱ በተግባር ማሳየት እንዳለበት ነበር የሚያስተምረው። ይህ ደግሞ ፈሪሣዊ ወይም አይሁዳዊ ከመሆን ጋር የሚገናኝ አይደለም። እንዲያውም ከኢየሱስ ጋር ግንኙነት በመፍጠሩ የብሉይ ኪዳኑን እምነቱን በበለጠ ሊያከብር ችሏል።

ጳውሎስ ከዚህ በመቀጠል እሱ የሚያስተምረው ነቢያትና ሙሴ ያስተማሩትን ማለትም:- ክርስቶስ መከራን እንደሚቀበልና በሙታን ትንሣኤ ለአሕዛብ ብርሃን እንደሚሆንላቸው የሚገልጸውን ትምህርት እንደነበር ያስረዳቸዋል።

ጥያቄ 7:- የክርስቶስ መምጣት አንዳንዶቹን የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች እንዴት እንደፈጸመ ሠፋ አድርገህ ግለጽ።

ስለ ነቢያት ጽሑፍ ምንም ግንዛቤ ያልነበረው ጳውሎስ በሙታን ትንሣኤ ማመኑን ሲገልጽ ፊስጦስ ይህ ትምህርት ዕብድ አድርጎሃል ይለዋል። ይህንንም ሊለው የቻለው የአንድ ሰው ከሞተ በኋላ ይነሣል የሚለው ነገር ሊዋጥለት ስላልተቻለ ነው።

ጳውሎስ ዕብድ እንዳልሆነ ይናገራል። በመቀጠልም የተናገረውን ነገር ንጉሥ አግሪጳ እንደሚያውቀው ስለተረዳ «ንጉሥ አግሪጳ ሆይ ነቢያትን ታምናለህን?» ብሎ ይጠይቀዋል።

አግሪጳ ባለው እውቀት ላይ ተመሥርቶ የጳውሎስ ንግግር እውነተኛ እንደሆነ ሊመሠክር ይችል ነበር! ምክንያቱም ያለ ጥርጥር በዚህ ሰዓት መንፈስ ቅዱስ ሳያሳምነው አይቀርምና ነው። ታዲያ ይህም ሁሉ ሲሆን አግሪጳ «በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ?» ብሎ ጳውሎስን ይጠይቀዋል። ስለዚህም በዚህ ሰዓት የቃሉን እውነተኛነት ሊክድ ባይችልም ነገሩን ለመቀበል ዝግጁ አለነበርም።

ጥያቄ 8:- ለመሪዎች ወይም ሃብታም ለሆኑ ሰዎች ወንጌልን መቀበሉ በጣም የሚያዳግታቸው ለምንድነው?

ጳውሎስ በጥቂትም ቢሆን በብዙ አንተ ብቻ አይደለህም ነገር ግን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ደግሞ ከእዚህ እሥራት በቀር እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ ብሎ ይመልስለታል።

ንጉሡም፥ አገረ ገዢዎም፥ በርኒቄም፥ ከእነርሱም ጋር ተቀምጠው የነበሩት ተነሡ፤ ፈቀቅ ብለውም እርስ በርሳቸው ይህ ሰው እንኳንስ ለሞት ለእሥራትም የሚያደርስ ምንም አላደረገም ብለው ተነጋገሩ። አሁንም እንደገና እንደምናየው መሪዎችም ሆኑ የአይሁድን ሕግ ጠንቅቆ የሚያውቀው ንጉሥ አግሪጳ ጳውሎስ ንጹሕ ሰው እንደሆነ ተገንዝበዋል። ሆኖም፥ እግዚአብሔር በዕቅዱ ውስጥ ጳውሎስ እሥረኛ ሆኖ ወደ ሮም እንዲሄድ በመፈለጉ፥ ነገሮች በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሊፈጸሙ ችለዋል።

አግሪጳ ፊስጦስን ይህ ሰው ወደ ቄሣር ይግባኝ ባይል ኖሮ መፈታት ይችል ነበር ይለዋል። የእግዚአብሔር ዕቅድ ግን ጳውሎስ ነፃ እንዲወጣ ሳይሆን ወደ ሮም እንዲሄድ ነበር።

በዚህ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፥ የጳውሎስን ምሥክርነት ሦስት ጊዜ ተጽፎ እናገኘዋለን። በእያንዳንዱም ጊዜ ምሥክርነቱ ለተለያዩ ሰዎች ለተለየ ዓላማ ነበር የተሰጠው። ሆኖም ሁሉም ጳውሎስ በክርስቶስ በማመኑ በሕይወቱ ውስጥ የተገኘውን ለውጥ በጉልህ ያሳያሉ። ብዙ ጊዜም ወንጌሉ ሕይወትን የመለወጥ ኃይል እንዳለው እንዘነጋለን። ክርስቲያኖችም ብዙ ጊዜ በኢየሱስ ሲያምኑ ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ በሕይወታቸው አይታይም። ሆኖም፥ የወንጌሉ መልእክት ካመንና ከተቀበልነው አስተሳሰባችን አኳኋናችን አነጋገራችን ወዘተ. ... ሙሉ በሙሉ ይለወጣል። ምንም ለውጥ በሕይወታችን የማናይ ከሆነ እውነት በኢየሱስ አምነን እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ፥ እራሳችንን በደንብ መመርመር አለብን።

ጥያቄ 9፡- የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክበት ጊዜ አንሥቶ በሕይወትህ ውስጥ ያየሃቸውን ለውጦች በዝርዝር ጻፍ።

# ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 27፡ 1-12

ጳውሎስ ምሥክርነቱን፥ በአይሁድ ሃይማኖትና ባህል በቂ ዕውቀት በነበረውና የጳውሎስን ንጹሕ መሆን በመሰከረው በንጉሥ አግሪጳ ፊት ካቀረበ በኋላ፥ እንደ እሥረኛ ሆኖ ወደ ሮም ለመሄድ ይዘጋጃል።

ጳውሎስ ጉዞውን ወደ ሮም የጀመረው በ59 ዓ.ም ነው። ይህንን ጉዞውን ያደረገው በመርከብ ሲሆን የአንድ ዓመት የጉዞ ጊዜ ውስጥ ብዙ ችግሮችና አደጋዎች አጋጥመውታል። ታዲያ ይህ ጊዜ ጳውሎስን ተስፋ የሚያስቆርጥ ጊዜ ቢመስልም፥ በዚህ ውስጥ የእግዚአብሔርን ጥበቃ በጉልህ ልናይ እንችላለን። ከዚህም በላይ በዚህ አደገኛ ጉዞ ላይ መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ሊሰጠው የሚችለውን የልብ ዕርጋታና ሠላም እናያለን።

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 1-26 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 10፡- ሀ) ጳውሎስን ከቂሣሪያ በወሰዳቸው መርከብ ውስጥ የነበሩትን ሰዎች በሙሉ በዝርዝር ግለጽ። ለ) ጳውሎስ ወደ ጓደኞቹ እንዲሄድ የተፈቀደለት የትኛው ወደብ ላይ ነው? ሐ) ጳውሎስ ከቂሣሪያ ተነሥቶ በቀርጤስ በስተደቡብ እስከምትገኘው እስከ መልካም ወደብ የሚሉአት

ሥፍራ ድረስ ያደረገውን ጉዞ በካርታው ላይ በእርሳስ ምልክት አድርግበት። መ) የጠመ ወራት ካለፈ በኋላ እናርፋለን ብለው የሚያስቡት በየትኛው ወደብ ነበር? ሠ) ጳውሎስ ለመቶ አለቃው፥ ለመርከቡ መሪና፥ ለመርከቡ ባለቤት የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን ነበር?

ጳውሎስ በንጉሥ አግሪጳ ፊት ምሥክርነቱን ካቀረበ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከሌሎች እሥረኞች ጋር ይሆንና ወደ ኢጣልያ ጉዞውን ይጀምራል። ምንም እንኳ ይህ ጉዞ በደህና ጊዜ የአንድ ወር ጉዞ ቢሆንም ለእነሱ ብዙ ወራት ፈጅቶባቸዋል። በዚህ ጉዞ ላይም የእሥረኞቹ አለቃ የነበረው ዩልዩስ የተባለ መቶ አለቃ ነበር። በዚህ መርከብ ውስጥም የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጸሐፊ ሉቃስ ነበር፤ ይህንንም የምንለው፥ «በእስያ ዳርቻ ወዳሉት ሥፍራዎች ይሄድ ዘንድ ባለው በአድራሚጢስ መርከብ ገብተን ተነሣን» የሚል ነገር ስለምናነብ ነው።

በመርከቡ ውስጥ ከሉቃስ ሌላ አርስጥሮኮስ የተባለ ሰው ከእነጳውሎስ ጋር ነበር። እንደምታስታውሰው ይህ አርስጥሮኮስ የተባለ ሰው የመጣው ከመቄዶንያ ሲሆን፥ በኤፌሶን ቆይታውም ከጳውሎስ ጋር የነበረና ለኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያ ስጦታ ይዘው ከመጡት የየአብያተ ክርትስቲያን ተወካዮች ውስጥ አንዱ የነበረ ነው (ሐዋ. 19፡ 29፤ 20፡ 4)። ምናልባት በዚህ ጊዜ ውስጥ ጢሞቴዎስና ሌሎች አብረውት የሚሄዱ ሰዎች አብረውት ሳይሆኑ አይቀርም። ሆኖም ጳውሎስ ከዚህ ገጠመኝ በኋላ በጻፋቸው ። መልእክቶች ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር በሮም ስለመሆኑ የምናውቀው ነገር የለም። ታዲያ ይህም ቢሆን፥ እግዚአብሔር በጉዞው ላይ ሁሌ ለጳውሎስ ወዳጆችን ያዘጋጅለት ነበር።

**ጥያቄ 11፡- እግዚአብሔር በችግር ጊዜ ያዘጋጀልህን የአንዳንድ ወዳጆችህን ስም በዝርዝር ጻፍ። ጌታ እነዚህን ወዳጆች ስለሰጠህ አመስግነው።**

የይሁዳ ወደብ ከሆነችው ከቂሣሪያ በመነሣት መርከቧ በስተሰሜን ጥግ ጥጉን በማድረግ ወደ ሲዶና ትደርሳለች። የእሥረኞችም አለቃ ዩልዩስ በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ ወደ ክርስቲያን ወንድሞቹ ሄዶ ዕርዳታ እንዲቀበል ይፈቅድለታል። ስለዚህም ጳውሎስ ካሁኑ በመሪው ዘንድ አመኔታን አግኝቷል ማለት ነው።

በሜዲቴራኒያን ባሕር ላይ፥ በመርከብ መጓዝ በጣም አደገኛ የሚሆኑባቸው የተወሰኑ ወራት አሉ። እነ ጳውሎስ በሲዶና የደረሱትም በዚህ ወቅት ነው። ታዲያ ይህም ቢሆን፥ እንሄዳለን ብለው ቆርጠው ተነሡ። በዚህም መሠረት ከሲዶና ሲነሡ ነፋሱ በጣም ይከለክላቸው ስለነበር በቆጵሮስ፥ በኪልቅያና በጵንፍልያም ያለውን ባሕር ከተሻገሩ በኋላ ተተግነው በስተሰሜን በሉቅያ ወዳለችው ወደ ሙራ ይደርሳሉ።

በሙራ ሳሉም መቶ አለቃው፥ ወደ ኢጣልያ የሚሄድ የእስክንድርያ መርከብ ያገኝና ጳውሎስንና ጓደኞቹን በዚያ ያገባቸዋል። በንፋሱም ምክንያት በብዙ ጭንቅ ወደ ቀኒዶስ አንፃር ይደርሳሉ። ከዚያም ንፋሱ ስለከለከላቸው፥ በቀርጤስ ተተግነው በሰልሙና በኩል ያልፉና በብዙ ጭንቅ ለላሲያ ከተማ ወደ ቀረበችው መልካም ወደብ ወደሚሏት ሥፍራ ይደርሣሉ፤ እ.ኤ.አ ከኅዳር አንሥቶ እስከ ጥር ድረስም በዚህ በኩል

በመርከብ ማለፍ አይቻልም ነበር። የጦም ወራት ተብሎ የተጠቀሰውም የአይሁድ በዓል የነበረው «ታላቁ የስርየት ቀን» ነበር። በ59 ዓ.ም ላይም፥ ይህ በዓል ይውል የነበረው እ.ኤ.አ. ጥቅምት 5 ቀን ነበር። ስለዚህም በዚህ ወቅት በሰሜን ምሥራቅ በኩል የሚነፍስ ኃይለኛ ነፋስ በመኖሩ፥ የነፋሱን ኃይል የሚቋቋሙበት ሞተር የሌላቸው ጀልባዎችም ነፋሱን በጭራሽ ሊቋቋሙት አይችሉም ነበር።

ጳውሎስም ነፋሱ እስኪቆምና በመርከብ የመጓጓዣ ጊዜው እስኪደርስ ድረስ በመልካም ወደብ እንዲቆዩ የመርከቡን መሪዎች ያማክራቸዋል። እንዲያውም ከዚህ በላይ መልካም ወደብን ትተው ከተነሡ በመርከቡ በውስጡ ባለው ዕቃ ላይና በሕይወታቸው ትልቅ ጉዳትና ጥፋት እንደሚሆን ተንብዮአል። ሆኖም ይህ ወደብ ይከርሙበት ዘንድ የማይመች ስለነበር፥ መሪዎቹ ትንሽ ራቅ ብላ ወዳለችው ፍንቄ ወደሚሏት ወደ ቀርጤስ ወደብ ለመሄድ ይወስናሉ።

መሪዎቹ ለእግዚአብሔር ታዛዦች ባለመሆናቸው በሰዎች ላይ ምን ያህል ጉዳት እንደሚያደርሱ ተመልከት። ለእግዚአብሔር ታዛዥ አለመሆን ሁልጊዜ ችግር ያመጣብናል። ምንም እንኳ ለትንሽ ጊዜ እግዚአብሔርን የማይታዘዙ ሰዎች የበለፀጉ ቢመስሉም፥ አንድ ቀን መከራ ይወርድባቸዋል። ይህ ነገር በተለይ መሪዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይከተሉ ሲቀሩ፥ በእውን ይታያል። ታዲያ በዚህ ጊዜ ባለመታዘዛቸው መከራ የሚቀበሉት እነሱ ብቻ ሳይሆኑ፥ እንደ ጳውሎስም ያሉ ሰዎች ናቸው። በዚህም መልኩ ስናየው ለእግዚአብሔር ታዛዥ ያልነበረው የመርከቡ መሪ ነው እንጂ ጳውሎስ አልነበረም። ይህ አለመታዘዝ ደግሞ እንዴት በማዕበል መርከቧን እንደሠባበራትና የጳውሎስን ሕይወት አደጋ ላይ እንደጣለው እናያለን። የቤተክርስቲያን መሪዎችም እግዚአብሔርን በቅርብ መከተልና ሙሉ በሙሉ መታዘዝ ያለባቸው ለዚሁ ምክንያት ነው። የእነሱ የተሳሳተ ውሳኔ ደግሞ እነሱን ብቻ ሳይሆን የሚጎዳው በእነሱ ሥር ያሉትን ሰዎች ጭምር ነው።

ጥያቄ 12፡- ሀ) ይህን ዓይነት በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ተከስቶ ያየኸው እንዴት ነው?
ለ) ምን ዓይነት ውሳኔ ነበር የተደረገው? የዚያስ ውሳኔ መጨረሻ ምን ሆነ?

## አራተኛ ቀን የሐዋርያት ሥራ 27፡ 13-26

ጳውሎስን ይዛ ወደ ሮም ትጓዝ የነበረችው መርከብ በመጥፎ የአየር ሁኔታ እንድትዘገይ ከተገደደች በኋላ፥ በመጨረሻ ላይ በቀርጤስ በስተደቡብ ወደምትገኘው መልካም ወደብ ወደሚሏት ሥፍራ ልትደርስ ችላለች። ከዚህም በኋላ በዚህ ቦታ ሊከርሙበት የማይችሉ በመሆኑ መቶ አለቃውና የመርከቡ መሪ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይጠብቁ ለመከረም ሻል ወዳለው ወደ ቀርጤስ ወደብ ለመሄድ ቆርጠው ይነሣሉ።

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 13-26 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 13፡- ሀ) የመርከቡን መሪ ባለቤትና መቶ አለቃውን ወደ ቀርጤስ ወደብ እንዲሄዱ ያነሣሣቸው ነገር ምንድነው?

ለ) 1. በድንገት የገጠማቸው አደጋ ምንድነው? 2. ታንኳይቱ እንዳትነዳ ሲሉ ያደረጉት ነገር ምንድነው?

ሐ) 1. ጳውሎስ በመርከቡ ውስጥ ላሉት ሰዎች በሙሉ ምን ዓይነት የማጽናናት ቃል ነው የሰጣቸው? 2. ጳውሎስ ይህን የተስፋ ቃል ያገኘው ከማነው? 3. ጳውሎስ ሰዎቹን ምን እንዲያደርጉ ነው የጠየቃቸው?

ልከኛ የደቡብ ንፋስ በነፈሰ ጊዜ፥ እንዳሰቡት የሆነ መስሏቸው ከመልካም ወደብ ተነሥተው በቀርጤስ አጠገብ ጥግ ጥጉን በማለፍ ፍንቄ ለመከረም ጉዞአቸውን ይጀምራሉ። ነገር ግን ትንሽ ሳይቆዩ በድንገት አውራቂስ የሚሉት አውሎ ንፋስ ይወርድባቸውና ወደ ደቡብ ይነዳቸዋል። ከዚያም ቄዳ በሚሏት ደሴት አካባቢ ሲደርሱ ተተግነው ታንኳይቱን ሊቆጣጠሩ በገመድ አስታጥቀው ሊያጸኗት ችለዋል። ሶርቲስም ወደሚሉት ወደ አሸዋ እንዳይወድቁ ብለው ሸራውን አውርደው እንደዚሁ ተነዱ። በማግሥቱም እንደዚሁ ንፋሱ በርትቶ ሲያስጨንቃቸው ከጭነቱ ወደ ባሕር ይጥላሉ። ለሦስት ቀንም እንደዚህ ከዋለ በኋላ የመርከቡን ዕቃ መወርወር ይጀምራሉ።

ንፋሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ ለብዙ ቀን በመቆየቱ ብዙዎቹ ሰዎች የመዳን ተስፋቸው ይጠፋና ለብዙ ቀን ሳይበሉ ይቆያሉ። ሆኖም በዚያ መርከብ ላይ እግዚአብሔር የራሱ ወኪል የሆነውን ጳውሎስን አስቀምጦ ነበር! ሥራውንም እስኪፈጽም ድረስ እንዲሞት አያደርገውም። እግዚአብሔር ለጳውሎስ ሮም ትደርሳለህ የሚል የተስፋ ቃል ሰጥቶታል! ይህ ቃል ደግሞ እንዲፈጸም የጳውሎስ ሕይወት መትረፍ አለበት።

ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ እናንተ ሰዎች ሰምታችሁኝ በሆነ ኖሮ ከቀርጤስ እንዳትነሡ ይህንንም ጥፋትና ጉዳት እንዳታገኙ በተገባችሁ ነበር ይላቸዋል። ከዚህም በመቀጠል ይህ መርከብ እንጂ ከእናንተ አንድ ነፍስ እንኳ አይጠፋም ብሎ ያጽናናቸዋል። ይህንንም ሊላቸው የቻለው የእግዚአብሔር መልአክ በዛች ሌሊት በአጠገቡ ቆሞ «ጳውሎስ ሆይ አትፍራ! በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል! እነሆም እግዚአብሔር ከአንተ ጋር የሚሄዱትን ሰጥቶሃል» ስላለው ነው። ጳውሎስ በእግዚአብሔር ይታመን ስለነበር ሊያጽናናቸው ችሏል! እነሱ ግን ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው መርከቡንና ዕቃቸውን እስከማጣት ይደርሳሉ።

ጥያቄ 14፡- እግዚአብሔር ወደ ጳውሎስ መልአኩን የላከው ለምንድነው?

የመኖር ተስፋ ሙጥጥ ብሎ በጠፋበት ጊዜ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ ጳውሎስም ሆነ አብረውት ያሉት ሰዎች እንደማይጠፉ ይነግረዋል። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በእውነት የሚፈጸሙ ናቸው! በዚህም ወቅት ወደ ሮም የመሄዱ ጉዳይ እርግጠኛ እንደሆነ መልአኩ መጥቶ ለጳውሎስ ይገልጽለታል።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን የዘነጋው ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ሲያዘገይ አልፈጽምም ብሎ እንደወሰነ አድርገን

ልንቆጥረው አይገባንም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች በእርግጥ የሚፈጸሙ ናቸው።

ጥያቄ 15፡- ይህ ሁሉ ችግርና መከራ በጳውሎስና አብረውት በነበሩት ሰዎች ላይ እንዲወርድ እግዚአብሔር የፈቀደው ለምን ይመስልሃል?

ጥያቄ 16፡- ሀ) እግዚአብሔር አደገኛ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንድታልፍ አድርጎህ ያውቃልን? ለ) ይህን ያደረገበትን ምክንያት ልትገነዘበው ችለሃልን? ሐ) ምክንያቶቹንም ባታይ እስከመጨረሻው በእርሱ ለመታመን ቆርጠህ ተነሥተሃልን?

በሚቀጥለው ሳምንት፥ እግዚአብሔር ጳውሎስን እንዴት ጠብቆ በሮም መሪዎች ፊት እንዲቀርብ እንዳደረገው እናያለን። እንደ እግዚአብሔር ልጆችም አንዱ የተሰጠን የተስፋ ቃል፥ በሁሉ ነገር፥ በአደጋም፥ በመርከብ መሰበርም ይሁን ወይም በችግር፥ ወዘተ. ... እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች በሙሉ ለበጎ እንደሚጠቀምባቸው ነው። ይህም የሆነው እነዚህ ነገሮች በሙሉ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር በላይ የሆኑ ነገሮች ባለመሆናቸው ነው።

ጥያቄ 17፡- ሮሜ 8፡ 28-39 አንብብ። እግዚአብሔር የሰጠንን የተለያዩ የተስፋ ቃሎች በዝርዝር ጻፍ። እነዚህ የተስፋ ቃሎች በሕይወትህ የተፈጸሙት እንዴት ነው? እግዚአብሔር እነዚህን የተስፋ ቃሎች ስለሰጠህ አመስግነው።

## አምስተኛ ቀን፡- ክለሳ

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

1. ሀ) ንጉሥ አግሪጳ ማነው? ለ) ፊስጦስ ስለ ጳውሎስ አግሪጳን ያማከረው ለምንድነው?
2. ጳውሎስ ክስ የቀረበበትን ምክንያት የገለጸው እንዴት በማለት ነው?
3. ሀ) ስለ ብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ጳውሎስ የተናገረውን ነገር ንጉሥ አግሪጳ ተቀብሎታል ወይስ አልተቀበለውም? ለ) ለዚህ ነገር ማረጋገጫ የሚሆነውን ነገር ለፊስጦስ ምን በማለት ነው የተናገረው?
4. ወደ ሮም ባመራችው መርከብ ውስጥ ከጳውሎስ ጋር አብረውት የነበሩት ወዳጆቹ እነማን ናቸው?
5. በባሕር መጓዝ በዚያን ጊዜ አደገኛ የነበረው ለምንድነው?
6. መቶ አለቃውና የመርከቡ መሪ ጳውሎስ ከመልካም ወደብ እንነሣ ብሎ ሲያስጠነቅቃቸው ያልተቀበሉት ለምንድነው?
7. እግዚአብሔር ለጳውሎስ የሰጠው የተስፋ ቃል ምንድነው?

ለሳምንታዊው ስብሰባ ለመዘጋጀት እነዚህን የመወያያ ጥያቄዎች ተመልከት።

## ሳምንታዊው ስብሰባ

*1.* የአምልኮ ጊዜ

3. ክለሳ

2. የጸሎት ጊዜ

4. ውይይት:-

ሀ) መሪዎች፥ ሃብታም ሰዎች፥ ... ወዘተ. ክርስቶስን እንደ አዳኝ መቀበሉ የሚያዳግታቸው ለምንድነው? (1ቆሮ. 1፡ 18-31 ተመልከት)።

ለ) 1. የአንድ ሰው ክርስቲያን መሆን ሀ) በሥራው ለ) በቤቱ አካባቢ ሐ) በአስተሳሰቡ መ) በመኖር ዓላማው ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምን ዓይነት ነው?

2. ክርስቲያን በመሆንህ ምክንያት በሕይወትህ ውስጥ የተከሰቱት ለውጦች ሰፋ አድርገህ ግለጽ።

3. ክርስቲያኖች በበለጠ ሁኔታ ለዓለም ብርሃን ለመሆን መለወጥ ያለባቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?

ሐ) 1. የአንድ ቤተክርስቲያን መሪ የተሳሳተ ውሳኔ ንጹሐን ሊጎዳ የሚችለው እንዴት ነው?

2. አንድ መሪ የተሳሳተ ውሳኔ ሲያደርግ አንድ ክርስቲያን በዛኛው ሰው ላይ ምን ዓይነት አመለካከት ነው ሊኖረው የሚገባው በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ አንድ ክርስቲያን መመካት ያለበት በምንድነው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 19

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 27-28፤ 31

## የመጀመሪያ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 27፡ 27-44

የመርከቡ መሪ በጳውሎስ በኩል ከእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ሳይቀበል ይቀርና ወደ ፍንቄ ከተማ ጉዞ ይጀምራል። እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸውም በመርከቡ ላይ የነበረውን ዕቃና እራሱን መርከቡን ሊያጡ ችለዋል። እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ምንኛ ትልቅ ዋጋ ያስከፍላል!!

በመሪው አለመታዘዝ የጳውሎስ ሕይወት እንኳ በአደጋ ላይ ወድቋል። እግዚአብሔርን በመከተሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ጳውሎስ መከራ የተቀበለው በዚህ ጊዜ አይደለም። የጳውሎስ ሕይወት ከዚህም በፊት በችግር የተሞላ ነበር። ታዲያ በሚያጋጥመው ችግር በመጠቀም እግዚአብሔር ለሰዎች የሚመሠክርበትን አጋጣሚ ያዘጋጅለት ነበር። በዚህ መልኩም እንደገና እግዚአብሔር ጳውሎስን ከአደጋ

ይጠብቀውና በምንም አጋጣሚ የወንጌሉን መልእክት ሊሰሙ ለማይችሉ ሰዎች እንዲመሠከር ያደርገዋል።

ጥያቄ 1፡- ሀ) የሐዋርያት ሥራ 27፡ 27-28፡ 31 አንብብ። እግዚአብሔር በዛች ደሴት ላይ ወንጌሉ እንዲስፋፋ የመርከቡን መሰበር የተጠቀመበት እንዴት ነው ለ) በሮም ሳለስ ጳውሎስ ወንጌልን ሊሰብክ የቻለው እንዴት ነው?

የሐዋርያት ሥራ 27፡ 27-44 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 2፡- ሀ) 1. በነፋስ ወዲህና ወዲያ ሲነዱ የቆዩት ለምን ያህል ቀን ነው? 2. በየትኛው ባሕር ውስጥ ነበሩ?

ለ) 1. መርከበኞቹ በሌሊት ላይ ወደ ምድር የቀረቡ የመሰላቸው እንዴት ነው? 2. በመርከቡ ውስጥ የነበረውን ስንዴ ለማቃለል የተገደዱት እንዴት ነው?

ሐ) 1. መርከበኞቹ ከመርከቡ ለመሸሽ የሞከሩት እንዴት ነው?

2. ጳውሎስ ለምንድነው ያስጠነቀቃቸው?

3. መርከቡ ከመሰበሩ በፊት ጳውሎስ የነበሩትን ሰዎች ምን እንዲያደርጉ ነው የለመናቸው?

መ) 1. ጳውሎስ የሰጣቸው የተስፋ ቃል ምንድነው? 2. በመርከቡ ላይ ምን ያህል ሰው ነበር?

ሠ) 1. መርከቡ ከዲብ ጋር ሲጋጭ ወታደሮቹ ምን ለማድረግ አሰቡ?

2. የመቶ አለቃው ይህ እንዳይሆን የከለከለው ለምንድነው?

3. ሰዎቹ ወደ ምድር የደረሱት እንዴት ነው?

ጳውሎስን ወደ ጣልያን ይዛ ትሄድ የነበረችው መርከብ በአድርያ ባሕር ውስጥ ለአሥራ አራት ቀን ያህል ወዲህና ወዲያ ስትነዳ ነበር። (በጥንት ጊዜ በጣልያን፥ ማልታ፥ ቀርጤስና ግሪክ መካከል የነበረው ባሕር አድርያቲክ ባሕር ነበር የሚባለው)። በአሁኑ ጊዜ ግን ሜዲቴራኒያን ባሕር ይባላል። እኩለ ሌሊትም ላይ መርከበኞቹ ወደ ምድር የቀረቡ ይመስላቸውና የውሃውን ጥልቀት ሲለኩት 40 ሜትር ገደማ ይሆናል። ጥቂትም ቆይተው እንደገና መለኪያቸውን ሲጥሉ 30 ሜትር ይሆናል። ከዚያም ወደ ድንጋያማ ሥፍራ እንዳይወድቁ ፈርተው፥ ከመርከቡ በስተኋላ አራት መልሕቅ አወረዱ፤ ቀንም እንዲሆን ተመኙ።

መርከበኞቹ ከመርከቡ ፊት መልሕቅ የሚጥሉ መስለው ከመርከቡ ለመሸሽ ይሞክራሉ። በዚህን ጊዜም ጳውሎስ ለመቶ አለቃውና ለወታደሮቹ እነዚህ መርከበኞች በመርከቡ ውስጥ ካልቆዩ ነፍሳቸውን ሊያድኑ እንደማይችሉ ይነግራቸዋል። ያን ጊዜም ወታደሮቹ ጳውሎስ የተናገረውን ነገር ያምኑና የታንኳይቱን ገመድ ቆርጠው ትወድቅ ዘንድ ይተዉአታል። ስለዚህም ሊድኑ የሚችሉት የእግዚአብሔርን የማዳኛ መንገድ ከተከተሉ ብቻ ነበር።

ጥያቄ 3:- ይህ ሁኔታ ከመንፈሳዊ ደኅንነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

በመርከቡ የነበሩት ሰዎች ለብዙ ቀን ስላልበሉ ሊነጋጋ አካባቢ ጳውሎስ ምግብ እንዲበሉ ይለምናቸዋል። በመቀጠልም፥ ይህ ለደኅንነታችሁ ያስፈልጋችኋል፤ ከእናንተ ከአንዱም የራሱ ጠጉር እንኳ አትጠፋም ይላቸውና እግዚአብሔርን አመስግኖ እንጀራ በመቁረስ መብላት ይጀምራል። ሁሉም ይጽናኑና ምግብ ይበላሉ፤ ከዚያም ወደ ምድር ለመድረስ እንዲያዳግታቸው ብለው ስንዴውን ወደ ባሕር ይጥሉታል።

በነጋም ጊዜ የአሸዋ ዳር ያለውን የባሕር ሰርጥ ይመለከታሉ። ምድሩም ምን እንደሆነ ሳያውቁ መርከቡን ወደዚያ ይገፉ ዘንድ ይቀርባሉ። በዚህም መሠረት መልሕቁን ፈትተው ነፋሱ ወደ ምድሩ ይዟቸው እንዲሄድ ትንሹን ሸራ ለነፋስ ከፍ ያደርጉታል፤ ይሄን ጊዜም መርከቡን በጺብ ላይ ይነዱትና መርከቡ መሰባበር ይጀምራል።

ወታደሮቹም እሥረኞቹ እንዳያመልጡ ይገድሏቸው ዘንድ ይማከራሉ። በሮም ሥርዓት መሠረትም አንድ ወታደር እሥረኞቹ እንዲያመልጡ ካደረገ በእነሱ ፈንታ ይገደል ነበር። ታዲያ ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ የመቶ አለቃው ጳውሎስን ለማዳን ስለፈለገ ምክራቸውን ይቃወምና ዋና የሚችሉት ከመርከብ እራሳቸውን እየወረወሩ አስቀድመው ወደ ምድር እንዲደርሱ፥ የተቀሩት ደግሞ በሳንቃዎችና በመርከቡ ስባሪ ይወጡ ዘንድ ያዛል። ከዚህም በኋላ መርከቧና በውስጧ የነበረው ነገር ይወድምና ሰዎቹ በሙሉ ይተርፋሉ።

እግዚአብሔር ለጳውሎስ ሕይወት ዓላማ ስለነበረው፥ ይህ ዓላማው እስኪፈጸም ድረስ ይጠብቀውና ያጽናናው ነበር። ጳውሎስ ደግሞ በሌላ በኩል የታመነ ምሥክር ነበር። ስለዚህም የእግዚአብሔርን ዓላማ ከመፈጸም ሊያግደው የሚችል አንዳች ነገር ሊኖር አይችልም።

ጥያቄ 4:- ሀ) የኛ ሕይወት እንደ ጳውሎስ መሆን ያለበት እንዴት ነው?

ለ) እግዚአብሔር ለሕይወታችን ዕቅድ እንዳለውና ይህንንም ዕቅድ ምንም ሊያስቀርብን የሚችል አንዳች ነገር አለመኖሩን መገንዘባችን በምን መልኩ ነው የሚያጽናናን?

ጥያቄ 5:- በጣም አደገኛ ወይም አስቸጋሪ በሆኑ አጋጣሚዎች ነፍስህን ለእግዚአብሔር አደራ መስጠትን ተምረሃልን? ይህን ነገር እንዴት በሕይወትህ እንደተፈጸመ ምሳሌዎችን ስጥ።

የእኛ ፈተና እንደ ጳውሎስ እንደዚህ በእውን የማይታይ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም፥ ብዙዎቻችን በብዙ ችግሮችና ፈተናዎች ውስጥ እናልፋለን። ታዲያ «እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ ሐሳቡም ለተጠሩት ነገሩ ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» (ሮሜ 8፡ 28)።

## ሁለተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 28፡ 1-10

በእግዚአብሔር ጥበቃ ጳውሎስና አብረውት የነበሩት በደህና ወደ ምድር ይደርሳሉ። ታዲያ እግዚአብሔር የጳውሎስን የሮም መንገድ እንደገና በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ያዘገየው ለምንድነው? በዛሬው ዕለት ይህ መዘግየት በአንዲቱ ደሴት ላይ ላሉ ሰዎች እንዴት ወንጌሉን የመስማትና የማመን ዕድል እንደከፈተላቸው እናያለን።

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 1-10 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 6፡- ሀ) 1. መርከብ የተሰበረባቸው ሰዎች ያረፉባት ደሴት ስም ምን ትባላለች?

2. የደሴቲቱ ሰዎች ምን ዓይነት አቀባበል ነው ያደረጉላቸው?

ለ) 1. ስለ ጳውሎስ ማንነት ሰዎቹ እርስ በርሳቸው የተንሾካሾኩት ለምንድነው? 2. ጳውሎስ ምን ይሆናል ብለው ነበር የሚጠብቁት?

ሐ) 1. የደሴቲቱ አለቃ ማን ነበር? 2. ጳውሎስ ይህን ሰው የረዳው እንዴት ነው? 3. በዛች ደሴት ላይ ለምን ያህል ጊዜ ነው የቆዩት?

መ) 1. ጳውሎስ በደሴቲቱ ላይ ያገለገለው እንዴት ነው? 2. ጳውሎስንና አብረውት የነበሩትን ሰዎች የረዱቸው እንዴት ነው?

ጳውሎስና ሌሎቹ 275 ተጓዦች፥ መላጥያ በምትባል ደሴት ላይ እንዳረፉ ይገነዘባሉ። ይህች ደሴት «መሸሸጊያ» የሚል ትርጓሜ ያለው ሌላ ሜሊታ የሚል ስም ነበራት። ይህም የሆነው ምናልባት ለብዙ መርከቦች መሸሸጊያ በመሆኗ ይሆናል።

በደሴቲቱ ላይ እንደደረሱም፥ በዚያ የሚኖሩት አረማውያን በደንብ ይረዷቸው ጀመር። ዝናብ አበስብሷቸው ብርድ ብርድ ይላቸው ስለነበርም ቶሎ ብለው እሳት አያያዙላቸው። በዚህ ሥፍራ ላይ ጳውሎስ የነበረውን የአገልጋይነት መንፈስ አስተውል። ጳውሎስ በዛን ጊዜ ዕድሜው ወደ 60 ዓመት የሚጠጋ ሐዋርያ ነበር። ታዲያ እንዲያገለግሉት ለሌሎች ቦታውን መልቀቅ ሲኖርበት ከደሴቲቱ ሕዝቦች ጋር ሆኖ ለእሳት የሚሆን ጭራሮ ይሰበስብ ነበር።

ጥያቄ 7፡- ሀ) ብዙ ጊዜ በመሪነት ያሉ ሰዎች በትናንሽ ኃላፊነቶች ውስጥ ገብቶ የመሥራትን ፍላጎት የሚያጡት ለምንድነው? ለ) ከላይ ባየነው ሥፍራ፥ ከጳውሎስ ሕይወት መሪነትን በተመለከተ ልንማረው የምንችለው ነገር ምንድነው?

ጳውሎስ ብዙ ጭራሮ አከማችቶ ወደ እሣት በመጨመር ላይ ሳለ ከሙቀቱ የተነሣ ከጭራሮው ውስጥ አንዲት እፉኝት ትወጣና እጁን ትነድፈዋለች። እሱ ግን ምንም ጉዳት ሳይደርስበት እባቧን ወደ እሣት ውስጥ ያራግፋታል። ሁሉም እባቧ መርዘኛ መሆኗን ያውቁ ስለነበር ካሁን ካሁን ይሞታል ብለው ይጠብቁት ነበር።

አረማውያኑንም ለዚህ ለሆነው ነገር ወዲያውኑ የተለየ ትርጓሜ ይሰጡታል። በዚህም መሠረት ይህ ሰው በእርግጥ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ከባሕር እንኳ በደሕና ቢወጣ

የእግዚአብሔር ፍርድ በሕይወቱ ይኖር ስለነበር ይኸው እባብ ነድፎት ሊሞት ነው ብለው አሰቡ። ነገር ግን ቢጠብቁ ቢጠብቁ ምንም ነገር ሳይሆን በመቅረቱ ይህ አምላክ ነው ብለው ደመደሙ። ይህችም ተአምር ወዲያውኑ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሰክርበትን በር ከፈተችለት።

እሣት በሚያነዱበት አካባቢ የነበረው መሬት የዛች ደሴት አለቃ የነበረው የፑፕልዩስ መሬት ነበር። እሱም በእንግድነት ለሦስት ቀን ያህል ከሞት የተረፉትን ሰዎች ይቀበላል። በዚህም ጊዜ የፑፕልዩስ አባት ታመው ነበር። ጳውሎስም ወደተኙበት ክፍል ገብቶ እጁን ጭኖ ይጸልይላቸዋል፤ ከዛም ይፈወሳሉ። ይህን ሲሰሙም፣ በደሴቲቱ ደዌ የነበረባቸው ሰዎች ወደ ጳውሎስ እየመጡ ተፈወሱ።

ጳውሎስና ሌሎቹ ሰዎች በደሴቲቱ ላይ የቆዩት ለሦስት ወር ነው። ከዚህም በኋላ በመርከብ ወደ ሮም ለመሄድ ይችሉ ስለነበር ተነሥተው ይሄዳሉ። ሰዎቹም ለጳውሎስና ለጓደኞቹ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሰጥተው በክብር ይሸኟቸዋል።

ሉቃስ፣ ጳውሎስ በደሴቲቱ ላይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መስበኩን የሚጠቅሰው ነገር የለም። ይህም ቢሆን፣ ጳውሎስ የተገኘውን ተጠቅሞ ለሰዎቹ እንደሚመሠክር እርግጠኞች ነን።

ጥያቄ 8፡- ይህ አደጋ እነ ጳውሎስን ባያጋጥማቸውና በመላጥያ ባይቆዩ ኖሮ፣ የወንጌሉን መልእክትና የክርስቶስን ኃይል በፍጹም መስማትና ማየት የማይችሉት ሰዎች በዚህ ታሪክ ውስጥ የትኞቹ ናቸው?

## ሦስተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 28፡ 11-16

ከመርከባቸው መሰበር በኋላ፣ ጳውሎስና ጓደኞቹ በመላጥያ ደሴት ላይ ለሶስት ወር ያህል ይቆያሉ። በዚህም ጊዜ ጳውሎስ ሉቃስና አርስጥሮኮስ ያለምንም ጥርጥር ጊዜያቸውን ያሳልፉ የነበረው ስለ ክርስቶስ በመመሥከር ነበር። ከዚህም በላይ ጳውሎስ በደዌ የተያዙትን ይፈውስ ስለነበር፣ የመሄጃቸው ጊዜ ሲደርስ የሚያስፈልጋቸውን ሰጥተው በክብር ይሸኟቸዋል።

ጳውሎስ አሁን ሮም ሊደርስ ትንሽ ነው የቀረው። ወደ ኢየሩሳሌምም ከመሄዱ በፊት መንፈስ ቅዱስ በወኅኒ ቤት እንደሚታሠርና ብዙ መከራ እንደሚቀበል አስጠንቅቆት ነበር። ሆኖም አንዱና ብቸኛው የጳውሎስ ምኞት የእግዚአብሔርን የፀጋ ወንጌል መመሥከር ስለነበር ነገሩን በፀጋ ሊቀበለው ችሏል (ሐዋ. 20፡ 22-24)።

የሐዋርያት ሥራ 28፡ 11-16 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 9፡- ሀ) 1. በመላጥያ ደሴት ላይ ጳውሎስ ለምን ያህል ጊዜ ነው የቆየው? 2. ጉዟቸውን የቀጠሉበት ምን ዓይነት መርከብ ነበር?

ለ) 1. ደሴቲቱን ከለቀቁ በኋላ በመጀመሪያ ያመሩት ወዴት ነው? 2. በዚህ ሥፍራ ጳውሎስ ማንን ነው የሚያገኘው? 3. በዚህስ ቦታ ለስንት ቀን ቆዩ?

ሐ) 1. ከዚህ ቀጥሎ ጳውሎስና ጓደኞቹ ከእነማን ጋር ነው የተገናኙት? 2. በየት ነው የተገናኙት? 3. ጳውሎስ ሲያያቸው ምን አደረገ?

መ) ጳውሎስ በሮም ሲደርስ እሥረኛ ነበር? 2. እንዴት ነበር የሚኖረው?

በመላጥያ ደሴት ወደብ አካባቢ ከርሞ በነበረው በእስክንድርያ መርከብ ወደ ኢጣልያ ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ። የሰሜኑን አቅጣጫ በመያዝ በትልቁ ደሴት ሲሲሊ ወደ የሚገኘው ስራኩስ ወደ ተባለው ወደብ ያመራሉ። ከዚያም በዚሁ ደሴት ላይ የነበረው ሬጊዮም ወደተባለው ወደብ ያመራሉ። ከሁለት ቀንም በኋላ የደቡቡ ንፋስ በነፈሰ ጊዜ በኢጣልያ በስተምሥራቅ ወደሚገኘው ፑቲዮሉስ ወደተባለ ቦታ ይደርሳሉ። በዚህም ሥፍራ ክርስቲያን ወንድሞችን ያገኙና ለአንድ ሳምንት ያህል ይቆያሉ። ከዚያም ወደ ሮም ሲገቡ ጳውሎስ በጥበቃ ሥር ነበር።

የባሕሩ ጉዞ አሁን ይፈጸማል። ከፑቲዮሉስ በኋላ ያደረጉት የየብስ ጉዞ ነው። ከዚያም ወደ ሮም እየተቃረቡ ሲመጡ ወንድሞች ስለነ ጳውሎስ ሰምተው ስለነበር እስከ አፍዩስ ፋሩስና ሦስት ማደሪያ እስከሚባለው ሥፍራ ድረስ ወጥተው ይቀበሏቸዋል። ይህም ቦታ ከሮም በ33 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ነው።

ለብዙ ዓመታት ጳውሎስ ሮምን የመጎብኘት ምኞት ነበረው። አስቀድሞም «የሮሜ ሰዎች» መልእክቱን ጽፎላቸው ስለነበር ወሬን ከመስማትና ከጻፈላቸው መልእክት እሱን ያውቁት ነበር። ሊቀበሉት ወጥተው ሲያያቸውም ጳውሎስ ልቡ ይጽናናል! እግዚአብሔርንም ያመሰግናል። ዋናውንም መንገድ ተከትለው ከጳውሎስ ጋር ወደ ሮም ይገባሉ። ጳውሎስም የሮሜ ሰዎች መልእክቱን ከጻፈ ሦስት ዓመት አልፎታል። በዚህ ጊዜ ውስጥም ስለእነሱ ይጸልይ ስለነበር እሱን ለመቀበል መውጣታቸውን ሲያይ በጣም ይጽናናል።

ጥያቄ 10፡- ክርስቲያን ወንድሞችንና እህቶችህን የምታጽናናበትን አጋጣሚዎች ትፈልጋለህን?

# አራተኛ ቀን፡- የሐዋርያት ሥራ 28፡ 17-31

ጳውሎስ በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ላይ በኤፌሶን የነበረውን አገልግሎት ሊጨርስ አካባቢ ሮምን የማየት ፍላጎት እንዳለው ይናገራል (ሐዋ. 19፡ 21)። ሆኖም በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ የመራው ወደ መቄዶኒያ፥ አካይያና ኢየሩሳሌም ነው። ያለምንም ጥርጥርም ወደ ሮም እሄዳለሁ ብሎ ያሰበ የነበረው ከጥቂት ወራት በኋላ ነበር! ሆኖም ይኸው ሮም እስኪደርስ ድረስ አራት ዓመት ፈጅቶበታል።

እስካሁን ድረስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንዳየነው ጳውሎስ አንድ አዲስ ከተማ ውስጥ በገባ ጊዜ መጀመሪያ ይሄድ የነበረው የራሱ ወደሆኑት ወደ አይሁዳውያን ነው። በዚህም መሠረት በሮም የሦስት ቀን ቆይታ ካደረገ በኋላ የአይሁድ መሪዎች ይሰበስባል። ስለእሱ የሰሙት ምን እንደሆነ ባያውቅም፥ የሱን ታሪክ ከነገራቸው በኋላ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊመሠክርላቸው ይወድድ ነበር። ይህንንም ያደረገው፥

ኢየሩሳሌም ከሚገኙት የአይሁድ ታላላቆች እሱን የሚያማ ሪፖርት እንደሚላክ ያውቅ ስለነበረ ነው።

በመጀመሪያም የሮሙ አቀባበል ምንም ተቃውሞ ስለነበረውም። ሆኖም ልክ እንደተለመደው «ኢየሱስ መሚሕ ነው የሚለውን መልእክቱን ሲያሰማ ብዙዎቹ አልተቀበሉትም።

የሐዋርያት ሥራ 28: 17-31 አንብብና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ጥያቄ 11፡- ሀ) ጳውሎስ በሮም የአይሁድን መሪዎች የሰበሰባቸው ለምንድነው? ለ) ጳውሎስ የታሠረበትን ምክንያት ምን በማለት ነው የገለጸው? ሐ) ስለ እሥራቱ ሲነግራቸው አይሁዳውያኑ የተናገሩት ሦስት ነገሮች ጥቀስ። መ) ጳውሎስ አይሁዳውያኑን ሲያናግራቸው ሊያሳምናቸው የፈለገው ነገር ምንድነው? ሠ) 1. ጳውሎስ የጠቀሰው የየትኛውን ነቢይ ትንቢት ነው? 2. ጳውሎስ ለአይሁድ መሪዎች ያደረገው የመጨረሻው ንግግር ምንድነው? ረ) አይሁዳውያኑ ለጳውሎስ መልእክት ምን ዓይነት ምላሽ ነው የሰጡት?

ጳውሎስ በመጀመሪያ ሮም እንደደረሰ ያስብ የነበረው ለራሱ ሕዝቦች ነበር። በዚህም መሠረት ምንም እንኳ በጥበቃ ሥር ቢሆንም የአይሁድ መሪዎች እንዲሰበሰብ ተፈቅዶለት ነበር። በመጀመሪያም ሕዝቡን ወይም የአባቶችን ሥርዓት የሚቃወም አንዳች ነገር እንዳላደረገ ይገልጻል። ከዚህም ጋር አስታክኮ በኢየሩሳሌም እንዴት እንደታሠረና ለሮማውያን እንደተሰጠ ከዚያም ለሞት የሚገባ ነገር ባለማግኘታቸው ሊፈቱት እንዳሰቡ ይነግራቸዋል። በመቀጠልም «አይሁድ በተቃወሙኝ ጊዜ ወደ ቄሣር ይግባኝ እንድል ግድ ሆነብኝ እንጂ ሕዝቤን የምከስበት ነገር ኖሮኝ አይደለም። ስለዚህም ምክንያት አያችሁና አነጋግራችሁ ዘንድ ጠራኋችሁ» ይላቸዋል። ጳውሎስ ከሕዝቦቹ ጋር የነበረውን ግንኙነት ግልጽና እውነተኛ ለማድረግ ሲል የማያደርገው ነገር አልነበረም።

ጥያቄ 12፡- ሀ) ለቤተሰብህ ለጓደኞችህና ለቤተክርስቲያንህ ግልጽና ታማኝ ነህን? ለ) አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ጋር ጥሩ ግንኙነት የሌላቸው ለምንድነው? ሐ) እንደ ክርስቲያን ግንኙነታቸው ጥሩ ዓይነት እንዲሆን ማድረግ ያለባቸው ነገር ምንድነው?

የአይሁድ መሪዎችም «እኛ ከይሁዳ ስለ አንተ ደብዳቤ አልተቀበልንም፤ ከወንድሞችም አንድ ሰው እንኳ መጥቶ ስለ አንተ ክፉ ነገር አላወራልንም ወይም አልተናገረብህም። ነገር ግን ይህንን ወገን በየሥፍራው ሰዎች እንደሚቃወሙት እናውቃለንና፤ የምታስበውን ከአንተ እንሰማ ዘንድ እንፈቅዳለን» አሉት። በሮም አንዲት ትንሽ ቤተክርስቲያን ነበረች፤ በዚያ ይኖሩ የነበሩት አይሁዳውያን ደግሞ ስለ ክርስትና መጥፎ ወሬ ሲወራ ይሰሙ ነበር፤ ስለዚህም እውነተኛውን ነገር ለማወቅ ሲሉ በሌላ ቀን እንዲገናኙ ከጳውሎስ ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ።

በቀጠሮውም ዕለት ብዙ ሆነው ጳውሎስ ወደሚኖርበት ሥፍራ ይሄዳሉ። ከጥዋት እስከ ማታም ስለእግዚአብሔር መንግሥት ሲመሠክርላቸው ከሙሴ ሕግና ከነቢያትም በመጥቀስ ስለ ኢየሱስ ሲያስረዳቸው ይቆያል። ከዚያም የአይሁዳውያን ልብ እንደሚደነድን የሚገልጸውን የነቢዩ ኢሣይያስን ትንቢት ይጠቅስላቸዋል። ቢሰሙና በልባቸውም ቢያስተውሉ ኖሮ እግዚአብሔር ይፈውሳቸውና ያድናቸው ነበር። አይሁዳውያን ግን በተደጋጋሚ ወንጌልን ይቃወሙ ስለነበር ከተቃውሞአቸው ጋር የልብ መደንደን አብሮ ቅጣት ይሆንባቸው ዘንድ በእነሱ ላይ ይመጣል። ከዚህም በኋላ ወንጌሉን አዳምጠው መገንዘብና ማመን ይሳናቸዋል።

ሰዎች ወንጌል ሲሰሙ የመቀበል ወይም የመቃወም መብት አላቸው። ሆኖም፥ ወንጌልን መቃወም ሲጀምሩ በልባቸው ውስጥ አንድ ነገር መከሰት ይጀምራል። ይህም የልብ መደንደን ነው። በተደጋጋሚ ወንጌልን ሲቃወሙም የልባቸው መደንደን ሙሉ በሙሉ መጨረሻው ደረጃ ላይ ይደርሳል፤ ከዚህም እነሱን ለማሳመን የማይቻልበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። ታዲያ በጳውሎስም ጊዜ ይሁን ባሁኑ ጊዜ ያሉ አይሁዳውያን የሚገኙት በዚህ ደረጃ ላይ ነው።

ጥያቄ 13፡- እስከ ዛሬ በነበረህ የመመሥከር ልምድ ይህን ነገር ያየኸው እንዴት ነው?

ከአይሁዳውያኑ መካከል አኩሌቶቹ ጳውሎስ የተናገረውን አመኑ፤ ሌሎቹ ደግሞ አላመኑም። ጳውሎስም ይህ የእግዚአብሔር ደኅንነት ለአሕዛብ እንደተላከ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን በማለት ንግግሩን ያቆማል።

ጳውሎስ በሮም በተከራየው ቤት ውስጥ ጥበቃ እየተደረገለት ሁለት ዓመት ያሳልፋል። ሊያየው የፈለገ ሰውም በፈለገበት ሰዓት መጥቶ ሊያየው ይችል ነበር። በዚህም ጊዜ ሁሉም በደስታ እየተቀበለ በድፍረት ስለእግዚአብሔር መንግሥት ይመሠክርና ስለ ጌታ ኢየሱስ ያስረዳቸው ነበር።

ጳውሎስ በሮም ያሳለፈው የእሥር ጊዜ ዛሬ ላለነው ሰዎች በጣም ጠቅሞናል። ይህም የሆነው የኤፌሶን፥ የፊሊጵስዩስ፥ የቆላስያስና የፊሊሞናን መልእክቶቹን የጻፈው በዚህ ጊዜ ውስጥ በመሆኑ ነው።

ሉቃስ ለምን በዚህ ሥፍራ መጽሐፉን እንዳቆመው አናውቅም። ሆኖም ሉቃስ ይህን ያደረገው ምናልባት በሮም ሳለ የጻፈው ይህ መጽሐፍ ጳውሎስ የሥራቱን ጊዜ ከመፈጸሙ በፊት በመጠናቀቁ ይሆናል። በመጀመሪያም ቢሆን ከሉቃስ ወንጌል ጀምሮ ዓላማው «ኢየሱስ ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለጀመረው» ነገር መጻፍ ነው (ሐዋ. 1፡ 1)። ወንጌልም ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ እስከሮም ድረስ እንደተስፋፋ እውነተኛውን ነገር በመጥቀስ በግልጽ አስቀምጦታል። እንግዲህ ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በመነሣት፥ ከ60 ዓመት በኋላ ክርስትና በሮማው ዘመነ መንግሥት የታወቀ ሃይማኖት ሊሆን ችሏል።

የጳውሎስ ሕይወት መጨረሻ ይህ አይደለም። ምንም እንኳ ባይጠቀስም በሮም ለሁለት ዓመት ከታሠረ በኋላ ጳውሎስ ይለቀቃል። ከዚያም ለትንሽ ጊዜ በሮም ሲያገለግል ከቆየ በኋላ ወደ እስፓኝና ወደ ሌሎች ቦታዎች ለመመሥከር ሳይሄድ

አይቀርም። ከሁኔትውም እንደምናየው በእስያና በግሪክ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት እንደገና ለመጎብኘት ዕድል ሳያጋጥመው አልቀረም። ከዚህም በኋላ ለአራት ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ ጳውሎስ በሮማውያን እንደገና ይታሠርና ይገደላል። ለመጨረሻ ጊዜ ከታሠረ ጊዜም ከመሞቱ በፊት ሁለተኛውን የጢሞቴዎስን መልእክት ይጽፋል።

ጥያቄ 14፡- እስቲ መለስ በልና የጳውሎስን ሕይወትና አገልግሎት ተመልከተው። ሀ) ለእግዚአብሔር በክብር እንዴት መኖር እንደሚገባህ የሚገልጹልህ በሕይወትህ ውስጥ ተግባራዊ ልታደርጋቸው የምትችላቸውን አንዳንድ ነገሮች እስቲ በዝርዝር ጻፍ። ለ) አንድ ክርስቲያን መሪ በተለይ አንድ ወንጌላዊ ወንጌልን ለማስፋፋት መከተል ያለበትን ነገሮች ደግሞ እስቲ በዝርዝር ጻፍ።

# አምስተኛ ቀን፡- ክለሳ

የዚህን ሳምንት ትምህርት ክልስና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

1. መቶ አለቃውና መርከበኞቹ የጳውሎስን ምክር ሰምተው ቢሆን መርከቧ ከመሰበር ትድን ነበር ወይ? (ሐዋ. 27፡ 10)
2. በመርከቧ መሰበር የተገኘው ጥቅም ምንድነው? (ሐዋ. 28፡ 7-9)
3. ከፑቲዮሉስ እስከ ሮሞ ባደረገው የእግር ጉዞ ላይ ጳውሎስን ያጽናናው ነገር ምንድነው?
4. ጳውሎስ በሮም እንደደረሰ በመጀመሪያ ያሰበው ስለምን ነበር?
5. በሮም የሚገኙት አይሁዳውያን ምላሽ በሌሎች ሥፍራዎች ከነበሩት የሚለየው በምን መልኩ ነው? የሚመሳሰለውስ?
6. ጳውሎስ በሮም ስለነበረው አገልግሎት አጠር ያለ ማብራሪያ ስጥ። ይህ አገልግሎት እስከዛሬ ድረስ በመቀጠል ላይ ያለው እንዴት ነው?
7. ብዙ አይሁዳውያን ስላለማመናቸው ጳውሎስ የሰጠው ምክንያት ምንድነው?

ለመጨረሻው ፈተና ዝግጁ እንድትሆን ካሁን ሰዓት ጀምሮ የዚህ መጽሐፍ ጥናት ክለሳ ጀምር።

ለሳምንታዊው ስብሰባ ዝግጁ ለመሆን የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት።

# ሳምንታዊው ስብሰባ

| | |
|---|---|
| 1. የአምልኮ ጊዜ | 3. ክለሳ |
| 2. የጸሎት ጊዜ | 4. ውይይት፡- |

ሀ) 1. ጳውሎስ ስለ ትንሣኤ ሲያስተምር ሁልጊዜ በአይሁዳውያን መካከል ክርክር ይፈጠር የነበረው ለምንድነው? 2. በዛሬ ጊዜ ይህ ነጥብ የሚያከራክር ነው ወይ? ከሆነ በምን ዓይነት መንገድ ነው? 3. ሰዎች ከሞት በኋላ ሕይወት ስለመኖሩ ማሰብ የማይፈልጉት ለምንድነው?

ለ) ጳውሎስ ከጌታ የተቀበለውን ተልእኮ እንዲፈጽም የረዱትን ባሕሪዎች ተወያዩባቸው።

ሐ) 1. ለእግዚአብሔር ክብር እንዴት መኖር እንደሚገባህ የሚገልጹልህ አንዳንድ ከሐዋርያት ሥራ ያገኘሃቸው ተግባራዊ የምታደርጋቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? 2. በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናትን ስንመሠርት ልንከተላቸው የሚገቡን መመሪያዎች ምን ምንድናቸው? 3. በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አንድ ክርስቲያን መሪ በተለይ አንድ ወንጌላዊ ወንጌልን ለማስፋፋት እንዴት መሥራት እንዳለበትና ከሥራው ምን መጠበቅ እንዳለበት የሚገልጹት መመሪያዎች ምን ምንድናቸው?

5. ጸሎት

# ትምህርት 20

## የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሙሉ ክለሳ

### የመጀመሪያ ቀን:-

በሐዋርያት ሥራ ጥናታችን እንዳየነው ይህ መጽሐፍ የሉቃስ ወንጌል ቀጣይ ነው። ሁለቱም መጽሐፍት የተጻፉት በሉቃስ ሲሆን የተጻፉትም ለቴዎፍሎስ ነው። የሉቃስ ወንጌል ትኩረት የሚያደርገው በኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ላይ ሲሆን በመጨረሻ ላይ መጽሐፉ የሚያልቀው ኢየሱስ የአብ ተስፋ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ ብሎ በሰጠው የተስፋ ቃል ነው (ሉቃስ 24፡ 49-53)።

የሐዋርያት ሥራ ደግሞ ከሉቃስ ወንጌል መጨረሻ ተነሥቶ ያለውን ታሪክ ያካተተ ነው። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ኢየሱስ በደቀመዛሙርቱ በኩል ሥራውን መሥራቱን እንደቀጠለ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው ልንለው እንችላለን። ይህም ሥራ ተፈጻሚነትን ያገኘው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው።

ጥያቄ 1፡- እኛ የኢየሱስን ሥራ ተተክተን እየሠራን ነው ልንል የምንችለው እንዴት ነው?

የሐዋርያት ሥራ መክፈቻ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት የሚያበሥረውን የተስፋ ቃልና እስከ ምድር ዳርቻ ሂዱ የሚለውን ትዕዛዝ የያዘ ነው።

ጥያቄ 2:- በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ቁልፍ የሆነችው ጥቅስ የትኛዋ ናት? እስቲ ሳታይ በቃልህ ደብተር ላይ ለመጻፍ ሞክር።

ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከማረጉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ የመጨረሻውን ትዕዛዝ ይሰጣቸዋል። በሐዋርያት ሥራ 1፡ 8 ላይም ኢየሱስ የሱን መመለስና የእሱን መንግሥት ምሥረታ በሚጠባበቁበት ጊዜ ዋናው ሥራቸው ወንጌልን መመሥከር እንደሆነ ለደቀመዛሙርቱ ይገልጽላቸዋል።

ጥያቄ 3:- ከሐዋርያት ሥራ ጥናታችን እንዳየኸው ምሥክሮች መሆን ያለብን በተለይ ስለምን ዋና ዋና ነገሮች ወይም ቁልፍ እውነታዎች ነው? ወንጌል ምንድነው?

ወንጌሉ ጌታ ኢየሱስ ስለ ዓለም ኃጢአት እንደሞተና ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው የሞት ዋጋን መክፈል እንደሌለባቸው የሚናገር የምሥራች ዜና ነው። ከዚህም ሌላ ኢየሱስ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ከሙታን እንደተነሣና በአሁኑ ሰዓት በአብ ቀኝ እንደተቀመጠም ይናገራል። ከዚህም በኋላ ሰዎች ሁሉ ኃጢአታቸውን ተናዝዘው በኢየሱስ አምነው ኢየሱስ የሰጣቸውን ትዕዛዞች ለመጠበቅ ቁርጥ ውሣኔ እንዲያደርጉ ልመና ያቀርባል። በሌላ በኩል ደግሞ አይሁዳውያንም ይሁኑ አሕዛብ በኢየሱስ ካመኑ ያለምንም ሌላ ተጨማሪ መመዘኛ የዘላለማዊ ሕይወትንና የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን እንደሚያገኙ የሚገልጽ የተስፋ ቃል ይዟል። የሮማውን ዘመነ መንግሥት የለወጠው የጥንት ክርስቲያኖች ያምኑትና ሐዋርያቱም ያስተማሩት ይህንኑ የምሥራች ወንጌል ነው።

በሐዋርያት ሥራ 1:8 ላይ ኢየሱስ ወንጌሉ በዓለም ላይ እንዴት መስፋፋት እንዳለበት የሚገልጽ ቅደም ተከተል ሁኔታዎችን አስቀምጧል። ይህ በተለያዩ ዘመናት ያሉ ወንጌላውያን ሐላፊነታቸውን እንዴት መወጣት እንዳለባቸው የሚገልጽ መሠረተ ሐሳብ ነው። በመጀመሪያ ወንጌሉ መስበክ የነበረበት የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን በተመሠረተችበት በኢየሩሳሌም ውስጥ ነው። በዚህም ሥፍራ ያሉ ሰዎች በዙዎቹ አይሁዳውያን ናቸው። ታዲያ በኢየሩሳሌም ውስጥ ወንጌሉ እንዴት እንደተስፋፋ የሚገልጹ የመጀመሪያዎቹ ሰባት የሐዋርያት ሥራ ምዕራፎች ናቸው። እንግዲህ ለእኛ ኢየሩሳሌም አድርገን የምንወስደው ቤተክርስቲያናችን አካባቢ የሚኖሩትንና የሚሠሩትን ሰዎች ነው።

ጥያቄ 4:- ለቤተክርስቲያንህ ኢየሩሳሌም የሆነው ሥፍራ ምንድነው?

ከዚህ በኋላ ወንጌሉ ወደ ይሁዳ መስፋፋት ነበረበት። በዚህም ሥፍራ ይኖሩ የነበሩት በኢየሩሳሌም ውስጥ እንዳሉት አይሁዳውያን ተመሳሳይ በሃልና ቋንቋ የነበራቸው አይሁዳውያን ናቸው፤ ሆኖም እነዚህን ሰዎች ትንሽ ለየት የሚያደርጋቸው ገጠር በሆነው አካባቢ መኖራቸው ነው።

ጥያቄ 5:- ለቤተክርስቲይንህ ይሁዳ የሆነው ሥፍራ ምንድነው?

የኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን ሐላፊነት የነበረበት ለራሷ ሕዝቦችና በአካባቢዋ ለሚኖሩት ሰዎች ብቻ አልነበረም። ወደ ሰማሪያም ሄዳ ወንጌሉን መስበክ ነበረባት።

እንደምታስታውሰውም ሳምራውያን ግማሽ ጎናቸው አይሁዳዊ ሌላኛው ደግሞ ከአሕዛብ ወገን ነበር። ታዲያ ብዙ ነገራቸው ከአይሁዳውያን ጋር ቢመሳሰልም፥ አንዳንድ መሠረታዊ የሆኑ ልዩነቶች ነበራቸው። በእነዚህም ልዩነቶች ምክንያት ለሳምራውያኑ መመሥከሩ ችግር ነበረበት። ሆኖም፥ ኢየሱስ የሞተው ለእነሱ ጭምር ስለሆነ ደቀመዛሙርቱ ለእነሱ የመመሥከር ግዴታ ነበረባቸው። የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ስምንትም እንዴት ለሳምራውያን እንደተመሠከረ ይነግረናል። የወንጌላ አንዱ ክፍልም እግዚአብሔር ከየትኛውም ወገን የሆኑትን ሰዎች ደሃም ይሁኑ ሃብታም እንደሚቀበላቸው ይገልጽልናል።

ጥያቄ 6:- ሀ) ለአንተ ቤተክርስቲያን ሰማሪያ የሚሆነው ሥፍራ ምንድነው? ለ) ቤተክርስቲያንህ በዚህ ሥፍራ ወንጌልን የምታሥፋፋው እንዴት ነው? ሐ) ትንሽ ለየት ያለ ባህልና ሃይማኖት ላላቸው ሰዎች መመሥከሩ የሚከብደው ለምንድነው?

በዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ከሕዝብ፥ ከነገድ፥ ከወገንና ከቋንቋዎም ሁሉ ብዙ ሰዎች በበጉ ዙፋን ፊት ቆመው አመሰገኑ የሚል ነገር እናነባለን (የዮሐንስ ራዕይ 7:9-10)። የእግዚአብሔር ዓላማ ይህ ነው! ኢየሱስም በመስቀል ላይ የሞተው ይህን ነገር ለመፈጸም ነው። ከዚህም በላይ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እስከምድር ዳርቻ ድረስ ሄዳችሁ መሥክሩ ብሎ ትዕዛዝ የሰጣቸው በዚሁ ምክንያት ነው። ስለዚህም የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13-28 በዚያን ጊዜ ይታወቅ በነበረው ዓለም ውስጥ በተለይ በጳውሎስ አማካኝነት እንዴት ወንጌሉ እንደተስፋፋ ይገልጽልናል።

ጥያቄ 7:- ሀ) እስከ ምድር ዳርቻ የመድረስ ሐላፊነቷን ቤተክርስቲያን የምትወጣው እንዴት ነው? ለ) ይህን ሐላፊነቷን በበለጠ ሁኔታ በተገቢው መንገድ ለመፈጸም ከዚህ በላይ ምን ማድረግ አለባት?

እውነቱ ሲታይ በዓለማችን ገና ብዙው ክፍል ውስጥ ወንጌሉ አልተስፋፋም። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያልሰሙ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ። ሌላው ይቅርና እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልሰሙ ብዙ ናቸው። ታዲያ ወንጌልን በዓለም የማዳረሱ ሐላፊነት የምዕራቡ ክፍለ ዓለም ሐላፊነት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ነው። ይህ ትዕዛዝ እዚህ ኢትዮጵያ ላለነውም ተሰጥቶናል። በትውልድ ዝመናችን ይህ ሐላፊነት እንወጣ ዘንድ እግዚአብሔር ታማኞችና ታዛዦች ያድርገን!!

# ሁለተኛ ቀን:-

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የሚተርከው በጥንቱ የሮማው ዘመነ መንግሥት ክርስትና እንዴት እንደተስፋፋ ብቻ አይደለም። አንድ ጤነኛ የሆነ ቤተክርስቲያን እንዴት መሆን እንዳለበትና በዓለም ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚገባም ይገልጻል። የሐዋርያት ሥራን በምናጠናበት ወቅትም እነዚህ ቤተክርስቲያንን የሚያጸኑና የሚያጠነክሩ ነገሮችን አይተናል። ታዲያ ቤተክርስቲያናችን ጤነኛ መሆኗን ወይም አለመሆኗን በእነዚህ ነገሮች ላይ በመመሥረት ልንመረምር እንችላለን።

1. አንድ ጤነኛ ቤተክርስቲያን ሁሌ የምትጸልይ ናት፡- እግዚአብሔር እንድንጸልይ ትዕዛዝ ሰጥቶናል። የጥንቷ ቤተክርስቲያንም በጸሎት ላይ ምን ያህል ትኩረት ታደርግ እንደነበር አይተናል። ለመጥቀስ ያህልም መንፈስ ቅዱስ የወረደባቸው በጸሎት ላይ ሳሉ ነበር። ጴጥሮስም ከወኅኒ ቤት ሊወጣ የቻለው በቁዱሳን ጸሎት ነው። ለአንድ ክርስቲያን የሃይል ምንጩ ጸሎት ነው። የሰይጣንን ምሽጎች ልናፈራርስ የምንችለው በጸሎት ነው። ይህ ነገር በጣም አስፈላጊ በመሆኑም ብዙ ጊዜ ሰይጣን በቤተክርስቲያን የጸሎት ሕይወት ላይ ጥቃት ይሰነዝራል። በዚህም መሠረት ጸሎታችን ከልብ የመነጨ ሳይሆን ዝም ብሎ በዘልማድ የምናደርገው ሥርዓት እንዲሆንብን ያደርጋል። ወይም ደግሞ አንዳንዴ በጣም በሥራ እንጠመድና ለጸሎት ጭራሹኑ ጊዜ እናጣለን። ቤተክርስቲያኖቻችን እንደዚህ ደካማ የሆኑበት አንዱ ምክንያት ይህ ይሆንን?

ጥያቄ 8፡- ሀ) ለጸሎት የምትወስደው ጊዜ ምን ያህል ነው? ለ) በቤተክርስቲያንህ ለጸሎት የሚሠጠው ሥፍራ ምን ያህል ነው? በሌላ አነጋገር በቤተክርስቲያንህ የጸሎት አስፈላጊነት ምን ያህል ነው?

2. አንድ ጤነኛ ቤተክርስቲያን ሁሌ የምትመሠክር ናት፡- ምንም እንኳ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ወንጌልን ለማስፋፋት በሰፊው እግዚአብሔር በተጠቀመባቸው በጳውሎስና በጴጥሮስ ላይ ቢያተኩርም፥ በተደጋጋሚ መላው ቤተክርስቲያን እንዴት በምሥክርነቱ ሥራ ውስጥ እንደተሣተፈች እናያለን። ለምሳሌ ስደት እንደተነሣ ክርስቲያኖቹ ወንጌሉን በየአካባቢው ወደሚገኙት ከተሞች እንዴት ይዘው እንደሄዱ አይተናል። በየትኛውም ሥፍራ ያሉ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ የመመሥከር ሐላፊነት አለባቸው።

ጥያቄ 9፡- የቤተክርስቲያንህ አባላት፥ በሥራቸውና በሌሎች አካባቢ ያላቸው ምሥክርነት በሌሎች ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እያሳደረ ነው?

3. አንድ ጤነኛ ቤተክርስቲያን ሁሌ የምትማር ናት፡-

ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ እንደምናነበው አማኞቹ ሁሌ እየተሰበሰቡ እግዚአብሔርን ከማመስገን ሌላ ከሐዋርያቱ ትምህርት ይቀስሙ ነበር። እግዚአብሔር ልጆቹ በቂ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በጭራሽ አይፈልግም። ስለዚህም ቤተክርስቲያኖቻችን የእግዚአብሔር ቃል በትክክልና በጥራት የሚሰበክባቸው በታዎች መሆን አለባቸው።

ጥያቄ 10፡- ቤተክርስቲያንህ ክርስቶስን ወደመምሰል ደረጃ እንድትደርስ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎችን እየተገለጡ በቤተክርስቲያንህ ትምህርት የሚሰጠው እንዴት ነው?

4. አንድ ጤነኛ ቤተክርስቲያን ሁሌ የምታድግ ናት፡-

ብዙ ጊዜ አብያተ ክርስቲያናት ባላቸው ዕውቀትና የአባላት ብዛት ይኩራራሉ። ታዲያ እነዚሁ አባላት በየዓመቱ ወደ ቤተክርስቲያን ይመጣሉ! ነገር ግን ምንም ዕድገት የላቸውም። አንድ ቤተሰብ የሚያድገው ልጆች ሲወልዱ እንደሆነ ሁሉ፥

ቤተክርስቲያንም በዚሁ መንገድ ማደግ አለባት። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፥ ቤተክርስቲያናችችን ሳያድጉ ያደጉ ይመስለናል፤ ነገር ግን ወደ ቤተክርስቲያናችን የተጨመሩት የአባላት ልጆች ብቻ እንጂ አዳዲስ ነፍሳት አይደሉም። የማያምኑ ሰዎች በየጊዜው ወደ ቤተክርስቲያናችን ሕይወታቸው እየተለወጠ የማይመጡ ከሆነ ወይም ደግሞ እነዚህ ሰዎች በክርስትና ሕይወታቸው ጸንተው የማይቆሙ ከሆነ ቤተክርስቲያናችን ድክመት ላይ እንዳለች ያሳዩናል።

ጥያቄ 11:- ሀ) በዚህ ዓመት ከዳኑ ቤተሰቦች ያልሆኑ ምን ያህል ሰዎች ናቸው በቤተክርስቲያንህ የዳኑት? ለ) በቤተክርስቲያንህ ይከታተሉ ከነበሩ ሰዎች ውስጥ ምን ያህሉ ጌታን ትተው ወደ ዓለም የተመለሱት?

5. እንዲት ጤነኛ ቤተክርስቲያን አባላቷ በሙሉ የተጠመቁና የጌታን እራት የሚወስዱ ናቸው:-

አንዱ የኢየሱስ ትዕዛዝ አማኞች ይጠመቁ የጌታንም እራት ይውሰዱ የሚል ነው። በተደጋጋሚ በጥናታችን ውስጥ እንዳየነው የሚያምኑት ሰዎች ይጠመቁ ነበር። አሁን ደግሞ በየቤተክርስቲያናችችን የሚመጡት ብዙዎቹ ሰዎች ያልተጠመቁና የጌታን እራት የማይወስዱ ናቸው። ታዲያ እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ ቢድኑም የጌታ ኢየሱስን ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ስላልጠበቁ መንፈሳዊ ድክመት ይኖርባቸዋል።

ጥያቄ 12:- ሀ) በቤተክርስቲያንህ የሚመጡት ብዙዎቹ ሰዎች የተጠመቁ ናቸውን? ለ) ብዙዎቹስ የጌታን እራት ይወስዳሉ? ካልሆነስ ለምን?

6. በአንድ ጤነኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መኖር በጉልህ ይታያል:-

ይህን ስንል አባላቷ በልሳን መናገር አለባቸው፥ ሁልጊዜ የፈውስ ሥርዓት መኖር አለበት ማለታችን አይደለም። በእርግጥ መንፈስ ቅዱስ እራሱን በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ አንዳንዴ ይገልጻል፤ ቢሆንም በግድ መታየት ያለባቸው ነገሮች ናቸው ሊባሉ አይችሉም። ከዚህ ይበልጥ ግን የመንፈስ ቅዱስ መኖር በቤተክርስቲያን ውስጥ ገሃድ የሚሆነው የአንድ ቤተክርስቲያን አባላት በፍቅር ሲኖሩ፥ የቀድሞው አኗኗራቸው እየተለወጠ በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑት ፍቅር፥ ደስታ፥ ሠላም፥ ... ወዘተ. ሲታዩባቸው ነው (ገላ 5፡ 22)። ከዚህም ሌላ የአንድ ቤተክርስቲያን አባሎች በተለያዩ ስጦታዎቻቸው እየተጠቀሙ ሲያገለግሉ የመንፈስ ቅዱስ መኖር ጉልህ ይሆናል።

የቤተክርስቲያንን መመሥረት ያበሠረው የመንፈስ ቅዱስ መምጣት ነው። ይህ የአዲስ ዘመንን መምጣት ያሳየናል። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ ይወርድ የነበረው ለተወሰነ ሥራ በተመረጡ መሪዎች ላይ ብቻ ነበርና ነው። አንዳንድ ጊዜም፥ ለዛ መሪ የተሰጠው ሥራ ከተገባደደ ወይም ሰውዬስ ኃጢአትን መለማመድ ከጀመረ መንፈስ ቅዱስ ከሕይወቱ ውስጥ ይወጣ ነበር። በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ መምጣቱን ኢየሱስን በሚያምኑትና በተቀበሉ ክርስቲያኖች (መጀመሪያ አይሁዳውያን፥ ቀጥሎ ሳምራውያን፥ ቀጥሎ አሕዛብ) በጉልህ ያሳየው በእሣትና የልሳን ስጦታ በመስጠት ነው። ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን እያንዳንዱ አማኝ በልሳን ቢናገር ወይም

ባይናገር፥ አንድ ጊዜ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ ከተቀበለ በኋላ፥ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል።

ጥያቄ 13:- በቤተክርስቲያንህ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መኖር የሚገለጸው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

የበዓለ ሐምሳ ዋነኛ እውነታ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔር ለልጆቹ በገሃድ የመስጠቱ ጉዳይ ነው። በዚያን ጊዜ የነበሩትን ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳ፥ በሰማሪያና ብሎም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምሥክር እንዲሆኑ ብቃት የሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው (ሐዋ. 1፡ 8፤ 2፡ 1-6)። ነቢዩም እንደተነበየው፥ የእግዚአብሔር መንፈስ በአይሁዳውያንና በአሕዛብ ላይ ይወርድ ነበር። ከዚህም በኋላ፥ የእግዚአብሔርን ስም የጠራ በሙሉ ይድናል (ትንቢተ ኢዩኤል 2፤ 22-32፤ ሐዋ. 2፡ 17-21)። በበዓለ ሐምሳ ለትም ከብዙ አገር የመጡ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን ከተሞሉት የኢየሱስ ተከታዮች የክርስቶስን መልእክት በራሳቸው ቋንቋ ሰሙ (ሐዋ. 2፡ 5)።

በበዓለ ሐምሳ ዕለት የወረደው መንፈስ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን ግዳጅዋን ልትወጣበት የምትችልበትን ኃይል ሰጥቷታል። በዚህም መሠረት ለጴጥሮስና ለዮሐንስ ቃሉን እንዲሰብኩ ድፍረትን ሰጣቸው (ሐዋ. 4፡ 13-31)፤ የተመረጡት ሰባት ዲያቆናት በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ነበሩ (ሐዋ. 7፡ 55-58)፤ በሳምራውያኑ መካከል የተሠራው ሥራ እውነተኛ መሆኑ የተረጋገጠው በመንፈስ ቅዱስ መውረድ ነው (ሐዋ. 8፡ 17)፤ የጳውሎስ መለወጥም ይፋ የወጣው በመንፈስ ቅዱስ ነው (ሐዋ. 9፡ 17-18)፤ ወንጌላውያኑን በርናባስንና ሳውልን የላካቸውና የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ነው (ሐዋ. 13፡ 2፤ 4፤ ጳውሎስና ሲላስ የሐዋ. 16፡ 7፤ የጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ በተመለከተ ሐዋ. 12፤ 21)።

7. አንድ ጤነኛ ቤተክርስቲያን ስደት ይኖርባታል:-

በጥናታችን ላይ እንዳየነው አንድን ጤነኛ ቤተክርስቲያን ለማጥፋት ሰይጣን የሚጠቀምበት አንዱ ዘዴው ስደት ነው። ታዲያ ይህ ስደት በተለያየ መንገድ ቢፈጸምም ዋነኛው ዓላማው ቤተክርስቲያንን ለማውደምና አባላቷንም ከመመሥከር ለማገድ ነው። ሐዋርያው ያዕቆብ ለምሳሌ ሕይወቱን እስከማጣት ደርሷል። የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጸድቅ ሰማዕት ደግሞ ዲያቆን እስጢፋኖስ ነበር። ከዚህም ሌላ ወንጌል ይዞ በሚሄድበት ሁሉ ጳውሎስ ስደት ይደርስበት ነበር። ታዲያ እግዚአብሔር በአንድ ጤነኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይህንን ስደት ለማጣሪያና ወንጌልን ለማሰራጫ እንደ መሣሪያ አድርጎ ይጠቀምበታል። ስለዚህም ደቀመዛሙርቱ እንዳሉት «ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ልንታዘዝ ይገባል»።

ጥያቄ 14:- ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን መታዘዛቸው በዚህ መጽሐፍ የታየው እንዴት ነው?

8. እንዲት ጤነኛ ቤተክርስቲያን ንጽሕት ናት:-

ሰይጣን ቤተክርስቲያንን የሚያጠቃበት ሁለተኛው መንገዱ ቤተክርስቲያንን ማርከስ ነው። ሐናንያና ሰጲራ እግዚአብሔርን ለማታለል ቢሞክሩ እግዚአብሔር አጠፋቸው። ሀሰተኛ መምህራን የወንጌሉን እውነታ ሊያጣምሙ ቢሞክሩ ጊዜም መገታት ነበረባቸው። የጥንቷን ቤተክርስቲያንና እኛን እስከ ዛሬ የሚያስቸግረን የሐሰት ትምህርት እግዚአብሔርን መቀበል በተመለከተ በፀጋ በሚገኘው ደኅንነት ላይ ለደኅንነት ብቁ ለመሆን ይህን መጨመር አለባችሁ የሚለው ትምህርት ነው። ሆኖም እኛ የምንድነው ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን እንደሞተ ስናምን ብቻ ነው። ከዚህ ሌላ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመድረስ የምንሠራው ምንም ሥራ የለም። ስለዚህም ሰይጣን ሁልጊዜ የቤተክርስቲያን አባላትን ቅድስናና የወንጌሉን መልእክት ለማጣመም ይጥራል። እንግዲህ እግዚአብሔርን በሚያስከብር ሁኔታ እንድናድግ፣ በእነዚህ ሁለት ነገሮች ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

ሰይጣን የጥንቷን ቤተክርስቲያን ያጠቃበት የነበረው ሌላኛው መንገድ አለመግባባትን መፍጠር ነበር። በዚህም መሠረት፣ የደቀመዛሙርቱ ቁጥር እንዴት እንደጨመረና በሄሌናውያኑ አይሁዳውያንና በተቀሩት አይሁዳውያን መካከል ልዩነት እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ አይተናል። በዚህም ጊዜ ሐዋርያቱ አማኞቹን በሙሉ ጠርተው፣ ቤተክርስቲያንን የሚያስተዳድሩ ሰባት ሰዎችን እንዲመርጡ ያደርጋሉ። ስለዚህም በውስጧ ክፍፍል ያለበት ቤተክርስቲያን የተሸነፈች ናት፤ ምክንያቱም ምንም ምሥክርነትና ኃይል የላትምና ነው።

ጥያቄ 15፡- በእነዚህ ከላይ በጠቀስናቸው ሦስት መንገዶች ሰይጣን ቤተክርስቲያንህን ያጠቃው እንዴት ነው?

## ሦስተኛ ቀን፡-

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ብዙ ትኩረት የሚያደርገው በሁለት ሰዎች ላይ ነው። በዚህም መሠረት የመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ምዕራፎች ትኩረት የሚያደርጉት የአይሁዳውያኑ ሐዋርያ የነበረው በጴጥሮስ ላይ ነው። እንደምታስታውሰውም በማቴዎስ 16፡ 17-19 ላይ ኢየሱስ ለጴጥሮስ በቤተክርስቲያን ውስጥ የተለየ ቦታ ሰጥቶታል። ቤተክርስቲያን የሚመሠረትበት ድንጋይ ጴጥሮስ ነበር። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም ውስጥ ይህ እንዴት እንደተፈጸመ እናያለን። በመጀመሪያም የኢየሩሳሌሟ ቤተክርስቲያን መሪ የነበረው ጴጥሮስ ነው። አሥራ ሁለተኛው ሐዋርያ የተመረጠው በእሱ አነሳሽነት ነው፣ የሳምራውያኑን እምነት እውነተኛነት ያረጋገጠና መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጣቸው የጸለየላቸው፣ ቤተክርስቲያን በተመሠረተችበት ጊዜ ለተሰበሰበው ሦስት ሺህ ሕዝብ ንግግር ያደረገው፣ የመጀመሪያውን ተአምራት የፈጸመውና የቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ቃል አቀባይ ሆኖ በካህናት ፊት የቀረበው ጴጥሮስ ነው። ከዚህም ሌላ ጴጥሮስ አሕዛብ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲገቡ ለቆርኔሌዎስ ቤተሰቦች በመስበክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሩን የከፈተና በአሕዛብ መካከል መንፈስ ቅዱስ መውረዱን ያበሠረ ነው።

ጥያቄ 16:- የኢትዮጵያዋ ቤተክርስቲያን በጴጥሮስ ላይ ነው የተመሠረተችው ልንል የምንችለው በምን ዓይነት መንገድ ነው?

የተቀረው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ደግሞ ትኩረት የሚያደርገው የአሕዛብ ሐዋርያ በነበረው በጳውሎስ ላይ ነው። እግዚአብሔርም ይህን የተማረ፣ ቤተክርስቲያንን ያሳድድ የነበረና ቀናተኛ የነበረ አይሁዳዊ ሕይወት በመለወጥ ወንጌልን ለተቀረው ዓለም ይዞ እንዲሄድ ያደርገዋል። በሦስት ሚሲዮናዊ ጉዞዎችና በአንድ ወደ ሮም በተደረገ ጉዞ ጳውሎስና ጓደኞቹ በዚያን ጊዜ የነበረውን ዓለም ያዳርሱታል። በመጀመሪያው ሚሲዮናዊ ጉዞው ጳውሎስ ወንጌሉን ይዞ የሄደው በእስያ (የዛሬ ቱርክ) በተለይም በገላትያ ክፍለ ሃገር ውስጥ ነበር። በሁለተኛውም ሚሲዮናዊ ጉዞው ደግሞ ትኩረቱን በቆሮንቶስ ከተማ ላይ በማድረግ ወንጌሉን ወደ አውሮፓና ግሪክ ይወስዳል። በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ላይ ደግሞ ብዙ ጊዜውን ያሳለፈው ከዚህ ቀደም ብሉ የመሠረታቸውን ቤተክርስቲያኖች በመጎብኘት ነው። ሆኖም በዚህ ጊዜ ብዙ ቆይታ አድርጎ ያገለገል የነበረው በኤፌሶን ከተማ ነው። ከዚህም ከተማ በመነሣት ወንጌሉ መላውን እስያ እንደሚያዳርስ ሉቃስ ይነግረናል። ከዚህም በኋላ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ታሪክ የሚገባደደው በዚያን ጊዜ የነበረው የሮማው መንግሥት መዲና የሆነችው ሮም ውስጥ ወንጌል እንዴት እንደደረሰ በማተት ነው። ከዚህ ጊዜ በኋላም ለብዙ ምዕተ አመታት ሮም የዓለም የቤተክርስቲያኖች ዋና መሰብሰቢያ በመሆን አገልግላለች። ዛሬም እንኳ ቢሆን፣ የካቶሊኩ ጳጳስ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኘው በሮም ነው።

ጥያቄ 17:- የጳውሎስን ጉዞ የሚያሳዩ አራት ካርታዎችን ተመልከት። በጳውሎስ አገልግሎት ላይ ተመሥርተው ቤተክርስቲያናት የተመሠረቱባቸው ዋና ዋና ከተሞች በዝርዝር ጻፍ።

# አራተኛና አምስተኛ ቀን:-

በዚህ የሐዋርያት ሥራ ማጥኛ መጽሐፍ የተማርካቸውን ትምህርቶች ከልስና በሳምንታዊው ስብሰባ ወቅት ለምትወስደው የመጨረሻ ፈተና ተዘጋጅ። ፈተናው ሙሉ በሙሉ የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ያካተተ ይሆናል።

# ሳምንታዊው ስብሰባ:-

1. ሳምንታዊው የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. የመጨረሻ ፈተና
4. የጸሎት ጊዜ